## ከአላህ (ዐ.ወ.) ጋር ወደመሆን የመግባት ምክኒያትና መልካም ውጤቱ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{هُوَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ اسْتَوَى عَلَى الْعَرْشِ يَعْلَمُ مَا يَلِجُ فِي الْأَرْضِ وَمَا يَخْرُجُ مِنْهَا وَمَا يَنْزِلُ مِنَ السَّمَاءِ وَمَا يَعْرُجُ فِيهَا وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنْتُمْ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}

ለአላው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፡፡ ከዚያም (ለክብሩ በሚስማማ መልኩ) በዐርሹ ላይ ተደላደለ፡፡ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል፡፡ ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡) ከፍ አለ ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ከአላህ (ዐ.ወ.) ጋር መሆን ማለት አላህ የሚቆጣጠረው እንድሁም አላህ የሚያግዘው መሆንን ማወቅና በልብ ማዘውተር ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የፍጥረታቱን ሁሉ እንቅስቃሴ በእወቀቱ የሸፈነ መሆኑን እንድህ በመለት ጠቁሟል

{وَعِنْدَهُ مَفَاتِحُ الْغَيْبِ لَا يَعْلَمُهَا إِلَّا هُوَ وَيَعْلَمُ مَا فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَمَا تَسْقُطُ مِنْ وَرَقَةٍ إِلَّا يَعْلَمُهَا وَلَا حَبَّةٍ فِي ظُلُمَاتِ الْأَرْضِ وَلَا رَطْبٍ وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُبِينٍ}

ትርጉሙም (የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፡፡ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም፡፡ በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል፡፡ ከቅጠልም አንዲትም አትረገፍም የሚያውቃት ቢኾን እንጅ፡፡ ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ

የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ቢኾን እንጅ፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

(أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۖ مَا يَكُونُ مِن نَّجۡوَىٰ ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمۡ وَلَا خَمۡسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمۡ وَلَآ أَدۡنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكۡثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمۡ أَيۡنَ مَا كَانُواْۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُواْ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ)

ትርጉሙም (አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውን በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ መኾኑን አታይምን? ከሦስት ሰዎች መሾካሾክ አይኖርም እርሱ አራተኛቸው ቢኾን እንጅ፡፡ ከአምስትም (አይኖርም) እርሱ ስድስተኛቸው ቢኾን አብሯቸው ቢሆን እንጅ፡፡ ከዚያ ያነሰም የበዛም (አይኖርም) እርሱ የትም ቢኾኑ እንጂ፡፡ ከዚያም በትንሣኤ ቀን የሠሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አላህ ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ፍጡሩን ሁሉ ያግዛል፣ ስኬትን ይለግሳል፣ ይጠብቃል፣ ይጠግናል እንድሁም ይንከባከባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ከባሮቹ ነብያቱን ወልዮቹንና ፃዲቃንን ከነሱ ጋር በመሆን ከሌሎች ባሮቹ ለይቷቸዋል፡፡ ይህን ከፍጥረታቱ የመረጣቸው ባሮቹ የተቸሩትን ታላቅ አብሮነት ቅዱስ ቁርአን በበርካታ ምእራፎች የጠቀሰው ሲሆን አላህ (ዐ.ወ.) በሰይዲና ሙሳና በሰይዲና ሃሩን ልሳን እንድህ ሲል የጠቀሰው በቅድሚያ ይወሳል፡

{ اذْهَبْ أَنْتَ وَأَخُوكَ بِآيَاتِي وَلَا تَنِيَا فِي ذِكْرِي * اذْهَبَا إِلَى فِرْعَوْنَ إِنَّهُ طَغَى * فَقُولَا لَهُ قَوْلًا لَيِّنًا لَعَلَّهُ يَتَذَكَّرُ أَوْ يَخْشَى * قَالَا رَبَّنَا إِنَّنَا نَخَافُ أَنْ يَفْرُطَ عَلَيْنَا أَوْ أَنْ يَطْغَى * قَالَ لَا تَخَافَا إِنَّنِي مَعَكُمَا أَسْمَعُ وَأَرَى}

ትርጉሙም («አንተም ወንድምህም በተዓምራቶቼ ኺዱ፡፡ እኔንም ከማውሳት አትቦዝኑ፡፡ «ወደ ፈርዖን ኺዱ፡፡ እርሱ ወሰን አልፏልና፡፡ «እርሱም ይገሰጽ ወይም ይፈራ ዘንድ፤ ለእርሱ ልዝብን ቃል ተናገሩት፡፡» «ጌታችን ሆይ! እኛ በእኛ ላይ ክፋት በመሥራት መቸኮሉን ወይም ኩራትን መጨመሩን እንፈራለን» አሉ፡፡ (አላህም) አለ «አትፍሩ፡፡ እኔ በእርግጥ ከእናንተ ጋር ነኝና፡፡ እሰማለሁ፤ አያለሁም፡፡) ማለት ነው፡፡ ይህን አብሮነት የነብዩ ሙሳ ህዝቦች ‹እኛ ፈርዓውንና ወታደሮቹ የሚደርሱብን ነን› ባሉ ጌዜ ነብዩ ሙሳ ተ‹ዉ ጌታዬ ከኔ ጋር ነው በእርግጥ ይመራኛል› በማለት የፈጣሪ ረድኤትና ድሉ የማይለያቸው መሆኑን በእርግጠኝነት እንዲናገሩ ያደረጋቸው ነው፡፡

የዚህ አይነት የአላህ እርዳታ አብሮነት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከባልደረባቸው ከአቡበክር አሲዲቅ ጋር ስደት በወጡ ጊዜ በግልጽ የታዬ ሲሆን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ በክር አሲዲቅ እንድህሲሉ አብራርተውታል፡ (እኔ ከነብያችን ጋር በዋሻው በነበርኩበት ወቅት ወደአጋሪዎች ጫማዎች ተመለከትኩና ‹የአላህ መልክተኛ ሆይ!

አንዳቸው ወደጫማው ቢመለከት ቀጥታ ያየናል አልኩኙ፡፡› ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አቡ በክር ሆይ! (አላህ ሦስተኛቸው በሆኑ ሁለት ሰዎች ምን ትገምታለህ) አሉኝ፡፡ ይህን ጉዳይ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል ገልጾታል፡

{إِلَّا تَنْصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللَّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُوا ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لَا تَحْزَنْ إِنَّ اللَّهَ مَعَنَا فَأَنْزَلَ اللَّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُوا السُّفْلَى وَكَلِمَةُ اللَّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ} .

ትርጉሙም ((ነቢዩን) ባትረዱት እነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፡፡ የአላህም ቃል ለእርሷ ከፍተኛ ናት፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አንድ ባሪያ ምንጊዜም አላህ ከሱ ጋር መሆኑን አለመዘንጋቱ ታላቅ ነገር ነው፡፡ አላህ ከሱ ጋር የሆነ ሰው ደጋፊውም ይሁን ተቀናቃኙ ምንም አያሳስበው፡፡ አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር እንዲሆን ካሰበ ወደሱ በሚያደርሰው ቀጥተኛ መስመር መጓዝ አለበት፡፡ እንድሁም ለሱ መሰረትየ ሆኑ ነገሮችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ በመጀመሪያ ትክክለኛ ሙእሚን መሆን አላበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አላህ በእርግጥ ከመእምናን ጋር ነው ይላል፡፡ አንድ ሰው ምእምን ይባል ዘንድ በአላህ፣ በመላእከት፣ በመጽሐፍት፣ በመልከተኞችና በመጨረሻው ቀን እንድሁም በጎም ይሁን መጥፎ ነገሮች በሙሉ ከአላህ ዘንድ የተፈረዱ በመሆኑ ማመን አለበት ስንል የዚህ እምነቱ ገጽታ በአለው ስነ ስርኣትና ከሰዎች ጋር በሚዋዋልበት ወቅት ጎልቶ መታየት አለበት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና ከእጁ ተንኮል የዳኑ ነው፡፡ ሙእሚን ማለት ደግሞ ሰዎች በሕይዎታቸውና በገንዘባቸው እመነት የጣሉበት ነው፡፡)

አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር ይሆን ዘንድም አላህን ፈሪና በጎ ሰሪም መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አላህ ከነዚያ እሱን ከሚፈሩትና ከመልካም ሰሪዎች ጋር ነው ይላል፡፡ እንድሁም እወቁ አላህ ከነዚያ እሱን ከሚፈሩት ጋር ነው ይላል፡፡ አሁንም አላህ ከነዚያ መልካም ከሚሰሩት ጋር ነው ይላል፡፡ አላህን መፍራት ማለት አላህ የሚወደውን ነገር መሥራት እሱን ከሚያስቆጣ ነገር ሁሉም መራቅ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መልካም ነገርን ሁሉ ኣካቶ ይዟል፡፡ ቅዱስ ቁርኣን አላህን መፍራት ምን ማለት እንደሆኑ እነደሚከተለው ጠቁሟል፡፡

{لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَى حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ

**إِذَا عَاهَدُوا وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ أُولَئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ} .**

ትርጉሙም (መልካም *ሥራ ፊቶቻችሁን* ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም *ሥራ* በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ *ያመነ* ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ *ጋር* ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች *ሥራ*) ነው፡፡ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም *ታጋሾችን* (እናወድሳለን)፡፡ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ አንዳችሁ ሌላውን አይመቅኝ፣ እንድሁም አንዳችሁ በሌላችሁ ላይ አይጫረት፣ አትጠላሉም፣ ጀርባም አትሰጣጡ፡፡ አንዳችሁም የሌላውን ነውር አያውጣ፣ ወንድም ተማማች የአላህ ባሪያዎች ሁኑ፡፡ ሙስሊም የሙስሊም ወንድም ነው፡፡ አይበድለውም አያቃልለውም አይንቀውም አላህን ፍራቻ እዚህ ውስጥ ነው፡፡) ሦስት ጊዜ ቃሉን ሲደጋግሙ ወደልባቸው አያመለከቱ ነበር፡፡ (አንድ ሰው ወንወጀል ለመፈጸም ሙስሊም ወንድሙን ማንኳሰሱ ይበቀዋል፡፡ የአንደን ሙስሊም ደም፣ንብረትና ክብር በማንኛውም ሙስሊም ላይ የተከለከለ ነው፡፡ )መልካም *ሥራ* መን ማለት እንደሆነ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሲያብራሩ አንድህ ይላሉ፡ (አላህን ስትገዛ ልክ ከፊት እንዳለ አድረገህ መሆን አለበት፡፡ አንተ ባታየውም እሱ ያሃልና፡፡) በዚህም አንድ ባሪያ ጌታው በምስጢርም ሆነ በይፋ አየተንቀሳቀሰም ይሁን ጽጥ ብሎ የሚሰራውን ነገር ሙሉ በሙሉ የሚቆጣተረው መሆኑን በግልጽ የተገነዘበ ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ‹አላህ የሚያይ መሆኑን አላወቀምን› ይላል፡፡

አንድ ሰው አላህ ከሱ *ጋር* እንዲሆን ከሚያደርጉ ነገሮች ሌላው ትእግስት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) *ታገስ* አላህ ከነዚያ *ከታጋሾቹ ጋር* ነውና ይላል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ وَبَشِّرِ الصَّابِرِينَ * الَّذِينَ إِذَا أَصَابَتْهُم مُّصِيبَةٌ قَالُوا إِنَّا لِلَّهِ وَإِنَّا إِلَيْهِ رَاجِعُونَ * أُولَئِكَ عَلَيْهِمْ صَلَوَاتٌ مِّن رَّبِّهِمْ وَرَحْمَةٌ وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُهْتَدُونَ}**

ትርጉሙም (*ታጋሾችንም* (በገነት) አብስር፡፡ እነዚያን መከራ፤ በነካቻቸው ጊዜ «እኛ ለአላህ፤ ነን እኛም ወደርሱ ተመላሾች» ነን የሚሉትን (አብስር) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (እወቅ በምትጠላው ነገር በመታገሰው በዙ ደግ ነገር አለ) ትእግስት ማለት ስቃይ በሚደርስ ጊዜ መፍስን ሮሮ እንዳታሰማ፣ ምላስን አቤቱታ እንዳያበዛ፣ ሌሎችንም አካላት ከመርበርበት መግታት ነው፡፡ እሱም መንፈስን መዋጋት ግድ ይላል፡፡ ነብያችን ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለትግስት

የተዘጋጀን ሰው ትእግስት ይሰጠዋል፡ አንድ ሰው ከተሰተው ነገር ሁሉ ከትእግት የሰፋ ነገር አልተሰጠም፡፡)

አላህ (ዐ.ወ.) ከባሪያወ ጋር እንዲሆን የሚያደርገው ሌላው ነገር ደግሞ የአእምሮ ንቃት ነው፡፡ አንድ ሰው አላህ (ዐ.ወ.) በመንገድም ሆነ በአገር ቤት፣ ቤት ውስጥም ይሁን በአደባባይ የሚሰራውን ስራ በእውቀቱ ያከተተው መሆኑን ሲገነዘብ አይምሮ ንቁ ይባላል፡፡ ይህን ጉዳይ ሰይዲና ዩሱፍ (በአላህ እጠበቃለሁ እርሱ (የገዛኝ) ጌታዬ ኑሮዬን ያሳመረልኝ ነውና፤ (አልከዳውም)፡፡ እነሆ! በደለኞች አይድኑም») በማለታቸው ግልጽ አድርገውታል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በቁድስ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (በአሸናፊነቴ ይሁንብኝ እኔ በባሪያዬ ላይ ሁለት ፈርሃትን እንድሁም ሀለት አለመፍራትን በአንድ ላይ አልፈርድበትም፡፡ በዚህች አለም እኔ የማይፈራ ከሆነ በትንሳኤ ቀን እንድፈራ አደርገዋለሁ፡፡ በዚህች ዓለም የሚፈራኝ ከሆነ ደግሞ በትንሳኤ ቀን ፍርሃት እንዳያገኘው አደርጋለሁ፡፡)

አንድ ሰው አላህን አብዝቶ በማውሳቱም አላህ ከሱ ጋር ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (አስታውሱኝ አስታውሳችኋለሁ፡፡ ለኔ አመስግኑ አትካዱኝም፡፡) ነብኛችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡ እኔ ባሪያዬ እንደሚያስበኝ ከሱ ጋር ያገኘኛል ለብቻው ካሰበኝ እንደዚሁ አስበዋለሁ፡፡ ከሰዎችም ጋር ካስታወሰኝ ከነሱ በበለጡ በሪያወች ፊት አስታውሰዋለሁ፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር በመሆኑ በዚህች ዓለምም ሆነ በመጨው ዓለም የሚያገኘው ታላቅ መልካም ውጤት አለው፡፡ አላህ ከሱ ጋር የሆነ ሰው እሱ ከማንኛውም ተንኮል ይጠብቀዋል፡፡ ጎጂ ነገር ሁሉ ከሱ ገለል ያደርግለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَانًا وَقَالُوا حَسْبُنَا اللَّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ}

ትርጉሙም(እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- «ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው» ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!» ያሉ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{ وَمَنْ يَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ فَهُوَ حَسْبُهُ إِنَّ اللَّهَ بَالِغُ أَمْرِهِ قَدْ جَعَلَ اللَّهُ لِكُلِّ شَيْءٍ قَدْرًا}

ትርጉሙም (በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡ አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው፡፡ አላህ ለነገሩ ሁሉ የተወሰነ ጊዜን በእርግጥ አድርጓል፡፡) ማት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡ (አላህ ባሪያውን በቂ አይደለምን?)

በአላህ የተመካና እሱ እንደሚያግዘው እርግጠኛ የሆነ ሰው ጠላት አይደፍረውም፣ ቢጠይቅ አያሳፍረውም፣ የፈለገውንም አያሳጣው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለነብዩ ሙሳ «ለነፍሴም (በመልእክቴ) መረጥኩህ፡፡» እንድሁም «በእኔም ጥበቃ ታድግ ዘንድ፡፡» ለነብያችን (ሶ.ወ.) ደግሞ «ለጌታህ ፍርድም ታገሥ፡፡ አንተ በጥበቃችን ውስጥ ነህና፡፡» እንድሁም «ለእነሱ ከጌታቸው ዘንድ መልካም ምንዳ ያላቸው መኾኑን አብስር» ማለቱን ስንመራመር የአላህ ከኛ ጋር መሆንን ታላቅነትና መልካም ውጤቱን በግልጽ አእንገነዘባለን፡፡

ወደአላህ አብሮነት መግባት በሱም በዘላቂነት መቆየት የእርጋታና የመንፈስ እርካታ እንድሁም ከጭንቀትና መረበሽ የመራቅ መሰረት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ምክኒያቱም ትክክለኛውን መሰረት የጣለና ማንኛውም ነገር በአላህ እጅ መሆኑን ያረጋገጠ ሰው ለምን ይጨነቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{قُلِ اللَّهُمَّ مَالِكَ الْمُلْكِ تُؤْتِي الْمُلْكَ مَنْ تَشَاءُ وَتَنْزِعُ الْمُلْكَ مِمَّنْ تَشَاءُ وَتُعِزُّ مَنْ تَشَاءُ وَتُذِلُّ مَنْ تَشَاءُ بِيَدِكَ الْخَيْرُ إِنَّكَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ}

ትርጉሙም ((ሙሐመድ ሆይ!) በል፡- «የንግስና ባለቤት የኾንክ አላህ ሆይ! ለምትሻው ሰው ንግሥናን ትሰጣለህ፡፡ ከምትሻውም ሰው ንግሥናን ትገፍፋለህ፡፡ የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ፡፡ የምትሻውንም ሰው ታዋርዳለህ፡፡ መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና፡፡» ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{مَا يَفْتَحِ اللَّهُ لِلنَّاسِ مِنْ رَحْمَةٍ فَلَا مُمْسِكَ لَهَا وَمَا يُمْسِكْ فَلَا مُرْسِلَ لَهُ مِنْ بَعْدِهِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}.

ትርጉሙም (አላህ ለሰዎች ከችሮታ የሚከፍታት ለእርሷ ምንም አጋጅ የላትም፡፡ የሚያግደውም ከእርሱ በኋላ ለእርሱ ምንም ለቃቂ የለውም፡፡ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡) ማት ነው፡፡

የአላህ ባሮች አላህ ከነሱ ጋር መሆኑን ሲያስቡ የእሱን ማሰብ ታላቅነት ሲገመግሙ ለነሱ የመንፈስ እርካታ የመልካም አብሮ መኖርና የማህበረሰብ ደህንነት መረጋገጡን ይገነዘባሉ፡፡ የአላህ ባሮች በማንኛውም ጊዜና ቦታ አላህ ከነሱ የማይርቅ መሆኑን ሲያረጋግጡ ስርአተ ጥሩና ጠባየ መልካም ይሆናሉ፡፡ የአላህን ትእዛዝ ይፈፈጽማሉ የከለከለውንም ሁሉ አጥብቀው ይርቃሉ፡፡ የዚህችን ዓለምና የመጭውን ዓለም ጉዳዮች ለማሻሻልም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ያ ግለሰቡም ከቤተሰቡ፣ ከማህበረሰቡ፣ ከጓደኞቹ ጋር በሰላምና በጸጥታ ይኖራል፡፡ ይህም ለሰዎች እዝነት የመጣው የእስልምና ሃይማኖት ዋና መልእክት ነው፡፡

ጌታችን ሆይ! የእርዳታህ አብሮነት አይለየን፡፡ በሰፊው ችሮታህም የተካተትን አድርገን፡፡ ጸጋዎችህንም አስፋልን፡፡ በነገራችን ሁሉ ታማኝነተን ለግሰን፡፡ ሀገራችንም ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# (2)

# ይህ ነው እስልምና ማለት

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَاتَّبَعَ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا وَاتَّخَذَ اللَّهُ إِبْرَاهِيمَ خَلِيلًا}

ለአለው ለዐለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እርሱ መልካም ሠሪ ኾኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲኾን ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማን ነው አላህም ኢብራሂምን ፍጹም ወዳጅ አድርጎ ያዘው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

እውነተኛ እስልምና ማለት ለአላህ (ዐ.ወ.) ሙሉ በሙሉ እጅ መስጠት ለሱ መታዘዝና መገዛት ነው፡፡ እንድሁም እስልምና ማለት የአላህ መልከተኛ ሰይዲና ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) መውደድ፣ መከተልና አሳቸውንም አርአያ ማድረግ ነው፡፡ አሁንም እስልምና ማለት መልካም ምግባር፣ ለሱ መጋዛት፣ ለሱም ራስን ዝቅ ማድረግ፣ መንፈሰ መልካም መሆን፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር የአለው እንቅስቃሴ ፈካ ባለ ፊት መሆን፣ እዝነትና ርህራሄ ማሳየት፣ አለመን መገንባትና ማነጽ፣ ስልጣኔና ልማትን ማስፋፋት ነው፡፡ እስልምና ተከታዮቹ በርጋታም ሆነ በእንቅስቃሴ እንድሁም በመላ ሥራዎቻቸው ጎልቶ የሚታይ የሕይወት ስርአት ነው፡፡

የእስልምና እምነት ነገሮችን እንድናሻሻልና እንዲናድስ፣ ለዚህች ዓለምም ሆነ ለመጭው ዓለም የሚጠቅም ልማትን እንዲናከናውን የሚያዝ እንጂ በሃይማኖት ስም እንድናፈርስ የሚያዝ ሃማኖት አይደለም፡፡ እምነቱ ርህራሄ፣ ሰላምና ጸጥታ እንድሁም ሰላም በመላ የዓለማችን ክፍል እንዲሰፍን የሚሰብክ እምነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ} .

ትርጉሙም ((ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡) ማለት ነው፡፡

በጅብሪል (ዐ.ሰ.) ሐዲስ የሰፈሩትን የእስልምና ማእዛናት የሚመራመር ሰው እነዚህ ማእዘናት ቅን የሆነን ሰው በመገንባት ታላቅ ሚና ያላቸው መሆኑን በትክክል ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ጅብሪል ከአለታት አንድ ቀን ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በመምጣት (ሙሐመድ ሆይ! እስኪ ስለእስልምና ንገረኛ በማለት ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (እስልምና ብሎ ማለት ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም እንድሁም ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው ብለህ መመስከርህ፣ ስግደትን ደንቡን ጠብቀህ ማድረስህ፣ ዘካን መስጠትህ፣ ረመዳንን የምትፆም መሆንህና ወደሱም ለመድረስ የምትችል ከሆነ የሐጅን ሥራ ማከናውነህ ነው) አሉ፡፡

አንድ ሰው አላህ አጋር የሌለው ብቸኛ ፈጣሪ መሆኑንና ሰይዲና ሙሐመድ የሱ ባሪያና መልክተኛ መሆናቸውን ሲገነዘብ ለአላህ በመታዘዝና እሱ መላ ተግባራቱን የሚቆጣጠር መሆኑን በእርግጠኝነት እምኖ ትእዛዙን ይፈጽማል፡፡ ከከለከለውም ነገር አጥብቆ ይርቃል ወሰን ከመተላለፍም ይታቀባል፡፡ የታዘዘውን ነገር ከመፈጸም አይቦዝንም፡፡ እንድሁም የሱ ያልሆነን ሙብት ለማግኘት አይሞክርም፡፡ ይህ ምእምን ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) መከተሉን ለማሳመር ይጣጣራል፡፡ እሳቸው ያደርጉ እንደነበረውም ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት በርህራሄ፣ በእዝነት፣ ራስን ዝቅ በማድረግና በለዘብተኝነት የታነጸ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡

ከእስልምና ማእዘናት ዋናው የሆነው ስግደት ከአጸያፊና ከተጠላ ነግር በመከላከልና በአላህ መንገድ ቀጥ ብሎ እንዲጸና በማድረግ ለአላህ ባሪያ ያለው ጥቅም እጅጉን ከፍተኛ ነው፡፡ ያን ጊዜም ማንኛውም ሙስሊም በራሱ መንፈስም ሆነ በማህበረሰቡ መካከል በሰላም ይኖራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

اتْلُ مَا أُوحِيَ إِلَيْكَ مِنَ الْكِتَابِ وَأَقِمِ الصَّلَاةَ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ وَاللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ} .

ትርጉሙም (ከመጽሐፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ፡፡ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡) ማለት ነው፡፡

ዘካንም መስጠት ከእምነትና ከሰብአዊነት አንፃር ያለው ፋይዳ በጣሙን ከፍተኛ ነው፡ እሱ መንፍስን በቁሳቁስ ያለመጠን ከመተሳሰር ያድናል፡፡ በዚህም አንድ ሰው ገንዘብ ወደአንድ ነገር መድረሻ መሳሪያ እንጅ እሱ ራሱ መዳረሻ አለመሆኑን ይገነዘባል፡፡ ዘካን መስጠት ወደትብብር፣ መተዛዘንና የሌሎችን ስሜት ወደመገንዘብ የሚያደርስ በር ነው፡፡ እውነተኛ ሙስሊም ማህበረስብ ራሰወዳድነትም ሆነ አሉታዊነት የለበትም፡፡ ይህን ማለትም ሃይማኖታችን የስጦታ፣ የችሮታ፣

የመስዋእትነት፣ የመበገሮት፣ ሰዎችን ከራስ የማስቀደም ሃማኖት ሲሆን ለኔ ብቻ ማለትን፣ ግበጋባነትንና ስስታምነትን አጥብቆ ይዋጋል፡፡ ምእምን ገራገር፣ ቸርና ለጋስ ሊሆን ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አንሷሮችን ሲያመስግናቸው እንድህ ብሏል፡
{وَالَّذِينَ تَبَوَّءُوا الدَّارَ وَالْإِيمَانَ مِنْ قَبْلِهِمْ يُحِبُّونَ مَنْ هَاجَرَ إِلَيْهِمْ وَلَا يَجِدُونَ فِي صُدُورِهِمْ حَاجَةً مِمَّا أُوتُوا وَيُؤْثِرُونَ عَلَى أَنْفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ وَمَنْ يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِ فَأُولَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ}.

ትርጉሙም (እነዚያም ከበፊታቸው አገሪቱን መኖሪያ ያደረጉት እምነትንም የለመዱት ወደእነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ፡፡ (ስደተኞቹ) ከተሰጡትም ነገር በልቦቻቸው ውስጥ ቅሬታን አያገኙም፡፡ በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ፡፡ የነፍሱንም ንፍገት የሚጠበቅ ሰው እነዚያ እነሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
ፆምም እንደዘለሁ የሙስሊምን መልካም ምግባር በማስተካከል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መልካም ምግባሩ ሲስተካከል አላህ (ዐ.ወ.) ዘውትር የሚሰራውን ሁሉለ የሚቆጣጠር መሆኑን ባለመዘንጋት መንፈሱን በትእግስተና መከራን በመቻል ይገራታል፡፡ አላህን ከሚያስቆጣ ነገርም ከፍ እንዲትል ያደርጋታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ፆም ጠባቂ ነው፡፡ አንዳችሁ ፆም በሚይዝበት ቀን ጽያፍ ቃል አይናገር ድምጹንም ከፍ አያድርግ አንድ ሰው ቢሳደበው ወይም ሊታገለው ቢመጣ እኔ ፆም የያዝኩ ሰው ነኝ ይበል) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የሀሰት ቃልንና በሀሰት መሥራትን ያልተወ ሰው ለአላህ የሱ ምግብና መጠት መተው አያስፈልገውም፡፡)
ሐጅ ሥራውን ከማከናወኑ በፊት፣ በሚያከናውንበት ወቅትና ከፈጸመውም በኋላ የስነ ምግባርና የስርኣት ግዴታን መወጣት የሚጠይቅ ታላቅ ዒባዳ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{الْحَجُّ أَشْهُرٌ مَعْلُومَاتٌ فَمَنْ فَرَضَ فِيهِنَّ الْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي الْحَجِّ وَمَا تَفْعَلُوا مِنْ خَيْرٍ يَعْلَمْهُ اللَّهُ وَتَزَوَّدُوا فَإِنَّ خَيْرَ الزَّادِ التَّقْوَى وَاتَّقُونِ يَا أُولِي الْأَلْبَابِ}

ትርጉሙም (ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፡፡ በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም፡፡ ከበጎም ሥራ የምትሠሩትን ሁሉ አላህ ያውቀዋል፡፡ ተሰነቁም፤ ከስንቅም ሁሉ በላጩ ጥንቃቄ (አላህን መፍራት) ነው፡፡ የአእምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ፡፡) ማት ነው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ይላሉ፡ ‹እኔ የአላህ መልክተኛ እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (ሴትን ከመገናኘትና ከአመጽ ነፃ በሆነ መልኩ ሐጅን ያከናወነ ሰው እናቱ አንደወለደችበት ቀን (ንጹህ) ሆኖ ይመለሳል፡፡) በዚህ መልኩ ሁሉም የእስልምና ማእዘናት በማህበረሰቡ ደግን ነግር፣ ሰላምንና ደህንነት በማስፈን ረገድ ስፊ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ቀጥተኛውን ሃይማኖታችንን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው የመልካም ምግባር ሃይማኖትና ተልእኮውም ይህን መልካም ምግባር የተሟላ ማድረግ መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (እኔኮ የተላኩት መልካም መግባርን የተሟላ ለማድረግ ነው፡፡) እውነት፣ ቃልን ማክበር፣ አመኔታ፣ መልካም ሥራ፣ ዝምድናን መቀጠል፣ ቸርነት፣ ለጋስነት፣ ሰውን መርዳት፣ አክብሮት፣ ሰብእነት፣ በሰዎች ላይ ተንኮል ከመፈጸም መታቀብ፣ እርዳታ የሚጠይቅን ሰው ማገዝ፣ ጭንቀትን ማቃለልና ለእንስሳት ርህራሄ ማድረግ የሚሉት ተግባራት በሚፈጸሙበት ቦታ ትክክለኛው የእስልምና አላማ ተተግብሯል ማለት ይሆናል፡፡

የእስልምናን ስር መሰረት መገንዘብ፣ ገራገር የሆነውን የተልእኮውን ምስጢር ማወቅ አጅግ የላቁ የሆኑትን አላማዎቹንና ግቦቹን በጥልቅ መረዳት ይህንም ሁሉ ከዘመኑ አዳድስ ነገሮችና አስፈላጊነቱ ጋር አጣትሞ ገቢራዊ ማድረግ የዘመኑን ተግዳሮቶች ለመቋቋም፣ የጸንፈኛ አሻባሪ ቡድኖችን ልጓም ለመግታት፣ አፈንጋጭ እሳቦቶችን እንዳይስፋፉ ለመከበብ፣ አንድሁም ደረቅ፣ ግትርና ዝግነት ከአለቸው አዞረቶች፣ ከተሳሳተ ግንዛቤና ከጠባብነት ለመውጣት፣ ከዚያም ሰፊ፣ ቀላል፣ በጣም በሳልና ንቃት ወዳለበት ዐለም ለመግባት፣ የህዝብና የሀገርን ጥቅም ለማስከበር፣ ሰላም፣ ደህንነትና ጸጥታን፣ መረጋጋትን ለማረጋገጥ፣ ለመላ የሰው ልጅ ደስታን እውን ለማደርግ ሰፊ ሚና ያለቸውን የላቁ የሰብኣዊ እሴቶችን ለማስፋፋት አመራጭ የሌለውና አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ማንኛውም ሙስሊም ሊያከናውነው የሚገባ ከሆነ ተቀዳሚ ግዴታና እጅጉን አስፈላጊ ከሆኑ ተግባራት ቅድሚያ የሚሰጠው ለሰዎች ሁሉ የእስልምና መልካም ገጽታዎችን አጉልቶ ማሳየት የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህውም የዓለም ህዝብ ሁሉ እስልምና የሰላም እምነትና ሰላም እንድሰፍን የሚገፋፉ ሃማኖት መሆኑን እንድገነዘብ ነው፡፡ ሰላም ከአላህ ባሕርይ አዘል ስሞች አንድኛው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ}

ትርጉሙም (እርሱ አላህ ነው፡፡ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ... ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና ሰላምታ ሰላም የሚል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንድህ ላል፡

{وَلَا تَقُولُوا لِمَنْ أَلْقَىٰ إِلَيْكُمُ السَّلَامَ لَسْتَ مُؤْمِنًا}

ትርጉሙም (ሰላምታንም ወደናንተ ላቀረበ ሰው የቅርቢቱን ሕይወት ጥቅም የምትፈልጉ ኾናችሁ ምእመን አይደለህም አትበሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ በጀነት የጀነት ሰዎች ሰላምታም ሰላም -የሚል- ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَالْمَلَائِكَةُ يَدْخُلُونَ عَلَيْهِم مِّن كُلِّ بَابٍ سَلَامٌ عَلَيْكُم بِمَا صَبَرْتُمْ فَنِعْمَ عُقْبَى الدَّارِ}

ትርጉሙም (መላእክትም በእነርሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ፡፡ ሰላም ለእናንተ ይኹን፡፡ (ይህ ምንዳ) በመታገሳችሁ ነው፡፡ የመጨረሻይቱም አገር ምን ታምር!»

(ይሏቸዋል)፡፡ ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከስግደት በኋላ በሚከተሉታ ቃላት አላህን ይጸልዩ ነበር፡

(اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلاَمُ ، وَمِنْكَ السَّلاَمُ ، تَبَارَكْتَ يا ذَا الْجَلاَلِ وَالإِكْرَامِ) .

ትርጉሙም( ጌታዬ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ ሰላምም ካንተ ነው፡፡ በረከትህ በዛ አንተ የሞገስና የማክበር ባለቤት የሆንህ ጌታ፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት የሰውን ልጅ ክብር ለማስጠበቅ ሃሜትን፣ አሉባልታን፣ መቅኘነትን፣ በቃልም ይሁን በተግባር ወይም ጣትን በመቀሰር ሰው ማንኳሰስን አጥብቆ ይጠላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَى أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَى أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا بِالْأَلْقَابِ بِئْسَ الِاسْمُ الْفُسُوقُ بَعْدَ الْإِيمَانِ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُولَئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ}**

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፡፡ ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ፡፡ ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ወደወንድሙ በቁራጭ ብረት ያመለከተ ሰው ይህን ተግባሩን እስከሚያቆም ድረስ መላእክት ይረግሙታል፡፡ የናት ያባቱ ልጅ ወንድሙም እንኳን ቢሆን፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፊትን መምታትን እንድሁም በፊት ላይ ትኩሳት ማድረግን ከለክለዋል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ፊቱ ላይ የተተኮስን እንሰሳ ባዩ ጊዜ (የተኮሰውን ሰው አላህ ከእዝነቱ ያርቀው አሉ፡፡) ነብያችን (ሶ.ኢ.ወ.) ስለአንድት ቀንን ጹዋሚና ሌሊትን ቋሚ ነገር ግን ጎረቤተቿን የምታሰክፋ ሴትዮ በተጤቁ ጊዜ የሰጡት መልስ ( እሷ በገሀነም ውስጥ ናት፡፡) የሚል ነበር፡፡ ነብያችን እንድህ ማለታቸው ተወርቷል፡ (በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ጎረቤቱን አያስከፋ፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው እንግዳውን ያክብር፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው ደግን ነገር ይናገር አለዚያም ዝም ይበል፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትና በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰይዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ገራግሩ የእስልምና እምነት አስተምህሮ፣ መልካም ስነ መግባሮቹና የላቁ እሴቶቹ በባልደረቦቻቸው ልብ እንድሰርጹ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በመሆኑም በመጨረሻም አነዚህ አስተምህሮዎች ከሁሉም ሰው ጋር በአላቸው ግንኙነትም ሆነ በራሳቸው የእለት ከእለት ኑሮ ጎልቶ የሚታይ የሕይወት ስርኣታቸው ሆኗል፡፡ ለዚህም ነው (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጀዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብ ከሐበሻው ንጉስ ነጃሺ ፊት በቆሙ ጊዜ መጀመሪያ ለመግለጽና ለማብራራት የሞከሩት ከነዚህ እሴቶች ጥቂቶቹን ነበር፡፡ ሲያብራሩም እንድህ ብለዋል፡ ‹አንተ ንጉስ ሆይ! እኛ ታቦት የምንገዛ፣ በክት የምንበላ፣ ዝሙት የምንፈጽም፣ ዝምድንናን የምንቆርጥ፣ ጉርብትናን ፈጽሞ የማናከብርና ከኛ ጉልበተኛው ደካማውን የሚበላ የድንቁርና ሰዎች ነበርን፡፡

በዚህም ላይ እያለን ዘሩን፣ እውነተኛነቱን፣ ታማኝነቱን፣ ጥብቅነቱን የምናውቀውን ከኛ የሆነን መለከተኛ አላህ ወደኛ ላከ፡፡ አላህን በአንድ አምላክነቱ እንድንገዛው፣ ከሱም ሌላ ያለን እኛና አባቶቻችን እናመልከው የነበረውን ድንጋም ይሁን ጣኦት በኣድ አምላክን እርግፍ አድርገን እንድንተው ጥሪ አደረጉልን፡፡ በወሬያችን እውነተኞች፣ አደራ ጠባቂዎች፣ ዘምድን ቀጣዮች፣ መልካም ጎረቤቶች እንድንሆን፣ እርም ከሆኑ ነገሮችና ደመን ከማፍሰስ እንድንታቀብ አዘዙን፡፡ ጽያፍ እንዳንናገር፣ ሀሰት እንዳናወራ፣ የሙት ልጅ ገንዘብን ያላግባብ እንዳንበላና ንጹሃንን እንዳንዘልፍ ከለከለን፡፡ አንድ አላህን በሱ ማነንም ያለማጋራት እንድናመልክ፣ ስግደትን እንድናደርስ፣ ዘካንም እንድንሰጥ፣ ጾምንም እንድንጾም አዘዘን...›

እውነተኛ ሙስሊም አይዋሽም፣ አያታልም፣ አይከዳምም፡፡ እውነተኛ ሙስሊም ማለት ሰዎችን በምላሱም ሆነ በእጁ ተንኮል የማይጎዳ ሰው ነው፡፡ እውነተኛ ምእምን ማለተም ሰዎች በደማቸው፣ በክብራቸው፣ በገንዘባቸውና በሕይወታቸው እምነት የሚጥሉበት ሰው ነው፡፡ እውነተኛ ሙስሊም ማለት ከሱ ደግ ነገርና መልካም ሥራ እንጂ ወደሰዎች የማይደርስ በመሆኑ የእስልምና ሰነ ምግባር ገጽታ ጎልቶ የሚታይበት ሰው ነው፡፡

እውነተኛን ሙስሊም ግልጽ በሆነ ማብራሪያ ለማሳወቅ ብንፈልግ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሰጡት ማብራሪያ የተሻለ መግለጫ አናገኝም፡፡ እሳቸው እንድህ ብለዋል፡ (ምእምን ማን እንደሆነ ልንገራችሁን? ምእምን ማለት ሰዎች በገንዘባቸውና በሕይዎታቸው እምነት የጣሉበት ሰው ነው፡፡ ሙስሊም ማለት ደግሞ ሰዎች ከእጁና ከምላሱ ተንኮል የዳኑ የሆነ ሰው ነው፡፡ ታጋይ ማለትም ለአላህ በመታዘዝ ቀጥ እንድትል ነፍሱን የታገለ ሰው ነው፡፡ ሀገሩን የተወ ስደተኛ ማለትም ኃጢአትንና ወንጀልን የተወ ሰው ነው፡፡)

የአስልምና ሃይማኖት ተልእኮ የሰብእነት፣ የጥበብ፣ የመቻቻል፣ የርህራሄ፣ የሰፊነትና የለዘብተኝነት ተልእኮ ነው፡፡ የሚበታትን ሳይሆን የሚያሰባስብ፣ የሚያለያይ ሳይሆን የሚዋህድ ተልእኮ ነው፡፡ እስልምና ማለት ሙሉበሙሉ ፍትህ፣ እዝነት፣ መቻቻል፣ ማግራትና ሰብእነት ማለት ነው፡፡ እነዚህን የላቁ የሆኑ አላማዎችን የሚያራምድ ሰው በእውነተኛ እስልምና መመሪያዎች እየተመራ ነው፡፡ ከነዚህ አላማዎች ጋር የሚፃረር

ነገር የሚፈጽም ደግሞ ከትክክለኛዎቹ የእስልምና አላማዎችና ግቦች ጋር በሚጋጭ መመሪያ እየተመራ ነው፡፡
ጌታችን ሆይ! ለመልካም ጠባይ ምራን ወደመልካም ጠባይ የሚመራ አንተ እንጂ የለምና መጥፎ ጠባይንም ከኛ አርቅልን መጥፎ ጠባይንም የሚያርቅ ካንተሌላ የለምና፡፡ አንተ አዛኝና ርህሩህ ጌታ ሆይ! ሀገራችንና ህዝባችንን ጠብቅልን አሜን፡፡

# (3)

## የእምነት ፍሬዎች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ يَهْدِيهِمْ رَبُّهُمْ بِإِيمَانِهِمْ تَجْرِي مِنْ تَحْتِهِمُ الأَنْهَارُ فِي جَنَّاتِ النَّعِيمِ}**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ጌታቸው በእምነታቸው ምክንያት (የገነትን መንገድ) ይመራቸዋል፡፡ ከሥራቸው ወንዞች ይፈስሳሉ፡፡ በመጠቀሚያ ገነቶች ውስጥ ይኖራሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
አላህ (ዐ.ወ.) ለባሮቹ ከቸራቸው ጸጋዎች አንዱ የሰው ልጅ የሚሥራው መልካም ሥራ በመጨረሻ ደግ ፍሬ እንዲኖረው ማድረጉ ነው፡፡ መልካም ውጤታቸው ግለሰቡንና ማህበረሰቡን ከሚያካትቱ ተላላቅ ሥራዎች በመጀመሪያ የሚጠቀሰው መልካም ሥራ በአላህ (ዐ.ወ.) ማመን ነው፡፡ ሰይዲና ጅብሪል (ዐ.ሰ.) በጠየቃቸው ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሙእሚን ልብ ሊሰፍን ስለሚገባው እውነተኛ እምነት (በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ደግም ሆነ መጥፎ ማንኛውም ተግባር የአላህ ፍርድ በመሆኑ ማመነህ ነው) ብለዋል፡፡ እሱም እውነትህ ነው አላቸው)፡፡

ይህም የሚጠቁመው እምነት በምላስ የምንናገረው ቃል ሳይሆን በልብ የሚቀረጽ፣ በምላስ የምንገልጸውና በአካላት የምናከናውነው ተግባር መሆኑን ነው ይላሉ ሊቃውንት፡፡ ይህን ማለትም እምነት በልብ የጸናና የአላህን ትእዛዛት በመፈጸምና ከከለከለውም ነገር በመራቅ በተግባር የሚከናወን ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡

ሐሰን አል በስሪ የተሰኙት ሊቅ አንተ ሙእሚን ነህ ወይ? የሚል ጥያቄ በተሰነዘረላቸው ወቅት እንድህ በማለት ነበር የመለሱት፡ (እምነት ሲባል ሁለት ዓይነት ነው፡፡ የምትጠይቀኝ በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በጀነት፣ ሙቶ በመነሳትና በሒሳብ ስለማመን ከሆነ አዎ ሙእሚን ነኝ፡፡ ነገር ግን የምትጠይቀኝ እንድህ ስለሚለው የአላህ ቃል ከሆነ፡

{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَاناً وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ * الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلاَةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنْفِقُونَ * أُولَئِكَ هُمُ الْمُؤْمِنُونَ حَقّاً}

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በእውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡ በአላህ ይሁንብኝ እኔ ከነሱ አንዱ ልሁን አልሁን የማውቀው ነገር የለኝም፡፡

እውነተኛ እመነት ማለት የልብን ማእከላዊ ክፍል የሚነካና መላ መንፈስን የሚገዛ ሲሆን ጠንካራ ተጸእኖው በመንፈስና በአእምሮ እንድሁም በግለሰቡና በማህበረሰቡ ውጫዊ ገጽታም ይንጸባረቃል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ እውነተኛ እምነት ፍሬዎች አንዱ ለአማኙ የአላህ ባሪያ መልካም ስነ ምግባርን የሚያወርስ መሆኑ ነው፡፡ እምነትና ታማኝነት የማይለያዩ ባለአንድ ስር ሁለት ዛፎች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ታማኝነት የጎደለው ሰው እምነት የለውም፡፡ ቃሉን የማያከብር ሰውም ሃማኖት የለውም)፡፡ እንድሁም እመነትና የአክብሮት ይሉኝታ የማይለያዩ ጣምራዎች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የአክብሮት ይሉኝታና እምነት ባንድ ላይ ጣምራዎች ሆነዋል፡፡ አንደኛው በሚወገድበት ወቅት ሌላውም ይወገዳል)፡፡ እምነትና እውነተኛነት የተያያዙ ናቸው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰፍዋን ኢብን ሱለይም የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ሰዎች ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሙእሚን ቦቅቧቃ ይሆናል ወይ? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸው (አዎን) በማለት መለሱ፡፡ ሙእሚን ንፉግ ይሆናልን? ተብለው ቢጠየቁም (አዎን) አሉ፡፡ ከዚያም ሙእሚን ውሸታም ይሆናል ወይ? ተብለው ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም (አይሆንም) በማለት መለሱ፡፡

በርካታ ሊቃውንት እመነትን እውነት ነው በማለት ገልጸውታል፡፡ ሲያብራሩም እውነተኛ እምነት ጉዳት ሊያደርስበት የሚችል መሆኑን ቢገምትም እንኳ አውነትን መናገርና ሊጠቅመው የሚችል መሆኑን ቢገምትም እንኳ ሀሰትን ከመናገር መታቀብ ነው ይላሉ፡፡ በመልካም ምግባር የታነጸ ሰው ብታገኝ ይህ የእውነተኛ እመነት ፍሬ መሆኑን እወቅ፡፡ ወደወነት አዘንባዩ ሃይማኖታችን የመልካም ምግባር፣ የማበጀት፣

የግንባታና የልማት ሃይማኖት ነው፡፡ ከዚህ የሚጨምር ሰው ካየህ ከሃይማኖት ደንቦች ውጭ ባእድ ነገር የጨመረ መሆኑን እወቅ፡፡

ከአምነት ፍሬዎች ሌላው ደግሞ ቀስታና መረጋጋት ነው፡፡ እመነት በአንድ ሰው መንፈስ ውስጥ በሚመቻችበት ወቅት ያን ጊዜ መንፈሱ በርጋታ፣ በእርግጠኝነትና በርካታ ትሞላና በዚህች ዓለምና በመጨውም ዓለም ተደሳች ትሆናለች፡፡ እውነትኛ ሙእሚን ከደረሰበት መከራ በምን ዓይነት ሊያመልጥ የማይችል እንድሁም ያ ከሱ ያመለጠው መከራ በምን መልኩ ሊደርስበት የማይችል መሆኑን በእርግጠኝነት ያውቃል፡፡ በመሆኑም በደስታ ጊዜ ከሚያደርሰው የምስጋና ደረጃ በስቃይ ጊዜ ወደትእግስት ደረጃ ይሸጋገራል፡፡ ማንኛውም አላህ በሱ ላይ የፈረደበት ነገር ለሱ ደግ መሆኑን በመገንዘብ መንፈሱ ትረካለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

{وَمَن يُؤْمِن بِاللَّهِ يَهْدِ قَلْبَهُ}

ትርጉሙም (በአላህም የሚያምን ሰው ልቡን (ለትዕግስት) ይመራዋል...) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የሙእሚን ነገር የሚገርም ነው፡፡ ነገሩ ሁሉ ለሱ መልካም ነው፡፡ ያም ነገር ለሙእሚን ብቻ እንጂ ለማንም አይሆንም፡፡ እሱ ደስታ ቢያጋጥመው ያመሰግናል፡፡ ያም ለሱ መልካም ነገር ነው፡፡ መከራም ቢደርስበት ይታገሳል ያም ለሱ መልካም ነገር ነው)፡፡

ከእምነት ፍሬዎች ሌላው ደግሞ እምነት አማኙነት አጥፊ ኃጢአቶችን እንዳይፈጽም የሚጠብቀው መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ዝሙተኛ ዝሙት ሲፈጽም እሱ አማኝ ሆኖ አይደለም፡፡ አስካሪ ነገር የሚጠጣም እሱን ሲጠጣ አማኝ ሆኖ አይደለም፡፡ ሌባም ሲሰርቅ እሱ አማኝ ሆኖ አይደለም፡፡ ሰዎች እሱን ሲያነሳ ዓይኖቻቸውን ወደሱ እየሰነዘሩ ዘረፋን ሲፈጽምም እሱ አማኝ ሆኖ አይደለም)፡፡

እንደዚሁም እውነተኛ ሙእሚን በማሾፍ፣ በማፌዝና በምጥፎ ጥርጣሬ የሰዎችን ስሜት ከመጉዳት አጥብቆ ይርቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَى أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَى أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا بِالْأَلْقَابِ بِئْسَ الِاسْمُ الْفُسُوقُ بَعْدَ الْإِيمَانِ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُولَئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፡፡ ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ፡፡ ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اجْتَنِبُوا كَثِيرًا مِّنَ الظَّنِّ إِنَّ بَعْضَ الظَّنِّ إِثْمٌ وَلَا تَجَسَّسُوا وَلَا يَغْتَب بَّعْضُكُم بَعْضًا أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ أَن يَأْكُلَ لَحْمَ أَخِيهِ مَيْتًا فَكَرِهْتُمُوهُ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ تَوَّابٌ رَّحِيمٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፤ ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና፡፡ ነውርንም አትከታተሉ፡፡ ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፡፡ አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፤ (ሐሜቱንም ጥሉት)፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{لَّوْلَا إِذْ سَمِعْتُمُوهُ ظَنَّ الْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بِأَنفُسِهِمْ خَيْرًا وَقَالُوا هَٰذَا إِفْكٌ مُّبِينٌ} .

ትርጉሙም ((ውሸቱን) በሰማችሁት ጊዜ ምእምናንና ምእምናት በጎሶቻቸው ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም..) ማለት ነው፡፡

ድጋፍና ድል ሌላው የእምነት ፍሬ ነው፡፡ እውነተኛ እምነት አንድን ባሪያ ዘወትር ከአላህ ጋር እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَنَّ اللَّهَ مَعَ الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም ( አላህም ከምእምናን ጋር ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِن تَنصُرُوا اللَّهَ يَنصُرْكُمْ وَيُثَبِّتْ أَقْدَامَكُمْ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን (ሃይማኖቱን) ብትረዱ፤ ይረዳችኋል፡፡ ጫማዎቻችሁንም ያደላድላል፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{إِنَّا لَنَنصُرُ رُسُلَنَا وَالَّذِينَ آمَنُوا فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيَوْمَ يَقُومُ الْأَشْهَادُ}

ትርጉሙም (እኛ መልክተኞቻችንን፣ እነዚያንም ያመኑትን በቅርቢቱ ሕይወት ምስክሮችም በሚቆሙበት ቀን በእርግጥ እንረዳለን፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡

{وَكَانَ حَقًّا عَلَيْنَا نَصْرُ الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም( ምእመኖቹንም መርዳት በእኛ ላይ ተገቢ ሆነ፡፡) ማለት ነው፡

{الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُواْ لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَاناً وَقَالُواْ حَسْبُنَا اللّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ* فَانقَلَبُواْ بِنِعْمَةٍ مِّنَ اللّهِ وَفَضْلٍ لَّمْ يَمْسَسْهُمْ سُوءٌ وَاتَّبَعُواْ رِضْوَانَ اللّهِ وَاللّهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ} .

ትርጉሙም(እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- «ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው» ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!» ያሉ ናቸው፡፡ ከአላህም በኾነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ፡፡ የአላህንም ውዴታ ተከተሉ፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡) ማት ነው፡፡

ከእምነት ፍሬዎች ሌላው ደግሞ አላህ (ዐ.ወ.) የዚያን የሙእሚን ባሪያውን ውዴታ በፍጥረታቱ ዘንድ የሚያሰፍን መሆኑ ነው፡፡ ትክክለኛ ሙእሚን ልዝብ፣ ሰዎችን የሚለምድና እነሱም የሚለምዱት መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጹኣል፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ سَيَجْعَلُ لَهُمُ الرَّحْمَنُ وُدًّا}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና በጎ ሥራዎችን የሠሩ አልረሕማን ለእነሱ ውዴታን ይሰጣቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡

አንድ እውነተኛ ሙእሚን በንጹህ ልቡ ወደአላህ (ዐ.ወ.) ከዞረ አላህ በቀጥታ የሚቀበለው መሆኑን ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ባወሩት የቁድስ ሐዲስ እንድህ ሲሉ አብራርተዋል፡ (አላህ አንድን ባሪያ ሲወደው ጅብሪልን ይጠራና አላህ እገሌን ይወደዋልና ዉደደው ይለዋል፡፡ ጅብሪልም ይወደዋል፡፡ ጀብሪልም በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድ አላህ እገሌን ይወደዋልና ውደዱት ሲል ጥሪ ያስተላልፋል፡፡ የሰማይ ነዋሪዎችም ይወዱታል፡፡ ከዚያም በምድር ለሱ ቅቡልነትን ይቸረዋል፡፡ በሌላ ቁድስ ሐዲስም እንድህ ይላሉ፡ (በሪያዬ ዘወትር በፈቃዱ በሚያደርሳቸው ዒባዳዎች ወደኔ አይቃረብም በዚያ ጥረቱ የምወደው ብሆን እንጂ፡፡ ከወደድኩትም የሚሰማበት መስሚያው፡ የሚያበት ማያው፣ በሱ የሚሠራበት እጁና በሱ የሚራመድበት እግሩ እሆነዋለሁ)፡፡

ችግር መወገድና መከራ መነሳትም ሌላው የእምነት ፍሬ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እነድህ ይላሉ፡ (እኔ በአንድ ሰው ላይ ጭንቀት ወይም ከዚህች ዓለም መከራዎች አንዱ በሚደርስበት ጊዜ በሱ አላህን ሲጸልይ አላህ መፍትሄ የሚሰጥበትን ነገር አልነግራችሁም ወይም? ) ሰዎችም እሺ ነገሩን አሉ፡፡ እሳቸውም (የአሳው ባለቤት ጸሎት ነው፡፡ አሉና፡

{لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنْتُ مِنَ الظَّالِمِينَ}

ትርጉሙም (ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ጥራት ይገባህ፡፡ እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ .. ፡፡ የምትለዋን አንቀጽ ጠቀሱና አላህ እንድህ ብሏል አሉ፡

{فَاسْتَجَبْنَا لَهُ وَنَجَّيْنَاهُ مِنَ الْغَمِّ وَكَذَلِكَ نُنجِي الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም(ለርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ ከጭንቅም አዳነው፡፡ እንደዚሁም ምእመናንን እናድናለን፡፡) ማለት ነው፡፡ ይህ ጸሎትና የአላህ መቀበለም ለመላ ምእምናን አላህ የፈረደው ጸጋ ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ከእመነት ደጋግ ፍሬዎች እጅጉን ታላቁ የማህበራዊ ሰላምና ደህንነት የሚያረጋግጥ መሆኑ ነው፡፡ አንድ ትክክለኛ ሙእሚን እመነት በልቡ ሙሉ ለሙሉ ሲሰርጽ የደህንነት፣ የሰላምና የመረጋጋት ምንጭ ስለሚሆን ሰዎች በሐይወታቸውም ሆነ በንበረታቸው ሙሉ እምነት ይጥሉበታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሙስሊም ማለት ሰዎች በምላሱም ሆነ በእጁ ከሱ በኩል ምንም ተንኮል የማያገኛቸው የሆነ ሰው ነው፡፡ ሙእሚን ማለትም ሰዎች በገንዘባቸውም ሆነ በክብራቸው እምነት የሚጥሉበት የሆነ ሰው ነው)፡፡

የእስልምና እምነት ተከታይ ባይሆኑምንኳ በሰላም የሚኖሩን ሰዎች ሰላም ማደፍረስና በነሱም ላይ ጥቃት መሰንዘር የሙእሚን ጸባይ አይደለም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ቃል የተጋባን ሰው የገደለ ሰው የጀነትን ጠረን አያገኝም፡፡ ጠረኗ ከአርባ ዓመት ርቀት ባሻገር የሚሸት ሆኖ ሳለ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጎረቤቱን የሚጎዳና ጎረቤቱ ተርቦ እያለ ጠግቦ ያደረ ሰው እምነት የሌለው መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (በአላህ ይሁንብኝ አላመነም በአላህ ይሁንብኝ አላመነም በአላህ ይሁንብኝ አላመነም አሉ)፡፡ ሰዎችም እሱ ማነው ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ጎረቤቱ ከተንኮሉ የሚፈራ የሆነ ሰው) አሉ፡፡ አንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (አጠገቡ ያለ ጎረቤቱ የተራበ መሆኑን እያወቀ ጠግቦ ያደረ ሰው በኔ አላመንም)፡፡ ትክክለኛ እመነት የሚባለው ያ መልካም ለመስራት እንድሁም ሌሎችን ለማገዝ የሚገፋፋ የሆነው እምነት ነው፡፡ እሱም የባለቤቱን ጸባይ ያሳምራል የአላህን ወዴታ በመፈለግ በእዝነትና ርህራሄ የተሞላው የፍጥረታት ጋር ግንኙነቱ መልካምነትም ጎልቶ ይታያል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንደህ ይላል፡

**﴿وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَى حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا * إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنْكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا﴾.**

ትርጉሙም (ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ «የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡) ማለት ነው፡፡

ሌላው ታላቁ የእምነት ፍሬ ደግሞ በመጭው ዓለም አላህ (ሱ.ወ.) ለምእምናን ባሮቹ ያሀጋጀው ታላቅ ምንዳና ዘላቂው ጸጋ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**﴿إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ يَهْدِيهِمْ رَبُّهُم بِإِيمَانِهِمْ تَجْرِي مِن تَحْتِهِمُ الْأَنْهَارُ فِي جَنَّاتِ النَّعِيمِ﴾**

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ጌታቸው በእምነታቸው ምክንያት (የገነትን መንገድ) ይመራቸዋል:: ከሥራቸው ወንዞች ይፈስሳሉ:: በመጠቀሚያ ገነቶች ውስጥ ይኖራሉ::) ማለት ነው::

{وَبَشِّرِ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أَنَّ لَهُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي مِنْ تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ}

ትርጉሙም (እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችንም የሠሩትን ለነርሱ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያሏቸው መኾኑን አብስራቸው:: ) ማለት ነው::

{وَالَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أُولَئِكَ أَصْحَابُ الْجَنَّةِ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ}

ትርጉሙም (እነዚያም ያመኑት በጎ ሥራዎችንም የሠሩት እነዚያ የገነት ጓዶች ናቸው:: እነርሱ በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው:: ) ማት ነው::

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ إِنَّا لَا نُضِيعُ أَجْرَ مَنْ أَحْسَنَ عَمَلًا}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችንም የሠሩ እኛ ሥራን ያሳመረን ሰው ምንዳ አናጠፋም::) ማለት ነው::

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلًا * خَالِدِينَ فِيهَا لَا يَبْغُونَ عَنْهَا حِوَلًا} .

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው:: በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ከእርሷ መዛወርን የማይፈልጉ ሲኾኑ፤ (መስፈሪያቸው ነው):: ማለት ነው:: ነብያችን (ሱ.ወ.) አላህ በመጭው ዓለም ለደጋግ ባሮቹ ዓይን አይቶት የማያውቅና በማንኛውም ሰው ልብ ውል ብሎ የማያውቅ ነገር ማዘጋጀቱን ገልጸው የሚከተለውን አንቀጽ አንብበዋል፡

{فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَا أُخْفِيَ لَهُمْ مِنْ قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ} .

ትርጉሙም (ይሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም::) ማለት ነው::

እኛ ሁላችንም መተዛዘን፣ መተባበርና የአክብሮት ይሉኝታ የተሞላ እምነት እውን ማድረግ እጅጉን ያስፈልገናል:: ከሀሰት፣ ከማታለል፣ ከክህደት፣ ከሀሜትና ከበደል ልንርቅ ይገባል:: የማንኛውንም ሰው ህይዎትና ንብረት መጠበቅ፣ የሀገረንም ክብር ማስከበር ይጠበቅብናል::

ጌታችን ሆይ እምነትን እንድንወድ አድርገን በልባችንም አውበው:: ክህደትን፣ ብልሹነትንና አመጽን እንድንጠላ አድርገን:: ቅንን መንገድ ከሚከተሉትም አድርገን:: ሀገራችንንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን::

# (4)

## የበጎ ሥራና የመጥፎ ሥራ ግንዛቤ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{مَّنْ عَمِلَ صَالِحًا فَلِنَفْسِهِ وَمَنْ أَسَاءَ فَعَلَيْهَا وَمَا رَبُّكَ بِظَلَّامٍ لِّلْعَبِيدِ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (መልካም የሠራ ሰው ለነፍሱ ነው፡፡ ያጠፋም ሰው በእርሷ ላይ ነው፡፡ ጌታህም ለባሮቹ በዳይ አይደለም፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ከጌታቸው በማውራት አላህ (ሱ.ወ.) (ባሮቼ ሆይ! እነሱ እኔ የምመዘግብላችሁ ሥራዎቻችሁ ናቸው፡፡ የነሱንም ምንዳ አሟልቼ ስሰጣችሁ ደግን ያገኘ አላህን ያመስግን፡፡ ከደግ ሌላን ያገኘ ደግሞ ራሱን እንጂ ማነንም አይውቀስ ብሏል) ያሉት ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ዐ.ወ.) የሰውን ልጅ በእጁ በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጥሮ በውስጡም ከመንፈሱ ነፍቶበታል፡፡ በአእምሮ ከሌሎች ፍጥረታት ለይቶታል፡፡ መላእክት እንዲሰግዱለት አደርጓል፡፡ በዓለም ያለውን ነገር ሁሉ ለሱ ተገዥ አድርጎ ከብዙ ፍጥረታትም አብልጦታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي ءَادَمَ وَحَمَلْنَاهُمْ فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَرَزَقْنَاهُمْ مِّنَ الطَّيِّبَاتِ وَفَضَّلْنَاهُمْ عَلَى كَثِيرٍ مِّمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلاً}

ትርጉሙም (የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፡፡ በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው፡፡ ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው፡፡ ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህውም የሰው ልጅ ስማይና ምድር እንድሁም ተራራዎች እንዲቀበሉ ቀርቦላቸው አንችልም እንፈራለን ያሉትን ታላቅ አደራ ተሸክሟልና ነው፡፡ ይህ አደራ ሥራና ድካም የሚጠይቀው ግዴታና ምድርን የማልማት አደራ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

{فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِن فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيرًا لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}.

ትርጉሙም (ሶለቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ሙስሊም በሕይወቱ የሚያከናውነው ተግባር ሁሉ በመልካም ወይም በመጥፎ የሥራ ሚዛኑ የሚካተት መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ላል፡

{فَمَنْ يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَه * وَمَنْ يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَه}

ትርጉሙም (የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል፡፡ የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል፡፡) ማት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{ يَوْمَ تَجِدُ كُلُّ نَفْسٍ مَّا عَمِلَتْ مِنْ خَيْرٍ مُّحْضَرًا وَمَا عَمِلَتْ مِن سُوءٍ تَوَدُّ لَوْ أَنَّ بَيْنَهَا وَبَيْنَهُ أَمَدًا بَعِيدًا وَيُحَذِّرُكُمُ اللَّهُ نَفْسَهُ وَاللَّهُ رَءُوفٌ بِالْعِبَادِ}

ትርጉሙም (ነፍስ ሁሉ ከመልካም ነገር የሠራችውን የቀረበ ኾኖ የምታገኝበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ከመጥፎም የሠራችው በርስዋና በርሱ (በኀጢአትዋ) መካከል በጣም የሰፋ ርቀት ቢኖር ትመኛለች፡፡ አላህ ነፍሱን ያስጠነቅቃችኋል፡፡ አላህም ለባሮቹ ሩኅሩኅ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ሥራ ስንል ማንኛውም ሰው በቃልም ሆነ በተግባር የሚፈጽመውን ነገር ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ መልካም ሥራ ደግሞ ለአላህ የጠራና በጥንቃቄም የተሰራ መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاءَ وَيُقِيمُوا الصَّلَاةَ وَيُؤْتُوا الزَّكَاةَ وَذَلِكَ دِينُ الْقَيِّمَةِ}

ትርጉሙም (አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)፡፡ ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (አላህ አንዳችሁ ሥራ ሲሠራ በጥራት ሲያከናውነው ይወድለታል፡፡) በእስልምና እምነት መልካም ሥራ ሲባል እንደ ስግደት፣ጾም፣ ዘካ፣ ሓጅና አላህን ማውሳት ያሉ አላህ በባሮቹ ላይ ግድ ያደረጋቸውን ነገሮች የሚያካትት ሰፊ ፍች ያዘለ ቃል ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች አላህ (ሱ.ወ.) ባሮቹ እንዲፈጽሟቸው ግድ ያደረጋባቸው የሰው ልጅ ተግባራት መሆናቸው አላህ (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ሲክ አመልክቷል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا ارْكَعُوا وَاسْجُدُوا وَاعْبُدُوا رَبَّكُمْ وَافْعَلُوا الْخَيْرَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! (በስግደታችሁ) አጎንብሱ፣ በግንባራችሁም ተደፉ፣ ጌታችሁንም ተገዙ፣ በጎንም ነገር ሥሩ፣ ልትድኑ ይከጀልላችኋልና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ}

ትርጉሙም (ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ፡፡ ምጽዋትንም ስጡ፡፡ መልክተኛውንም ታዘዙ፡፡ ለእናንተ ሊታዘንላችሁ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)እንድህ ይላሉ (ነጽህና የእምነት ግማሽ አካል ነው፡፡ ምስጋና ለአላህ ይገባው የምትለው ቃል ሚዛንን ትሞላለች፡፡ ጥራትና ምስጋና ለአላህ ይሁን የሚሉት ቃላት ከሰማያትና ከምድር መካከል ያለውን ቦታ ይሞላሉ፡፡ ስግደት ብርሃን ነው፡፡ ምጽዋት መረጃ ነው፡፡ ትእግስት ችቦ ነው፡፡ ቁርኣን ለአንተ የሚመሰክርልህ ወይም በአንታ ላይ የሚመሰክርብህ ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ ማለዳ ይወጣሉ፡፡ ከነሱም ራሱን የሚሸጥ አለ፡፡ በዚህ ተግባሩም ከእሳት ያድናታል ወይም ያጠፋታል)፡፡

ማንኛውም ሙስሊም ሊታነጽበት የሚገባው ሌላው መልካም ሥራ ደግሞ እውነተኝነትና መልካም አንድበት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَقُلْ لِعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ}

ትርጉሙም (ለባሮቼም በላቸው፡- ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ እኔ ዘንድ በጣም ተወዳጁ እነዚያ በመልካም ጸባያቸው በላጭ የሆኑት፣ ለሰዎች የሚመቹት፣ እነዚያም ሰዎችን በቀላሉ የሚለምዱትና ሰዎችም በፍጥነት የሚለምዷቸው ናቸው)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ ደግሞ የምእምናንን ሁኔታ እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (የሙሐመድ መንፈስ በእጁ በሆነው ጌታ ይሁንብኝ የምእምን ምሳሌ ደግን ነገር ተምግባ ደግን ፍሬ እንዳፈራች ወደቃም እንዳልተሰበረችና እንዳልተበላሸችም የቴምር ዛፍ ዓይነት ነው)፡፡

መልካም ሥራ በአንድ በኩል ተፍጽሞ በሌላ በኩል የሚተው ተግባር አይደለም፡፡ ይልቁንም ማንኛውንም እሴት የሚያረጋግጥ፣ ጥሩ መንፈስ ያለው በመስማማትና በመተባበር የተሞላና ፍቀር መተዛዘንና መታቻቸል የሰፈነበት የተሳሰረ ማህበረሰብ በመገንባት ታላቅ ድርሻ ያለው ተግባር መልካም ሥራ ይባላል፡፡ የእስልምና እምነት አንድ ሰው ራሱን ከእርም ነገር ለማዳን ወደተፈቀደ ሥራ መውጣቱን እንድሁም በላቡ ልጆቹንና መላ ቤተሰቡን ማስተዳደሩን ከአላህ ዘንድ ምንዳ የሚያገኝበት መልካም ሥራ አድርጎለታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ይህ ዓይነቱ ተግባር በአላህ መንገድ እንደመውጣት መሆኑን አብስረዋል፡፡

አንድ ቀን በነብያችን አጠገብ አንድ ሰውዬ ሲያልፍ ብርታቱንና ጠንካራ ጥረቱን ባልደረቦቻቸው አዩ፡፡ እነሱም የአላህ መልከተኛ ሆይ ይህ ሥራው በአላህ መንገድ በሆነ ኖሮ እንዴት ደስ ይል ነበር አሉ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ጥረቱ ለህፃናት ልጆቹ ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ ለአረጋዊያን ወላጆቹም የሚተጋ ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ ራሱን ከእርም ነገር ለመጠበቅም ወጥቶም ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ጥረቱና ትግሉ ለይዩልኝ ይስሙልኝና ለመፎከር ከሆነ በሰይጣን መንገድ ነው)፡፡

እኛ በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መልካም መከተል ሊኖረን ይገባል፡፡ ነብያችን በራሳቸው በርካታ ነገሮችን ያከናውኑና ቤተሰቦቻቸውንም ያግዙ ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ

ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ ‹የአላህ መልክተኛ ጫማቻውን ይጠፍሩና ልብሳቸውን ይሰፉ እንድህም እንደማንኛችሁም ቤት ውስጥ አንዳንድ ሥራዎችን ያከናውኑ ነበር›፡፡ ይላሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ለቤተሰቡ ወጭ ሲያወጣ ከአላህ ዘንድ ምንዳ ማግኘትን ካሰበ ያወጭ ለሱ እንደምጽዋት ይቆጠርለታል)፡፡ አንድሁም በሌላ ሐዲስ ( ከናንት ደጋችሁ ለቤተሰቡ በጣም ደግ የሆነው ሰው ነው፡፡ እኔ ልቤተሰቤ ከናንተ የበለጥ ደግ ነኝ) ብለዋል፡፡

ከመልካም ሥራዎች ሌላው ደግሞ ይነስም ይደግም የቁሳቁስም ይሁን የመንፈስ ድጋፍ ለማድረግ አንድ ሰው ሌላውን ለመጥቀም የሚሠራው ተግባር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَمَنْ يَفْعَلْ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ مَرْضَاتِ اللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا}

ትርጉሙም (ይኸንንም (የተባለውን) የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ትርፍ የጭነት ከብት ያለው የጭነት ከብት ለሌለው ሰው ይስጥ፡፡ ትርፍም ስንቅ ያለው ሰው ስንቅ ለሌለው ይስጥ)፡፡ የደግ ሥራ መስኮች በርካታ መሆናቸው ሲያበስሩ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)እንድህ ይላሉ፡ ( የደግ ሥራ በሮች አያሌዎች ናቸው፡፡ አላህን ማጥራት፣ ማመስገን፣ ከፍከፍ ማድረግ፣ ሌላ አምላክ እነደሌለ መግለጽ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል፣ ከመንገድ ጎጂን ነገር ማስወገድ፣ መስማት የተሳነውን ማሰማት፣ ማየት ያቃተውን መንገድ መምራት፣ ጉዳይ ለማውጣት የሚጠይቅን ሰው ወደጉዳዩ መምራት፣ ድረሱልኝ የሚልን ሰው ለማዳን በሙሉ ጉልበት መስራት፣ ደከማን ለማገዝ በጠንካራ ክርን መንቀሳቀስና የመሳሰሉት ተግባራት ለነፍሳችን ስንል የምንፈጽመው ምጽዋት ይሆናል)፡፡

ማበጀትና ማልማትም መልካም ስራ ነው፡፡ በቅዱስ ቁርአን ስለሥራ የሚያወሱ ሦስ መቶ ስድሳ የሚሆኑ አንቀጾች ሰፍረው እናገኛለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ الأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا}

ትርጉሙም (እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ማለትም በእርሻ፣ በኢንዱስትሪና በንግድ ዘርፍ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ ከአላህ ዘንድ ታላቅ ምንዳ አላቸው ማለት ነው፡፡

{وَأَنزَلْنَا الْحَدِيدَ فِيهِ بَأْسٌ شَدِيدٌ وَمَنَافِعُ لِلنَّاسِ}

ትርጉሙም (ብረትንም በውስጡ ብርቱ ኀይልና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያልሉበት ሲኾን አወረድን፡፡ ) ማለት ነው፡፡ አንድሁም እንድህ ይላል፡

{فَأَوْحَيْنَا إِلَيْهِ أَنِ اصْنَعِ الْفُلْكَ بِأَعْيُنِنَا وَوَحْيِنَا}

ትርጉሙም (ወደርሱም (እንዲህ ስንል) ላከን «በተመልካችነታችንና በትእዛዛችንም ታንኳን ሥራ...) ማለት ነው እንድሁም እንድህ ይላል፡

وَمِنْ{أَصْوَافِهَا وَأَوْبَارِهَا وَأَشْعَارِهَا أَثَاثًا وَمَتَاعًا إِلَى حِينٍ}

ትርጉሙም (ከበግዋ ሱፎች፣ ከግመልዋም ጠጉሮች፣ ከፍየልዋም ጠጉሮች የቤት ዕቃዎችን እስከ ጊዜም ድረስ መጠቃቀሚያን (አደረገላችሁ)፡፡ ማለት ነው፡፤ አንድህም ይላል፡

{وَجَعَلَ لَكُمْ سَرَابِيلَ تَقِيكُمُ الْحَرَّ وَسَرَابِيلَ تَقِيكُمْ بَأْسَكُمْ }

ትርጉሙም (ሐሩርንም (ብርድንም) የሚጠብቋችሁን ልብሶች የጦራችሁንም አደጋ የሚጠብቋችሁን ጥሩሮች ለእናንተ አደረገላችሁ፡፡ እንደዚሁ ትሰልሙ ዘንድ ጸጋውን በእናንተ ላይ ይሞላል፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ላል፡

{وَجَعَلَ لَكُمْ مِنْ جُلُودِ الأَنْعَامِ بُيُوتًا تَسْتَخِفُّونَهَا يَوْمَ ظَعْنِكُمْ وَيَوْمَ إِقَامَتِكُمْ}.

ትርጉሙም (ከእንስሳዎችም ቆዳዎች በጉዟችሁ ቀን በመቀመጫችሁም ቀን የምታቀልላቸውን ቤቶች ለናንተ አደረገላችሁ፡፡ ) ማት ነው፡፡

መልካም ሥራ ሰውን በሚጠቅም ነገር ብቻ አይወሰንም፡፡ እንሰሳትና ማንኛውንም ነገር የሚያካትት መሆንም አለበት፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በአንድ የከሳ ግመል አጠገብ ሲያልፉ ባዩት ጊዜ (እነዚህን የማይናገሩ እንስሳት በተመለከተ አላህን ፍሩ፡፡ ደህና ሲሆኑ ተቀመጧቸው፡፡ እንድሁም ስተተዋቸውም ደህና ይሁኑ) አሉ፡፡ በሌላ ሐዲስ ደግሞ (አንድ ሰውዬ በመንገድ ሲያልፍ እሾክ ያለበት የዛፍ ቀንዘል አየ፡፡ እሱንም ከመንገድ ገለል አደረገው፡፡ ይህን ተግባሩን አላህ (ዐ.ወ.) ወደደለትና ምህረት አደረገለት) ብለዋል፡፡ አሁንም በሌላ ሐዲስ ( እኔ አንድ ሰውዬ በመንገድ ማሀል ሰው ታሰቃይ የነበረችን ዛፍ በመቁረጡ በጀነት ሲንጎራደድ እይቻለሁ) ብለዋል፡፡

መጥፎ ስራ ደግሞ የሰውን ልጅ ከማበጀት ወደማጥፋት መስመር የሚያወጡና አላህ (ዐ.ወ.)ን የሚያስቆጡ ተግባራትን ሁሉ ያካትታል፡፡ በዚያን ጊዜ አንድ ሰው ግድ ከሆኑ የአላህ ትእዛዛት መራቅ በአንፃሩም ለወላጆች አለመታዘዝና በሌላ ሰው ንብረትና ክብር ወሰን መተላለፍና የመሳሰሉ የተጠሉ ነገሮችን መፈጸም ይጀምራል፡፡ ከዚያም ስለቤተሰቡ ያለበትን ግዴታ ይዘነጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا قُوا أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ!! ራሳችሁንና ቤተሰቦቻችሁን ከእሳት አድኑ፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ደግሞ (አንድ ሰው ወንጀል ለመፈጸም የሚያስዳድራቸውን ሰዎች ቀለብ ማጥፋቱ በቂው ነው) ይላሉ፡፡

አፍራሽ ሀሳቦችን በማስፋፋት፣ አሉባልታን በመንዛትና ሽብር በመፍጠር በምድር ላይ ማበላሸት ሌላው አላህን የሚያስቆጣ መጥፎ ተግባር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلاَ تُفْسِدُوا فِي الأَرْضِ بَعْدَ إِصْلاحِهَا}

ትርጉሙም( በምድርም ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{إِنَّمَا جَزَاءُ الَّذِينَ يُحَارِبُونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَيَسْعَوْنَ فِي الأَرْضِ فَسَاداً أَنْ يُقَتَّلُوا أَوْ يُصَلَّبُوا أَوْ تُقَطَّعَ أَيْدِيهِمْ وَأَرْجُلُهُمْ مِنْ خِلافٍ أَوْ يُنفَوْا مِنَ الأَرْضِ ذَلِكَ لَهُمْ خِزْيٌ فِي الدُّنيَا وَلَهُمْ فِي الآخِرَةِ عَذَابٌ عَظِيمٌ}

ትርጉሙም (የእነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር መባረር ነው፡፡ ይህ በነሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው፡፡ በመጨረሻይቱም ለእነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{وَلا تَبْغِ الْفَسَادَ فِي الأَرْضِ إِنَّ اللَّهَ لا يُحِبُّ الْمُفْسِدِينَ}

ትርጉሙም (በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፡፡ አላህ አጥፊዎችን አይወድምና» (አሉት)፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ (ከናንተ ደጉ ሰው የሚባለው ደግ ነገሩ የሚጠበቅና ተንኮሉ የማይፈራ ሰው ነው፡፡ ከናንተ መጥፎው ሰው የሚባለው ደግሞ ደግ ነገሩ የማይከጀልና ተንኮሉ የሚፈራ ሰው ነው)፡ ፡ በመንገድ ላይ ችግር መፍጠር ሌላው መጥፎ ተግባር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሙስሊሞችን በመንገዳቸው ላይ የሚያስቸግር ሰው የነሱ እርግማን አይስተውም)፡፡

ከሰዎች መካከል ጥላቻን መፍጠር ሌላው መጥፎ ተግባር ነው፡፡ ሰውን ማነወር፣ ሃሜት፣ በሰዎች ላይ ማሾፍ፣ ለነሱም መጥፎ ስም መስጠት፣ መሳደብ፣ አጸያፊ ቃል መሰንዘር የሚሉትና ሌሎችም የእስልምና እምነት የከለከላቸው ተግባራት በሙሉ ከቀጥተኛው የሰው ልጅ ተፈጥሮና ሥነ ምግባር ጋር ስለሚፃረሩ ከመጥፎ ተግባራት ተካተዋል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ እኔ ዘንድ እጅጉን የተጠሉት ሰዎች እነዚያ ሃሜት የሚስፋፉት ወዳጅን ከወዳጅ የሚለዩትና የንጹሃንን ስም ለማጉደፍ የሚሯሯጡት ናቸው)፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ማንኛውም የአላህ ባሪያ የሚሠራው ስራ በዚህች ዓለምና በመጭውም ዓለም ሥራው ወደባለቤቱ ይመለሳል፡፡ ከዚያም የመልካም ሥራ ፍሬ በዚህች ዓለምና በመጭውም ዓለም ያማረ ኑሮ እንደሚሆን አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አብስሯል፡
مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِنْ ذَكَرٍ أَوْ أُنْثَى وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةًوَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُمْ بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ}

ትርጉሙም (ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፡፡ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡

የመልካም ስራ ሌላው ጥቅም ደግሞ ከሞትም በኋላ ምንዳው የሚቀጥል መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሰባት ነገሮች አንድ የአላህ ባሪያ ከሞተ በኋላ ምንዳው እንድቀጥል ያደርጋሉ፡ እነሱም እውቀት ያስተላለፈ፣ ወንዘን የቀደደ፣ የውሃ ጉድጓድን የቆፈረ፡ የቴምር ዛፍን የተከለ፣ መስጊድን የገነባ፡ ቁርአንን ያወረሰ ወይም ከሞተ በኋላ ከአልህ ምህረት የሚጠይቀለት ልጅ ትቶ ያለፈ የሚሉት ናቸው)፡
፡

ሌላው የመልካም ሥራ ፍሬ ደግሞ ስለሃጢአት የሚያስተሰርይና እነሱንም ወደመልካም ሥራ እንድለውጡ የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَالَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ لَنُكَفِّرَنَّ عَنْهُمْ سَيِّئَاتِهِمْ وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَحْسَنَ الَّذِي كَانُوا يَعْمَلُونَ}

ትርጉሙም (እነዚያም ያመኑ፤ መልካሞችንም የሠሩ መጥፎዎቹን ሥራዎቻቸውን ከእነሱ ላይ እናብስላቸዋለን፡፡ በዚያም ይሠሩት በነበሩት መልካም ሥራ በእርግጥ እንመነዳቸዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡

የመልካም ሥራ ሌላው ፍሬ ደግሞ ታላቅ ምንዳ አስገኝቶ ከነብያት፣ ከፃድቃን ከሰምኣታት ጋር እንድኖር የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلًا}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እነድህ ላል፡

{وَمَنْ يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِمْ مِنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ وَحَسُنَ أُولَئِكَ رَفِيقًا} .

ትርጉሙም (አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ፡፡ የእነዚያም ጓደኝነት አማረ፡፡) ማለት ነው፡፡

መልካም ስራ ወደባለቤቱ የሚመለስ ታላቅ ጥቅም እንዳለው ሁሉ መጥፎ ሠራም በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም ወደባለቤቱ የሚመለስ ውጤት አለው፡፡

ከነሱም መካከል አንዱ ጥሜት፣ ግራ መጋባትና መንገዳገድ የሚያስከትል መሆኑ ነው፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{أَفَمَنْ زُيِّنَ لَهُ سُوءُ عَمَلِهِ فَرَآهُ حَسَنًا فَإِنَّ اللهَ يُضِلُّ مَنْ يَشَاءُ وَيَهْدِي مَنْ يَشَاءُ}

ትርጉሙም (መጥፎ ሥራው የተሸለመለትና መልካም አድርጎ ያየው ሰው (አላህ እንዳቀናው ሰው ነውን?) አላህም የሚሻውን ሰው ያጠምማል፡፡ የሚሻውንም ያቀናል፡ ፡) ማለት ነው፡፡ ሌላው የመትፎ ስራ ውጤት ደግሞ ላልተረጋጋ ሕይወት ምክኒያት መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ أَعْرَضَ عَنْ ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنْكًا}

ትርጉሙም («ከግሣጼዬም የዞረ ሰው ለእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው፡፡ ) ማት ነው፡፡

ሌላው የመጥፎ ሥራ ውጤት ደግሞ በትንሳኤ ቀን መጥፎ መመለሻን የሚስከትል መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ يَأْكُلُونَ أَمْوَالَ الْيَتَامَى ظُلْمًا إِنَّمَا يَأْكُلُونَ فِي بُطُونِهِمْ نَارًا وَسَيَصْلَوْنَ سَعِيرًا}

ትርጉሙም (እነዚያ የየቲሞችን ገንዘብ በመበደል የሚበሉ በሆዶቻቸው ውስጥ የሚበሉት እሳትን ብቻ ነው፡፡ እሳትንም በእርግጥ ይገባሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (መብቱ ያልሆነን ነገር ከምድር የወሰደ ሰው በትንሳኤ ቀን ወደሰባት ምድር ያሰምጠዋል፡፡)

እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት ጠቃሚ የሆኑ ደጋግ ነገሮቸሮችን ሁሉ አጥበቀን መያዝና ከጎጂና ተንኮል ከሚፈጠሩ መጥፎ ስራዎች ሁሉ መራቅ እጅጉን ያስፈልገናል፡ ፡ በእውነትና በመተባበር አደራ መባባልም ይገባናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَالْعَصْرِ *إِنَّ الإِنْسَانَ لَفِي خُسْرٍ *إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَتَوَاصَوْا بِالْحَقِّ وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْرِ} .

ትርጉሙም (በጊዜያቱ እምላለሁ፡፡ ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው፡ እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

ጉታችን ሆይ መልካም ሥራ መሥራትን፣ ከተጠሉ ስራዎች መራቅንና ምስኪኖችን መውደድን እንድትቸረን እንለምንሃለን፡፡ በሥራችንም ታመኘትና ተቀባይነትን እንለምንሃለን፡፡ ሀገራችንንም ከመጥፎ ነገር ተብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# አላህን ማውሳትና ለሰው ልጅ መንፈስ ቀጥተኛነት ያለው አስተዋጽኦ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكْرِ اللَّهِ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም ((እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው:: ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ::) ማለት ነው::
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ:: ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ::

**ከዚህም በመቀጠል፡**
አላህ(ዐ.ወ.) ባሮቹ እሱን ማስታወስ እንዲያበዙ አዟል:: በሱም ታላቅ ምንዳ እንደሚሰጣቸው እንድህ በማለት ቃል ገብቶላቸዋል፡

**{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اذْكُرُوا اللَّهَ ذِكْرًا كَثِيرًا *وَسَبِّحُوهُ بُكْرَةً وَأَصِيلًا}**

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት::
በቀኑ መጀመሪያና መጨረሻም አጥሩት::) ማለት ነው:: እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

**{وَالذَّاكِرِينَ اللَّهَ كَثِيرًا وَالذَّاكِرَاتِ أَعَدَّ اللَّهُ لَهُمْ مَغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا}**

ትርጉሙም (አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም፣ አላህ ለእነርሱ ምሕረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል::) ማለት ነው:: በሌሎችም አንቀጾች እንድህ ብሏል፡

**{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ *الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنْفِقُونَ *أُولَئِكَ هُمُ الْمُؤْمِنُونَ حَقًّا لَهُمْ دَرَجَاتٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ وَمَغْفِرَةٌ وَرِزْقٌ كَرِيمٌ}**

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡ እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በእውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው፡፡ ለእነሱ በጌታቸው ዘንድ ደረጃዎች ምህረትና የከበረ ሲሳይም አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ህዝቦቻቸው አላህን በብዛት እንዳዎሱ እንድህ በማለት ገፋፍተዋል፡ (ንቁ ከሥራዎቻችሁ እጅግ መልካም፣ ከንጉሳችሁ ዘንድ በጣም ጥሩ፣ ከፍተኛ ደረጃ የሚያሰገኝ እንድሁም ወርቅና ብር ምጽዋት ከመስጠት የበለጠና ከጠላታችሁ ጋር ተጋጥማችሁ አንገታቸውን የምትመቱና አንገታችሁን የሚመቱ ከመሆን የበለጠ የሆነውን ልንገራችሁ፡፡) ባልደረቦችም ይሁን ይንገሩን ያላህ መልክተኛ ሆይ! አሉ፡፡ እሳቸውም (አላህን ማውሳት ነው) አሉ፡፡ አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጥቶ ያላህ መልክተኛ ሆይ! የእስልምና ህግጋት በጣም በዙብኝ፡፡ ከነሱ አጥብቄ የምይዘውን ነገር ንገሩኝ ባለ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ምላስህ አላህን በማውሳት ከእርጥብነት አይወገድ) ነበር ያሉት፡፡

አላህን ማውሳት ታለቅ ቦታ የሚሰጠው፣ በቀላል የሚፈጸምና ትሩፋቱ ቁጥር ስፍር የሌለው ኢባዳ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) አቡ ሰዒዲኒል ኹድሪ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዊያ መስጊድ ሲገቡ ሰዎች ተሰባስበው ተቀምጠው አዩ፡፡ ምንድን ነገር ነው እዚህ እንዲትቀመጡ ያደረጋችሁ? ሲሉም ጠየቁ፡፡ አነሱም አላህን ለማውሳት ነው የተቀመጥነው በማለት መሱ፡፡ እሳቸውም በአላህ ይሁንባችሁ እሱ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጣችሁም? አሉ፡፡ አነሱም በአላህ ይሁንብን እሱ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጠንም አሉ፡፡ እኔኮ ያስማልኳችሁ እናንተን በመጠራጠር አይደለም፡፡ ከአላህ መልክተኛ ዘንድ በኔ ደረጃ ካለ ሰው ከርሳቸው የሚያወራው ሐዲስ ከኔ ያነሰ የሆነ ሰው የለም፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ቀን ባልደረቦቻቸው መስጊድ ተስብስበው አገኙ፡፡ (እዚህ ምን አስቀመጣችሁ?) ሲሉም ጠየቁ፡፡ አነሱም አላህን ለማውሳት፣ ለእስልምና ስለመራንና እሱንም ሰለለገሰን ልናመሰግነው ነው የተቀመጥነው አሉ፡፡ እሳቸውም (በአላህ ይሁንባችሁ ይሻችሁ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጣችሁም?) ሲሉ ጠየቁ፡፡ እነሱም በአላህ ይሁንብን እሱ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጠንም አሉ፡፡ እሳቸውም (እኔኮ እናንተን በመጠራጠር አደለም ያስማልኳችሁ፡፡ ነገር ግን ጅብሪል ወደኔ መጥቶ አላህ (ዐ.ወ.) በናንተ መላእክት ዘንድ እንደሚፎክርባችሁ ስለነገረኝ ነው) አሉ፡፡

አላህን የማውሳት ቃል የልቦች ሕይወትና አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ እጅጉን የተወደደ ቃል ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሙሳ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ ( ጌታውን የሚያወሳና ጌታውን የማያወሳ ሰው ምሳሌ እንደ ሕያውና ሙት ሰው ነው)፡፡ ሙስሊም ባወሩት ሌላ ቃል ደግሞ እንድህ ብለዋል፡ (አላህ የሚወሳበት ቤትና አላህ የማይወሳበት ቤት ምሳሌ እንደሕያውና

ሙት ሰው ምሳሌ ነው)፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ዘር የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹እንደቀን ታመው እያለ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሊጠይቋቸው በመጡ ጊዜ ከእናትና አባቴ የማስቀደመዎት ያአላህ መልክተኛ ሆይ! ከአላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆነው ቃል የተኛው ነው በማለት በጠየቁ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት መለሱ፡ (አላህ ለመላእክቱ የመረጠው፡

( سُبْحَانَ رَبِّي وَبِحَمْدِهِ، سُبْحَانَ رَبِّي وَبِحَمْدِهِ)

የሚለውን ቃል ነው፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰሙራህ ኢብን ጁንዱብ ደግሞ ነብያችን እንድህ ማለታቸውነ እውረተዋል፡ (አላህ ዘንድ እጅጉን የተወደዱት አራት ቃላት ናቸው፡፡

( سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلَّهِ، وَلَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ )

በማንኛቸውም ብትጀመር የሚጎዳህ ነገር የለም፡፡) ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አግላዮች ቀዳሚዎች ሆኑ) አሉ፡፡ ባልደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! አግላዮች እነማን ናቸው? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (አነዚያ አላህን ብበዛት የሚያወሱ ወንዶችና አላህ በብዛት የሚያወሱ ሲቶች ናቸው) በማለት መለሱ፡፡ በመሆኑም ነብያችን ሙዓዝ ለተባሉት ባልደረባቸው ያስተላለፉት ምክር አላህን ማውሳት ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሏቸው፡ (ሙዓዝ ሆይ! እኔ በአላህ ይሁንብኝ እወድሃለሁ) ሙዓዝም ከአባትና እናቴ የማስቀድምሁ የአላህ ምልክተኛ ሆይ! እኔም በአላህ ይሁንብኝ እወደዎታለሁ አሉ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሙዓዝ ሆይ! አደራ የምልህ ነገር ቢኖር በየስግደት መጨረሻ፡

(اللَّهُمَّ أَعِنِّي عَلَى ذِكْرِكَ وَشُكْرِكَ وَحُسْنِ عِبَادَتِكَ) .

ማለትን እንዳትተው) አሉ፡፡ ትርጉሙም ‹ጌታዬ ሆይ! አንተን በማስታወስ በማመስገንና ኢባዳህን በማሳመር ረደኤትህ ከኔ ጋር ይሁን፡፡ ማለት ነው፡፡
አላህ (ዐ.ወ.)ን ማውሳት አንድን ባሪያ በማንኛውም ቦታና ጊዜ የማይለይ ኢባዳ ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ እንዲፈጽመው የታዘዘ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አስታውሷል፡

{إِنَّ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ وَاخْتِلَافِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ لَآيَاتٍ لِّأُولِي الأَلْبَابِ الَّذِينَ يَذْكُرُونَ اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَى جُنُوبِهِمْ}

ትርጉሙም(ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ፡፡ እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ... ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

የማንኛውም ሙስሊም ሕይወት ሁሉም አላህን በማስታወስ የተሞላ ነው፡፡ አላህን ማስታወስ በኢባዳው ሁሉ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ለምሳሌ ስግደት አላህን ማስታወስ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَقِمِ الصَّلَاةَ لِذِكْرِي}

ትርጉሙም (ሶላትንም (በእርሷ) እኔን ለማውሳት ስገድ፡፡) እንድሁም አንድህ ይላል፡

{وَأَقِمِ الصَّلَاةَ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنْكَرِ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ}

ትርጉሙም (ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ማለትም ስግደት ሁለት ተላላቅ አላማዎች አሏት ማለት ሲሆን የመጀመሪያው ከሚጠላ ነገር የምትከለክል መሆና ሁለተኛው ደግሞ እሷ አላህን ማስታወስ መሆኗ ነው፡፡ እሱም ታላቁና ከፍተኛው የስግደት አላማ ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ማንኛውም ሙስሊም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የሆኑን በርካታ የአላህ ማውሻ ቃላትን ደንግገውልናል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሌሊት በሚነጋ ጊዜ እንድህ ይሉ ነበር፡

(اللَّهُمَّ بِكَ أَصْبَحْنَا ، وَبِكَ أَمْسَيْنَا ، وَبِكَ نَحْيَا ، وَبِكَ نَمُوتُ ، وَإِلَيْكَ النُّشُورُ)

ቀኑ ሲመሽ ደግሞ

(اللَّهُمَّ بِكَ أَمْسَيْنَا ، وَبِكَ أَصْبَحْنَا ، وَبِكَ نَحْيَا ، وَبِكَ نموت ، وإليك المصير)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ሌሊቱ በሚነጋ ጊዜ

(اللَّهُمَّ مَا أَصْبَحَ بِي مِنْ نِعْمَةٍ أَوْ بِأَحَدٍ مِنْ خَلْقِكَ فَمِنْكَ وَحْدَكَ لَا شَرِيكَ لَكَ ، لَكَ الْحَمْدُ ، وَلَكَ الشُّكْرُ)

የሚል ሰው የዚያን ቀን ምስጋና ያደረሰ ሆናል፡፡ ቀኑም ሲመሽ ይህን ያለ የዚይን ሌሊት ምስጋና ያደረሰ ሆናል) ብለዋል፡፡ አንድ ሰው ቀኑን አላህን በማውሳት እንድሁም ሌሊቱን አላህን በማውሳት መጀመሩ እጅጉን መልካም ተግባር ሲሆን በመካከል ያለውንም ጊዜ አላህን በማውሳት እንዳሳለፈ ይቆጠራል፡፡

እንድሁም አንድ ሰው ከቤት ሲወጣና ሲገባ የሚያደርሳቸው አላህን ማውሻ ቃላት አሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ማላታቸው ተወርቷል፡፡ አንድ ሰው ከቤቱ ሲወጣ፡

(بِسْمِ اللَّهِ توكَّلْتُ عَلَى اللَّهِ ، وَلَا حوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلاَّ بِاللَّهِ)

ያለ ሰው ቅኑን መንገድ ተመራህ፣ ከተንኮልም ተበቃህ፣ ከደባም ተጠበቅህ፣ ይባላል፡፡ ሰይጣንም ከሱ ያገላል፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኡሙ ሰለማህ

እንድህ ብለዋል፡ ነብያችን ከኔ ቤት አይናቸውን ወደሰማይ ከፍ አድርገው እንድህ ሳይሉ ውጥተው አያውቁም፡
**اللّهُم اني أعوذُ بِكَ أن أَضِلَّ أو أُضَلَّ، أو أَزِلَّ أو أُزَلَّ، أو أَظْلِمَ أو أُظلَم، أو أجهَل أو يُجْهَل عَلَيَّ)**

እቤት ስንገባ የምንለው የአላህ ማውሳትን አስመልክቶ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ አንድ ሰው ከቤቱ ሲገባ እንድህ ይበል፡
اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ خَيْرَ الْمَوْلَجِ ، وَخَيْرَ الْمَخْرَجِ ، بِسْمِ اللَّهِ وَلَجْنَا ، وَبِسْمِ اللَّهِ خَرَجْنَا ، وَعَلَى اللَّهِ رَبِّنَا تَوَكَّلْنَا)

ከዚያም ለቤተሰቡ ሰላምታ ይበል፡፡) እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አንዳችሁ በየቀኑ አንድ ሺህ መልካም ሥራ መስራት ያቅጠዋልን? )አሉ፡፡ አብረው ተቀምጠው ከነበሩት ሰዎች አንደኛው አንዳችን አንድ ሺህ መልካም ሥራ እንዴት ሊሠራ ይችላል? ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (መቶ ጊዜ አላህን በማጥራት አንድ ሺህ መልካም ሥራ ይመዘገብለታል እንድሁም አንድ ሺህ ኃጢአት ይነሳለታል) አሉ፡፡ እንድሁም በምንበላና በምንጠጣ ጊዜ በመጀመሪያ በአላህ ስም ማለትና በመጨረሻም ለአላህ ምስጋና ማቅረብና የመሳሰሉ አላህን የምናወሳባቸው ቃላት አሉ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አቢ ሰለማህ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንድ ቀን ህፃን ሆኘ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እያሳደጉኝ ሳለ ምግብ ስንበላ እጄ ትሪውን በሙሉ ትቃኝ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የአላህ መልክተኛ እንድህ አሉኝ (አንተ ልጅ ሆይ! በአላህ ስም ብለህ ጀምር፣ በቀኝ እጅህ ተመገብ፣ ባንተ በኩል ካለውም ተመገብ)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ተመግበው ሲጨርሱ እንድህ ይሉ ነበር፡
الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَطْعَمَنَا ، وَسَقَانَا ، وَجَعَلَنَا مُسْلِمِينَ) .
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደገበያም ስንገባ አላህን የምናወሳባቸው ቃለት እንድህ በማት ደንግገውልናል፡ አንድ ሰው ወደገበያ ሲገባ
لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ ، يُحْيِي وَيُمِيتُ ، وَهُوَ حَيٌّ لَا يَمُوتُ ، بِيَدِهِ الْخَيْرُ كُلُّهُ ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ)

ያለ ሰው አላህ አልፍ አላፍ መልካም ሥራ ይመዘግብለታል፣ እንድሁም አልፍ አላፍ ወንጀልን ያብስለታል በጀነትትም ቤት ይሠራለታል) እንድሁም አንድ ሰው የሚያስደስት ነገር በሚያይበት ወቅት ‹አላህ ያለው ሆነ፡፡ በአላህ እገዛ ቢሆንጂ ኃይል የለም ልንል ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድ
{ولولا إذ دخلت جنتك قلت ما شاء الله لا قوة إلا بالله}

ትርጉሙም («አትክልትህንም በገባህ ጊዜ አላህ የሻው ይኾናል፤ በአላህ ቢኾን እንጂ ኀይል የለም፤ አትልም ኖሯልን...) ማለት ነው፡፡

አንድሁም አንድ ሰው መከራ የደረሰባቸውን ሰዎች በሚያይ ጊዜ በምስጢር አላህን ሊያወሳና ከዚያ መሰል መከራም ስለሰወረው እሱን ሊያመሰግን ይገባል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የአንድ መከረኛ ስቃይ አስደንግጦት ‹ለአንተ ከሰጠው መከራ ለአዳነኝና ከብዙኃን ፍጥረታቱ ማብለጥን ለአበለጠኝ ለአላህ ምስጋና ይገባው፡ ፡ ያለሰው ምንም ይሁን ምን ከዚያ ዓይነት መከራ ይጠበቃል፡፡) እንድሁም አንድ ምእምን በራሱ ላይ ጭንቀት ሲደርስበት ጌታውን በማውሳት ወደሱ ይጠጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንድህ ብሏል፣

{وَذَا النُّونِ إِذ ذَّهَبَ مُغَاضِبًا فَظَنَّ أَن لَّن نَّقْدِرَ عَلَيْهِ فَنَادَى فِي الظُّلُمَاتِ أَن لَّا إِلَهَ إِلَّا أَنتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ الظَّالِمِينَ * فَاسْتَجَبْنَا لَهُ وَنَجَّيْنَاهُ مِنَ الْغَمِّ وَكَذَلِكَ نُنجِي الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም (የዓሳውንም ባለቤት ተቆጥቶ በኼደ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መኾናችንን ጠረጠረ፡፡ (ዓሳም ዋጠው)፡፡ በጨለማዎችም ውስጥ ኾኖ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ጥራት ይገባህ፡፡ እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ በማለት ተጣራ፡፡ ለርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ ከጭንቅም አዳነው፡፡ እንደዚሁም ምእመናንን እናድናለን፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጭንቅ ሲያጋጥማቸው እነድህ ይሉ ነበር፡

(لاَ إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ العَظِيمُ الحَلِيمُ ، لاَ إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ رَبُّ السَّمَوَاتِ وَالأَرْض ، وَرَبُّ العَرْش العَظِيم) .

ከፍ ሲል ያየናቸው ነብያችን አላህን ማውሻ እንድናደርጋቸው የደነግጉልን ቃላቶች ናቸው፡፡ እነሱንም ዘወትር የአላህ ማውሻ ያደረገ ሰው ቅኑን መንገድ ይመራል፣ ከዝንጋታም ይድናል፡፡ ከሰይጣንም ይጠብቁታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{اللَّهُ نَزَّلَ أَحْسَنَ الْحَدِيثِ كِتَابًا مُّتَشَابِهًا مَّثَانِيَ تَقْشَعِرُّ مِنْهُ جُلُودُ الَّذِينَ يَخْشَوْنَ رَبَّهُمْ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمْ وَقُلُوبُهُمْ إِلَى ذِكْرِ اللَّهِ ذَلِكَ هُدَى اللَّهِ يَهْدِي بِهِ مَنْ يَشَاءُ وَمَنْ يُضْلِلِ اللَّهُ فَمَا لَهُ مِنْ هَادٍ}**

ትርጉሙም (አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን፣ ተመሳሳይ፣ ተደጋጋሚ የኾነን መጽሐፍ አወረደ፡፡ ከእርሱ (ግሣጼ) የእነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ፡፡ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ማስታወስ ይለዝባሉ፡፡ ይህ የአላህ መምሪያ ነው፡፡ በእርሱ የሚሻውን ሰው ይመራበታል፡፡ አላህም የሚያጠመው ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም፡፡) ማት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ብሏል፡

{ وَاذْكُرْ رَبَّكَ فِي نَفْسِكَ تَضَرُّعًا وَخِيفَةً وَدُونَ الْجَهْرِ مِنَ الْقَوْلِ بِالْغُدُوِّ وَالْآصَالِ وَلَا تَكُنْ مِنَ الْغَافِلِينَ}

ትርጉሙም (ጌታህንም በምስጢር ተዋድቀህና ፈርተህ ከጩኸት በታችም በኾነ ቃል በጧትም በማታም አውሳው። ከዘንጊዎቹም አትኹን።) ማለት ነው። አሁንም እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ يَعْشُ عَنْ ذِكْرِ الرَّحْمَنِ نُقَيِّضْ لَهُ شَيْطَانًا فَهُوَ لَهُ قَرِينٌ}.

ትርጉሙም (ከአልረሕማን ግሣጼ (ከቁርኣን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን። ስለዚህ እርሱ ለእርሱ ቁራኛ ነው።) ማለት ነው።

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ።

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው። የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ።

**ሙስሊም ወንድሞች**

አላህን ማውሳት የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች በተግባር ያሳዩት የነበረ የሕይወት ስርኣት ነበር። በዚያን ወቅት ማህበረሰቡ አላህን በመቆጣጠርና ወሰን ከማለፍ በመራቅ የታነጸ ነበር። እዚህ ላይ የኸሊፋው አቡበክርና የዑመረን ታሪክ ብንጠቅስ ጠቃሚ ይሆናል።

በኸሊፋው አቡበክር ዘመን ዑመር ኢብንል ኸጣብ የበላይ ዳኛ ሆነው ተሾሙ። አንድም ቀን ከሳሽ ወደቦታቸው ሳይመጣ ሙሉ አመት አለፈ። በዚይን ጊዜ የኃላፊነት መልቀቂያቸውን ለአቡ በክር አሲዲቅ አቀረቡ። እሳቸውም ዑመር ሆይ! የዳኝነት ሥራ ስላደከመህ ነው ኃላፊነት መልቀቅ የፈልግህው? ሲሉ ጠየቋቸው። ዐመርም አይደለም የአላህ መልክተኛ ኸሊፋ ሆይ! ነገር ግን እያንዳንዱ መብቱን አውቆ ከሱ ያለፈን ነገር የማይጠይቅ፣ በሱ ላይ ያለበትንም ግዴታ አውቆ እሱን ከመወጣት ወደኋላ በማይል ምእምን ማህበረሰብ ውስጥ እኔ ስለማላስፈልግ ነው። እነሱ ሁሉም ለራሱ የሚወደውን ነገር ለወንደድሙ የሚወድ፣ አንዳቸው በሚሰወር ጊዜ የሚናፍቁት፣ በተማመም ጊዜ የሚጠይቁት፣ በሚደህይ ጊዜ የሚያግዙት፣ እርዳታ በሚያስፈልገውም ጊዜ የሚረዱት፣ መከራ ሲየሰጋጥመውም የሚያጽናኑት፣ ሃይማኖታቸው ምክርን መለገስ፣ ጠባያቸው በመልካም ነገር ማዘዝና ከመጥፎ ነገር መከልከል የሆነ ማህበረሰብ አባል ስለሆኑ በምን ይካሰሳሉ? በምን ነገር ይካሰሳሉ?› አሉ።

አንድ ሙስሊም ባሪያ በልቡ አላህን ማስታውስ በሚሰፍንበት፣ በምላሱ በሚደጋግመውና አካላቱም ተግባራቸው ባደረጉት ጊዜ መንፈሱ ቀጥተኛ ትሆናለች የአላህንም ውዴታ ያገኛል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ጸጋውን ይባርክለታል፡፡ ሐዘኑም ይወገዳል ርጋታና የአላህ እዝነትም ያጥለቀልቀዋል፡፡
ጌታችን ሆይ! አንተን በማስታወስና በማመሰገንም እገዘን ሀገራችንንም ጠብቅልን ጸጥተዋን ሰላሟን አስከብርልን ሲሳያዋንም የተትረፈረፈ አድርግልን፡፡ አሜን፡፡

# (6)

## ቅዱስ ቁርአን ለሥነ ምግባራዊ እሴቶች የሰጠው ልዩ ትኩረት

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{إِنَّ هَذَا الْقُرْآنَ يَهْدِي لِلَّتِي هِيَ أَقْوَمُ وَيُبَشِّرُ الْمُؤْمِنِينَ الَّذِينَ يَعْمَلُونَ الصَّالِحَاتِ أَنَّ لَهُمْ أَجْرًا كَبِيرًا}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ይህ ቁርአን ወደዚያች እርሷ ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል፡፡ እነዚያንም በጎ የሚሠሩትን ምእመናን ለእነሱ ታላቅ ምንዳ ያላቸው መኾኑን ያበስራል፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
በቅዱስ ቁርአን በኩል ያሉት የክብር ዓይነቶች ቁጥር ስፍር የላቸውም፡፡ የተከበረው ቁርአን ጠንካራ የአላህ ገመድ፣ ጠበብ የተሞላበት እውቀት፣ ግልጽ ብርሃንና ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡ እሱም ያ ማጣመም የማያገኘው፣ ከፊቱም ሆነ ከኋላው ውሸት የማይመጣበት፣ ሙሁራን ከሱ የማይጠግቡ፣ በመልስ ብዛት የማይደበዝዝ፣ አስደናቂ ነገሮቹ የማያልቁ፣ በሱ የተናገረ እውነተኛ፣ በሱም የሰራ ምንዳው የላቀ፣ በሱ የፈረደ ፍትሃዊና ወዱሱም የጠራ ትክክለኛውን መንገድ የሚመራ የሆነ ክቡር መጽሐፍ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِكُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَى لِلْمُسْلِمِينَ}

ትርጉሙም (መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{مَا فَرَّطْنَا فِي الْكِتَابِ مِنْ شَيْءٍ}

ትርጉሙም (በመጽሐፉ ውስጥ ምንንም ነገር አልተውንም) ማለት ነው፡፡

ከቅዱስ ቁርኣን እሴቶች አንዱና በመጀመሪያ የሚጠቀሰው በግለሰብና በህዝቦች ሕይወት ለአለው የሥነ ምግባራዊ ግንባታ የሚሰጠው ልዩ ትኩረት ነው፡፡ ለዚህም ጉዳይ በመልካም መንፈስና በንጹህ ልቦና የታነጸ እንድሁም በማህሉም እውነተኛነት፣ እምነት፣ ርህራሄና እዝነት የሰፈነበት አንድነቱም የጠነከረ ማህበረሰብ ለማዋቀር የሰውን ልጅ የእለት ከእለት ስርኣት ቅን የሚያደርጉ በርካታ እሴቶችን ደንቦችንና ህግጋትን አስቀምጧል፡፡ በዚህ መልኩም የተዋቀረው ማህበረሰብ ከሰዎች መካከል ባለው ተፈጥሯዊ ልዩነት የሚያምን ሲሆን ተቻችሎ ለመኖርና ሌላውንም ለመቀበል መርህ ይገዛል፡፡ በሃይማኖትም መሰረት ይህችን ዓለም ለማልማት ይጥራል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُمْ مِنْ ذَكَرٍ وَأُنْثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِنْدَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡) በማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَجَعَلَ النَّاسَ أُمَّةً وَاحِدَةً وَلَا يَزَالُونَ مُخْتَلِفِينَ * إِلَّا مَنْ رَحِمَ رَبُّكَ...}

ትርጉሙም (ጌታህም በሻ ኖሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ሕዝብ ባደረጋቸው ነበር፡፡ የተለያዩም ከመሆን አይወገዱም፡፡ ጌታህ ያዘነለት ብቻ ሲቀር፤ (ከመለያየት አይወገዱም)፡፡ ...) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡

{هُوَ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الْأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا} .

ትርጉሙም (እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡ ) ማለት ነው፡፡

የቅዱስ ቁርኣንን አንቀጾች ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው ቁርኣን እንድንመራባቸው ያዘዘን ሥነ ምግባራዊ እሴቶች ባንድ ወቅት ልንተወው ወይም በአንድሁኔታ ልንተገብረውና በሌላ ሁኔታ ልናልፈው የምንችል የቅንጦት ተግባራት አለመሆናቸውን በእርግጠኝነት ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ይልቁንም እነዚህ እሴቶች ዘመን በለወጥም ሆነ

ቦታ በመቀየር የማይለወጡ ቋሚ እሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በተግባር የፈጸሟቸውና ሰዎችም እንድመሩባቸው ያዙባቸው የነበሩ ናቸው፡፡ እናታችን ዓኢሻ ስለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጠባይ በተጠየቁ ጊዜ የተላያዩ ተግባራትን አልቆጣጠሩም፡፡ ግን አጭር መልሳቸው ጠባያቸው ቁርኣን ነበር የሚል ነበር፡፡ ሰዕድ ኢብን ሂሻም አንድ ቀን ፣

{وَإِنَّكَ لَعَلَى خُلُقٍ عَظِيمٍ}

(አንተ በመልካም ጸባይ ላይ ነህ) ስለምትለው አንቀጽ ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም እኔ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዓኢሻን እነድህ ስል ጠየቅሁኝ፡ የምእምናን እናት ሆይ! እስኪ ስለአላህ መልክተኛ ጠባይ ንገሩኝ? እሳቸውም ‹ቁርኣን ታነባለህ አይደል? አሉኝ፡፡ እኔም አዎን አልኩኝ፡፡ ‹የአላህ መልክተኛ ጠባይ ቁርኣን ነበር› አሉኝ፡፡ የእናታችን ዓኢሻ አባባል በቁርኣን የተካተቱት የእምነት መመሪያዎች፣ ህግጋት፣ የአምልኮት ደንቦችና የግንኙነት ስርኣቶች የሰውን ልጅ በተሟላ ሥነ መግባር ለመገንባት መሰረተ መዋቅር መሆናቸውን በቀጥታ ይጠቁማል ይላሉ፡ ሊቃውንት፡፡ የናታችን ዓኢሻ አባበል አሁንም ነብያችን በተለያዩ የሕይወት ጊዜያቸው ለዚህ ዓይነቱ መዋቅር አርኣያ እንደነበሩ በግልጽ ያሳያል፡፡

ከተመለከቱት እሴቶች ዋና ዋና ከሚባሉት አንዱ ደግሞ የሰውን ልጅ ሰብእነት ማክበርና ክብሩን መጠበቅ እንድሁም እሱን አለማጣጣል የሚለው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በተከበረው መጽሐፉ ማንኛም ሰው እንደማሾፍና ማፌዝ ባሉ ተግባራት የሌሎችን ስሜት ከሚጎዳ ነገር መራቅ ያለበት መሆኑን እንድህ ሲል ገልጹአል፡

يَا {أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَى أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَى أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا بِالْأَلْقَابِ بِئْسَ الِاسْمُ الْفُسُوقُ بَعْدَ الْإِيمَانِ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُولَئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፡፡ ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ፡፡ ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

يَا {أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اجْتَنِبُوا كَثِيرًا مِّنَ الظَّنِّ إِنَّ بَعْضَ الظَّنِّ إِثْمٌ وَلَا تَجَسَّسُوا وَلَا يَغْتَب بَّعْضُكُم بَعْضًا أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ أَن يَأْكُلَ لَحْمَ أَخِيهِ مَيْتًا فَكَرِهْتُمُوهُ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ تَوَّابٌ رَّحِيمٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፤ ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና፡፡ ነውርንም አትከታተሉ፡፡ ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፡፡ አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፤

(ሐሜቱንም ጥሉት)፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ቁርኣን ልባችንን እንድናጠራ፣ ከርኩስ አስተሳሰብ፣ ከቂምና ከመጥፎ ጥርጣሬ እንድታቀብ እንድህ በማለት ያዘናል፡

{لَّوْلَا إِذْ سَمِعْتُمُوهُ ظَنَّ الْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بِأَنفُسِهِمْ خَيْرًا وَقَالُوا هَذَا إِفْكٌ مُّبِينٌ}.

ትርጉሙም ((ውሸቱን) በሰማችሁት ጊዜ ምእምናንና ምእምናት በጎሶቻቸው ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም፡፡) ማት ነው፡፡

ቅዱስ ቁርኣን ልዩ ትኩረት የሰጠው ሌላው እሴት ደግሞ በመልካም ነገርና አላህ በመፍራት ዘርፎች ያለው የትብብር የመተጋገዝና የመተዛዘን እሴት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አንድህ ላል፡

{وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ}

ትርጉሙም (በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ከማህበረሰቡ አባላት መካከል የሚደረገው ትብብር ጠንካራ ሀገር ለመገንባትና ለማህበረሰቡ ደህንነት ዋና መሰረት ነው፡፡ ለያንዳንዱ ሰው ሊያሳካው የሚፈለገው አላማ አለው፡፡ እያንድንዱም ሰው የመደጋገፍን መርህ እውን ለማድረግ ቀድሞ ከጣረ አላማው በቀላሉ ይሳካል፡፡ እንድህ የሚለው ግጥም ደራሲ እጅጉን ይደነቃል፡

ዐረብም ሁን ከዐረብ ውጭ ለሰው ልጅ ደራሹ ሰው ነው፡፡ ምንም እንኳን ባይሰማቸውም ከፊላቸው ለከፊሉ አገልጋይ ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የትብብርን እሴት ታላቅነት እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና በመተጋገዛቸው የምእምናን ምሳሌ አንዳካል እንቅልፍ በማጣትና በህመም ሲሰቃይ ሌሎችም የዚያ አካል ክፍሎች እንዲመሰማቸው ዓይነት ነው)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስስ እንድህ ብለዋል፡ (ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ ነው፡፡ አይበድለውም ለጠላትም አሳልፎ አይሰጠውም የአንድን ሰው ጉዳይ ለማውጣት የሚጥር ሰው አላህ ጉዳዩን ያወጣለታል፡፡ ከአንድ ሙስሊም ጭንቀት ያቃለለ ሰው አላህ ከትንሳኤ ቀን ጭንቀቶች አንዱን ያቃልለታል፡፡ የአንድን ሙስሊም ነውር የሸፈነ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን ከውርደት ይሰውረዋል)፡፡

በቅዱስ ቁርኣን ከተካተቱ እሴቶች ሌላው ደግሞ የማስብና አእምሮን የማሰራት እሴት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ባሮቹ በመስማትና በምድርም ባሉ ፍጥረታት እንድመራምሩ አዟል፡፡ እንድሁም ተመራማሪዎችን እንድህ በማለት አሞግሷል፡

{إِنَّ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَاخْتِلَافِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ لَآيَاتٍ لِّأُولِي الْأَلْبَابِ * الَّذِينَ يَذْكُرُونَ اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَى جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَذَا بَاطِلًا سُبْحَانَكَ فَقِنَا عَذَابَ النَّارِ}

ትርጉሙም (ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ፡፡ (እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡- «ጌታችን ሆይ! ይኸን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ፤ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን» የሚሉ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

{أَوَلَمْ يَنْظُرُواْ فِي مَلَكُوتِ السَّمَاوَاتِ والأَرْض}

ትርጉሙም (በሰማያትና በምድር ግዛት ውስጥ... አያስተውሉምን፡፡) ማለት ነው፡፡ ለኛ የመራመርን በር ከፍት ያደረገልን መሆኑንም እንድህ ሲል ገለጧል

{اللَّهُ الَّذِي رَفَعَ السَّمَوَاتِ بِغَيْر عَمَدٍ تَرَوْنَهَا}

ትርጉሙም (አላህ ያ ሰማያትን የምታዩዋት አዕማድ ሳትኖር ያነሳት ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{قُلْ أَرَأَيْتُمْ إِنْ جَعَلَ اللَّهُ عَلَيْكُمُ النَّهَارَ سَرْمَدًا إِلَى يَوْمِ الْقِيَامَةِ مَنْ إِلَهٌ غَيْرُ اللَّهِ يَأْتِيكُمْ بِلَيْلٍ تَسْكُنُونَ فِيهِ أَفَلَا تُبْصِرُونَ}

ትርጉሙም (አያችሁን «አላህ በእናንተ ላይ ቀንን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ዘውታሪ ቢያደርገው ከአላህ ሌላ በውስጡ የምታርፉበትን ሌሊት የሚያመጣላችሁ አምላክ ማን ነው (ንገሩኝ) አታስተውሉምን» በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

{أَوَلَمْ يَتَفَكَّرُواْ في أَنفُسِهِمْ}

ትርጉሙም (በነፍሶቻቸው (ሁኔታ) አያስተውሉምን?) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንዲህ ይላል፡

{وَفِي الْأَرْض آيَاتٌ لِلْمُوقِنِينَ وَفِي أَنْفُسِكُمْ أَفَلَا تُبْصِرُونَ}

ትርጉሙም (በምድርም ውስጥ ለሚያረጋግጡ ሰዎች ምልክቶች አልሉ፡፡ በነፍሶቻችሁም ውስጥ (ምልክቶች አልሉ)፤ ታዲያ አትመለከቱምን?)ማለት ነው፡፡

ይህ ምርምር ለአላህ የሚደረግ አምልኮ መሆኑን የነብያችን ባልደረቦች ፈጥነው ተገንዝበውታል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ አደርዳእ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹አንድ ሣዓት ስለአላህ ፍትረታት መመራመር ሌሊቱን ቁሞ ከመስገድ ይበልጣል›፡፡ (አላህ መህረት ያደርግላቸውና) ወህብ ኢብን ሙነቢህ የተባሉት ሊቅም እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹የአንድ ሰው ምርምር አይረዝምም በመጨረሻ የሚገነዘብ ቢሆን እንጂ፡፡ አይገነዘብም እውቀት የሚቀስም ቢሆን አንጂ፡፡ እውቀት አይቀስምም የሚሰራበት ቢሆን እንጂ›፡፡

የውይይትና የሌላውን ማክበር እሴትም በቅዱስ ቁርኣን ተካቷል፡፡ በርከታ የቁርኣን አንጾች በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ውይይት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ውይይት መልእክቱን ሲያስተላለፉ እንድተቀሙበት አላህ ለነብያቱና መልክተኞቹ የመረጠላቸው ስልት ነው፡፡ የአስልምና እምነት የሃይማኖት ነጻነት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ قَدْ تَبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ}**

ትርጉሙም (በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡) ማለት ነው፡፡

እነሆ ነብዩ ኑሕ ለረዥም ጊዜ በዘለቀው የሃይማኖት ጥሪያቸው እንድህ ማለታቸውን ቅዱስ ቁርአን አውስቷል፡

**{يَا قَوْمِ أَرَأَيْتُمْ إِنْ كُنْتُ عَلَى بَيِّنَةٍ مِنْ رَبِّي وَآتَانِي رَحْمَةً مِنْ عِنْدِهِ فَعُمِّيَتْ عَلَيْكُمْ أَنُلْزِمُكُمُوهَا وَأَنْتُمْ لَهَا كَارِهُونَ} .**

ትርጉሙም («ሕዝቦቼ ሆይ! ንገሩኝ ከጌታዬ በግልጽ ማስረጃ ላይ ብሆን ከእርሱም ዘንድ የሆነን ችሮታ (ነብይነት) ቢሰጠኝና በእናንተ ላይ ብትደበቅባችሁ እናንተ ለርሷ ጠይዎች ስትሆኑ እርሷን (በመቀበል) እናስገድዳችኋለን» አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብዩ ኢብራሂምም ለአመጸኛው ንጉስ መረጃ ሲያቀርቡ እንድህ ብለዋል፡

**{أَلَمْ تَرَ إِلَى الَّذِي حَاجَّ إِبْرَاهِيمَ فِي رَبِّهِ أَنْ آتَاهُ اللَّهُ الْمُلْكَ إِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّيَ الَّذِي يُحْيِي وَيُمِيتُ قَالَ أَنَا أُحْيِي وَأُمِيتُ قَالَ إِبْرَاهِيمُ فَإِنَّ اللَّهَ يَأْتِي بِالشَّمْسِ مِنَ الْمَشْرِقِ فَأْتِ بِهَا مِنَ الْمَغْرِبِ فَبُهِتَ الَّذِي كَفَرَ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ}**

ትርጉሙም (ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው ሰው አላየህምን ኢብራሂም «ጌታዬ ያ ሕያው የሚያደርግና የሚገድል ነው» ባለ ጊዜ «እኔ ሕያው አደርጋለሁ እገድላለሁም» አለ፡፡ ኢብራሂም፡- «አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል (አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት» አለው፡፡ ያም የካደው ሰው ዋለለ፤ (መልስ አጣ) አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም፡፡) ማለት ነው፡፡

በዚሁ ዓይነት ስርኣት ነበር ነብዩ ሙሳ ከፎርኦን ጋር ወይይት ያደረጉት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

**{قَالَ فِرْعَوْنُ وَمَا رَبُّ الْعَالَمِينَ * قَالَ رَبُّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا إِنْ كُنْتُمْ مُوقِنِينَ * قَالَ لِمَنْ حَوْلَهُ أَلَا تَسْتَمِعُونَ * قَالَ رَبُّكُمْ وَرَبُّ آبَائِكُمُ الْأَوَّلِينَ * قَالَ إِنَّ رَسُولَكُمُ الَّذِي أُرْسِلَ إِلَيْكُمْ لَمَجْنُونٌ * قَالَ رَبُّ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَمَا بَيْنَهُمَا إِنْ كُنْتُمْ تَعْقِلُونَ * قَالَ لَئِنِ اتَّخَذْتَ إِلَهًا غَيْرِي لَأَجْعَلَنَّكَ مِنَ الْمَسْجُونِينَ} .**

ትርጉሙም (ፈርዖን አለ «(ላከኝ የምትለው) የዓለማትም ጌታ ምንድነው» (ሙሳ) «የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታ ነው። የምታረጋግጡ ብትኾኑ (ነገሩ ይህ ነው)፤» አለው።
(ፈርዖንም) በዙሪያው ላሉት ሰዎች «አትሰሙምን» አለ፡ (ሙሳ) «ጌታችሁና የመጀመሪያዎቹ አባቶቻችሁም ጌታ ነው» አለው። (ፈርዖን) ያ ወደናንተ የተላከው መልክተኛችሁ በእርግጥ እብድ ነው አለ። (ሙሳ) «የምሥራቅና የምዕራብ በመካከላቸውም ያለው ነገር ሁሉ ጌታ ነው። ታውቁ እንደኾናችሁ (እመኑበት)» አለው። (ፈርዖን) «ከእኔ ሌላ አምላክን ብትይዝ በውነቱ ከእስረኞቹ አደርግሃለሁ» አለ።) ማለት ነው።

ቅዱስ ቁርኣን የውይይትን እሴት ለማጠናከር የጠቀሳቸው አንቀጾች ቀለምን፣ ሃይማኖትንና ዜግነትን መሰረት ሳያደርግ የሰው ልጅ ስልጣኔን እድገት ያንጸባረቃሉ። ቅዱስ ቁርኣን የሰው ልጅ ክብር በሰብእነቱ ብቻ መሆኑን አረጋግጦ የሁሉም ሰው መሰረት አንድ መሆኑን አመልክቷል። አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي آدَمَ وَحَمَلْنَاهُمْ فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَرَزَقْنَاهُمْ مِنَ الطَّيِّبَاتِ وَفَضَّلْنَاهُمْ عَلَى كَثِيرٍ مِمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلًا}**

ትርጉሙም (የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው። በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው። ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው። ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው።) ማለት ነው። እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُمْ مِنْ نَفْسٍ وَاحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَاءً وَاتَّقُوا اللَّهَ الَّذِي تَسَاءَلُونَ بِهِ وَالْأَرْحَامَ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا}**

ትርጉሙም (እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ። ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ። አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና።) ማለት ነው።

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን አለምናለሁ።

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ቅዱስ ቁርአን ካካተታቸው እሴቶች ሌላው ደግሞ በቁጣ ራሱን መቆጣጠርና ቁጭትንም መግታት የሚለው ነው፡፡ አንድ ሰው በዚህች ዓለም ሲኖር በአንድ ወቅት ቁጣውን የሚያስነሳ ነገር የሚያጋጥመው መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ በዚህን ወቅት ታድያ ራሱን እንድቆጣጠር ታዟል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ وَسَارِعُوا إِلَى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّمَاوَاتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ الَّذِينَ يُنْفِقُونَ فِي السَّرَّاءِ وَالضَّرَّاءِ وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ}**

ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡ ለእነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም ገቺዎች ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)፡፡ አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

**وَلَا يَأْتَلِ أُولُو الْفَضْلِ مِنْكُمْ وَالسَّعَةِ أَنْ يُؤْتُوا أُولِي الْقُرْبَى وَالْمَسَاكِينَ وَالْمُهَاجِرِينَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَلْيَعْفُوا وَلْيَصْفَحُوا أَلَا تُحِبُّونَ أَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ}**

ትርጉሙም (ከእናንተም የችሮታና የክብረት ባለቤቶች የኾኑት ለቅርብ ዘመዶችና ለድኾች በአላህም መንገድ ለተሰደዱ ሰዎች ላይሰጡ አይማሉ፡፡ ይቅርታም ያድርጉ፡፡ (ጥፋተኞቹን) ይለፉም፡፡ አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡

**{ وَلَا تَسْتَوِي الْحَسَنَةُ وَلَا السَّيِّئَةُ ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ كَأَنَّهُ وَلِيٌّ حَمِيمٌ وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا الَّذِينَ صَبَرُوا وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٍ}**

ትርጉሙም (መልካሚቱና ክፉይቱም (ጸባይ) አይተካከሉም፡፡ በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጸባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፡፡ ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡

**فَمَنْ عَفَا وَأَصْلَحَ فَأَجْرُهُ عَلَى اللَّهِ } .**

ትርጉሙም (ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

በቅዱስ ቁርኣን ከተካተቱ እሴቶች ሌላው ደግሞ ሰዎችን ማስታረቅ ነው፡፡ ሰዎችን በማስታረቅ ዙሪያ የወረዱ የቅዱስ ቁርኣን አንቀጾች በርካታዎች ናቸው፡ ይህ ተግባር ከአላህ ዘንድ መንዳ የሚያስገኝ መሆኑን አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አመልክቷል፡

**{لاَ خَيْرَ فِي كَثِيرٍ مِنْ نَجْوَاهُمْ إِلَّا مَنْ أَمَرَ بِصَدَقَةٍ أَوْ مَعْرُوفٍ أَوْ إِصْلاَحٍ بَيْنَ النَّاسِ وَمَنْ يَفْعَلْ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ مَرْضَاةِ اللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا}**

ትርጉሙም (ከውይይታቸው በምጽዋት ወይም በበጎ ሥራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በብዙው ውስጥ ደግ ነገር የለበትም፡፡ ይኸንንም (የተባለውን) የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡

**{فَمَنْ خَافَ مِنْ مُوصٍ جَنَفًا أَوْ إِثْمًا فَأَصْلَحَ بَيْنَهُمْ فَلَا إِثْمَ عَلَيْهِ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ}**

ትርጉሙም (ከተናዛዢም በኩል (ከውነት) መዘንበልን ወይም (ከሚሶ በመጨመር) ኃጢኣትን ያወቀና በመካከላቸው ያስታረቀ ሰው በእርሱ ላይ ኃጢኣት የለበትም፡፡ አላህ በጣም መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{وَيَسْأَلُونَكَ عَنِ اليَتَامَى، قُلْ إِصْلاَحٌ لَهُمْ خَيْرٌ، وَإِنْ تُخَالِطُوهُمْ فَإِخْوَانُكُمْ وَاللَّهُ يَعْلَمُ الْمُفْسِدَ مِنَ الْمُصْلِحِ ، وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَأَعْنَتَكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ}**

ትርጉሙም (ከየቲሞችም ይጠይቁሃል፡፡ «ለእነርሱ (ገንዘባቸውን በማራባት) ማሳመር በላጭ ነው፡፡ ብትቀላቀሏቸውም ወንድሞቻችሁ ናቸው፡፡ አላህም የሚያጠፋውን ከሚያበጀው (ለይቶ) ያውቃል፡፡ አላህም በሻ ኖሮ ባስቸገራችሁ ነበር፤ አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና» በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ከሰዎች መካከል ጠብ የሚፈጠርን ሰው እንድህ በማለት በጥብቅ አስጠንቅቋል፡

**{وَمِنَ النَّاسِ مَنْ يُعْجِبُكَ قَوْلُهُ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيُشْهِدُ اللهَ عَلَى مَا فِي قَلْبِهِ وَهُوَ أَلَدُّ الْخِصَامِ * وَإِذَا تَوَلَّى سَعَى فِي الْأَرْضِ لِيُفْسِدَ فِيهَا وَيُهْلِكَ الْحَرْثَ وَالنَّسْلَ وَاللهُ لَا يُحِبُّ الْفَسَادَ * وَإِذَا قِيلَ لَهُ اتَّقِ اللهَ أَخَذَتْهُ الْعِزَّةُ بِالْإِثْمِ فَحَسْبُهُ جَهَنَّمُ وَلَبِئْسَ الْمِهَادُ} .**

ትርጉሙም (ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲኾን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚደንቅህና በልቡ ውስጥ ባለው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አልለ፡ (ካንተ) በዞረም ጊዜ በምድር ላይ በውስጧ ሊያበላሽና አዝመራንና እንስሳዎችን ሊያጠፋ ይሮጣል፡፡ አላህም ማበላሸትን አይወድም፡፡ ለእርሱ «አላህን ፍራ» በተባለም ጊዜ፤ ትዕቢቱ በኃጢኣት (ሥራ) ላይ ትገፋፋዋለች፡፡ ገሀነምም በቂው ናት፤ (እርሷም) በእርግጥ የከፋች ምንጣፍ ናት፡፡) ማለት ነው፡፡

እኛ ሁላችንም ቅዱስ ቁርኣን ያካተታቸውንና ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ግቢራዊ ያደረጓቸውን ሥነ ምግባራዊ እሴቶች ገቢራዊ ማድረግ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡

ይህውም አባቶቻችን የደረሱበትን ስልጣኔ እንደገና ለማስመልስ ያስችለናል፡፡ አሕመድ ሸውቂ የተባለው ግብጻዊ የግጥ ምደራሲ እንድህ በማለታቸው ይደነቃሉ፡

የህዝቦች ህልውና ሥነ መግባራቸው ነው፡፡ ሥነ ምግባራቸው ከተወገዱ እነሱም ከምድረ ገጽ ይወገዳሉ፡፡

ጌታችን ሆይ! ወደመልካም ሥነ ምግባር ምራን ወደመልካም ሥነ መግባር ያለ አንተ የሚመራ የለምና፡፡ መጥፎ ምግባርንም ከኛ አርቅልን፡፡ መጥፎ ምግባርንም ከኛ ያለ አንተ የሚያርቅ የለምና፡፡ ሀገራችንን ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን ሰላምና ደህንነትንም በኛ ላይ አስፍን፡፡ አሜን፡፡

# (7)

## የስበአዊ እሴቶች በሑጁራት ምእራፍ

በተከበረው መጽሐፉ

قُلْ إِنَّنِي هَدَانِي رَبِّي إِلَى صِرَاطٍ مُسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም («እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲኾን የአብርሃምን መንገድ መራኝ፡፡ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም» በል፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በላቀው ሐዲሳቸው (እኔኮ የተላኩት የመልካም ምግባርን ለማሟላት ነው)፡፡ ያሉት ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ቅዱስ ቁርኣን የመልካም ምግባርና የላቁ እሴቶች መሰረት የሆኑ በርካታ አንቀጾችን አካቷል፡፡ ይልቁንም እንደ ሑጁራት ያሉ የሰለጠነ ማህበረስብ ለማዋቀር ሙሉ መርህ ያካተቱ ምእራፎችንም አካቷል፡፡ የሑጁራት ምእራፍ ስለማንኛውም ነገር ማጣራትና ማረጋገጥ እንዳለብን የሚያስተምሩና የመሳሰሉ በርካታ ጠቃሚ እሴቶችን አቅፋለች፡፡

ምእራፏ ጉዳዩ የሰዎችን ሁኔታና አቋም የሚመለከት ከሆነ በተለየ መልኩ ማጣራት ያለብን መሆኑን እንድህ በማለት ትገልጽልናለች፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}

ትርጉሙም (እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሥራችሁት ነገር ላይ ተጸጸኞች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡) ማለት ነው፡፡

የእስልምና እምነት ሁሉም ነገር በእርግጠኝነት እንድዋቀር ያዘናል፡፡ እነሆ (በርሳቸው ላይ ሰላለም ይውረድና) ሰይዲና ሱለይማን እንድርማሚት የተሰኘው ወፍ አላህን ትተው በጸሓይ ስለሚያመልኩ ሰዎች ወሬ በነገራቸውና አርግጠኛም ወሬ ነው ባላቸው ጊዜ ቃሉን እንድሁ በደፈናው አልተቀበሉትም፡፡ ነገር ግን የማረጋገጥና የማጣራት ሂደቶችን የተከተሉ መሆኑን በልሳናቸው ቁርኣን እንድህ በማለት አብራርቷል፡

{قَالَ سَنَنْظُرُ أَصَدَقْتَ أَمْ كُنْتَ مِنَ الْكَاذِبِينَ}

ትርጉሙም ((ሱለይማንም) አለ «እውነት እንደ ተናገርክ ወይም ከውሸታሞቹ እንደ ኾንክ ወደፊት እናያለን፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ ( አንድ ሰው ወንጀል ለመፈጸም የሰማውን ሁሉ ማውራቱ ይበቃዋል) ብለዋል፡፡ ይህን ሐዲስ ሲያብራሩ ኢማሙ አነወዊ እንድህ ብለዋል፡ ‹እሱ በተልምዶ እውነትንም ሀሰትንም ይሰማል፡፡ የሰማውን ሁሉ ካወራ ያልሆነ ነገር ስለአወራ ወንጅል ፈጸመ ማለት ነው፡፡› ከእለታት አንድ ቀን የሆነ ሰውዬ ወደዑመር አብድል አዚዝ ሄደና ሰለአንድ ሌላ ሰውዬ አውራላቸው፡፡ እሳቸውም እንድህ አሉት ከፈለግህ ጉዳህን እንመለከታልን፡፡ ወሸታም ከሆንህ፡

{إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا}

የምተለዋ አንቀጽ ከተቀሰቻቸው ሰዎች ትመደባለህ፡፡ ትርጉሚም (ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ አረጋግጡ፡፡) ማለት ነው፡፡ እውነተኛ ከሆንክ ደግሞ፡

{هَمَّازٍ مَشَّاءٍ بِنَمِيمٍ}

የምትለዋ አንቀጽ ከጠቀሰቻቸው ሰዎች ትመደባለህ አሉት፡፡ ትርጉሚም (ሰውን አነዋሪንና በማሳበቅ ኺያጅን፡፡) ማለት ነው፡፡

በትፈልግ ደግሞ ይቅርታ እናደርግለሃለን አሉት፡፡ እሱም የምእምናን አዛዥ ሆይ ይቅርታ አድርጉለኝ ሁለተኛ ለዚህ ዓይነት ተግባር አልንቀሳቀስም አለ፡፡ እኛ ሁላችንም ስለማንኛውም ነገር ውሳኔ ከመስጠታችን ወይም ያገኘነውን ወሬ ሁሉ ከማሰረጨታችን በፊት ለማረጋገጥ ትኩረት ስጥተን ብንንቀሳቀስ አሉባልታ ወጤቱን ያጣ ነበር፡፡ ከሰዎች መካከለም ለመስፋፋት አቅም አይኖረውም ነበር፡፡

ምእራፏ ካቀፈቻቸው መልካም እሴቶች ሌላው ደግሞ ከሀሜት መራቅ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَلَا يَغْتَب بَّعْضُكُم بَعْضًا أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ أَن يَأْكُلَ لَحْمَ أَخِيهِ مَيْتًا فَكَرِهْتُمُوهُ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ تَوَّابٌ رَّحِيمٌ}

ትርጉሙም (ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፡፡ አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፤ (ሐሜቱንም ጥሉት)፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሰቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ አንድህ ይላሉ፡ የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ አሉ፡፡ (ሀሜት ማለት ምን ማለት ነው?) ሰዎችም አላህ ያውቃል መልክተኛውም አሉ፡፡ እሳቸውም (ወንድምህን በሚጠላው ነገር ማንሳትህ ነው) አሉ፡ ፡ ከሰዎችም አንድ በወንድሜ ያ የምለው ነገር ካለበትስ? አለ፡፡ እሳቸውም (የምትለው ነገር ካለበት በእርግጥ አምተሀዋል፡፡ በሱ ያ የምትለው ነገር ከሌለ ደግሞ በእብለት ሰደበከው ማለት ነው) አሉ፡፡ ሰዎች ወገኖቻቸውን ለማማት የሚያደርሳቸው የራሳቸውን ወንጀል ዘንግተው የሌሎችን ወንጀል መከታታልን ሥራቸው አድርገው በመያዛቸው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ አንዳችሁ በወንድሙ ዓይን ላይ ያለውን ጉድፍ በግልጽ ይመለከታል፡፡ ነገር ግን በራሱ ዓይን ላይ ያለውን ቀንዘል ይዘነጋል)፡፡

ይልቁንም የሰው ልጅ ስለወንድሙ ክብር የመከላከል ግዴታ አለበት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ስለወንድሙ ክብር የተከላከለ ሰው አላህ (ዐ.ወ.) በትንሳኤ ቀን አካሉን ከእሳት ይከለክልለታል)፡፡

ምእራፏ ካቀፈቻቸው እሴቶች ለሌላው ደግሞ ሰዎችን ከማነውር መራቅ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንደድህ ይላል፡፡

{وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ}

ትርጉሙም (ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡) ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ቁርኣን በቃልም ይሁን መተግባር ሰዎችን ከማነውር እንድህ በማለት አስጠንቅቋል፡

{ وَيْلٌ لِّكُلِّ هُمَزَةٍ لُّمَزَةٍ}

ትርጉሙም (ለሃሜተኛ ለዘላፊ ሁሉ ወዮለት፡፡) ማለት ነው፡፡ እነሱም እነዚያ ሰዎችን የሚያንኳስሱ፣ የሚያነውሩና በሚጠሉትም ስም የሚጠሯቸው ናቸው፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር እነዚያ ሰዎች ከፍተኛ ጥፋት እንደሚጠብቃቸው በግልጽ ያመለክታል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ መስዑድ የተባሉት ባልደረባ እንደህ ይላሉ፡ ‹ምጽዋት እንድንሰጥ በታዝን ጊዜ እየተሰላችን ነበር የምንፈጽመው፡፡ በዚያን ወቅት አቡ ዓቂል የተባለ ሰው ግማሽ ቁና አመጣ፡፡ አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ከሱ እጅጉን የበለጠ አመጣ፡፡ መናፍቃንም አላህ የዚህን ሰው ግማሽ ቁና ምጽዋት አይፈልጋትም፡፡ ያኛውም ይህን ብዙ ገንዘብ የሰጠው ሰዎች አደረገ እንድሉት ነው በማት ሁለቱንም አነወሩ፡፡ ያንጊዜ እንድህ የምትለዋ አንቀጽ ወረደች፡፡

{الَّذِينَ يَلْمِزُونَ الْمُطَّوِّعِينَ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ فِي الصَّدَقَاتِ وَالَّذِينَ لَا يَجِدُونَ إِلَّا جُهْدَهُمْ فَيَسْخَرُونَ مِنْهُمْ سَخِرَ اللَّهُ مِنْهُمْ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ} .

ትርጉሙም (እነዚያ ከምእምናን በምጽዋቶች ፈቃደኛ የኾኑትን፣ እነዚያንም የችሎታቸውን ያክል እንጅ የማያገኙትን ሰዎች የሚያነውሩ፣ ከእነሱም የሚስቁ አላህ ከነሱ ይሳለቅባቸዋል፤ (ይቀጣቸዋል)፡፡ ለእነሱም አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

የሑጁራት ምእራፍ ካካተተቻቸው መልካም እሴቶች ሌላው ደግሞ በሰዎች ላይ ከመቀለድ መራቅ ነው፡፡ እውነተኛ ምእምን በማነም ሰው ላይ አይቀልድም፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَىٰ أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَىٰ أَن يَكُنَّ خَيْرًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ሃማኖታችን በሌሎች ጉዳት የሚያደርሱን ነገሮች በሙሉ ከልክሎናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቃልም ይሆን ተግባር እንድሁም ምልከታ ሰዎችን ከሚጎዳ ነገር ሁሉ ከልክለዋል፡፡ በአንፃሩም በሰዎች ዓይን ላይ የአንድን ሰው ደረጃ ከፍ የሚያደርግንና ትሩፋቱን የሚያጎላን ነገር ሁሉ ያሳውቁለት ነበር፡፡ ኡሙ ሙሳ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ይላሉ፡ ‹አንድ ቀን ዓልይ ዘንድ ስለአብዱላህ ኢብን መስዑድ ተነሳ፡፡ ያን ጊዜ ዓልይ በርካታ ትሩፋታቸውን ዘረዘሩ፡፡ ከዚያም አንድህ አሉ፡ አንድ እለት ለጓደኞቻቸው ትምር ለማውረድ ወደዛፍ ወጡ፡፡ እነሱም የእግራቸውን ቅጥነት ባዩ ጊዜ ሳቁ፡፡ በዚያን ወቅት የአላህ መለክትኛ እንድህ አሉ፡ (ምን ያስቃችኋል? እሱ በትንሳኤ ቀን ሚዛን ከኡሁድ ተራራ የከበደ ይሆናል)፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የሑጁራት ምእራፍ ካቀፈቻቸው እሴቶች እጅጉን ታላቁ ደግሞ ወንድም አማማችነትንና ከሰዎች መካከል የማስታረቅ መርህ ከፍተኛ መሆኑን መጠቆሟ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ فَأَصْلِحُوا بَيْنَ أَخَوَيْكُمْ وَاتَّقُوا اللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ}**

ትርጉሙም (ምእመናኖች ወንድማመቾች ናቸው፡፡ በሁለት ወንድሞቻችሁም መካከል አስታርቁ፡፡ ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህን ፍሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

የዚህ ዓይነቱ የማስታረቅ እሴት የጠነከረና በመቻቻል የታነጸ ማህበረሰብ ለማዋቀር ታላቅ ሚና አለው፡፡ እሱም ለማንኛውም ግጭትና አለመግባባት ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡

በቤተሰብ ማእቀፍ ዙሪያ ከባልና ሚስት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በራሳቸው መፍታት የማይችሉበት ደረጃ ከደረሱ ከመካከላቸው የማስታረቅ ብቃት ያለው ሰው እንዲላክ ቁርአን አንድህ በማለት ያዘናል፡

**{وَإِنْ خِفْتُمْ شِقَاقَ بَيْنِهِمَا فَابْعَثُوا حَكَمًا مِنْ أَهْلِهِ وَحَكَمًا مِنْ أَهْلِهَا إِنْ يُرِيدَا إِصْلَاحًا يُوَفِّقِ اللَّهُ بَيْنَهُمَا إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيمًا خَبِيرًا} .**

ትርጉሙም ((እናንተ ዋቢዎች) የመካከላቸውንም ጭቅጭቅ ብታውቁ ከቤተሰቦቹ ሽማግሌን ከቤተሰቦችዋም ሽማግሌን ላኩ፡፡ ማስታረቅን ቢሹ አላህ በመካከላቸው ያስማማል፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የማስታረቅ መንፈስ ወደማህበረሰቡም የሚሸጋገር መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ያመለክታል፡

**{لَا خَيْرَ فِي كَثِيرٍ مِنْ نَجْوَاهُمْ إِلَّا مَنْ أَمَرَ بِصَدَقَةٍ أَوْ مَعْرُوفٍ أَوْ إِصْلَاحٍ بَيْنَ النَّاسِ وَمَنْ يَفْعَلْ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ مَرْضَاةِ اللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا} .**

ትርጉሙም (ከውይይታቸው በምጽዋት ወይም በበጎ ሥራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በብዙው ውስጥ ደግ ነገር የለበትም፡፡ ይኸንንም (የተባለውን) የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የማስታረቅን ታላቅ ምንዳና ሰዎችን የማጣላት አደጋን እንድህ በማለት ገጸዋል፡ ( እኔ ከሰግደትና ከምጽዋት ስለሚበልጠው ታላቅ ደረጃ አልነግራችሁም ወይ?) አሉ፡፡ ሰዎችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይሁን ይንገሩን አሉ፡፡ እሳቸውም (ከሰዎች መካከል ማስታረቅ ነው፡፡ ሰዎችን ማጣላት ደግሞ የሚላጭ ነገር ነው፡፡ ጸጉርን ይላጫል ማለቴ አይደልም ነገር ግን ሃይማኖትን ይላጫል ማለቴ ነው) አሉ፡፡

እውነተኛ ሙእሚን ማበጀትንና ማስታረቅን የህይወቱ ስርኣት የሚያደርግ ሲሆን እሱ ባለበት ቦታ ሁሉ ደግ ነገር ይኖራል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከሰዎች መካከል የደግ ነገር መከፍቻ የመጥፎ ነገር መዝጊያ የሆኑ አሉ፡፡ ከሰዎችም ደግሞ የመጥፎ ነገር መከፈቻ የደግ ነገር መዝጊያ የሆኑ አሉ፡፡ አላህ የደግ ነገር መከፈቻን በእጁ ያደረገለት ሰው ደስ ይበለው፡፡ አላህ የመጥፎ ነገር መከፈቻን በእጁ ያደረገበት ደግሞ ወዮለት)፡፡

ጌታዬ ሆይ ወደመልካም ምግባር ምራን፡፡ ያለንተ ወደመልካም ምግባር የሚመራ የለምና፡፡ ከኛም መጥፎ ጠባይን አስወግድልን፡፡ ያላንተ መጥፎ ጠባይን የሚያስወግድ የለምና፡፡ ሀገራችንንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# (8)

## የተከበሩት ነብያዊ ፈለጎችና በህግጋት ዘርፍ ያላቸው ታላቅ ቦታ

ምስጋን ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانْتَهُواۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም (መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት፡፡ ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡ አላህንም ፍሩ፡ ፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ሱ ወ.) የሰውን ልጅ ቅኑን መንገድ ለመምራት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማውጣት እንድሁም ከጥፋት መንገድ ወደደህንነትና ስኬት መንገድ ለማሸጋገር መልክተኞችንና ነብያትን ልኳል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላ፡

{لَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلَنَا بِالْبَيِّنَاتِ وَأَنْزَلْنَا مَعَهُمُ الْكِتَابَ وَالْمِيزَانَ لِيَقُومَ النَّاسُ بِالْقِسْطِ}

ትርጉሙም (መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን፡፡ ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደእነርሱ አወረድን፤..) ማለት ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) ነብያች መሐመድን የነሱ መደምደሚያ መሆናቸውን እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{ شَاهِدًا وَمُبَشِّرًا وَنَذِيرًا وَدَاعِيًا إِلَى اللَّهِ بِإِذْنِهِ وَسِرَاجًا مُنِيرًا}

ትርጉሙም (አብሳሪና አስፈራሪም አድርገን ላክንህ፡፡ ወደ አላህም በፈቃዱ ጠሪ፣ አብሪ ብርሃንም (አድርገን ላክንህ)፡፡ ማለት ነው፡፡

ይህ የመደምደሚያ መልእክት ለማንኛውም ጊዜና ቦታ ተስማሚ ሲሆን ከበፊቱም ሆነ ከበስተኋላው ብልሹነት የማይመጣበትና ታምራዊ የሆነውን ቅዱስ ቁርኣንን አውርዶለታል፡፡ ከዚያም ለቁርኣን አብራሪና ተንታኝ ይሆኑ ዘንድ አላህ (ሱ.ወ.) ለነብዩ ፈለጎችን በትንቢት መልክ ያሳወቀ መሆኑን እንድህ በማለት አስታውቋል፡

{وما ينطِقُ عَنِ الهوَى * إنْ هُوَ إلاّ وَحْيٌ يُوحَى}

ትርጉሙም (ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡ እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَأَنْزَلْنَا إِلَيْكَ الذِّكْرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيْهِمْ وَلَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ}

ትርጉሙም (ወደ አንተም ለሰዎች ወደእነሱ የተወረደውን (ፍች) ልትገልጽላቸውና ያስተነትኑም ዘንድ ቁርኣንን አወረድን፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሱ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላል፡ (ንቁ እኔ ቁርኣንና ሌላንም እሱን የሚያክል ተሰጥቻለሁ) ቅዱስ ቁርኣንን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው አላህ (ሱ.ወ.) በበርካታ አንቀጾች የሱንና የነብዩን ትእዛዛት በጣምራነት ያወሳ መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اسْتَجِيبُوا لِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ إِذَا دَعَاكُمْ لِمَا يُحْيِيكُمْ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! (መልክተኛው) ሕያው ወደሚያደርጋችሁ እምነት በጠራችሁ ጊዜ ለአላህና ለመልክተኛው ታዘዙ፡፡) ማለት ነው፡፡

በቀጣዩዋ አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ.) የሱንና የነብዩን ውዴታ በጣምራነት አውስቷል፡

وَٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥٓ أَحَقُّ أَن يُرۡضُوهُ إِن كَانُواْ مُؤۡمِنِينَ يَحۡلِفُونَ بِٱللَّهِ لَكُمۡ لِيُرۡضُوكُمۡ

ትርጉሙም (አላህንና መልክተኛውን ሊያስወድዱ ተገቢያቸው ሲኾን እናንተን ያስወደዷችሁ ዘንድ በአላህ ይምሉላችኋል፡፡ ምእምናኖች ቢኾኑ (አላህንና መልክተኛውን ያስወድዱ)፡፡ ማለት ነው፡፡

አንድሁም አላህ (ዐ.ወ.) ለነብዩ መታዘዝን ከሱ መታዘዝ ጋር እንድህ በማለት አውስቷል፡

{مَنْ يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللَّهَ}

ትርጉሙም (መልክተኛውን የታዘዘ በእርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡) ማለት ነው

አላህ (ዐ.ወ.) ለሱና ለነብዩ መታዘዝ የእዝነት ምክኒያት መሆኑን እንድህ በማለት አብራርቷል፡

{وَأَطِيعُوا اللَّهَ وَالرَّسُولَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ}

ትርጉሙም ( አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ፡፡ ሊታዘንላችሁ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡ እነድሁም እንድህ ይላል፡

{وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ}

ትርጉሙም (መልክተኛውንም ታዘዙ፡፡ ሊታዘንላችሁ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህ መታዘዝም እውን የሚሆነው ነብያችንን በመከተል መሆኑን አንድህ በማለት ገልጾልናል፡

{قُلْ إِنْ كُنْتُمْ تُحِبُّونَ اللَّهَ فَاتَّبِعُونِي يُحْبِبْكُمُ اللَّهُ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ}.

ትርጉሙም (በላቸው፡- «አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና፡፡ ኀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፡፡ አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

የእስልምና እምነት ሙሁራንና የህግ ባለሙያዎች በነብያችን ፈለጎች አስረጅነትና ከህግ መሰረቶች ከቅዱስ ቁርኣን ቀጥሎ ሁለተኛው መሰረት በመሆናቸው አንድ አቋም ወስደዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَنزَلَ اللَّهُ عَلَيْكَ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَعَلَّمَكَ مَا لَمْ تَكُنْ تَعْلَمُ وَكَانَ فَضْلُ اللَّهِ عَلَيْكَ عَظِيمًا}

ትርጉሙም( አላህም በአንተ ላይ መጽሐፍንና ጥበብን አወረደ፡፡ የማታውቀውንም ሁሉ አስተማረህ፡፡ የአላህም ችሮታ በአንተ ላይ ታላቅ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَاذْكُرْنَ مَا يُتْلَى فِي بُيُوتِكُنَّ مِنْ آيَاتِ اللَّهِ وَالْحِكْمَةِ إِنَّ اللَّهَ كَانَ لَطِيفًا خَبِيرًا}

ትርጉሙም (ከአላህ አንቀጾችና ከጥበቡም በቤቶቻችሁ የሚነበበውን አስታውሱ፡፡ አላህ እዝነቱ ረቂቅ ውስጠ ዐዋቂ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያዊ ፈለጎች የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ቃላት፣ ተግባራትና አይተው ያልተቃወሟቸውን ተግባራት ያካትታሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيرًا}

ትርጉሙም( ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

አብደላህ ኢብን ዐምር እንድህ ይላሉ፡ ‹እኔ ከነብየችን (ሰ.ዐ.ወ.) የምሰማውን ሁሉ እየመዘግብኩ በቃሌ ለመያዝ እሞክር ነበር፡፡ የቁረይሽ ነገዶች የአላህ መልክተኛ በደስታም በቁታም የሚናገሩትን ሁሉ እንዴት ትመዘግባለህ? በማለት ክለከሉኝ፡፡ እኔም መመዝገቤን አቆምሁኝ፡፡ በኋላም ይህን ነገር ለነብያችን ሰ.ዐ.ወ.) አወራሁላቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ወደአፋቸው አመለከቱና (መዝግብ መንፈሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ ከሱ እውነት እንጂ አይወጣም) አሉ፡፡

በእስልምና እምነት ህግጋት የመጀመሪያው ምንጭ ቅዱስ ቁርኣን ሲሆን ሁለተኛው የህግ ምንጭ የነብያችን ፈለጎች ናቸው፡፡

ምክኒያቱም እነሱ በአላህ መጽሐፍ ለተጠቀሱ ነገሮች ተንታኝና አብራሪ ናቸውና፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) በቁርኣን ለሚነግረን ነር ሁሉ ምን እንዳሰበ ከነብያችን በላይ የሚያውቅ ማንም የለም፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የሚሰጡት ፍርድ የአላህ ፍርድ መሆኑን አላህ (ሱ..ወ.) እንድህ በማለት አመልክቷል፡

{وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلَا مُؤْمِنَةٍ إِذَا قَضَى اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَمْرًا أَن يَكُونَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْ أَمْرِهِمْ}

ትርጉሙም (አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም! የአላህንና የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّى يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنفُسِهِمْ حَرَجًا مِّمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا}

ትርጉሙም (በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)፡፡ ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{وَإِذَا جَاءَهُمْ أَمْرٌ مِّنَ الْأَمْنِ أَوِ الْخَوْفِ أَذَاعُوا بِهِ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى الرَّسُولِ وَإِلَىٰ أُولِي الْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ الَّذِينَ يَسْتَنبِطُونَهُ مِنْهُمْ}

ትርጉሙም( ከጸጥታ ወይም ከፍርሃት አንዳች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ፡፡ ወደ መልከተኛውና ከእነርሱ ወደ ትዕዛዙ ባለቤቶች (ወደ ዐዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር፡፡) ማለት ነው፡

አላህ (ሱ.ወ.) ነብያችን ከመንቀፍ እንድንርቅ እንድህ በማለት አስጠንቅቆናል፡

{فَلْيَحْذَرِ الَّذِينَ يُخَالِفُونَ عَنْ أَمْرِهِ أَن تُصِيبَهُمْ فِتْنَةٌ أَوْ يُصِيبَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ}.

ትርጉሙም (እነዚያም ትዕዛዙን የሚጥሱ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ፡፡) ማለት ነው፡፡

የነብያችን ፈለጎች በርካታ በጥቅሉ በቅዱስ ቁርኣን የተወሱ ነገሮችን አብራርተዋል፡፡

ለምሳሌ የስግደትና የጾም ግዴታነት በቁርኣን እንድህ በማለት በጥቅሉ ተወስተዋል፡

{وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ}

ትርጉሙም (ስግደትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ ዘካንም ስጡ) ማለት ነው፡፡

በመሆኑም የእስልምና መእዘናት የሆኑትን ስግደትን፣ ዘካንና ሐጅን ያለነብያዊ ፈለጎች ማብራሪያ እንዴት ለንከናውን እንችላለን? ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) (እኔ ስሰግድ እዳያችሁኝ አድርጋችሁ ስገዱ) ብለዋል፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስም (ስግድት ለማድረስ በምታስብ ጊዜ አላህ አክብር በል፡፡ ከዚያም በቃል ከያዝከው ቁርኣን የቻልከውን አንብብ፡፡ ከዚያም አጎምብስ፡፡ ተጎንብሰህ እስከምትረጋጋ ደረስ፡፡ ከዚያም ቀጥ ብለህ ቁም፡፡ ተስተካክለህ እስከምትቆም ድረስ፡፡ ከዚያም በግምባርህም ተደፋ፡፡ በግንባርህ ተደፍተህ እስከምትረጋጋ ድረስ፡፡ ከዚያም ቀና ብለህ ተቀመጥ ተቀምጠህ እስከምትረጋጋ ድረስ፡፡ ከዚይም በስግደቶችህ ሁሉ እንደዚሁ አድርግ) በማለት አብራርተውልናል፡፡

እንድሁም የግዴታ የምጽዋትን (ዘካትን) አስመልክቶ ነብያዊ ፈለጎች በርካታ ማብራሪያዎች ሰጥተዋል፡፡ መጠናቸውንም ወስነዋል፡፡ የሐጅን ግዴታ አስመልክቶ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ከኔ ሀጅ የሀጅ ሥራዎቻችሁን ተማሩ) በማለት የሀጅ ሥራዎችን በተግባር አሳይተዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዒምራን ኢብን ሑሶይን የተባሉት የነብያችን ባልደረባ አንድ ሰውዬ ‹እነዚህ ቁርኣንን ቸል ብላችሁ የምታወሯቸው ሐዲሶች ምንድን ናቸው? ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ነበር፡ ‹አንተና ጓደኞችህ ቁርኣንን ብቻ በመያዝ ብትወሰኑ ኖሮ የዙህር (የቀትር) ስግደት ስንት ረከዓ እንደሆነ፣ እንድህም የዓስር (የቀትር በኋላ) ስግደት ስንት ረከዓ እንደሆነ እንዴት ታውቀ ኖሯል? እንደዚሁም የመግሪብ (የጳይ ግባት) ስገደት በሐጅ ሥራ የዐረፋ መቆሚያ ቦታን የጠጠር መወርወሪያ ቦታን እንዴት ታውቅ ኖሯል....›

ነብያዊ ፈለጎች በብዙ ሁኔታዎች በጥቅሉ በቁርአን የተጠቀሱትን ነገሮች እንደሚያብራሩ ሁሉ ያለወሰን ለተጠቀሱ ነገሮችም ወሰን ያስቀምጣሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ከህልፈቱ በኋላ ከገንዘቡ ለምጽዋት የሚውለው በአንድ ሦስተኛ የሚወሰን መሆኑን ያወቅነው በነብያዊ ፈለጎች ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሳዕድ ኢብን አቢ ወቃስ እንድህ ብለዋል፡ ‹መካ በነበርንበት ጊዜ ታመምኩና ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሊጠይቁኝ መጡ፡፡ እኔም ቀላል የማይባል ገንዘብ አለኝ፡፡ ሁሉም ገንዘቤ መጽዋት እንዲሆን መናዘዝ እችላለሁን? ስል ጠየቅኋቸው፡፡ እሳቸውም (እይሆንም) አሉኝ፡፡ እኔም ግማሹንስ? አልኩኝ፡፡ እሳቸውም (አይሆንም) አሉኝ፡፡ እኔም አንድ ሦስተኛውንስ ? አልኩኝ፡፡ እሳቸውም (አንድ ሦስተኛውን አድርግ፡፡ አንድ ሦስተኛውም ሲበዛ ነው፡፡ ወራሾችህን ባለጸጋ አድረገው ማለፈህ ሰዎችን የሚለምኑ ችግረኞች አድርገህ ከመተውህ የተሻለ ነው...) አሉኝ፡፡ ነብያዊ ፈለጎች የምጽዋት ኑዛዜ ለሚወርስ ዘመድ የማይፈቀድ፣ አንድ ሰው ከሚስቱ ላይ አክስቷን ማግባት የማይችል መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድት ሴት በእባቷ አህት ወይም በእናቷ እህት ላይ አትገባም)፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

*   *   *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የነብያዊ ፈለጎች ደረጃ ከፍተኛ፣ አስረጅነታቸው የተረጋገጠና በህግጋት ዘርፍ ያላቸው ቦታ ሰፊ መሆኑን ስናረጋግጥ በአምልኮት ከሚካተቱና በተለምዶ ከሚጠቃለሉ ተግባራት መካከል ሰፊ ልዩነት ያለ መሆኑን በግልጽ ማብራራት ይኖርብናል፡፡ በአልባሳት፣ በጉዞ ዘደዎችና በመሳሰሉ መስኮች የሚከናወኑ የተለምዶ ተግባራት እንደየክልሉና አንደየባህሉ ይለያያሉ፡፡ ምክኒያቱም አንደ ዘመን ካለፈው ዘመን የተለየ ባህል ሊኖረው ይችላልና፡፡ በመሆኑም የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ፈለግ ነው በሚል ከንቱ ምክኒያት ሰዎች የተወሰነ ተራንሰፖርት እንዲጠቀሙ፣ የተለዩ አልባሳት እንዲለብሱና በአንድ ዓይነት የአመጋገብ ዘዴ አንዲወሰኑ ማዘዝ በእርግጥ እእምሮ የማይቀበለው ነገር ነው፡፡

ማንኛውም ልማድ መሰረቱ ቋሚ የሃይማኖቱን ደንብ በማይጻረር መልኩ የሚከሰተው የዚያ ህብረተሰብ ትውፊት ነው፡፡ ኢማሙ አሻፊዒ ራስን መግለጥ ክብርን ዝቅ ያደርጋል ያሉት በዚያ ዘመን በተልመዶ ራሱን ገልጦ የሚሄድ ሰው ለክብሩ ምንም ዓይነት ትኩረት የማይሰጥ ሰው ብቻ ስለነበር ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ራሱን ገልጦ መሄድ ክብርን ዝቅ አያደርግም፡፡ መክኒያቱም ራስን መግለጥም ሆነ መሸፈን ከክብር ጋር ግንኙነት የሌለው ነገር ሆኗልና፡፡

እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የምንፈልገው ነገር የነብያዊ ፈለጎች ቀንደኛ ጠላት ሁለት ወገኖች መሆናቸውን ነው፡፡ ከእነሱም አንደኛው ወገን በሃይማኖት የሚነግዱና ለግል ጥቅማቸው እንዲስማማ የቃላትን ፍች የሚያጣምሙ ሰዎችን ያካትታል፡፡ እነዚህ ሰዎች በዚህ ተግባራቸው መልካም የሰራን እየመሰላቸው በሃይማኖት ስም በምድር ብልሹነትን ያስፋፋሉ፡፡ እነዚህ አጋናኝ ተፈላሳፊዎች ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሦስት ጊዜ በመደጋገም (እነዚያ የሚያጋንኑት ጥፋት ደረሰባቸው) በማለት ያስጠነቀቁን ወገኖች ናቸው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ እንድህ ይላሉ፡ ‹የአላህ መልክተኛ እንድህ አሉ፡ (በህዝቦቼ ላይ እጅጉን የምፈራላቸው የልሳን አዋቂ ምናፍቅን ተንኮል ነው)፡፡

ሁለተኛው ወገን ደግሞ እነዚያን ልባቸውን በእውቀት ብርሃንና በእውቀት መሳሪያዎች ያላነጹ ወገኖችን ያካትታል፡፡ የዚህን ወገን አደገኛነት ነብያችን እንዲህ በማለት አስጠንቅቀውናል፡ (አላህ ከዚህች ዓለም እውቀትን ከባሪያዎች ልብ በመንቀል አይደለም የሚያነሳው፡፡ ነገር ግን አውቀትን የሚየነሳው ሙሁራንን በማንሳት ነው፡፡ በምድር ላይ አንድም ሙሁር በማይኖርበት ወቅትም ሰዎች ማሀይማንን መሪ አድርገው ይይዛሉ፡፡ አነሱም ሲጠየቁ ያለእውቀት ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ በዚህም ተግባራቸው ራሳቸው ጠመው ሰውን ያጠማሉ፡፡ ነብያዊ ፈለጎች ከዋና መስመራቸው ስለሚያጋድል ጸንፈኛ እንድሁም በጠቅላላ ስለሚከዳቸው ልቅ ወገን ተጠያቂዎች አይደሉም፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ምንጣፉ ላይ ጋደም ብሎ ስለኔ ፈለጎች ያወራና ለሰዎች እኔንና እናንተን የሚያገናኘን የአላህ መጽሐፍ ብቻ ነው፡ ፡ በሱም የተፈቀደ ሆኖ ያገኘነውን የተፈቀደ እናደርጋለን፡፡ በሱም እርም የተደረገውን እርም እናደርጋለን፡፡ የሚልበት ቀን ተቃርቧል፡፡ ይህም የአላህ መልክተኛ እርም ያደረጉት ነገር አላህ እርም እንዳደረገው ነገር መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ ነው)፡፡

ማጋነንና ጸንፈኝነት ከልከኛው የእስልምና እምነት ደንብና ስርኣት እጅጉን የራቁ ናቸው፡፡ የቅኑ ሃይማኖታችን አጠቃላይ አላማዎች ሙሉ ፍትህ፣ ርህራሄና እንድሁም መቻቻልና ሰብእነት የተሞላበት ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ባህርያት እውን የሚያደርግ ማንኛውም ተግባር የእስልምና መመሪያ ሊሆን ይገባል፡፡ በአንፃሩም እነሱን የሚጻረር ሁሉ ከእምነቱ መመሪያ ውጭ ነው በሚለው አቋም ሊቀውንት ተስማምተዋል፡፡

እዚህ ላይ ይህን ጠማማነት ለማረቅና የዚህ ዓይነቱን ማጋደል ለማስተካከል የባለሞያ ሙሁራን ድርሻ በጣሙን የላቀ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ይህን እውቀት ከየተተኪዎቹ ፍትሃዊያን የአበላሾችን ማጣመም እያረቁ፣ የማሃይማንንም አንድምታ እያስተካከሉና የአጋናኞችን የተጣመም ፍች እያረሙ ያሸጋግሩታል)፡፡

እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት በቃላት ውጫዊ ገጽታ ከመወሰን ይልቅ የነብያዊ ፈለጎችን መሰረታዊ አላማ ጠለቅ ብለን መገንዘብ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ያን ጊዜም ከዘመኑ መንፈስና አዳድስ ነገሮች ጋር የሚጣጣሙ ዘመናዊ ግንዛቤ ኖሮን የነብያዊ ፈለጎችን አጠቃላይ አላማ ለህዝብ የቀረቡ ማደረግ እንችላልን፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) (ለዚህ ህዝብ በየመቶ ዓመቱ አጥቢያ ላይ ሃይማኖቱን የሚያድስለት ሰው ይፈጥርለታል) በማለት ያሰቡት እድሳትም የዚህ ዓይነቱን እድሳት ነው፡፡

*ጌታችን ሆይ የተከበረውን መጽሐፍ እንድሁም የመልክተኛህን ፈለጎች በተገቢው መንገድ መረዳትን ስጠን፡፡ የሚጠቅመንንም አሳውቀን፡፡ በአሳወቅህንም ሁሉ ተጠቃሚዊች አድርገን፡፡ አገራችንንም ከመጥፎ ነገር ሁሉ ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡*

## (9)

### የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)ሕይወት የትክክለኛው እስልምና ተጨባጭ ምሳሌ ነው

*ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ*

لَقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِمَنْ كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيرًا}

*ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡*

*ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡*

**ከዚህም በመቀጠል፡**

*አላህ (ዐ.ወ.) መልከተኛውን ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.)የላከው አቅኚ አብሳሪ እንድሁም ወደአላህ በፈቃዱ ጠሪና አብሪ ብርሃንም አድርጎ ነው፡፡ መልእክቱም መደምደሚያና አለም አቀፋዊ ሲሆን ለሁሉም ዘመንና ቦታ ተስማሚና አዳሽም ነው፡፡ ይህም የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቃላት፣ ተግባራትና አጠቃላይ የእለት ተእለት ኑሯቸው ለትክክለኛው እስልምና ተጨባጭ ምሳሌ መሆኑን በግልጽ አሳይቷል፡፡ ይህ መሆኑም አያስደንቅም ምክኒያቱም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከጌታቸው ጋር ለአላቸው ግንኙነቱም ሆነ ጎሳቸው፣ ቀለማቸውና እምነታቸው የተለያየ ቢሆንም እንኳ ከመላ ሰዎች ጋር በነበራቸው ውለታ የቁርኣንን ስርኣት ይከተሉ ነብርና፡፡ በመሁኑም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አናታችን ዓኢሻ ስለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጠባይ በተጠየቁ ጊዜ የሰጡት መልስ (ጠባያቸው ቁርኣን ነበር) የሚል ነበር፡፡*

የነብየችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ህይወት ታሪክ የሚመራመር ሰው በቃላታቸው፣ በተግባራታቸውና በማንኛውም የእለት ተእልት ኑሯቸው የነበራቸው ገጽታ ሊከተሉት የሚገባና አርአያነት ያለውም መሆኑን በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ጥቂቶቹን በንጠቅስ እውነተኛና ታማኝነታቸው ተቀዳሚ ሆነው እናገኛለን፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እድሜ ልካቸውን እውነተኛና ታማኝ በመሆናቸው ከህዝባቸው መካከል መልእክተኛ ሆነው ከመላካቸው በፊት ‹እውነተኛታማኙ› የሚል ስያሜ ተሰጥተዋል፡፡ አሕመድ ሸውቂ የተሰኘው የግብጽ የግጥም ደራሲ ይህን ሁኔታ ሲገልጹ እንድህ ብለዋል፡

‹በህፃንነቱ የሰዎች ታማኝ ብለው ሰየሙት በቃል ታማኝ የሆነ ሰው በምንም ተጠርጣሪ ሊሆን አይችልም፡፡›

የሩሞች ንጉስ ሂረቅል -የእስልምናን እምነት ከመቀበላቸው በፊት- አቡ ሱፍያን አቡ ሐርብን ጠርቶ ስለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በጠየቃቸው ጊዜ በሰጡት ሰፊ ማብራሪያ የሚከተለው ተካቷል፡ ሂረቅል ለአቡሱፍያን እንድህ ሲል ጠየቃቸው፡ ‹የሚለውን ከማለቱ በፊት በውሸት ትጠረጥሩት ነበርን? አቡ ሱፍያንም ኧረ አንጠረጥረውም ነበር አሉ፡፡ እሱም ክዳትስ ነበረውን? አለ፡፡ አቡ ሱፍያንም ኧረ የለም አሉ፡፡ ይሁንጂ ቃል ኪዳን የተጋባንበት ጊዜ አላለቀም ምን እንደሚያደርግም አናውቅም አሉ፡፡ አቡ ሱፍያን ታሪኩን ሲተርኩ ከዚህች ዐረፍተ ነገር ሌላ አጉዳፊ ቃል ማስገባት አልቻልኩም ነበር አሉ፡፡

የአመኔታ ጠባይ በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ማንነት በብሩህ ገጸታው እጅጉን ጎልቶ የታየው በተባረከው የሂጅራ ሌሊት ነበር፡፡ በዚያን ሌሊት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ ከምንጣፋቸው እንዲተኙና ሰዎች ያስመጡባቸውን አደራ ለባለቤቶቹ እንድመልሱ አዘዋቸው ነበር፡፡ ይህን ያደረጉትም እነዚህ አደራ ያስቀመጡት ሰዎች እሳቸውን የሚጠሉ፣ እሳቸውንና ባልደረቦቻቸውን የሚያሰቃዩዋቸውና ንብረታቸውን የሚቀሙ እንድሁም ከሀገርም እያበረሯቸው ሳሉ ነበር፡፡ ይሀውም ማንኛውም ምእምን ጠላቱ እንኳን ቢሆንም አንድን ሰው መክዳት አይፈቀድለትምና ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَإِمَّا تَخَافَنَّ مِنْ قَوْمٍ خِيَانَةً فَانْبِذْ إِلَيْهِمْ عَلَى سَوَاءٍ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْخَائِنِينَ}

ትርጉሙም (ከሕዝቦችም ክዳትን ብትፈራ (የኪዳኑን መፍረስ በማወቅ) በመተካከል ላይ ኾናችሁ ኪዳናቸውን ወደነሱ ጣልላቸው፡፡ አላህ ከዳተኞችን አይወድምና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አደራን ላስቀመጠብህ ሰው መልስ፡፡ የከዳህንም አትካድ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከማነም በላይ ቃልና አደራ አክባሪ ነበሩ፡፡ እሳቸው አንድም ቀን አንድን ክዳት ፈጽመውና የአንድንም ሰው ውለታ ክደው አያውቁም፡፡ ውለታ ለዋለላቸው ሁሉ ተመሳሳይ ውለታ ሳይመልሱ አሳልፈው አያውቁም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከዚህች ዓለም ከመለየታቸው በፊት እንድህ ብለዋል፡ (አንድም ሰው በኛ ላይ ስጦታ አልነበረውም አጸፋውን የመለስንለት ቢሆን እንጂ፡፡ አቡ በከር ሲቀር ለእሱ በትንሳኤ ቀን አላህ የሚመለስለት ስጦታ በኛ ላይ አለብን፡፡)

ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቃልና አደራ አክባሪነት ገጽታዎች ሌላው ደግሞ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ለእናታችን ኸዲጃ ያሳዩት የነበረው የውለታ አክባሪነት ገጽታ ነው፡፡ እሳቸው እናታችን ኸዲጃ በሕይወት በነበሩበት ወቅት አፍቃሪ፣ አክባሪና ታማኝ ነበሩ፡ ከሞቱ በኋላም በልባቸው ያላቸውን ታላቅ ቦታ በመገለጽ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) ከሷ በበለጠ ሰው አልተካኝም፡፡ እሷ ሰዎች በካዱኝ ወቅት አምናብኛለች፡፡ ሰዎችም ሀሰተኛ ባሉኝ ጊዜ እውነትህን ነው ብላኛለች፡፡ ሰዎች በከለከሉኝ ጊዜ በገንዘቧ አግዛኛለች፡፡ ከሌሎች ሳይሆን ከሷ አላህ (ዐ.ወ.) ልጆችን ሰጥቶኛል፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ ይላሉ፡ ‹ከንብዩ ሚስቶች በአንዷም በኸዲጃ የቀናሁትን ያህል ቀንቼ አላውቅም፡፡ አይቻት አላውቅም ነገር ግን ነብዩ ስሟን ማንሳት ያበዙ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፍየል ያርዱና ስጋዋን ቆራርጠው ለኸዲጃ ወዳጆች ያከፋፍሉት ነበር፡፡›

ሌላው የውለታ መላሽነት ገጽታቸው ደግሞ በበድር ጦርነት የእስልምና አምነት ተከታይ ስላልሆኑት ሰዎች ሁኔታ የተናገሩር ቃል ነው፡፡ በዚያን እለት እንድህ ብለዋል፡ (ሙጥዒም ኢብን ዓዲይ በሂዎት ኖሮ ስለነዚህ እስረኞች ቢጠይቀኝ ኖሮ ሁሉንም በለቀቅኋቸው ነበር፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከጧኢፍ በተመለሱ ጊዜ ወደመካ የገቡት ሙጥዒም ኢብን ዓዲይ በተባለው ሰው አስጠጊነት ስለነበር ውለታውን በማክበር ነው ይህን ያሉት፡፡

ነብያችን (ሶዐ.ወ.) ለጠላቶቻቸው ቢሆንም እንኳ ቃል ከማክበር ወደኋላ አይሉም ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሑዘይፋ ኢብንል የማን የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹በበድር ጦርነት ከመሳተፍ የከለከለኝ ሌላ ነገር አልነበረም ነገር ግን እኔና አባቴ ከመካ ለመውጣት ባሰብን ጊዜ የቁረይሽ ከሃዲዎች ያዙንና እናንተ ወደሙሐመድ እየሄዳችሁ ነው አሉን፡፡ እኛም አይደለም ወደመዲና ነው የምንሄደው አልን፡፡ እነሱም ቀጥታ ወደመዲና እንድንሄድና ከነብያችንም ጋር ተሰልፈን እንዳንዋጋ ቃል ኪዳን አስገቡን፡፡ ወደአላህ መልክተኛ በደረስን ጊዜም ይህን ወሬ ነገርናቸው፡፡ እሳቸውም ሂዱ -ወደመዲና- ቃላቸውን እናከብርላቸዋለን በነሱም ላይ ድል ለመቀዳጀት የአላህን እርዳታ አንለምናለን አሉ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሚስቶቻቸው ጋርም የነበራቸው ግንኙነት ተወዳዳሪ የሌለውና ሊከተሉት የሚገባ አርኣያነት ያለው እንደነበረ ይነገራልን፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሚስቶቻቸው ጋር ያሳለፉት ሕይወት በፍቅር፣ በርህራሄ፣ ራስን ዝቅ በማድረግና በለዘብተኝነት የተሞላ ነበር፡፡ ነብያችን አንድም ቀን በሚስቶቻቸው ላይ ኩራት የሚባል ነገር አሳይተው አያውቁም፡፡ ይልቁንም ከሁላቸውም ጋር የነበራቸው ግንኙነት በመልካም ምግባር የታነጸ ነበር፡፡ ይህውም አንድህ የሚለውን የአላህን ቃል መሰረት በማድረግ ነበር፡

{وَعَاشِرُوهُنَّ بِٱلۡمَعۡرُوفِ}

ትርጉሙም (በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፡፡)ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ የምትለዋ አንቀጽ የያዘችውን ትርጉም በመተግበር ነበር፡

{وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُمْ مِنْ أَنْفُسِكُمْ أَزْوَاجاً لِتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُمْ مَوَدَّةً وَرَحْمَةً إِنَّ فِي ذَلِكَ لَآيَاتٍ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ}.

ትርጉሙም (ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አዘኘ ባል ነበሩ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናችን ሶፍያ ሲያለቅሱ ባዩ ጊዜ አንባቸውን በተከበሩት እጆቻቸው በማበስ ያረጋጓቸው መሆኑ ተወርቷል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ይላሉ፡ ‹እናታችን ሶፍያ ከእለታት አንድ ቀን ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር በጉዞ እያሉ ወደኋላ ዘገዩ፡፡ ነብያችነም ጠብቀዋቸውና ሲቀበሏቸው በጎታታ ግመል አስቀምጠውኝ በማለት አለቀሱ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በእጆቻቸው ዓይኖቻቸውን እያበሱ አረጋግተው ዝም አሰኟቸው፡፡›

ነብያችን ከልጆቻቸውም ሆነ ከልጅ ልጆቻቸው ጋር የነበራቸውም ግንኙነት አርኣያነት ያለው ነበር፡፡ ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ጥልቅ ፍቅር፣ እዝነትና ርህራሄ ያላቸው መልካም አባትና ደግ አያት ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ ይላሉ ‹በመልካም ገጽታዋ፣ በደግ ሁኔታዋና በውብ ባህርይዋ ከአላህ መልክተኛ ልጅ ከፋጢማ የበለጠ ነብያችንን የሚመስል ሰው አይቸ አላውቅም፡፡ እንድህም አሉ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በምትመጣ ጊዜ ቁመው ይቀበሏትና ስመውም ከመቀመጫቸው ያስቀምጧት ነበር...፡፡)

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ብለዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) አል አቅረዕ ኢብን ሓርቢኒተይምይ የተባለው ሰውዬ አጠገባቸው ተቀምጦ እያለ የዓሊይን ልጅ ሐሰንን ሳሙት፡፡ አል አቅረዕ ይህን ባየ ጊዜ እኔ ዐሥር ልጆች አሉኝ አንድ ቀን አንዳቸውንም ስሜ አላውቅም አለ፡፡ እሳቸውም ላፍታ ተመለከቱትና (የማያዝን አይታዘንለትም)አሉ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን ሰዎችን በስግደት ሲመሩ ሱጁድን በጣም አስረዘሙ ስግደቱ ካለቀ በኋላ ሰዎች ያለህ መልክተኛ ሆይ በዚህ በዛሬው ስግተዎ ያደረጉት ሱጁድ ከዚህ በፊት አድርገውት የማወቁት የሱጁድ ዓይነት ነው እሱ የታዘዙት ነገር ነውን ወይስ ትንቢት እየወወረደለዎት ነበር? በማለት ጠየቁ፡፡ ነብያችንም ያለችሁት ሁሉ አልሆነም፡፡ ነገር ግን ልጄ ከጀርባዬ ላይ ተቀምጦ ነበርና የልቡን ሳያደርስ ማቋረጡን ስለጠላሁ ነው) አሉ፡፡

እዚህ ላይ ለማረጋገጥ የምንፈልገው ይህ ሁኔታ በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ልጆችና ልጅ ልጆች ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ነብያችን ለሁሉም ሰው ማስተማር የፈለጉት ስርኣት ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኡሳማ ኢብን ዘይድ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሀሰን ጋር ይዘዋቸው ሲንቀሳቀሱ (ጌታዬ ሆይ እኔ እወዳቸዋለሁና አንተም ውደዳቸው) ይሉ ነበር ሲሉ አውርተዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ይላሉ፡ ‹እኔ የአላህ መልክተኛን አስር አመታት አገልግያለሁ፡፡ አንድም

ቀን ኤጭ ብለውኝ፣ የሰራሁትን ነገር ይህን ለምን አደረግህው፣ የተውኩትንም ነገር ይህን ለምን አላደረግህም ብለውኝ አያውቁም፡፡›

ነብያችን እንደዚሁም ከባልደረቦቻቸው ጋር የነበራቸው መልካም ግንኙነት ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌነት ያለው ግንኙነት ነበር፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦቻቸውን በደስታቸውም ሆነ በሀዘናቸው ይጋሯቸው ነበር፡፡ የተሰወረውን ሰው የትሄደ ይሉና ከነሱም የታመመውን ሄደው ይጠይቁ ነበር፡፡ ጉዳዮቻቸውን በትኩረት ይከታተሉና በማንኛውም ሁኔታ ስሜታቸውን ለማስከበር ይጥሩ እንድነበር ይታወቃል፡፡ ሲማክ ኢብን ሐርብ የተባሉት ባልደረባ እኔ ‹ከአላህ መልክተኛ ጋር ትቀመጥነበርን? ብዬ ጃቢር ኢብን ሰሙራህን ጠየቅሁ፡፡ እሳቸውም አዎን ብዙን ጊዜ የሱብህን ሰግደት ከሰገዱበት ቦታ ጸሐይ አስከምትወጣ አይነሱም ነበር፡፡ ጸሓይ ከወጣች በኋላ ይነሱ ነበር፡፡ ባልደረቦች ተቀምጠውም ያወሩና የደንቁርናውን ዘመን እያነሱም ይስቁ ነበር በዚያን ጊዜ ነብያችንም (ሰ.ዐወ.) ፈገግ ይሉ ነበር፡፡ በማለት መለሱልኝ፡፡›

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በሰበአዊነታቸውና በስነ ምግባራቸው ለትክክለኛው እስልምና ተጨባጭ ምሳሌ ነበሩ፡፡ እንድሁም በለዘብተኝነታቸውና በእርጋታቸው ልንከተላቸው የሚገባ አርኣያ ናቸው፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጥሪ ያደረጉለትን ህግና ደንብ የሚመራመር ሰው በሁሉም ዘርፍ ያለውን የርጋታና የለዘብተኝነት ስርኣትን በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ ይላሉ፡ (የአላህ መልክተኛ ሁለት ነገሮች እንዲመርጡ ተጠይቀው ኣውቁም ወንጀል እስካልሆነ ድረስ ከነሱ ቀላሉን የሚመርጡ ቢሆን እንጂ፡፡ ወንጀል ከሆነ ደግሞ ከማነም የበለጠ ከሱ ይርቁ ነበር፡፡) እንድሁም ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡፡ (ሃማኖት ገር ነው፡፡ አንድም ሰው ሃይማኖትን አይታገለውም እሱ የሚያሸንፈው ቢሆን እንጂ፡፡ አጅግ አጥባቂ ወይም ሲበዛ ችልተኛ ሳትሆኑ መካከለኛ ሁኑ፡፡ የተሟላ ማድረግ ቢያቅታችሁ ወደሱ ለመቃረብ ጥረት አድርጉ፡፡ ቀላልም አንኳ ቢሆን ዘላቂነት ያለው መልካም ሥራ መንዳው የማይቀነስ መሆኑን አብስሩ፡፡ መልካም ሥራችሁን ዘላቂ ለማድረግ በማለዳ፣ በማታና በከፊል ሌሊት ንቁ በምትሆኑባቸው ጊዜያት ታገዙ፡፡)

የተጠቀሰውን ለዘብተኝነትና እርጋታን ዘላቂ ለማድረግ አንድቻል ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ከማንኛውም የማጋነን ገጽታ በተለይም ደግሞ ከሃይማኖተኝነት ማጋነን

አስጠንቅቀዋል፡፡ ነብያችን ከባልደረቦች በአምልኮት ከለዘብተኝነት በሚያወጣ መልኩ ያሳዩትን ማጋነን እንድህ በማለት አውግዘዋል፡ (እናንተ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖት እንዳታጋኑ አደራ እላችኋለሁ፡፡ ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ያጠፋቸውኮ የሃማኖት ማጋነን ነው፡፡)
እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) መከተል፣ በቀደዱት ቅን መስመር መጓዝና ብርሃንና መሪ የሆነውን መልእክታቸውን አላህ(ዐ.ወ.) ወደመላው የሰው ልጅ እንዳወረደው ምንም ያልተቀላቀለበት በሆነ መልኩ በለዘብተኝነት፣ በርህራሄና በእዝነት እንድሁም ልቦችን በሚያቃርብ መልኩ ለማሰራጨት መጣር በጣሙን ያስፈልገናል፡፡ የእስልምና መልእክት ሙሉ ፍትህ፣ ሰፊ መቻቻል፣ አጠቃላይ ጥቅምና ጥልቅ ሰብእነት ነው፡፡
ጌታችን ሆይ! አንተን እንድሁም መልክተኛህን መውደድን ለግሰን፡፡ ወደአንተ መውደድ የሚያቃርበንን ሥራ ሁሉ ገር አድርግልን፡፡ አገራችንን ሰላም አድርግልን ሌሎችን አገራት እንድሁ፡፡

## (10)

## ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለባልደረቦቻቸው የሰጡት የምስክርነት ቃል፣ የበላይነታቸው ማብራሪያና ከሱም የምንቀስመው ትምህርት፡፡

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጸሐፉ
{وَالسَّابِقُونَ الأَوَّلُونَ مِنَ الْمُهَاجِرِينَ وَالأَنصَارِ وَالَّذِينَ اتَّبَعُوهُم بِإِحْسَانٍ رَّضِيَ اللّهُ عَنْهُمْ
وَرَضُواْ عَنْهُ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي تَحْتَهَا الأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ذَلِكَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ የረገባው፡፡ ትርጉሙም (ከስደተኞቹና ከረዳቶቹም ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች ከነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው አላህ ከነሱ ወዷል፡፡ ከርሱም ወደዋል፡፡ በስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲሆኑ ለነርሱ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ እድል ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

### ከዚህም በመቀጠል፡

አላህ (ሱ.ወ.) ልባቸውን ንጽህ፣ አይምሯቸውን ብሩህ፣ ተፈጥሯቸውን ክቡርና ስነ ምግባራቸውን ታላቅ አድርጎ የፈጠራቸው መሆኑን መሰረት በማድረግ ለመልክቱ ከባሮቹ የፈለገውን እንደሚመርጥ ሁሉ ለነብያቱ ጎደኝነት፣ ለመልክቱ ተከላካዮችንና ከነሱም በኋላ መልክቱን በተማኝነትና መስዋእትነት በመከፈል ለማድረስ ብቃት ያለቸውን ሰዎች ይመርጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ٱللَّهُ يَصْطَفِي مِنَ ٱلْمَلَائِكَةِ رُسُلًا وَمِنَ ٱلنَّاسِ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ بَصِيرٌ}

ትርጉሙም (አላህ ከመላእክት ውስጥ መልክተኞችን ይመርጣል፡፡ ከሰዎችም (እንደዚሁ) አላህ ሰሚ ተመልካች ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ልባቸው ከዚህ ህዝበ በሙሉ ባጥም ምርጥ፣ አእምሯቸው እጅግ ብሩህና ከማስመሰልም ነፃ የሆነ ነበር፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለነቢዩ ባልደረባነት፣ ሃይማኖቱን ለማቃናትና ለአለም ህዝብም ለማድረስ የመረጣቸው በመሆኑ ይህ መሆኑ አያስደንቅም፡፡
ስለአላህ መልክትኛ ባልደረቦች ስናወራ ከነብያትና ከመልክተኞች ቀጥሎ ከሰው ልጅ ምርጥ ስለሆኑ ሰዎች እያወራን መሆኑ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) ኢብን አባስ እንድህ ይላሉ፡

{قُلِ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ وَسَلَامٌ عَلَىٰ عِبَادِهِ ٱلَّذِينَ ٱصْطَفَىٰ}

በምትለው አንቀጽ የተጠቀሱት ምርጥ ባሮች የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ናቸው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም (ሙሐመድ ሆይ! በል ምስጋና ለአላህ ይገባው፡፡ በነዚያም በመረጣቸው ባሮቹ ላይ ሰላም ይውረድ፡፡) ማለት ነው፡፡ ኢብን መስኡድ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፡ ‹አላህ የባሮቹን ልብ ተመለከተ እናም ካበሮቹ ሁሉ ልብ የሚበልጠው የሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ልብ ሆኖ አገኘው በመሆኑም ለራሱ መረጣቸው መልክተኛውም አደረጋቸው፡፡ ከዚያም ከሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ልብ በኋላ ያለውን የባሮቹን ልብ ተመለከተ ከባሮቹ ልብ ሁሉ የሚበልጠው የባልደረቦች ልብ ሆኖ አገኘው በመሆኑም ስለሃይማኖቱ የሚከላከሉ የነቢዩ ሚኒስተሮች አደረጋቸው፡፡ ለሙስሊሞች መልካም ሆኖ የታየ ነገር ሁሉ አላህ ዘንድም መልካም ነው፡፡ መጥፎ ሆኖ የታያቸውም አላህ ዘንድ መጥፎ ነው፡፡›
የተላቁ አላህን (ሱ.ወ.) ኪታብ የሚያስተነትን ሰው የነብያችን ባልደረቦች ቦታ ከፍተኛ፣ ደረጃቸውም የላቀ፣ የበላይነታቸውም እጅግ ታላቅ፣ መሆኑን ሊገነዘብ የሚችል መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ እነሱ አላህ (ሱ.ወ.) ከነሱ የወደደላቸውና እምነታቸው እውነተኛ መሆኑን እንድህ በማለት የመሰከረላቸው ናቸው፡

{لَّقَدْ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنِ ٱلْمُؤْمِنِينَ إِذْ يُبَايِعُونَكَ تَحْتَ ٱلشَّجَرَةِ فَعَلِمَ مَا فِي قُلُوبِهِمْ فَأَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ عَلَيْهِمْ وَأَثَابَهُمْ فَتْحًا قَرِيبًا}

ትርጉሙም (ከምእምናኖቹ በዛፉቱ ስር ቃል ኪዳን በሚጋቡህ ጊዜ አላህ በእርግጥ ወደደ፡፡ በልቦቻቸውም ውስጥ ያለውን ዐወቀ፡፡ በነሱም ላይ እርጋታን አወረደ፡፡ ቅርብ የሆነንም መከፈት መነዳቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ የቅዱስ ቁርአት ተንታኞች

‹በልቦቻቸውም ውስጥ ያለውን ዐወቀ› ሲል በልባቸው ያለውን ትእግስት፣ እውነተኛነት፣ ቃል አክባሪነት፣ ሰሚ ታዛዥነት፣ ወደሱ አላህ ለመራቸው እውነት መልካም አመለካከታቸውን ዐወቀ ማለት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) የመልክተኛውን ባልደረቦት በተቀደሰው ኪታቡ በበርካታ ቦታዎች አወድሷቸዋል፡፡ እንድህም ይላል፡
{الَّذِينَ اسْتَجَابُوا لِلَّهِ وَالرَّسُولِ مِنْ بَعْدِ مَا أَصَابَهُمُ الْقَرْحُ لِلَّذِينَ أَحْسَنُوا مِنْهُمْ وَاتَّقَوْا أَجْرٌ عَظِيمٌ * الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَانًا وَقَالُوا حَسْبُنَا اللَّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ * فَانقَلَبُوا بِنِعْمَةٍ مِّنَ اللَّهِ وَفَضْلٍ لَّمْ يَمْسَسْهُمْ سُوءٌ وَاتَّبَعُوا رِضْوَانَ اللَّهِ وَاللَّهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ}

ትርጉሙም (እነዚያ መቁሰል ካገኛቸው በኋላ ለአላህና ለመልክተኛው የታዘዙት ከነሱ ለነዚያ በጎ ለሰሩትና ለተጠነቀቁት ታላቅ ምነንዳ አላቸው፡፡ እነዚያ ሰዎቹ ለነርሱ ሰዎች ለናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሯቸው ያሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው በቂያችንም አላህ ነው ምን ያማረም መጠጊያ ያሉ ናቸው፡፡ ከአላህም በሆነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ሆነው ተመለሱ፡፡ የአላህንም ውዴታ ተከተሉ፡፡ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡
{لِلْفُقَرَاءِ الْمُهَاجِرِينَ الَّذِينَ أُخْرِجُوا مِنْ دِيَارِهِمْ وَأَمْوَالِهِمْ يَبْتَغُونَ فَضْلًا مِنَ اللَّهِ وَرِضْوَانًا وَيَنْصُرُونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ أُولَئِكَ هُمُ الصَّادِقُونَ * وَالَّذِينَ تَبَوَّءُوا الدَّارَ وَالْإِيمَانَ مِنْ قَبْلِهِمْ يُحِبُّونَ مَنْ هَاجَرَ إِلَيْهِمْ وَلَا يَجِدُونَ فِي صُدُورِهِمْ حَاجَةً مِمَّا أُوتُوا وَيُؤْثِرُونَ عَلَى أَنْفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ وَمَنْ يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِ فَأُولَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ

ትርጉሙም (ለነዚያ የአላህን ችሮታና ውዴታውን የሚፈልጉ አላህንና መልክተኛውንም የሚረዱ ሆነው ከአገሮቻቸውና ከገንዘቦቻቸው ለተወጡት ስደተኞች ድሆች (ይሰጣል) እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው፡፡ እነዚያ ከበፊታቸው አገሪቱን መኖሪያ ያደረጉት እምነትንም የለመዱት ወደነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ፡፡ (ስደተኞቹ) ከተሰጡትም ነገር በልቦቻቸው ውስጥ ቅሬታን አያገኙም፡፡ በነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ፡፡ የነፍሱንም ንፍገት የሚጠበቅ ሰው እነዚያ እነሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
የጥበበኛው አላህ አንቀጾች የነብዩን ባልደረቦች ጥልቅና በመዐዛ የታነጸ ውዳሴ፣ ታለቅና ውብ አክብሮታቸውን በመታሰቢያነት እንዳሰፈሩ ሁሉ ነብያዊ ሐዲሶችም እንደዚሁ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ዘንድ ለአላቸው ከፍተኛ ቦታ መስከር፣ የከፈሉትን መስዋእትነት አንጸባራቂና ቁርጠኝነታቸው በግልጽ ኣሳይ ሆነው በመተሳቢያነት ሰፍረው እናገኛቸዋለን፡፡ እነሱ እነዚያ ነብያችንን ያከበሩ፣ የረዷቸውና ያንን ከርሳቸው ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ፣ የነብያችንን ውዴታ ከራሳው፣ ከቤተሰቦቻቻውና ከሰውም ሁሉ ወዴታ ያስቀደሙ ናቸው፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ከፍተኛውን ኒሻን በማጥለቅና የተላላቅ ውዳሴ ዘውድን በመጫን የነበሯቸውን ድንቅ አቋሞችና ከፍተኛ

ደረጃቸውን እንዲህ በማለት መስክረዋላቸዋል፡ (ከሰዎች ደጎቹ በኔ ክፍለ ዘመን ያሉት ከዚያም ከነሱ ቀጥሎ ያሉትና እነሱም የሚለጥቁት ናቸው፡፡) ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ ከዋክብት የሰማይ ደህነነት ዋስተና ናቸው ከዋክብት ከተወገዱ ስለሰማይ የተነገረው ይከሰታል፡፡ እኔም የባልደረቦቼ ደህንነት ዋስትና ነኝ፡፡ እኔ በምሄድ ጊዜ ስለባልደረቦቼ የተነገረው ይደርሳል፡፡ ባልደረቦቼም የህዝቦቼ ደህንነት ዋስትና ናቸው፡፡ ባልደረቦቼም በሚሄዱ ጊዜ ስለህዝቦቼ የተነገረው ይፋ ይወጣል፡፡) ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ መካከል እኔን ያየና ለኔም ባልደረባ የሆነ ሰው እስካለ ድረስ በአማን ከመሆን አትወገዱም፡ በአላህ ይሁንብኝ ከናንተ መካከል እኔን ያዬኝን ያየና በልደረባዬን ባልደረባው ያደረገ ሰው አስካለ ድረስ በአማን ከመሆናችሁ አትወገዱም፡፡ በአላህ ይሁንብኝ ከናንተ መካከል  እኔን ያዬኝን ያየን ያየና የኔ ባልደረባን ባልደረባ ባልደረባው ያደረገ ሰው እስካለ ድረስ በአማን ከመሆናችሁ አትወገዱም፡፡) ኢብን አቡ ሸይባ ዘግበውታል፡፡ ከነሱ በኋላ የመጣ ማንኛውም ሰው ክብር ያገኘው በነብያችን ባልደረቦች ክብር እንጅ በሌላ እንዳልሆነ የተጠቀሰው ሐዲስ ያመለክታል፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ከፊል ባልደረቦችን በተለይም የመጀመሪያ ቀዳሚዎችን ቀዳሚነታቸውን በማውሳት በተጨማሪ ውዳሴ ለይተዋቸዋል፡፡ እንድህም ይላሉ፡ (ከህዝቦቼ ለህዝቦቼ በጣም አዛኙ አቡ በክር ነው፡፡ ከነሱም በአላህ ጉዳይ ብርቱው ዑመር ነው፡፡ በአክብሮት ሀፍረትም እውነተኛው ኡስማን ነው፡፡ ከነሱም ፍርድ አዋቂው ዓሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ ነው፡፡ ከህዝቦቼ እጅግ ታማኙ አቡ ዑበይዳህ ኢብን አል ጀራሕ ነው፡፡ ከህቦቼ የተፈቀደና እርም የሆነን ነገር በጥልቅ አዋቂው ሙዓዝ ነው፡፡ ከነሱም ቁርኣንን በማንበብ ተቀዳሚው ኡበይ ነው፡፡ ከነሱም የወርስ ህግ አዋቂው ዘይድ ነው፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ወደኡሑድ ተራራ ከአቡ በክር፣ ዑመርና ኡስማን ጋር በወጡ ጊዜ ተራራው በንብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ተደስቱ ተንቀጠቀጠ፡፡ ነብያችንም (ሰ.ዐ.ወ.) ኡሑድ ሆይ ተረጋጋ ባንተ ላይ ያሉት ነብይ፣ የአማኞች አማኝና ሁለት ምስክሮች እንጅ ሌላ አይደለም አሉት፡፡) ቡኻሪ ዘግበውታል፡፡ በሌላ ሐዲስ ነብያችን (ከነርሱ አላህ ይውደድና) የአቡ በክርና ዑመርን ታላቅ ደረጃ ሲገልጹ እንድህ ብለዋል፡ (የከፍተኛ ደረጃ ባለቤቶች ከነሱ በታች ያለ ሰው ከሰማይ አድማሶች በአንደኛው አድማስ የሚወጣ ኮከብ እንዲሚታይ ሁሉ ያያቸዋል፡፡ አቡ በክርና ዑመር ከነሱ መካከል ናቸው እንዳውም ይጨምራሉ፡፡) ኢብን ማጀህ ዘግበውታል፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የህዝቡ ሁሉ አርኣያ ይሆኑ ዘንድ ለማበረታትና ወኔያቸውንም ለማጠንከር የባልደረቦቻቸውን ከፍተኛ ቦታና ታላቅ ደረጃ ይፋ ከማድረግ  ወደኋላ አይሉም ነበር፡፡ ለምሳሌ ስለአቡ በክር እንድህ ብለዋል፡ (በባልደረባዬ አታስከፉኝ፡፡ አላህ (ኢ.ወ.) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት በላከኝ ጊዜ ውሸታም አላችሁ፡፡ አቡ በክር ደግሞ እውነትህን ነው አለ፡፡ አላህ (ኢ.ወ.) ባልደረባ ብሎ ባይጠራው ኖሮ

ወዳጄ አለው ነበር፡፡ ነገር ግን የአላህ ወንድምነት...) ቡኻሪና ሌሎችም ዘግበውታል የሰፈረው ቃል የጠበራኒ ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለዑመር ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡ ( ታላቁ አላህ እውነትን በዑር ምላስና ልብ አድርጓል፡፡) ኢማሙ አሕመድ ዘግበውታል፡፡ ነብያችን ስለኡስማንም እንዲህ ብለዋል፡ (እኔ መላእክት በአክብሮት የሚያፍሩትን ሰውዬ በአክብሮት አላፍረውምን?) ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ ስለዓሊይም እንድህ ብለዋል፡ (አንተ ከኔ ነህ እኔም ካንተ ነኝ፡፡) ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለባልደረቦቻቸው የተናገሩትን ሐዲሶችና የሰጡትንም መስክርነት የሚከታተል ሁሉ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለባልደረቦቻቸው ቃልን በመክበር፣ እውነተኛን ፍቅር በማሳየትና በመልካም ምግባር ዘርፎች በታሪክ የማይደገም የሆነን ድንቅ የሚባል አርኣያነት ማሳየታቸውን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የባልደረቦች ህመም ይሰማቸው ነበርና በጣም ያዝኑላቸው ነበር፡፡ ስለተሰውሩትም ይጠይቁ፣ የተማሙትንም ይጎበኙ፣ ሙታቸውንም ይሸኙ፣ ጥሪያቸውንም ያከብሩ፣ በነገሮችም ሁሉ ያማክሯቸው፣ በርህራሄያቸውም ይሸፍኗቸው፣ እዳቸውንም ይከፍሉላቸው፣ ለሳቸውና ለልጆቻቸውም ጸሎት ያደርጉላቸው ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን አኢሻ የሚከተለውን አውረተዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ ኡስማን ኢብን መዝኡን በሞቱ ጊዜ ወደከፍላቸው ገቡና ወደአስክሪናቸው ተደፍተው አለቀሱ ያን ጊዜ እንበቸው በጉንጮቻቸው ሲወርዱ አየሁ›፡፡ አብደራዚቅ ዘግበውታል፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከእለታት አንድ ቀን ከአጋሪዎች ጋር የተደረገ ውጊያ እንደተጠናቀቀ ባልደረቦቻቸውን እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ (ያልተገኘ ሰው አለንዴ) ሲሉ ጠየቁ፡፡ እነሱም አዎን አገሌ፣ እገሌና እገሌ አልተገኙም ሲሉ መለሱ፡፡ እሳቸውም (ሌላስ ያልተገኘ አለን) ሲሉ ጠየቁ፡፡ እነሱም አዎን አገሌ፣ እገሌና እገሌ አሉ፡፡ አሳቸውም (ሌላስ ያልተገኘ አለን) ሲሉ አሁንም ጠየቁ፡፡ እነሱም የለም ሲሉ መለሱ፡፡ ያን ጊዜ (ነግር ግን እኔ ጁለይቢብን አላየሁትም አስኪ ፈልጌት) አሉ፡፡ ሲፈልጉት ሰባቱን የጠላት ወገን ከገደለ በኋላ ከገደሉት አስክሪኖች መካከል አገኙት፡፡ ከዚያም ነብያችን ወደአስክሪኑ ቦታ መጡና አጠገቡ ቆመው (ሰባቱን ገድሎ ከዚያ በኋላ ገደሉት፡፡ ይህ ሰው ከኔ ወገን ነው እኔም ከሱ ወገን ነኝ) አሉና ከክንዳቸው ውስጥ አስገብተው መቃብሩ ውስጥ አስገቡት፡፡ ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡፡ (እኔ ለማንኛውም ምእምን ከነፍሱ ተቀዳሚ ነኝ፡፡ ገንዘብ የተወ ሰው ገንዘቡ ለቤተሰቡ ውርስ ይሁን፡፡ እዳን ወይም የሚጠፋ ነገር የተወ ሰው በኔ ላይ ግዴታ ነውና ወደኔ ይምጣ) ይሉ ነበር፡፡ ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ህዝቡ መላ ባልደረቦቻቸውን እንዲያገብር ኑዛዜ ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም እነሱን የሚያስከፉ ወይም ክብራቸውን የሚያንኳሰስ ነገር እንዳንፈጽም አስጠንቅቀዋል፡፡ ከዚያም አልፎ አነሱን መውደድ ነብዩን የመውደድ፣ እንሱን መጥላት ደግሞ ነብሑን የመጥላት ምልክት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ስለባልደረቦቼ አላህን ፍሩ አሁነም አላህን ፍሩ፡፡ ከኔ በኋላ የጽያፍ ቃል መሰንዘሪያ ኢላማ አታድረጓቸው፡፡ የወደዳቸው እኔን በመውደዱ ነው የሚወዳቸው፡፡ የጠላቸውም እኔን በመጥላቱ ነው የሚጠላቸው፡፡ እነሱን ያሰከፋ በአርግጥም እኔን እስከፍቷል፡፡ እኔን ያሰከፋም በእርግጥ አላህ (አ.ወ.)ን አስከፍቷል፡፡ አላህን ያስከፋ ሳይቀጣው አይቀርም፡፡) ኢማሙ አሕመድና ቲርሚዚ ዘግበውታል፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ባልደረቦችን አትሳደቡ፡፡ ከናንተ እንዳችሁ የኡሑድ ተራራን የሚመዝን ወርቅ ምጽዋት ቢሰጥ አንኳ የነሱን አፍኝ ወይም ግማሹን ሊደርስለት አይችልም፡፡) ቡኻሪ ዘግበውታል፡፡ እንድሁም አንድህ ላሉ፡ (የበረከት ባለቤት የሆነው አላህ እኔን መረጠኝ በኔም ባልደረቦችን መርጦ ከነሱ ለኔ ሚኒስተሮች፣ ረዳቶችና አማቾች አደረገለኝ፡፡ የሰደባቸው ሰው የአላህ፣ የመላእክትና የሰዎች በሙሉ ርግማን ይድረስበት፡፡ ያ ሰው በቂያማ እለት የሱ ጸጸቱም ሆነ መዳኛ ቤዛው ተቀባይነት አያገኝም፡፡)

የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦችን ህይወት ታሪክ በጥሞና የሚመለከት ሰው አነሱ ከዚህ ከፍተኛ ደረጃና የላቀ ቦታ ለአላህ (አ.ወ.) በታማኝነት በመገዛታቸው፣ ለመልክተኛው የነበራቸው ፍቅር አውነተኛ በመሆኑ፣ ነፍሳቸውን ለማሸነፍ ባደረጉት ትግል፣ እውነትን በመደገፋቸውና ለሱም በመከላከላቸው፣ የህዝቡን ጥቅም ከግል ጥቅም በማስቀደማቸው፣ በመልካም ምግባራቸውና ከሁሉም ጋር ያለቸው ግንኙነት ያማረ በመሆኑ እንጂ በሌላ ነገር አንዳላገኙት በቀላሉ ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡ ባልደረቦች ይህን ሁሉ በማድረጋቸው የአላህ (አ.ወ.)ን ውዳሴ ተቸሩ፡፡ ለነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ወዴታና እምነት ሙሉ ብቃትን አገኙ፡፡ የሚከተለው ግጥም ደራሲ እጅጉን ይደነቃል፡፡

እነሱ የሰዎች ሁሉ ወላላ ናቸውና ደረጃቸውን እወቅ፡፡ በነሱም መርህ አንተ ስኬትን የምትፈልግ ሰውዬ ተከተል፡፡

የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ትውልድ ከነብያችን መላክ በፊት በምድር ተስፋፍቶ የነበረውን ከንቱ. በደልና ወሰን መተላለፍ በመለኮታዊ ትንቢት በመታገዝ ወደእውነት፣ ፍትህና እኩልነት በመቀየር የህይወትን ገጽታ በመለወጥ ረገድ ተቀዳሚው ትውልድ ነበር፡፡ በመሆኑም የነብያችንን ባለደረቦች መውደድ የነብዩን ፈለግ እንደመከተል መከተል፣ ለነሱም ጸሎት ማድረግ ወደአላህ መቃረቢያ ኢባዳ፣ እነሱን አርኣያ ማደረግ የስኬት መሰረት እንድሁም ፋናቸውን መከተል ታላቅ ክብር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ከባልደረቦች የስደተኞችና ረዳቶችን ባህርይ ከገለጸ በኋላ እንዲህ ይላል፡

وَالَّذِينَ جَاءُوا مِنْ بَعْدِهِمْ يَقُولُونَ رَبَّنَا اغْفِرْ لَنَا وَلِإِخْوَانِنَا الَّذِينَ سَبَقُونَا بِالْإِيمَانِ وَلَا تَجْعَلْ فِي قُلُوبِنَا غِلًّا لِلَّذِينَ آمَنُوا رَبَّنَا إِنَّكَ رَءُوفٌ رَحِيمٌ}

ትርጉሙም (እነዚያ ከበኋላቸው የመጡት ጌታችን ሆይ! ለኛም ለነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምህረት አድርግ፡፡ በልቦቻችን ውስጥ ለነዚያ ለአመኑት (ሰዎች) ጥላቻን አታድርግ ጌታችን ሆይ! አንተ ርህሩህ አዛኝ ነህና ይላሉ፡፡) ማለት ነው፡፡
ኢማመሙ ራዚ የተባሉት ሊቅ ከስደተኞችና ረዳቶች ባልደረቦች በኋላ የመጣ ሰው ሁሉ እነሱን በጸሎት ሊያስታውሳቸው ይገባል ይላሉ፡፡
እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የሚገባ ነገር ቢኖር የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦችን ከፍተኛ ቦታና ታላቅ ደረጃ ስንገልጽ ለልጆቻችንና ለወጣቶቻችን አማራጭ የሌለውን የመልካም አርኣያነት ሚናን ማጠናከርን ኢላማ በማድረግ ነው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አርኣያነትን መሰረት ያደረገ አስተዳደግ አጠቃላይ በማህበረሰቡ በተለይም ደግሞ በታዳጊው ልብ ጠቃሚ እሴቶችን፣ መልካም ምግባሮችንና አወንታዊ ስርኣቶችን በማስረጽ ረገድ ጥልቅ ተጽእኖ አለው፡፡ በመሆኑም ወጣቶቻችን የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ግንዛቤን መሰረት ያደረጉትን ትክክለኛ የእስልምና መመሪያዎችን ለመተግበር ለዘብተኛና መካከለኛ አስተሳሰብን መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም መልእክትንና አደራን ለማድረስ፣ ህብረተሰቡን ካለበት ግልጽ ያልሆነ አስተሳሰብ ወዝግብ አዘቅጥ ለማውጣትና ወደቅኑ፣ ሰላሙ፣ መረጋጋቱና ብልጽግናው መስመር ለማድረስ ሙሉ ብቃት እንዲኖራቸው የተለየ ማንነታቸውንም ማዋቀር ይጠበቅባቸዋል፡፡
እኛ በአሁኑ ወቅት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦችን ከፍተኛ ቦታና ታላቅ ደረጃን መገንዘብ፣ ስነ ምግባራቸውንና ፈለጋቸውን መከተል እንድሁም ከሕይወት ታሪካቸው የመስዋእትነት፣ የስጦታ፣ ለእምነታችን የነፍስ፣ የገንዘብና የልጅ ቤዛ የመከፈል መንፈስን መማር፣ የእስልምናን እውነተኛ ገጽታና ገራገርነቱን በሚገልጽ መልኩ ይህችን ዓለም ለመገንባት፣ ስልጣኔን ለማስፋፋት፣ ህዝብና አገርን የሚጠቅም ተግባርን ለማከናወን በነሱ ፈር መጓዝ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡
ለኛና በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምህረት አድርግል፡፡ በልቦቻችን ለነዚያ ላመኑት ሰዎች ጥላቻ አታድርግ፡፡ ጌታችን ሆይ! አንተ አዛኝ ርህሩህ ነህና፡፡

# (11)

## (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ከባልደረቦች አንጸባራቂ ገጽታዎች በጥቂቱ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَالسَّابِقُونَ الأَوَّلُونَ مِنَ الْمُهَاجِرِينَ وَالأنصَار وَالَّذِينَ اتَّبَعُوهُم بِإِحْسَانٍ رَّضِيَ اللَّهُ عَنْهُمْ
وَرَضُوا عَنْهُ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَنَّاتٍتَجْرِي تَحْتَهَا الأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ذَلِكَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከሰደተኞቹና ከረዳቶቹም ሲኾኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው አላህ ከእነሱ ወዷል ከእርሱም ወደዋል፡፡ በሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲኾኑ ለእነርሱ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ ዕድል ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ሱ.ወ.) ከፍጥራታቱ ነብያቶቹንና መልከተኞቹን (ዐ.ሰ.) መርጧል፡፡ እንድህም ይላል፡

{اللَّهُ يَصْطَفِي مِنَ الْمَلَائِكَةِ رُسُلًا وَمِنَ النَّاسِ إِنَّ اللَّهَ سَمِيعٌ بَصِيرٌ}

ትርጉሙም (አላህ ከመላእክት ውስጥ መልከተኞችን ይመርጣል፡፡ ከሰዎችም (እንደዚሁ)፤ አላህ ሰሚ ተመልካች ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
አሁንም አላህ (አ.ዐ.) መልከተኞቹ የጌታቸውን መልከት ሲያደርሱ የሚያግዟቸውን ባልደረቦች መርጦላቸዋል፡፡ አላህ (ጀ.ወ.) ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሱ ያመኑበትንና ያገዙትን፣ የረዱትንና በእሳቸው ላይ የወረደውን ብርሃን የተከተሉ ንጻሃን ሰዎችንና ምርጥ ባልደረቦችን አመቻችቶላቸዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን መስኡድ እንድህ ይላሉ፡ ‹አላህ የባሮቹን ልብ ተመለከተና ለመልክቱ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) መረጠና ላካቸው በእውቀትም ለያቸው፡፡ ከዚያም ከሳቸው በኋላ የሰዎችን ልብ ተመልክቶ ባልደረቦችን መረጠላቸው፣ የሃይማኖቱ አጋዥና የነብዩም ሚኒስተሮች አደረጋቸው፡፡ በመሆኑም ምእምናን በመልካምነት ያዩት ነገር ሁሉ አላህ ዘንድም መልካም ነው፡፡ ምእምናን በመጥፎነት የተመለከቱት ነገር ደግሞ አላህ ዘንድም መጥፎ ነገር ነው፡፡›
(ከነሱ አላህ ይውደድና) ባልደረቦች በእምነት ረገድ ከሰዎች ሁሉ የበለጠ እውነተኞች፣ በእውቀትም በላጮቹ፣ በግንዛቤም ተቀዳሚዎቹና በመልካም ሠራም ቀደም ተጠቃሾቹ እነሱ ነበሩ፡፡ እነሱም በጥበብና በመልካም ጥሪ የሃይማኖትን ሰንደቅ አላማ በማንገብ የጌታቸውን መልከት ወደተለያዩ የአለማችን ክፍል በተገቢው መልኩ አድርሰዋል፡፡ ከዚህም አኳያ ለመልከተኛው የለያቸው ምርጥ የአላህ ፍጥረታት የሚል ስያሜ ሊሰጣቸው ተገቢ ሆኗል፡፡ ኢብን ዓባስ የተባሉት ባልደረባ እንድህ የሚለውን የአላህን ቃል ሲያብራሩ፡

{قُلِ الْحَمْدُ لِلَّهِ وَسَلَامٌ عَلَى عِبَادِهِ الَّذِينَ اصْطَفَى}

ትርጉሙም ((ሙሐመድ ሆይ) በል «ምስጋና ለአላህ ይግባው፡፡ በእነዚያም በመረጣቸው ባሮቹ ላይ ሰላም ይውረድ፡፡ አላህ በላጭ ነውን ወይስ ያ የሚያጋሩት (ጣዖት)፡፡) ማለት ነው፡፡
የሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦችን ማለቱ ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ለነብዩ (ሶ.ዐ.ወ.) የመረጣቸው ሲሆን እነሱም የእስልምናን ስርኣት ከንጹህ መንጩ የጠጡት እነሱ በመሆናቸው ከቀጥተኛው መንገድ አንድም ጊዜ አላፈነገጡም ብለዋል፡፡
የባልደረቦች የእለት ተእለት ኑሮ የትክክልኛውን እስልምና ተጨባጭ ተግባር በአንጸባረቁ አኩሪ ገጸታዎች የተሞሉ ነበሩ፡፡ ከነዚህ ገጽታዎች በቅድሚያ የሚጠቀሰው ርህራሄያቸው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የርህራሄን ጠባይ በባልደረቦቻቸው ልቦች ጠለቅ አድርገው ነበር የተከሉት፡፡ ይህንም ከሚከተለው አጭር ታሪክ እንገነዘባለን፡፡ ከእለታት አንድ ቀን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይዲና ዑመር ኢብን አልኸጣብ ከልጆቻቸው አንደኛውን ከጭናቸው ላይ አስቀምጠው ሲስሙት ዑይይና ኢብን ሒስን የተባለ ሰው አያቸው፡፡ በተግባራቸው ተደንቆ እርሰዎ የምእምናን መሪ ሆነው ሳለ ልጅ ትስማለሁን? እኔ የምእምናን መሪ ብሆን ኖሮ አንዱንም ልጄን ባልሳምኩ ነበር ሲል ተናገረ፡፡ ያን ጊዜ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አላህ (ዐ.ወ.) ከልብህ እዝነትን አስወግዶ ከሆነ እኔ ምን ላደርግልህ እችላለሁ? አላህ ከባሮቹ የሚያዝነውኮ አዛኞች ለሆኑት ነው› አሉ፡፡›
ሰይዲና ዑመር በዚህ ተግባራቸው ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የተማሩትን በተግባር እያሳዩ ነበር፡፡ የዚህ ዓይነት አቋም ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እና አል አቅረዕ ኢብን ሓቢስ መካከልም ተከስቷል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አል አቅረዕ በአለበት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የዓሊ ልጅ የሆኑትን ሐሰንን ሳሙ፡፡ ያን ጊዜም፡፡ እሱ በተግባራቸው ተገርሞ እኔ አስር ልጆች አሉኝ አንድም ቀን አንዳቸውንም ስሜ አላውቅም አለ፡፡ የአላህ መልክተኛም ላፍታ ተመለከቱትና (የማያዝን አይታዘንለትም) አሉ፡፡
የነብያችን ባልደረቦች ምህረት በማድረግና በመቻቻልም አርኣያነት ያለቸው ተግባራት ነበሯቸው፡፡ በዚህ መስክ ከታዩ የላቁ ገጽታዎች በመጀመሪያ የሚጠቀሰው ሰይዲና አቡ በከር አሲዲቅ ለሚስጦሕ ኢብን ኡሳሳ ያደረጉት ምህረት ነው፡፡ አቡ በክር አሲዲቅ ድሃ ስለሆነና ስለዝምድናውም ለሚስጦሕ ቀለብ ይሰፍሩለት ነበር፡፡ ሚስጦሕ «በኢፍክ» ጊዜ ስለእናታችን ዓኢሻ ወሬ ካናፈሱ ሰዎች አንደኛው ነበር፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የእናታችን ዓኢሻ ነጻነት ያዘሉ አንቀጾች ካወረደ በኋላ አቡ በከር ለሚስጦሕ ይሰፍሩ የነበረውን ቀለብ ለማቆም አሰቡ፡፡ በዚያን ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) የምትከተለውን አንቀጽ አወረደ፡

**وَلَا يَأْتَلِ أُولُو الْفَضْلِ مِنْكُمْ وَالسَّعَةِ أَنْ يُؤْتُوا أُولِي الْقُرْبَى وَالْمَسَاكِينَ وَالْمُهَاجِرِينَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَلْيَعْفُوا وَلْيَصْفَحُوا أَلَا تُحِبُّونَ أَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ}**

ትርጉሙም (ከእናንተም የችሮታና የክብረት ባለቤቶች የኾኑት ለቅርብ ዘመዶችና ለድኾች በአላህም መንገድ ለተሰደዱ ሰዎች ላይሰጡ አይማሉ፡፡ ይቅርታም ያድርጉ፡፡

(ጥፋተኞቹን) ይለፉም፡፡ አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን አላህም መሐሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
በዚያን ጊዜ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ በከር አሲዲቅ ‹በአላህ ይሁንብኝ እኔ አላህ ምህረት እንዲያደርግለኝ እወዳለሁ› አሉና የሚስጦሕን ቀለብ መስፈራቸውን ቀጠሉ፡፡ በአላህ ይሁንብኝ እድሜ ልኬን አላቋርጥም አሉ፡፡
ከባልደረቦች ሕይወት አኩሪ ገጾታ ሌላው ደግሞ የነበራቸው ከፍተኛ ወኔና በመልካም ሥራ ያደረጉት የነበረው መሽቀዳደም ነው፡፡ ባልደረቦች ጠንከራ ወኔን በመልከም ሥራ መሽቀዳደምንና ከነገሮችም ከፍተኛ የሆነውን መፈለግን ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ተምረዋል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (... አላህን በምትለምኑ ጊዜ ፊርደውስን ለምኑት፡፡ ፊርደውስ ማለት የጀነት እጅግ ሰፊውና የላይኛው ክፍል ነው፡፡ ሐዲሱን የሚያወሩት -ይመስለኛል እንድህም ብለዋል-፡ ከሱ በላይ የራሕማን ዙፋን ይገኛል  ከሱም የጀነት ወንዞች ይመጫሉ፡፡)
ከዚህም አንጻር ባልደረቦች በማንኛውም ነገር ከፍተኛውን ነበር ለማከናውን የሚንቀሳቀሱት፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይዲና ኡመር ኢብን አልኸጣብ እንድህ ይላሉ፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጽዋት እንድንሰጥ አዘዙን፡፡ በጋጣሚ በዚያን ወቅት ዳጎስ ያለ ገንዘብ ነበረኝ፡፡ እኔም ዛሬ አቡ በከርን እቀድመዋለሁ፡፡ አንድ ቀን እንኳን ልቅደመውንጂ ብዬ አሰበኩኝ፡፡ ከንብረቴ ግማሹን ይዤ ሄድኩኝ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለቤተ ሰብህ ምን ያህል አስቀረተህለቻዋል? ሲሉ ጠየቁኝ፡፡ እኔም ይህ ያመጣሁት ያህል አስቀርቼላቸዋለሁ አልኩኝ፡፡ ኡመር በመቀጠል እንድህ አሉ፡ በዚያን ቀን አቡበከር ንብረታቸውን ሁሉ ይዘው መጡ፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ለቤተሰብህ ምን ተውክላቸው? ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ አላህንና መልከተኛውን ትቸላቸዋለሁ አሉ፡፡ እኔም አቡበከር ሆየ! ከዛሬ ጀምሮ አድሜ ልኬን በምንም ነገር ልቀድምህ አልሞክርም አልኩኝ፡፡›
(ከርሳቸው አላህ ይደድና) ካዕብ አልአስለሚይ የተባሉት ባልደረባ ደግሞ የሚከተለውን ተርከዋል፡ ‹እኔ በአንድ ወቅት ከአላህ መልክተኛ ጋር አድር ነበር፡፡ የወዱ ውሃና ሌሎችም የሚያስፈልጉ ነገሮችን አቀረብኩላቸው፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የምትፈልገውን ነገር ጠይቀኝ አሉኝ፡፡ እኔም በጀነት የርሰዎ አብሮ ኗሪ መሆንን እፈልጋለሁ አልኳቸው፡፡ እሳቸውም (ሌላ ነገር መጠየቅ አትችልም) አሉኝ እኔም ይህን ብቻ ነው የምፈልገው አልኳቸው፡፡ (እንገዳውስ ሱጁድን በማብዛት እገዘኝ ) አሉኝ፡፡
ሌላው የባልደረቦች አኩሪ ገጽታ ደግሞ ሰዎችን ከራስ ማስቀደማቸውና ጥብቅነታቸው ነበር፡፡ ባልደረቦች ሌሎችን ከራስ በማስቀደም ይታወቁ ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና)አቡ ሁረይራህ የሚከተለውን ዘግበዋል፡ ‹አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ወደነብያችን ሄደና ያላህ መልክተኛ ሆይ! ከፍኛ ጉዳት ደርሶብኛል አለ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን ወደሚስቶቻቸው መልክት ላኩ፡፡ ነገር ግን ከነሱ ዘንድ ምንም ነገር አልተገኘም፡፡ ያን ጊዜም ነብያችን (ዛሬን የሚያሳድረውና አላህ ምህረት የሚያደርግለት ሰው የለምን?) ሲሉ ጠየቁ፡፡ ከአንሷሮች አንድ ሰው ቆመና የአላህ መልከተኛ ሆይ! እኔ አሳድረዋለሁ አለ፡፡ ወደሚስቱም በሄደ ጊዜ ይህውና ይህ የአላህ

መልተኛ እንግዳ ነው መንም ነገር መቆጠብ እንዳትስቢ አላት፡፡ እሷም በአላህ ይሁንብኝ የህፃናቶች ምግብ እንጂ ሌላ ነገር የለም አለች፡፡ እሱም ልጆቹ እራት በሚጠይቁ ጊዜ አስተኛቸውና ነይ መብራቱንም አጥፊ ዛሬ ሆዳችንን እነጠፍ አላት፡፡ እሷም እንደተባለችው አደረገች፡፡ ያ ሰውየም ማለዳ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በመጣ ጊዜ (አላህ በእገሌና በእገሊት ተግባር ተገረመ) አሉ፡፡ ያን ጊዜ እንድህ የምተለዋ አንቀጽ ወረደች፡፡

﴿وَيُؤْثِرُونَ عَلَى أَنْفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ﴾ .

ትርጉሙም (በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ፡፡) ማለት ነው፡፡
አንሷሮች የነበሩበትን ሌላን ከራስ ማስቀደምና ሙሃጂሮች የታነጹበተን ራስ አክባሪነትን ሲገልጹ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ከአንሷሮች ወገን የነበሩት ሰዕድ ኢብን አልረቢዕ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ብለዋል፡ ‹ከሙሃጂሮች ወገን ለሆኑት አብደራሕማን ኢብን ዓውፍ ገንዘቤን ለማካፈል ሀሳብ ባቀረብኩበት ወቅት በከፍተኛ ክብር ገንዘብህን አላህ ይባርክልህ ገበያችሁን አሳየኝ አሉ፡፡ ነግደውና ከፍተኛ ጥረት አድርገው ከመዲና ከበርቴዎች በመጀመሪያ ከሚጠቀሱት አንደኛው ሆነ፡፡›
ሌላው የባልደረቦች አኩሪ ገጽታ ወደእውነት ተመላሽነታቸው ነበር፡፡ የነብያችን ባልደረቦች እውነትን ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ ከሱም ካጋደሉ ወደሱ ለመመለስ ምንም ዓይነት ትእቢት አያግዳቸውም ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ መስዑድ የተሰኙት አንሷራዊ ባልደረባ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹እኔ አንድ ቀን አገልጋዬን እየመታሁ ሳለ ከኋላ (አቡ መስዑድ ሆይ! አንተ እሱን ከማሸነፍ የበለጠ አላህ አንተን የሚያሸንፍ መሆኑን እወቅ) የሚል ደምጽ ሰማሁ፡፡ ዞር ስል የአላህ መልክትኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ናቸው፡፡ እኔም ወዳውኑ እሱን ለአላህ ስል ነፃ ብየዋለሁ አልሁኝ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አንተ እንድህ ባታደርግ ኖሮ እሳት በገረፍችህ ወይም በነካችህ ነበር) አሉኝ፡፡
ቃልና አደራን ማክበር ሌላው የባልደረቦች እኩሪ ገጽታ ነበር፡፡ ነብያችን በባልደረቦቻቸው መንፈስ ቃልና አደራ ማክበርን አስርጸዋል፡፡ እሱንም አጥብቀው እንዲይዙ ይመክሯቸው ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ አጉልቶ የሚያሳየው የሰይዲና ሙዓዊያና የሩም ቃል ኪዳን ሁኔታ ነው፡፡ ሰይድና ሙዓዊያ ከሩሞች ጋር ቃል ተጋብተው በነበረበት ወቅት የቃል ኪዳኑ ጊዜ እንዳለቀ በደንገት ሊወሯቸው አሰቡ፡፡ በሩሞች ደንበር እንደደረሱም አንድ የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረባ ከኋላ አላህ ታላቅ ነው አላህ ታላቅ ነው ቃልን ማክበር እንጂ ክዳትን ምን አመጣው የሚል ዐረፍተ ነገር ተናገሩ፡፡ ሙዓዊያም አትኩረው ሲመለከቱ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዓምር ኢብን ዓብሳህ ናቸው፡፡ ሙዓዊያም አስጠሯቸውና ስለሁኔታው ጠየቋቸው፡፡ እሳቸውም እኔ የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) (ከሰዎችና ከሱ መካከል ቃል ኪዳን ያለበት ሰው ጊዜው እስከሚያልቅ ወይም በቀጥታ ወደነሱ ቃል ኪዳኑን እስከሚመልስ ደረስ ቁጥሩን አያጥብቅ ወይም አይፍታ) ሲሉ ሰምቻለሁ አሉ፡፡ በዚያን ጊዜም ሙዓዊያ ከዚያ ከሀሳባቸው ተመለሱ፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረት እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የነብያችን ባልደረቦች ይህችን ዓለም በሃይማኖት በማልማት ረገድ መልካም አርአያ ነበሩ፡፡ ከነሱ ለያንዳንዳቸው በግሉ የሚያከናውነው ሥራ ነበረው፡፡ ያን ሥራ ታዲያ በጥራትና በጥንቃቄ ይፈጽመው ነበር፡፡ ከነሱ መካከል ነጋዴ፣ የጦር መሪ፣ የሃይምናኖት ሊቅና ሌሎችም ይካተቱ ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከህዝቦቼ ለህዝቦቼ እጅጉን አዛኙ አቡ በክር ነው፡፡ በአላህ ሃይማኖት ጠንከራው ደግሞ ዑመር ነው፡፡ በዓይናፋርነት ጥልቁም ዑስማን ነው፡፡ የተፈቀዱና እርም የሆኑን ነገሮች ጠንቅቆ የሚያወቀውም ሙዓዝ ኢብን ጀበል ነው፡፡ የአላህን መጽሐፍ ደንቡን ጠብቆ የሚያነበው ደግሞ ኡበይ ነው፡፡ በውርስ ዘርፍ ጥልቅ እውቀት ያለው ዘይድ ኢብን ሳቢት ነው፡፡ ለሁሉም ህዝብ አንድ ታማኝ ሰው አላቸው፡፡ የዚህ ህዝብ ታማኝ አቡ ዑበይዳ ኢብን አልጀራሕ ናቸው፡፡)

የባልደረቦች መልካም ሥራዎች ደጋግ ፍሬዎች ነበሯቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦቻቸውን አጣርተው በሚሰሩት ሥራቸው በማክበር ያነሷቸው ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና)ዑስማን አብን ዓፋን በተቡክ ጦርነት ዝግጂት ጊዜ አንድ ሺህ ዲናር አምጥተው በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጭን ላይ ዘረገፉት፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ከዛሬ በኋላ ዑስማንን የሚሠራው ማንኛውም ሥራ ፈጽሞ ሊጎዳው አይችልም) አሉ፡፡

ሌላው የባልደረቦች አኩሪ ገጽታ ደግሞ የተፈቀዱን ነገሮች በማጣራትና አላህ (ዐ.ወ.) እንደሚቆጣጠራቸው ጠንቅቀው ማወቃቸው ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ከእለታት አንድ ቀን አገልጋያቸው ፈረስ እንዲገዛ ላኩት፡፡ አገልጋዩም በሦስት መቶ ድርሃም አንድ ፈረስ ተስማምቶ ሰዉዬውን ገንዘቡን እንደቀበል ይዞት መጣ፡፡ ጀሪርም ፈረሱን አዩና ፈረስህ ከሦስት መቶ ደርሃም በላይ ያወጣል አሉና በአራት መቶ ድርሀም ትሸጠዋለህ? ሲሉ ጠየቁት እሱም ይህ እንግድህ ያንተ ፈንታ ነው አለ፡፡ አንደገናም ፈረስህ ከዚያ በላይ ያወጣል በአምስት መቶ ድርሀም ትሸጠዋለህ? በማለት ጠየቁት፡፡ በዚህ መልኩ እየጨመሩ ሰምንት መቶ ድርሀም አድርሰው በሱ ገዙት፡፡ ለምን እንድህ አደረገህ ብለው ሰዎች ቢጠይቋቸው ‹እኔ ለሁሉም ሙስሊሞች ምክርን በመለገስ ለአላህ መልክተኛ ቃል ገብቻለሁና ነው› አሉ፡፡

ሁሉም የነብያችን ባልደረቦች ያለባቸውን ግዴታዎች ያውቁና ይፈጽሙ ነበር ወሰናቸውንም በምንም መልኩ አይተላለፉም ነበር፡፡ አቡ በክር አሲዲቅ አንድ ወቅት ዑመር አብንል ኸጣብን ጠቅላይ ቃዲ አድርገው ሾሙ፡፡ አንድም ሰው ክስ ይዞ

ሳይመጣ ሙሉ ዓመት አለፈ፡፡ ያን ጊዜ ዑመር ከቃዲነት ሥራ እንዲያነሷቸው ለአቡ በክር ጠየቁ፡፡ አቡበክርም የቃዲነት ሥራ አድካሚ ስለሆነ ነው፡፡ ከሥራው መነሳት የፈለግሀው? በማለት ጠየቋቸው፡፡ ዑመርም አይደለም የአላህ መልክተኛ ኸሊፋ ሆይ! ነገር ግን እኔ ሁለም አባላቱ ያለውን መብቱን አውቆ ከዚያ በላይ የማይጠይቅ እንድሁም ያለበትን ግዴታ አውቆ የሚፈጽም በሆነ ህብረተሰብ መካከል የማላስፈልግ በመሆኔ ነው አሉና፡ ከነሱ ለያንዳናዳቸው ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ የሚወድ፣ አንዳቸው ሲሰውር የሚፈለጉት፣ በተማመም ጊዜ የሚጠይቁት፣ በደሀየም ጊዜ የሚያግዙት፣ እርዳታ በሚያስፈልገውም ጊዜ የሚረዱት፣ መከራ በደረሰበትም ጊዜ የሚያጽናኑት እንድሁም ሃይማኖታቸው ምክርን መለገስ፣ ጠባያቸውም በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል በመሆኑ በምን ይነታረካሉ በምንስ ይካሳሉ አሉ፡፡
እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት ወደነብያችን ባልደረቦች መልካም ጠባይ መመለስ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ የእዝነት፣ የመቻቻል፣ የሰብእነትና የሰላም ሃይማኖት የሆነውን የእስልምና ሃይማኖት ትክክለኛ ባሕርይን የማጉላት ሀላፊነትም አለብን፡፡

ጌታችን ሆይ! አገራችንና ህዝባችን ጠብቅልን ሀገራችን የሲሳይና የቸርነት አገር አድርግልን አሜን፡፡

(12)

## እስልምና ማለት ሥራና ስርኣት ነው
## «ከተከታዮች ሕይወት ለናሙና ያህል»

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

وَ{الَّذِينَ جَاءُوا مِنْ بَعْدِهِمْ يَقُولُونَ رَبَّنَا اغْفِرْ لَنَا وَلِإِخْوَانِنَا الَّذِينَ سَبَقُونَا بِالْإِيمَانِ وَلَا تَجْعَلْ فِي قُلُوبِنَا غِلًّا لِلَّذِينَ آمَنُوا رَبَّنَا إِنَّكَ رَءُوفٌ رَحِيمٌ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያም ከበኋላቸው የመጡት «ጌታችን ሆይ! ለእኛም ለእነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምሕረት አድርግ፡፡ በልቦቻችንም ውስጥ ለእነዚያ ለአመኑት (ሰዎች) ጥላቻን አታድርግ፡፡ ጌታችን ሆይ! አንተ ርኅሩህ አዛኝ ነህና» ይላሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ሱ.ወ.) ለሃይማኖቱ የሚሠሩና ለሃይማኖቱና ለመልእክቱ በታማኝነት የሚያገለግሉ ባሪያዎችን መርጧል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከዚህ ህዝብ እጅግ ተመራጭ የሆኑት (ከነርሱ አላህ ይውደድና) ባልደረቦቻቸው ከዚያም ተከታዮቻቸውና የነሱ ተከታዮች መሆናቸውን ነግረውናል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን መስዑድ የተባሉት በልደረባ ነብያችን እንደህ ማለታቸውን አውርተዋል፡ (ከሰዎች ደጎቹ እኔ ባለሁበት ክፍለ ዘመን ያሉት ናቸው ከዚያም ከነሱ የሚቀጥሉት ከዚያም ከነሱ ቀጥሎ የሚመጠት... ናቸው) ባልደረቦችና ተከታዮቻቸው ደግ የተባሉት ምርጥ ሰዎች ሲሆኑ የአጋናኞችን ማጉደፍን፣ የአበላሾችን ማዛባትና ያለውቀት ተንታኞችን አንድምታ እያጣሩ የእውቀትን አደራ ወደኛ ያደረሱ በመሆናቸው ታላቁ አላህ እንድህ ሲል አሞግሷቸዋል፡

**{وَالسَّابِقُونَ لأَوَّلُونَ مِنَ الْمُهَاجِرِينَ وَالأنصَار وَالَّذِينَ اتَّبَعُوهُم بِإِحْسَانٍ رَّضِيَ اللّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا عَنْهُ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي تَحْتَهَا الأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ذَلِكَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ}**

ትርጉሙም (ከስደተኞቹና ከረዳቶቹም ሲኾኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው አላህ ከእነሱ ወደ፟ል ከእርሱም ወደዋል፡፡ በሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲኾኑ ለእነርሱ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ ዕድል ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
ተካታዮች የምንላቸው ከባልደረቦች ትውልድ ቀጥሎ ባለው ትውልድ የሚካተቱ በመሆኑ በዘመን ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እጅግ የቀረቡ ናቸው፡፡ የተከታዮች ተከታይ ደግሞ (ከነርሱ አላህ ይወደድና) ከተከታዮች ትውልድ የሚቀጥሉት ናቸው፡፡
ኢማሙ አል ቡሶይሪ የተባሉት የመንፈሳዊ ግጥም ደራሲ እንድህ በማለታቸው ይደነቃሉ፡
ሁላቸውም ከአላህ መልክተኛ እውቀት የቀሰሙ ናቸው፡፡ ከፊሉ ከባህሩ የጨለፈ ሲሆን ከፊሉ ደግሞ ከዝናባቸው የተጎነጨ ነው፡፡
ተከታዮች (ከነርሱ አላህ ይውደድና) የነብያችን ባልደረቦች ባልደረባ ሆነው ከነሱ በተለያዩ ዘርፎች ትምህርት የቀሰሙና ባልደረቦችም በትሩፋትና በጥልቅ እውቀታቸው ምስክርነት የሰጡባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዑመር ሰዒድ ኢብን አል ሙሰየብ ተባሉት የባልደረቦች ተከታይ ማንነት ሲመሰክሩ እንድህ ብለዋል፡ ‹እሱ በአላህ ይሁንብኝ ከሙፍቲዎች -በእስልምና ህግ በቀጥታ ብያኔ የሚሰጡ- አንዱ ነው፡፡› እንድሁም ‹ሰዒድ ኢብን ሙሰየብን ጠይቁ እሱ ከፃዲቃን ጋር

ይቀመጥ ነበር ይሉ እንደነበር ታውቋል፡፡ ሰዒድ ኢብን ሙሰየብ ባልደረቦች በሕይወት እያሉ በእስልምና ህግጋት ብያኔ ይሰጡ እንደነበር ይታወቃል፡፡
ዐጣእ ኢብን አቢ ረባሕ የተባሉት ተከታይም መካ ውስጥ አብደላህ ኢብን አባስ የተባሉት ሊቅ ከሞቱ በኋላ በህግጋት ብያኔ ለመስጠት ተቀምጠው በነበረበት ወቅት ኢብን ዑመር ከመዲና ሲመጡ ሰዎች ስለተለያዩ ነገሮች ሲጠይቋቸው እናንተ የመካ ሰዎች ከናንተ መካከል ዐጣእ ኢብን አቢ ረባሕ እያለ ለኔ እንደት ጥያቄ ትሰበስባላችሁ ይሉ ነበር፡፡
ተከታዮች ለአላህ መልክተኛ የነበራቸው ፍቅር እውነተኛና ጥልቅ ነበር፡፡ ሐሰን ኢልበስሪ የተባሉት ተከታይ ስለግንዱና ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሮሮ ማሰማቱን ሲያወሩ አለቀሱና እናንተ የአላህ ባሮች ሆይ! አንጨቱ ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ናፍቆ ከሳቸው በመለየቱ ማዘኑን ገለጸ፡፡ እናንተ ከሱ ይልቅ በዚህ ተግባር ተቀዳሚ መሆን ነበረባችሁ፡፡ እርሳቸውን ለመገናኘት መናፈቅ ይጠበቅባችኋል ብለዋል፡፡
ኢማሙ ማሊክ አንድ ቀን መቼ ነው ከአዩብ አሰኽተያኒ የሰማሁት ተብለው በተጠየቁ ጊዜ እሳቸው ሁለትጊዜ ሐጅ ሲያደርጉ እኔም ሐጅ አድርጊያለሁ በዚያን ወቅት እመለከታቸው ነበር እንጂ መስማት ግን አልችለም ነበር፡፡ ይሁንና የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ስም ሲያነሱ እዝነት እስከሚሰማኝ በጣም ያለቅሱ ነበር፡፡
የነብያችን ባልደረቦች ተከታዮች ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) እጅግ በጣም ከማክበራቸው የተነሳ የነብዩን ቃል በመልካም ሁኔታና በተሻለ ገጽታ ሆነው እንጂ አያወሩም ነበር፡፡ ተከታዮቻቸውም ይህን መሰል አክብሮታቸውን ሙሉ በሙሉ ቀስመው ተግባራዊም አደርገውታል፡፡ አቡ ሰለማህ አል ኹዛዒይ የተባሉት ሊቅ ኢማሙ ማሊክ ኢብን አነስ የነብያችንን(ሶ.ዐ.ወ.) ሐዲስ ለሰዎች ለማስተማር ወደትምህርት ቦታ መውጣት ከፈለጉ ቀድመው ለስግደት የሚያደርጉትን ዓይነት ውዱ ያደርጉ፣ ከዚያም ምርጥ ልብሳቸውን ይጎናጸፉና ጺማቸውን ያበጥሩ ነበር፡፡ ለምን እንድህ እንደሚያደርጉ በተጠየቁ ጊዜ የነብያችንን ሓዲስ እያከበርኩበት ነው ሲሉ መልሰዋል በማለት አውርተዋል፡፡
ከባልደረቦች ተከታዮች ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለነሱ ያሩላቸው የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡ ከነሱም መካከል ኡወይስ አልቀረኒ የተባሉት ለናታቸው ታዛዥ በመሆናቸው የተዋቁት አንደኛው ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለኚህ ሰውዬ ለባልደረቦቻቸው ሲያወሩላቸው ጸሎቱ አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ገልጸውላቸዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አል ኸጣብ እንድህ ብለዋል፡ ‹እኔ የአላህ መልክተኛ እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (ከተከታዮች እጅግ ደጉ ኡወይስ የሚባለው ሰውዬ ነው፡፡ የሚታዘዛት እናት አለችው፡፡ በሱም የቆዳ በሽታ አለበት ከአላህ ዘንድ ምህረት እንዲለምንላችሁ ጠይቁት፡፡) የየመን ሰዎች በመጡ ጊዜ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልጣብ ሲያፈላልጉ ከቆዩ በኋላ ተገናኙት፡፡ ያን ጊዜም ከአላህ ዘንድ ምህረትን ለምንለኝ አሉት፡፡ እሱም እርሰዎ ነዎት ይልቅ ከአላህ ዘንድ ምህረት ሊለምኑልኝ የሚገባው እርሰዎ የአላህ መልክተኛ ባልደረባ ነዎት አለ፡፡ እሳቸውም ከአላህ ዘንድ ምህረት እስከለመነላቸው ጊዜ ድረስ አልተውትም ነበር፡፡
ተከታዮች ሃይማኖቱን በትክክለኛ መልኩ ከነብያችን ባልደረቦች ተምረዋል፡፡ ከተከታዮች ታላቁ የሆኑት ሐሰን አል በስሪ እርሰዎ ምእምን ነዎትን? ተብለው

በተጠየቁ ጊዜ እንድህ ብለዋል፡ ‹እምነት ሲባል ሁለት ዓይነት ነው፡፡ የምትጠይቀኝ በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በጀነት፣ ሙቶ በመነሳትና በሒሳብ ስለማመን ከሆነ አዎ እኔ ምእምን ነኝ፡፡ ነገር ግን የምትጠይቀኝ እንድህ ስለሚለው የአላህ ቃል ከሆነ፡

**{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَاناً وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ * الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلاةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنْفِقُونَ *أُولَئِكَ هُمُ الْمُؤْمِنُونَ حَقّاً}**

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በእውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው፡፡) ማለት ነው በአላህ ይሁንብኝ እኔ ከነሱ ውስጥ አንዱ ልሁን አልሁን አላውቅም አሉ፡፡› አልበይሃቂ የተባሉት ሊቅ ስለዚህ ስለ ኢማሙ ማሊክ አባባል ማብራሪያ ሲሰጡ ‹ስለመሰረት እምነት ምንም ያለማወላወልና ያለመዳዳት መልሱ ሰጡ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.)

**{ لَهُمْ دَرَجَاتٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ وَمَغْفِرَةٌ وَرِزْقٌ كَرِيمٌ} .**

ትርጉሙም (ለእነሱ በጌታቸው ዘንድ ደረጃዎች ምህረትና የከበረ ሲሳይም አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

በማለት ለባለቤቶቹ ጀነትን ቃል ሰለገባለት ስለምሉእነቱ ነው ማረጋጥን የፈሩት ብለዋል፡፡

ተከታዮች የሃይማኖቱን ገርነት ከባልደረቦች የተማሩት ሲሆን በእለት ተእለት ኑሯቸው ተግባራዊ አድርገውታል፡፡ ሱፍያን አሰውሪ የተባሉት ተከታይ እንድህ ይላሉ፡ ከኛ ዘንድ እውቀት ማለት በእምነት የታነጸ የአላህ ፈቃድ ነው፡፡ ማጥበቅንማ ማነም ሰው ይችልበታል፡፡› አልአዝረቅ ኢብን ቀይስ የተባሉት ሊቅ ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን አህዋዝ ውስጥ በአንድ ውሃው በደረቀ ወንዝ ተቀምጠን እያለ አቡ በርዛህ አል አስለሚ የተባለ ሰውዬ መጣና ፈረሱን አቁሞ ስግደት ጀመረ፡፡ ፈረሷም መራቅ በጀመረች ጊዜ ስግደቱን አቋርጦ ተከተላትና መልሷት ስገደቱን እንደገና ሰገደ፡፡ ከኛ መካከል ሰዎች የሚያከብሩት ሰውዬ እዩ ይህን ሼህ ለፈረስ ብሎ ስግደቱን ተወ ሲል ተናገረ፡፡ እሱም ወደኛ መጣና ከአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ከተለየሁበት ጊዜ ጀምሮ አንድም ሰው እንደዚህ አልገላመጠኝም አለና ቤቴ ሩቅ ነው ፈረሷን ትቼ ስግደቴን ብቀጥል ኖሮ ፈረሷ ታመልጠኝና ወደቤተሰቦቼ እስከማታም መመለስ አልችልም ነበር በማለት አብራራ፡፡ ይህን የተማረው ከሁለት ነገሮች እንዲመርጡ ሲጠየቁ ኃጢአት እስካልሆነ ድረስ ቀላሉን እንጂ ከማይመርጡት ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አግራሩ አታጨናንቁ አብስሩ አታደንብሩ፡፡) ይላሉ፡፡ እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (ማግራት በአንድ ነገር አይደረግም የሚያውብው ቢሆን እንጂ ከአንድም ነገር አይነሳም የሚያነውረው ቢሆን እንጂ፡፡)

ተከታዮች እዝነትን፣ መደጋገፍንና የሌሎችን ስሜት መገንዘብን በሕይወታቸው ተግብረውታል፡፡ እነሆ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና)የዓሊይ የተባሉት የዓሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ ልጅ የሑሰይን ልጅ አንድም ሰው ሳያውቅ በርካታ ቤተሰቦችን ያግዙ ነበር፡፡ በሞቱ ጊዜ ሲያጥቧቸውም ለምስኪኖችና ባል ለሞተባቸው እርዳታ ሲያደርሱ የሚሸከሙት ገመድ ምልክት ተገኘ፡፡ ያን ጊዜም ለነዚያ ሰዎች በሌሊት ምግብ እየተሸከሙ ያመጡ የነበሩት እርሳቸው እንደነበር ታወቀ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሰይዲና ዓሊ የሑሴን ልጅ መዲና ውስጥ አንድ መቶ ቤተሰብ ይረዱ እንደነበር አውርተዋል፡፡
ተተኪዎች እዝነትና መደጋገፍን በሙስሊሞች ብቻ የጠወሰነ ሳያደረጉ ሙስሊሞችና የሌላ እምነት ተከታዮችንም ያከተተ አድርገውት ነበር፡፡
እነሆ ሰይዲና ዐመር ኢብን አብደል ዓዚዝ በዝራ ከተማ ይገኙ ለነበሩ ወኪላቸው ደብዳቤ ሲጽፉ እንደዚህ ብለዋል፡ ‹ካንተ ዘንድ የሌላ እምነት ተከታይ ከሆኑት እድሜው የገፋውን፣ ኃይሉ የደከመውንና ሥራውን ያጣ የሆነውን አጣራና ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ገንዘብ ወስደህ የሚያስፈልገውን አድርግለት፡፡› ሰይድና ዑመር ኢብን ዐብደል ዓዚዝ ይህን ያደረጉት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብን አርኣያ በማድረግ ነው፡፡ ሰይድና ዑመር አንድ ቀን አንድ ከመጽሐፍ ባለቤቶች የሆነ አረጋዊ ከሰዎች እርዳታ ሲጠይቅ ባዩ ጊዜ ‹በአላህ ይሁንብኝ ይህን ሰውዬ ወጣትነቱን በልተን በሽምግልናው የምንጥለው ከሆነ መብቱን አላስከበርነም አሉና ከግምጃ ቤት የሚበቃው ገንዘብ እንድደረግለት ትእዛዝ አስተላለፉ፡፡
ኻሊድ ኢብን አል ወሊድ ደግሞ ከሒራ ሰዎች ጋር ባደረጉት የሰላም እርቅ ‹እኔ ከነሱ ከሥራ ለደከመ ሽማግሌ፣ እንከን ለደረሰበት ሰው ወይም ነብረቱን አጥቶ ለደሀዬ ሰው ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ጡሬታ እንደደረግለት ወስኛለሁ...) የሚል ጽሁፍ አስፍረዋል፡፡ ሁላቸውም ታድያ ይህን ሁሉ ያደረጉት ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.)አርኣያ በማድረግና ትክክለኛውን ሃይማኖትም በመከተል ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡
**{لا ينهاكم اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّين وَلَمْ يُخْرِجُوكُمْ مِنْ دِيَارِكُمْ أَنْ تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ} .**

ትርጉሙም (ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለከላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህ የተከታዮች እዝነት በሰው ልጅም ብቻ አልተወሰነም ነበር፡፡ ይልቁንም እንሰሳትን አእዋፍንና ሌሎችንም ነገሮች አካቷል፡፡ ዑመር ኢብን አብደል ዓዚዝ ግብጽ ለነበረው ወኪላቸው ለግመሉ ርህሩህ እንዲሆን ሲመክሩት እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጽፈዋል፡ ‹እኔ ግብጽ ውስጥ አንድ ሺህ ርጥል የሚሸከም የጭነት ግመል መኖሩን ሰዎች ነግረውኛል ይህ ደብዳቤዬ ከደረሰህ ጊዜ ጀምሮ አንድም ግመል ከስደስት መቶ ርጥል በላይ እንዳይጫን፣ ለግመሎችም ርህራሄ ይደረገላቸው፣ እታራክሷቸው እንድሁም ያለምክኒያት አይመቱ...› ዑመር ኢብን አብደልዓዚዝ ይህን ያደረጉት የአላህን መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) በመከተል ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድን ባለ ግመል ሲመክሩ

እንድህ ብለውታል፡ (በዚህ አላህ (ዐ.ወ.) ለአንተ አገልጋይ እንዲሆን በገራልህ ከብት አላህን አትፈራምን? እሱ የምታስረበውና የምታደከመው መሆነህን ለእኔ አቤቱታ አቅርቦልኛል፡፡) አሉት፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረተን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ተከታዮች ከሚለዩባቸው ነገሮች እጅግ ታላቁ ለሰዎች የሚያሳዩት የመቻቻልና የርህራሄ ገጽታ ነበር፡፡ ተካታዮች ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት እጅጉን ገራገርና ለዘበተኞችም ነበሩ፡፡ ቀታዳ የተባሉት ተከታይ እንድህ ይላሉ፡ ‹አንድ ቀን ከሐሰን አል በስሪ ቤት ስንገባ ተኝተው ከራስጊያቸውም የዳቦ ቅርጫት ተቀምጦ አገኘን፡፡ ቅርጫቱን ሳብ አድርገን ስንመለከት ውስጡ ዳቦና ፍራፍሬ አገኘን፡፡ መብላት እንደጀመርን ነቁና ሁኔታችንን ባዩ ጊዜ አጅጉን ተደሰቱ፡፡ ፈገግ አሉና የምተከተለዋን አንጽ አነበቡ፡

{أَوْ صَدِيقِكُمْ لَيْسَ عَلَيْكُمْ جُنَاحٌ}

ትርጉሙም ( ወይም ከወዳጃችሁ ቤት (ብትበሉ) ኀጢአት የለባችሁም፡፡) ማለት ነው (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር ኢብን ሓዚም እንድህ ብለዋል፡ አንድ ቀን ከሐሰን አል በስሪ ዘንድ እያለን እኩለ ቀን ሆነ ልጃቸው በቃችሁ ኧረ ለሼሁችሁ አታዝኑም አንዴ በጣም ችግር ፈጥራችሁብቸዋልኮ፡፡ እስካሁን ምንም ዓይነት መግብም ሆነ መጠጥ አልቀመሱም አለ፡፡ እሳቸውም ተዋቸው በአላህ ይሁንብኝ ከነሱ የበለጠ የዓይኔ መረፊያ የሚሆን ነገር የለም አሉ፡፡
ይህም አንድ ሰው ለሰዎች ብሎ ራስን መዘንጋትንና የእውቀትን ደረጃና ክብሩን ማወቁን እንድሁም በመንፈስ ውስጥ ለአላህ ሃይማኖት ያለውን ከፍተኛ ደረጃ በግልጽ ያሳያል፡፡ እሱም በቂ እውቀት ሳይኖረው የአላህን ሃይማኖት አስተምራለሁ ብሎ ተነስቶ ጠሞ ሰዎችን ለሚያጠም ደፋር ሰው ታላቅ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ እውቀትን ከባሮች መንጭቆ በመወሰድ አይደለም የሚያነሳው፡፡ ነገር ግን እውቀትን የሚያነሳው ምሁራንን በሚያነሳበት ወቅት ነው፡፡ በምድር ላይ አንድም እውቀት ያለው ሰው ሲጠፉ ሰዎች ደንቆሮዎችን መሪ አድርገው ይይዙና ሲጠየቁ ያለ እውቀት ብያኔ -ፈትዋ- ይሰጣሉ በዚህም ተግባራቸው ራሳቸው ጠመው ሰዎችንም ያጠማሉ፡፡)

ተከታዮች ከነሱ በኋላ ለመጣው ትውልድ አርአያ ነበሩ፡፡ የተከታዮች ተከታይ የሆኑት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢማሙ ማሊክ ኢብን አነስ «አቡ ጀእፈር አል መንሱር» የተባሉት ሀገረ ገዥ ‹ሙወጠእ› የተባለውን መጽሐፋቸውን በኮፒ አባዝተው ለያንዳንዱ ሙስሊም ከተማ ኮፒ ልከው እሱን ብቻ መመሪያ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ለማስተላለፍ ማሰባቸውን ነገሯቸው፡፡ ያን ጊዜ ኢማሙ ማሊክ የምእምናን አዛዥ ሆይ ይተው እንዲህ አያደርጉ፡፡፡ ምክኒያቱም ሰዎች የተለያዩ ወሬዎች ደርሰዋቸዋል፣ በርከታ የነብያችን ሐዲሶችም ተወርተውላቸዋል፡፡ ሁሉም ማህበረሰብ ቀድሞ የደረሰለትን ይዟል በሱም እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ካሉበት እንደሚለሱ ማስገደድ በነሱ ላይ ጫና ማሳደርና ማጥበቅ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ሰዎች ባሉበት እንዲቆዩና በመረጡት እንደጸኑ መተዉ በጣም የተሸለ ነው አሉ፡፡ አቡ ጀዕፈርም በአላህ ይሁንብኝ እሺ ብትሉኝ ኖሮ ይህን ትእዛዝ ባስተላለፍኩኝ ነበር አሉ፡፡

እጅግ ደንቅ ከተባለው ራስን ዝቅ የማድረግ ገጽታ ኢማሙ አሻፊዒ ከተማሪያቸው ጋር በደረጉት ውይይት የተንጸባረቀው እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ኢማሙ አሻፊዒ ‹ዩኑስ ኢብን አብደል ዓእላ ከተባለው ተመሪያቸው ጋር በአንድ ጉዳይ የተለያየ አቋም በያዙ ጊዜ ዩኑስ ተቆጥቶ የትምህርት ገበታውን አቋርጦ ሄደ፡፡ ምሽት ላይ ዩኑስ ቤቱ ሲንኳኳ ሰማ፡፡ ማነው ሲልም ጊዜ ሙሐመድ ኢብን ኢድሪስ ነኝ አሉ፡፡ ዩኑስ በዚህ ስም የማውቀው ሰው አላገኘሁም አሉ፡፡ በሩን ሰከፍት ኢማሙ አሻፊዒ ናቸው፡፡ ነገሩ አንግዳ ሆነብኝ አሉ፡፡ በመቀጠለም እንድህ አሉኝ አሉ፡ ‹ዩኑስ ሆይ! በሙቶዎት የሚቆጠሩ ነገሮች እያሰተሳሰሩን ሳለ አንድ ጉዳይ እንዴት ይለየናል፡፡ ዩኑስ ሆይ! በሁሉም አለመግባባት አሸናፊ ለመሆን አትሞክር፡፡ በአንዳንድ ወቅት በሁኔታ ከመሸነፍ ይልቅ ቀልብን መሳብ ይመረጣል፡፡ ዩኑስ ሆይ! ገንበተህ የተሻገርክበትን ድልድይ አታፍረስ፡፡ ምናልባትም አንድ ቀን ለመመለስ ብትፈልግ ይጥቅመሃልና፡፡ ስህተትን ምንጊዜም መጥላት ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ተሳሳችን መጥላት የለብህም፡፡ ወንጀልን ከልብህ ጥላ፡፡ ነገርን ግን የወንጀለኛውን ስህተት አለፍ እዘንለትም፡፡ ዩኑስ ሆይ! ቃልን መንቀፍ ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ቃሉን የተናገረውን ሰው ማክበር ይጠበቅብሃል፡፡ የኛ አላማ በሽታን ማስወገድ አንጅ በሽተኛውን ማውደም አለመሆኑን ምንጊዜም አትዘንጋ፡፡›

ኢማሙ ሻፊዒ አንድህ ይላሉ፡

ከነሱ ወገን ባልሆንም ጻዲቃንን አወዳለሁ፡፡ ምናልባትም ከነሱ የሚታደገኝ አገኝ ይሆናልና፡፡

በቁሳቁሳችን ተመሳሳይ ብንሆንም ንግዱ ወንጀሎችን መዛወር የሆነን ሰው እጠላለሁ፡፡ የተከበሩ ሊቃውንቶቻችንም በዚህ ዓይነቱ ጎዳና ነበር የሚጓዙት፡፡ በመሆኑም ትክክለኛውን የአላህን ሃይማኖት አደራ በማስተላለፍ፣ በጥበብና በመልካም ተግሳጽ ሰዎችን በመመከር አርአያ ሁነውናል፡፡

ጌታችን ሆይ ቃልን ሰምተው መልካሙን ከሚከተሉት አድርገን አነዚያ አላህ ያቀናቸው አነዚያ ልበኞቹ ናቸውና፡፡ አሜን፡፡

# (13)

## ከእስልምና ህግ ታላቅነት ገጽታዎች አንዱ
## መቻቻልና ገርነት ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ }

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገበው፡፡ ትርጉሙም (አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (እኔ የተላክሁት ገራገር በሆነው ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡፡**

የእስልምና ህግጋት ታላቅነት ገጽታዎች ቁጥር ስፍ የሌላቸው መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ የእስምና እምነት ከተለየበት ታላቅና ብሩህ ገጽታም ቃላቱ ባዘሉት ታላቅ ፍች የመቻቻልና ገርነት ገጽታው ነው፡፡ በእምነቱ ችግርም ሆነ አስጨናቂ ነገር እንዲሁም የማጥበቅም ሆነ የማከረር ገጽታ አይታይበትም፡፡ እዚህ ላይ በእምነቱ ተከታይነት የሚካተቱና በሃይማኖት ጥንቁቅ ለመሆን ማጥበቅን ግድ እንደሚል የሚገምቱ አንዳንድ አጥባቂዎች ማከረር የእምነቱ ጉድለት ሊሆን እንደማይገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የነዚህ ወገኖች አመለካከት ደንብን መጠበቅና ጥንቁቀነት በሚል ስያሜ በጸንፈኝነት ጎዳና በዙዎችን እያግበሰበ የሚወስድ በር በህዝቡ ዘንድ በሰፊው የከፈተ ከመሆኑም ባሻገር ጸንፈኝነት በጣም ያጠበቀ እውነተኛ ምእምንና ፈሪሀ አላህ ነው በማለት በዙዎቹ የሚፎካከሩበት ሰፊ መደረረክ ሆኗል፡፡

ይህ ተግባራቸው ታድያ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ስለእምነቱ ታላቅነት፣ ስለአዘለው የመቻቻልና የገራገርነት ገጽታ ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينِ مِنْ حَرَجٍ مِّلَّةَ أَبِيكُمْ إِبْرَاهِيمَ هُوَ سَمَّاكُمُ الْمُسْلِمِينَ مِن قَبْلُ وَفِي هَذَا لِيَكُونَ الرَّسُولُ شَهِيدًا عَلَيْكُمْ وَتَكُونُوا شُهَدَاءَ عَلَى النَّاسِ}

ትርጉሙም (በናንተም በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡ የአባታችሁን የኢብራሂምን ሃይማኖት ተከተሉ፡፡ እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል፡፡ በዚህም (ቁርአን) መልክተኛው በናንተ ላይ መስካሪ እንዲሆን እናንተም በሰዎች ላይ መስካሪዎች እንድትሆኑ (ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል)፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ (ሃይመኖት ገር ነው፡፡ አንድም ሰው ሃይማኖትን ትግል አይገጥምም የሚያሸንፈው ቢሆን እንጅ፡፡ ትክክለኛዎች ሁኑ፡፡ (ካልቻላችሁ) ወደትክክለኛነት የተቃረባችሁ ሁኑ፡፡ ማለዳ፣ ወደማታ ላይና በጥቂቱ ሌሊት መልከም ሥራን ሥሩ፡፡ በነዚህ ጊዚያት ተገቢውን ተግባር ማከናወን ይቀላልና፡፡) ሱፍያን አሰውሪ የተባሉት ሊቅ እንደህ በማለታቸወው እጅጉን ይደነቃሉ፡ ‹ከኛ ዘንድ እውቀት የምንለው በአመኔታ የተሰጠንን ፈቃድ መጠቀማችንን ነው፡፡ ማከረርንማ ማንም ሰው ይችልበታል፡፡›

በእስልምና ህግ መቻቻል በምላስ የምንናገር ቃል ወይም የምናነግበው መፈክር ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ የሕይወት ስርአትና አላህ (ሱ.ወ.) ከባሮቹ ጋር የተዋዋለበትና ከመካከላቸውም በሱ እንዲዋዋሉ ትእዛዝ የሰጠበት መርህ ነው፡፡ አላህ (ኢ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

{لَا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا}

ትርጉሙም (አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ}

ትርጉሙም ((አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡) ማለት ነው፡፡

አሁንም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{يُرِيدُ اللَّهُ أَنْ يُخَفِّفَ عَنْكُمْ وَخُلِقَ الْإِنْسَانُ ضَعِيفًا}

ትርጉሙም (አላህ ከናንተ ሊያቀልላችሁ ይሻል፡፡ ሰውም ደካማ ሆኖ ተፈጠረ፡፡) ማለት ነው፡፡

በአላህ መጽሐፍ ለሁሉም ባሮቹ የተስፋን፣ የምህረትንና የአዝነትን በር በመክፈት ሰፊ ተስፋ በሚጣልባት አንቀጽም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

{قُلْ يَا عِبَادِيَ الَّذِينَ أَسْرَفُوا عَلَى أَنْفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا مِنْ رَحْمَةِ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ جَمِيعًا إِنَّهُ هُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ}

ትርጉሙም (በላቸው እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፡፡ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና፡፡ እንሆ አርሱ መሃሪው አዛኙ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡

{ وَرَبُّكَ الْغَفُورُ ذُو الرَّحْمَةِ}

ትርጉሙም (ጌታህ መሃሪው የእዝነት ባለቤት ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡
{إِلَّا الَّذِينَ تَابُوا وَأَصْلَحُوا وَبَيَّنُوا فَأُولَئِكَ أَتُوبُ عَلَيْهِمْ وَأَنَا التَّوَّابُ الرَّحِيمُ. }

ትርጉሙም (እነዚያ (ከመደበቅ) የተጸጸቱና (ስራቸውን) ያሳመሩ (የደበቁትን) የገለጹም ብቻ ሲቀሩ፡፡ እነዚያም በነሱ ላይ (ጸጸታቸውን) እቀበላለሁ፡፡ እኔም ጸጸትን በጣም ተቀባይ አዛኙ ነኝ፡፡) ማለት ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (አላህ (ሱ.ወ.)ፍጥረታትን በፈጠረበት ጊዜ እሱ ዘንድ ከዙፋኑ በላይ እዘነቴ ቁጣዬን ይቀድማል የሚል ቃል ጻፈ፡፡) አለህ (ሱ.ወ.) በተቀደሰ ሓዲስ እንዲህ ይላል፡ (ያድም ልጅ ሆይ! አንተ በጸለይከኝና ተስፋ በጣልክብኝ ጊዜ አንተ የፈጸምከውን ሁሉ ኃጢአት ከምንም ሳልቆጥር ምህረት አድርግልሃለሁ፡፡ ያድም ልጅ ሆይ! ኃጢአትህ ሰማይ የነካ ከሆነ በኋላ ምህረት ብትጠይቀኝ ብዛቱን ከምንም ሳልቆጥር ምህረት አደርግልሃልሁ፡፡ ያድም ልጅ ሆይ! አንተ በምድር ሙሉ የሚሆን ኃጢአት ተሸክመህ በኔ ማነንም ሳታጋራ በትገናኘኝ በምድር ሙሉ ምህረት አዘጋጅቼ እጠብቅሃለሁ፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) በተከበረው መጽሐፉ በበርካታ ቦታዎች ባሮቹ ምህረት እንዲያደርጉና ነገሮችን በትእግስት እንዲያሳልፉ አዟል፡፡ እንዲህም ይላል፡
{ خُذِ الْعَفْوَ وَأْمُرْ بِالْعُرْفِ وَأَعْرِضْ عَنِ الْجَاهِلِينَ}

ትርጉሙም (ገርን ጠባይ ያዝ፡፡ በመልካምም እዘዝ፡፡ ባለጌዎችንም ተዋቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
እንድህም እንድህ ይላል፡
{ وَلَا تَسْتَوِي الْحَسَنَةُ وَلَا السَّيِّئَةُ ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ كَأَنَّهُ وَلِيٌّ حَمِيمٌ وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا الَّذِينَ صَبَرُوا وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٍ}

ትርጉሙም (መልካሚቱና ክፉይቱም (ጠባይ) አይተካከሉም፡፡ በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍተር፡፡ ያን ጊዜ ያ ባንተና በርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደአዛኝ ዘመድ ይሆናል፡፡) ማለት ነው እንድህም ይላል፡
{ وَلْيَعْفُوا وَلْيَصْفَحُوا أَلَا تُحِبُّونَ أَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ. }

ትርጉሙም (ይቅርታም ያድርጉ (ጥፋተኞችን) ይለፉም፡፡ አላህ ለናንተ ሊምር አትወዱምን? አላህም መሃሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
የነብያችንን (ሶ.አ.ወ.) የሕይወት ታሪክ የሚከታተል ሰው እሳቸው በመቻቻልና ነገሮችን በማቃለል ልህዝቦቻቸው ብሎም ለሰው ልጅ ሁሉ ምን ያማሩ አርአያ እንደነበሩ በግልጽ ሊገነዘብ የሚችል መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ይህን ጉዳይ ሲገልጹ

እናታችን አዒሻ እንድህ ብለዋል፡ (የአላህ መልክተኛ ከሁለት ነገሮች መካከል እንዲመርጡ ተጠይቀው አያቁም ወንጅል የሌለበት እስከ ሆነ ድረስ ቀለል ያለውን የመረጡ ቢሆን እንጅ፡፡ ወንጅል ከሆነ ግን ከሰዎች የበለጠ ከሱ በጣም ይርቁ ነበር፡፡ የአለህ መልክተኛ ለራሳቸው አንድም ቀን በቀል ፈጽመው አያውቁም፡፡ የአላህ ወሰኖች የሚደፈሩ ሲሆን እንጅ፡፡ ያን ጊዜ ለአላህ ወሰኖች ክብር ይበቀላሉ፡፡)
እዚህ ላይ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሕይወት ታሪክ ወደ አላህ (አ.ወ.)እምነት በብልሃትና በመልካም ግሳጼ ጥሪ ሲያደርጉ በነበረበት ወቅት ስለነበሩ የነብያችን ሶ.ዐ.ወ.) አቋሞች አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን ከነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ዘንድ በነበርኩበት ወቅት አንድ ሰውየ መጠና እንድህ አለ፡፡ እኔ ቅጣት የሚያሰከትል ወንጅል ፍጽሚያለሁና ቅጣቱን ፈጽሙብኝ አለ፡፡ ምን ዓይነት ወንጀል እንደፈጸ አልጠየቁትም፡፡ ስግደት ሣዓት ደረሰና ከነብያችን ጋር ሰገደ፡፡ ሶላቱን ከጨረሱ በኋላ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቀረበና የአላህ ምልክተኛ ሆይ! እኔ ቅጥት የሚያስከትል ወንጀል ፈጽሚያለሁና የአላህን ትእዛዝ ይፈጽሙብኝ አለ፡፡ አሳቸውም (እኛ ጋር ሰግደሃል አይደለም እንዴ? አሉት፡፡ አሱም አዎን አለ፡፡ ያን ጊዜ አላህ ወንጀልህን ምሮልሃል አሉት፡፡›
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ የሚከተለውን አውርተዋል፡ (አንድ ቀን አንድ ዘላን አረብ እመስጊድ ውስጥ እያለ ተነሳና ሽንቱን ሸና፡፡ ሰዎችም ሊያቋርጡት ተነሱ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ተውት ከሽንቱ ቦታም ሽንኬሎ ወይም አኮሌ ውሃ አፍሱበት እንንተ የተላካችሁት እኮ የምታቃልሉ ስትሆነ ነው፡፡ የምታከብዱ ሆናችሁ አልተላካችሁም፡፡) አሉ፡፡ እናታችን አዒሻም እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ አንድ ቀን አንድ ህፃን ተሰጣቸው፡፡ አቅፈውት እያለም እልብሳቸው ላይ ሽንቱን ሸና፡፡ ያለህ መልክተኛ ውሃ አምጡልኝ አሉና እሽንቱ ቦታ አፈሰሱበት፡፡›
ሙዓዊያ ኢብን አልሐከም አሰለሚ የታበሉት ባልደረባም የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን እኔ ከአላህ መልክተኛ ጋር እየሰግድሁ ሳለ ከሰዎች አንድ አስነጠሰው፡፡ አላህ ይዘንልህ አልኩኝ፡፡ ሰዎችም በግልምጫ ሲመለከቱኝ አየሁ፡፡ እኔም በምን ምክኒያት ነው እንደዚህ የምትገለምጡኝ አልኩኝ፡፡ በእጆቻቸው ጭኖቻቸውን መምታት ጀመሩ፡፡ ዝም እንድል መልክት በሰጡኝ ጊዜም ዝም አልሁኝ፡ ፡ እናትና አባቴ ቤዛቸው ይሁኑና የአላህ መልክተኛ ስግደት ከጨረሱ በኋላ ከሳቸው በፊትም ይሁን በኋላ ከሳቸው የበለጠ መልካም አስተማሪ አይቼ አላውቅም፡፡ በአላህ ይሁንብኝ አልገላምጡኝም፣ አልመቱኝም እንዲሁም አልሰደቡኝ፡፡ ነግር ግን እንዲህ አሉኝ፡ (ይህ ስግደት በሱ የሰዎች ንግግር ተስማሚ አይሆነውም፡፡ በሱ የሚስማማው ጌታን ማጥራት፣ ማክበርና ቁርኣን ማንበብ ነው፡፡)
የጌታችንን (ሱ.ወ.) መጽሐፍና የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈለጎች በምንከታተለበት ጊዜ በማንኛውም መልኩ ጸንፈኝነትንና ማጋነን ድባቅ የሚመቱ የተላያዩ የመቻቻል፣ ነገሮችን የማቃለልና የማግራት ገጽታዎች የምናገኝ መሆኑን አያጠራጥርም፡፡
በአሁኑ ወቅት በአለም ዙሪያ ውጥረት እየፈጠረ ያለውን ህውከት ብንምለከት የእስልምና እምነት በማንኛውም መልኩ ከመንስኤዎቹ አንዱ ነው ሊባል አይችልም፡፡

በመሰረተ እምነት በኩል እስልምና ማንንም በእምነቱ እንዲገባ አያስገድድም፡፡ ይልቁንም ለሁሉም የእምነት ነፃነት ዋስትና ሰጥቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ قَد تَّبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ}

ትርጉሙም (በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَن فِي الْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًا أَفَأَنتَ تُكْرِهُ النَّاسَ حَتَّىٰ يَكُونُوا مُؤْمِنِينَ.

ትርጉሙም (ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታድያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንድሆኑ ታስገድዳለህን? ) ማለት ነው፡፡

በአምልኮት በኩልም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከማጥበቅ ርቀን እንዲናገራና ቀለል እንዲናደርግ እንድህ በማለት ጥሪ አስተላልፈዋል፡ (ከናንት መካከል ሰዎችን የሚያስደነብሩ አሉ፡፡ ሰዎችን በስግደት የሚመራ ሰው ቀለል ያደርግ፡፡ ከነሱ መካከል በሽተኛ፣ ደካማና አፋጣኝ ጉዳይ ያለው ሰው አለና፡፡)

አንዳንድ ሰዎች (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) ሙዓዝ ሶላት እያስረዘሙብን ነው ብለው አቤቱታ ባቀረቡ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በማስተማር መልኩ እንድህ አሏቸው (ሙዓዝ ሆይ! አንተ ፈተና ፈጣሪ ነህንዴ ሦስት ጊዜ ከደጋገሙ በኋላ አነዚህን ምእራፎች፡

(وَالشَّمْسِ وَضُحَاهَا)،و(سَبِّحِ اسْمَ رَبِّكَ الأَعْلَى)

እና የመሳሰሉትን አንብብ አሏቸው) በአንዳንድ ወሬዎች (ካንተ በኋላ አረጋዊ፣ ደካማና አፋጣኝ ጉዳይ ያለው ሰው ይሰግዳልና) የሚል አረፍተ ነገር ተካቶ ይገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ ‹አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እመስጊድ ገቡ ከመስጊዱ ሁለት ወጋግራዎች መካከል ተወጥሮ የታሰረ ገመድ አዩ (ይህ ገመድ መንድን ነው? ) ሲሉ ጠየቁ፡፡ ይህ የዘይነብ ገመድ ነው በምትደክምበት ጊዜ የምትደገፍበት አሏቸው፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አይሆንም በሉ ፍቱት አንዳችሁ ንቃት አስካለው ድረስ ይሰገድ ከደከመው ደግሞ ይቀመጥ) አሉ፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር የተባሉት ባልደረባ እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ (ከእለታት አንድ ቀን መንገድ ወጣን ከኛ መካከል አንዱን ሰውየ ድንጋይ ራሱን ፈነከተው፡፡ ሌሊትም ሰውነቱን መታጠብ ግድ የሚያደርግ ሕልም አየ (በሕልሙ ፍተወት ፈሰሰው) ተየሙም ማደረግ የሚፈቀድልኝ መሆኑን የሚያቅ ሰው አለን? ሲል ባልደረቦቹን ጠየቀ፡፡ አንተ ውሃ ሳታጣ ተየሙም ማድረግ የሚፈቀድልህ ለመሆኑ የምናውቀው ነገር የለም አሉት፡፡ ሰውነቱን ታጠበ በሱም ምክኒያት ሞተ፡፡ በተመለስንም ጊዜ ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለጉዳዩ ተነገራቸው፡፡ ያን ጊዜም (አላህ ይግደላቸውና ገደሉት፡፡ ካለወቁ አይጠይቁም ነበርን የበሽታ ፈውሱኮ መጠየቅ ነው፡፡

እሱ ማድረግ የነበረበት ቁስሉን በራፊ ማሰርና እሱን አብሶ ሌላውን አካሉን መታጠብና ተየሙም ማድረግ ነበር፡፡) አሉ፡፡
ዑምራን ኢብን ሑሶይን የተባሉት ባልደረባ በታመሙ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ የሚል መመሪያ ሰጧቸው፡ (ቁመህ ስገድ፡፡ ባትችል ደግሞ ተቀምጠህ ስገድ፡፡ አቅም ካጣህ በጎንህ ተኝተህ ስገድ፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ብለዋል፡ ( ምድር ለኔ መስገጃና ንጹህ ተደርጋልኛለች፡፡ ከህዝቦቼ ማንኛውም ሰው የስግደት ወቅት በደረበት ጊዜ (በየትኛውም ቦታ) ይስገድ፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መቻቻልንና ገርነትን  በተጨባጭ በተግባር በማሳየታቸው ለእስልምና ታላቅነት ብርሃን የሚሰጥ አንፀባራቂ ስእል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ነብያችን ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እኔ ስግደት ስገባ ለማስረዘም አስብና የህፃናትን ለቅሶ እሰማለሁ፡፡ በዚህን ጊዜ በለቅሶው የእናቱን ቀልብ መንጠልጠል በማወቁ ስግደትን አሳጥራለሁ፡፡)
ከሰዎች መካከል ባአሉት ውሎች በኩል ደግሞ የእስልምና ህግ ከሰዎች ጋር ግብይት ስናደርግና ስንፋረዳቸውም ችግርና ጭንቀትን አስወግደን መቻቻልንና ገርነትን እንድንከተል ያዛል፡፡ አላህ (አ.ወ.) እንደህ ይላል፡
يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ إِلَّا أَنْ تَكُونَ تِجَارَةً عَنْ تَرَاضٍ مِنْكُمْ
لَا تَقْتُلُوا أَنفُسَكُمْ إِنَّ اللَّهَ كَانَ بِكُمْ رَحِيمًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን ከመካከላችሁ ያለአግባብ አትብሉ፡፡ ግን ከናንተ በመዋደድ የሆነችውን ንግድ (ብሉ) ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ፡ ፡ አላህ ለናንተ አዛኝ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ላል፡
{وَإِنْ كَانَ ذُو عُسْرَةٍ فَنَظِرَةٌ إِلَى مَيْسَرَةٍ وَأَنْ تَصَدَّقُوا خَيْرٌ لَكُمْ إِنْ كُنْتُمْ تَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም (የድህነት ባለቤት የሆነም (ባለእዳ) ሰው ቢኖር እማግኘት ድረስ ማቆየት ነው፡፡ (በመማር) መመጽወታችሁም ለናንተ በላጭ ነው፡፡ የምታውቁ ብትሆኑ፡፡ (ትሰሩታላችሁ) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሲሸጥ፣ ሲገዛና ሲፋረድም ገራገር የሆነን ሰው አላህ አዝነትን ይለግሰው፡፡) እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (በሚፋረድ ወይም በሚፋረዱት ወቅት ገራገር የሆነን ባሪያ አላህ ይዘንለት፡፡) በግብይት ገራገር መሆን ማለት በሽያጭ ሻጩ ስግብግብ፣ ለትርፍ ዋጋ ሰቃይ፣ እቃን በሞኖፖል ያዥና በሚዛን አጭበርባሪ አለመሆን ማለት ሲሆን በግዥም ገዢው ለሻጩ ገርና የሰዎችን ገንዘብ የማያጎድል መሆኑ ነው፡፡ በመፋረድ ገርነት ማለት ደግሞ አንድ ሰው ሙብቱንና ብድሩን በሚጠይቅበት ወቅት ልዝብ፣ ገርና ትእግስተኛ መሆኑ ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) በመዋዋል ገርነትና ታጋሽነት በመጭው አለም ከቅጣት መዳኛ እንደሚሆን እንደህ በማለት አብስረዋል፡ (አንድ ሰው በሚፋረድና በየሚፋረዱትም ጊዜ ገር በመሆኑ ገነት ገብቷል፡፡) አሁንም እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በፊት ከነበሩት ህዝቦች አንድ ሰው በጌታ ፊት ለሂሳብ ቀረበ፡፡ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ አልተገኘለትም፡፡ ነገር ግን እሱ ከሰዎች ጋር ይቀላቀል ነበር ባለጸጋም ነበርና

አገልጋዮቹ የሚከፍለው የሌለውን ሰው እዳ ከፈል ብለው ከመያዝ እንዲያልፉት ያዘ ነበር፡፡ ነብያችን አላህ (ሊ.ወ.) እንደህ አለ አሉ በዚህ አይነቱ ተግባር እኛ ከሱ ተቀዳሚዎች ነን እለፉት፡፡)
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከአለተ ቂያማ እይታዎች አንዱን ሲገልጹ አንድህ ብለዋል፡ ( አላህ (ሊ.ወ.) እንድህ ይላል፡ አስኪ እሳት ውስጥ ተመልከቱ አንድ ጊዜ አንኳ ቢሆንም መልካም ሥራ የሰራ ሰው ታገኛለችሁ እንዴ? አነሱም አንደ ሰው ያገኛሉ አንድ ቀን አንኳን ቢሆን መልካም ሥራ ሰርተህ አታውቅም? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም የለም ነገር ግን በሽያጭ ለሰዎች ገር ነበርሁኝ አለ፡፡ ያን ጊዜ አላህ (ሊ.ወ.) ለባሪያ ገር እንደሆነ ሁሉ ለባሪያ ገር ሁኑ አለ፡፡)
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ፡፡ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡
* * *
ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

በእስልምና እምነት የመቻቻልና ገርነት መርህ ሙስሊሞች ከመካላቸው በሚያደርጉት ውል ብቻ አይወሰንም፡፡ ይልቁንም ሰዎችን በሙሉ የሚያካትት አጠቃላይ የሕይወት ስርአት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ምእምናን ባሮቹ ከመላ ሰዎች ጋር ያለቸው መስተጋብር መልካም እንዲሆን በማዘዝ እንድህ ይላል፡

{وَقُولُوا لِلنَّاسِ حُسْنًا}

ትርጉሙም( ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡
{لاَ يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُمْ مِنْ دِيَارِكُمْ أَنْ تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ}

ትርጉሙም (ከነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጧችሁ (ከሃዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደርነሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡ አብደላህ ኢብን ዑመር የተባሉት ባልደረባ ፍየል ባረዱ ጊዜ ለአገልጋያቸው ለይሁዳው ጎረቤታችን ስጠታውን ልከሃልን? አረፍተነገሩን ከደገሙለት በኋላ እኔ የአላህ መልልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (ጂብሪል ስለጎረቤት አደራ ማለቱን አላቋረጠም እኔ ባንድ ወቅት መናልባትም ከንብረትህ ይውረስ ይለኝ ይሆን ብየ እስከመጠራጠር ደርሼ ነበር፡፡) አሉት፡፡
ከገርነት ገጽታዎች አንዱ የነፍስ ገርነት ነው፡፡ ማለትም ነፍስ ቸር፣ ለጋስመሆኗና ለሁሉም ሰው መልካም ውለታ መዋሏ ማለት ነው፡፡ (አላህ ይዘንላቸውና) ኢማሙ አሻፊዒ እንድህ ይሉ ነበር፡

በቸርነት ተደበቅ፡፡ ማንኛውም ነውር በቸርነት ይሰወራል እንድሉ፡፡
ለጠላቶች በምንም አይነት ውርደትን አታሳይ፡፡ የጠላቶች መሳለቅ መከራ ነውና፡፡
ከስግብግብ ገርነትን አትጠብቅ፡፡ ጥመኛ ከእሳት ውስጥ ውሃ ሊያገኝ አይችልምና፡፡
ጌታችን ሆይ! ሃይማኖታችንን በተተካከለ መልኩ መረዳትን ስጠን፡፡ ቅኑን መንገድ ምራን፡፡ በኛ ሰዎችን ቅኑን መንገድ እንድመሩም አድርግ፡፡ ቅኑን መንገድ ለተመራም ሰው የቅን መንገድ መመራቱ ምክኒያት አድርገን፡፡

## (14)

## የወላጆችና የዝምድና ባለቤቶች መብቶች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَقَضَى رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوا إِلَّا إِيَّاهُ وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا إِمَّا يَبْلُغَنَّ عِندَكَ الْكِبَرَ أَحَدُهُمَا أَوْ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل لَّهُمَا أُفٍّ وَلَا تَنْهَرْهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوْلًا كَرِيمًا * وَاخْفِضْ لَهُمَا جَنَاحَ الذُّلِّ مِنَ الرَّحْمَةِ وَقُل رَّبِّ ارْحَمْهُمَا كَمَا رَبَّيَانِي صَغِيرًا}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፡- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፡፡ በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፡፡ በአንተ ዘንድ ኾነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፡፡ አትገላምጣቸውም፡፡ ለእነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው፡፡ ለሁለቱም ከእዝነትህ የመዋረድን ክንፍ ዝቅ አድርግላቸው፡፡ «ጌታዬ ሆይ! በሕፃንነቴ (በርኅራኄ) እንዳሳደጉኝ እዘንላቸውም» በል፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
የእስልምና እምነት በመልካም ምግባር የያዘ፣ አጅግ ቅን የሆነን መርህ ያዘለ፣ ወደቀጥተኛው ስርአት የሚመራ፣ የህይወት ስርአቱን አርአያነት ያለቸው እሴቶች አድርጎ፣ የመጣ ገራገር መልእክት ነው፡፡ እምነቱ ከሰዎች መካከል ለአለው እውነተኛ ግንኙነት ሚዛን ፍትህ፣ እዝነት፣ ፍቅርና ሰብአዊነትን አድርጎ የመጣ መልእክት መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾልናል፡

{إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَى وَيَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَالْبَغْيِ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ} .

ትርጉሙም (አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፡፡ ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡

ከአስልምና ህግጋቶች ታላቅነት ገጽታ ዋነኛው ከወላጆችና ከዝምድና ባለቤቶች ጋር ለአሉት ግንኙነቶች ደንቦች፣ ስርአቶችና መብቶች ግልጽ መመሪያ ያስቀመጠ መሆኑ ነው፡፡ ወላጆች ከማነም የበለጠ የመከበር፣ ታላቅ ቦታ የመሰጠትና የእንክቤም መብት አላቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ወላጆቻችን እንድናከበርና መልካም ውለታ እንድንውላለቸው ግድ መሆኑን ይህንም ጉዳይ ከእሱ አምልኮት በማቆራኘት እንድህ ሲል አብራርቷል፡

{وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا}

ትርጉሙም (አላህንም ተገዙ፡፡ በእርሱም ምንንም አታጋሩ፡፡ በወላጆች ላይ መልካምን ሥሩ..) ማለት ነው፡፡

ታላቁ አላህ ሰዎች እንዲያመሰግኑት ባዘዘበት ወቅትም ትሩፋታቸው ታላቅና ደረጃቸው ከፍተኛ መሆኑን ለመግለጽ ወላጆችንም እንድናመስግ አዟል (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይድና አብደላህ ኢብን አባስ እነድህ ብለዋል፡ ‹ሦስት አንቀጾች በሦስት ነገሮች ተቆራኝተው ወረደዋል፡፡ በመሆኑም ከነሱ አንደኛዋ ከቁራኛዋ ተለይታ ተቀባይነት አይኖራትም፡፡ አንደኛዋ

{أَنْ اشْكُرْ لِي وَلِوَالِدَيْكَ}

ትርጉሙም (ለኔም ለወላጆችህም አመስግን...) ማለት ነው፡፡

ይህች አንቀጽ አላህን ቢያመሰግንም ወላጆቹን የማያመሰግን ከሆነ ምስጋናው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ትገልጻለች፡፡ የእስልምና እምነት የዋለጆች ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን አረጋግጦ ለነሱ እንዲንታዘዝና መልካም ውለታቸውን እንዳንረሳና እንድንከባከባቸውም አዞናል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን አምር እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰዎዬ ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና በጂሃድ እንድሳተፍ ይፈቅዱለት ዘንድ ጠየቀ፡፡ ነብያችንም (ወላጆችህ በሕይወት አሉን?) ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም አዎን በማለት መለስ፡፡ እሳቸውም (አነሱን በማገልገል ታገል) አሉት፡፡›

በሰይዲና ሙሳ ታሪክ የጻዲቁ ሰውዬ ሴት ልጆች ለአባታቸው በመታዘዝ አርአያነት ያለው ተግባራቸውን በግልጽ አሳይተዋል፡፡ አባታቸው ሥራ የማይችሉ አቅመ ደካማ ነበሩ፡፡ በመሆኑም ያለመበሳጨት በአባታቸው ፊንታ ይሠሩ አንደነበር ታላቁ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በምትለው አንቀጽ ገልፆልናል፡

{وَلَمَّا وَرَدَ مَاءَ مَدْيَنَ وَجَدَ عَلَيْهِ أُمَّةً مِّنَ النَّاسِ يَسْقُونَ وَوَجَدَ مِن دُونِهِمُ امْرَأَتَيْنِ تَذُودَانِ قَالَ مَا خَطْبُكُمَا قَالَتَا لَا نَسْقِي حَتَّى يُصْدِرَ الرِّعَاءُ وَأَبُونَا شَيْخٌ كَبِيرٌ}

ትርጉሙም( ወደ መድየንም ውሃ በመጣ ጊዜ በእርሱ ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን (መንጋዎቻቸውን) የሚያጠጡ ሆነው አገኘ፡፡ ከእነርሱ በታችም (ከውሃው መንጎቻቸውን) የሚከለክሉን ሁለት ሴቶች አገኘ፡፡ «ነገራችሁ ምንድን ነው» አላቸው፡፡ «እረኞቹ ሁሉ (መንጋዎቻቸውን) እስከሚመልሱ አናጠጣም፡፡ አባታችንም ትልቅ ሽማግሌ ነው» አሉት፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር እንድህ ብለዋል፡ ‹አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ለነብያችን የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኔ ገንዘብና ልጅ አለኝ፡፡ ይሁንና አባቴ ገንዘቤን ሊወስድ ይፈልጋል ሲል ጠየቀ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንተም ገንዘብህም ያአባትህ ናችሁ) በማለት መለሱለት፡፡

እኛ የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ልጅ ፋጢማ ለአባቷ ለአላህ መልክተኛ ታሳየው ከነበረው ፍቀር፣ አክብሮትና እዝነቷ ከፍተኛ አርአያነት ያላቸው ትምህርት ሰጭ ተግባራትን እናገኛለን፡፡

የእስልምና እምነት ወላጆቻችንን እንድናከብርና በነሱም ላይ ጉዳት ከማድረስ እንድንቆጠብ አዞናል፡፡ ታላቁ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

إِمَّا يَبْلُغَنَّ عِندَكَ الْكِبَرَ أَحَدُهُمَا أَوْ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل لَّهُمَا أُفٍّ وَلَا تَنْهَرْهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوْلًا كَرِيمًا}

ትርጉሙም( በአንተ ዘንድ ኾነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፡፡ አትገላምጣቸውም፡፡ ለእነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) እጅግ ዝቅተኛ የሆነችውን የብስጭት ቃል እንኳን ለወላጆች እንዳንሰነዝር ከልክሏል፡ የአምነቱ ሊቃውንት ‹‹ኤጭ›› ከምትለዋ የብስጭት ቃል ያነስ ቢኖር ኖሮ አላህ እሷንም ይከለክል ነበር ይላሉ፡፡ (ካርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ አንድን ሰውዬ ለአባቱ ታዛዥ እንድሆን ሲመክሩት እንድህ ብለዋል፡ ‹ከአባትህ ፊት ፊት አትሂድ፣ ከሱም በፊት ቀድመህ አትቀመጥ፣ በስሙም አትጥራው፣ ሰዎችን ሰድበህ እሱን ከማሰደብ ታቀብ፡፡› ማንኛውም ሙስሊም ለአባቱ ጉዳት መከሰት ምክኒያት መሆን የለበትም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ከተላላቅ ወንጀሎች ታላቁ አንድ ሰው ዋለጆቹን መርገሙ ነው፡፡) ሰዎችም የአላህ መልክተተኛ ሆይ! አንድ ሰው አንዴት ወላጆቹን ይረግማል? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (አንድ ሰው ሌላውን ሲሰድብ አባቱን ይረግማል ያ ሰውዬም የሱን አባት ይረግማል አንድሁም እናቱን ይሰድባል ያም ሰውዬ የሱን እናት ይሰድባል፡፡) አሉ፡፡

የአስልምና እምነት የሌላ እምነት ተከታዮች ቢሆኑም እንኳን ወላጆችን የማክበር ግዴታ እንዲያለብን ያረጋግጣል፡፡ ይህን ጉዳይ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልፆልናል፡

{وَإِن جَاهَدَاكَ عَلَى أَن تُشْرِكَ بِي مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ فَلَا تُطِعْهُمَا وَصَاحِبْهُمَا فِي الدُّنْيَا مَعْرُوفًا}

ትርጉሙም (ለአንተ በእርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው፡፡ በቅርቢቱም ዓለም፤ በመልካም ሥራ ተወዳጃቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

በዚህ ዘርፍ ሰይድና ኢብራሂም አባታቸው እስስልምናን እንድቀበሉ ጥሪ ሲያደርጉ ያሰዩት አክብሮት በሚከተሉት አንቀፆች ሰፍሯል፡

وَاذْكُرْ فِي الْكِتَابِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّهُ كَانَ صِدِّيقًا نَّبِيًّا * إِذْ قَالَ لِأَبِيهِ يَا أَبَتِ لِمَ تَعْبُدُ مَا لَا يَسْمَعُ وَلَا يُبْصِرُ وَلَا يُغْنِي عَنكَ شَيْئًا * يَا أَبَتِ إِنِّي قَدْ جَاءَنِي مِنَ الْعِلْمِ مَا لَمْ يَأْتِكَ فَاتَّبِعْنِي أَهْدِكَ صِرَاطًا سَوِيًّا * يَا أَبَتِ لَا تَعْبُدِ الشَّيْطَانَ إِنَّ الشَّيْطَانَ كَانَ لِلرَّحْمَٰنِ عَصِيًّا * يَا أَبَتِ إِنِّي أَخَافُ أَن يَمَسَّكَ عَذَابٌ مِّنَ الرَّحْمَٰنِ فَتَكُونَ لِلشَّيْطَانِ وَلِيًّا} .

ትርጉሙም(በመጽሐፉ ውስጥ ኢብራሂምንም አውሳ፡፡ እርሱ በጣም እውነተኛ ነቢይ ነበርና፡፡ ለአባቱ ባለ ጊዜ (አስታውስ) «አባቴ ሆይ! የማይሰማንና የማያይን ከአንተም ምንንም የማይጠቅምህን (ጣዖት) ለምን ትግገዛለህ፡፡ አባቴ ሆይ! እኔ ከዕውቀት ያልመጣልህ ነገር በእርግጥ መጥቶልኛልና ተከተለኝ፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና፡፡ አባቴ ሆይ! ሰይጣንን አትግገዛ፡፡ ሰይጣን ለአልረሕማን አመጸኛ ነውና፡፡ አባቴ ሆይ! እኔ ከአልረሕማን ቅጣት ሊያገኝህ ለሰይጣንም ጓደኛ ልትኾን እፈራለሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሷ አላህ ይውደድና) አስማእ ቢንት አቡበክር እናቷ በፈጣሪ አጋሪ ሆና እያለ ልትጠይቃት በመጣች ጊዜ ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ›የአላህ መልክተኛ ሆይ! እናቴ ልተጠይቀኝ መጣች እኔ እናቴን መቀበል እችላሁን ? › በማለት ጠየቀች፡፡ እሳቸውም (አዎን እናትሽን ተቀበይ) አሏት፡

ወላጆችን በመታዘዝና እነሱን በማክበር አንድ የአላህ ባሪያ በዚህች አለምና በመጭውም አለም የሚያገኘው ከፍተኛ ጥቅምና ወሰን የለሽ ትሩፋት አለው፡፡ ከነሱም አንደኛው የአላህን ውዴታ የሚያስገኝ መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የአላህ ውዴታ በወላጆች ውዴታ ይገኛል፡፡ የአላህም ቁጣ በወላጆች ቁጣ ሊከሰት ይችላል)፡፡

የወላጆች መታዘዝ ሌላው ጥቅም ደግሞ ጭንቀት የሚያስወግድ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ነብያችን ባወሩልን በሦስቱ ሰዎች ታሪክ በግልጽ ይታያል፡፡ ታሪኩም እንድህ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ሦስት ሰዎች ሲጓዙ ከፍተኛ ዝናብ መውረድ ጀመረ፡፡ እነሱም ለመጠለል ወደ አንድ ዋሻ ገቡ፡፡ ወዲያውኑ ከገደሉ ታላቅ አለት ተንሸራቶ የዋሻውን በር ዘጋባቸው፡፡ እነሱም ከዚህ አለት አደጋ ሊያወጣችሁ የሚችል ነገር አይኖርም በመልካም ሥራችሁ አላህ (ዐ.ወ.)ን መጻለይ ቢሆን እንጂ ተባባሉ፡፡ ከነሱም አንደኛው ሰውዬ እንድህ አለ፡ ‹ጌታዬ ሆይ! እኔ ታላላቅ አረጋዊያን አባትና እናት ነበሩኝ፡፡ ትንንሽ ህፃናትም እንደዚሁ ነበሩኝ፡፡ ከብት እየጠበቅሁ እነሱን እስተዳድር ነበር፡፡ ማታ ማታ ስመለስ ላሞችን አልቤ ከልጆቼ አስቀድሜ መጀመሪ

የማጠጣው ወላጆቸን ነበር፡፡ አንድ ቀን ማታ በጣም አምሽቼ ተመለስሁ፡፡ ወላጆቼ ተይተው አገኘሁ፡፡ ሁል ጊዜ እንደማደርገው ላሞችን አለብሁኝ፡፡ እናም በራስጊያቸው በኩል ቁምሁኝ፡፡ ለቀሰቅሳቸውም ፈራሁ፡፡ እግሬ ስር በራህብ ስቃይ የሚጮኹትን ልጆቸን ማጠጣትም አልፈቀድሁም፡፡ በዚህ ሁኔታም ጎህ እስቀሚቀድ ቆየሁ፡፡ ጌታየ ሆይ! ያን ነገር ያደረግሁት ያንተን ውዴታ ፍለጌ መሆኑን የምታውቅ ከሆነ ከዚህች አለት ሰማይ የምናይባት ክፍተትን ከፍትልን አለ፡፡ አላህ (አ.ወ.)ም ከፈት አደረገላቸውና ሰማይን አዩ ...› እነሆ ለናት አባቱ መታዘዙ ከጨንቀት ለመወጣቱ ምክኒያት ሆነለት፡፡

ለናት አባት መታዘዝ ሌላው ጥቅም ደግሞ ወላጆቹን የሚያከብር ሰው ልጆቹ የሚያከብሩት መሆኑ ነው፡፡ ይህውም የማንኛውም ነገር ምንዳ የሥራው ዓይነት ስለሚሆን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ነብዩ ኢብራሂም አባታቸውን በአላህ አንድነት እምነትን እንዲቀበሉ ጥሪ ባደረጉበት ወቅት ለአሳዩት መልካም ውለተና ታዛዥነት ወሮታ አድርጎ ወሰን የለሽ ትእዛዝ የሚፈጽሙትን ልጃቸውን ኢስማኢልን ስጧቸዋል፡፡ ይህን ጉዳይ ታላቁ አላሕ እንድህ በማለት አብራርቶታል፡

{فَلَمَّا بَلَغَ مَعَهُ السَّعْيَ قَالَ يَا بُنَيَّ إِنِّي أَرَى فِي الْمَنَامِ أَنِّي أَذْبَحُكَ فَانظُرْ مَاذَا تَرَى قَالَ يَا أَبَتِ افْعَلْ مَا تُؤْمَرُ سَتَجِدُنِي إِن شَاءَ اللَّهُ مِنَ الصَّابِرِينَ}

ትርጉሙም (ከእርሱ ጋርም ለሥራ በደረሰ ጊዜ «ልጄ ሆይ! እኔ በሕልሜ እኔ የማርድህ ሆኜ አያለሁ፡፡ ተመልከትም፤ ምን ታያለህ?» አለው፡፡ «አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ሥራ፡፡ አላህ ቢሻ ከታጋሾቹ ሆኜ ታገኘኛለህ» አለ፡፡) ማለት ነው፡፡

ለወላጆች የመታዘዝ ሌላው ፋይዳ ደግሞ በዚህች አለም ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ጀነት በመግባትም የአላህ ባሪያዎች ይደሰቱበታል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር እንድዘመት ፈቃድ ለመጠየቅ በሄደ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (እናት አልችህን?) ሲሉ ጤቁት፡፡ አሱም አዎን አለ፡፡ ከእሷ አትለይ ጀነት ከግሮቹዋ ስር ናትና) አሉት፡፡ እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ (አባት የጀነት በሮች ማህል ክፍል ነው በትፈልግ ይህን በር አጥብቀህ ያዝ ብትፈልግም አጥፋው)፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዑመር ለአንድ ሰውዬ ‹እሳትን ትፈራለህ? ጀነትም መግባትን ትፈልጋለህ አይደል? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም አዎን በአላህ ይሁንብኝ አላቸው፡፡ እሳቸውም አባትህ በሕይዎት አለ? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም እናቴ አለች በማለት መለሰ፡፡ እሳቸውም በመልካም አንደበት የምታናግራት፣ የሚያስፍልጋትን ምግብ የምታቀርብላት ከሆነና ተላላቅ ኃጢአቶችን የማትዳፈር ከሆነ በአላህ ይሁንብኝ ጀነት ትገባለህ አሉት፡፡›

ይሁንና እኛ ሁላችንም ለወላጆቻችን ታላቅና ብዙ የሚመስለንን ውለታ ብንውልም የሚገባቸውን መብት አናሟላም፡፡ ወሰን የለሽ ውለታቸውንም አንመልስም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አንድ ልጅ የአባቱን ውለታ በሙሉ ሊመለስ አይችልም በባርነት የሰው ንብረት ሆኖ አግኚቶት ገዝቶ ነፃ ቢያደርገው ጊዜ እንጂ)፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የእስልምና እምነት ወላጆችን እንድናከብር እንዳዘዘን ሁሉ የዝምድን ባለቤቶችንም እንደዘሁ እንድናከበር መክሮናል፡፡ እነሱም እንደሰው በስጋ የሚዛመዳቸውና አላህ (ሱ..ወ.) ለነሱ ሙብት ያደረገላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَأُولُو الْأَرْحَامِ بَعْضُهُمْ أَوْلَى بِبَعْضٍ فِى كِتَابِ اللَّهِ}

ትርጉሙም (የዝምድናዎች ባለቤቶችም በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው በከፊሉ (መውረስ) የተገቡ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችንም (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ሱ.ወ.) ፍጥረታትን ፈጠሮ በጨረሰ ጊዜ ዝምድና ተነሳችና ይህ ቦታ ከመቁረጥ ለመዳን ባንት የሚጠበቁበት ቦታ ነው አለች፡፡ አላህም አዎን የሚቀጥለሽን የምቀጥል እንድሁም ደግሞ የሚቆርጥሽን የምቆርጥ መሆኔ አያረጋሽምን? አላት፡፡ አሷም አዎ ያረካኛል አለች፡፡ እሱም እሱን ላንች አድርጊያለሁ አላት፡፡ ከፈለጋችሁም የምትከተለዋን አንቀጽ አንብቡ አሉ፡

فَهَلْ عَسَيْتُمْ إِنْ تَوَلَّيْتُمْ أَنْ تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ وَتُقَطِّعُوا أَرْحَامَكُمْ * أُولَئِكَ الَّذِينَ لَعَنَهُمُ اللَّهُ فَأَصَمَّهُمْ وَأَعْمَى أَبْصَارَهُمْ}) .

ትርጉሙም( ብትሸሹም በምድር ላይ ማበላሸትን ዝምድናችሁንም መቁረጥን ከጀላችሁን? እነዚህ እነዚያ አላህ የረገማቸው፣ ያደነቆራቸውም፣ ዓይኖቻቸውንም ያወራቸው ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

የዝምድና ባለቤቶች ሙብት እነሱን በመጠየቅ፣ ሁኔታቸውን በመከታተልና እገዛ በማድረግ ይረጋገጣል፡፡ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለምስኪን መስጠት አንድ ምጽዋት ነው  ለዝምድና ባለቤት ደግሞ ሁለት ምጽዋት ሲሆን ዝምድና መቀጠልና ምጽዋት ናቸው)፡፡ እንድሁም የዝምድና ባለቤቶችን ጥሪ መቀበል፣ በሽተኛቸውን መጠየቅ፣ ሙታቸውን መሸኘት እንድሁም ተላላቂቻቸውን ማክበር ለህጻናቶቻቸው ማዘን ለነሱም ጸሎት ማድረክ ሙብታቸውን ከማክበር ይካተታል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ዝምድናን መቀጠል ለሲሳይ መጨመርና ለእድሜ በረከት ምክኒያት አድርጎታል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (እድሜው እንድረዝምለት ሲሳዩም እንድበዛለት የሚፈለግ ሰው ወላጆቹን ያክብር ዝምድናንም ይቀጥል)፡፡ ነብያችን

(ሶ.ዐ.ወ.) ዝምድናን መቀጠል ለወንጀል ምህረት ምክኒያት እንደሚሆንም አብስረዋል፡ ፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጣና የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኔ ታላቅ ኃጢአት ፈጽሚያለሁ ጸጸቴ ተቀባይነት ያገኛል ወይ? ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (እናትህ በህይወት አለችን? በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም የለም የለችም አለ፡፡ የእናትህ እህት አክስትህስ በህይወት አለችን? በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም አዎን አለች ሲል መለሰ፡፡ እሳቸውም (እሷን ታዘዝ ውለታም ዋልላት) አሉት፡፡

ማንኛውም ሰው ዝምድናን ከመቁረጥ እንድሁም ለመጥፎ ተግባር ተመሳሳይ አጸፋ ከመስጠት መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡ ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ዝምድና ቀጣይ የሚባለው ውለታ መላሽ አይለም፡፡ ነገር ግን ቀጣይ የሚባለው ዝምድናው በሚቋረጥበት ጊዜ የሚቀጥል ሰው ነው፡፡) ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጣና እንድህ አለ፡ ‹ የአላህ መልክተኛ ሆይ! የኔ ዘመዶች እኔ ዝምድናቸው ስቀጥል እነሱ ይቆርጣሉ፡፡ እኔ መልካም ሰውልላቸው እነሱ ያስከፉኛል፡ ፡ እኔ ስታገሳቸው እነሱ ስህተት ይፈጽሙብኛል፡፡› ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (አንተ እንደምትለው ከሆንክ አንተ ረመጥ እያጠጣሃቸው ነው፡፡ አንተ በዚሁ ሁኔታ ላይ እስካለህ ድረስ ከአላህ ዘንድ በነሱ ላይ የሚያግዝህ የጀርባ አጋዥ አይለይህም፡፡)

እኛ ሁላችንም አባቶቻችንን እናቶቻችንን አላህን በመፍራት ማክበር ይኖርብናል፡፡ ዝምድናችንን መቀጠል እንድሁም ከሁሉም ሰው ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖርን ይገባል፡፡

ጌታችን ሆይ! ለአባቶቻችንና ለእናቶቻችን ተዛገሮች እንድንሆንና ዝምድናችንን እንድንቀጥል ረደኤትህ ከኛ ጋር ይሁን ህዝባችንን ጠብቅልን ሀገራችንን የሰላምና የብልጽግና አገር አድርግልን የሌሎችንም አገር እንደዚሁ አሜን፡፡

## (15)

.

## ያስተማሪና የተማሪ ግዴታ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

(يَرْفَعِ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَالَّذِينَ أُوتُوا الْعِلْمَ دَرَجَاتٍ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ)

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (አላህ ከናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም ዕውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች ከፍ ያደርጋል፡፡ አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ። እንዲሁም ነብያችን ሰይዷና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ። ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማም ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ።

**ከዚህም በመቀጠል፡**

እኛ በአሁኑ ወቅት ለአድሱ የትምህርት ዓመት እየተቃረብን እንገኛለን። ይህ አድሱ የትምህርት ዓመት የታታሪነት፣ የጥረትና ለመላ ልጆቻችን የስኬት ዓመት እንድሆን አላህ (ዐ.ወ.)ን እንለምናለን። የእስልምና እምነት ለእውቀት በተለየ መልኩ ቅድሚያ እንዲሁም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። እውቀት የልቦች ሕይወትና የዓይኖች ብርሃን ሲሆን ባለቤቱን በዚህችም ዓለም ሆነ በመጭው ዓለም ወደ ምርጦች ቦታና ወደከፍተኛ ደረጃ ያደርሳል። በእውቀት ዝምድና ይቀጠላል፣ እርም ነገሮች ከተፈቀዱት ነገሮች ይለያሉ፣ በሱም አላህ (ሱ.ወ.) ሰዎችን ከፍ አድርጎ የበጎ ተግባር መሪና ሰዎች የሚከተሏቸው አርኣያዎች ያደርጋቸዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{قُلْ هَلْ يَسْتَوِي الَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَالَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ}.

ትርጉሙም (እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይስተካከላሉን?» በላቸው።) ማለት ነው። እስልምና ለአውቀት ትኩረት የሰጠውና እሱንም ሰዎች እንደፈልጉት ያዘዘው የቅዱስ ቁርኣን የመጀመሪያው አንቀጽ በወረደበት ጊዜ ነበር። አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{اقْرَأْ بِاسْمِ رَبِّكَ الَّذِي خَلَقَ خَلَقَ الإِنسَانَ مِنْ عَلَقٍ *اقْرَأْ وَرَبُّكَ الأَكْرَمُ *الَّذِي عَلَّمَ بِالْقَلَمِ *عَلَّمَ الإِنسَانَ مَا لَمْ يَعْلَمْ}

ትርጉሙም (አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም። "ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።" አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ፣ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን።) ማለት ነው።

የመጀመሪያው የትንቢት ትእዛዝ የእውቀት ዋና በር የሆነው የንባብ ትእዛዝ ነበር። ከዚያም እውቀትን በማህደር የምናሰፍርበትና እሱን ከቦታ ቦታ የምናዛውርበት የብእር ጥቆማ ተከተለ። ይህም ታድያ የእውቀትን አስፈላጊነት የሚጠቁም ከመሆንም ባሻገር እውቀትን ለመቅሰም ሰዎች እንድጥሩ ግድ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። እውቀት ታላቅ ደረጃ አለው። የእውቀት ሰዎችም ከፍተኛ ቦታ ይሰጣቸዋል። እውቀትና ሙሁራን

ባይኖሩ ኖሮ ሰዎች በጥሜት ጎዳና ላይ ይገኙ ነበር፡፡ እውቀት ባለቤቱ የነገሮችን ምስጢር የሚያይበት ብርሃን ነው፡፡ ሙሁራንም ሰዎች በነሱ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንደሚያውቁባቸው የሰማይ ከዋክብት ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{أَفَمَن يَعْلَمُ أَنَّمَا أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ الْحَقُّ كَمَنْ هُوَ أَعْمَى إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُولُوا الأَلْبَابِ}

ትርጉሙም (ከጌታህ ወዳንተ የተወረደው እውነት መኾኑን የሚያውቅ ሰው እንደዚያ እርሱ ዕውር እንደኾነው ሰው ነውን የሚገሠጹት የአእምሮ ባለቤቶች ብቻ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በዚህች አንቀጽ ሰዎችን አዋቂና እውር ብሎ ወደሁለት እንደከፈላቸው ሁሉ እውቀትንም የእውርነት ተጻራሪ አድርጎታል፡፡ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ዓይን የመመልከቻ ሳይሆን የእውቀት ዓይን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَإِنَّهَا لَا تَعْمَى الأَبْصَارُ وَلَكِن تَعْمَى الْقُلُوبُ الَّتِي فِي الصُّدُورِ}

ትርጉሙም( እነሆ ዓይኖች አይታወሩም ግን እነዚያ በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ይታወራሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ቁርአን የእውቀትን ደረጃ ከፍ ሲያደርግ አስረጅ ብሎ የጠራው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ يُجَادِلُونَ فِي آيَاتِ اللَّهِ بِغَيْرِ سُلْطَانٍ أَتَاهُمْ كَبُرَ مَقْتًا عِنْدَ اللَّهِ وَعِنْدَ الَّذِينَ آمَنُوا

.

ትርጉሙም (እነዚያ፤ የመጣላቸው አስረጅ ሳይኖር በአላህ ተዓምራቶች የሚከራከሩ (ክርክራቸው) አላህ ዘንድና እነዚያም አመኑት ዘንድ መጠላቱ በጣም ተለቀ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የእውቀትን ታላቅ ደረጃና እሱን መፈለግ ያለውን ትሩፋት እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (እውቀትን በመፈለግ መንገድ የገባ ሰው አላህ (ሱ.ወ.) ከጀነት መንገዶች አንዱን ይመረዋል፡፡ መላእከትም በእውቀት ፈላጊ ተግባር በመደሰት በክንፋቸው ይከልሉታል፡፡ አንድ ሙሁር በምድርም በሰማይም ያለ ሁሉ በከርሰ ባሕር ያሉም አሳ ነባሪዎች ሳይቀሩ ከአላህ ምህረትን ይለምኑለታል፡፡ ሙሁር ከአላህ ተገዢ ጋር ሲነጻጸር ያለው ብልጫ ሙሉ ጨረቃ ሌሎችን ከዋክብት እንደሚበልጥ ነው፡፡ ሙሁራን የነብያት ወራሾች ናቸው፡፡ ነብያት ደግሞ ወርቅም ይሁን ብርን አላወረሱም ያወረሱት እውቀትን ብቻ ነው፡፡ እሱን የያዘ ሙሉ እድል ይዟል፡፡)

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ዘር የተባሉት ባልደረባ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልክተኛ እንድህ አሉኝ፡ (አባ ዘር ሆይ! ጧት ከቤትህ ወጥተህ አንድት የአላህ መጽሐፍ አንቀጽን መማርህ መቶ ረካዓ ከመስገድህ የበለጠ

ነው፡፡ ጧት ከቤትህ ወጥተህ -ይሰራበትም አይሰራበትም- አንድ የእውቀት ምእራፍ መማርህም አንድ ሺህ ረካዓ ከመስገድህ ይበልጣል፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢማሙ ዓልይ እንድህ ይላሉ፡ ‹እውቀት ከገንዘብ ይበልጣል፡፡ ምክኒያቱም እውቀት አንትን ይጠብቀሃል ገንዘብን ግን አንተ ትጠብቀዋለህ፡፡ እውቀት ገዢ ነው፡፡ ገንዘብ ደግሞ ተገዢ ነው፡፡ ገንዘብ ስትሰጥለት ይጎድላል፡፡ እውቀት ግን ስትሰጥለት ይጨምራል፡፡›

እውቀት አስተማሪውም ይሁን ተማሪ በአንድ ላይ ሊጎናጸፉት የሚገባ ታላቅ ጠባይና የተከበሩ ስርኣተች አሉት፡፡ ከነሱም መካከል የመጀመሪያው ለአላህ (ዐ.ወ.) ብቻ እንድሆን በታማኝነት መስራት የሚለው ነው፡፡ ማለትም አስተማሪውም ሆነ ተማሪው በዚህ በእውቀት የአላህን ውዴታ የሚፈልግ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም በማስማሩም ሆነ በመማሩ ከይውልኝና ይስሙልኝ መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡ በእውቀት ውስጥ በአንድ ሰው ልብ በሚሰርጽበት ወቅት ልታይ የማለት ዝንባሌንና ተቀዳሚ ልሁን የማለት ፍላጎትን የሚያስከትል ምስጢራዊ ስሜት አለ፡፡ እሱም በዚያ ሰው ጠባይና ስርኣት ተጽእኖ አሳድሮ በሰዎች ላይ እንዲኮራ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ከዚህ ጉዳይ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አስጠንቅቀዋል፡ (ሞኞችን ሊከራከርበት ወይም ከሙሁራን ጋር ሊፎካከርበት ወይም የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ እውቀትን የሚፈልግ ሰው እሱ በእሳት ውስጥ ነው፡፡)

ሌላኛው የእውቀት ስርኣት ደግሞ ራስን ዝቅ ማድረግ ነው፡፡ ኢማሙ ማሊክ ለረሺድ በላኩት መልክት እንድህ ብለዋል፡ ‹አንድን እውቀት በቀስምክ ጊዜ የሱ ገጽታ፣ ርጋታው፣ ጠባዩ፣ ክብሩና ትእግስቱ ባንተ ላይ እንዲታይ ጥረት አድርግ፡፡› (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይዲና ዐመር በበኩላቸው ‹እውቀትን ገብዩ ለሱም ርጋታና ክብርን ተማሩለት፡፡› ይህውም እውቀት ከትእቢት ጋር ስለማይጣጣም እንድሁም ከወንጀል ጋር አብሮ ሊገበይ ስለማይችል ነው፡፡ እውቀት በጥረት የሚገበይ ሲሆን አላህን በመፍራትም ይጨምራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَاتَّقُوا اللَّهَوَيُعَلِّمُكُمُ اللَّهُ وَاللَّهُبِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ}

ትርጉሙም (አላህንም ፍሩ፡፡ አላህም ያሳውቃችኋል፡፡ አላህም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡ ፡) ማለት ነው፡፡ የጥንት አበው እንድህ ይላሉ፡ ‹በቀሰመው እውቀቱ የሰራበት ሰው አላህ የማያውቀው የሆነን እውቀት ይሰጠዋል፡፡› ለመለኮታዊም ይሁን ለሃይማኖታዊ እውቀት እውን መሆን ሥራ ቅድመ መስፈርት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በከህፍ ምእራፍ ስለጻዲቁ ባሪያ ሲያብራራ እንድህ ይላል፡

{فَوَجَدَا عَبْدًا مِنْ عِبَادِنَاآتَيْنَاهُ رَحْمَةً مِنْ عِنْدِنَاوَعَلَّمْنَاهُ مِنْ لَدُنَّا عِلْمًا }

ትርጉሙም (ከባሮቻችንም ከእኛ ዘንድ ችሮታን የሰጠነውን ከእኛም ዘንድ ዕውቀትን ያስተማርነውን አንድን ባሪያ (ኸድርን) አገኙ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{فَفَهَّمْنَاهَا سُلَيْمَانَ وَكُلًّا آتَيْنَا حُكْمًا وَعِلْمًا}

ትረጉሙም (ለሱለይማንም (ትክክለኛይቱን ፍርድ) አሳወቅናት፡፡ ለሁሉም ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠን፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{يَا يَحْيَى خُذِ الْكِتَابَ بِقُوَّةٍ وَآتَيْنَاهُ الْحُكْمَ صَبِيًّا وَحَنَانًا مِّن لَّدُنَّا وَزَكَاةً وَكَانَ تَقِيًّا}

ትርጉሙም (የሕያ ሆይ! መጽሐፉን በጥብቅ ያዝ!» (አልነው)፡፡ ጥበብንም በሕፃንነቱ ሰጠነው፡፡ከእኛም የሆነን ርኅራኄ ንጽሕናንም (ሰጠነው)፡፡ ጥንቁቅም ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በመላእክት ልሳን እንድህ ይላል፡

{سُبْحَانَكَ لَا عِلْمَ لَنَا إِلَّا مَا عَلَّمْتَنَا.}

ትርጉሙም (ጥራት ይገባህ፤ ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም፡፡) ማለት ነው፡፡

ቀጣዩ የመማር ማስተማር ስርአት ደግሞ በአክብሮት የታነጸ መሆን የሚለው ነው፡፡ እውቀት ክብርና ግርማ መጎስ አለው፡፡ በመሆኑም አንድ ሙሁር ለመልካም ገጽታው፣ ለንጽህናውና ለመልካም ጠረኑ ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡ እንድሁም ከጨዋታ ቦታ መራቅ ይጠበቅበታል፡፡ ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ቅንን መንገድ መከተል፣ መልካም ገጽታን መጠበቅና ከነገሮች ሁሉ መጠነኛውን መከተል ከነብይነት አንድ ሃያ አምስተኛው ነው፡፡) አንድ ሙሁር ለጠያቂ ሰው እንደሐኪም ለህመምተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ለዘብተኛ ሊሆንለት፣ እጁን ይዞ ቅኑ መንገድ ሊያደርሰውና ትክክለኛውን መንገድ ሊያብራራለት ይገባል፡፡

ሙዓዊያ ኢብነልሐከም የተባሉት ባልደረባ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን ከነብየችን ጋር እየሰገድሁ ሳለ ከሰዎች አንደኛውን አስነጠሰው፡፡ እኔም አላህ ይማርህ አልኩኝ፡፡ ሰዎችም በዓይናቸው ገላመጡኝ፡፡ እኔም ዋ የናቱ ስቃይ! ለምን እንደዚህ ታዩኛለችሁ? አልኩኝ፡፡ እነሱም በጆቻቸው ጭኖቻቸውን መምታት ጀመሩ፡ ፡ እኔን ዘም ለማሰኘት እየጣሩ መሆኑን ተገነዘብኩና ዝም አልኩኝ፡፡ ስግደታቸውን በጨረሱ ጊዜ እናትና አባበቴን የማሳልፍላቸው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከርሳቸው በፊትም በኋላም እንደሳቸው ያለ አስተማሪ አይቼ አላውቅም፡፡ በአላህ ይሁንበኝ አልገላመጡንም አልመቱኝም አልሰደቡኝምም፡፡)

በተጨማሪም በተማሪ ሊሟሉ የሚገባ በርካታ ነገሮችም አሉ፡፡ ከነሱም መካከል ለትምህርት ተገቢውን ትኩረት መስጠት፣ ያለመሰላቸትና ያለመታከት በትምህርት ገበታ ዘወትር መገኘት፣ እንድሁም በማይጠቅም ነገር ጊዜውን አለማጥፍ የሚሉት ይካተታሉ፡፡ የጥንት አበው ‹እውቀት ከፊል አካሉን አይሰጥህም ሙሉ ትኩረትህን የምትሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡፡› ይላሉ፡፡ (አላህ ይዘንላቸውና) ኢማሙ አሻፊዒ ለእውቀት ያለዎት ፍላጎት ምን ይመስላል ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ‹በቃል ያለሰማሁትን ነገር እሰማለሁ፡፡ አካላቴ ሁሉ በሱ ጆሮዎች እንደሚረኩ ሁሉ የሚረኩበት መስሚያ ቢኖራቸው ይመኛሉ፡፡› አሉ፡፡ ለእውቀት የምትሰጡት ትኩረትስ ምን ይመስላል ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ‹በገንዘብ ለመርካት ገንዘብ ሰብሳቢና አጥብቆ ያዥ የሚሰጠው ትኩረት ዓይነት ነው፡፡› አሉ፡፡ እውቀተን በምን ዓይነት መልኩ ለመቅሰም ይጥራሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ‹ከሱ ሌላ ልጅ የሌላት ልጇን ያጠፋች ሴት እንድምትፈልግ ዓይነት ነው፡፡) አሉ፡፡ በተማሪ ሊሟላ የሚገባው ሌላው ጉዳ ደግሞ አስተማሪን ማክበር ነው፡፡ አንድ ተማሪ አስማሪውን በቃልም ሆነ በተግባር ሊዳፈረው አይገባም፡፡ አላህ ይዘንላቸውና ኢማሙ አሻፊዒ እንድህ ይላሉ፡ ‹ከኢማሙ ማሊክ ፊት በመሆንበት ጊዜ ወረቀትን ስገለብጥ በቀስታ ነበር፡፡ ይህውም የወረቀቱን ድምጽ እንዳይሰሙ በመፍራት ነው፡፡› አረቢእ የተባሉት የሻፊዒ ተማሪ ደግሞ ለሻፊዒ ከነበረኝ አክብሮት አንጻር አንድቀም አሳቸው እያዩኝ ውሃ ተጥቼ አላውቅም ይላሉ፡፡› አሕመድ ሸውቂ የተባሉት የግጥም ደራሲ እንድህ በማለታቸው ይደነቃሉ፡

ለአስተማሪህ ተነስና ሙሉ አክብሮትን ስጠው፡፡ አስተማሪኮ ያለህ መልክተኛ ሊሆን የተቃረበ ነው፡፡

እኛ በአሁኑ ወቅት የሃይማኖታችን ነገሮች እንዲስተካከሉ እውቀቶች የሚያስፈልጉንን ያህል የዚህች ዓለም ኑሮን ለማስተካል የሁሉንም ዓይነት ትምህርት ማካበት እጅጉን የሚያስፍለግን መሆኑ አያነጋግርም፡፡ ሳይንሳዊ ምርምርና ፈጠራ ጊዜውን ሁሉ የሚወስድ በመሆነ የምናጠፋው ወቅት ሊኖር አይገባም፡፡ ይህውም በእውቀት ምጥቀት እንዲንቀላቀል ወይም በጉዞው ካመለጠን ብዙ ነገር ጥቂቱን ለማካከስ እንድንችል ነው፡፡ ሁላችንም ለፈጠራና ለምርምር ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡ ያ ቢቀር ህብረተሰቡ በሁሉም ጥበና እውቀት የነበረውን የመሪነት ደረጃ ለማስመለስ ጽኑ ፍላጎት ሊያድርብን ተገቢ ነው፡፡ አባቶቻችን ይገነቡ እንደነበር ሁሉ እንገንባ የሚል አርማ አንግበን መንቀሳቀስም ግዴታችን መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡

እዚህ ላይ ታድያ አስተማሪም ሆነ ተማሪ መልካም ስነ ምግባር ሊላበሱ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተፈላጊውን ተጽእኖ ያሳድሩ ዘንድ ተግባራቸውና ቃላቸው የተጣጣሙ ሊሆን ይገባል፡፡ የጥንት ሙስሊሙ ህብረተሰብ አባላት እውቀት፣ ሥራና ስነ ምግባርን

አቀናጅተው በመንቀሳቀሳቸው በዓለም ህዝብ ውስጥ በክብርና በጉልህ ብልጽግና ይኖሩ ነበር፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡
* **

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**
የእስልምና እምነት ለእውቀትና ማንነታቸውም ቢለያይም ለሙሁራን ከፍተኛ ቦታ ስጥቷል፡፡ ጠቃሚ እውቀት ሲባል በዚህችም ዓለም ይሆን በመጭው ኣለም ለሰው ልጅ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም እውቀት ያካትታል፡፡ አንድህ የሚለው የአላህ ቃል፡
{إِنَّمَا يَخْشَىاللَّهَ مِنْ عِبَادِهِ الْعُلَمَاءُ}
ትርጉሙም (አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት ዐዋቂዎቹ ብቻ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ ስለዓለም ምንነት ማብራሪያ በሚሰጥበት እንድህ በሚለው አጠቃላይ ዝርዝር ተካቶ ነበር የተጠቀሰው፡
{أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ أَنْزَلَ مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَخْرَجْنَابِهِ ثَمَرَاتٍ مُخْتَلِفًا أَلْوَانُهَا وَمِنَ الْجِبَالِ جُدَدٌ بِيضٌ وَحُمْرٌ مُخْتَلِفٌ أَلْوَانُهَاوَغَرَابِيبُ سُودٌ * وَمِنَ النَّاسِ وَالدَّوَابِّوَالأَنْعَامِ مُخْتَلِفٌ أَلْوَانُهُ كَذَلِكَإِنَّمَا يَخْشَى اللَّهَمِنْ عِبَادِهِ الْعُلَمَاءُإِنَّاللَّهَ عَزِيزٌغَفُورٌ}

ትርጉሙም (አላህ ከሰማይ ውሃን ማውረዱን አላየህምን? በእርሱም ዓይነቶቻቸው የተለያዩ ፍሬዎችን አወጣን፡፡ ከጋራዎችም መልኮቻቸው የተለያዩ ነጮች፣ ቀዮችም፣ በጣም ጥቁሮችም የኾኑ መንገዶች አልሉ፡፡ ከሰዎችም፣ ከተንቀሳቃሾችም፣ ከቤት እንስሳዎችም እንደዚሁ መልኮቻቸው የተለያዩ አልሉ፡፡ አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት ዐዋቂዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ አላህ አሸናፊ መሓሪ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡
{إِنَّ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِوَالأَرْضِ وَاخْتِلاَفِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِلآَيَاتٍلأُولِي الأَلْبَابِ الَّذِينَ يَذْكُرُونَاللَّهَ قِيَاماًوَقُعُوداًوَعَلَى جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِوَالأَرْضِ.}

ትርጉሙም (ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ፡፡ እነርሱም እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣

በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡-..) ማለት ነው፡፡
ጠቃሚ እውቀት ስንልም እንደየህግ ትምህርት፣ የዓረበኛ ቋንቋ፣ የህክምና ጥናት፣ የፊዚክስ፣ የኬሚስትሪ፣ የሥነ ፈለክ፣ የምህንድስና፣ የሃይል ምንጭና ሌሎችም ትምህርቶችና እውቀቶች ይካተታሉ፡፡ እውቀት የአንድ ፈጣሪና ተፈላሳፊ አገር ማንነት ነው፡፡ ለዚህም አላህ (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَاسْأَلُوا أَهْلَ الذِّكْرِ إِنْ كُنْتُمْ لَا تَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም (የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡) ማለት ነው፡፡ በአንቀጹዋ -እውቀት- የሚለው ቃል አንድ የተወሰነን እውቀት ብቻ አይጠቁምም፡፡ በመሆኑም ነገሩ ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆነን ማንኛውንም ትምህርት ያጠቃልላል ማለት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው እኛ ሁላችንም አገርን ለመንገባት ሁሉንም ትምህርት መቅሰም ያስፈልገናል፡፡ ከዚህ ላይ የእምነቱ ሊቃውንት በሃይማኖት ትምህርት ስለእስልምናና ሙስሊሞች የተሰራጩ የተሳሳቱ ግንዛቢዎችን የማስተካከልና ትክክለኛውን ግንዛቤ ማሳወቅና ማስፋፋት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን መጠቆም አስፈላጊ ነው እንላለን፡፡
ከነዚያ በዚህ ዘርፍ ጥረት ከሚያደረጉት ሰዎች እንድንሆን፣ የማናውቀውን እንዲያሳውቀን፣ የረሳነውንም እንዲያስታውሰን ለኛም ከነገራችን ቅንን አድርግልን አላህን እንለምናለን፡፡ አሜን፡፡

**( 16)**

## የአንብብና ... የአሳምር ህብረተሰብ
## ከህብረተሰቡ ሙሁራንና ከሁከት ፈጣሪ ሙሁራን መካከል

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{قُلْ هَلْ يَسْتَوِي الَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَالَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُولُو الْأَلْبَابِ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም («እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይስተካከላሉን?» በላቸው፡፡ የሚገነዘቡት ባለ አእምሮዎቹ ብቻ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የእስልምና እምነት እውቀትን እንድናካብት እንድሁም እውቀትን ለመግብየት ጥረትና ትግል እንድናደርግ ይገፋፋናል፡፡ ለዚህ ዋና መረጃ የሚሆነው መጀመሪያ በነብዩ ላይ (ሶ.ዐ.ወ.) የወረዱት አንቀጾች የሚከተሉት መሆናቸው ነው ሲሉ ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡

**{اقْرَأ بِاسْمِ رَبِّكَ الَّذِي خَلَقَ * خَلَقَ الْإِنسَانَ مِنْ عَلَقٍ * اقْرَأ وَرَبُّكَ الْأَكْرَمُ * الَّذِي عَلَّمَ بِالْقَلَمِ * عَلَّمَ الْإِنسَانَ مَا لَمْ يَعْلَمْ}**

ትርጉሙም (አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ፡፡ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ማለትም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰማይ በትንቢት የወረደው ትእዛዝ አንብብ የሚል ሲሆን ንባብ ከእውቀት በሮች የመጀመሪያው በር ነው፡፡ ከዚያም አንቀጾቹ እወቀትን በማህደር ለማስፈርም ሆነ ከትውልድ ወደትውልድ ለማሸጋገር ዋና መሳሪያ የሆነውን ብእርን ጠቁመዋል፡፡ ይህም የሆነው ለመላው የሰው ልጅ  የእውቀትን የበላይነት ለማሳወቅ፣ እውቀትን ለማካበትም ጥረት እንዲያደርጉ ለመገፋፋት ነው፡፡ ከዚያም አልፎ የእስልምና እምነት የእውቀትና የግንዛቤ እምነት መሆኑን እንድሁም ሙስሊሙ ህብረተሰብ የእውቀት፣ የስልጣኔና ግንባታ ህዝብ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ ራሱን የቻለ በበእር የጠሰየመ ምእራፍ አለ፡፡ ይህን ምእራፍ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ነው የጀመረው፡

**{ن * وَالْقَلَمِ وَمَا يَسْطُرُونَ}**

ትርጉሙም (ነ.(ኑን)፤ በብርእ እምላለሁ በዚያም (መልአኮች) በሚጽፉት፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህውም የትምህርት መሳሪያዎችና የመማሪያ ዘደዎች እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ለእውቀት ክብር ታላቅነት አላህ (ዐ.ወ.) ነብዩ በዚህች ዓለም ከእውቀት እንጂ ከአንድም ነገር ጭማሬን እንድፈልጉ አለማዘዙ ብቻውን በቂ ነው፡፡ ይላሉ ሊቃውንት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَقُلْ رَبِّ زِدْنِي عِلْمًا}**

ትርጉሙም (ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ» በል፡፡) ማለት ነው፡፡

ይልቁንም ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እውቅት ፍለጋ መውጣትን በአላህ መንገድ መውጣት ነው ብለውታል፡፡ እንድሁም እወቀትን ለመቅስም ጥረት ማድረግ ጀነት ከሚስገቡ ነገሮች አንዱ መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (እውቀትን ለመፈለግ የወጣ ሰው እስኪመለስ ድረስ በአላህ መንገድ ላይ ነው)፡፡ በሌላ ሐድስም እንድህ ብለዋል፡ (እውቀት ማግኘትን አስቦ መንገድ የጀመረ ሰው አላህ ወደጀነት የሚያደርስን መንገድ ቀኝ በቀኝ ያደርግለታል)፡፡ እውቀት ሀገራትን ለመገንባት ከሚያስፈልጉ መዋቅሮች አንደኛው አምድ ነው፡፡ በሱም ህዝቦች ህዳሴን እውን ያደርጋሉ ይበለጽጋሉም፡፡ በሱም አንድ ሰው ከፍተኛን ቦታ ያገኛል ደረጃውም ከፍ ይላል፡፡

ቅዱስ ቁርኣን ሞያቸው የተለያየ ቢሆንም የሙሁራን ደረጃ ታላቅ መሆኑን ሲገልጽ እንድህ ይላል፡

يَرْفَعِ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَالَّذِينَ أُوتُوا الْعِلْمَ دَرَجَاتٍ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ}

ትርጉሙም (አላህ ከናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም ዕውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች ከፍ ያደርጋል፡፡ አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.)እሱን ከሚፈሩ ሰዎች ተቀዳሚዎቹ ሙሁራን መሆናቸውን ሲመሰከርላቸውም እንድህ ብሏል፡

{نَّمَا يَخْشَى اللَّهَ مِنْ عِبَادِهِ الْعُلَمَاءُ إِنَّ اللَّهَ عَزِيزٌ غَفُورٌ}

ትርጉሙም (አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት ዐዋቂዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ አላህ አሸናፊ መሓሪ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

የሙሁራን ደረጃ ከፍ ያለና ታላቅ ቦታ የሰጣቸው መሆኑንም እንድህ በማለት በታላቅ ምስክሩ አካቷቸዋል፡

شَهِدَ اللَّهُ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَالْمَلَائِكَةُ وَأُولُو الْعِلْمِ قَائِمًا بِالْقِسْطِ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ} .

ትርጉሙም (አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ፡፡ መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)፡፡ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን ጉዳይ ሲያረጋግጡ ሙሁራን ለሰዎች ቅኑን መንገድ በመምራት እጃቸውን ይዘውም ወደእውነትና ብሩህ መንገድ በማድረስ እንድሁም በማስተካከልና በግንባታ ዘርፍ የነብያት ወራሾት መሆናቸውን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (በእርግጥ ሙሁራን የነብያት ወራሾች ናቸው፡፡ ነብያትም ድናርንም ይሁን ድርሃምን አላወረሱም፡፡ ነገር ግን ያወረሱት እውቀትን ነው፡፡ እሱን የያዘ ሰው ሰፊ እድልን ያዘ፡፡) በሌላም ሐዲስም እንድህ ብለዋል፡ (ሙሁር ለአምልኮት የጠቀመጠን ሰው የሚበልጠው ሙሉ ጨረቃ ሌሎችን ከዋክብት እንደሚበልጥ ዓይነት ነው፡፡)

አላህ (ዐ.ወ.) ያላቃቸውና ደረጃቸውን ከፍ ያደረገላቸው እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ያሞገሷቸው ሙሁራን እነሱ እነዚያ ታማኝ የሆኑት የህብረተሰቡ ሙሁራን ሲሆኑ የእውቀትን፣ የሰበካንና የማብራራትን አደራ በሚገባ ያደረሱት ሙሁራን መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ንግግሬን ሰምቶና በቃል ይዞ ልክ እንደሰማው አድረጎ ለሌላ ሰው ያደረሰን ሰው አላህ ፊቱን ያሳምርለት)፡፡

ታማኝ የማህበረሰቡ ሙሁራን የሚባሉት እነዚያ ስለሱ አላህ የመረጣቸውን ሃላፊነት ምንነት በጥልቅ የተገነዘቡት አንድሁም ይህ ሃላፊነት በእውቀት ብቻ ሊውጡት የማይችል ጉዳ መሆኑን የተረዱት ሙሁራን ሲሆኑ የሚያደርሱት መልእክት ከዚያ በጣም የላቀ መሆኑንም የሚያውቁት ሙሁራን ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ይህን ጉዳይ በነብያችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ልሳን ሲገልጽ እንድህ ብሏል፡

{قُلْ مَاأَسْئَلُتُكُمْ مِنْ أَجْرٍ فَهُوَ لَكُمْ إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى اللّٰهِ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ}

ትርጉሙም («ከዋጋ ማንኛውም የጠየቅኋችሁ ቢኖር እርሱ ለእናንተው ነው፤ ዋጋዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነው» በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{قُلْ مَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ إِلَّا مَنْ شَاءَ أَنْ يَتَّخِذَ إِلَى رَبِّهِ سَبِيلًا}

ትርጉሙም (በእርሱ ላይ ዋጋን በፍጹም አልጠይቃችሁም፡፡ ግን ወደ ጌታው (መልካም) መንገድን ለመያዝ የሻ ሰው (ይሥራ)» በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

እንድሁም በነብዩ ኑሕ፣ በነብዩ ሁድ፣ በነብዩ ሷሊሕ፣ በነብዩ ሉጥና በነብዩ ሹዓይብ ልሳን እንድህ ይላል፡

{وَمَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى رَبِّ الْعَالَمِينَ}

ትርጉሙም (በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፡፡ ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም፡፡) ማለት ነው፡፡

እውነተኛ የህብረተሰቡ ሙሁራን የሚባሉት እነዚያ ጊዜያቸውንና ጥረታቸውን ልህብረተሰቡ የቸሩት እንድሁም እውቀታቸውን ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው አገልግሎት ያዋሉት፣ ሰዎችም በመቻቻልና መተዛዘን የተሞላውን ለዘብተኛ መስመር እንዲዙ ያገዙት ሙሁራን ሲሆኑ ጥረታቸው ፍሬያማ ሆኖ የሚያፈርስ ሳይሆን የሚገነባን፣ የሚያበላሽ ሳይሆን የሚያለማን እንድሁም ውብ የሰብአዊ እሴቶችን የሚያሳደግን፣ የሰውን ልጅ ክብር ከፍ የሚያደርገውን ከማንም ሰው ጋር በመቻቻል፣ በሰላምና ጸጥታ ያለማደፍረስ የሚኖርን ጠቃሚ ትውልድ አዋቅሯል፡፡

ይህም ነው እንግድህ አንድ ሰው ከሞትም በኋላ ድልብ ይሆነዋል የተባለው ጠቃሚ እውቀት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የሰው ልጅ ሲሞት ከሦስት ነገሮች በስተቀር ሥራው በሙሉ ይቋረጣል፡፡ (እነሱም) ዘላቂነት ያለው ምጽዋት፣ ወይም ሰዎች የሚጠቀሙበት እውቀት ወይም ጸሎት የሚያደርግለት ጻዲቅ ልጅ)

ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አላህ ከማይጠቅም፣ ከማይገነባ፣ ከማያለማ ስነ መግባርን ወይም ስርአትን ከማያበጅ እውቀት እንዲጠብቃቸው ይለምኑት ነበር፡፡ እንድሁም ለባልደረቦቻቸውም (አላህ ጠቃሚን አውቀት እንዲሰጣችሁ ለምኑት፡፡ እንድሁም ከማይጠቅም እውቀት በአላህ ተጠበቁ) እያሉ ይመክሩ ነበር፡፡ እንድሁም እንድህ በማለት ይጸልዩ ነበር፡

(اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عِلْمٍ لاَ يَنْفَعُ ، وَمِنْ قَلْبٍ لاَ يَخْشَعُ ، وَمِنْ نَفْسٍ لاَ تَشْبَعُ ، وَمِنْ دَعْوَةٍ لاَ يُسْتَجَابُ لَهَا) .

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ፡፡ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እተይቃለሁኝ

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ታማኝ የህብረተሰቡ ሙሁራን የሚባሉት ትክክለኛውን መመሪያ የያዙት፣ ቅንን መንገድ የተከተሉትና ምጥን ለዘብተኝነትን የተላበሱት እነዚያ በማንኛውም ጊዜና ቦታ የአጋናኞችን ማጣመም፣ የአላዋቂዎችን አንድምታና የአበላሾችን ማስመሰል ከአላህ ሃይማት ለመከላከል የልከኝነትን ስንደቅ ዓላማ አንግበው የሚጓዙት ናቸው፡፡

የህውከት ፈጣሪ ሙሁራን የሚባሉት ደግሞ እነዚያ ፍላጎታቸውን ለማሟላትና የግል አላማቸውን  እውን ለማድረግ የአላህን ሃይማኖት መሸጋገሪያ ድልድይ ያደረጉት የአላህን (ዐ.ወ.) ሃይማኖት ክብር በመዳፈር ጥቅም የሌላቸውንና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ከአንድነት ይልቅ መለያየትን፣ ከመገንባት ይልቅ ማፍረስን የሚያስከትሉ ሃይማኖታዊ ብያኔዎችን የሚያናፍሱት ናቸው፡፡ እነዚህ ሙሁራን በዚህ ዓይነቱ ተግባራቸው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሱ አንዳንገባ የከለከሉትን ሰዎችን ከሃዲ የማደረግን በር ይከፍታሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ማንኛውም ሰው ሙስሊም ወንድሙን አንተ ከሃዲ! ካለ ከሁለት አንደኛቸው ከሃዲ ይሆናል፡፡ እንዳለው ከሆነ ሰውዬው ካሃዲ መሆኑ ይረጋገጣል እንዳለው ካልሆነ ደግሞ ወደሱ ይመለስበትና እሱ በዚህ ቃሉ ብቻ ወደከህደት ይገባል)፡፡

ህውከት ፈጣሪ ሙሁራን ማጥበቅን፣ ግትርነትንና በሰዎች ላይ ነገሮችን ማጠበብን ስረርአተ ሕይዎታቸው አደርገው ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ ይህ ስርአት ደግሞ ከገራገሩና ከልከኛው የእስልምና ስርአት እጅጉን የራቀ ስርአት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ከሰዎች ላይ ጭንቀትን አንስቷል ችግርንም አስወግዷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينِ مِنْ حَرَجٍ }

ትርጉሙም (በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ብስራት ስጡ እንጂ አታደንብሩ አቃሉ እንጂ አታካብዱ)፡፡ በሃይማኖታዊ ብያኔ ነገሮችን ማካበድ የእስልምና እምነት ከሚለይበት ከልከኘነት ጋር ይፃረራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَكَذَلِكَ جَعَلْنَاكُمْ أُمَّةً وَسَطًا لِتَكُونُوا شُهَدَاءَ عَلَى النَّاسِ}

ትርጉሙም (እንደዚሁም (እንደመራናችሁ) በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑና መልክተኛውም በናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ምርጥ ሕዝቦች አደረግናችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

ልከኛነት ማለት ፍትህ ሲሆን ለህዝቦች ጥፋት ምክኒያት ከሚሆነው ከማጋነን መራቅ ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እናንተ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖት ከማጋነን ተጠንቀቁ ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ያጠፋቸው በሃይማኖት ማጋነናቸው ነው)

ሱፍያን አሰውሪ የተባሉት ሊቅ እንድህ ይላሉ፡ ‹እኛ ዘንድ እውቀት ማለት በህግ የተፈቀዱ ነገሮችን ለይቶ ማወቅ ነው፡፡ ማክረርንማ ማንኛውም ሰው ሊፈጽመው ይችላል፡፡›

እነዚያ ያለእውቀት በሚሰጡት ቃል የሰዎችን አመለካከት የሚያዘበራረቁ ሙሁር ነን ባዮችም ከህውከት ፈጣሪ ሙሁሮች ይመደባሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ማህበረሰቡ ምንም ቢሆን ምን ምክኒያትን መጠቀም እጅግ የሚያስፈልገው መሆኑን የዘነጉ ከመሆናቸውም ባሻገር ይህችን ዓለም ማልማት ከሃማኖት ዋና ዋና አላማዎች አንደኛው መሆን ያልተገነዘቡ፣ ህዝቦች በዓለማዊ ጉዳዮቻችን የበላይነትን ካልያዝን ሊያከብሩን የማይችሉ መሆኑን ያልተረዱ የማህበረሰቡ ክፍል ናቸው፡፡ ይህን ሁሉ ምስጢር ያልተረዱት ሙሁር ነን ባዮች በደፈናው በዚህች ዓለም ከመሸንገል ራቁ እያሉ የሚሰጡት መግለጫ በተራው ህዝብ ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡ በመሆኑንም በዚህች ዓለም ከመታለል መዳን ማለት እሷን እርግፍ አድርጎ መተውና ከሰዎች ራስን ማግለል አደርገው ወስደውታል፡፡ ይህውም እንድህ የሚለውን የአላህን ቃል በመዘንጋት ነው፡፡

{رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ}.

ትርጉሙም (ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን» የሚሉ ሰዎች አልሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የምንፈልገው ነገር ቢኖር ብቃት ሳይኖረው ሃይማኖታዊ ብያኔ በመስጠት መዳፈር ጠሞ ማጥመም መሆኑን ነው፡፡ በርካታ ያለእውቀት የሚሰጡ ሃይማኖታዊ ብያኔዎች በሰዎች ሕይወት ላይ ወሰን የሌላቸው ችግሩችን ሲያስከትሉ ተስተውሏል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር ኢብን አብደላህ

የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹በአንድ ወቀት መንገድ ወጣን፡፡ ከኛ መካከል አንድ ሰውዬ ራሱን ድንጋይ ፈነከተው፡፡ በተናም ጊዜ በህልሙ ፍተወት ፈሰሰው፡፡ ባልደረቦቹን መታጠብ ስለሚያስፈራኝ ተየሙም ማድረግ እችል እንደሆነ የሚያውቅ ሰው የለም? ሲል ጠየቀ፡፡ አነሱም አንተ ውሃን ሳታጣ ተይሙምን የሚፈቅድ ነገር አናውቅም አሉት፡፡ እሱም ታጠበና አደጋው ለህልፈተ ሕይወት አደረሰው፡፡ በተመለስንም ጊዜ ለነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ተነገራቸው፡፡ እሳቸውም ((ገደሉት አላህ ይግደላቸውና ካላወቁ ታዲያ አይጠይቁም ነበር፡፡ የህመምመ ፈውሱኮ መጠየቅ ነው፡፡ እሱኮ ተየሙም ማድረግ፣ ቁስሉን በራፊ አስሮ እሱን ማበስና ቀሪ አካላቱን ማጠብ ይበቃው ነበር)፡፡

እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት ለያንዳንዱ በሞያው ተወስኖ መስራት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ በዚህም አላህን የፈራን እውቀትንም ያከበርንና የቃልን አደገኛነት የተገነዘብን እንሆናለን፡፡ አያሌ ቃላት ያለእውቀት በመሰንዘራቸው ወሰን የለሽ መፈራረስ፣ ውድመትና ብልሹነት አስከትለዋል፡፡ ጎጂ ቃልን ከመሰንዘር ዝምታ ይመረጣል ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንደደህ ይላሉ፡ (... በአላህና በመቸረሻውም ቀን የሚያምን ሰው ደግን ነገር ይናገር አለዚያም ዝም ይበል)፡፡

ጌታችን ሆይ እውነትን እውነት አድርገህ አሳየን እሱን መከተልንም ስጠን፡፡ ብልሹንም ብልሹ አድርገህ አሳየን ከሱም መራቅን ስጠን፡፡ የሚጠቅመንን አሳውቀን በአሳወቅህንም ጥቀመን ሀገራችንንም ጠብቅልን አሜን፡፡

# (17)

## በአሁኑ ዘመን ያለው የደህንነት ቃል  ኪዳን ግንዛቤ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَأَوْفُوا بِالْعَهْدِ إِنَّ الْعَهْدَ كَانَ مَسْؤُولاً }

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በኪዳናችሁም ሙሉ ኪዳን የሚጠየቁበት ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው(ከአላህ ባሮች ከአላህ ዘንድ ምርጦቹ እነዚያ ቃላቸውን የሚያከብሩና የሚያሳምሩት ናቸው፡፡) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡ ፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ

ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የእስልምና እምነት የጸጥታና የደህንነት፣ የአማንና የሰላም የበጎ ሥራና የመልካም ምግባር ሃይማኖት ነው፡፡ ቃል ኪዳንን ማክበር ታላቅ የሥነ ምግባርና ሰብአዊ እሴት መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ በቃል ኪዳን ማክበር ከህዝቦች መካከል አመኔታ ይስፋፋል፣ ጽጥታና ደህንነትም ይረጋገጣል፣ እንድሁም ከአንድ ማህበረሰብ ልጆች መካከል ያለው ትብብር፣ ፍቅር፣ እድገትና ብልጽግና ይጠናከራል፡፡ ለዚህም ነው ቃል ኪዳንን ማክበር ከእምነት አላባዎች አንደኛውና የታማኝነትና የመልካም ምግባር ምልክት ነው የተባለው፡፡ ቃልን ማክበር ፈጣሪ ለአንድ ሰው የሚቸረው ታላቅ ስርአት፣ ነብያዊ የተከበረ ስነ ምግባርና ቅን እስላማዊ ሥነ ስርአት ነው፡፡

የእስልምና እምነት ተካታዮቹ ማንኛውንም ቃል ኪዳን፣ ውልና ስምምነት እንዲያከብሩ ያዛል፡፡ ይህንም እውነት አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል አረጋግጦታል፡፡

{وَأَوْفُوْا بِالْعَهْدِ إِنَّ الْعَهْدَ كَانَ مَسْؤُولاً}

ትርጉሙም ( በኪዳናችሁንም ሙሉ ኪዳን የሚጠየቁበት ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَأَوْفُوا بِعَهْدِ اللهِ إِذَا عَاهَدتُّمْ وَلاَ تَنقُضُوا الأَيْمَانَ بَعْدَ تَوْكِيدِهَا وَقَدْ جَعَلْتُمُ اللهَ عَلَيْكُمْ كَفِيلاً إِنَّ اللهَ يَعْلَمُ مَا تَفْعَلُونَ}

ትርጉሙም (ቃል ኪዳንም በገባችሁ ጊዜ በአላህ ቃል ኪዳን ሙሉ፡፡ መሃሎቻችሁንነም ከአጠናከራችኋቸው በኋላ አላህን በናንተ ላይ በእርግጥ ምስክር ያደረጋችሁ ስትሆኑ አታፍርሱ፡፡ አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ያውቀልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ማለትም ከእናንተና ከአላህ (ኢ.ወ.) መካከልም ይሁን ከናንተና ከሰዎች መካል በራሳችሁ ላይ ግድ ያደረጋችሁትን ቃል ከማክበር ወደኋላ አትበሉ፣ ለመሃላዎቻችሁም የአላህን ስም በመጥራት እሱን መስክር በማድረግ ካረጋገጣችኋቸው በኋላ አታፍርሱ፣ እንድ ሰው በማንኛውም መልኩ ውል ከፈረመ ውሉን ማክበር አለበት፣ ቃለም የገባ ሰው በቃሉ የመገኘት ግዴታ አለበት ማለት ነው፡፡

ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ (ኢ.ወ.) ቃል ኪዳናቸውንና ውላቸውን የሚያከብሩ ቃል ኪዳን አክባሪዎች የሱ ወዳጆች እንድሁም ከፍጥራታቱ መካከል ፈሪሀ አላህና እውነተኞቹ መሆናቸውን እንድህ በማለት ገልጧል፡

{بَلَى مَنْ أَوْفَى بِعَهْدِهِ وَاتَّقَى فَإِنَّ اللهَ يُحِبُّ الْمُتَّقِينَ}

ትርጉሙም (አይደለም (ማወቅ አለባቸው እንጅ) በቃል ኪዳኑ የሞላና የተጠነቀቀ ሰው አላህ ጥንቅቆችን ይወዳል፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَاهَدُوا وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاء والضَّرَّاء وَحِينَ الْبَأْس أُولَـئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَأُولَـئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ}

ትርጉሙም (ቃል ኪዳን በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር፣ በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን) እነዚህ እነዚያ እውነትን ያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ አነርሱ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ጀ.ሸ.) ለእነሱ ታላቅ ምንዳ የተዘጋጀላቸውና የተከበሩ ሆነው ገነትን የሚወርሱ መሆኑን እንድህ በማለት ገልጧል፡

{وَمَنْ أَوْفَى بِمَا عَاهَدَ عَلَيْهُ اللَّهَ فَسَيُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا}

ትርጉሙም (በርሱ ላይ አላህን ቃል ኪዳን የተጋባበትን የሞላ ሰው ታላቅ ምንዳ በእርግጥ ይሰጠዋል፡፡) ማለት ነው፡፡

በሌላ አንቀጽም እንድህ ብሏል፡

{وَالَّذِينَ هُمْ لِأَمَانَاتِهِمْ وَعَهْدِهِمْ رَاعُونَ *وَالَّذِينَ هُمْ بِشَهَادَاتِهِمْ قَائِمُونَ *وَالَّذِينَ هُمْ عَلَى صَلَاتِهِمْ يُحَافِظُونَ *أُولَئِكَ فِي جَنَّاتٍ مُكْرَمُونَ.}

ትርጉሙም (እነዚያ እነሱ አደራዎቻቸውንና ቃል ኪዳናቸውን ጠባቂዎች የሆኑት፡፡ እነዚያም እነሱ በምስክርነታቸው ትክክለኞች የሆኑት፡፡ እነዚያም እነሱ በሶላቶቻቸው ላይ የሚጠባበቁት፡፡ እነዚህ (ከዚህ በላይ የተወሱት ሁሉ) በገነቶች ውስጥ የሚከበሩ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የቃል ኪዳን ማክበር እሴት እጅክ ከፍተኛ መሆኑን በገለጹበት ወቅት ውልን ከማፍረስና ቃል ኪዳንን ካለማክበር በጥብቅ አስጠንቀቀዋል፡፡ ቃልን በሙብላትና ውልን በማፍረስ በማህበረሰቡ መካከል ብልሹነት የሚስፋፋ፣ ከሰዎች መካከል አመኔታ እንደሚጠፋና አደራዎች ከንቱ እንደሚቀሩም እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (የምናፍቅ መለያዎች ሦስት ነገሮች ናቸው፡ ሲያወራ ይዋሻል፡፡ ቃል በሚገባም ጊዜ ቃሉን አያከብርም፡፡ አደራም ሲሰጠው ይክዳል፡፡) እንድሁም አንድህ ይላሉ፡ (ሙስሊሞች ባስቀመጡት መስፈርት ይወሰናሉ፡፡ መስፈርቱ እርምን የተፈቀደ፣ ወይም የተፈቀደን ነገር እርም ያደረገ እስካልሁነ ድረስ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የከዳተኛ ሰው ቅጣት ከፍተኛ መሆኑን እንድህ በማለት አስጠንቅቀዋል፡ (አላህ (ሱ.ወ.) በቂያማ እለት የመጀመሪያዎቹንም የመጨረሻዎቹንም በሚሰበስብ ጊዜ ለያንድንዱ ከዳተኛ ሰንደቅ ይተከልለትና ይህ የእገሌ ልጅ የእገሌ ክዳት ነው በመባል ይለፈፋል፡፡ ኢብን ከሲር የተሰኙት ሊቅ ይህ የሆነበት ጥበብ ክዳት በዚህች አለም አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ሳያዩ በደብቅ የሚፈጸም በመሆኑ በቂያማ እለት ሁሉም የሚያየው ሰንደቅ ይሆናል፣ በዚህ መልኩም ሰዎች ይደበቁት የነበረው ክዳትና ሴራ ይፋ ወጥቶ አላህ (ኢ.ወ.) ከዳተኞችን በፍጥረታት ፊት በአደባባይ ያዋርዳቸዋል ማለለት ነው ይላሉ፡፡

ሃማኖታዊ ህግጋት እንድናከብራቸው ካዘዙንና እንዳናፈርሳቸውም ካስጠነቀቁን ቃል ኪዳኖች መከካል አንዱ የድህንነት ቃል ኪዳን ነው፡፡ የደህንነት ቃል ኪዳን ማለት ባለነበት ዘመን ግንዛቤ አንድ አገር ለአንድ የለሌላ አገር ዜጋ የሚሰጠው የመግቢያ ፈቃድ ወይም ቪዛ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ለቶሪስት፣ ለጉብኝት ወይም ለመኖር የሚሰጠው የመግቢያ ፈቃድ ደፐሎማቶችንና መሰሎቻቸውን አስመልክቶ

በተቀመጡት አለም አቀፍ ደንቦች፣ ውሎችና ስምምነቶች መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ የዚህ ፈቃድ መሰረት አስተናጋጅ አገር በሀገር ውስጥ የሚሰራበትን ህግና ደንብ መሰረት ያደረገ ሆኖ ከሁለት አገሮች መካከል ያለ የሁለትዮሽ ስምምነት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ግለሰብ ወደአንድ አገር መግቢያ ወይም በዚያ አገር ለመኖር ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በዚያ አገር ድንበር ክልል ውስጥ የነዋሪዎች መብትና ክብር ይኖረዋል፡፡ ይህን ቃል ኪዳን የሰጠው አገርም ለዜጎች የሚሰጠውን መብትና ግዴታ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህን ቃል ኪዳን ማፍረስ፣ ከፊል መብቱን ለማገድ ምክኒያት መፍጠርም ሆነ መላ መብቱን ማገድ በሃይማኖቱ ደንብም ሆነ በህጉ መሰረት አይፈቀድም፡፡

ያ እንግዳ የሀገሩን ጸጥታ የሚያደፈርስ ወይም ህዝባዊ ስርአቱን የሚፃረር መስሎ የሚታይ ነገር ሲፈጽም አንድ ተራ የሀገሪቱ ዜጋ ቢመለከት  ጉዳዩን አጥንቶ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት እንድፋረደው ለሚመለከተው የመንግስት ክፍል ከማሳወቅ ሌላ ምንም ማድረግ አይችልም፡፡ ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ ያ እንግዳ ስለፈጸመው ነገር የራሱ የሆነን ውሳኔ የማሳለፍና ለአደጋ የማጋለጥ መብት የለውም፡፡ አለዚያ ነገሮች ሁሉ ወደስርአት አልባነት ይላወጣሉ፡፡

የዚህ ዓይነቱን ቃል ኪዳን ማክበር ከሃይማኖት፣ ከህግ፣ ከሀገራዊና ከሰብአዊ መብት አንፃር የግዴታዎች ግዴታ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ቅኑ ሃይማኖታችን የደህንነትን ቃል ኪዳን ምንነት በጣም ከፍ ባደረገበት ወቅት በዚህ ጉዳይ የሙስሊሞች ኪዳን አንድ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡ ይህን ማለትም አንድ ሙስሊም በራሱ ላይ የሚቆርጠው ቃል ኪዳን መላ ሙስሊሞች የማክበር ግዴታ አለባቸው ማለት ነው፡፡ ነገሩ እንድህ ከሆነ ይህ የሃይማኖት ህግና ደንብ በአንድ ላይ ተባብረው አጠቃላይ ውል ያደረጉት ቃል ኪዳን (ቪዛ) በይበልጥ ሊከበር ይገባል፡፡ በመሆኑም ይህን ቃል ኪዳን ማክበር፣ አለማፍረስ፣ አለማጠፍ እንዲያውም እሱን ለአደጋ ማጋለጥ  የማይፈቀድ መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡

የእስልምና እምነት ቃል ኪዳንና ውሎች የማክበር ሃማኖት ሲሆን ማታለልን፣ ማምታታትንና ክዳትን አያውቅም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደእስልምና ጥሪ ማድረግ ከጀመሩ ጀምሮ እንደሁም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ከባልደረቦቻቸውም አንድንም ሰው ደህንነቱን የተጋፉ፣ ወይም የሰጡትን የደህንነት ቃል ኪዳን ያፈረሱ መሆኑን የሚያረግጥ ምንም ዓይነት መረጃ የለም፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَإِمَّا تَخَافَنَّ مِن قَوْمٍ خِيَانَةً فَانبِذْ إِلَيْهِمْ عَلَى سَوَاء إِنَّ اللّهَ لاَ يُحِبُّ الخَائِنِينَ}

ትርጉሙም (ከሕዝቦችም ክዳትን ብትፈራ (የኪዳንን መፍረስ በማወቅ) በመተካከል ላይ ሆናችሁ ኪዳናቸውን ወደነሱ ጣልላቸው አላህ ከዳተኞችን አይድምና፡፡) ማለት ነው፡፡ ስይድና ሙዓዊያ ቢን አቡ ሱፈያን ከሩማኖች ጋር ቃል ኪዳን በተጋቡበት ወቅት ሙዓዊያ ወደሮማናዊያን ድንበር ጦር ልከው የቃል ኪዳኑ ወቅት እንዳለቀ በድንገት ጥቃት ሊጥሉባቸው አሰቡ፡፡ ጉዞ እንደጀመሩም ከኋላቸው አንድ የነብያችን

(ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረባ አላህ አክበር አላህ አክበር ቃልን ማክበር እንጅ ክዳትን ምን አመጣው እያሉ ደረሱባቸው፡፡ ዞር ብለው ሲመለከቱ ዐምር ኢብን አብሳ የተባሉት ባልደረባ ናቸው፡፡ ሙዓዊያም ወደርሳቸው እንዲመጡ ላኩባቸው፡፡ ሲመጡም ጊዜ ምን ማለትህ ነው ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ እሳቸውም እንድህ አሉ ‹የአላህ መልክተኛ እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (ከሱና ከሰዎች መካከል ቃል ኪዳን ያለበት ሰው ጊዜው አስከሚያልቅ ድረስ ቁጥሩን አያጥበቅ ወይም አይፍታ ወይም የተተካከለ ሲሆን ወደነሱ ቃል ኪዳናቸውን ይጣልላቸው፡፡)› በዚያን ጊዜ ሙዓዊያም ከእቅዳቸው ተመለሱ፡፡

ይልቁንም የእስልምና ታላቅነት በጣም ጎልቶና ብሩህ ገጽታውም በይፋ የሚታየው አላህ (ሱ.ወ.) ነብዩ  አጋሪ ብሎም ተዋጊ እንኳን ቢሆንም መጠለያ የፈለገን ሁሉ እንዲያስጠጉና ደህንነቱን እንዲያስከብሩ እንድህ ሲል ባዘዘበት ወቅት ነው፡

{وَإِنْ أَحَدٌ مِنَ الْمُشْرِكِينَ اسْتَجَارَكَ فَأَجِرْهُ حَتَّى يَسْمَعَ كَلَامَ اللهِ ثُمَّ أَبْلِغْهُ مَأْمَنَهُ ذَلِكَ بِأَنَّهُمْ قَوْمٌ لَا يَعْلَمُونَ. }

ትርጉሙም (ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነት ቢጠይቅህ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው ከዚያም ወደመጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፡፡ ይህ እነሱ የማያውቁ ህዝቦች በመሆናቸው ነው፡፡) ማለት ነው

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እነዚህን ለመላው የሰው ልጅ ጸትና ደህንነት የሚያረጋግጡትን ክቡር እሴቶች እንድህ በማለት በሰው ልጅ መንፈስ እንድሰርጥ አደርገዋል፡ (ታማኝነት የሌለው ሰው እምነት የለውም፡፡ ቃል ኪዳኑን የማያከብር ሰው ሃይማኖት የለውም፡፡ እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (ቃል የተጋባውን ሰው የገደለ የገነትን ጠረን አያገኝም፡፡ ጠረኗ ከአርባ ዓመት ጉዞ ርቀት የሚሸት ሆኖ እያለ፡፡) በሌላም ሐዲስ አንድህ ይላሉ፡ (ሙስሊም ብሎ ማለት ሰዎች ከምላሱና ከእጁ ተንኮል ነፃ የሆኑ ሰው ነው፡፡ ምእምን ብሎ ማለት ደግሞ ሰዎች በደማቸውና በንብረቶቻቸው እምነት የጣሉበት ሰው ነው፡፡)

እነሆ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከጠላቶቻቸው ጋር እንኳን ቢሆን ቃልን በማክበር ድንቅ አርኣያነት ያለውን ተግባር በተጨባጭ አሳይተዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሑዘይፋ ቢን አል የማን ስለበድር ጦርነት እንድህ ይላሉ፡ ‹በበድር ጦርነት ከመሳተፍ ያገደኝ ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን እኔና አባቴ ከመካ በወጣንበት ወቅት የቁረይሽ ከሃዲዎች ያዙንና አላማችሁ ሙሐመድ  ነው አይደል አሉን እኛም ወደሙሐመድ አይደለም አላማችን መዲና መሄድ ነው አልን፡፡ ወደመዲና እንድንሄድና ከሙሐመድ ጎን ተሰልፈን ላንዋጋ በአላህ ቃል ኪዳን አስገቡን፡፡ ወደነብያችን በመጣን ጊዜ ይህን ወሬ ነገርናቸው፡፡ እሳቸውም (ሄዱ (ወደመዲና) ቃል ኪዳናቸውን እናከብርላቸው እነሱንም ለማሸነፍ ከአላህ እርዳታን እንለምናለን አሉ፡፡›)

ከዚህ አንፃር እኛ ሁላችንም የሀራችን መንግስት ለማንኛውም ወደሀገራችን ለሚገባ ሰው የሚሰጣቸውን ቃል ኪዳኖችንና ውሎች የመጠበቅና የማግበር ግዴታ ያለብን መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ምንጊዜም ሕይወቱን፣ ክብሩን፣ ገንዘቡንና የግል ጉዳዮችን ለማስከበር መተባበርና እግዛ ማድረግም ይጠበቅብናል፡፡ እንድሁም መልካም

አቀባበል የማደረግና የማከበር ግዴታም አለብን፡፡ ይህውም ስለሃይማኖታችን ታላቅነት፣ ስለስልጣኒያችን ጥልቅነትና ስለሰብአዊ መብት አክብሮታችን እኛ በምንመኘው መልኩ ሊወስደው የሚችለውን ህሌናዊ ግንዛቤ ለማጠናከር ሲሆን ይህም ከፍተኛ እድገት ያስመዘገበና የሰለጠነ ህዝብ ሁሉ ስነ መግባር ነው፡፡
የህን ቃሌን ተናገርሁ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡
* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**
እስልምና ማለት የፍትሕ፣ የመቻቻልና በሰላም አብሮ የመኖር ሃይማኖት ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በሀገሩም ሆነ ከሀገሩ ውጭ በየትኛውም በሄደበት ቦታ በጸጥታና ደህንነት እንድሁም በሰላምና በአማን ይኖራል፡፡ አንድ ሙስሊም ከአገሩ ወደሌላ የሙስሊምም ሆኖ የሌላ እምነት ተከታይ አገር ሲዛወር ከሚዛወርበት አገር በሚያገኘው የመግቢያ ቪዛ ለሕይወቱ ደህንነት አንደቃል ኪዳን የሚቆጠር ሲሆን እሱም የዚያ አገር ነዋሪዎች በሕይወታቸውና በንብረታቸው እንዳይሰጉ የደህንነት ቃል ኪዳን የገባ ይሆናል፡፡ ይህ ቃል ኪዳኑም ለዚያች አገር ህግጋት እንዲገዛና ባህል ልምዳቸውን እንዲያከብር እንድሁም ያለበትን ግዴታ በታማኝነትና በእውነተኛነት እንዲወጠጣ ያስገድደዋል፡፡ በመሆኑም ከንብረታቸው እንድንም ነገር ያለመብት መውሰድ፣ ክብራቸውን መዳፈርና በማንኛውም መልኩ ክዳት መፈጸም እርም ይሆንበታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ግዴታውን ሲወጣም ለሃማኖቱ፣ ለሀገሩና ለስልጣኔው መልካም ልኡክ ይሆናል፡፡ ይህ ሰውዬ ወደዚያ አገር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ግዴታውን በሚገባ ሊወጣ ከአላህ (ሊ.ወ.) ጋር ቃል የተጋባ ይሆናል፡፡ እንድህ የሚለው የኣል ቃል እንዳያካትተው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡
{وَالَّذِينَ يَنْقُضُونَ عَهْدَ اللَّهِ مِنْ بَعْدِ مِيثَاقِهِ وَيَقْطَعُونَ مَا أَمَرَ اللَّهُ بِهِ أَنْ يُوصَلَ وَيُفْسِدُونَ فِي الْأَرْضِ أُولَئِكَ لَهُمُ اللَّعْنَةُ وَلَهُمْ سُوءُ الدَّارِ}

ትርጉሙም (እነዚያ የአላህን ቃል ኪዳን ከጠበቁ በኋላ የሚያፈርሱ አላህም እንዲቀጠል በርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቆርጡ በምድርም ላይ የሚያበላሹ እነዚያ ለነሱ ርግማን አለባቸው፡፡ ለነሱም መጥፎ አገር (ገሀነም) አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
(የአላህ እዝነት ይውረድባቸውና) ኢማሙ አሻፊዒ (ኡም) በተሰኘው መጽሐፋቸው እንድህ ይላሉ፡ ‹አንድ ሙስሊም ወደሌላ እምነት ተከታዮች አገር እነሱ በሰጡት የደህንነት ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ ከሙስሊሞች ጋር የሚዋጉ ቢሆኑም እንኳ ይነስም ይብዛም ከነሱ ንብረት ምንም ነገር መውሰድ አይፈቀድለትም፡፡ ምክኒያቱም እነሱ የደህንነት ኪዳን የሰጡት በመሆኑ እነሱም ከሱ የደህንነት ኪዳን ይጠብቃሉና፡፡

እንደሁም እነሱ የደህንነት ኪዳን በሰጡበት ወቅት ከሙስሊሞች ገንዘብ የሚፈቀድለት ዓይነት እንጂ ሌላ ነገር አይፈቀድለትም፡፡
ኢማሙ አሻፊዒ ያሉትን ብቻ በማውሳት ተወስኛለሁ፡፡ ቃሉም (ኡም) በተሰኘው መጽሐፍ መስፈሩን የጠቀስኩት አንዳንድ ሰዎች ወደማይቀበሉት የሃይማኖት ህግ አከራካሪ ጉዳይ መግባትን በመፍራት ነው፡፡ ጉዳዩን ለናንተው መተውንም መርጫለሁ፡፡
የሚከተለው ግጥም ደራሲ እጅጉን ይደነቃል፡፡
ቃል ኪዳንን ማክበር የክቡራን ጠባይ ነው፡፡ ቃል ኪዳንን ማፍረስ ደግሞ የባለጌዎች ጠባይ ነው፡፡
ከኔ ዘንድ መልካም ተፈጥሮ የምለው ወዱታንና ቃል ማክበርን እንጅ ሌላን አይደለም፡፡
ጌታየ ሆይ! ወደ መልካም ምግባር ምራን፡፡ አንተ አንጅ ወደመልካም ምግባር የሚመራ የለምና፡፡ መጥፎ ምግባርን ከኛ አርቅ፡፡ መጥፎ ምግባርን ያለንት ከኛ የሚያርቅ የልምና፡፡ አሜን፡፡

# (18)

## የህዝብን ጉዳይና አጠቃላይ ጥቅምን ማስከበር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَىوَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም ( በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
እስልምና እውነተኛን አገር አዋቅሯል፡፡ መሰረቱን ያጠነከረና መዋቅሩንም ተመጣጣኝ ያደረገ ሲሆንም እሱን ለመጠበቅና ስለሱ ለመከላከል ሰዎች ጥረት እንዲያደርጉ

ያሳስባል፡፡ የሀገረን አጠቃላይ ጥቅም ማስከበርና መጠበቅ ለዚህም ጉዳይ አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት የመላው የሀገሪቱ ነዋሪዎች የጋራ ሃለፊነት መሆኑንም በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ስለአጠቃላይ የህዝብ ጉዳዮችና አሴቶች አስፈላጊነት እንድሁም እነሱን ማጣጣል ስለሚያስከትለው ችግር አደገኛነት የማህበረሰቡ አባላት ግንዛቤ ባደገ ቁጥር እሱን ለመጠበቅ የሚኖረው ትብብር፣ አንድነትና ትስስር በዚያው ልክ ይጠናከራል፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ መዋቅር ኃይል ጠንካራ ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ያበሰረለትም የአንድ አካል ስሜት እውን ይሆናል፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አንድ ምእምን ለሌላው ምእምን ከፊሉ ድንጋይ ሌላውን እንደሚያጠናክር የአንድ ግንብ አካል ነው፡፡ ጣቶቻቸውን በማጠላለፍም ሁኔታውን አስረድተዋል፡፡) አንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (ምእምናን በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና በመተጋገዛቸው ከሱ የአንዱ አካል ክፍል ባሰሞተ ጊዜ የሌላው አካል ከፍሎች እንቅልፍ በማጣትና በህመም እንደሚጠራራ አንድ አካል ናቸው፡፡)

የሰውን ልጅ መንፈስ ከለኔ ብቻ ባይነት ተንኮል ለማዳን ሲባል ፋይዳው ለመላው የማህበረሰቡ አባላት የሆነውን የሰፊውን ህዝብ ጥቅም ፋይዳው ለግለሰቦች ብቻ ከሆነው ጠባቡ ጥቅም ማስቀደም ከአጠቃላይ ጉዳይ ጥበቃ መዋቅሮች ዋነኛው መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ ይህውም አጠቃላይ ጥቅም ለመላ ማህበረሰቡ ቁሳዊም በሆኑም ይሁን ቁሳዊ ባልሆኑ ነገሮች ለሰዎች ደግን ሁሉ የሚያሚያመጣ፣ በአንፃሩም መጥፎ ነገሮችንና ብልሹነትን የሚከላከል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚያም አልፎ ለሀገር ደህንነትና መረጋጋት እንድሁም ለሀገር አንድነት እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ የህዝብ አጠቃላይ ጥቅም መከበር የሃይማኖት ህግ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች አንደኛው ነው፡፡

የተከበረው ቁርኣን የመላ ማህበረሰቡን ጥቅም ማስከበርና እሱንም ከግለሰብ ጥቅም ማስቀደም የመላ ነያብት ስርኣት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) አንድንም ነብይ ወይም መልክተኛን አላከም ቁሳዊ ምንዳንና ዓለማዊ ጥቅምን ያለመፈለግ የህዝቡን ደስታ እውን ለማድረግ ቢሆን እንጂ፡፡ ታላቁ አላህ በነብዩ ኑሕ (ዐ.ሰ.) ልሳን እንድህ ይላል፡

**وَيَا قَوْمِ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ مَالًا إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى اللَّهِ وَمَا أَنَا بِطَارِدِ الَّذِينَ آمَنُوا إِنَّهُمْ مُلَاقُو رَبِّهِمْ وَلَٰكِنِّي أَرَاكُمْ قَوْمًا تَجْهَلُونَ}**

ትርጉሙም («ሕዝቦቼም ሆይ! በርሱ (በተላከሁበት ማድረስ) ላይ ገንዘብን አልጠይቃችሁም፡፡ ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ እኔም እነዚያን ያመኑትን አባራሪ አይደለሁም፡፡ እነርሱ ጌታቸውን የሚገናኙ ናቸውና፡፡ ግን እኔም የምትሳሳቱ ሕዝቦች ሆናችሁ አያችኋለሁ፡፡») ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሁድ (ዐ.ሰ.) ልሳን እንድህ ይላል፡

**يَا قَوْمِ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى الَّذِي فَطَرَنِي أَفَلَا تَعْقِلُونَ}**

ትርጉሙም («ሕዝቦቼ ሆይ! በእርሱ (በማድረሴ) ላይ ምንዳን አልጠይቃችሁም፡፡ ምንዳዬ በዚህ በፈጠረኝ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ አታውቁምን) ማለት ነው፡፡ በሹዓይብ ልሳን ደግሞ እንድህ ይላል፡

{إِنْ أُرِيدُ إِلَّا الْإِصْلَاحَ مَا اسْتَطَعْتُ وَمَا تَوْفِيقِي إِلَّا بِاللَّهِ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَإِلَيْهِ أُنِيبُ} .

ትርጉሙም (በተቻለኝ ያክል ማበጀትን እንጂ አልሻም (ለደግ ሥራ) መገጠሜም በአላህ እንጂ በሌላ አይደለም፡፡ በእርሱ ላይ ተመካሁ፡፡ ወደእርሱም እመለሳለሁ፤» አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

የቅኑ ሃይማኖት ህግጋቶች ለሰው ልጅ አእምሮ ተስማሚ ሆነው ነው የተቀመጡት፡፡ በመሆኑም ለመላ የሀገር ነዋሪዎች ጥቅም የሚያስከብርን ነገር ሁሉ እውን እንድናደርገው አዞናል፡፡ እንድሁም እንደያስፈላጊነቱ እጅግ አስፈላጊውን እንዲናስቀድምም አስገንዝቦናል፡፡ ለምሳሌ ድሆችን ለማከምና ለመንከባከብ ጤና ጣቢያ ማዋቀርና በአስፈላጊ መገልገያዎች ማነጹ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ከሆነ ለሱ ቅድሚያ መስጠት ግዴታ ይሆናል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት ተቋማትን መዋቀር መገልገያዎችን ማሟላት እንድሁም ለተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማቅረብ በጣም ተፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት ይኖርብናል፡፡ አሁንም እዳ ያለባቸውን ሰዎች እዳ መክፈል፣ የችግረኞችን ጭንቀት ማቃለል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለሱ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡ የሰዎችን ጉዳይ ማውጣት የህግና የሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ካጠገቡ ጎረቤቱ መራቡን እያወቀ እስኪጠግብ በልቶ ያደረ ሰው በኔ አላመነም፡፡)

ከአጠቃላይ ጉዳዮች ጥበቃ ሌላው ደግሞ መላ ነዋሪዎች የሚጋሩበት የህዝብን ገንዘብ መጠበቅ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በውስጡ የተካተቱት መብቶች ብዛት ያላቸው በመሆኑና የባለመብቶቹ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ የህዝብ ገንዘብ እርምነት ከግል ገንዘብ እርምነት በጣም ይጠብቃል፡፡ በመሆኑም የአስልምና እምነት የህዝብን ገንዘብ ከማጥፋት፣ ከመስረቅና በሱም ላይ ጉዳት ከማድረስ እንድንታቀብ በጥብቅ አስጠንቅቆናል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ يَغْلُلْ يَأْتِ بِمَا غَلَّ يَوْمَ الْقِيَامَةِ ثُمَّ تُوَفَّى كُلُّ نَفْسٍ مَا كَسَبَتْ وَهُمْ لاَ يُظْلَمُونَ}

ትርጉሙም (ሰለባንም የሚደብቅ ሰው በትንሣኤ ቀን በደበቀው ነገር (ተሸክሞ) ይመጣል፡፡ ከዚያም ነፍስ ሁሉ የሥራዋን ዋጋ ትሞላለች፡፡ እነርሱም አይበደሉም፡፡) ማለት ነው፡፡

የህዝብ ገንዘብ የመላ ነዋሪዎች ንብረት እንጂ የግለሰብ ወይም የተለየ ቡድን ገንዘብ አይደለም፡፡ በመንግስት ገንዘብ ዙሪያ የሚሰሩ ሰዎች አደራ ጠባቂዎች በመሆናቸው ከሱ ቦጭቀው መውሰድ ወይም በሱ ጉዳት ማድረስ በደልና ክዳት መፈጸም እንድሁም የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ መብላት ይሆንባቸዋል፡፡

የእስልምና እምነት አጠቃላይ የህዝብ መገልገያዎችንም እንድነጠብቅ አዞናል፡፡ የአምልኮ ማድረሻ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የህዝብ መዝናኛዎችና

ሌሎችም አጠቃላይ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የህዝብ ንብረቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በነሱ ላይ ጉዳት ማድረስን፣ ማውደምንና በማንኛውም መልኩ ማበላሸትን የእስልምና እምነት በጥብቅ ከልክሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تُفْسِدُوفِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا}

ትርጉሙም (በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፡፡) ማለት ነው፡፡
አንዳንድ ሰዎች በህዝብ ንብረት የጋራ መብት አለን በማለት በፈለጉት መልኩም መጠቀም እንደሚችሉ በከንቱ በማሰብ ከመሳሳት ሊጠነቀቁ ይገባል፡፡ የህዝብ መገልገያ ተቋማት በአንድ ዘመን የሚኖር ግለሰብ ወይም ቡድን ንብረት ሳይሆኑ በአሁኑ ዘመን የሚኖሩ የሁሉም ህዝብና የመጭውም ትውልድ ንብረት በመሆናቸው ልንጠበቃቸው፣ ልንከባከባቸውና ልናበለጽጋቸው ይገባል፡፡
ከአጠቀላይ መገልገያዎች ሌላው ደግም መጓዣ መንገድ ነው፡፡ መንገድን መጠበቅና የሱንም መብት ማስከበር የሁሉም ሰው ግዴታ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አደራ በመንገዶች ላይ እንዳትቀመጡ፡፡) ባለደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ በመንገዶች ተቀምጠን መጨዋወታችን አይቀሬ ነው አሉ፡፡ ያን ጊዜ የአላህ መልክተኛ (ከመቀመጥ መታቀብን አሻፈረኝ ካላችሁ ደግሞ የመንገድን መብት ማስከበር ይኖርባችኋል) አሉ፡፡ እነሱም የመንገድ መብቱ ምንድን ነው? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ዓይንን ማየት ከማይፈቀድላት ነገር መከልከል፣ ጉዳት ከማድረስ መታቀብ፣ ለሰላምታ መልስ መስጠት፣ በመልካም ምግባር ማዘዝና ከመጥፎ ነገርም መከልከልነው) አሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (እምነት ሰባ ከምናምን ወይም ስድሳ ከምናምን ከፍሎች አሉት፡፡ እጅግ በላጩ፡

لا إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ

« ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም» ማለት ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ ጎጂነ ገርን ከመንገድ ማስወገድ ነው፡፡ የአክብሮት ሀፍረትም የእምነት አካል ነው፡፡)
ከአጠቃላይ ጉዳዮች ሌላው ደግሞ የብሄራዊ አገልግሎት ግዴታን መወጣት ነው፡፡ የብሄራዊ አገልግሎት ግዴታን መወጣት አንድ ሰው ለሃይማኖቱና ለሀገሩ ከሚወጣቸው ግዴታዎች በጣም ታላቁ ሲሆን ለሀገሩ ያለውን ፍቅርና ታማንነት የሚገልጽበት ግዴታም ነው፡፡ ሀገርና ክብር ለአንድ ሰው ከሕይወቱ፣ ከሃይማኖቱና ከንብረቱ ያነሰ ግምት ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ የብሄራዊ ግዴታ በአንድ ሰው ጀግንነት፣ ወኔና መልካም እሴት በማስረጽ ታላቅ ሚና አለው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሁለት ዓይኖች እሳት አይነካቸውም፡፡ እነሱም አላህን በመፍራት ያለቀሰች ዓይንና በአላህ መንድ ዘብ ያደረች ዓይን ናቸው፡፡)
መከበር ካለባቸው አጠቃላይ ጥቅሞች ሌላው ደግሞ ከመንግስትና ከሌላ አገር ወይም ከመንግሰትና ከውጭ ድርጂቶች መካከል ያሉ ጉዳዮችን ማክበር ነው፡፡ ማንኛውም ህጋዊ፣ ሀሳባዊ ወይም ሰበካዊ ሂደት ከሀገረ ገዢው ወይም ከወኪሉ የተላለፈ ውሳኔ ያለው ድርጂታዊ ገጽታ የያዘ ሂደት መሆን አለበት፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መግለጫ

የሚሰጥ ሰው ሁሉ ከወቅታዊ ተባጩ ሁኔታ ወይም ደግሞ ከአላም አቀፍ ህግ፣ ቃል ኪዳንና ስምምነቶች ጋር የሚጋጭ መልእክት እንዳያስተላለፍ ማህበራዊ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ ደንቦችን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ አላህ (ሶ.ወ.) ቃልን እንድናከብር እንድህ በማለት አዞናል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَوْفُوا بِالْعُقُودِ}

ትርጉሙም(እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በቃል ኪዳኖች ሙሉ፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህች አንቀጽ አንድ ሰዎ ከሌላው ሰው ጋር የሚያደርጋቸውን ሁሉንም ውሎች፣ ቃል ኪዳኖችና ስምምነቶችን የሚያካትት አጠቃላይ ደንብ ያቀፈች መሆኑን ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሙስሊሞች እርም የሆነን ነገር የተፈቀደ ወይም የተፈቀደውን ነገር እርም ያደረገ እስካልሆነ ድረስ ያስቀመጡትን መስፈርት አክባሪዎች ናቸው፡፡)
እነሆ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከቁረይሾች ጋር የገቡተን የሑደይቢያን ቃል ኪዳን በማክበር ችገር ሊደርስባቸው የሚችል መሆኑ ቢገመተም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ በሲርን ወደ ቁረይሾች መለሰዋል፡፡ ይህ ተግባር በአንድ በኩል ቃል ኪዳንን ማክበር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰቡን ጥቅም ከገለሰቡ ጥቅም ማስቀደም ነው፡፡
አንድ ሰው ያለ ሙሉ ግንዛቤ በአጠቃላይ ጉዳይ መግለጫ በመስጠት የሀገረን መዋቅር ሊያዛባ ይችላል፡፡ ምክኒያቱም በዚህ ተግባሩ የሀገርን ደህንነት እንደራሱ የግል ግጦሽ መስክና እንደመዝናኛ ቁስ በማድርግ በሚያውቀውም በማያውቀውም ሲያወራ ጥቅም በማምጣት ፋንታ ምድር ላይ ብልሹነትን ያስፋፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ነገሮችን ወደአዋቂዎች እንድንመልስ እንድህ በማለት አዞናል፡

{وَإِذَا جَاءَهُمْ أَمْرٌ مِّنَ الْأَمْنِ أَوِ الْخَوْفِ أَذَاعُوا بِهِ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى الرَّسُولِ وَإِلَىٰ أُولِي الْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ الَّذِينَ يَسْتَنبِطُونَهُ مِنْهُمْ وَلَوْلَا فَضْلُ اللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُ لَاتَّبَعْتُمُ الشَّيْطَانَ إِلَّا قَلِيلًا} .

ትርጉሙም (ከጸጥታ ወይም ከፍርሃት አንዳች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ፡፡ ወደ መልክተኛውና ከእነርሱ ወደ ትዕዛዙ ባለቤቶች (ወደ ዐዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር፡፡ በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከጥቂቶች በስተቀር ሰይጣንን በተከተላችሁ ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህ ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁኝ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

የአጠቃላይ ጉዳይ ግንዛቤ ከተወሰነው የግል አስተሳሰብ በላይ በአለው በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም አንፃር ይህ ጉዳይ ለግለሰቦች የተፈቀደ ወሰን የለሽ ጉዳይ ሳይሆን የተጣለባቸውን ኃላፊነት እሴት ጠንቅቀው የሚያውቁ የግል ባለሞያዎች ድርሻ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች የብሄራዊ ደህንነት፣ የሰዎች ህይወት፣ የህዝብ ጥቅም፣ የእምቅ ሀገር ሀብት፣ የሀገርን ክልላዊና አለም አቀፋዊ ቦታ በማስከበር፣ የፖሊቲካ፣ የማህበራዊ፣ የሳይንሳዊና የሌሎችንም የህዝብ መገልገያ ነገሮችን አስመልክቶ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በሚገባ የመወጣት ብቃት አላቸው፡፡
የእውቀት ባለቤቶች አንድ የምርምር ጥናት የማድረግ ብቃት ያለው ሰው የተለየ ሞያ ባካበተበት ዘርፍ ለህዝብ ጥቅም የምርምር ጥናት አድጎ በሰጠው ብያኔ ቢሳሳት አንድ መንዳ(የጥናቱ ጥረት) ካልተሳሳተ ደግሞ ሁለት ምንዳ ያለው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ የዚህ እሳቦት ተቃራኒ ግንዛቤም አንድ ሰው እውቀት ሳይኖረው በዘርፉ የተለየ ሞያ ሳያካብት የምርምር ጥናት አድርጎ ብያኔ በሚሰጥበት ወቅት ባይሳሳትም ያለእውቀት በመዳፈሩ አንድ ወንጀል ቢሳሳት ደመግሞ የማዳፈሩና የስህተቱ ሁለት ወንጀል እንደፈጸመ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የእስልምነ እምነት ለባለእውቀቶችና ለባለልዩ ሞያወች ልዩ ክብር ሰጥቷል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَاسْأَلُوا أَهْلَ الذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም (የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡) ማለት ነው፡፡
የእውቀት ባለቤት ማለት የእውቀትና የልዩ ሞያ ባለቤቶች ማለት ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ያለ እውቀትና ያለመረጃ በመቻኮል የሚሰጥ የሃይማኖት ብያኔ ተከልክሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ افْتَرَى عَلَى اللَّهِ كَذِبًا لِيُضِلَّ النَّاسَ بِغَيْرِ عِلْمٍ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ}

ትርጉሙም ( ሰዎችንም ያለ ዕውቀት ሊያጠም በአላህ ላይ ውሸትንም ከቀጠፈ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማን ነው አላህ በደለኞችን ሕዝቦች (ቅኑን መንገድ) አይመራም፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَقُولُوا لِمَا تَصِفُ أَلْسِنَتُكُمُ الْكَذِبَ هَذَا حَلَالٌ وَهَذَا حَرَامٌ لِتَفْتَرُوا عَلَى اللَّهِ الْكَذِبَ إِنَّ الَّذِينَ يَفْتَرُونَ عَلَى اللَّهِ الْكَذِبَ لَا يُفْلِحُونَ * مَتَاعٌ قَلِيلٌ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ}

ትርጉሙም (በአላህም ላይ ውሸትን ልትቀጣጥፉ ምላሶቻችሁ በሚመጥኑት ውሸት «ይህ የተፈቀደ ነው፤ ይህም እርም ነው» አትበሉ፡፡ እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ አይድኑም፡፡ ጥቂት መጣቀም አላቸው፡፡ ለእነሱም አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ያለእውቀት ብያኔ የሰጠ ሰው የዚያ ብያኔ የሰጠበት ነገር ኃጢያት አለበት፡፡) (ከነርሱ አላህ ይውደድና) ተላላቅ የነብያችን ባልደረቦች በምንም ነገር ብያኔ ከመስጠት ይሳቀቁ ነበር፡፡ ይህውም ሊያስከትለው የሚችለውን አደጋ ስለተገነዘቡ ነው፡፡ እነሆ ሰይዲና አቡ በክር አሲዲቅ ‹ከአለህ (ዐ.ወ.) መጽሐፍ የማላውውን ነገር ከተናገርኩኝ የተኛው ሰማይ ይጠልለኛል የትኛዋስ መድር ትሸከመኛለች፡›) ይሉ ነበር፡፡ ሻዕቢይ የተባሉት ሊቅ ስለአንድ ነገር ተጠየቁና አላውቅም አሉ፡፡ ያንጊዜ ባልደረቦቻቸው እኛ ስለርሶ አፈርን አሏቸው፡፡ እሳቸውም ነገር ግን የአላህ መላእክት (ያሰወቅህንን እንጂ ሌላን ነገር አናውቅም) ባሉ ጊዜ አላፈሩም በማለት መለሱ፡፡

የአጠቃላይ ጉዳይ ጥበቃ ሁሉም በአለበት ቦታና በችሎታው መጠን  የያንዳንዱ ባለሞያ ሃላፊነት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ፡፡ ሁላችሁም ስለምትጠብቁት ነገር ትጠየቃላችሁ፡፡ አንድ መሪ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ይጠየቃል፡፡ አንድ ሰው የቤተሰቡ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ይጠየቃል፡፡ አንድ ሴትም የባሏ ቤት ጠባቂ ናት፡፡ ስልምትጠብቀውም ነገር ትጠየቃለች፡፡ አንድ አገልጋይ የጌታው ገንዘብ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ይጠየቃል፡፡)

በርካታ ሰዎች የሚናገሩትን፣ የሚጽፉትን ወይም በማህበራዊ ደረ ገጽ የሚሳተፉበተን ነገር እንደቀላል ነገር ይመከቱታል፡፡ ይልቁንም ከፊሎቻችን እንደመዝናኛ እንመለከተዋልን፡፡ ይህውም ከሰዎች መካከል አሉባልታን መፍጠርና ማናፈስ የከንቱ ሰዎች ከእውነት ሰዎች ጋር በሚያደርጉት ትግል የሚጠቀሙበት የማፍረሻ አደገኛ መሳሪያ መሆኑን በመዘንጋት ነው፡፡ ውጤቱም የአንድ አካል ህዝቦች አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ ዓይን መመልከት እንድሁም አንዱ ሌላውን ማስፈራራት ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አንድ ሰው ለመዋሸቱ መረጃነት የሰማውን ሁሉ ማውራቱ በቂ ነው) ያሉት፡፡

አንድ ሰው የሰማውን ሁሉ ማውራቱ የሚቀጣበት የውሸት መረጃ ከሆነ ያላየውን ያልሰማውንና የማያውቀውን ፈጥሮና ቀጥፎ የሚያወራ ሰው ቅጣት ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡ አድማስ የሚሻገሩና በትንሳኤ ቀን ለባለቤታቸው ስቃይ ምክኒያት የሚሆኑ ቀላት እጅግ በርካቶች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (አንድ የአላህ ባሪያ ግምት የማይሰጠው መልካም ቃል ይናገርና አላህ ዘንድ ተወዳጅ ሆኖ አላህ በሱ ከፍተኛ ደረጃዎችን ሊሰጠው ይችላል፡፡ እንድሁም አንድ የአላህ ባሪያ ግምት የማይሰጠው መጥፎ ቃል ይናገርና አላህን አስቆጥቶ አላህ በሱ ጀሀነም ሊዘፍቀው ይችላል፡፡) ከዚህም አንጻር ልብ ማለትና ጥንቃቄ ማድረግና ስለማናውቀው ነገር ከመናገር እንድሁም ያለእውቀት ብያኔ ከመስጠትም መታቀብ ይኖርብናል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ስለማንኛውም የምንሰማው ወሬ ቀድመን እንድናረጋግጥና እንዲናጣራ አንድህ በማለት አዞናል፡

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}**

ትርጉሙም (እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጸኞች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንድህ ብለዋል፡ (እርጋታ ከአላህ ነው፡፡ መቻኮል ደግሞ ከሰይጣን ነው፡፡)

እኛ በአሁኑ ወቅት ስለአጠቃላይ ጉዳይ ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖርን ይገባል፡፡ የአጠቃላይ ጥቅምን ማስቀደም፣ ስለሚሸመንልን አደጋ ማወቅ ለኛ አጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በሌሎች መገሰጽ ሲኖርብን ጠላች እንደሌሎች አዳልጦን እንዲንወድቅ ለሚያደርጉት ጥረት አድል ላለመስጠት አንድነታችን ማጠናከር አንድሁም ጥቅሙ መላ የሰው ልጅን የሚሸፍን በሆነ በመልካም ሥራ መተጋገዝና መተባበር ያስፈልገናል፡፡

ጌታችን ሆይ የሀገራዊ ግዴታችንን እንድንወጣ ረደኤትህ ከኛ ጋር ይሁን፡፡ ህዝባችንን መሪዎቻችንን አንድሁም ሀገራችንን ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# (19)

## የገበያ ስርኣቶችና ደንቦች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ አንዲህ ለአለው የአለማት ጌታ ይገባው

وَيْلٌ لِلْمُطَفِّفِينَ *الَّذِينَ إِذَااكْتَالُوا عَلَى النَّاسِ يَسْتَوْفُونَ *وَإِذَا كَالُوهُمْ أَوْ وَزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ *أَلَا يَظُنُّ أُولَئِكَ أَنَّهُمْ مَبْعُوثُونَ * لِيَوْمٍ عَظِيمٍ *يَوْمَ يَقُومُ النَّاسُ لِرَبِّ الْعَالَمِينَ}

አጋር ከሌለው ብቸኛ አንድ አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት እምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እምሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው አንዲሁም እስከቂያማ እለት በመልካም ምግባር በተከተሏቸውም ሰዎች ሁሉ ላይ እዝነትህን አውርድ፡፡

**ከዚህ በመቀጠልም**

አላሁ (አዘ ወጀል) ለባሮቹ ጉዳያቸው እንዲሳካና ፍላጎታቸው እንዲሟላ መሸጥ መለወጥን ፈቅዶላቸዋል፡፡ እንዲህም ይላል፡

وَأَحَلَّ اللَّهُ الْبَيْعَ وَحَرَّمَ الرِّبَا

ትርጉሙም ‹መሸጥን አላህ ፈቅዷል አራጥንም እርም አድርጓል› ማለት ነው፡፡ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ ጥቅም የሚለዋወጡበትና የሚያስፍልጋቸውን ነገር የሚሸምቱበት ገበያ ቀንና ቦታ ወስነው መገበያትን ልምድ አደርገዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ የወረዱት የቅዱስ ቁርኣን አንቀፆች ይህ ዓይነቱ ተግባር የሰው ልጅ ገፅታና ጠባይ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደዎረዱ የእምነቱ ሊቆች ይጠቁማሉ፡፡ ታላቁ አላህ (ሱ. ወ.) እንዲህ ይላል

وَمَا أَرْسَلْنَا قَبْلَكَ مِنَ الْمُرْسَلِينَ إِلَّا إِنَّهُمْ لَيَأْكُلُونَ الطَّعَامَ وَيَمْشُونَ فِي الْأَسْوَاقِ

‹ትርጉሙም ከአንተ በፊትም ምልእክተኞች እነሱ በርግጥም ምግብን የሚበሉ በገበያዎችም የሚሄዱ ሁነው በስተቀር አላክንም› ማለት ነው፡፡ ቁርኣን አጀጋሪዎች ስለ ነብዩ ( ሶ.ዐ.ወ.) ያወሩትን እንዲህ በማለት ገልጹዋል፡፡

وَقَالُوا مَالِ هَٰذَا الرَّسُولِ يَأْكُلُ الطَّعَامَ وَيَمْشِي فِي الْأَسْوَاقِ

ትርጉሙም ‹ለዚህም መልእክተኛ ምግብን የሚበላ በገበያዎችም የሚሄድ ሲሆን ምን (መልእክተኛነት) አለው› አሉ ማለት ነው ፡፡ቁርኣን የዋሻው ባለቤቶች ታሪክና ሁኔታን እንዲህ በማለት አብራርቷል፡፡

فَابْعَثُوا أَحَدَكُم بِوَرِقِكُمْ هَٰذِهِ إِلَى الْمَدِينَةِ فَلْيَنظُرْ أَيُّهَا أَزْكَىٰ طَعَامًا فَلْيَأْتِكُم بِرِزْقٍ مِّنْهُ

ትርጉሙም ‹ከዚህችም ብራችሁ ጋር አንዳችሁን ወደከተማይቱ ላኩ ከምግቦቹዋ የትኛው ንጹህ እንደሆነም ይመልከት ከርሱም ምግብን ያምጣላችሁ› ማለት ነው፡፡

የገበያዎች ሁኔታ ከትክለኛው የእስላምና ተግባራዊ ገፅታዎች አንዱ መሆኑ አያከራክርም፡፡ የስነ ምግባርን መልከም ገጽታ ለማየት ከፈለግን ወደ ገበያ ጎራ ማለት ጠቃሚ ነው፡፡ ሃይመኖትን እውነተኛ ወይም በገጽታ ብቻ የተወሰነ መሆኑን አስመልክቶ ፍርድ መስጠት የምንሻ ከሆነም ያን ሰው ሲሸጥና ሲገዛ ያለውን ሁኔታ ማጤን ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ላይ (አላህ ይወድላቸውና) ከስይዲና ዑመር ፊት የቆመውን ሰውዩ ሁኔታ ልናስታውስ ይገባል፡፡

ሰይዲና ዑመር እንዲህ አሉት፡ ‹እኔ አንተን አላቅህም እኔ አንተን አለማወቄም አይጎዳህም፡፡ አንተ የምትከበረው በሚያውቅህ ሰው ነው፡፡ ያን ጊዜ አንድ ሰውዬ እኔ አውቀዋለሁ አለ፡፡ እሳቸወውም በምን በምን ታውቀዋለህ ሲሉ ተየቁት፡፡ በፍትህና በትሩፋት በማለትም መለሰ፡፡ እሳቸውም መግቢያ መውጫውንና የሌት ተቀን ሁኔታውን የምታወቀው ቅርብ ጎረቤትህ ነውን ሲሉ እንደገና ጠየቁት፡፡ አሱም አይ

አይደልም በማለት መለሰ፡፡ እሳቸውም አንግዳውማ ጽድቅነት በሚለይባቸው በብርና ወርቅ የምተዋዋለው የንግድ አጋርህ ነዋ በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም ኸረ እንደዚያም አይደልም በማለት መለሰ፡፡ ታዲያ መልካም ምግባር የሚለይበት የጉዞ ጓደኛህ ይሆን ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም ኸረ አይደለም በማለት መለሰ፡፡ አሳቸውም አንገዳውስ አንተም አታውቀውም አሉና ወደሰውው ዞር በማለት አንተ የምትከበረው በሚያውቀህ ሰው ነው አሉት እንደገና፡፡

የመገበያየት ውል አንድ ሰው ትክክለኛ ሃይማኖተኛ ወይም በገጽታ አስመሳይ የሆነ ሰው ይለይበታል፡፡ ልቡ ከጸሎት እጅግ በጣም ሩቅ ሆኖ እያለ ሰዎችን ለማምታታትና ለማታለል በምላሱ ጸሎት የሚያዘወትር ስንትና ስንት ሰው አለ፡፡ በይዩልኝ ይስሙልኝ ገጽታ ተከልሎ ግንዘብ ለማግኘት የሚጠረው ሰው፣ ሰዎች ሃይማኖት የሚወዱ እንዲሁም ሃይማኖተኛን የሚያከብሩ መሆናቸውን ተመርኩዞ በተንኮል ገበያውን የሚያጧጡፈውም ሰው እጅግ ብዙ ነው፡፡

በሃይማኖት ለመነገድ አንዳንድ ሰዎች ከተጫበጩ ጋር የማይጣጣም ስያሜ ለበርካታ ነገሮች ሲጡ እናያለን፡፡ ይህውም በሃማኖት ስም ተከልሎ ገንዘብ ለማካበት በማሰብ ነው፡፡ ይህ ሰው በዚህ ዓይነት ተግባሩ ሃይማኖቱን እየጎዳና በሰዎች መንፈስ ዘንድም መጥፎ መንፈስ እየፈጠረ መሆኑን አያውቅም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.ዐ.) እንዲህ ይላል፡

وَمِنَ النَّاسِ مَن يُعْجِبُكَ قَوْلُهُ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيُشْهِدُ اللَّهَ عَلَىٰ مَا فِي قَلْبِهِ وَهُوَ أَلَدُّ الْخِصَامِ؛ وَإِذَا تَوَلَّىٰ سَعَىٰ فِي الْأَرْضِ لِيُفْسِدَ فِيهَا وَيُهْلِكَ الْحَرْثَ وَالنَّسْلَ وَاللَّهُ لَا يُحِبُّ الْفَسَادَ

ትርጉሙም ‹ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲሆን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚደንቅህና በልቡ ውስጥ ባለው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አለ፡፡ (ካንተ) በዞረም ጊዜ በምድር ላይ በውስጧ ሊያበላሽና አዝመራንም እንሰሳትንም ሊያጠፋ ይሮጣል ፡፡ አላህም ማበላሸትን አይወድም፡፡› ማለት ነው፡፡

የእስልምና ሃይማኖት አንድ ሙስሊም ከሰዎች ጋር ገበያ በሚገበያይበት ወቅት የሚፈጽማቸው የገበያ ደንቦችና ስርኣቶች አስቀምጧል፡፡ ከነዚህ ደንቦች አንደኛውና ዋነኛው አላህን ማስታወስና ትእዛዙን መጠበቅ የሚለው ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ጊዜ ከቶ ሊለየው የማይገባ ነገር ቢኖር አላህን ማስታወስ የሚለው ጉዳ ነው፡፡ አላህን ማስታወስ ስንል በቃል ማወደስና የአካላት ተግባራትም ይካተታሉ፡፡ አንድ ሙስሊም ሴትም ይሁን ወንድ ወደገበያ ከመግባቱ በፊት የገባያ ጸሎትን ማድረስ ይኖርበታል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ወደገበያ ሲገባ

**(لاإله لا الله وحده لا شريك له، له الملك وله الحمد، يحي ويميت، وهو حي لايموت، بيده الخير كلُّه وهو على كل شيئ قدير)**

የሚለውን ጸሎት ካደረሰ (ታላቁ አላህ እልፍ አላፍ መልካም ስራ ይምዘግብለታል እልፍ አላፍ ኃጢያትም ያብስለታል በጀነትም ቤት ይሰራለታል፡፡) ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ አላህን ማስታወስ ወይንም መዝከር ስንል በምላስ ብቻ አለመሆኑን ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡ አላህን መዝከር የተፈቀዱ ነገሮችን በማጣራትና ከተከለከሉ ነገሮች በመራቅ መታነጽ ይኖርበታል፡፡

ሌላው የገበያ ደንብ ደግሞ እውነተኛ መሆንና ከሃሰት መራቅ የሚለው ጉዳይ ነው፡ ፡ በመሰረቱ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ወቅት እውነተኛ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

(ياأيها الذين أمنوا اتقوا الله وكونوا مع الصادقين)

ትርጉሙም ‹እናንን ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ ከጻድቃንም ጋር ሁኑ፡፡› ማለት ነው፡፡ ይህን ማለትም አንድ ሙስሊም በሚሸጥና በሚለውጥበት ጊዜ ገበያውን ለማሳካትና ለማጧጧፍ ሲል መዋሸት የለበትም ማለት ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የገበያ ውሸት በዚህች አለም በረከትን ያስወግዳል በመጭው አለም ደግሞ ከታላቁ አላህ እዝነት ያርቃል፡፡ የሌላውን ሰው ገንዘብ በከንቱ ለመውሰድ በሀስት ለመማል እርኩስ መንፈሱ ገፋፍታው የማለ እንደሆነ ደግሞ ወንጀሉ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ማለታቸው ተወርቷል፡፡ (ሺያጭና ገዥ እስካልተለያዩ ድርስ የማፍረስ ምርጫ አላቸው፡፡ እውነተኛና ግልጽ ከሆኑ በገበያቸው አላህ በረከትን ያሰፍናል፡፡ የዋሹና የደበቁ እንደሆነ ግን ከገበያቸው አላህ በረከትን ያነሳል፡፡) እንዲሁም ነብያችን እንደዚህ ብለዋል፡ (ሦስት ሰዎች ታላቁ አላህ የቂያማ እለት አያናግራቸውም አይመለከታቸውምም እንሱም አንት ካቀረብከው የበለጠ ዋጋ ተሰጥቸ ነበር በማለት በገበያ በሃሰት የማለ ሰው፣ የአንድን ሙስሊም ገንዘብ ቦጭቆ ለመወሰድ በሃስት የማለ ሰውና የተረፈውን ውሃ ሌላ ሰው እንዳይጠቀምበት የከለከለ ሰው ሚሉት ናቸው፡፡ ይህን ሰውዬ አላህ (ሱ.ዐ.) የቂያማ እለት እንዲህ ይለዋል (ዛሬ እኔ ትሩፋቴን እከለክልሃለሁ አንት በዚያች በጠፊዋ አለም አንት በእጅህ ያልሰራሃውን ውሃ እንደከለከልህ ሁሉ፡፡) ነብያችን አሁንም እንዲህ ይላሉ (የአንድን ሙስሊም ገንዘብ ቆርጦ ለመውሰድ ሀሰተኛ ሆኖ የማለ ሰው አላህን በሱ የተቆጣበት ሆኖ ይገናኛል) ነብያችን (ሰ..ዐ.ወ.) ባለደረቦቻቸውን አደራ በመሸጥ መለውት ወቅት ማሃላ እንዳታበዙ እሱ ንፍቅናን ያወርሳል እንዲሁም በረከት ያስወግዳልና በማለት ያስጠነቅቁ እንደነበር ተውርቷል፡፡

እንደሁም ከገበያ ደንቦች ሌላው አመኔታ፣ እርካታና አለማታለል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡አመኔታ በገበያ ወቅት ሁለቱ ወገኖች ይረኩ ዘንድ ሙሉ ግልጸነትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ታላቁ አላህ እንዲህ ይላል፡

(إلا أن تكون تجارة عن تراض منكم)

ትርጉሙም ‹ግን ከናንተ በመዋደድ የሆነችን ንግድ(ብሉ)› ማለት ነው፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ለውስማን ቢን አፋን(አላህ ይደድላቸውና) እንዲህ ብለዋል (በምትገዛበት ወቅት ይስፈሩለህ በምትሸጥበት ወቅት ደግሞ ራስህ ስፈር) አሳኢብ የተባሉት የነብያችን ባልደረባ ደግሞ እንዲህ ብለዋል ከእለታት አንድ ቀን ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሄድኩኝ ሰዎችም ያመሰግኑኝና ያሞግሱኝ ጀመር ነብያችን ያን ጊዜ እኔ ከናንት የበለጠ አውቃለሁ አሉ፡፡ ስለሱ ማለታቸው ነበር እኔም አውነተዎን ነው እናትና አባቴን የማሳለፍለሁ የአላህ መልእክተኛ ሆይ የንግድ ሸሪኬ ነበሩ ምንም የማትደብቁና ማነንም የምትጠረጠሩ አጅግ መልካም ሸሪኬ ነበሩ አልኩኝ አሉ፡፡
ነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዚያን አላህን የማይፈሩ የእርኩስ መንፈስ ባለቤት የሆኑትንና ሰዎችን ለማታለልና ገንዘባቸውን በከንቱ ለመውሰድ መጥፎ መንፈሳቸው የምተገፋፋቸውን ሰዎች ከማታለል እንዲርቁ (ያታለልን ሰው ከኛ አይመደብም) በማለት አጥብቀው አስጠንቅቃዋል፡፡

ነብያችን በሸርክ የሚሰሩ ሰዎች የኢጋርነታቸው መሰረት ታማኝነትና እውነተኛነት እንዲሆን ምክር ለግሰዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል (ታላቁ አላህ አንዱ ሌላውን አስካላታለለ ድረስ እኔ የሁለት ሸርክ ሰራተኞች ሦስተኛ ወገን ነኝ አንዱ ካታለለ ከመካከላቸው ገለል እላለሁ ብሏል)

ቀጣዩ የገበያ ደንብ ደግሞ በሚዛን አለማታለል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ተጥፊፍ የሚለው የዐረበኛ ቃል ከሰውች ሲሰፍሩ ወይንም ዚመዝኑ አሟልቶ መስፈርና መመዘን ለሰዎች ሲሰፍሩ ወይንም ሲመዝኑ ደግሞ አጉድሎ መስፈር ወይም መመዘን ማለት ነው፡፡ ሌሎች መለኪያዎች ሁሉ እንደመስፈሪያና መመዘኛ ይወሰዳሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ሚዛንን በትክክል እንዲንመዝን አዞናል እንደዚህም ይላል፡

وَأَوْفُوا الْكَيْلَ إِذَا كِلْتُمْ وَزِنُوا بِالْقِسْطَاسِ الْمُسْتَقِيمِ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا

ትርጉሙም ‹በሰፈራችሁም ጊዜ ስፍርን ሙሉ፡፡ በትክክለኛው ሚዛንም መዝኑ ይህ መልካም ነገር ነው መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡› ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የዚህ ዓይነት የሚዛን ማተለል የሚፈጽምን ሰው እንዲህ የሚል ዛቻ ሰንዝሮበታል፡፡

وَيْلٌ لِّلْمُطَفِّفِينَ الَّذِينَ إِذَا اكْتَالُوا عَلَى النَّاسِ يَسْتَوْفُونَ * وَإِذَا كَالُوهُمْ أَو وَّزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ

ትርጉሙም ‹ለሰላቢዎች ወዮላቸው! ለነዚያ ከሰዎች ባሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ፡፡ ለነሱም (ለሰዎች) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎድሉ (ለሆኑት)፡፡›

ነብዩ ሹአይብ (ዐ.ሰ.) ህዝቦቻቸውን የሰዎችን ገንዘብ አታሎ ከመውሰድና ከሚዛንና ከመስፈር ከማታለል እንዲርቁ ማስጠንቀቃቸውን ቁርኣን እንዲህ በማለት አውስቷል፡፡

وَإِلَىٰ مَدْيَنَ أَخَاهُمْ شُعَيْبًا قَالَ يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُ قَدْ جَاءَتْكُم بَيِّنَةٌ

مِّن رَّبِّكُمْ فَأَوْفُوا الْكَيْلَ وَالْمِيزَانَ وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ

بَعْدَ إِصْلَاحِهَا ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ

ትርጉሙም ‹ወደ መድያንም ውንደማቸውን ሸዓይብን (ላክን) እንዲህም አላቸው ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ ከርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በርግጥ መጥታላችኋለች፡፡ ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ፡፡ ሰዎችንም አንዳቾቻቸውን (ገንዘባቸውን) አታጉድሉባቸው በምድርም ውስጥ ከተበጀ በኋላ አታበላሹ፡፡ ይሃችሁ ምእምናን እንደሆናችሁ ለናንተ የተሸለ ነው፡፡› ማለት ነው፡፡

ሌላው የገበያ ደንብ ደግሞ የሌሎችን መብት አለመጋፋት የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ወንድሙ የተስማማውን ነገር ለመግዛት እንዳይቀርብ አስጠንቀቀዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል (ከፊላችሁ ወንድሙ ለጊዛ ያሰበውን ነገር አይግዛ) በሌላ ሓዲስ ደግሞ (ወንድሙ ሊገዛ ያሰበውን ነገር አይግዛ ካልፈቀደለት ወይም ትቶ እስካልሄደ ደረስ ወንድሙ አየተስማማ ያለውን ነገር ለመስማማት አይቅረብ) ብለዋል፡፡ አንድ ሰው ሌላው ሊጊዛ ካሰበው ነገር መራቁና የሱን እቃ ለመሸጥ ሲል የወንድሙን ሸቀጥ ከማራከስ መራቁ ከገበያ ተላላቅ ስርአቶች አንዱ አንደሆነ የእምነቱ ሊቆች አመልከተዋል፡፡

የሰዎችን ምግብ አደጋ የሚጥለውና በሀገር ላይ ከፍተኛ ወድቀት ሊያስከትል የሚችለው ሸቀጥን በሞኖፖል ማካበት የሰዎችን መብት እንደመጋፋት ይቆጠራል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል (ስህተተኛ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሸቀጥን በሞኖፖል የሚያካብት ሰው አይኖርም) ሸቀጥን በሞኖፖል የሚያካብት ሰው በዚህ መልኩ የሚያገኘው ትርፍ የእርም ገንዘብ መሆኑን የዘነጋና ራስ ወዳድነት አሸንፎት ለሰዎች ከማለት ይልቅ ለራሴ ማለትን የመረጠ ሰው ነው፡፡ ይህ እርም ገንዘብ በዚህች አለም እሱን አውዳሚ ከመሆኑም ባሻገር በመጭው አለምም ከአላህ እዝነት ለመራቁ ምክኒያት ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል (የሰዎችን የመምግብ ሸቀጥ በሞኖፖል ያካበተ ሰው አላህ (ሱ.ወ.) በጎንድሽ በሽታና በደድህነት ይቀጠዋል፡፡ እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል (የምግብ ሸቀጥን ለአርባ ቀን ያህል በሞኖፖል

ያካበት ሰው እሱ ከአላህ ርቋል አላህም ከሱ ርቋል ማንኛውም በሰው ራህብ ለማድረስ ምክኒያት የሆነ ሰው የአላህ ጥበቃ ርቆታል)

እዚህ ላይ ገበያዎችን መቆጣጠር ከመንግስት አጠቃላይ ስልጣን አንደኛው መሆኑን ስናረጋግጥ የማታለል፣ የሞኖፖልና የብዝበዛን ወንጀሎች ለመከላከል ከሚመለከተው ወገን ጋር መተባበር መስራት የህዝቡ ግዴታ ነው እንላለን። ምክኒያቱም የዚህ ዓይነቱን አሉታዊ ገጽታ ማጥፋት የህብረተሰቡን የመንፈስ ደህንነት እውን በማደረግ ረገድና ለኢኮኖሚ ሂደቱ መፋጠን ታላቅ ሚና ስለሚኖረው ነው። በአንፃሩ ደግሞ ማታለልና ማጭበርበር ከብልሹነት በሮች ታለቁ ሲሆን የሀገሮችን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ያወድማል።

እንዲሁም ገበያዎችን መቆጣጠርና ማስተባበር ታለቅ ሃላፊነት ሲሆን ተጠያቂዎች የተጣለባቸውን ሃላፊነት ተወጥተዋል ወይስ አጓድለዋል የሚል ጥያቄ ከታላቁ አልህ በኩል ይቀርብባቸዋል።

ይህን ዓይ ነት ቃሌን ተናግሪያለሁ። ስለሱም ከአላህ ዘንድ ለኔና ለናንትም ምህረትን እጠይቃለሁ።

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው። ከአለህ በስተቀር የሚገዙት አምላክ የለም ብቸኛ ሸሪክም የሌለው በመሆኑ እምሰክራለሁ። እንዲሁም ነብያችን ሙሐመድ የአላህ ባሪያና መልእክተኛው በመሆናቸውም እመሰክራለሁ። በርሳቸው በቤተሰቦቻቸው፣ በመላ ባልደረቦቻቸው የአላህ እዝነት ይውረድ።

**ሙስሊም ወንድሞቸ ሆይ!**

የሰዎች ምግብ፣ መጠጥና የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ዋስትና ከሰብአዊ ሙብት ቀደምትነት ያለቸው ማህበራዊና ሰብአዊ ጉዳዮች ናቸው። አንድ ሰው የምግቡና የመድሃኒቱ ደህንነት ሳይከበርለት ከበሬታ ያለው ኑሮ ያገኛል ማለት ዘበት ነው። በመሆኑም የማጭበርበርና የሸቀጥ በተለይም ደግሞ የምግብና የመድሃኒትን ሞኖፖል አደጋን ለመቋቋም የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ይሁንጂ ሃይመኖቱን ጠንቅቆ የሚያቅ ነጋዴ የአላህ ኢባዳ በማደረስ፣ በመስግድና መፆም እንዲሁም እንደምጽዋትና አመኔታ በአሉ መልካም ምግባሮቹ ይታወቃል። በርካታ ፆመኞች ከረሃብና ከውሃ ጥም የዘለል ትርፍ የላቸውም። አያሌ የሌለት ሰጋጆችም ከድካምና እንቅልፍ ከማጣት ያለፈ ጥቅም አያገኙም። ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እውነተኛና ታማኝ የሆነ ነጋዴ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል። እንዲህም ብለዋል። (እውነተኛና ታማኝ የሆነ ነጋዴ ከነብዮች፣ ከጻዲቃንና ከሰምአታት ጋር ይሆናል።) እንደዘሁም እንዲህ በለዋል፡ ( እጅግ ጥሩ የሆነው ስራ የነዚያ በተናገሩ ጊዜ

የማይዋሹት፣ አደራ በተሰጣቸውም ወቅት አደራን የማይበሉት፣ ቃልም በገቡ ጊዜ ቃላቸውን የሚያከብሩት፣ በሚገዙም ጊዜ የማያንቋሸሹት፣ በሸጡም ጊዜ ከልክ በላይ ያማያወድሱት፣ በተበደሩም ጊዜ ነገ ዛሬ ያማይሉት፣ በአበደሩም ጊዜ ውጥር አድርገው የማይዙት ነጋዴዎች ስራ ነው፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እውነተኛ ነጋዴ የሱ ጥላንጂ ሌላ ጥላ በሌለበት በቂያማ እለት በአላህ ጥላ ስር እንደሚሆን እንዲህ በማለት አብስረዋል (እውነተኛ ነጋዴ በቂያማ እለት በዐርሽ ጥላ ስር ይሆናል፡፡)
ሁላችንም የውጤቱ ተጠቃሚ የምንሆንበት አጠቀላይ እርቀ ሰላም እንዲሰፍን ቢጋራ መስራት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ እያንዳንዳችን ወንድሞቻችንን በእዝነት ዓይን ማየትና ለራሳችን የምነወደውን ነገር ሁሉ ለነርሱም ልንወድላቸው ይገባል፡፡ ይህን ዓይነት መልካም ምግባር እውን ለማድረግ ደግሞ ሻጭ ለገዜ ልክ አሱ አንዲመገዛ ሆኖ ታማኝ እንዲሁም ገዢው ልክ እሱ እንደሚገዛ ሆኖ ታማን መሆንን ግድ ይላል፡፡ ይህም ገጽታ የእምነት መገለጫ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡፡ (አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙም እስካልወደደ ድረስ ሙእሚን አይሆንም፡፡)
ጌታችን ሆይ! አንተ የፈቅደከው ነገር በቅቶን እርም ወደአደረግህ ነገር እንዳንገባ ጠብቅን የአንተ ትሩፋትም ከአንተ ሌላ ወገንን እንዳንከጅል ያደርገን ዘንድ ፈቃድህ ይሁን፡፡ አሜን፡፡

# (20)

## የጋራ ሥራ መንፈስና መስፈርቶቹ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَقُلِ اعْمَلُوا فَسَيَرَى اللَّهُ عَمَلَكُمْ وَرَسُولُهُ وَالْمُؤْمِنُونَ وَسَتُرَدُّونَ إِلَى عَالِمِ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ فَيُنَبِّئُكُمْ بِمَا كُنْتُمْ تَعْمَلُونَ}

ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በላቸውም ሥሩ አላህ ሥራችሁን በእርግጥ ያያልና መልከተኛውና መእምናንም (እንደዚሁ ያያሉ) ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ወደሆነው (አላህ) በርግጥ ትመለሳላችሁ፡፡ ትሰሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው
ብቸኛ ከሆነው ለሱም ተጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም (ሶ.ዐ.ወ.) የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡፡**

እንድ ማህበረሰብ የሚገነባው በቃላትና በመፈክሮች ሳይሆን በእውቀት፣ በስጦታና መስዋእትነት በመክፈል ነው፡፡ ለአንድን ህብረተሰብ ግንባታና ብልጽግና መሰረቱ ጥንቃቄ ያልጎደለው የሥራ ታታሪነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَقُلِ اعْمَلُوا فَسَيَرَى اللَّهُ عَمَلَكُمْ وَرَسُولُهُ وَالْمُؤْمِنُونَ وَسَتُرَدُّونَ إِلَى عَالِمِ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ فَيُنَبِّئُكُمْ بِمَا كُنْتُمْ تَعْمَلُونَ}

ትርጉሙም ((በላቸውም ሥሩ አላህ ሥራችሁን በእርግጥ ያያልና መልክተኛውና መእምናንም (እንደዚሁ ያያሉ) ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ወደሆነው (አላህ) በርግጥ ትመለሳላችሁ፡፡ ትሰሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ሊ.ወ.) አንዳችሁ ሥራን በሚያከናውን ጊዜ አሳምሮ እንድሰራው ይወዳል፡፡) ሃይማኖትና ሀገር ወዳድነት በአንድ ላይ ታታሪነትን፣ ላብአደርነትን፣ ሥራንና ምርትን ከኛ ይጠብቃሉ፡፡ በተለይም የሥራና አጣርቶ የመስራት ሃይማኖት የሆነው እምነታችን በተለየ መልኩ የተጠቀሱትን ተግባራት እንዲናከናውን በጥብቅ ያዘናል፡፡

አንድ ግለሰብ በማህበረሰቡ መዋቅር መሰረታዊ አካል ነው ስንል በዚህ ግንባታ ያለው እውነተኛ ሚና ምሉእ ሊሆን የሚችለው ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር በሚፈጸመው ተግባሩ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ አንድ ሰው ብቻውን አንዳንድ ነገሮችን ማከናወን ቢችልም ሀሳቡ ከሌላው ሀሳብ፣ ጥረቱም ከሌካው ሰው ጥረት ጋር ሲዋሀድ ደግሞ ስኬቱ የበለጠ፣ ታላቅና ጥቅሙም እጅጉን የሰፋ መሆኖ ጥርጥር የለበትም፡፡ በመሆኑም የእስልምና እምነት ለገራ ሥራ ልዩ ክብር የሰጠው ከመሆኑም በላይ ኃይልን ለማጠንከር፣ ወኔዎችን ለማዋሀድና ለመላ ሰው ልጅ ደግ ነገር ያዘሉ የጋራ አላማዎችን እውን ለማድረግ ያለውን ትብብር ለማሻሻል የሚጫወተውን ሚና መሰረት በማድረግ ሀገሮችንና ስልጣኔዎችን ለመገንባት ዋና ዋልታ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ.}

ትርጉሙም( በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

የቁርኣንን አንቀጾች የሚመራመር ሰው የገራ ሥራ መንፈስን እንድናሰራጭና ሥራዎችን እንደ አንድ ቡድን ሆነን እንድናከናውን የሚያዙት አንቀጾች የተለያዩና በጣም በርካታ መሆናቸውን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ከነሱም መካከል አላህ (ሱ.ወ.) እምልኮቱን እንዴት እንደምንፈጽም የሚያዝባት የምትከተለዋ አንቀጽ እንዱ ነች፡፡

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اعْبُدُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُمْ وَالَّذِينَ مِنْ قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ}

ትርጉም (እናንተ ሰዎች ሆይ የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፡፡ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡ ከሃይማኖቱ ስርአተ አምልኮት እጅጉን ታላቅ ስለሆነው ስለስግደት ሲያዝም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَنْ أَقِيمُوا الصَّلَاةَ}

ትርጉሙም ( ሶላትንም በደንቡ ስገዱ..) ማለት ነው፡፡ ስገዱ የሚለው ቀል ትእዛዙን ፈጻሚዎቹ በገራ የሚሰሩ ብዙዎች መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا ارْكَعُوا وَاسْجُدُوا وَاعْبُدُوا رَبَّكُمْ وَافْعَلُوا الْخَيْرَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

ትርጉሙም ( እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! (በስግደታችሁ) አጎንብሱ በግንባራችሁም ተደፉ፡፡ ጌታችሁንም ተገዙ፡፡ በጎንም ነገር ሥሩ፡፡ ልትድኑ ይከጀልላችኋልና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ተነጋሪ በማድረግ አላህ (አ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَاصْبِرْ نَفْسَكَ مَعَ الَّذِينَ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ بِالْغَدَاةِ وَالْعَشِيِّ يُرِيدُونَ وَجْهَهُ وَلَا تَعْدُ عَيْنَاكَ عَنْهُمْ تُرِيدُ زِينَةَ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَلَا تُطِعْ مَنْ أَغْفَلْنَا قَلْبَهُ عَنْ ذِكْرِنَا وَاتَّبَعَ هَوَاهُ وَكَانَ أَمْرُهُ فُرُطًا}

ትርጉሙም (ነፍስህንም ከነዚያ ጌታቸውን ፊቱን (ውዴታውን) የሚሹ ከሆነው፣ በጧትና በማታ ከሚገዙት ጋር አስታግስ፡፡ የቅርቢቱንም ሕይወት ሽልማት የምትሻ ሆነህ ዓይኖችህ ከነሱ (ወደሌላ) አይለፉ፡፡ ልቡንም እኛን ከማስታወስ ያዘነጋነውን፣ ፍላጎቱንም የተከተለውን፣ ነገሩም ሁሉ ወሰን ማለፍ የሆነውን ሰው አትታዘዝ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا}

ትርጉሙም (የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ አትለያዩም...) ማለት ነው፡፡ መለያየት የሚያደርሰውን አደጋ ሲያስጠነቅቀን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَطِيعُوا اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَلَا تَنَازَعُوا فَتَفْشَلُوا وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ وَاصْبِرُوا إِنَّ اللَّهَ مَعَ الصَّابِرِينَ. }

ትርጉሙም (አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ፡፡ አትጨቃጨቁም ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትሄዳለችና፡፡ ታገሱም አላህ ከትግስተኞች ጋር ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ ሥራዎችን ማከናወን በዚህ ዓይነት የጋራ መንፈስ ኃላፊነትን መወጣት ከአንድ ማህበረሰብ ልጆች መካከል ያለውን የመዋደድ፣ መፋቀር፣ የወንድም ተማማችነት፣ የአንድነት ትስስር የሚያጠናክር መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ እንድህ ሲል አላህ (ሱ.ወ.) የሰጠው ማብራሪያ እውን ይሆንበታል፡

{وَإِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً }

ትርጉሙም (ይህችም (በአንድ አምላክ የማመን ህግጋት) አንድ መንገድ ስትሆን ሃይማኖታችሁ ናት፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ የሚለው የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቃልም እውነትነት ይረጋገጥበታል፡ (የምእምናን መዋደድ፣ መተዛዘንና መተሳሰብ ምሳሌ አንድ የሰውነት ክፍል ሲታመም ሌሎችም የሰውነቱ አካላት እንቅልፍ በማጣትና በመሰቃየት እንደሚጠራሩለት አካል ነው፡፡) አንድ አስተማሪ ስለአንድነት

አስፈላጊነትና አሱም የኃይል ምንጭ ስለመሆኑ፣ በአንፃሩም መለያየት አደገኛ መሆኑን፣ እሱም የመበታተንና የጥፋት መነሻ መሆኑን ለልጆች ማስተማር በአሰበበት ወቅት አቅፍ አንጨት አመጠና ከናንተ ይህን እቅፍ እንጨት በአንድ ምት ወይም በሁለት ጊዜ መት መስበር የሚቸለው ማነው ሲል ጠየቀ፡፡ ሁሉም እያንዳነንዱ መከሩ ነገር ግን ለማነም አልተሳካም፡፡ ከዚያ በኋላ እቅፍ እንጨቱን በተነና ለልጆቹ አከፋፈላቸው፡፡ እያንዳንዱም ልጅ የተሰጠውን እንድ እንጨት በአንድ ምት ብቻ ሰበረ፡፡ ያንግዜ እንድህ የሚለውን ግጥም አነበበላቸው፡
የጦር ዛቢያዎች በተሰባሰቡ ጊዜ ከመሰበር አሻፈረኝ ይላሉ፡፡ በሚለያዩ ጊዜ ግን ለያንዳንዱ በቀላል ትሰበራለች፡፡
ቁርኣን ለጋራ ሥራ እንድንነሳሳ የሚገፋፉና ታላላቅ አላማዎችን ለማሳካት ከፍተኛ ሚና እንደነበረው የሚጠቁሙ በርካታ አስደናቂ ምሳሌዎችን አስፍሮ እናገኛለን፡፡ እነሆ ኢብራሂም አላህ (ሱ.ወ.) የተከበረውን ካዕባን እንዲገነቡ አላህ በአዘዛቸው ጊዜ ወደ ልጃቸው ወደኢስማኤል ሄደው እንድህ አሏቸው፡ ‹አላህ አንድ ነገር እንድሰራ አዘዘኝ፡፡ ኢስማኢልም ጌታህ ያዘዘህን ነገር ሥራ እንጂ አሉ፡፡ ኢብራሂምም ታግዘኛለህ አሉ፡፡ ኢስማኢልም አግዝሃለሁ አሉ፡፡ ኢብራሂምም አላህ እዚህ ቦታ ላይ ቤተ ጸሎት እንድሰራ አዞኛል አሉ፡፡ ከዚያም በኋላ ሁለታቸውም የቤቱን መሰረቶች ከፍ ማድረግ ጀመሩ፡፡ ኢስማኢል ከያቅጣጫው ድንጋይ ሲያቀርቡ ኢብራሂም ግንባታውን ተያያዙ ሁለቱም ተባብረው በምድር የመጀመሪያውን ቤተጸሎት አነጹ፡፡ ይህን ታላቅ አቋም አላህ በቁርአን እንድህ ሲል ለዘላለም እንዲታወስ አድርጎታል፡
{وَإِذْ يَرْفَعُ إِبْرَاهِيمُ الْقَوَاعِدَ مِنَ الْبَيْتِ وَإِسْمَاعِيلُ رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ أَنْتَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ.}

ትርጉሙም ( ኢብራሂምና ኢስማኢልም ጌታችን ሆይ ከኛ ተቀበል፡፡ አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተ ነህና የሚሉ ሲሆን ከቤቱ መሰረቶቹን ካፍ ባደረጉ ጊዜ (አስታውስ)፡፡) ማለት ነው፡፡ በካህፍ ምዕራፍ አላህ (ሱ.ወ.) በዙልቀርነይን ታሪክ አማካይነት ስለትብብር፣ መተጋገዝና ስለጋራ ሥራ መንፈስ የላቀ አርኣያነት ያለው ምሳሌ አስፍሮ እናገኛለን፡፡ ታሪኩ ስለአንድ ንጉስ ሲሆን በአንድ ወቅት በጉዞ ላይ ሳለ እሱ በማያውቃቸው እነሱም በማያውቁት ሰዎች አካባቢ ደረሰ፡፡ እነሱ እርዳታ በጠየቁት ጊዜ እርዳታ ለማድረግ ተስማማ፡፡ ይሁንጂ እነሱም እንዲያግዙት መስፈርት አስቀመጠ፡፡ ሁላቸውም እጅና ጓንት ሆነው በመስራታቸው ከያእጁጅና ማእጁጅ አደጋ የሚጠብቃቸውን ያነን ታላቅና ግዙፍ ግንብ ለማቆም ቻሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{حَتَّى إِذَا بَلَغَ بَيْنَ السَّدَّيْنِ وَجَدَ مِنْ دُونِهِمَا قَوْمًا لَا يَكَادُونَ يَفْقَهُونَ قَوْلًا *قَالُوا يَا ذَا الْقَرْنَيْنِ إِنَّ يَأْجُوجَ وَمَأْجُوجَ مُفْسِدُونَ فِي الْأَرْضِ فَهَلْ نَجْعَلُ لَكَ خَرْجًا عَلَى أَنْ تَجْعَلَ بَيْنَنَا وَبَيْنَهُمْ سَدًّا * قَالَ مَا مَكَّنِّي فِيهِ رَبِّي خَيْرٌ فَأَعِينُونِي بِقُوَّةٍ أَجْعَلْ بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُمْ رَدْمًا * آتُونِي زُبَرَ الْحَدِيدِ حَتَّى إِذَا سَاوَى بَيْنَ الصَّدَفَيْنِ قَالَ انْفُخُوا حَتَّى إِذَا جَعَلَهُ نَارًا قَالَ آتُونِي أُفْرِغْ عَلَيْهِ قِطْرًا *فَمَا اسْطَاعُوا أَنْ يَظْهَرُوهُ وَمَا اسْتَطَاعُوا لَهُ نَقْبًا.}

ትርጉሙም ( ወደጸሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት፡፡ ባጠገቧም ህዝቦችን አገኘ፡፡ ዙልቀርነይን ሆይ! ወይም (በመግደል) ትቀጣለህ ወይም በነርሱ መልካም ነገርን (መማረክን) ትሰራለህ አልነው፡፡ የበደለን ሰውማ ወደፊት እንቀጣዋለን፡፡ ከዚያም ወደጌታው ይመለሳል፡፡ ብርቱንም ቅጣት ይቀጠዋል አለ፡፡ ያመነም ሰውማ መልካምንም የሰራ ለርሱ ከምንዳ በኩል መልካሚቱ (ገነት) አለችው፡፡ ለርሱም ከትእዛዛችን ገርን ነገር እናዘዋለን (አለ)፡፡ ከዚያም መንገዱን (ወደምስራቅ) ቀጠለ፡፡ ወደጸሐይ መውጫ በደረስም ጊዜ ለነሱ ከበታቹዋ መከለያን ባላደረግንላቸው ሰዎች ላይ ስትወጣ አገኛት፡፡ (ነገሩ) እንደዚሁ ነው እርሱም ዘንድ ባለው ነገር ሁሉ በእርግጥ በእውቀት ከበብን፡፡ ከዚያም (ወደሰሜን አቅጣጫ) መንገድን ቀጠለ፡፡ በሁለቱ ጋራዎችም መካከል በደረሰ ጊዜ በአቅራቢያቸው ንግግርን ለማወቅ የማይቀርቡ ህዝቦች አገኘ፡፡ ዙልቀርነይን ሆይ! የእጁጅና ማእጁጅ በምድር ላይ አበላሽዎች ናቸውና በኛና በነሱ መካከል ግድብን ታደርግልን ዘንድ ግብርን እናድርግልህን? አሉ፡፡ አለ ጌታዬ በርሱ ያስመቸኝ ሀብት (ከናንተ ግብር) በላጭ ነው፡፡ ስለዚህ በጉልበት እገዙኝ፡፡ በናንተና በነርሱ መካከል ብርቱን ግድብ አደርጋለሁና፡፡ የበረቱን ተላላቅ ቁራጮች ስጡኝ (አላቸው)፡፡ በሁለቱ ኮረብታዎች (ጫፍ) መካከልም ባስተካከለ ጊዜ አናፉ አላቸው፡፡ (ብረቱን) እሳት ባደረገው ጊዜ የቀለጠውን ነሐስ ስጡኝ በርሱ ላይ አፈስበታለሁና አላቸው፡፡ (የእጁጅና ማእጁጅ) ሊወጡትም አልቻሉም ለርሱ መሸንቆርንም አልቻሉም፡፡) ማለት ነው፡፡

ከሊሙላህ ሙሳ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ.) በወንድማቸው በሃሩን እንዲያግዛቸውና የአላህን ትእዛዝ ለማድረስ ትከሻና አጋዥ እንዲሆኑላቸው አላህን ለምነዋል፡፡ ይህንም ጉዳይ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{ قَالَ رَبِّ اشْرَحْ لِي صَدْرِي *وَيَسِّرْ لِي أَمْرِي *وَاحْلُلْ عُقْدَةً مِنْ لِسَانِي *يَفْقَهُوا قَوْلِي *وَاجْعَلْ لِي وَزِيرًا مِنْ أَهْلِي *هَارُونَ أَخِي * اشْدُدْ بِهِ أَزْرِي *وَأَشْرِكْهُ فِي أَمْرِي * كَيْ نُسَبِّحَكَ كَثِيرًا * وَنَذْكُرَكَ كَثِيرًا إِنَّكَ كُنْتَ بِنَا بَصِيرًا. }

ትርጉሙም (ሙሳም አለ ጌታዬ ሆይ! ልቤን አስፋልኝ፡፡ ነገሬንም ለኔ አግራልኝ፡፡ ከምላሴም መኮላተፍን ፍታልኝ፡፡ ንግግሬን ያውቀሉና፡፡ ከቤተሰቦችም ለኔ ረዳትን አድርግልኝ፡፡ ሃሩን ወንድሜን፡፡ ኃይሌን በሱ አበርታልኝ፡፡ በነገሬም አጋራው፡፡ በብዙ እናጠራህ ዘንድ፡፡ በብዙም እንድናወሳህ፡፡ አንተ በኛ ነገር ዐዋቂ ነህና፡፡) ማለት ነው፡፡

እንድሁም ባለጥሩ መዐዛውን ነብያዊ የሕይወት ታሪክ የሚመራመር ሰው በነብያቸን (ሰ.ዐ.ወ.)ና በባልደረቦቻቸው የእለት ተእለት ኑሮ ስለትብብር፣ መተጋገዝና ስለጋራ ስራ አንጸባራቂ መዕራፎችን በሰፊው ያገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑስማን ኢብን አፋን እንድህ ይላሉ፡ ‹እኛ በአላህ ይሁንብኝ በከተማም ሆነ በጉዞ የነብያችን ባልደረቦቸረ ነበርን፡፡ እሳቸውም በጥቂቱም በብዙውም ያዝናኑን ነበር፡፡)

ባልደረቦቻቸው እንደሚሉት ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በሥራና በግንባታ ይጋሯቸው ነበር፡፡ በገራ እንደሰሩም ያዟቸው ነበር፡፡ በራእ ኢብን ዓዚብ የተባሉት ባልደረባ ስለኸንደቅ

ጦርነት ሲያብራሩ እንድህ ይላሉ፡ ‹በአሕዛብ ቀን የአላህ መልክተኛ አፈር ሲያመላልሱ አፈር የሆዳቸውን ነጭነት ሸፍኖት አይቻለሁ፡፡ እንድህም ሲሉ ሰምቻለሁ (ጌታችን ሆይ! ያለአንት ቅንን መንገድ ልንመራ አንችልም ነበር፡፡ ምጽዋትም አንሰጥ ስግደትንም አናደርስ ነበር፡፡ በኛ ላይ እርጋታን አውርድ፡፡ ጠላትን በምንገናኝበት ወቅትም ግንባራችንን አጠንክር፡፡ እነዚያ የበደሉን ጥቃት አደረሱብን፡፡ እነሱም በሃይማኖታችን ፈተና ሊፈጥሩብን በተነሱ ጊዜ እኛ አሻፈረኝ አልን፡፡)

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይድና ሰልማን ኢልፋርሲ ከባርነት ነፍሳቸውን ለመታደግ ሦስት መቶ የትምር ዛፍ እንድተክሉ በተጠየቁ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለባልደረቦቻቸው (ወንድማችሁን እገዙ) አሉ፡፡ ሰልማንም እንድህ አሉ ‹ ተምሩን በመትከል አገዙኝ፡ አንዱ ሰለሳ እንቡጥ ያመጣልኛል፣ ሌላውም ሃያ ያመጣልኛል እንድሁም ሌላው ደግሞ ዐሥራ አምስት ያመጣል ሌላውም የቻለውን ያህል ሲያመጣልኝ በመጨረሻ ሙሉ ሦስት መቶ የተምር እንቡጦችን አሰባሰበኩ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ለያንዳንዱ እንቡጥ ጉድጓድ ቆፍር፡፡ በጨረስክም ጊዜ ናና ንገረኝ እኔ በራሴ እተክላቸዋለሁ) አሉኝ፡፡ ባልደረቦችም እያገዙኝ ሦስት መቶ ጉድጓዶችን ቆፍሬ ጨረስኩ፡፡ ወደነብያችንም ሄጀ ነገርኳቸው፡፡ አሳቸውም ከኔጋር መጡና እኛ እየሰጠናቸው ሁሉንም እንቡጦች በጆቻቸው ተከለዋቸው፡፡›

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በተለያዩ አቋሞች በተለይም ደግሞ በችግር ጊዜ የሚያከናውኑትን የአሸዓሪዎችን የገራ ሥራ መንፈስ እንድህ በማለት በከፍተኛ ደረጃ አድንቀዋል፡ (አሽዓሪያዊያን በጦርነት ጊዜ ስንቃቸው ሲጓደል ወይም በመከተማ ቀለባቸው ሲመናመን ያለቸውን ሁሉ በአንድ ጭርቅ ያከማቹና እንደገና በየእቃቸው እኩል ይካፈሉታል እነሱ ከኔ ወገን ናቸው እኔም ከነሱ ወገን ነኝ፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርሁ፡፡ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

እኛ እውን እንዲሆን ጥረት የምናደርገው የጋራ ሥራ የሚገነባውን አንጂ የሚያፈርሰውን አይደለም፡፡ የሚያዋህደውን እንጂ የሚለያየውን አይደለም፡፡ እሱም ህግጋትን መሰረት ያደረገው የአንድ ማህበረሰብ ለጆች ትብብር ነው፡፡ ይህውም ከመካከለቸው ረሀብተኛና ድሃ እንደይኖር የሚያደርጉት ትብብር ነው፡፡ ወይም አውቀትንና ትምህርትን መሰረት ያደረገው ሲሆን ሳይንቲስቶች በቤተ ሙከራቸው የሚያደርጉት ትብብርና ተማሪዎች በጥናታቸው የሚያደርጉት ትብብር ነው፡፡ ወይም

ደግሞ ሀገራዊነትን መሰረት ያደረገው ሲሆን ለሀገር ተሃድሶና በተለያዩ ዘርፎች ማህበረሰቡን ለባልጸግ የሚደረገው ትብብር ነው፡፡
በአንፃሩም ግድያን፣ ማፍረስን፣ ደም ማፍሰስን፣ ሀገር ማውደምንና ሀገር ማዳከምን አላማ አደርጎ ከሃማኖት፣ ከብሄራዊነትና ከህሌና የተራቆተ በሆነ መልኩ በውሸት፣ በቅጥፈትና እውነትን በማጣመም የሚሰበክለትን አፍራሽ የጋራ ሥራ አይደለም፡፡
እውን እንዲሆን ጥረት የምናደርገው የጋራ ሥራ የሃይማኖት፣ የሀገርና የሰብአዊ ጥቅሞችን ለማጎልበት የሚደረገውን የጋራ ሥራ ነው፡፡ እነዚህን አላመዎች መሰረት ያደረገውን የጋራ ሥራ መንፈስ ለልጆቻችን ማስተማርና በመንፈሳቸው ተቀርጸው ከአንድ ማህበረሰብ ልጆች መካከል ሰላምና ፍቅርን የሚያስፋፉ እንድሁም ውህደት እንድፈጠር የሚያደርግ የሕይወት ስርኣት እንድሆን ከፍተኛ ምኞታችን ነው፡፡ ያን ጊዜ ህዝባችን በተለያዩ መስኮች ወደተገቢው የእድገት ደረጃ ከፍ ይላል፡፡
እዚህ ላይ ልናረጋጠው የምንፈለገው ነገር ቢኖር የግብጽ ህዝብ ከልጆቹ መካከል የጋራ ሥራ መንፈስ በሚጠናከርበት ጊዜ ሌላው ህብረተሰብ ሊሳካ የማችል ብሎ የሚገምተውን ነገር በቀላሉ ሊፈጸመው የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ይህን እውነት በጥንትም ሆነ በአሁኑ ዘመን የተከናወኑ ተጨባጭ ተግባራት ያረጋግጡታል፡፡
ኬታችን ሆይ! በአገራችን በአማን አኑረን፡፡ ለመሪዎቻችን ስኬትን ስጥ፡፡ ሀገራችንን ከተንኮለኞች ተንኮልና ከአበላሾች ብልሽት ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

## (21)

### የመከራ መነሳት ገሀዳዊና ምስጢራዊ ምክኒያቶችና የስልጣን ባለቤትን የመታዘዝ ግዴታ

**ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ**

رَبَّنَا عَلَيْكَ تَوَكَّلْنَا وَإِلَيْكَ أَنَبْنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ}

**ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ይገባው፡፡ ትርጉሙም** (ጌታችን ሆይ! በአንተ ላይ ተመካን፡፡ ወደ አንተም ተመለስን መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው፤» (ባለው ተከተሉት)፡፡ ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣

በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

መከራ በዚህች ዓለም በሚኖሩ ሰዎች ላይ የወሰነው የአላህ ፍርድ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**إِنَّا خَلَقْنَا الْإِنْسَانَ مِنْ نُطْفَةٍ أَمْشَاجٍ نَبْتَلِيهِ فَجَعَلْنَاهُ سَمِيعًا بَصِيرًا.**

ትርጉሙም (እኛ ሰውን (በሕግ ግዳጅ) የምንሞከረው ስንኾን ቅልቅሎች ከኾኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፡፡ ሰሚ ተመልካችም አደረግነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ሆኖም አላህ (ዐ.ወ.) የዚህ ዓይነቱ መከራ ከሰዎች ላይ እንድነሳ ገሀዳዊና ምስጢራዊ ምክኒያቶችን አድርጓል፡፡ አጥብቅን ልንይዛቸው ከሚገባው ገሀዳዊ ሰበቦች መካከል በቀደምትነት የሚጠቀሱት በእውቀት የተመረኮዘው፣ ከልዩ ባለሙያዎች የሚሰነዘረው ማስጠንቀቂያና ከመንግሰት ድርጂቶች የሚወጡ ትእዛዞችን መፈጸም የሚሉት ሰበቦች ናቸው፡፡ የስልጣን ባለቤትን ወይም የሱን እንደራሲና በሱ ትእዛዝ የሚሰሩ ድርጂቶችን ትእዛዛት ማክበርና ለነሱም መገዛት የሁሉም ሰው ግዴታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**وَأَطِيعُوا اللهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الأَمْرِ مِنْكُمْ**

ትርጉሙም (አላህን ተገዙ፡፡ መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

**فَاسْئَلُوا أَهْلَ الذِّكْرِ إِنْ كُنْتُمْ لا تَعْلَمُونَ**

ትርጉሙም (የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡) ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ የእውቀት ባለቤት የተባሉት በማንኛውም ዘርፍ የልዩ ባለሞያዎች መሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም ባለ ልዩ ባለሞያዎችን ያካተተው የአንድ መስክ የመንግስት ድርጅት የሚያስተላለፈው ውሳኔ ህዝቡ ሊፈጽመው የሚገባ ግዴታ ነው ማለት ነው፡፡

ሌላው ገሀዳዊ ምክኒያት ደግሞ ለንጽህና አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ለንጽህና ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ ሲሆን የሰውን ልጅ ከጉዳትና ከበሽታ ለመጠበቅ ሃይማኖታዊ ግዴታም አድርጎታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ التَّوَّابِينَ وَيُحِبُّ الْمُتَطَهِّرِينَ}**

አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችንም (ሰ.ዐ.ወ.) (ንጽህና የእምነት ግማሹ አካል ነው፡፡) ብለዋል፡፡ አንድሁም በሌላ ሐዲስ (ደጃችሁን አጽዱ) ይላሉ፡፡ ደጅ የሚለው ቃል የቤትን ግቢ

የትምህርት ቤትና የኢንዱስትሪ ቦታ ቅጥር ግቢዎችን እንድሁም ጎዳናና አደባባዮችንም ያካትታል፡፡ የእስልምና እምነት ለአጠቃላይ ንጽህና ትኩረት የሰጠ ሲሆን እጅን ለማጠብ ደግሞ በተለየ መልኩ ትኩረት ስጥቶታል፡፡ ለስግደት ስንዘጋጅ ውዱ በምናደርግበት ወቅት መታጠብ ያለባቸውን አካላት አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አመልክቷል፡

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا قُمْتُمْ إِلَى الصَّلَاةِ فَاغْسِلُوا وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى الْمَرَافِقِ وَامْسَحُوا بِرُءُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى الْكَعْبَيْنِ وَإِنْ كُنْتُمْ جُنُبًا فَاطَّهَّرُوا}**

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ፡፡ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)፡፡ (ሴት ጋር በመገናኘት ወይም በሌላ ምክንያት «ጀናባ») ብትኾኑ (ገላችሁን) ታጠቡ፡፡) ማለት ነው፡፡

እጅን ከክርን ጋር መታጠብ ከውዱ ግዴታዎች አንዱ መሆኑ በዚህ መልኩ ተጠቅሷል፡፡

ከዚያም አልፎ ዉዱ ማድረግ ስንጀምር ቀደመን ሦስት ጊዜ እጆቻችን መታጠብ፣ አፋችንን መጉመጥመጥና አፍንጫችንን መሰርነቅ የነብያችን ፈለግ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንዳችሁ ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ እጆቹን ሦስት ጊዜ ከማጠቡ በፊት ከማንኛውም እቃ አይከተታቸው፡፡) ከምግብ በፊትና ከምግብ በኋላ እጆችን መታጠብ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የደረሰን ሱና ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ከሳይንስና ከሃይማኖት መካከል ምንም ዓይነት ግጭት እንደሌለ አንገነዘባለን፡፡ የሰውን ልጅ ጤና መጠበቅ ከሃይማኖት አላማዎች ተቀዳሚው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ለሰው ብሎ መጎዳትም ሆነ ሰዎችን መጉዳት የተከለከለ ነው፡፡) ይላሉ፡፡

በመሆኑም በሽታዎችና ወረርሽኞች እንዳይሰራጩ የሚደረጉ የጥንቃቄ ሂደቶችን ማክበር የሁሉም ሰው ግዴታ ነው፡፡ ከነዚህ የጥንቃቄ ሂደቶች መተቃቀፍን፣ መሳሳምን ጨርሶ መራቅና የእጅ ሰላምታንም መቀነስ የሚሉት ይካተታሉ፡፡

እዚህ ላይ ለናረጋግጠው የሚገባ ነገር ቢኖር የሰው ልጅ መልካም ጸባይና ጥሩ መሰረቱ ግልጽ የሚሆነው በችግርና በመከራ ጊዜ መሆኑን ነው፡፡ ከመካከላችን መተዛዘን መስፋፋት ይኖርበታል፡፡ ከራስ ወዳድነትና ሸቀጦችን በአንድ ወቀት ወጋን ለመጨመር አስቦ በመኖፖል ከመያዝ መራቅም በዚህ ወቅት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ አንድሁም በገበያ ያሉ አላስፈላጊ ነገሮችን ያለመጠን በመግዛት የገበያን ሁኔታ ማዛባት ከራስ ወዳድነት አንዱ ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ማንኛውንም ነገር በሞኖፖል የሚያካበት ስህተተኛ ብቻ ነው) ይላሉ፡ በሌላ ሐዲስ ደግሞ ( እቃን የሚያካበት ከአላህ ምህረት የተባረረ ነው፡፡) ብለዋል፡፡ በሌላም ሐዲስ ( አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙም እስከሚወድ ደረስ በአላህ ያመነ አይሆንም፡፡) ብለዋል፡፡

* * * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ምንጊዜም ልንዘነጋቸው የማይገባ ከሆኑ ምስጢራዊ ሰበቦች አንደኛ በአላህ ያለን መመካት ያማረ እንድሆን ጥረት ማድረጋችን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُتَوَكِّلِينَ}

ትርጉሙም (በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡ ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ፡፡ አላህ በርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡ በአላህ መመካት ግዴታ ነው ስንልም ሰበብን ከማድረስ ጋር የማይፃረር መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ከአለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ግመሌን አስሬያት በአላህ ልመካ ወይስ ለቀወቂያት በአላህ ልመካ ሲል በጠየቃቸው ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (እሰራትና በአላህ ተመካ) ብለው ነበር መልስ የሰጡት፡፡

አሁን በአለንበት ወቅት ያለብን ግዴታ በጤና ዙሪያ የሚሰጡ ይፋዊ መግለጫዎችንና ግምት የሚሰጣቸውን ሳንሳዊ የጥንቃቄ ሂደቶችን መተግበር ሲሆን በመጨረሻ ነገሮችን ሁሉ ፍጥረታት በእጁ ለሆኑት ለታላቁ አላህ መተው ነው፡፡ በዚህም እውነተኛውን በአላህ መመካት የፈጸምን እንሆናለን፡፡

ከተጠቀሱት መስጢራዊ ሰበቦች ሌላው ደግሞ ለአላህ (ዐ.ወ.) ራሱን ዝቅ ዝቅ አድረጎ እሱን መጸለይ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَلَوْلَا إِذْ جَاءَهُم بَأْسُنَا تَضَرَّعُوا}

ትርጉሙም (ታዲያ ቅጣታችን በመጣባቸው ጊዜ አይዋደቁም ኖሯልን...) ማለት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ከልብ ራሳችንን ለአላህ ዝቅ ዝቅ ማድረግና ይህን መከራ እንዲያነሳልን ልብቻንን አጥረትን አላህን መለመን እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ይህ አጋጣሚ ሁላችንም ከጌታችን ጋር ያለንን ግንኙነት እንድንገመግም መልካም አጋጣሚ ሊሆን ይገባል፡፡

ከነዚህ ሰበቦችም አንዱ አንድ ሰው አላህን ዘወትር በማስታወስ ራሱን የሚጠብቅ መሆኑ ነው፡ ነብያችን አንድህ ይላሉ፡ (ማንኛውም በሌሊት ንጋትና በቀን ምሽት አንድህ በሚሉት ቃላት ሦስት ጊዜ የሚጸልይ የአላህ ባሪያ ምንም ነገር አይጎዳውም፡

بِسْمِ اللهِ الَّذِي لا يَضُرُّ مَعَ اسْمِهِ شَيْءٌ فِي الأَرْضِ وَلا فِي السَّمَاءِ وَهُوَ السَّمِيعُ العَلِيمُ،

አሁንም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (በአንድ ቦታ ያረፈ ሰውና

أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ

በማለት የሚጸልይ ከሆነ ከዚያ ቦታ እስከሚለቅ ደረስ ምንም ነገር አይጎዳውም፡፡)

ከነዚህም ምስጢራዊ ሰበቦች ሌላው በምጽዋት ወደአላህ በመቃረብ መከራው እንደወገድ መጸለይ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ገንዘባችሁን ዘካችሁን በማውጣት ጠብቁ፡፡ በሽተኛዎችችሁንም ምጽዋት በመስጠት ፈውሱ፡፡ ለመከራም ጸሎትን አመቻቹ፡፡)
ጌታችን ሆይ ጤና ካደርጋሃቸው ጋር ጤና አድርገን፡፡ አንተ ከጠበቅሃቸው ጋርም ጠብቅን የፈረድከውንም መጥፎ ነገር ከኛ አርቅልን አገራችንንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን አሜን፡፡

# (22)

## አላህ ለዓለም ካስቀመጣቸው ደንቦች አንዱ ለያንዳንዱ ነገር ሁሉ ሰበብ ያደረገለት መሆኑ ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَقُلِ اعْمَلُوا فَسَيَرَى اللَّهُ عَمَلَكُمْ وَرَسُولُهُ وَالْمُؤْمِنُونَ وَسَتُرَدُّونَ إِلَى عَالِمِ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በላቸውም ሥሩ አላህ ሥራችሁን በእርግጥ ያያልና፡፡ መልክተኛውና ምእምናንም (እንደዚሁ ያያሉ)፡፡ ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ወደ ኾነውም (አላህ) በእርግጥ ትመለሳላችሁ፡፡ ትሠሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
አላህ (ሱ.ወ.) ለዚህ ዓለም የሚንንቀቀስበት ደንብና ህግጋት አድርጎለታል፡፡ እንድሁም ተከታዩ ቀዳሚውን እንዳያልፍ ወይም ቀዳሚው ከተከታዩ እንዳይዘገይ እንቅስቃሴው የሚመጠንበት ቀጥተኛ የመጓዣ መስመር አስቀምጦለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{لَا الشَّمْسُ يَنبَغِي لَهَا أَن تُدْرِكَ الْقَمَرَ وَلَا اللَّيْلُ سَابِقُ النَّهَارِ وَكُلٌّ فِي فَلَكٍ يَسْبَحُونَ}

ትርጉሙም(ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም፡፡ ሌሊትም ቀንን (ያለ ጊዜው) ቀዳሚ አይኾንም፡፡ ሁሉም በመዞሪያቸው ውስጥ ይዋኛሉ፡፡") ማለት ነው፡፡ እንድሁም አንድህ ይላል፡

{فَلَن تَجِدَ لِسُنَّتِ اللَّهِ تَبْدِيلًا وَلَن تَجِدَ لِسُنَّتِ اللَّهِ تَحْوِيلًا}

ትርጉሙም(ለአላህ ደንብም መለለወጥን አታገኝም፡፡ ለአላህ ደንብም መዛወርን አታገኝም፡፡") ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) እነዚህን ደንቦች ያስቀመጠው የህይወት ስርአቶች የሚመጥኑ ሚዛን ይሆኑ ዘንድና ምድርን ማልማት እሷንም መጠበቅ እውን እንድሆን ነው፡፡ ይህም ተግባር ምድር ለሱ የተፈጠረችበት አላማ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾልናል፡

{هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ الْأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا}

ትርጉሙም (እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንዲህ ይላል፡

{وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا}

ትርጉሙም (በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፡፡) ማለት ነው፡፡

የነዚህን መለኮታዊ ደንቦችና ህግጋቶች ምንነት ተገንዝበው ይዘታቸውን ገቢራዊ ያደረጉ ማህበረሰቦች የእስልምና እምነት ተከታይ ባይሆኑም ወይም ከነመሰረቱ እምነት የለሽም እንኳን ቢሆኑም በልጽገው በዓለም ተቀዳሚውን ቦታ መያዛቸው አያጠራጥርም፡፡ ምክኒያቱም እንዚህ የፈጣሪ ደንቦች ለማንም አያደሉም ወይም አይወግኑምና፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ለዓለም እንቅስቃሴ ካስቀመጣቸው ደንቦች አንዱ አመክንዮ ያላቸው ነገሮች ሰበብ እንድከሰት ማድረጉ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለአንዳንድ ነገሮች ምክኒያትና አመክንዮአቸውን የፈጠረ ሲሆን ምክኒያቱን እንድናደርስም አዞናል፡፡ ይህውም ምክኒያቶቹ ሲከናወኑ ውጤቱ ይገኛልና ነው፡፡ ይህ ደንብ አላህ (ሱ.ወ.) ያስቀመጠው ድንቅ አጠቃላይ ህግ ሲሆን በማንኛውም ቦታና ዘመን ሊለወጥ አይችልም፡፡ ይህን ማለትም ለማንኛውም ነገር የራሱ የሆነ አመክንዮ አለው ማለት ነው፡፡ እሳት ቃጠሎን ያስከትላል፣ ግድያም ሞትን ያስከትላል፣ እርሻና ዘርም አዝርእትን ያስከትላል፣ መብላትም ጥጋብን ያስገኛል፣ ትጋትም ስኬትን ያስገኛል፣ ስንፍናና ችልተኝነት የነገሮች መክሸፍን ያስከትላል፣ ሌሎቹም እንደዚሁ፡፡

በምድር ላይ በትጋት መስራት ሃይማኖታዊና ብሄራዊ ግዴታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ይላል፡

{هُوَ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ ذَلُولًا فَامْشُوا فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُوا مِن رِّزْقِهِ وَإِلَيْهِ النُّشُورُ}

ትርጉሙም (እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፡፡ በጋራዎችዋና በመንገዶችዋም ኺዱ፡፡፡ ከሲሳዩም ብሉ፡፡ (ኋላ) መመለሻውም ወደእርሱ ብቻ ነው፡፡ ) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِن فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيرًا لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

ትርጉሙም(ሶለቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

የእስልምና እምነት በዚህች ዓለም የሚደረገውን ጥረት፣ ትጋት፣ ሥራ፣ የምድር ልማት በዚህ መልኩ ነው የሚገነዘበው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ዘርፎች በአሉ የስልጣኔ ጎዳናዎች በህዝቦች ጀርባ ለመገኘታችን ከሃማኖት ጋር ግንኙነት የለላቸውን ምክኒያቶች በመደርደር ስንፍናችንና ችልኻተኛቸን ለመሸፍን የምናደርገው ሙከራ ተቀባይነት የለውም፡፡

የነብያትንና የጻድቃንን ሕይዎት ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት በተለያዩ የእለት ተእለት ኑሯቸው ምክኒትን ለማድረስ ወሰን የለሽ ጥረት ያደርጉ እንደነበር በግልጽ እንገነዘባለን፡፡ እነሆ ሰይዲና ኑሕ (ዐ.ሰ.) በአናጺነት ይተዳደሩ ነበር፡፡ ለረዢም ጊዜ ህዝቦቻቸው አላህን እንዳመልኩ ጥሪ ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ አላህ (ሱ.ወ.) መርከብ እንዲሰሩ እንድህ በማለት አዘዛቸው፡

{وَاصْنَعِ الْفُلْكَ بِأَعْيُنِنَا وَوَحْيِنَا وَلَا تُخَاطِبْنِي فِي الَّذِينَ ظَلَمُوا إِنَّهُم مُّغْرَقُونَ}

ትርጉሙም (አላህም) «በጥበቃችንና በትእዛዛችንም ሆነህ መርከቢቱን ሥራ፡፡ በእነዚያም በበደሉት ሰዎች ነገር አታናግረኝ እነሱ በእርግጥ ሰማጮች ናቸውና» (አለው)፡፡ ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ አላህ (ሱ.ወ.) ያለምክኒያት ነብዩ ኑሕንና አማኞችን አድኖ ከሃዲዎችን ማጥፋት ይችል እንደነበር ልንገነዘብ ይገባል፡ ነገር ግን አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ያደረገው ምክኒያትን ማድስ በዓለም ያስቀመጠው ደንብ መሆኑን ሊያስተምረን ነው፡፡ ነብዩ ኑሕም የጌታቸውን ትእዛዝ በመቀበል መርከብ መስራት ጀመሩ፡፡ ሰዎች ቢያፌዙባቸውና ቢሳለቁባቸውም ያለችልታ ሥራቸውን ቀጥለዋል፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَيَصْنَعُ الْفُلْكَ وَكُلَّمَا مَرَّ عَلَيْهِ مَلأٌ مِنْ قَوْمِهِ سَخِرُوا مِنْهُ قَالَ إِنْ تَسْخَرُوا مِنَّا فَإِنَّا نَسْخَرُ مِنْكُمْ كَمَا تَسْخَرُونَ}

ትርጉሙም (ከወገኖቹም መሪዎቹ በእርሱ አጠገብ ባለፉ ቁጥር ከእርሱ እየተሳለቁ መርከቢቱን ይሠራል፡፡ «ከእኛ ብትሳለቁ እኛም እንደተሳለቃችሁብን ከናንተ እንሳለቅባችኋለን» አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ምክኒያትን ለማድረስ ያለመሰላቸት ሥራቸውን ስላከናወኑ አላህ ብችሮታው ነብዩ ኑሕንና አማኞችን ከጥፋት አድኗቸዋል፡፡

እንድሁም ሰይድና ዳውድ በብረት ሥራ ነበር የሚተዳደሩት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለርሳቸውና ለህዝቦቻቸው አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ ይህን ሥራ ያሳወቃቸው መሆኑን እንድህ በማለት ይገልጻል፡

{وَلَقَدْ آتَيْنَا دَاوُودَ مِنَّا فَضْلًا يَا جِبَالُ أَوِّبِي مَعَهُ وَالطَّيْرَ وَأَلَنَّا لَهُ الْحَدِيدَ * أَنِ اعْمَلْ
سَابِغَاتٍ وَقَدِّرْ فِي السَّرْدِ وَاعْمَلُوا صَالِحًا إِنِّي بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}

ትርጉሙም (ለዳውድም ከእኛ የኾነን ችሮታ በእርግጥ ሰጠነው፡፡ (አልንም)፡- «ተራራዎች ሆይ! ከእርሱ ጋር ውዳሴን መላልሱ፡፡ በራሪዎችንም (ገራንለት)፡፡ ብረትንም ለእርሱ አለዘብንለት፡፡ ሰፋፊዎችን ጥሩሮች ሥራ፡፡ በአሠራርዋም መጥን፡፡ መልካምንም ሥራ ሥሩ፡፡ እኔ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና (አልነው)፡፡ ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ከእጁ ሥራ ውጤት የተሻለ ምግብን መቼም ሊበላ አይችልም፡፡ የአላህ ነብይ ዳውድ (ዐ.ሰ.) ከእጃቸው ሥራ ውጤት ነበር የሚመገቡት)፡፡

የአላህ ነብይ ዩሲፍ (ዐ.ሰ.) ታሪክን ስንመለከት ህዝብና ሀገር አጥፊ ከሆነ ረሃብና ከአደገኛ አደጋ የዳነው ሰበብን በማድረስና ቅን የሆነን እቅድ በመንደፍ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ነብዩ ዩሱፍ ምክኒያትን በማድረስ በጥናት የተደገፍን የረዥም ጊዜ እቅድ በመንደፋቸው በዓለም ዙሪያ ከተከሰተው አጥፊ ረሃብ ሀገራቸውን ለማዳን ችለዋል፡፡ በሀገራቸውም ብልጽግናና የሲሳይ መትረፍረፍ ስለሰፈነ የተለያዩ ሀገራት ህዝቦች ከግብጽ ሲሳይ ለመቋደስ ወደክልሉ ይጎርፉ ነበር፡፡ ይህን ታሪክ ታላቁ አላህ በሚከተሉት አንቀጾች አስፍሮት እናገኛለን፡፡

{قَالَ تَزْرَعُونَ سَبْعَ سِنِينَ دَأَبًا فَمَا حَصَدتُّمْ فَذَرُوهُ فِي سُنبُلِهِ إِلَّا قَلِيلًا مِّمَّا تَأْكُلُونَ * ثُمَّ
يَأْتِي مِن بَعْدِ ذَلِكَ سَبْعٌ شِدَادٌ يَأْكُلْنَ مَا قَدَّمْتُمْ لَهُنَّ إِلَّا قَلِيلًا مِّمَّا تُحْصِنُونَ * ثُمَّ يَأْتِي مِن بَعْدِ
ذَلِكَ عَامٌ فِيهِ يُغَاثُ النَّاسُ وَفِيهِ يَعْصِرُونَ} .

ትርጉሙም (እርሱም) አለ፡- «ሰባትን የተከታተሉ ዓመታት ትዘራላችሁ፡፡ ያጨዳችሁትንም ሁሉ ከምትበሉት ጥቂት በስተቀር በዘለላው ውስጥ ተዉት፡፡ ከዚያም ከእነዚያ በኋላ ካደለባችሁት ጥቂት ሲቀር ለእነሱ ያደለባችሁትን ሁሉ የሚበሉ ሰባት የችግር ዓመታት ይመጣሉ፡፡ ከዚያም ከእነዚያ በኋላ ሰዎቹ በርሱ የሚዘነቡበት በርሱም (ወይንን) የሚጨምቁበት ዓመት ይመጣል፡፡) ማለት ነው፡፡

እነሆ የዒሳ እናት መርየም (ዐ.ሰ.) የአላህ ነብይ ዘከርያም ሳይቀሩ የተደነቁበት ሲሳይ በሰፊው ይመጣላት ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{كُلَّمَا دَخَلَ عَلَيْهَا زَكَرِيَّا الْمِحْرَابَ وَجَدَ عِندَهَا رِزْقًا قَالَ يَا مَرْيَمُ أَنَّى لَكِ هَذَا قَالَتْ هُوَ
مِنْ عِندِ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يَرْزُقُ مَن يَشَاءُ بِغَيْرِ حِسَابٍ}

ትርጉሙም (በርሷ ላይ በምኹራቧ በገባ ቁጥር እርስዋ ዘንድ ሲሳይን አገኘ፡፡ «መርየም ሆይ! ይህ ለአንቺ ከየት ነው» አላት፡፡ «እርሱ ከአላህ ዘንድ ነው፡፡ አላህ ለሚሻው ሰው ሲሳዩን ያለ ድካም ይሰጣል» አለችው፡፡) ማለት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ደካማ ሁና እያለና በህመም በምትሰቃይበት ወቅት የዘንባባውን ቀንዘል እንድትወዘውዝ ያዘዛት መሆኑን አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ሲል አብራርቷል፡

وَهُزِّي إِلَيْكِ بِجِذْعِ النَّخْلَةِ تُسَاقِطْ عَلَيْكِ رُطَبًا جَنِيًّا}

ትርጉሙም(የዘምባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዢት ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ያለምንም ድካም ቴምሩን እሸት ሊያረግፍላት ሲችል ቴምሩ አንዲረግፍ ቀንዘሉን ወዝውዢ ሲል ያዘዛት ሰበብን ማድረስ ግዴታ መሆኑን ሊያስተምርን ነው ሲሉ ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡ የሚከተለውን ግጥም የደረሰው ሰው እጅጉን ይደነቃል፡

በማንኛውም ነገር በራህማን ተመካ፡፡ አንድንም ቀን እሱን ከመጠየቅ አትቦዝን፡፡

አላህ ለመርየም ትምሩ እንዲወርድልሽ ቀንዘሉን ወዝውዢ ማለቱን አልሰማህም እንዴ፡፡

አላህ ቢፈለግ ያለመወዝወዝ ሊያቀርብላት ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ለማንኛውም ነገር ምክኒያት አላው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በተባረከው የስደት ጉዟቸው ሰበብን በማድረስ ድንቅ አርአያነት ያለው ተግባር በተጨባጭ አሳይተዋል፡፡ በሱም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በጥንቃቄ የተነደፈ እቅድና የረቀቀ ዝግጂት ከስኬት ግደታዎች ዋነኛውና ለውዝግብ መሻገሪያም ድልድይ መሆኑን ለህዝባቸው አስተምረውበታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሁለት የጭነት ከብት አዘገጁ፣ ታማኝን ጓደኛ መረጡ፣ ለመውጣትም ተስማሚውን ቦታና ጊዜ መረጡ፣ በሌሊት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ከአቡ በክር ቤት ወጡ፡፡ በሀሳብም ሆነ በአስተያየት ብሎም በእምነትም መለያየት ቢኖርም አንኳ ብቃት ያለውን ማስቀደም ጠቃሚ ነው በሚለው መርህ ስለሚያምኑ በልዩ ከሀሎት የተካነን መንገድ መሪ መረጡ፡፡ ከዚያም ዓምር ኢብን ፉሃይራህ የተባለው ሰው ከኋላ ኋላቸው እየተከተለ ዱካቸውን እንዲያጠፋ አዘዙ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እሳቸውንና ባልደረባቸው ለማዳን ዋስትናውን የወሰደ መሆኑን ጠንቅቀው እያቁ ሳለ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ይህን ያደረጉት አላህ በዚህ ዓለም ያሰቀመጠው መክኒያትን የማድረስ ደንብ መኖሩን ሊያስተምሩን ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረት እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስይዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

እዚህ ላይ የስኬት ምክኒያትን ማድረስ በአላህ (ዐ.ወ.) ከመመካት ጋር የማይፃረርና የማይጋጭ መሆኑን ልናስገነዝብ እንወዳለን፡፡ እውነተኛ በአላህ መመካትን የሚያውቅ ሰው ሰበብን በማድረስ በሥራው ይተጋል፡፡ እውነተኛ በአላህ ተመኪ ሰበብን ያደርሳል፡፡ የችሎታውን ሁሉ ይሰራል፡፡ ከዚያም የነገሩን ሁሉ መጨረሻ የስኬት፣ የችሮታና የረደኤት ባለቤት ለሆነው ለአላህ (ዐ.ወ.) ይተዋል፡ አላህ (ሱ.ወ.) (አንትን ብቻ እንገዛለን ከአንትም ብቻ እርዳታን አንፈልጋለን) እንድንል አዞናል፡፡

በአላህ መመካትን በተጨባጭ ሲያሳዩ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እናንተ እውነተኛን መመካት በአላህ የምትመኩ ቢሆን ኖሮ ማለዳ ሆደ ሸላጋ ሆና ወጥታ ማታ ሆዷ ሞልቶ የምትመለስን ወፍ ሲሳይ እንደቸራት ሁሉ አላህ ለናንትም ሲሳዩን በለግሳችሁ ነበር፡፡)

ወፍ ምግብም ሆነ መጠጥ አታከማችም፡፡ ነገር ግን ከአላህ ችሮታ ሲሳይን ለመፈለግ ከአለት እለት ሥራዋ አትቦዝንም፡፡ በማለዳ ተነስታ ወደስራዋ ትሰማራለች፡፡ በመጨረሻም ማታ አላህ (ዐ.ወ.) በቸራት ሲሳይ ሆዷን ሞልታ ትመለሳለች፡፡ ለእድሜ ልኳ የሚበቃ ሲሳይ ቢኖራትም ይህን ተግባሯን አታቆምም፡፡ ይህውም ጧት ከሥራ መውጣትና መታ የአላህ ችሮታ አግኝቶ መመለስ ፈጣሪ በዚህ ዓለም ያስቀመጠው ደንቡ በመሆኑ ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በማንኛወም ነገር እውነተኛውን የምክኒያት ማድረስ ትረጉም ለባልደረቦቻቸው ያስተምሩ ነበር፡፡ የማይጠቅምና ጎጂ ከሆነው የይስሙላ በአላህ መመካት እንዲታቀቡም ይመክሯቸው ነበር፡፡ የእድገትና ብልጸግና ሰበብን ባለማደረሳችን ከፍተኛ ኃጢአት ፈጽመናል እንድሁም ራሳችንና ልጆቻንን በድለናል ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

ሃይማኖታችን በእውቀት፣ እድገት፣ ስልጣኔ፣ ውበትና ሁሉንም ሰው በመጥቀም የተመሰረተ እምነት ነው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ የአላህ መለከተኛ ሆይ! ግመሌን ለቅቂያት በአላህ ልመካ ወይንስ አስሪያት በአላህ ልመካ ሲል ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጠየቀ፡፡ አስቸውም (እሰራትና በአላህ ተመካ) አሉት፡፡ ግመሊቷን ማሰር ለመኖሯ ዋስትና የሚሆን ሰበብን ማድረስ ነው፡፡ ሳይስሩ መተው ደግሞ ለመጥፋቷ ወይም ለመሰረቋ ምክኒያት ሊሆን ይችላል፡፡

ጌታችን ሆይ! ለሃይማኖታችን ጠቃሚ፣ ለህዝባችን እድገትና ለሀገራችን ብልጽግና አጋዥ የሆነን ስኬት ስጠን፡፡ አሜን፡፡

# (23)

## መቻቻል ከሃማኖትና ከስርኣት አንፃር፣ ለብሄራዊ ውህደት መጠናከር የወቅቱ ግዴታ ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**{يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ}**

ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም ( አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም (ቅን በሆነው መቻቻል ነው የተላኩት) የኣሉት ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል**
ነብያችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.)መቻቻልና ገራገነትን የህይወት ስርአት ያደረገ ዓለም አቀፋዊ መልእክት ነው ይዘው የመመጡት፡፡ የሃይማኖት መጨነቅ፣ የግዴታ መቸገርና ማጥበቅም የለበትም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينِ مِنْ حَرَجٍ }**

ትርጉሙም (በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሃይማኖት ገር ነው፡፡ አንድም ሰው ሃይማኖትን እይታገለውም የሚያሸነፈው ቢሆን እንጂ በሚገባ አስተካክላችሁ ሥሩ ካልቻላችሁም ወደትክክሉ ለመቃረብ ሞክሩ፡፡ ማለዳ፣ ከሣዓትም በጥቂቱም ቢሆን በሌሊት ዒባዳን በማድረስ ታገዙ፡፡) በእስልምና ሃይማኖት መቻቻል የምንሰነዝረው ቃልና የምናነግበው መፈክር ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሙስሊም በእለት ተእለት ሕይወቱ የሚከተለው እምነት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) መቻቻል ባሮቹ እንዲመሩበት ያዘዘው መርህና የምህረቱና ይቀር የማለቱ ምክኒያት መሆኑን እንድህ በማለት ገልጾታል፡

**وَلْيَعْفُوا وَلْيَصْفَحُوا أَلَا تُحِبُّونَ أَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَكُمْ} .**

ትርጉሙም (ይቅርታም ያድርጉ፡፡ (ጥፋተኞቹን) ይለፉም፡፡ አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን..) ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ ልናስገነዝበው የምንፈልገው ነገር ቢኖር በአሁኑ ወቅት ጥረት የምናደርገው መቻቻል የሕይወት ሥነ ስርአት እንዲሆን መሆኑን ነው፡፡ ምክኒያቱም የእስልምና እምነት መቻቻልን እንዲንተገብር ያዘዘው ተጨባጭ የሕይወት ስርአት እንዲሆን በመሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ይቅርታና መቻቻል ከሰዎች መካከል እንዲሰፍን በበርካታ አንቀጾች አዟል፡፡ እንድህም ይላል፡

**{وَلَا تَسْتَوِي الْحَسَنَةُ وَلَا السَّيِّئَةُ ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ كَأَنَّهُ وَلِيٌّ حَمِيمٌ}**

ትርጉሙም (መልካሚቱና ክፉይቱም (ጸባይ) አይተካከሉም፡፡ በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጸባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፡፡ ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችነ (ሶ.ዐ.ወ.)ከሰዎች ጋር በነበራቸው ግንኙነት መቻቻልን ግልጽ በሆነ መልኩ በተጨባጭ አሳይተዋል፡፡ በመሆኑም ለተከታዱቻቸው ብሎም ለመላው የሰው ልጅ መልካም አርኣያ ነበሩ፡፡ እንዲህም ይላሉ፡ (እኔ ፈጣሪ ለሰው ልጅ የቸረኝ እዝነት ነኝ፡ ፡) ( ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የምእምናን እናት ዓኢሻ እንዲህ ይላሉ፡ ‹ ነብያችን ከሆለት ነገሮች እንዲመርጡ ተጠይቀው አያውቁም ወንጀል እስከሌለበት ድረስ ቀላሉን የሚመርጡ ቢሆን እንጂ፡፡ ወንጀል ያለበት ከሆነ ደግሞ ከማነም ሰው የበለጠ ይርቁታል፡፡)

ሁላችንም ራሰችንን ልንጠይቅና ግልጽ ልንሆበት የሚገባ ነገር ቢኖር እኛ በሃይማኖታችን ይህን ስርአት ገቢራዊ እያደረግነው ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ መቻቻል ሁሉም ሙስሊም በሁሉም የህይወቱ መስክ ገቢራዊ ሊያደርገው የሚገባ ስርኣት ነው፡፡ በዚህ የመቻቻል ዘርፍ ቀድሞ የሚጠቀሰው ከባልና ሚስት መካከል ያለው መቻቻል ነው፡፡ የባልና ሚስት ትስስር ከሰው ልጆች መካከል ካሉ ትስስሮች እጅግ የላቀው እንደሆነ ሊታውንት ይጠቁማሉ ፡፡ ይህ ትስስር በፍቅር፣ በእዝነትና በመልካም መቻቻል የተመሰረተ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

**{وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا لِّتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً}**

ትርጉሙም(ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

**{وَعَاشِرُوهُنَّ بِالْمَعْرُوفِ فَإِن كَرِهْتُمُوهُنَّ فَعَسَى أَن تَكْرَهُواْ شَيْئاً وَيَجْعَلَ اللّهُ فِيهِ خَيْراً كَثِيراً}**

ትርጉሙም (በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፡፡ ብትጠሉዋቸውም (ታገሱ)፡፡ አንዳችን ነገር ብትጠሉ አላህም በእርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይቻላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

{وَلَهُنَّ مِثْلُ الَّذِي عَلَيْهِنَّ بِالْمَعْرُوفِ}

ትርጉሙም (ለእነርሱም (ለሴቶች) የዚያ በእነርሱ ላይ ያለባቸው (ግዳጅ) ብጤ በመልካም አኑዋኑዋር (በባሎቻቸው ላይ መብት) አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ማለትም ለሴቶች ለወንዶች ያለቸው ዓይነት መብት አላቸው ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በላጩ ለቤተሰቡ ደግ የሆነው ነው እኔ ከናንት ይበልጥ ለቤተሰቤ ደግ ነኝ፡፡) ነብያችን ስለሴቶች አደራ በተለያዩ ሐዲሶቻቸው ተናግረዋል፡፡ እንድህም ይላሉ፡ (አንድ ሙእሚን ሙእሚን የሆንች ሚስቱን አያስቆጣ፡፡ ምክኒያቱም ከሷ አንድን ጠባይ ቢጠላም ሌላውን ጠባዩዋን ሊወድ ይችላልና፡፡) ከእለተ ህልፈታቸው በፊት ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የተውት ኑዛዜ (ስለሴቶች አደራ ተባባሉ) የሚል ነበር፡፡

በመሆኑም መቻቻል ከባልና ሚስት መካከል በእኩልነት የሚተገብር ስርኣትና ለቤተሰብ ሰላምና መልካም ስርኣት ዘላቂነት ሰብኣዊ ህግ ሊሆን ይገባል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡደርዳእ የተባሉት ባልደረባ ለባለቤታቸው ‹ ተናድቼ ስታይኝ እኔን ለማስደሰት ሞክሪ እኔም ተናደሽ ሳይሽ አንችን ለማስደሰት እሞክራለሁ› የሚል በሰብእ፣ መቻቻልና በፍትህ የተሞላ ደንብ አስቀምጠው ሕይወታቸውን በመምራታቸው ሲደነቁ ይኖራሉ፡፡

በሁለተኛ ደረቻ የሚጠቀሰው የመቻቻል ስርአት ደግሞ ከጎረቤት ጋር ያለው መቻቻል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እነድህ ይላል፡

{وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا وَبِذِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينِ وَالْجَارِ ذِي الْقُرْبَى وَالْجَارِ الْجُنُبِ وَالصَّاحِبِ بِالْجَنْبِ}

ትርጉሙም (አላህንም ተገዙ፡፡ በእርሱም ምንንም አታጋሩ፡፡ በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም፣ በቅርብ ጎረቤትም፣ በሩቅ ጎረቤትም፣ በጎን ባልደረባም፣..) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ስለጎረቤት የተናገሯቸው የአደራ ቃላት በርካቶች ናቸው፡፡ ከነሱም መካከል ( ጂብሪል ስለጎረቤት አዘውትሮ አደራ በማብዛቱ ካንት ንብረት ወራሾች እንዱ ይሁን ይለኛል ብዬ አስከመጠራጠር ደረሼ ነበር፡፡) እንድሁም (በአላህና በመጨረሻይቱም ቀን የሚያምን ሰው ጎረቤት ያክብር፡፡) እንድሁም ነብያችን (በአላህ ይሁንብኝ አያምንም በአላህ ይሁንብኝ አያምንም በአላህ ይሁንብኝ አያምንም) አሉ ሰዎችም እሱ ማነው በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ጎረቤቱ ተንኮሉን የሚፈራው ሰው) አሉ፡፡እንድሁም ( በአጠገቡ ያለው ጎረቤቱ ተርቦ እሱ ጠግቦ የሚያድር እሱ ሙእሚን ኤደልም) የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

እንድሁም ከሥራ ባልደረቦች፣ ከዩኒቨርስቲና ከትምህርት ቤት ጓደኛሞች መካከልም መቻቻል ሊሰፍን ይገባል፡፡ ከመላ የሰው ልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ጠንካራ ሊሆን እንደሚገባ ቅዱስ ቁርኣን እንድህ በማለት ጠቁሟል፡

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُمْ مِنْ نَكَرٍ وَأُنْثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِنْدَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከመላው የሰው ልጆች እንድሁም ከባልደረቦቻቸው ጋር በነበራቸው ግንኙነት በመልካም ጸባይ ይዋዋሉ እንደነበር አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾልናል፡

{فَبِمَا رَحْمَةٍ مِنَ اللَّهِ لِنْتَ لَهُمْ وَلَوْ كُنْتَ فَظًّا غَلِيظَ الْقَلْبِ لَانْفَضُّوا مِنْ حَوْلِكَ فَاعْفُ عَنْهُمْ وَاسْتَغْفِرْ لَهُمْ وَشَاوِرْهُمْ فِي الْأَمْرِ} .

ትርጉሙም (ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብከላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡ ከእነርሱም ይቅር በል፡፡ ለእነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው፡፡ በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

በመንገድና በተራንስፖርትም መቻቻል ሊስፋፋ ይገባል፡፡ ምክኒያቱም ሰዎች በተፈጥሮ ከፊላቸው ደግ ከፊላቸው ደግሞ ጨካኝ በመሆናቸው አንድ ሰው በመንገድም ሆነ በተራንስፖርት ሰዎች ችግር ሊያደርሱበት ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ታዳ በመቻል፣ በለዘብተኝነትና በስነ ስርአት ማሳልፍ ይጠበቅበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

{وَعِبَادُ الرَّحْمَٰنِ الَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى الْأَرْضِ هَوْنًا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ الْجَاهِلُونَ قَالُوا سَلَامًا}

ትርጉሙም (የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚኼዱት፣ ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ያመናችሁ እስካልሆናችሁ ድረስ ጀነትን አትገቡም፡፡ የምትዋደዱ እስከምትሆኑ ድረስ ደግሞ አማኞች አትሆኑም፡፡ እሱን ከፈጸማችሁት እንዲትዋደዱ የሚያደርጋችሁን ነገር ልንገራችሁን? ከመካከላችሁ ሰላምታን አስፋፉ፡፡) ለዳከሞችና ሴቶች መራራት እንድሁም የሌሎችን ስሜት ማከበር ተፈላጊ መሆኑን ነብያችን እንድህ በማለት ጠቁመዋል፡ ( ርህራሄ በአንድ ነገር ሊኖር አይችልም የሚያውበው ቢሆን እንጂ፡፡ ከአንድም ነገር ለሲውር አይችልም አስከፊ የሚያደርገው ቢሆን እንጂ)

በገንዘብ የወጭ ግዴታውን መወጣት በአላህና በመልክተኛው የማመን ምልክት እንደሁም የጻድቀነት ገጽታ መሆኑንና በሱም ልቦች የሚተሳሰሩ መሆኑን አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ሲል ገልጧል፡

{لَنْ تَنَالُوا الْبِرَّ حَتَّى تُنْفِقُوا مِمَّا تُحِبُّونَ}

ትርጉሙም (የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጎን ሥራ (ዋጋውን) አታገኙም። ማለት ነው።

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ ( ቸር ሰው ከአላህ፣ ከጀነትና ከሰዎች የቀረበ ነው። በአንጻሩም ከእሳት የራቀ ነው።)

ሌላው የመቻቻል ገጽታ ደግሞ በመሸፕ፣ በመግዛትና በመፋረድ ወቅት የሚከሰተው መቻቻል ነው። ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (በሽጠ፣ በገዛና በተፋረደም ጊዜ ገራገርነትን ያሰዬን ሰው አላህ ይማረው።)

አልዒርባድ ኢብነ ሳሪያ የተባሉ ባልደረባ እንድ ይላሉ፡ እኔ ለነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የግመል ወይፈን ሸፕኩላቸው ዋጋውን ልጠይቅ በሄድኩ ጊዜ አዎ አዳድስ ብሮች ነው እምሰጥህ አሉኝና በሚያስደስት መልኩ ከፈሉኝ። እንድሁም አንድ ዘላን መጣና ወይፈኔን ስጡኝ አለ እሳቸውም ከወይፈኑ ተለቅ ያለ ወይፈን ሰጡት አሱም ያላህ መልክተኛ ሆይ ይህኮ ከኔ ወይፈን በጣም የበለጠ ነው አለ። እሳቸውም ( ከሰዎች በላጬኮ በሚከፍል ጊዜ ከነሱ በተሻለ መልኩ የሚከፍል ሰው ነው ) አሉት።

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) መቻቻልንና ገራገርነትን እውን የሚያደርግን ነገር ሁሉ ሰዎች እንደከተሉ ገፋፍተዋል እዳ መክፈል ላልቻሉ ሰዎች እዳን መተው አለዚያም ጊዜ መስጠት ከሰዎች መከሰከል መተባበርን እንደሚፈጥር እንድህ በማለት አመልክተዋል፡ (እዳ መክፈል ላልቻለ ሰው ጊዜ የሰጠ ወይም እዳውን የተው አላህ በጥላው ሰር ያስገባዋል።)

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ።

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው። የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ።

**ሙስሊም ወንድሞች**

ከመቻቻልገጽታዎች እጅግ ቀላልና ትሩፋቱ የላቀ የሆነው የመልካም ቃል ገጽታ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንድፍ ይላል፡

**وَقُلْ لِعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ}**

ትርጉሙም (ለባሮቸም በል መልካሚቱን ይናገሩ) መለጽ ነው።

የሰው ልጆች ቀለማቸው፣ ሃይማታቸውና ዜግነታቸው የተለያየ ቢሆንም በመልካም አንደበት እጅጉን ይቀራረባሉ። መልካም አንደበት የደግ አስተዳደግና የመልካም ጸባይ መግለጫ ነው። መልካም ጸባይ ማለት ነገሮችን አለማወሳሰብ፣ ፈካ ባለ ፊትና በልዝብ ቃል ሰዎችን ማናገር እንደሆነ ሊታውንት ይጠቁማሉ። አላህ (ዐ.ወ.) ነብዩ ሙሳ ፎሮዖን ያለበትን ኩራትና ያለውን ግትር አቋም እያወቀ በልዝብ ቃል እንዲያናግሩት እንድህ በማለት አዟል፡

{اذْهَبَا إِلَى فِرْعَوْنَ إِنَّهُ طَغَى فَقُولَا لَهُ قَوْلًا لَيِّنًا لَعَلَّهُ يَتَذَكَّرُ أَوْ يَخْشَى}

ትርጉሙም (ወደ ፈርዖን ኺዱ፡፡ እርሱ ወሰን አልፏልና፡፡ «እርሱም ይገሰጽ ወይም ይፈራ ዘንድ፤ ለእርሱ ልዝብን ቃል ተናገሩት፡፡»)ማለት ነው፡፡ እንድሁም ከማንኛውም ውደቅ ንግግር ነገር እንድንርቅ እንድህ በማለት አዞናል፡

{ وَالَّذِينَ هُمْ عَنِ اللَّغْوِ مُعْرِضُونَ}

እንድሁም እንድህ ይላል፡ ትርጉሙም( እነዚያም እነርሱ ከውድቅ ንግግር ራቂዎች፡፡ ) ማለት ነው እንድሁ እንድህ ላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَقُولُوا قَوْلًا سَدِيدًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ፡፡) ማለት ነው እንድሁም እንድህ ይላል፡

{أَلَمْ تَرَ كَيْفَ ضَرَبَ اللَّهُ مَثَلاً كَلِمَةً طَيِّبَةً كَشَجَرَةٍ طَيِّبَةٍ أَصْلُهَا ثَابِتٌ وَفَرْعُهَا فِي السَّمَاءِ تُؤْتِي أُكُلَهَا كُلَّ حِينٍ بِإِذْنِ رَبِّهَا وَيَضْرِبُ اللَّهُ الأَمْثَالَ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ}

ትርጉሙም (አላህ መልካምን ቃል ሥርዋ (በምድር ውስጥ) የተደላደለች ቅርንጫፍዋም ወደ ሰማይ (የረዘመች) እንደሆነች መልካም ዛፍ አድርጎ ምሳሌን እንዴት እንደገለጸ አላየኸምን) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ (አንድ ሰው ምንም ትኩረት ሳይሰጠው አላህ የሚወደውን ቃል ተናግሮ አላህ በርካታ ደረጃዎችን ከፍ ሊያደርገው ይችላል፡ እንድሁም አንድ ሰው ምንም ዓይነት ትኩረት ሳይሰጠው አላህን የሚስቆጣ ቃል ተናግሮ በገሀነም ሊዘፈቅባት ይችላል፡፡) መጥፎ ቃል ከመሰንዘር መራቅም የመቻቻል ገጽታ ነው፡፡ ነብያችን እንድህ ይላሉ፡ (ሙእሚን ስድብ የሚያበዛ፣ ሰዎችን የሚያነውር፣ መጥፎና እርኩስ ቃልት ተናጋሪ አይደለም)

መቻቻል ወይም ገራገርነት ማለት ከማክረርና ከሀኬት መካከል ያለ ልከኝነት ሲሆን ሁለቱም በመቻቻልና በገራገርነት ከተሞላው ከእስልምና እምነት ስርኣት እጅጉን የራቁ ናቸው፡፡

ጌታችን ሆይ! በቃላችንም ሆነ በሥራችን መቻቻልን ለግሰን፡፡ ከመካከላችን ያለውን ነገር ሁሉ አብጅልን፡፡ አገራችንም ጠብቅልን አሚን፡፡

# (24)

## የአጠቃላይ ስርአት መከበርና ለህዝቦች እድገት ያለው አስተዋጽኦ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**قُلْ إِنَّنِي هَدَانِي رَبِّي إِلَى صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِّلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ}**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም (እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲኾን የአብርሃምን መንገድ መራኝ፡፡ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም» በል፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የሰለጠኑ ህዝቦችና የበለጸጉ አገራት የአጠቃላይ ስርአት ማክበርን የህዎታቸው መመሪያ አድርገው ይኖራሉ፡፡ በነዚህ ህዝቦች ዘንድ አጠቃላይ ስነ ስርአት እንደተቀጥላና በእት ተእለት ህይወት ህዳግ የሚገኝ ነገር ሳይሆን ከሰብአዊ ሰነ ምግባር እሴቶች ተለይቶ የማይታይ ተግባር ነው፡፡ይህም ከፈጣሪው እንድሁም ከአጠቃላይ ፍጥረታት ጋር ለአለው ለሰው ልጅ ግንኙነት በርካታ የአጠቃላይ ስነ ስርአት ደንቦች መሰረት ከአስቀመጠው ከቅኑ ሃይማኖታችን መርሆች ጋር የሚጣጣም ተግባር ነው፡፡ ከነዚህም ስርአቶች በመጀመሪያ የሚጠቀሰው ንጽህና ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ለአካል፣ ለአልባሳትና ለቦታ ነጽህና ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

ا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا قُمْتُمْ إِلَى الصَّلَاةِ فَاغْسِلُوا وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى الْمَرَافِقِ وَامْسَحُوا بِرُءُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى الْكَعْبَيْنِ وَإِنْ كُنْتُمْ جُنُبًا فَاطَّهَّرُوا وَإِنْ كُنْتُمْ مَرْضَى أَوْ عَلَى سَفَرٍ أَوْ جَاءَ أَحَدٌ مِنْكُمْ مِنَ الْغَائِطِ أَوْ لَامَسْتُمُ النِّسَاءَ فَلَمْ تَجِدُوا مَاءً فَتَيَمَّمُوا صَعِيدًا طَيِّبًا فَامْسَحُوا بِوُجُوهِكُمْ وَأَيْدِيكُمْ مِنْهُ مَا يُرِيدُ اللَّهُ لِيَجْعَلَ عَلَيْكُمْ مِنْ حَرَجٍ وَلَكِنْ يُرِيدُ لِيُطَهِّرَكُمْ وَلِيُتِمَّ نِعْمَتَهُ عَلَيْكُمْ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ፡፡ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)፡፡ (ሴት ጋር በመገናኘት ወይም በሌላ ምክንያት «ጀናባ») ብትኾኑ (ገላችሁን) ታጠቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም ወይም ከእናንተ አንዳችሁ ከዓይነ ምድር ቢመጣ ወይም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ ንጹሕን የምድር ገጽ አስቡ ፡፡ ከሱም ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁን አብሱ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ ምንም ችግር ሊያደርግ አይሻም፡፡ ግን ታመሰግኑ ዘንድ ሊያጠራችሁና ጸጋውን በእናንተ ላይ ሊሞላ ይሻል፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ}

ትርጉሙም (ልብስህንም አጽዳ) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ብለዋል፡ (አንዳችሁ ከእንቅልፉ በሚነሳበት ወቅት መጀመሪያ ሦስት ጊዜ ሳይታጠብ እጁን እቃ ውስጥ አይክተት፡፡...) በሌላ ሐዲስም እንድህ ብለዋል፡ (እርግማን የሚያመጡ ሁለት ነገሮችን ተጠንቀቁ) ሰዎችም እርግማን የሚያመጡ ሁለት ነገሮች ምን ምን ናቸው ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ሰዎች በሚያልፉበት መንገድና በጥላው በሚያርፉበት ጥላ ስር ሰገራ መውጣት ናቸው) በማለት መለሱ፡፡

የእስልምና እምነት ውጫዊ ንጽህና ለውስጣዊ ንጽህና ምክኒያት መሆኑን በመግለጽ የሁለቱን ንጽህናዎች ትስስር አረጋግጧል፡፡ አንድ ሰው የአካሉን ንጽህና በመጠበቁ የአላህን ምህረት ያገኛል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሙስሊም ወይም ሙእሚን የአላህ ባሪያ ውዱእ ሲያደርግ ፊቱን በሚያጥብ ጊዜ ከውሃው ወይም ከመጨረሻይቱ የውሃው ንጣፊ ጋር በዓይኑ የፈጸማቸው ወንጀሎች በሙሉ ከፊቱ ይወገዳሉ፡፡ እጆቹን በሚያጥብ ጊዜም ከውሃው ወይም ከውሃው የመጨረሻ ንጣፊ ጋር በእጁ የፈጸማቸው ወንጀሎቹ ይወገዳሉ፡፡ እግሩን በሚያጥብ ጊዜም ከውሃው ወይም ከውሃው የመጨረሻ ንጣፊ ጋር በእግሩ በመጓዝ የፈጸማቸው ወንጀሎች ይወገዳሉ፡፡ በመጨረሻም ከወንጀል ነፃ ሆኖ ይወጣል፡፡) የእስልምና እምነት ለግል ንጽህና ትኩረት የሰጠውን ያህል ለአጠቃላይ ንጽህናም ተኩረት ሰጥቷል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ግቢያችሁን አጽዱ)፡፡ ግቢ ሲባል የቤት፣ የትምህርት ቤት፣ የፋክቶሪ፣ የመዝናኛ ማእከልና የክበባት ግቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያም አልፎ መንገዶች፣ አደባባዮችና ሌሎችንም የህዝብ መገልገያ ክልሎችን ያካትታል፡፡

ሌላው የአጠቃላይ ስርአት ክፍል ደግሞ የተለምዶ ደንቦችን ማክበር የሚለው ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ አጠቃላይ ጥቅሙን ለማስከበር፣ የአባላትን ስነ ምግባር ለመመጥንና ሰብኣዊ መብትን ለማስከበር የሚጠቀምባቸው በርካታ ደንቦችና ህግጋት አሉት፡፡ የበለጸጉ አገራትን መሃበረሰብ ስንመለከት ለዚህ ደረጃ ያበቃቸው ህግጋትን ማክበራቸውና ግዴታቸውን በሚገባ ለመወጣት ያደረጉት ጥረት መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ በእውነቱ ይህ ስርኣታቸው የሌሎችን መብት ማክበር፣ እንድሁም

መብትን ለማግኘት ግዴታን መወጣትና ከሰዎች ጋር ያለህ ውለታ ለአንት ሊሰጡህ የምተወደውን ዓይነት ለሰዎች አክብሮት መስጠት የሚሉትን ቅን መርሆች ያካተተ ነው፡፡
የዚህ ዓይነቱ ተግባር እምነትን ምሉእ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ጠቁመዋል፡ (አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙም እስከሚወድ ደረስ አማኝ አይሆንም፡፡) ይህን ጉዳይ እውን የማድረግም ሀላፊነት የመላ ማህበረሰቡ አባላት መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አመልከተዋል፡ ( ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ እያንዳንዳችሁም ስለሚጠብቀው ነገር ተጠያቂ ነው፡፡ የሀገር መሪ ጠባቂ ነው ስለሚጠብቀውም ይጠየቃል፡፡ አንድ ሰው የቤተሰቡ ጠባቂ ነው ስለሚጠብቀውም ይጠየቃል፡፡ አንድት ሴትም የባሏ ቤት ጠባቂ ናት ስለምትጠብቀውም ትጠየቃለች፡፡ አንድ አገልጋይም የጌታው ገንዘብ ጠባቂ ነው ስለሚጠብቀውም ይጠየቃል፡፡...) ደንብን በማክበርና መዋቅሮቹን በማጠናከር ፍትህ ይነግሳል፣ ፍቅር፣ መዋደድና የወንድም ተማማችነት መንፈስ ይሰፍናል፡፡ መላ የማህበረሰቡ አባላትም በሰላም፣ በጽጥታና በተረጋጋ መልኩ የመኖር እድሉ እጅጉን ይሰፋል፡፡
ከተጠቀሰው አጠቃላይ ስርአት ሌላው ደግም አጠቃላይ የህዝብ ስሜቶችን ማክበር የሚለው ነው፡፡ የእስልምና እምነት መመሪያዎች ስነ ምግባርን የሚያስተካክሉ፣ ስሜቶችን ረቂቅ የሚያደርጉ፣ የሰዎችን ልቦች የሚያስተሳስሩ ሲሆኑ የሰዎች ትውፊቶችንና ልምዶችን በማክበር ዘርፍ ተመጣጣኝ ደንቦችን ያቀፉ ናቸው፡፡ የእስልምና ህግጋት ሰዎችን የማያስደነበር መልካምን ነገር ሁሉ ያጸደቀ ሲሆን በሰዎች ላይ ጉዳት የሚያደርስን አርከስ ሁሉ እርም አድርጓል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ الرَّسُولَ النَّبِيَّ الأُمِّيَّ الَّذِي يَجِدُونَهُ مَكْتُوبًا عِندَهُمْ فِي التَّوْرَاةِ وَالإِنجِيلِ يَأْمُرُهُم بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَاهُمْ عَنِ الْمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ الطَّيِّبَاتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ الْخَبَائِثَ} .

ትርጉሙም (ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት (በእርግጥ እጽፍለታለሁ)፡፡ በበጎ ሥራ ያዛቸዋል፡፡ ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል፡፡ መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል፡፡ መጥፎ ነገሮችንም በእነርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡
አጠቀላለይ ደንቦችን ማክበር ስንል አንድ ሰው በአልባሳቱ፣ በምግቡና በመጠጡ መጠነኛ መሆን እንድሁም በህግ የተጠላ ከሆነው ከማባከን መራቅ ያለበት መሆኑን ያካትታል፡፡
{يَا بَنِي آدَمَ خُذُوا زِينَتَكُمْ عِنْدَ كُلِّ مَسْجِدٍ وَكُلُوا وَاشْرَبُوا وَلَا تُسْرِفُوا إِنَّهُ لَا يُحِبُّ الْمُسْرِفِينَ}

ትርጉሙም (የአዳም ልጆች ሆይ! (ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ፡፡ ብሉም፤ ጠጡም፤ አታባክኑም፡፡ እርሱ አባካኞችን አይወድምና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَوْفُوا بِالْعُقُودِ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በቃል ኪዳኖች ሙሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

እንድሁም በነዚህ ደንቦች የአንድ ሰው እንቅስቃሴና ገጽታውም ይካተታል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር የተባሉት በልደረባ ነብችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ተንጋሎ ተኝቶ አንድ እግሩን በሌላው እግሩ ላይ ማንሳቱን ከልክለዋል ሲሉ አውርተዋል፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የአንዳችሁ ጫማ ጠፈር ከተበጠስ ከመቀጠሉ በፊት በአንድ ጫማ ብቻ አይሂድ፡፡)

እንድ ሰው ሰዎች የሚጠሉትን ድምጽ ከማሰማትና የማይቀበሉትን ተግባር ከመፈጸም መታቀብ የአጠቃላይ ደንብ መከበር ሌላው ገጽታ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዑመር የሚከተለውን አውርተዋል፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አጠገብ አስገሳው ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ይህን ከኛ ዘንድ ማስገሳትህን አቁም ከናንት መካከል በዚህች ዓለም በብዛት የሚጠግብ ሰው ያ በትንሳኤ ቀን ለረዥም ጊዜ የሚራበው ሰው ነው) አሉ፡፡ ሊቃውንት እንደሚሉት ይህ በጥጋብ ምክኒት የሚከሰተው ማስገሳት በእምነቱ ደንብ የተከለከለ ባይሆንም ከአጠቃላይ ገብረገብነት ጋር የሚፃረር በመሆኑ ነብያችን ከልክለውታል፡፡ አላህ (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْفُؤَادَ كُلُّ أُولَـٰئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْؤُولًا} .

ትርጉሙም (መስሚያ፣ ማየም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ የአጠቃላይ ደንብ መከበር ሌላው ገጽታው ደግሞ ሰዎችን በመልካም አንደበትና ተስማሚ ቃላትን መርጦ ማናገር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَقُل{لِّعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِنَّ الشَّيْطَانَ يَنزَغُ بَيْنَهُمْ إِنَّ الشَّيْطَانَ كَانَ لِلْإِنسَانِ عَدُوًّا مُّبِينًا}

ትርጉሙም (ለባሮቼም በላቸው፡- ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ፡፡ ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና፡፡ ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (መልካም ቃል እንደምጽዋት ይቆጠራል) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይዲና ዑመር ኢብን አልኸጣብ አሳት አንድደው በዙሪያው በተቀመጡ ሰዎች አጠገብ ሲያልፉ እናንተ የእሳት ሰዎች ማለትን ጠሉና እናተ የብርሃን ሰዎች ሰላም ከናንተ ጋር ይሁን አሉ፡፡

የማንኛውንም ሰው የግል ጉዳዮች ማክበርና በማይመለከተው ነገር ጣልቃ ከመግባት መቆጠብ ከአጠቃላይ ደንብ መዋቅሮች አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ብሏል፡

{ وَلَا تَقْفُ مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ إِنَّ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْفُؤَادَ كُلُّ أُولَئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْئُولًا }

ትርጉሙም( ለአንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር አትከተል፡፡ መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ከአንድ ሰው እስልምና መስተካከል ገጽታዎች አንዱ የማይመለከተውን ነገር መተዉ ነው፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ለማንኛውም ማህበረሰብ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው ከአጠቃላይ ስርኣት መዋቅሮች ዋነኛው የአክብሮት ይሉኝታ ነው፡፡ ይህ ስነ ምግባር ከእስልምና ተላላቅ ስነ ምግባሮች አንደኛው ሲሆን አንድን ሰው የማይወቀስበትን ነገር ከመስራትና ጽያፍ ነገር ከመፈጸም የሚከለክል ስነ ምግባር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ይህ ስነ ምግባር ያለፉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች መለእክት እንደነበር እንድህ በማለት አመልክተዋል፡ (ሰዎች ካገኙት የቀደምት ነብያት ቃል ‹ይሉኝታ የሌለህ ከሆነ የፈለግህውን ሥራ› የሚለው ቃል ነበር)፡፡

ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) ከእለታት አንድ ቀን ከአንሷሮች ወገን የሆነ አንድ ሰው ወንድሙን ስለይሉኝታ አሉታዊነት ሲመክር ሰሙ ያን ጊዜም (ተወው ይሉኝታኮ የእምነት አካል ነው፡፡) አሉት፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን መስዑድ ነብያችን እንድህ ማለታቸውን አውርተዋል፡ (ለአላህ (ዐ.ወ.) እውነተኛ አለመዳፈር ይደርባችሁ -ይሉኝታ ይኑራችሁ-) አሉ፡፡ ባልደረቦችም ምስጋና ለአላህ ይሁን እኛ መደፋርም የለብን አሉ፡፡ እሳቸውም (እንደዚያኮ አይደለም ነገር ግን ለአላህ እውነትኛ ይሉኝታ ማሳደር ማለት ጭንቅላትና ያወቀውን፣ ሆድና ያዘለውን መጠበቅ፣ ሞትና አፈር መሆንን ማስታወስ ነው፡፡ መጭውን ዓለም የሚፈልግ ሰው የዚህችን ዓለም አሸብራቂ ነገሮች ይተዋል፡፡ ይህን ያደረገ ሰው በእርግጥም ለአላህ እውነተኛ ይሉኝታ አሳድሯል) አሉ፡፡ ይሉኝታ ማንኛውንም ሰው ከዳጥ ይጠብቃል፡፡ ይሉኝታ የሌለው ሰው ጠባቂ የለውም፡፡ የሚከተለውን ግጥም የደረሰው ሰው እጅጉን ይደነቃል፡፡

አንድ ሰው ይሉኝታ እስካለው ድረስ በሰላም ይኖራል፡፡ እንጨት የሚቆየውኮ ልጡ በላዩ ላይ ካለ ነው፡፡

የለም በአላህ ይሁንብኝ ህይወት መልካም አትሆንም ዓለማችንም እንደዚሁ ይሉኝታ ከጠፋ፡፡

የሌሊቶችን መጨረሻ ካልፈራህና ይሉኝታም ከሌለህ የፈለግህውን ሥራ፡፡

ሰብእነትም ዋና ከሚባሉት የአጠቃላይ ደንብ መዋቅሮች አንዱ ነው፡፡ ይህ ቃል የወንድነት ባህርይ የተካተተበት መሆኑን የቋንቋ ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡ ቃሉ መልካም ባህርይን፣ ደግ ጠባይን፣ ለሰዎች መልካም መዋልን፣ መንፈስን ከእርኩስ ነገሮች መጠበቅን፣ ከእኩይና ከጽያፍ ቃል ምላስን ማቀብንና ለይቅርታ እንድንገደድ ከሚያደርጉ ነገሮች መራቅን ያከተተ ነው፡፡ የጥንት አበውም እንዲህ ይላሉ፡ ‹ከሰዎች ጋር በአለው ውለታ ያልበደለ፣ ሲያወራቸውም ያልዋሸ፣ ቃል ሲገባላቸውም ያልከዳ ሰው ሰብእነቱ ምሉእ፣ ፍትሃዊነቱ ግልጽ፣ የሆነ ሰው ነው ወንድምነቱ ግዴታና እሱን ማማቱም የተከለከለ ይሆናል፡፡›
የአንድ ሰው ሰብእነት ገጽታውም ሆነ ወስጠ ልቡ ያመረ፣ በምስጢርም ሆነ በገሃድ ፈጣሪውን የሚቆጣጠር አገልጋይ ያደርገዋል፡፡ ከሰዎች መካከል በመልካም ገጽታ ታይቶ ሰዎች በማያዩበት ጊዜ የአላህን ወሰን የሚዳፈርም አይሆንም፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እኔ ከህዝቦቼ በትንሳኤ ቀን የቲሃማ ተራራን የሚካከሉ ነጫጭ መልካም ሥራዎችን ይዘው ይመጡና አላህ የሚበተኑ ትቢያ የሚያደርግባቸው ሰዎችን አውቃለሁ፡፡ ልብ በሉ እነሱ ወንድሞቻችሁና ወገኖቻችሁ ናቸው፡፡ በሌሊት እናንተ እንደምታደርጉት ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን እነሱ ሰው በሌለበት የአላህ ወሰኖች ዘንድ ሲደርሱ ይዳፈሯቸዋል፡፡)
ከሰው ጋር በአለው ግንኙነት የሚኖረው ሰብእነት ለእነሱ የእርዳታ እጅን በመዘርጋት፣ ጥቅማቸውን በማስከበርና ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ በመውደድ ይረጋገጣል፡፡ ነብይችን (ሰ.ዐ.ወ.o እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሙስሊም የሙስሊም ወንድም በመሆኑ ሊበድለውና ለጠላት አሳልፎም ሊሰጠው አይገባም፡፡ የወንድሙን ጉዳይ ያወጣ ሰው አላህ ጉዳዩን ያወጣለታል፡፡ ከአንድ ሰው ጭንቀትን ያስወገደ ሰው አላህ ከትንሳኤ ቀን ጭንቀቶች አንድን ጭንቀት ያቃልለታል፡፡ አንድን ሙስሊም ከማጋለጥ የታቀበ ሰውም አላህ በትንሳኤ ቀን ከውርደት ይሰውረዋል፡፡
እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ መካከል ከአላህ ዘንድ በጣም ተውዳጁ ለሰው ልጅ የሚያበረክተው ጥቅም ከፍተኛ የሆነው ሰው ነው ከሥራዎች አላህ ዘንድ እጅግ ተወዳጁ ደግሞ በአንድ ሙስሊም ልብ ደስታን ማስገባት፣ ወይም ከሱ ጭንቀትን ማቃለል፣ ወይም የአንድን ሰው እዳ መክፈል ወይም ከሱ ረሀብን ማስወገድ ነው፡፡በአላህ ይሁንብኝ እኔ የወንድሜን ጉዳይ ለማውጣት ከሱ ጋር መጓዜን በዚህ መስጊድ (በመዲና መስጊድ ማለታቸው ነው) አንድ ወር ያህል ለኢባዳ ከመቀመጤ አብልጬ እወደዋለሁ፡፡)
የእስልምና ሃማኖት ማንኛውም ማህበረሰብ አትብቆ ከያዛቸው ከፍተኛ ብልጽግናንና አድገትን ሊያረጋግጡለት የሚችሉን በርካታ ሰርኣቶችንና ደንቦችን አስቀምጧል፡፡ ይህ ተግባርም የማይለውጠውና የማይቀየረው አላህ በምድር ያስቀመጠው ደንቡ ነው፡፡ እነዚህን ደንቦች ገበራዊና የህወታችን መመሪያ ማድረግ በአሁኑ ወቅት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ይህን ብናደረግ ደግሞ በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ኣለም በደስታ እንኖራለን፡፡
ጌታችን ሆይ! ለዚህች ዓለምም ሆነ ለመጭው ዓለም የሚጠቅሙንን ነገሮች አሳውቀን ለሀገራችን የሚበጁ ነገሮችንም አሳካልን፡፡ ሀገራችንንም ጠብቅልን፡፡ አሚን፡፡

## (25)

### የማህበረሰቡ አጠቃላይ ስርኣቶችና መብቶች
### ለእድገቱና ለስልጣኔው ግንባታም ያላቸው ሚና

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

قُلْ {إِنَّنِي هَدَانِي رَبِّي إِلَى صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِّلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ አላህ ይገባው:: ትርጉሙም (እኔ ጌታየ ወደቀጥተኛው መንገድ፣ ትክክለኛን ሃይማኖት፣ ወደእውነት አዘንባይ ሲሆን የኢብራሂምን መንገድ መራኝ:: እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም::) ማለት ነው::

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (እኔን ጌታዬ ስርኣት አስተምሮኛል መልካምንም የስርኣት ትምህርት ነው ያስተማረኝ::) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ:: ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ::

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የእስልምና እምነት ከሰው ልጅና ከጌታው፣ ከሱና ከሰዎች እንድሁም ከሱና ከአለም መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመጥን የተሟላ መርሀ ግብር ይዞ ነው የመጣው:: የእስልምና ህግጋት ለማህበረሰቡ መሻሻል፣ እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው በርካታ አጠቃላይ ስርኣቶችንና ደንቦችንም አካቷል:: ከነዚህም ስርኣቶች መካከል ፈቃድ የመጠየቅ ስርኣት አንደኛው ነው:: እስልምና ፈቃድ መጠየቅን የደነገገ ሲሆን ከእስልምና ስርኣቶችም አንደኛው መሆኑን አረጋግጧል:: አለህ (ሱ.ወ.) ይህ ስርኣት ለሰዎች የግል ጉዳይ መከበር ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን እንድህ በማለት ይገልፃል፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَدْخُلُوا بُيُوتًا غَيْرَ بُيُوتِكُمْ حَتَّى تَسْتَأْنِسُوا وَتُسَلِّمُوا عَلَى أَهْلِهَا ذَلِكُمْ خَيْرٌ لَكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እስተምታስፈቅዱና በባለቤቶቿ ላይ ሰላምታን እስከምታቀርቡ ድረስ ከቤቶቻችሁ ሌሎች የሆኑን ቤቶች አትግቡ:: ይሃችሁ ለናንተ መልካም ነው:: እናንተ ትገነዘቡ ዘንድ (በዚህ ታዘዛችሁ):: ማለት ነው:: ነብያችን

(ሶ.ዐ.ወ.) ስለማስፈቀድ ደንቦች በርካታ ትምህርት ስጥተዋል፡፡ ከነሱም መካከል ፈቃድ የሚጠይቀው ሰው በመጀመሪያ ሰላምታ እንዳቀርብና ስሙን እንድጠራ ማዘዛቸው አንደኛው ነው፡፡

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ነብያችን ቤታቸው እያሉ ልግባ ይሆን? ሲል ፈቃድ ጠየቀ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን ለአገልጋያቸው እንድህ አሉት፡ (ውጣና ይህን ሰውዬ ፈቃድ ስለመተየቅ አስተምረው፡፡ ሰላም ለናንተ ይሁን ልግባ እንዴ? በል ብለህ ንገረው፡፡) ይህን ሲሉም ሰውየው ሰማና ሰላም ለናንተ ይሁን ልግባ እንዴ? አለ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈቀዱለትና ገባ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ቀን ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሄድኩና በር አንኳኳሁ፣ እሳቸውም (ማነው?) አሉ፡ ፡ እኔም እኔ ነኝ አልኩ፡፡ እሳቸውም (እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ) አሉ መልሴን የጠሉት ይመስል ነበር፡፡

ዓይንን ያልተፈቀደ ነገር ከማየት መከልከልና በበሩ ፊት ለፊት አለመቆም ለመግባት ከማስፈቀድ ስነ ስርኣቶች ይካተታሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ማስፈቀድ የተደረገው እኮ ለዓይን ሲባል ነው፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) ሰዕድ ኢብኑ ዑባዳ የሚከተለውን አውርተዋል፡ አንድ ቀን በበሩ ፊት ለፊት ቆመው ለመግባት ፈቃድ ጠየቁ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አንተ እበሩ ፊት ለፊት ቆመህ አታስፈቅድ) አሏቸው፡፡ በተለያዩ መጽሐፎች እንደሰፈረው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለመግባት ፈቃድ ለመጠየቅ ወደአንድ ሰው በር ሲደርሱ ወደቀኝ ወይም ግራ ገለል ብለው እንጂ ፊት ለፊት አይቆሙም ነበር፡፡ ከተፈቀደላቸው ደግ ከላሆነም ይመለሱ ነበር፡፡

የእስልምና እምነት ልዩ ትኩረት ከሰጣቸው አጠቃላይ ሥርአቶች ሌላው ደግሞ የመንገድና የህዝብ መገልገያ ቦታዎች ስነ ስርአት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ለመንገድ መፈጸም ያለበት መብት አስቀምጦለታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (አደራችሁን በመንገዶች ላይ እንዳትቀመጡ) ባልደረቦችም ያለህ መልከተኛ ሆይ! በመቀመጫዎቻችን አየተገናኘን ማውጋታችን የማይቀር ነው አሉ፡፡ ያን ጊዜ ያላህ መልክተኛ እንድህ አሉ፡ (መቀመጣችን አይቀርም ብላችሁ እምቢ ካላችሁ የመንገድን መብት አክብሩ፡፡) እሳቸውም መብቱ ምንድን ነው? አሉ፡፡ አሳቸውም (ዓይንን የማይፈቀድ ነገር ከማየት መከልከል፣ ችግር ከመፍጠር መታቀብ፣ ለሰላምታ መልስ መስጠት፣ በመልካም ምግባር ማዘዝና ከክፉ ነገር መከልከል፡፡) አሉ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (እምነት ሰባ ከምናምን ወይም ስድሳ ከምናምን ከፍሎች አሉት እጅጉን በላጩ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም) ማለት ሲሆን እጅጉን ዝቅተኛው ደግሞ ከመንገድ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ማስወገድ ነው፡፡ የአክብሮት ሀፍረትም በእምነት ክፍሎች ይካተታል፡፡)

ማንኛውም በመንድና በዝብ መገልገያ ተቋማት የሚጠቀም ሰው ድምጹን ያለ ልክ ከፍ አለማድረግ ወይም ረብሻ በሚፈጥር ከፍተኛ ድምጽ አለማውራት ከስርኣት ውጭ የሆነ ሳቅ አለመሳቅና በመንገድ ላይ ቆሻሻ አለመጣል ይኖርበታል፡፡ ቆሻሻዎችን በተመደበላቸው ቦታ ማስቀመጥ፣ ብሎም ከመንገድ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ሁሉ የማስወገድ ግዴታም አለበት፡፡ እንድሁም መንገዶችን የአለማስተጓጎል፣ አላፊ

አግዳሚዎችን አፍጥጦ በማያትና በቃልም ሆነ በተግባር ትንኮሳ አለማስቸገርም ሌላ ግዴታው ነው፡፡

ሌላውም ማህበራዊ ስርአት ደግሞ የጽዳት ስነ ስርአት ነው፡፡ የእስልምና እምነት የአካል፣ የልብስና የቦታ ንጽህናና ጽዳት ከሰው ልጅ ጠባይና ከስልጣኔ እሴት ጋር በሚጣጣም መልኩ ከአይቀሬ ደንቦቹ እንድካቱ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ወገኖቹ ከሱ እንዳይደነብሩና ገጽታውም የሚያስደስት እንድሆን የሚያደርጉ በርካታ የንጽህና ደንቦችን እንድከተል ታዟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እነዚያን ለሰውነታቸው ንጽህና ለውጫዊና ውስጣዊ ጽዳታቸው ልዩ ትኩረት የሚሰጡ ምእምናን እንድህ በማለት አውደሷቸዋል፡

{إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ التَّوَّابِينَ وَيُحِبُّ الْمُتَطَهِّرِينَ}

ትርጉሙም (አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፡፡ ተጥራሪዎችንም ይወዳል..) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ መልካም ነው መልካሞችን ይወዳል፣ ንጹህ ነው ንጽህናን ይወዳል...) አንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (ንጽህና የእምነት አንድ ክፍል ነው... ) ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) አንድ ቀፍራራ ሰውዬ ጸጉሩ ተንጨብሮ ቆሞ አዩ፡፡ ያን ጊዜም (ይህ ሰውዬ ጸጉሩን የሚያሳርፍበት ነገር አልበረውምን? ) አሉ፡፡ እንድሁም ሌላ ቀን አንድ የቆሸሸ ልብስ የለበሰን ሰውዬ አዩ፡፡ ያን ጊዜም (ይህ ሰውዬ ልብሱን የሚያጥብበት ነገር አላገኘምን? ) አሉ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የሰው ልጅ አፍ መዐዛ መልካም እንድሆንና ሰዎች ከሱ እንዲደነብሩ በሚያደርግ መጥፎ ጠረን ወገኖቹን አንዳያስቸግር ጥርሱን እንዲያጸዳ አዘዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ በዝቦቼ ወይም በሰዎች ላይ ችግርን ባልፈራ ኖሮ በየስግደቱ ሁሉ ጥርሳቸውን እንድፍቁ ባዘዝኳቸው ነበር፡፡)

ሌላው የማህበራዊ ስርአት ደግሞ የውይይት ስርአት ነው፡፡ ውይይት የመተዋወቅና የአስተሳሰብ ማረሚያ ዘዴ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የእስልምና እምነት ያለ ችግርና ያለ ገደብ ወደ ቅን መንገድና እውነት ለመድረስ እንዲቻል ከመላው የሰው ልጅ መካከል ውይይት እንድኖር በር ከፍቷል፡፡ ይሁን እንጂ ውይይቱ ሌሎችን ከማነወር ወይም በነሱ ከማሾፍና እነሱን ከማንኳሰስ የራቀ መሆን አለበት፡፡ አለህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَجَادِلْهُمْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ}

ትርጉሙም (በዚያችም እርሷ መልካም በሆነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው...) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَقُلْ لِعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ..}

ትርጉሙም (በለባሮቼም በላቸው ያችን እርሷ መልካም የሆነችውን (ቃል) ይናገሩ...) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (ምእምን ሲበዛ አነዋሪ፣ ዘወትር

ተራጋሚ፣ ጽያፍ ሠሪ ወይም ተናጋሪና ባለጌ አይሆንም፡፡) ማንኛውም ውይይት በመልካም አንደበት የታጀበ፣ አውቀትን፣ ተጨባጭነትንና የጉዳዩን ይዘት ትኩረት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡
ከውይይት ቅደመ መስፈርቶች አንዱ ወሬዎችን ወደሌላ ሰው ከማስተላለፋችን በፊት አለመቸኮልና ሰለወሬዎች ትክክለኛነት ማረጋገጫ መኖሩን መመርመር የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ሆናችሁ ህዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁትም ነገር ላይ ተጸጻቾች እንዳትሆኑ አረጋግጡ፡፡ ማለት ነው፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ዝግታ ከአላህ ነው፡፡ መቻኮል ደግሞ ከሰይጣን ነው፡፡) አንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (በማንኛውም ነገር ዘገምታ ደግ ነው፡፡ ለመጭው አለም የሚሰራ ሥራ ሲቀር፡፡) አሁንም እንድህ ይላሉ፡ (ለአንድ ሰው ውሸት የሰማውን ሁሉ በማውራት በቃ፡፡)
ሌላው ቅደመ መስፈርት ደግሞ አሉባልታዎችን አለመደጋገምና አለማናፈስ ነው፡፡ አሉባልታን ስንደጋግም በማስፋፋቱን ማሰረራጨቱ ተሳታፊዎች እንሆናለን፡፡ አሉባልታ በሰፊው የሚሰራጨው የሚደጋግሙ ልሳናትን፣ የሚያዳምጡ ጆሮዎችን፣ የሚቀበሉና የሚያምኑ መንፈሶችን ሲያገኝ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِذْ تَلَقَّوْنَهُ بِأَلْسِنَتِكُمْ وَتَقُولُونَ بِأَفْوَاهِكُمْ مَا لَيْسَ لَكُمْ بِهِ عِلْمٌ وَتَحْسَبُونَهُ هَيِّنًا وَهُوَ عِنْدَ اللَّهِ عَظِيمٌ}

ትርጉሙም (በምላሳችሁ በምትቀባበሉት ጊዜ ለናንተም በርሱ ዕውቀት በሌላችሁ ነገር በአፎቻችሁ በተናገራችሁና እርሱ አላህ ዘንድ ከባድ ኃጢአት ሆኖ ሳለ ቀላል አድርጋችሁ ባሰባችሁት ጊዜ (ከባድ ቅጣት በነካችሁ ነበር)፡፡ ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በአላህና በመጨረሻውም ቀን የሚያምን ሰው ጎረቤቱን አያስቸግር፣ በአላህና በመጨረሻውም ቀን የሚያምን ሰው እንግዳውን ያክብር በአላህና በመጨረሻውም ቀን የሚያምን ሰው ደግን ቃል ይናገር ወይም ዝም ይበል፡፡)
ከእስልምና አጠቃላይ ስርኣቶች ሌላው ደግሞ ድምጽን ዝቅ ማድረግ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሰውች ፊት በተለይም በደረጃ ከሱ በላይ የሆኑ ሰዎች በአሉበት ቦታ ደምጹን ከተለመደው በላይ ከፍ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ጠቢቡ ሉቅማን የሚያስተላልፉትን ምክር አላህ (ሱ.ወ.) በቁርኣን እንድህ ሲል አስፍሮታል፡

(وَاقْصِدْ فِي مَشْيِكَ وَاغْضُضْ مِنْ صَوْتِكَ إِنَّ أَنْكَرَ الْأَصْوَاتِ لَصَوْتُ الْحَمِيرِ)

ትርጉሙም (በአካሄደህም መካከለኛ ሁን፡፡ ከደምጽህም ዝቅ አድርግ፡፡ ከድምጾች ሁሉ አስከፊው የአህዮች ድምጽ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አነዚያን

በተለይም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባሉበት ቦታ ድምጻቸውን ዝቅ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድህ በማለት አመስግኗቸዋል፡
(إِنَّ الَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصْوَاتَهُمْ عِنْدَ رَسُولِ اللَّهِ أُولَئِكَ الَّذِينَ امْتَحَنَ اللَّهُ قُلُوبَهُمْ لِلتَّقْوَى لَهُمْ مَغْفِرَةٌ وَأَجْرٌ عَظِيمٌ)

ትርጉሙም (እነዚያ በአላህ መልክተኛ ዘንድ ድምጾቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ለፍርሃት የፈተናቸው ናቸው፡፡ ለነሱም ምህረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
ከእስልምና አጠቃላይ ስርአቶች ሌላው ደግሞ መንገድ የሳትን ሰው መንገድን መንገር ነው፡፡ አንድ ሰው መንገድ ከሳተ ምልክቶችን በመዘርዘር ወይም የሚመራው ልጅ በመላክ ማገዝ በእስልምና አጠቃላይ ስርአት ውስጥ ይካተታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡
(አደራችሁን በመንገዶች ላይ እንዳትቀመጡ) ባልደረቦችም ያለህ መልክተኛ ሆይ! በመቀመጫዎቻችን አየተገናኘን ማውጋታችን የማይቀር ነው አሉ፡፡ ያን ጊዜ ያላህ መልክተኛ እንድህ አሉ፡ (መቀመጣችን እይቀርም ብላችሁ እምቢ ካላችሁ የመንገድን መብት አክብሩ፡፡) እሳቸውም መብቱ መንድን ነው? አሉ፡፡ አሳቸውም (ዓይንን የማይፈቀድ ነገር ከማየት መከልከል፣ ችግር ከመፍጠር መታቀብ፣ ለሰላምታ መልስ መስጠት፣ በመልካም ምግባር ማዘዝና ከክፉ ነገር መከልከልና መንገድ የጠፋውን ሰው መንገዱን መምራት፡፡) አሉ፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአለላህ ዘንድ ምህረትን እጠይቃለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**
አሁንም በርካታ ሁሉም ሙስሊም ሊላበሳቸው የሚገባ የሆኑ አጠቃላይ ስርአቶች አሉ፡፡ የተጨነቀን ሰው ችግር ማቃለል ከነዚህ ስርአቶች አንዱ ነው፡፡ ይህን ተግባር የአስልምና እምነት እጅግ የተከበረ ተግባርና የላቀ ወደአላህ መቃረቢያ አምልኮ እንደሆነ ገልጧል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ዘር እንድህ ብለዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (የአዳም ልጅ መንፈስ ጸሓ በወጣችበት ቀን ሁሉ ምጽዋት ከመስጠት ወደኋላ ማለት አትችልም፡፡) ያነ ጊዜ ባልደረቦች የአላህ መልክተኛ ሆይ በየቀኑ ምጽት ለመስጠት ገንዘብ ከየት እናመጣለን? ሲሉ ጠየቁ፡፡ አሳቸውም (የመልካም ሥራ በሮች አጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ተስቢሕ፣ ተሕሚድ፣ ተክቢርና ተህሊል፣ በመልካም ሥራ ማዘዝና ከመጥፎ ነገር መከልከል፡፡ ከመንገድ ጉዳት የሚያደርሱን ነገሮች ማስወግድህ፣ ደንቆሮን ማስረዳትህ፣ ዓይነ ስውርን መምራትህ፣ ስለ ሆነ ጉዳይ የሚጠይቅን ሰው መምራትህ ድረሱልኝ ከሚል የተጨነቀ ሰው ጋር ጉልበትህን

ማጠንከርህ፣ ከደካማ ሰው ጋር ከንድህን ማበርታትህ ይህ ሁሉ ስለመንፈስህ የምታበረክተው ምጽዋት ነው፡፡)›
እንድሁም ደካሞችንና አካል ጉዳተኞችን መርዳት ከእስልምና አጠቃላይ ስርአት ሌላው ነው፡፡ የማህበራዊ ውህደት በሕይወት ሚዛናዊነትን ለማረጋገጥ ከደሃው ቀድሞ ለባለሀብቱ ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢማሙ ዓሊ እንድህ ይላሉ፡ አላህ (ሱ.ወ.) የድሆች ቀለብ በባለሀብቶች ገንዘብ ውስጥ እንድሆን ወስኗል አንድም ድሃ አይራብ በባለሀብት ስስታምነት ቢሆን አንጅ አላህም ስለዚያ ነገር ይጠይቃቸዋል፡፡› የዚህ ዓይነቱ የድሆች እንክብካቤ በማህበረሰቡ ላይ የተጣለ ግዴታ በመሆኑ ለሀገራዊ ትስስር ታላቅ እግዛ አለው፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) ቀልባቸው ለተሰበረ ሰውች ቅርብ ነው፡፡ ለባሮቹ ለሚያዝን ሰው አዛኝ ነው፡፡ መልካም ቃልም እንኳን ብትሆን ውለታን አያንኳስስም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ከመልካም ሥራ ምንንም አትናቅ ወንድምህን ፈካ ባለ ፊት መቀበልህ እንኳን ቢሆን፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (እናንተ በደካሞቻችሁ ቢሆን እንጂ ድል ትነሳላችሁን ሲሳይንም ትቸራላችሁን?) አንድ የአላህ ባሪያ ወንድሙን የሚያግዝ እስከሆነ ድረስ አላህ እሱን ያግዘዋል፡፡
ሌላው ስርአት ደግሞ ትልቅን ሰው ማክበር ነው፡፡ አንድ ሰው የእድሜ  ታላቅነቱና በእስልምና ቀዳሚነቱ መከበር ያለበት ሲሆን ደረጃውና ከፍተኛ ቦታውም እንደዚሁ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ታላቅ ሰውም ለትናንሾች እዝነትና ርህራሄ እንዲያሳይ ታዟል፡፡ ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው አረጋዊያንን አያከብርም አላህ በዚያ እድሜ ሲደርስ የሚያከብረው የሚያደርግለት ቢሆን እንጅ፡፡) ይህ ስርኣት ከእስልመና ታላቅነት፣ ገራገርነት፣ ፍትሃዊነትና ለሰው ልጅ ክብር ከሚሰጠው ልዮ ትኩረት ገጽታ አንደኛው ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባለሸበትን፣ ቁርኣን የሐፈዝን፣ ፍትሃዊ ገዥን ማክበር አላህን እንደማሞገስ መሆኑን እንድህ በማለት ጠቁመዋል፡ (ባለሸበት ሙስሊምን፣ የማያጋንንና እሱንም የማይርቅ የሆነን ቁርኣን የሐፈዘን እንድሁም ፍትሃዊ ባለሰልጣንን ማክበር አላህን ማክበር ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ ( ለህፃናቶቻችን የማያዝን፣ ተላላቆቻችንን የማያከብር፣ በመልካም ሥራ የማያዝና ከመጥፎ ነገርም የማይከለክል ከኛ ወገን አይደለም፡፡)
እዚህ ላይ ማረጋገጥ የምንፈልገው ነገር ቢኖር ባለሸበቱ ሰውዬ ይከበር ዘንድ ሙስሊም መሆኑ መስፈርት አለመሆኑን ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለአንድ አይሁድ ቤተሰብ ምጽዋት ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም እነሱም እንደዚሁ ይከበራሉ፡፡
እነሆ ሰይድና ዑመር በዝራ ለነበረው ወኪላቸው መልእክት በላኩበት ወቅት እንድህ ብለዋል፡ ‹የሌላ እምነት ተከታይ ከሆኑት ሰዎች እድሜው የገፋ፣ ኃይል የደከመ፣ የገቢ መንጩንም ያጣ ካለ ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ገንዘብ አንስትህ መክፈል ያለበተን ክፈልለት፡፡)
ማህበረሰቡ ነዋሪዎች የህዝብ መገልገያዎችን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ሙብቱ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ለምሳሌ የነዋሪዎች ቁጥር መጨመርን ብንወሰወድ፡ ሁለት ነገሮች መጠቀስ አለባቸው እንላለን፡

አንደኛው ችሎታ ሲባል የገንዘብ ችሎታ ብቻ መሆን የለበትም የሚለው ነው፡፡ እንድሁም ችሎታ ሲባል የግለሰቡ ችሎታ ብቻ ሳይሆን መንግስት መቅረብ ለአለባቸው አገልግሎቶች አቅርቦች ችሎታም ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት፡፡ ስነ ስርአት የጎደለው የነዋሪዎች ቁጥር መጨመር በግለሰብ ወይም በቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ተፅእኖው በሀገር ላይም ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ያለው ጥበትም ሆነ ስፋት ከሀገር ችሎታ ወጭ በግለሰብ መለኪያ ሊለካ አይገባም፡፡
ሁለተኛው ደግሞ ብርቱ የሆኑ ጥቂቶች ደከማና አቅም ቀላል ከሆኑ ብዙዎች የተሸሉ መሆኑን መገንዘብ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አንዳንድ አገሮች ያለቡት ሁኔታ እንደጤና ጥበቃ፣ ትምህርትና መሰረተ ግንባታ ያሉ መሰረታዊ ተቋማትን ማሟላት ባለመቻላቸው ብዙ ህዝባቸው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንደጠቀሱት ደካማነቱ እንደጎርፍ አረፋ ይሆናል፡፡ በመሆኑም መጠንና ምንነት በተፃረሩ ጊዜ ልበኛ ለምንነት ትኩረት ይሰጣል፡፡ እዚህ ላይ ታድያ ትንሽ ጠንካራ እልፍ አላፍ ጊዜ ከብዙ ደካማ የበለጠ ሁኖ ይገኛል፡፡
ይህውም ደካማነት፣ ደንቁርና የሚያስከትል እንድሁም ከዘመናዊ ስልጣኔ ጉዞ ወደኋላ የሚያስቀር ለሀገር ገቢና እድገት ከፍተኛ ጫና የሚሆን ብዛት የሚጎዳ እንጂ የሚጠቅም ብዛት አይሆንም ማለት ነው፡፡
ጌታችን ሆይ ለመልካም ጠባይ ምራን አንተ እንጂ ለመልካም ጠባይ የሚመራ የለምና ከኛም መጥፎ ጠባይን አርቅልን፡፡ መጥፎ ተባይንም ከኛ ያለንተ የሚያርቅ የለምና፡፡ አንተ ከመረጥካቸውም ባሮችህ አድርገን፡፡ አሚን፡፡

## (26)

## *የሀገራት ግንባታ ህግና ደንብ*

*ምስጋና ሁለ በተከበረው መጽሐፉ*

{وَتَعَاوَنُوا عَلَى البِرِّ وَالتَّقْوَى وَلاَ تَعَاوَنُوا عَلَى الإِثْمِ والعُدْوَان}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአለህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ሁሉም የዓለማት ህዝቦች የአላቸውን ኃይልና ሀብት በመጠቀም ጠንካራና የተረጋጋ ሀገር ለመገንባት ጥረት የሚያደርጉ መሆናቸው የሚያነጋግር ጉዳይ አይደልም፡፡ ይህውም አላማዎቻቸውን በተሳካ ሁኔታ ለማከናውን እንድችሉ ነው፡፡ የሀገራት ግንባታ ልምድና ሁኔታዎችንና የተደቀኑ ችግሮችን አስመልክቶ ሙሉ ግንዛቤን የሚጠይቅ ጥልቅ እውቀት ያሰፈልገዋል፡፡ አሁን ባለንበት በፍጥነት በሚለዋወጠውና ከደረጃ ወደደረጃ በተመሳሳይ ፍጥነት በሚሻጋገረው እንድሁም ቃል ኪዳናትንና የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚና የኢንዳስትሪ ክምችቶችን መሰረት ባደረገው ዓለም ከግልሰብ ወይም ከቡዲኖች ህግና ከሀገራት ግንባታ ህግና ደንብ መካከል ያለው ልዩነት እጅጉን ሰፊ ነው፡፡ ይህ ዘመናዊ የሀገራት ግንባታ ህግና ደንብ በአለም አቀፍ ህጎችና ቃል ኪዳኖች የተወሰነ በመሆኑ ከወቅታዊው ተጨባጭ ለመውጣት ወይም እሱን ዘንግቶ ከሱ ጋር በሚጻረር መልኩ መኖር የማይቻል መሆኑን ማነም ልበኛ ሊክደው የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡

ሀገር መጠለያ፣ ሀገር ደህንነት፣ ሀገር አመኔታ፣ ሀገር መረጋጋት፣ ሀገር ስርአት፣ ሀገር ድርጂቶች ነች፡፡ እንድሁም ሀገር የሀሳብ፣ የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የስርአትና የህግ ግንባታ ናት፡፡ ያለ ሀገር ስርአት አልባነት እንጂ ሌላ ነገር አይገኝም፡፡

ከሀገራት ግንባታ መዋቅሮች ዋና ዋናዎቹ ብሄራዊ የመንግስት ድርጂቶችን ማጠናከርና የህግ፣ የሀገ መንግስትና የፍትህ የበላይነትን እውን ማደረግ የሚሉት ናቸው፡፡ ይህም እውን ይሆን ዘንድ ግለሰቦች የመንግሰትን ህግጋትና ስርአቶች ማክበር፣ ለተራፊክ ህግ መገዛት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተራፊክን ህግ የሰው ልጅ ሕይወት ማጥፋትን ወይም ጉዳት ማድረስ ወይም ማሸበር በሚያስከትለው ያለመስመር በመሄድ፣ ፍጥነትን በመጨመርና በሌሎችም የመንገድና የሰው ልጅ መብቶችን በመዳፈር መጣስ የለባቸውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تُلْقُوا بِأَيْدِيكُمْ إِلَى التَّهْلُكَةِ وَأَحْسِنُوا إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ}

ትርጉሙም (በእጆቻችሁም (ነፍሶቻችሁን) ወደ ጥፋት አትጣሉ፡፡ በጎ ሥራንም ሥሩ፤ አላህ በጎ ሠሪዎችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በራስም ላይ ይሁን በሌሎች ላይ ጉዳት ማድረስ አይፈቀድም፡፡) ስርኣትን መጠበቅና ማክበር ጠንካራና የተረጋጋ ሀገር ለመገንባት ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ማንኛውም ህብረተሰብ የግልሰቦችን ጠባይና ተግባራት የሚወስኑ የሰብአዊ መብትን የሚያስከብሩና ግዴታውን እንዲወጣ የሚያደርጉ ህጎችና ደንቦች ሊኖሩት ይገባል፡፡ አንድ ሀገር ስርኣትን ያለማክበርና የህግ የበላይነት ሳይረጋገጥበት ሊረጋጋም ሆነ ፍትህ ሊሰፍንበት አይችልም፡፡

ሌላው ዋና የሀገር ግንባታ መዋቀር ደግሞ ህግጋትን ማክበርና ለህግ መገዛት ነው፡፡ ህግ የሁሉም የሀገር ነዋሪዎች መጠጊያ ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ ህግጋትን ሳያከብር የተረጋጋ ሁኖ ሊኖር ከቶ አይችልም፡፡ ማንኛውም ግለሰብ ሁሉም የማህበረሰቡ

አባላት የሚካተቱበት የአጠቃላይ ህዝብ ጥቅም እንዲከበር ሃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ፡፡ ሁላችሁም ስለምትጠብቁት ነገር ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡ ሴት በባሏ ቤት ጠባቂ ናት፡፡ ስለምትጠብቀውም ነገር ተጠያቂ ናት፡፡ አገልጋይ በጌታው ገንዘብ ዙሪያ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ተጠያቂ ነው… )፡፡ ሀላፊነት የሚሰማው ማህበረሰብ በውስጡ የተካተተው ግለሰብ ሁሉ ሚናውን የሚያውቅና ሌላውን የሚያከብር የሆነበት ውህደቱ የጠነከረ ማህበረሰብ ነው፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ፍትህ እንድስፋፋና መላ ህብረተሰቡ የድህነነት፣ የሰላምና የመረጋጋትን ፍሬ እንዲቋደስ ሀገርም በአለም አቀፍ ደረጃ ተገቢ ቦታዋን ይዛ ማየት እንድንችል ሰርአትን ማክበርና ለህግ መገዛት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡

ሌላው የሀገራት ግንባታ መዋቅር ደግሞ የኢኮኖሚ ግንባታ ነው፡፡ ኢኮኖሚ ያለሱ ሀገር ሊገነባ የማይችል መሰረታዊ መዋቅር ነው፡፡ ጠንካራ ኢኮኖሚ አንድ ሀገር የሀገር ውስጥም ሆነ አለም አቀፍ ግዴታውን እንድወጣና ለህዝቡ የተከበረ ሕይወት እንዲያሟላ ያስችለዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ኢኮኖሚ ሲዳከም ድህነትና በሽታ ይስፋፋል፣ ሕይወት ትወዛገባለች፣ ስነ ምግባርም ይበላሻል፣ ወንጀልም ይበዛል ሀገርን ለመጣልና መጨረሻ ወደሌለው ሰርአት አለባነት እንድትገባ ለማድረግ አድፈጠው ለሚጠብቁ ጠላቶች እድሉ በጣም ሰፊ ይሆናል፡፡ መሰረታዊ የሀገር መዋቀር የሌለው ሀገር በሌላው ሀገር ትከሻ የሚኖር ሲሆን ተሰሚ ቃልና ራሱን የቻለ ውሳኔ ሊኖረው እይችልም፡፡ በመሆኑም የእስልምና እምነት የሕይወት አውታር ስለሆነውና ያለሱ ጉዞ ከንቱ ለሆነው ለገንዘብ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

እንድን ሀገር በኢኮኖሚ ዘርፍ ጠንካራ ለማድረግ ሥራን በጥራት ማከናወንና ምርት ማሳደግን ይጠይቃል፡፡ አንድ ማህበረሰብ ወይም ድርጅት እንድሁም ቤተሰብ ሥራን በጥራት ሲያከናውን ብቻ ነው ተሀድሶን እውን ሊያደርግ የሚችለው፡፡ መላ የሀገር ግለሰቦች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ኢኮኖሚ ለመገንባት ሥራ ብቻ አንድሁም ምርትን መጨመር ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ነገር ግን በጥራት የታነጸ መሆን አለበት፡ ፡ ጌታችን አላህ (ሱ.ወ.) ለሥራ ዝግጁ እንድንሆንና በምድርም ታታሪዎች እንድን ሆን እንድህ በማለት አዞናል፡

{فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانْتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِنْ فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيرًا لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

ትርጉሙም (ሶላቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{هُوَ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ ذَلُولًا فَامْشُوا فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُوا مِنْ رِزْقِهِ وَإِلَيْهِ النُّشُورُ }

ትርጉሙም (እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፡፡ በጋራዎችዋና በመንገዶችዋም ኺዱ፡፡፡ ከሲሳዩም ብሉ፡፡ (ኋላ) መመለሻውም ወደእርሱ ብቻ ነው፡፡ ) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ከሚያገኘው ጸጋ እጅግ የሚወደደው በጥረቱና በድካሙ ያገኘው ጸጋ መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (አንድ ሰው መቼም ቢሆን በጁ ከሥራው የተሻለን ምግብ አይበላም የአላህ ነብይ ዳውድ (ዐ.ሰ.) በእጃቸው ከሰሩት ነገር ነበር የሚመገቡት፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (በእጁ ከሠራው ነገር ተምግቦ የዋለ ሰው ምህረት ተደርጎለት ይውላል፡፡) ነብይችን ለምርት እንድንዘጋጅ ሲገፋፉን ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው በእጁ የሚተከል ቀንዘል ይዞ የትንሳኤ ቀን ቢደርስ ከመነሳቱ በፊት ሊተከላት የሚችል ከሆን ሳይተክላት አይነሳ፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (እንድም ሙስሊም ተክል ተክሎ ወይም አዝርእት ዘርቶ ከሱ ወፍ ወይም ሰው ወይም እንሰሳ አይበላም በሱ ለሱ መጽዋት የሆነለት ቢሆን እንጂ፡፡) በሥራና በምርት ምድር ትለማለች ሀገራትም ይገነባሉ፡፡ የሰው ልጅም ማንነቱንና ክብሩን ይጠብቃል፡፡

ከሀገራት ግንባታ መዋቅር ሌላው ደግሞ የስልጣኔ፣ የሃማኖት፣ የሀሳብና የእውቀት ግንዛቤን ማሳደግ ነው፡፡ የግንዛቤ አለመኖር ወይም መዳከሙ ጠንካራና የተረጋጋ ሀገረን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በመሆኑም መላ የማህበረሰቡ አባላት ሙብትና ግዴታውን እንዲያውቅ ግንዛቤ ማስጨበጥ በጣሙን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ተግባር እውን ለማድረግ በስነ ምግባርና ጠቃሚ ስልጣኔ ትምህርት እንድሁም ድንቁረናን በመዋጋት አማካይነት ከመላው የማህበረሰብ አባላት ዘንድ ልዩ የጠባይና የስሜት ቅርጽ ሊኖር ይገባል፡፡ በመሆኑም የዚህ ዓይነት የስልጣኔ፣ የሃይማኖት፣ የሀሳብና የእውቀት ግንዛቤ ለማህበረሰቡ አባላት ለማስጨበጥ ሁሉም የመንግስት ድርጅቶች በቅንጀት መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ህዝቡ ሀገርን ለመጣልና በህዝብ ላይ ጉዳት ለማድረስ መንስኤ የሚሆኑ የተደቀኑ ችግሮችንና የሚናፈሱ አሉባልታዎችን ወደአደጋነት ሳይሸጋገሩ የመቋቋም ብቃት ይኖረዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{يَاأَيُّهَاالَّذِينَآمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}.**

ትርጉሙም (እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጸኞች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡) ማለት ነው፡፡

ከዚህ ላይ በሌሎች መከራ መገሰጽና ከሕይወት ተሞክሮም መጠቀም ይኖርብናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا خُذُوا حِذْرَكُمْ}**

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጥንቃቄያችሁን ያዙ፡፡) ማለት ነው ፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ምእምን ከአንድ ጎዶ ሁለት ጊዜ አይነከስም፡፡) እዚህ ላይ የሀገር ግንባታና ሀገርን መጠበቅ በሁላችንም ላይ የተጣለ ሃላፊነት መሆኑንና የአፍራሾችን እጅ የመያዝ ግዴታ ያለበን መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ግንቡ መቼ ይጠቃለላል አንተ ስትገነባ ሌላው የሚያፈርስ ከሆነ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (በዳይም ይሁን ተበዳይ ወንድምህን እርዳ፡፡) አንድ ሰውዬ የአላህ መልክተኛ ሆይ! ተበዳይ በሚሆን ጊዜ እረደዋለሁ፡፡ በዳይ ሲሆን እንዴት እረደዋለሁ ይመስለወታል? ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (ከበደል ታግደዋለህ ወይም ትከለክለወለህ በዚህም መልኩ እሱን ትረደዋለህ፡፡) ማንኛችንም ከብሄራዊ መስመር የሚወጣን ወይም የሀገርን ጥቅም የሚጎዳን አፍራሽን እጅ መያዝ ይጠበቅብናል፡፡ አባት የልጁን፣ ወንድም የወንድሙንና ጓደኛ የጓደኛውን እጅ መያዝ ይኖርበታል፡፡ በዙሪያችን ያለውን ሁሉ የዘነጋን አሉታዊያን መሆን የለብንም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሰዎች መልካም ከሰሩ መልካም እንሰራለን ከበደሉም እንበድላለን የምትሉ እምንቶች አትሁኑ፡፡ ነገር ግን ሰዎች መልካም ሲሰሩ መልካም እንድትሰሩ ሲያስከፉም የማትበድሉ እንድትሆኑ ራሳችሁን አለማመዱ፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የአላህን ወሰኖች የሚጠብቅ ሰውና የሚተላለፍ ሰው ምሳሌ በአንድ መርከብ ላይ እጣ እንደተጣጣሉና ከፊላቸው ላይኛውን ክፍል ከፊላቸውም ታችኛውን ክፍል እንዳገኙ ሰዎች ነው፡፡ በታችኛው ክፍል የሰፈሩት ውሃ ለማግኘት ሲፈልጉ በላይኛ ክፍል በሰፈሩት ሰውች ላይ ማለፍ ነበረባቸው፡፡ እነሱም ሁል ጊዜ እነሱን ከምናስቸግር በደርሻችን ቀዳዳ አውጥተን ብንጠቀምስ የሚል ሀሳብ መጣላቸው፡፡ (የላይኞቹ) ታችኞቹ ያሰቡትን እንዲፈጽሙ ከተዋቸው ሁላቸውም ይጠፋሉ፡፡ እጃቸውን ከያዙዋቸው (ከከለከሏቸው) እነሱ ይድናሉ ብሎም ሁላቸውም ይድናሉ፡፡) አንድ ሰው ደግ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የደረጃ ደንብ ከደግነት ሰዎች ደግ እንዲሆኑ ወደመጣር መሸጋገር ይኖርበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لا خير في كثير من نجواهم إلا من أمر بصدقة أو معروف أو إصلاح بين الناس ومن يفعل ذلك ابتغاء مرضات الله فسوف نؤتيه أجرا عظيما}

ትርጉሙም (ከውይይታቸው በምጽዋት ወይም በበጎ ሥራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በብዙው ውስጥ ደግ ነገር የለበትም፡፡ ይኸንንም (የተባለውን) የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁምእንድህ ይላል፡

{وما كان ربك ليهلك القرى بظلم وأهلها مصلحون}

ትርጉሙም (ጌታህም ከተሞችን ባለቤቶቻቸው መልካም ሠሪዎች ሆነው ሳሉ በመበደል የሚያጠፋቸው አልነበረም፡፡) ማለት ነው፡፡

ሰዎች ደግ እንድሆነ መስበክ የነብያትና የመልክተኞች ጎዳና ሲሆን በሱም አማካይነት ሀገራት ይገነባሉ፣ አንድነታቸውም ይከበራል ሃይላቸውና ትስስራቸው ይጠናከራል፡፡ ሰዎችም ንትርክ፣ ህውከትና ሽብር በግድያና በማፍረስ በምድር ማበለሸት በሌለበት በሰላም መኖር ይችላል፡፡

ይህ ቃሌን ተናግሪያለሁ እነሆ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ከሀገራት ግንባታና ጥበቃ መሰረቶች ሌላው ደግሞ የማህበራዊ ግንባትና እድገት መረጋገጥ ነው፡፡ የአስልምና ሃማኖት ከማህበረሰቡ አባላት መካከል ለአለው ግንኙነትና ትስስር መረዳዳትና መተዛዘን ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በአንጻሩም በሌሎች ላይ ጉዳት አለማድረስ ግዴታ መሆኑን አስገንዝቧል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለለዋል፡ (አንዳችሁ እምነቱ ምሉእ አይሆንም፡፡ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስከሚወድ ድረስ፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (በአላህ ይሁንብኝ አላመነም በአላህ ይሁንብኝ አላመነም በአላህ ይሁንብኝ አላመነም አሉ፡፡ ባልደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማነው እሱ? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም ጎረቤቱ ከተንኮሉ ያልዳነ ሰው) አሉ፡፡ አሁንም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (በአጠገቡ ጎረቤቱ መራቡን እያወቀ ጠግቦ ያደረ ሰው በኔ አላመነም)፡፡

ከማህበራዊ ግንባታ ገጽታዎች ጉልሁ የቤተሰብ ትስስር ነው፡፡ ቤተሰብ የማህበረሰቡ ማሕፈድ የሚገነባበት የመጀመሪያው ድንጋይ ነው፡፡ ቤተሰብ ታዳጊዎችን የሚንከባከብ ከመሆኑም በአሻገር አካላቸውንም ይሁን አእምሯቸውን ይገነባል፡፡ በቤተሰብ ጥላ ስር የፍቅር፣ የርህራሄና የተራድኦ ስሜቶች ይዋሀዳሉ፡፡ በተሳሰረ ቤተሰብ እቅፍ ውስጥ የተከበረው መልካም ባሕርይ ይፈጠራል፡፡ ፍቅርም በሰፊው ይሰፍናል፡፡ ይሁን እንጂ የቤተሰብ ሚና በዚህ ብቻ አይወሰንም፡፡ ቤተሰብ ልጆች መስመር እንደይስቱ መከታተልም ይጠበቅበታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ወንጀል ለመፈጸም የሚያሳድገውን ማጥፋቱ በቂው ነው)፡፡

ልጆችን ለጠማማ አስተሳሰብና ግዴታውን ያለመወጣት መስመር ለለቀቁ ብድኖች አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ልጅን የማጠፋት ወንጀል የለም፡፡ ልጆች ዘውትር ስለሀገራቸው ያለባቸውን ግዴታ እንዳይረሱ ልናስገነዝባቸው ይገባል፡፡ የሀገር ፍቀር ለልጆች የምናወርሰው ክቡር ሀብት ነው፡፡ አሕመድ ሸውቂ የተባለው የግብጽ ገጣሚ እንድህ ይላል፡

በህይወት እስካለን ሀገርን ለመጠበቅ ዘብ እንቆማለን እንዲቀጥሉም ለልጆቻችን እናስተላልፋለን፡፡

ግብጽ ሆይ በአንች እንደኖርን ሁሉ ለአንችም እንሞታለን መስዋእት የምንሆንለት ገጽታሽ ተከብሮ ይኑር፡፡

እሴቶችን፣ መልካም ምግባሮችንና ጠባዮችን ማሻሻል ሌላው የሀገራት ግንባታ መዋቅር ነው፡፡ ጠቃሚ እሴቶችንና መልካም ምግባሮችን መሰረት ያለደረገ ህዝብ አቋሙ በጣም ደካማ ነው፡፡ የአንድ ሙስሊም የእምነት ደረጃ በመልካም ምግባር ያድጋል

በሱም የሚዛን እለት ሚዛኑ ይደፋል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በትንሳኤ ቀን በአንድ ምእምን ሚዛን ከመልካም ምግባር የከበደ ነገር የለም፡፡ አላህ አስከፊና ጽያፍ ቃል ተናጋሪን ይጠላል፡፡) ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሰዎችን በብዛት ገነት ስለሚያስገባ ነገር በተጠየቁ ጊዜ (አላህን መፍራትና መልከም ጸባይ ነው) በማለት ነበር የመለሱት፡፡ ነብያችን የእምነት ምሉእነትና ጎደሎነት የሚለካው በጠባይ መሆኑን እንድህ በማለት ጠቁመዋል፡ (ከምእምናን እምነተ ምሉኡ በመልካም ጸባይ በላጫቸው ነው)፡፡ መልካም ጸባይ ባለቤቱን ከመጥፎ ነገሮችና አፍራሽ ከሆነው ጽያፍ ቃል ይጠብቃል አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

﴿وَمَثَلُ كَلِمَةٍ خَبِيثَةٍ كَشَجَرَةٍ خَبِيثَةٍ اجْتُثَّتْ مِنْ فَوْقِ الْأَرْضِ مَا لَهَا مِنْ قَرَارٍ﴾.

ትርጉሙም (የመጥፎም ቃል ምሳሌ ከምድር በላይ የተጎለሰሰች ለእርሷ ምንም መደላደል የሌላት እንደኾነች መጥፎ ዛፍ ነው፡፡) ማለት ነው

መልካም ጸባይንና ደግ ቃል መናገርን አንደቸርን ሰላም፣ ደህንነትና ጸጥታን ዘላቂ እንዲያደርግልን፣ ሀገራችንና ህዝባችንን ከመጥፎ ነገር እንዲጠብቅልን አላህን እንለምናልን፡፡ አሜን፡፡

## (27)

# አጠቃላይ የህዝብ ጥቅም በእስልምና ህግ መለኪያ ሲታይ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

﴿وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ﴾

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በበጎ ነገርና አላህን በመፍራት ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰን በማለፍ አትረዳዱ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ.) የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የአስልምና ህግጋትን በጥሞና የሚመለከት ሰው የሀገርንና የህዝብን ጥቅም ለማረጋጥ፣ የሰውን ልጅ መንፈስ ከፍ ለማድረግና ወደከፍተኛ ደረጃም ለማሰደግ የተደነገገ ህግ

መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ የሰዎችን አጠቃላይ ጥቅም እውን የሚያደርግ ነገር ሁሉ ግልጽ ማስረጃ ሰፍሮለት ባይገኝም እንኳ ከህጉ ጋር ተስማሚ ሆኖ ይገኛል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ከሰዎች ጥቅም ጋር የሚጋጭ ነገር ሁሉ በተከበረው የእስልምና ህግ ዘንድ መሰረት አይገኝለትም፡፡ ወደእውነት ያዘነበለው የእስልምና ሃይማኖት ለግልነት፣ ለራስ ወዳድነትና ለአሉታዊነት ቦታ አይሰጥም፡፡ እንድሁም የግለን ጥቅም ከአጠቃላይ ጥቅም አያስቀድምም፡፡ ሃይማኖቱ ለአጠቃላይ ጥቅም፣ ለስጦታና ለእውነት፣ በፍቀርና ሰዎችን በማስቀደም በተላበሰ መልኩ በበጎ ነገርና አላህን በመፍራት ለመተባበር ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

ይህውም ማህበረሰቡ የሚፈለገውን አድገትና የሚመሰገነውን ትስስር ማረጋገጥ እንድችል፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የግለሰቡ ጥረት የማህበረሰቡን ጥቅም መሰረት ያደረገ ሆኖ መልካም ውጤቱ ግለሰቡንና ማህበረሰቡን በአንድላይ ያከተት እንዲሆንና በሀገሪቱ ልጆች ልብ አንዱ አካል ህመም ሲሰማው ሌሎችም አካላት እንቅልፍ በማጣትና በስቃይ የሚጠራራ የሆነው የአንድ አካል ስሜት እንዲሰርጽ ለሚያደርግ ነው፡፡ ሸውቂ የተባለው የግጥም ደራሲ እንድህ በማለቱ እጅጉን ይደነቃል፡

እሱ ሊኖር (ሰማእታት) ወጣቶቹ የሞቱለት ሀገር፡፡ ሰዎችም ሊኖሩ ከነሱ በፊት የተሰወሩ(ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ)ወጣቶች፡፡

የአላህን (አ.ወ.) ኪታብ የሚመራመር ሰው ለሰዎች የተደነገጉ አጠቃላይና ሁለንተናዊ ህግጋቶች አላማ ጥቅምንና መልካም ነገሮችን ሁሉ በማምጣትና ጉዳትና ተንኮልን በማስወገድ የህዝቡን ጥቅም ማስከበር መሆኑን በትክክል የሚገነዘብ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ቅዱስ ቁርአን ጥቅምን ማስከበርና አጠቃላይ የህዝብ ጥቅምን እውን ማድረግ የመልክተኞችና የነብያት ስርአት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አላህ (አ.ወ.) አንድንም መልክተኛ ወይም ነብይ አላከም ህዝቦቹን ለማስደሰትና ከዚህች አለም ጥቅም የሆነን ዋጋ ሳይጠብቅ ለነሱ መልካምን ነገር ሁሉ እውን ሊያደርግ ቢሆን እንጂ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በነብዩ ኑሕ (ዐ.ሰ.) ልስን እንድህ ብሏል፡

{وَيَا قَوْمِ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ مَالًا إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى اللَّهِ}

ትርጉሙም (ህዝቦቸም ሆይ! በርሱ (በመልክቱ) ላይ ገንዘብን አልጠይቃችሁም፡፡ ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም...) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በነብዩ ሁድ (ዐ.ሰ.) ልሳን እንድህ ይላል፡

{يَا قَوْمِ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى الَّذِي فَطَرَنِي أَفَلَا تَعْقِلُونَ}

ትርጉሙም( ህዝቦቸም ሆይ! በሱ (በመልክቱ) ላይ ምንዳን አልጠይቃችሁም መንዳዬ በዚያ በፈጠኝ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም አታውቁምን?) ማለት ነው፡፡ እንሆ የራሕማን ወዳጅ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ወደጌታቸው (አ.ወ.) ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሰዎች ጥቅም እንድከበርና በዘለቄታም መልካም ሁሉ እንዳይለያቸው እንድህ በማለት ጸሎት አድርሰዋል፡

{رَبِّ اجْعَلْ هَٰذَا بَلَدًا آمِنًا وَارْزُقْ أَهْلَهُ مِنَ الثَّمَرَاتِ مَنْ آمَنَ مِنْهُمْ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ}

ትርጉሙም (ጌታዬ ሆይ! ይህንን ጸጥተኛ አገር አድርግ፡፡ ቤተሰቦቹንም ከነሱ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነውን ሰው ከፍሬዎች ስጠው ..) ማለት ነው፡፡
እንደሚታወቀው እዚህ ላይ ሀገር በማለት የታሰበው የዚያ ሀገር ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ነብዩ ኢብራሂም ነዋሪዎቹ ከሌላ ሰው እንዳይከጅሉ የሚያደርጋቸውን ሰፊ ሲሳይ እንድለግሳቸው ፈጣሪን የለመኑት አንደ ሀገር ጸጥታው እውን ሲሆንና በሱም ለሰው ልጅ ሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮች የተሟሉ ሲሆኑ ሰዎች ምድርን በመገንባትና በማልማት የአላህን (ሱ.ወ.) ትእዛዝ ለማሟላት በሰከነ መንፈስና በተረጋጋ ልቦና ታዛዦች ይሆናሉና ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{هُوَ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الْأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا}

ትርጉሙም (እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ ከውስጧም እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا.}

ትርጉሙም(በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፡፡) ማለት ነው፡፡
የነብያችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ህግጋት የተቀመጡት ይህን ሰብአዊ መርህና ትክክለኛ ተሃድሶ ከፍ ለማድረግ፣ የማህበረሰቡን መረጋጋት ዘላቂነት መሰረቶች ለማጠንከር፣ ከግል ጥቅም ይልቅ አጠቃላይ ጥቅሞችን በማስቀደም እድገቱንና ብልጽግናውን ለማስቀጠልና ሕይወት የተረጋጋችና ስርአት ያላት እንድትሆን የአስፈላጊነት ቅደም ተከተልን መስመር ለማስያዝ ነው፡፡ ንጹሃን ነብያዊ የህወት ታሪክና የተከበሩ ባልደረቦች የእለት ተእለት ኑሮ ይህን እውነታ በሚያንጸባርቁ ታላላቅ አቋሞች ያሸበረቁ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የምእምናን እናት ዓኢሻ እንድህ ብለዋል፡ ‹መጥገብ ብንፈልግ ኖሮ በጠገብን ነበር፡፡ ነገር ግን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ከራሰቸው ይልቅ ሰዎችን ማስቀደምን ይመርጡ ነበር፡፡› ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከራሳቸው እንደሁም ችግር ቢኖርባቸውም እንኳ ከቤተሰቦቻቸውም ሌሎችን ያስቀድሙ ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሰዒድንል ኹድሪይ እንድህ በለዋል ‹ከእለታት አንድ ቀን እኛ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር በጉዞ እያለን እንድ ሰውዬ አገኘን፡፡ እሱም በግምሉ ላይ ጠቀምጦ እያለ በዓይን ወደቀኝና ወደግራ ይቃኝ ጀመር፡፡ ያን ጊዜ የአላህ ምልከተኛ እንድህ አሉ፡ (ከሱ ጋር ትርፍ የጭነት ከብት ያለው ሰው የጭነት ከብት ለሌለው ሰው ይመልስ (ይስጥ)፣ ከስንቁም ትርፍ ያለው ሰው ስንቅ ለሌለው ሰው ይስጥ...) አቡ ሰዒድ ነብዩ እኛ በማንኛውም ትርፍ ነገር መብት የሌለን መሆኑን እንድንገምት ያደረገንን ስፍር ቁጥር የሌለው የገንዘብ ዓይነት ጠቀሱ አሉ፡፡›
ቡኻሪና ሙስሊም እናችን ዓኢሻ እንድህ ማለታቸውን አስፍረዋል፡ (ከእለታት አንድ ቀን እንድት ሁለት ሴት ልጆች ያዘች ምስኪን ሴት ምግብ ፈልጋ ወደኔ መጣች የነበሩኝን ሦስት ተምሮች ሰጠኋት፡፡ ለልጆቹዋ ለየአንዳንዳቸው አንዳንድ ተምር ከሰጠች በኋላ አንደኛዋን ተምር ለትበላ ወዳፏ አቀረበች፡፡ ሳትጎርሳት በፊት ለጆቹዋ ስጭን አሏት እሷም ያችን ልትበላት የነበረችውን ተምር ወደሁለት ከፍላ ሰጠቻቸው፡፡

ይህ ተግባሯ አስደነቀኝና ሴትዮዋ ያደረገችውን ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) አወራሁላቸው፡፡ እሳቸውም (አላህ በሷ ገነት በእርግጥ የተፈረደላት አደረገ ወይም በሷ ከእሳት ነፃ አደረጋት፡፡) አሉ፡፡

ይህ እንግድህ ከራሷ ልጆቿን ያስቀደመች ሴት ምንዳ ከሆነ ከራሱ ደካማን፣ ችግረኛንና ምስኪንን የሚያስቀድም ሰው ምንዳ ምን ይሆን ይመስላችኋል?!

ይሀውና (ከርሳቸው አላህ ውደድና) ዑስማን ኢብን ዓፋን አረሃብና ችግር በሙስሊሞች ላይ እጅግ በከፋበት በረማዳህ (አመዳማው) ዓመት ስንዴ፣ ዘይትና ዘቢብ የተጫነ ቁጥሩ አንድ ሺህ ግመል የሚደርስ ንግዳቸው ከሻም አገር በመጣ ጊዜ የመዲና ነጋዴዎች ተሰብስበው ወደቤታቸው ሄዱ፡፡ እሳቸውም ምን ፈልጋችሁ ነው? ሲሉ ጠየቋቸው እነሱም እኛ የምንፈለገውን ነገር እርሰዎ መቼ አጥተውት ይህን የመጣለዎትን ሸቀጥ ሸጡልን፣ እሱ ለሰዎች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃሉ አሉ፡፡

ሰይድና ኡስማንም እሱን በደስታና በአክብሮት እቀበለዋለሁ ነገር ግን በዚህ ሸያጬ ስንት ታተርፉኛላችሁ? አሏቸው፡፡ እነሱም በአንድ ድርሃም የገዘሃውን በሁለት ድርሃም እንገዛዎታለን አሉ፡፡ እሳቸውም ከዚያ በላይ ተሰጥቻለሁ አሉ፡፡ እነሱም አራት እጠፍ እንሰጠዎታለን አሉ፡፡ እሳቸውም ከዚያ በላይ ተሰጥቻለሁ አሉ፡፡ አምስት እጥፍ እናደርግለዎታለን አሉ፡፡ አሳቸውም ከዚያ በላይ ተሰጥቻለሁ አሉ፡፡

እነሱም የዕምር አባት ሆይ! እኛ ወደርሰዎ ስንመጣ ከመዲና ነጋዴ ማንም አልቀረም ከኛም በፊት ቀደሞን ወደርሰዎ የመጣ ነጋዴም የለ፡፡ ማነው እሱ ከዚያ በላይ የሰጠዎት አሉ፡፡ እሳቸውም አላህ (ሱ.ወ.) በእርግጥ በያንዳንዱ ደርሃም አሥር እጥፍ ሰጥቶኛል፡፡ እናንተ ከዚህ በላይ ልትጨምሩ ትችላለችሁን? ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ እነሱም የለም ኧረ አንችልም አሉ፡፡ እሳቸውም እኔ አላህ ምስክሬ ነው በነዚህ ግመሎች የተጫነውን ሁሉ አላህ ምንዳውን ሊሰጠኝ ለሙስሊም መስኪኖችና ድሃዎች ምጽዋት አድርጊየዋለሁ አሉ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የውሃውን ዋጋ እያስወደደ ባስቸገረው አይሁድ እጅ የነበረውን የሩማህን ውሃ ጉድጓድ ባልደረቦች እንዲገዙ ሀሳብ ባቀረቡ ጊዜ እንድህ አሉ፡ (የሩማህን ውሃ ጉድጓድ ገዝቶ መቅጃው ከሙስሊሞች መቅጃ ጋር እኩል እንድሆን የሚያደርግ ማነው?) አሉ፡፡ ዑስማን ወደአይሁዲው ቤት ሄዱና ውሃ ጉድጓዱን ለመግዛት እንደሚፈለጉ ነገሩት፡፡ ሁሉንም ከመሸጥ አሻፈረኝ አለ፡፡ እሳቸውም ግማሹን በአሥራ ሁለት ሺህ ድርሃም ገዝተው ለሙስሊሞች ምጽዋት አደረጉት፡፡ ለሰይድና ዑስማን አንድ ቀን ለአይሁዲው ደግሞ አንድ ቀን አድርገው ተከፋፈሉ፡፡ የሰይድና ዑስማን ተራ በሚሆንበት ቀን ሙስሊሞች ለሁለት ቀናት የሚበቃቸውን ይቀዱ ነበር፡፡ አይሁዲው ይህን ባየ ጊዜ ውሃ ጉድጓዴን በራሴ አበላሸሁ አለና ቀሪውን ድርሻውን ለመሸጥ ተስማማ፡፡ ሰይድና ዑስማን በስምንት ሺህ ድርሃም ገዙትና ለሙስሊሞች መገልገያ አደረጉት፡፡ ሰይድና ዑስማን ይህን ያደረጉት የአላህ መልክተኛን ትእዛዝ ለማድረስና የሙስሊሞች አጠቃላይ ጥቅም እንድከበር ከነበራቸው ጠንከራ ፍላጎት አንፃር ነበር፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በሰይድና ዑመር ዘመን መስጅድ አልሐራም በሰዎች መጨናነቅ በጀመረ ጊዜ መስጊዱን ለማስፋት በመስጊዱ ዙሪያ የነበሩ የቤት ባለቤቶች ‹እናንተ ናችሁ በካዕባ ላይ የሰፈራችሁት እንጂ ከዕባ በናንተ ላይ አልሰፈረችባችሁም› በማለት ቤቶቻቸውን እንድሸጡ አስገድደዋቸዋል፡፡

እንደዚሁም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይድና ዑስማንም ይህንኑ ተግባር ‹በኔ ላይ እንድትዳፈሩ ያደረጋችሁ ትእግስቴ ነው ዑመር የዚህ ዓይን እርምጃ በወሰዱ ጊዜ ምንም አልተናገራችሁም› በማለት እንደገና ደግመውታል፡፡ ዑስማን ኢብን አፋን አቋማቸውን ለማጠናከር እነዚያ (ቤቶቻቸውን ከመሸጥ አሻፈረኝ ያሉት) ሰዎች እንድታሰሩ ትእዛዝ ማስተላለፋቸው፡ መንገድንና መቃብርን ለማስፋፋት፣ መስጊድን ለመስራት፣ መከላከያ ግንብን ለማዋቀር፣ እንደሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፣ መጠለያና የመሳሰሉ የህዝብ ተቋማትን ለማቋቋም የግል ባለንብረትነትን መግፈፍ የተፈቀደ መሆኑን በግልጽ አመልክቷል፡፡ ይህውም የአጠቃላይ ህዝብ ጥቅም ከግል ጥቅም ተቀዳሚ በመሆኑ ነው፡፡

እዚህ ላይ ለማረጋጥ የምንፈለገው ነገር ቢኖር የሃማኖት ትክክለኛ ግንዛቤ ሃይማኖታችን እንድንፈጽማቸው ከገፋፋንና መልካምነታቸውን ከገለጻልን አጠቃላይ የህዝብ ጥቅም ዓይነቶች መካከል የሰዎችን ሁኔታና ጭብጣቸውን ማክበር አንደኛው እንደሆነ መረዳትን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡ እንድሁም የማህበረሰቡን አንገብጋቢ ችግሮች ለመቅረፍና ፍላጎታቸውን ለማሟላት የአስፈላጊነትን ቅደም ተከተል ስርኣት ማስያዝ ሌላኛው እንደሆነ መገንዘብንም ግድ ይላል፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ለማህበረሰቡ እጅጉን የሚስፈልገው ድሆችን ለማከምና ለመንከባከብ ሆስፒታል ማዋቀርና መገልገያዎቹን ማሟላት ከሆነ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት ግድ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለማህበረሰቡ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ትምህርት ቤትና ኢንስቲትዩቶች ማዋቀር፣ መገልገያዎቹን ማሟላት፣ የተማሪዎችን ወጭ መሸፈንና እነሱን መንከባከብ ከሆነ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚ መስጠት ግድ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም የድሆችን ትዳር መመስረት፣ እዳ ያለባቸውን ሰዎች እዳ መከፍል ወይም ማቃለል በወቅቱ የማህበረሰቡ ችግር ከሆነ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የእስልምና ሃይማኖት በመልካም ሥራም ሳይቀር ለአስፈላጊ ነገር ተቀዳሚነት ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ የግልና የአጠቃላይ ጥቅም በሚፃረሩበት ጊዜ ለአጠቃላይ ጥቅም መሳካት ቅድሚያ እንዲሰጥም አዟል፡፡ ይህውም የአጠቃላይ ጥቅም ሰፊና ተሻጋሪ ስለሆነና የግል ጥቅም ደግሞ ከባለቤቱ የማያልፍ በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌለ አንድ ሰው

በአንድ ድርጅት የሚሰራና በዚህ ሥራውም ደመወዝ እየተከፈለው ሳለ ሌሊቱን ሁሉ በስግደትና በጸሎት አሳልፎ ማለዳ ወደስራው ደክሞና ዝሎ በሚሄደ ጊዜ የተጣለበትን ሀላፊነት በሚገባ ሊወጣ የማይችል ከሆነና በዚህ ምክኒያትም የደረጅቱና ድርጅቱ አገልግሎት የሚሰጣቸው ሰዎች ጥቅም የሚተጓጎል ከሆነ ይህ ተግባር አደራ ማጥፋት፣ የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ መብላትና የተሰጠውን ሀላፊነት በሚገባ አለመወጣት አይሆንምን? ይህ ሰውዬ በእርግጥም ግዴታ ያልሆኑ ነገሮችን ለማከናውን ሲል ግዴታ የሆኑ ነገሮችን ከመፈጸም ቦዘነ ማለት ነው፡፡ ይህም ታድያ የሃይማኖትን መስጢራዊ አለማ ካለመገንዘብ የመነጨ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይድና አቡ በክር በሞት ምንጣፍ ላይ በነበሩበት ወቅት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ለሰይድና ዑመር ያስተላለፉት ምክራዊ ኑዛዜ እጅጉን የሚደነቅ ነው፡፡ ምክሩም እንድህ የሚል ነበር፡ ‹ታወቃለህ! ለአላህ በሌሊት የሚከናወንና በቀን ቢፈጸም የማይቀበለው ሥራ አለው፡፡ እንድሁም በሌሊት የሚሠራና በቀን ቢከናወን የማይቀበለው ሥራም አለው፡፡ እሱም (አላህ) ግዴታ የሆኑ ሥራዎች አስካልተሟሉ ድረስ በፈቃድ የሚሰሩ መልካም ሥራዎችን አይቀበለም፡፡›
የአላህን (ሊ.ወ.) ሃይማኖት ከዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም እንድሁም ለሰዎች ሁኔታና ለጉዳዮቻቸውም ትኩረት በሚሰጥ መልኩ በትክክል መገንዘብ ስንል የዚህ ግንዛቤ ወሰን የህጉን አላማ፣ ቅደምተከተሉን፣ ተጨባጩንና በወቅቱ ያለውን ነገር ያለመረዳት  አንዳንድ የህግ ደንቦችን በጭፍን በመመራት መልክ ከሰዎች አፍ ወይም ከመጽሐፍ በመውሰድ መገደብ የለበትም፡፡ ምክኒያቱም እንደዚያ ከሆነ የህግጋት ታላቅና የላቀ አላማ ሊሰወር ይችላልና፡፡
ከዚህ ዓይነቱ የሃማኖት ትዛዛት አላማ መር ግንዛቤና የህጉን ቅደም ተከተል ስርኣት ከማስያዝ በመነሳት የሰዎችንና የማህበረሰቡን ጉዳይ ማውጣት በተደጋጋሚ ሐጅና ዑምራ ከማድረግ የሚቀደም መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ይህውም ችግረኛን መርዳት፣ ለድሃ ምጽዋት መስጠትና የሚፈለገውን ነገር ማሟላትና በእዳ የታሰረ እስረኛን ማስፈታት በመላው ባይሆንም በከፊል ሙስሊሞች ላይ ግዴታ የሆኑ ተግባራት በመሆናቸው ነው፡፡ እንደሚታወቀው (ፈርዱል ኪፋያ) በከፊል ሙስሊሞች ግዴታ የሆኑን ነገሮች መፈጸም የሐጅና ዑምራ መደጋገምን ጨምሮ ከማንኛውም በፈቃድ ከሚደረሱ መልካም ሥራዎች ይቀደማል፡፡
እኛ በአሁኑ ወቅት ሃይማኖታችንን በትክክል መገንዘብ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ተጨባጭ ነገሮችን በንቃት መረዳታችን ደግሞ በአካባቢያችን የተደቀኑ ችግሮችን መጠን በትክክል ለመገምገም ያስችለናል፡፡ እንድሁም የአጠቃላይ ህዝብ ጥቅምን በታማኝነትና በሙሉ ገለልተኝነት ከግል ጥቅም አንድናስቀድም ይገፋፋናል፡፡ ይሀውም ወደእውነት ያዘነበለውን የሃይማኖታችንን አስተምህሮ ለመተግበር፣ የሀገራችንን አድገት፣ ከፍታና ተሃድሶ እውን ለማድረግ እንድሁም ለሱና ለነዋሪዎችም የሚመጣጠን የሆነን ከፍተኛ ቦታ እንድይዝ በማሰብ ነው፡፡
ጌታዬ ሆይ አገራችንን፣ ነዋሪዎቹን፣ መከላከያ ሃይሉን ጠባቂ ኃሎቹንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡

# (28)

## የሰማእትነት ትሩፋትና ለሰማእታት ቤተሰቦች ያለብን ግዴታ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
وَلاَ{تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوْا فِي سَبِيلِ اللّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاء عِندَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ * فَرِحِينَ بِمَا آتَاهُمُ اللّهُ مِن فَضْلِهِ وَيَسْتَبْشِرُونَ بِالَّذِينَ لَمْ يَلْحَقُوْا بِهِم مِّنْ خَلْفِهِمْ أَلاَّ خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلاَ هُمْ يَحْزَنُونَ*يَسْتَبْشِرُونَ بِنِعْمَةٍ مِّنَ اللّهِ وَفَضْلٍ وَأَنَّ اللّهَ لاَ يُضِيعُ أَجْرَ الْمُؤْمِنِينَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ፡፡ አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ተደሳቾች ሲኾኑ (ይመገባሉ)፡፡ በነዚያም ከኋላቸው ገና በእነርሱ ባልተከተሉት በእነርሱ ላይ ፍርሃት ባለመኖሩና እነርሱም የማያዝኑ በመኾናቸው ይደሰታሉ፡ከአላህ በኾነ ጸጋና ልግስና አላህም የምእምናንን ምንዳ የማያጠፉ በመኾኑ ይደሰታሉ፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
አላህ (ዐ.ወ.) የሰውን ልጅ የፈጠረው ምድርን እንዲያለማና እንዲያበጅ ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) የሰው ልጅ ለዚህ መሰሉ የምድር ማልማት የሚያስችለውን መብት አስከብሮለታል፡፡ አላህ ግዴታ የተጣለበትንም የሰውን ልጅ መንፈስ በጥብቃ አጠር የከበባት ሲሆን በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ጥቃት መፍጠርን ወይም በምድር ውስጥ የሚፈጸምን ማንኛውንም ማበላሸት በመላው የሰው ልጅ ላይ የተሰነዘረ ጥቃት አደርጎታል፡፡ እንድሁም የሰውን ልጅ ሕይወት መጠበቅንና ማንኛውንም በምድር ላይ የሚከናወንን ልማት ለመላው የስው ልጅ ጥበቃ የተፈጸመ መልካም ተግባር አድርጎታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{مَن قَتَلَ نَفْسًا بِغَيْرِ نَفْسٍ أَوْ فَسَادٍ فِي الأَرْضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ النَّاسَ جَمِيعًا وَمَنْ أَحْيَاهَا فَكَأَنَّمَا أَحْيَا النَّاسَ جَمِيعًا} .

ትርጉሙም (ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት (ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ማለትን ጻፍን፡፡) ማለት ነው፡፡

ልማትንና የሰው ልጅን ሕይወት መጠበቅ ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ታማኝ የሆኑ ሰዎች በሚያደርጉት ታላቅ መጽዋእትነት እንጂ የማይከናወን ታላቅ አላማ ነው፡፡ እነዚህ የዚህ ዓይነት መጽዋእትነት የሚከፍሉ ሰዎች ለሃይመናት፣ ሀገርና ለተረጋጋ ሕይዎት እሴቶች ያላቸው ግንዛቤ ከፍተኛ በመሆኑ ከአላህ ጋር በሚያደረጉት ትርፋማ ንግድ ይህን አላማ ለማሳካት ሕይወታቸውንና ንብረታቸውም አሳልፊው የሰጡ መሆናቸውን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾኣል፡

{إِنَّ اللّهَ اشْتَرَى مِنَ الْمُؤْمِنِينَ أَنفُسَهُمْ وَأَمْوَالَهُم بِأَنَّ لَهُمُ الجَنَّةَ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ وَعْدًا عَلَيْهِ حَقًّا فِي التَّوْرَاةِ وَالإِنجِيلِ وَالْقُرْآنِ وَمَنْ أَوْفَى بِعَهْدِهِ مِنَ اللّهِ فَاسْتَبْشِرُواْ بِبَيْعِكُمُ الَّذِي بَايَعْتُم بِهِ وَذَلِكَ هُوَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ}

ትርጉሙም (አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመኾን ገዛቸው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፡፡ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም፡ ፡ በተውራት በኢንጅልና በቁርአንም (የተነገረውን) ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ፡፡ ከአላህም የበለጠ በኪዳኑ የሚሞላ ማነው በዚያም በእርሱ በተሻሻጣችሁበት ሽያጫችሁ ተደሰቱ፡፡ ይህም እርሱ ታላቅ ዕድል ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ማንኛውም ምንዳ ከሥራ ጋር የተመጣጣነ መሆን ስለአለበት ለሌሎች ለማሟላት ካሰቡት የበለጠ የተረጋጋና ድህንነቱ የተሟላን ዘለአለማዊ ሕይወት ሰጣቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

{وَلاَ تَقُولُواْ لِمَنْ يُقْتَلُ فِي سَبيلِ اللّهِ أَمْوَاتٌ بَلْ أَحْيَاء وَلَكِن لاَّ تَشْعُرُونَ}.

ትርጉሙም (በአላህ መንገድ (ለሃይማኖቱ) የሚገደሉትን ሰዎችም «ሙታን ናቸው» አትበሉ፡፡ በእውነቱ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም፡፡) ማለት ነው፡፡

በአለህ መንገድ መጽዋእት መሆን እጅጉን የላቀ ደረጃና አላህ ለመረጣቸው ሰዎች እንጅ እውን ሊሆን የማይችል ታላቅ አላማ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَيَتَّخِذَ مِنكُمْ شُهَدَاءَ}

ትርጉሙም (ከናንተም ሰማእታትን ሊይዝ) ማለት ነው፡፡

ሰማእትነት ከነብያትና ከጸዲቃን ቀጥሎ አላህ (ዐ.ወ.) ለሚወደው ሰው የሚለግሰው ስጦታ መሆኑን እንድህ ሲል አስታውሷል፡

{وَمَن يُطِعِ اللّهَ وَالرَّسُولَ فَأُوْلَئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللّهُ عَلَيْهِم مِّنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاء وَالصَّالِحِينَ وَحَسُنَ أُولَئِكَ رَفِيقًا}

ትርጉሙም (አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ:: የእነዚያም ጓደኝነት አማረ::) ማለት ነው::

አንድ ቀን አንድ ሰውዬ የአላህ መለእክተኛ ሆይ! ከሰማእት በስተቀር ማንኛውም ምእምን በመቃብር መከራ የጋጥመዋል የተባለው ስለምንድን ነው? ሲል ጠየቀ:: እሳቸውም (የጎራዴ ነጸብራቅ በራሱ ሲያንጃብበት ያየው መከራ ስለሚበቃው ነው) በማለት መለሱለት:: ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ጅብሪልን በምትከተለው አንቀጽ የተጠቀሱት በድንጋጤ የማይሞቱት እነማን ናቸው ብለው በጠየቁ ጊዜ፡

{وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَصَعِقَ مَنْ فِي السَّمَاوَاتِ وَمَنْ فِي الأَرْضِ إِلا مَنْ شَاءَ اللَّهُ}

ትርጉሙም (በቀንዱም ይንነፋል:: በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡርና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል:: ከዚያም በእርሱ ሌላ (መንነፋት) ይንነፋል:: ወዲያውም እነርሱ (የሚሠራባቸውን) የሚጠባበቁ ኾነው ቋሚዎች ይኾናሉ::) ማለት ነው:: (እነሱ ሰማእታት ናቸው) በማለት መለሳቸው::

ሰማእት ለአለው ታላቅ ደረጃ የሚከተለው የነብያችን ቃል ብቻ ይበቀዋል ሲሉ ሊቃውንት ጠቁመዋል፡ (የማንኛውም ሰው ሥራ በማለፉ ያልቃል በአላህ መንገድ ዘብ የሚቆም ሰው ሲቀር:: እሱስ ሥራው ከሞት አስከሚነሳ ድረስ ይቀጥላል::)

በመሆኑም አላህ ሰማእትነትን የለገሰው ሰው ትሩፋቱንና ታላቅ ደረጃውን በሚያይበት ጊዜ እንደገና ሕያው ሆኖ በተደጋጋሚ ሰማእት መሆንን ይመኛል:: ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡( አንድም ሰው ጀነት ከገባ በኋላ በምድር ያለን ሁሉ ቢሰጡትምንኳ ወደዚህች ዓለም መመለስ የሚፈለግ ሰው የለም ከሰማእት በስተቀር:: እሱ ከሚያየው ታላቅ ክብር አንፃር ተመልሶ አስር ጊዜ መገደልን ይመኛል)::

በመሆኑም የነብያችን ባልደረቦች ሰማእት ለመሆን ይሽቀዳደሙ ነበር:: (ከርሳቸው አላህ ይውደድና)ዐምር ኢብን አልጀሙሕ በበድር ጦርነት ለውጊያ ለመውጣት ቢጠይቅም ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንካሳ በመሆናቸው እንዳይንገላቱ በመፍራት አልፈቀዱላቸውም ነበር:: በእሁድ ጦርነት ደግሞ ልጆቻቸውን ይዛችሁኝ ውጡ በማለት ጠየቁ:: እነሱም የአላህ መልክተኛኮ አንተ እንድትወጣ ግዴታ የለብህም ብለዋል ሲሉ አስታወሷቸው:: ሊሆን ከቶ አይችልም በበደር ቀን ጀነት ከለከሉኝ አሁንም ደግሞም በእሁድ ትከለክሉኛለችሁን! ብለው ከመውጣት የሚያግደኝ የለም ብለው አሻፈረኝ አሉ:: ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሄዱና ዛሬ የተገደለ ጀነት ይገባል ማለት ነው? ሲሉ ጠየቁ:: እሳቸውም (አዎን ) አሉ:: ይን ጊዜ በአላህ ይሁንብኝ እኔ ጀነት እገባለሁ እንጂ ወደቤተሰቦቼ አልመለስም አሉ:: በዚህን ጊዜ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ አምር ሆይ! በአላህ ላይ አትማል አሉ:: በዚያን ወቅት ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) (ቀስ በል ዑመር ሆይ! ከነሱ መካከል በአላህ ላይ ቢምል አላህ መሃላውን እውነት የሚያደርግለት ብዙ አለ:: ከነሱም መካከል አንዱ አምር ኢብን አልጀሙሕ ነው:: በጀነት በአንካሳው አግሩ ይንጎራደዳል) አሉ::

የእስልምና እምነት የሰብእነት፣ የጀግንነት፣ የወንድነት፣ የጥብቅንት እንድሁም ራስን፣ ክብርን፣ ንበረትና መብት የማስከበር ሃይማኖት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እነዚህን

ነሮች መጠበቅን የእምነት አካልና እነሱን መከላከልንም ታላቅ አላማ አድርጓል፡፡ ይህን ሲያደርግም የሞተ ሰማእት መሆኑን አብስሯል፡፡

ሰማእትነት የተላያዩ ገጽታዎች ያሉት መሆኑን ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አብራርተዋል፡ (ስለገንዘቡ የተገደለ ሰማእት ነው፡፡ ስለሃይማኖቱ የተገደለ ሰማእት ነው፡፡ ስለደሙ የተገደለ ሰማእት ነው፡፡ስለቤተሰቡ የተገደለ ሰማእት ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (... የተገደለ ሰው ሰማእት ነው፡፡ ቤት የተደረመሰበት ሰው ሰማእት ነው፡፡ በሆድ በሽታ የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ በውሃ ሰምጦ የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ አውሬ የበላው ሰው ሰማእት ነው፡ በመርዛማ ነፍሳት ተነድፎ የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ በአስም በሽታ የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ በአላህ መንገድ ዘብ ቆሞ የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ ለመተኛት ሲያስብ አላህን አውስቶ በዚያ መኝታው የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ የአላህ ቃል ከፍ እንዲልና የነዚያ የከሃዲዎች ቃል ዝቅ እንድል እያሰበ ታሞ የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡

ሰማእትነትን አላህ እንዲሰጠው ከልቡ የለመነ ሰው በእርግጥም አላህ የማይከለክለው መሆኑን ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አብራርተዋል፡ (ሰማእትነትን በእውነት ከአላህ ዘንድ የለመነ ሰው በመኝታው ቢሞትም አንኳን አላህ የሰማእታትን ደረጃ ይሰጠዋል)፡፡

እውነተኛ ሰማእት ማለት እውነትን አጥብቆ ያዘ፣ ለሱም ታማኝ  የሆነና እሱን እውን ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው ነው፡፡ ሰማእት በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም ታላቅ ክብር አለው፡፡ በዚህች ዓለም በማህበረሰቡ ዘንድ የሰማእትነትና የክብር ምሳሌ ሆኖ ይመዘገባል፡፡ ምንም እንኳን ጊዜ ቢረዝም ማንም ሰው አይዘነጋውም፡፡ በትንሳኤ ቀን ደግሞ በክብርና በውብ ገጽታ ይነሳል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (መንፈሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፡፡ አንድም ሰው በአላህ መንገድ አይቆሰልም -አላህ በሱ መንገድ የሚቆስልን ሰው ያውቃል- በትንሳኤ ቀን ቀለም የደም ቀለም መኣዛው ግን የሚስክ መኣዛ ሆኖ የሚነሳ ቢሆንእንጂ)፡፡

የተከበሩ ሰማእታቶቻችን ለሌሎች ደህንነት ቤተሰቦቻቸውን ከኋላቸው ትተው ሕይወታቸውን አሳለፈው ሰጥተዋል፡፡ እኛም እንሱን በአክብሮት መመልከትና አባቶቻቸው የከፈሉትን መጽዋእትነት የማድነቅ ግዴታ አለበን፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለናንተ ውለታ የዋልን ሰው ወሮታውን ክፈሉት፡፡ ባትችሉ ደግሞ ውለታውን ለመመለሳችሁ እርግጠኛ አስከምትሆኑ ደረስ ለሱ ጸሎት አድርጉለት፡፡) በኛ ላይ ያለበን ሌላው ግዴታ ደግሞ የአባት ማጣት መሬት እንዳይሰማቸው መጣርና ከነሱ ጋር ያለንን ግንኙነት መልካም ማድረግ ነው፡፡ ነብያችን በሙእታ ጦርነት ሰማእት ሆነው የወደቁትን የጃዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብን ልጆች ይንከባከቧቸው ነበር እንድሁም ሀላፊነታቸውን ወስደው አሳድገዋቸዋል፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁኝ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ለሰማእታቶቻችን ቤተሰቦች አስተማማኝና የተረጋጋ ህይወት የማሟላት ግዴታም አለብን፡፡ ይህ ድዴታ ድርጂቶችና መንግስትንም ያካትታል፡፡ እነሱ በሰማእተነት ያለፉት ለኛ የተመቻቸ ሕወት እውን እንዲሆን በማሰብ ነውና፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ለሰማእታት ቤተሰቦች እገዛ የሚያደርግ ሰው ታላቅ ምንዳ ያለው መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (ለአንድ ዘማች ስንቅና ትጥቅ የሚላ ሰው እንደዘመተ ይቆጠራል፡፡ ለዘማች ቤተሰቦችም እገዛ ሲል ከዘመቻ የቀረ ሰው እንደዘመተ ይቆጠራል፡፡) የሰማእታት ቤተሰቦችን መንከባከብ ለነሱ በከፊሉም ቢሆን ውለታቸውን መክፈል ማለትነው፡፡

ዘይድ ኢብን አስለም አባታቸውን ጠቅሰው የሚከተለውን ማውራታቸውን ቡኻሪ ዘግበዋል፡ የዘይድ አባት እንድህ አሉ፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ ጋር ወደገበያ ቦታ ወጣሁ፡፡ አንድት በወጣነት አድሜ ያለች ሴት ከኋላ መጣችና የምእምናን መሪ ሆይ! ባሌ ትንንሽ ህፃናት ትቶ ሞተ፡፡ በአለህ ይሁንብኝ ሰርተው መብላት አይችሉም እርሻም የላቻውም የምትታለብ እንሳሰም የለንም፡፡ የችግር ቀንም ያጠፋቸዋል የሚል ስጋት አድሮብኛል፡፡ እኔ የኹፋፍ ኢብን ኢማእ አልጊፋሪ ልጅ ነኝ፡፡ አባቴ ከአላህ መልክተኛ ጋር በሑዴቢያ ተሳትፏል አለች፡፡ ዑመርም ትንሽ ቆሙና ቅርብ ዘመድ ነሽኮ አንደምነሽ አሉ፡፡ ከዚያም እቤት አጠገብ ታስሮ ወደነበረው የጭነት ግመላቸው አመሩ፡፡ ሁለት አቁማዳዎችን በምግብ ሞልተው ከመካከላቸውም ቀለብን ልብስ አድርገው ልጓሙን ለሴትዮዋ ሰጧትና ሳቢው አላህ መልካሙን ነገር ሳይሳጣችሁ በፊት ይህ አያልቅም አሏት፡፡ በዚያን ወቅት እቦታው የነበረ አንድ ሰውዬ የምእምናን መሪ ሆይ! አበዙባት ሲል ተናገረ፡፡ እሳቸውም እናትህ ትጣህ! በአላህ ይሁንብኝ የዚህች ሴትዮ አባትና ወንድም ለረዢም ጊዜ የጠላትን ጦር ካምብ ከበው ከዚያም ሰብረው ከገቡ በኋላ እኛ የምርኮ ድርሻችንን ጠይቀን ተካፍለናል› አሉ፡፡

ዑመር ኢብን አልኸጣብ በዚህ ተግባራቸው ለሰማእታትና ከነሱም በኋላ ለቤተሰቦቻቸው መወጣት ያለብንን ግዴታ አስተምረውናል፡፡

ሌላው ለሰማእታት ቤተሰቦች ያለብን ግዴታ ደግሞ የሚገባቸውን ቦታ መስጠት የሚለው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሙእታ ጦርነት አባታው በሰማእትነት ለወደቁት ኡሳማ ኢብን ዘይድ በማስተማርና በማሳደግ 20 ዓመት ሳይሞላቸው የጦር መሪ እንድሆኑ ያበቋቸው መሆኑ ልንከተለው የሚገባ አርኣያነት ያለው ተግባር ነው፡፡

እኛ ለሰማእታት ቤተሰቦችና ልጆቻቸውም አላህ መልካም ሠራ ስለሰሩ አባቶቻቸውን ለማክበር ሲል ምንጊዜም የሚጠብቃቸው መሆኑን እናበስራልን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የአባቶች ደግነት ጥቅም ለልጆች በዚህችም ዓለም ሆነ በመጭው ዓለም የሚተላለፍ መሆኑን እንድህ በማለት ገልጾኣል፡

{وَأَمَّا ٱلۡجِدَارُ فَكَانَ لِغُلَٰمَيۡنِ يَتِيمَيۡنِ فِي ٱلۡمَدِينَةِ وَكَانَ تَحۡتَهُۥ كَنزٞ لَّهُمَا وَكَانَ أَبُوهُمَا صَٰلِحٗا فَأَرَادَ رَبُّكَ أَن يَبۡلُغَآ أَشُدَّهُمَا وَيَسۡتَخۡرِجَا كَنزَهُمَا رَحۡمَةٗ مِّن رَّبِّكَۚ وَمَا فَعَلۡتُهُۥ عَنۡ أَمۡرِي}

ትርጉሙም (ግድግዳውማ በከተማይቱ ውስጥ የነበሩ የሁለት የቲሞች ወጣቶች ነበር፡፡ በሥሩም ለእነርሱ የኾነ (የተቀበረ) ድልብ ነበረ፡፡ አባታቸውም መልካም ሰው ነበር፡፡ ጌታህም ለአካለ መጠን እንዲደርሱና ከጌታህ ችሮታ ድልባቸውን እንዲያወጡ ፈቀደ፡፡ በፈቃዴም አልሠራሁትም፡፡ (አለው)) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَالَّذِينَ آمَنُوا وَاتَّبَعَتْهُمْ ذُرِّيَّتُهُم بِإِيمَانٍ أَلْحَقْنَا بِهِمْ ذُرِّيَّتَهُمْ وَمَا أَلَتْنَاهُم مِّنْ عَمَلِهِم مِّن شَيْءٍ كُلُّ امْرِئٍ بِمَا كَسَبَ رَهِينٌ}.

ትርጉሙም( እነዚያም ያመኑትና ዝርያቸውም በእምነት የተከተለቻቸው ዝርያቸውን በእነርሱ እናስጠጋለን፡፡ ከሥራቸውም ምንም አናጎድልባቸውም፡፡ ሰው ሁሉ በሠራው ሥራ ተያዢ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ሁላችንም በእርግጠኝነት ለናውቀው የሚገባው ነገር ደግሞ የሳመእታቶቻችን መስዋእተነት በአገር ላይና በሀገር ወዳድ ዜጎች ራስ የተደፋ ዞፋን መሆኑን ነው፡፡ ማንኛውም ዜጋ ይህን የተዋደቁለትን አገር ለመጠበቅ በአለበት ቦታ ዘብ ሊቆምለት ይገባል፡፡ እዚህ ላይ ብሄራዊ ደርጅቶች በሙሉ የማህበረሰቡ ደህንነት ዋና መከላከያ መሆናቸውን ሁሉም ዜጋ ሊገነዘበው ግድ ይሆናል፡፡ ለሀገር ደህንነት ሳይሆን ለግል ጥቅማቸው የሚጥሩ የአሸበሪዎችን የህውከት ጥሪ መቋቋም ሃይማኖታዊ፣ ብሄራዊና ሰብአዊ ግዴታ ስለሆነ የመታገል ግዴታም አለብን፡፡

ሰማእታቶቻችን አላህ (ዐ.ወ.) በእዝነት ውስጥ እንዲያስገባቸውና ሀገራችንና ነዋሪዎቹዋን ከመጥፎ ነገር እንድጠብቅልን አላህን እንለምናለን፡፡ አሜን፡፡

## (29)

## የሰምኣታትና የሀገር መጽዋእትነት ታላቅ ደረጃ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ولا تقولوا لمن يقتل في سبيل الله أموات بل أحياء ولكن لا تشعرون}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለኣላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በአላህ መንገድ (ለሃይማኖቱ) የሚገደሉትን ሰዎችም «ሙታን ናቸው» አትበሉ፡፡ በእውነቱ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የግብጽ ህዝብ በዚህ ሳምንት በታሪኩ ዘላለማዊ ከሆኑ ክብረ በኣለት አጅግ ታላቁን እንድሁም አላህ (ዐ.ወ.) ለሀገሪቱ ድልን በመቸር፣ ምድርንና ክብርን ባንድ ላይ በማስመለስ ሞገስ የለገሰበትን ቅን በማክበር ላይ ይገኛል፡፡ እሱም እ.ኢ.አ. በኦክቶበር ስድስት 1973 - ሮመዳን ዐሥር 1393 ሂ. የተከናወነው የድል ባእል ነው፡፡ ይህ ድንቅ ክብረ ባእል አይበገሬው የግብጽ ጦር የጀግንነትና የመስዋእትነትን ታላቅ ትርጉም እንድሁም በአላህ እምነቱ፣ አላህ (ዐ.ወ.) በሚለግሰው ድል፣ አላማውንና ግቡን እውን ለማድረግ በራሱ በመተማመኑና ሀገሩን ነፃ ለማውጣት በነበረው ጽኑ ፍላጎት ያስመዘገበው የማይረሳ የተጋድሎ ክብረ ባእል ነው፡፡

አላማ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው፣ የታሰበውም ግብ የተገበረ ሲሆንና መዳረሻውም ለወገን ጠቃሚ ሲሆን መስዋእትነቱም በዚያው ልክ እጅጉን ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በአላህ መንገድ ሰማእትነትን አስቦ ራስን መስዋእት ከማድረግ የበለጠ መስዋእትነት የለም፡፡ አንድ ሰው ሃይማኖቱን፣ መድሩንና ክብሩን ለመከላከል ራሱን አሳልፎ በሚሰጥበት ወቅት ታላቅ የሆነውን የሰማእታት ደረጃ ያገኛል፡፡ የሰማእትነት ደረጃ አላህ (ዐ.ወ.) ከነብያትና ከፃድቃን ቀጥሎ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ችሮታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِمْ مِنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ وَحَسُنَ أُولَئِكَ رَفِيقًا}

ትርጉሙም(አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ፡፡ የእነዚያም ጓደኝነት አማረ፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) አንድ ሰው ሰማእት እንድሆን ሲመርጠው ስለሱ የወደደለት መሆኑን ያመልክታል ሲሉ ሊቃውንት ይገልፃሉ፡፡ ይህ የሰማእትነት ደረጃ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ቅዱስ ቁርአን እንድህ ሲል አመልክቷል፡፡

{ وَيَتَّخِذَ مِنْكُمْ شُهَدَاءَ}

ትርጉሙም (ከእናንተም ሰማዕታትን እንዲይዝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው የፈጣሪውን ውዴታ ለማግኘትና ሀገሩን ለመከላከል ራሱን አሳልፎ ሲሰጥ ከዚህች አላም ይልቅ መጭውን ዓለም መርጦና ስሜትና ፍላጎቱን አሸንፎ ነው፡ ፡ በመሆኑንም ይህን የተባረከ ታላቅ ደረጃ በማግኘቱና ገበያው በመሳካቱ እንኳን ደስ ያለህ  ሊባል ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ اللَّهَ اشْتَرَى مِنَ الْمُؤْمِنِينَ أَنفُسَهُمْ وَأَمْوَالَهُم بِأَنَّ لَهُمُ الْجَنَّةَ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ وَعْدًا عَلَيْهِ حَقًّا فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنجِيلِ وَالْقُرْآنِ}

ትርጉሙም (አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመኾን ገዛቸው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፡፡ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም፡ ፡ በተውራት በኢንጅልና በቁርኣንም (የተነገረውን) ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህ ምንዳው ጀነት የሆነ ገበያ እንዴት ትርፋማ ገበያ ነው፡፡ የሓሪሳ ኢብን ሱራቃ እናት ኡሙ ረቢዕ ቢንት ኢልበራእ ከእለታት አንድ ቀን ወደነብያችን ሄዳ እንድህ ማለቷ ተወርቷል፡ ‹ያላህ ነብይ ሆይ! ስለሃሪሳ ልታወሩልኝ ትችላለሁን? ልጇ ሓሪሳ በበድር ጦርነት ሰባቂው ባልታወቀ ጦር ተወግቶ ነበር የሞተው፡፡ በመቀጠልም እንድህ አለች፡ በጀነት እንደሆነ እታገሳለሁ፡፡ እንደዚያ ካልሆነ ደግሞ መርሬ አለቅስለታለሁ፡፡› ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (የሓሪሳ እናት ሆይ! በጀነት ውስጥኮ አያሌ ጀነቶች አሉ፡፡ ያች ልጅ የደረሰው ድግሞ ላይኛው ከተድላ ዓለም አጅግ ውቡና ታላቁ ነው፡፡)›

እውነተኛ ሰማእት የሚባለው የአላህን ቃል ከፍ ለማድርግና ያገሩን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጎ ለማውለብለብ እንድሁም ሀገሩን ለመከላከል ለአላህ ታማኝ በመሆን ራሱን የሰዋ ሰው ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሙሳ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጠና እንድህ አለ፡ ‹አንድ ሰው መርኮን ለማግኘት ይዋጋል፡፡ ሌላው ደግሞ ሰዎች እንዳስታውሱት ይዋጋል፡፡ ሌላውም ደረጃውን ሰዎች እንዲያቁለት ይዋጋል፡፡ ታድያ በአላህ መንገድ የሚዋጋ የሚባለው ማነው? በዚህን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (የአላህ ቃል ከፍ እንድል አስቦ የተዋጋ ሰው በአላህ መንገድ ተዋግቷል፡፡)

እንድሁም እውነተኛ ሰማእት የሚባለው በማንኛውም መልኩ ውርደትን አሻፈረኝ በማለትና እቃውን ወይም ንብረቱን ለመከላከል የተዋደቀ ሰው ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ እንድህ ብለዋል፡ ‹አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጠና ያለህ መልክተኛ ሆይ! አንድ ሰው ግንዘቤን ሊቀማኝ ቢመጣስ? እሳቸውም (ገንዘብህን አትስጠው) አሉት፡፡ እሱም ቢዋጋኝስ ምን ይላሉ? አለ፡፡ እሳቸውም

(ተዋጋው) አሉ፡፡ እሱም የገደለኝ እንደሆነስ? አለ፡፡ እሳቸውም (አንተ ሰማእት ነህ) አሉት፡፡ እሱም የገደልኩት እንደሆነስ? አለ፡፡ እሳቸውም (እሱ በገሀነም ነው) አሉ፡፡

አሁንም እውነተኛ ሰማእት ያ ምድሩን፣ ክብሩንና ሀገሩን ለመከላከል የተዋደቀ ሰው ነው፡፡ አንድ ሙስሊም ሀገርና ክብርን መከላከል ራስን፣ ሃይማኖትንና ገንዘብን እንደመከላከሉ ነው፡፡ ምክኒያቱም ሃይማኖት የሚመለክበት ሀገር ያስፈልገዋልና፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰዒድ ኢብን ዘይድ እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ የአላህ መልክተኛ እንድህ አሉ፡ (ስለገንዘቡ ሲከላከል የተጎዳ እሱ ሰማእት ነው፡፡ ቤተሰቡንም ሲከላከል የተጎዳ እሱ ሰማእት ነው፡፡ ሃይማኖቱን ሲከላከል የተጎዳ እሱም ሰማእት ነው፡፡)፣

በመሆኑም የሰማእት ስም ምንጊዜም የአላህን ቃል ከፍ ለማድረግና ምድርን ለመጠበቅ በአላህ መንገድ ራሱን ከሰዋ ስም ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ የሀገር ፍቅር ከእምነት መዋቅሮች አንዱ በመሆኑ ዘላለማዊ የሆነው የሲናይ ተሸጋሪ ሰማእታት ንጹሁ የግብጽ ምድር በደማቸው የተከበረና መንፈሳቸውም ወደፈጣሪ ያረገ በመሆኑ እንኳን ደስ ያላችሁ እንላለን፡፡ አላህም ከሰማእታት እንዲያደርገን እንለምናለን፡፡ በአላህ መንገድ ሰማእትነት ታላላቅ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከነሱም መካከል በመጀመሪያ የሚጠቀሰው ከአላህ ዘንድ ሕያው ሆነው የሚመገቡ መሆናቸው ሲሆን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَلَا{تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ *فَرِحِينَ بِمَا آتَاهُمُ اللَّهُ مِنْ فَضْلِهِ وَيَسْتَبْشِرُونَ بِالَّذِينَ لَمْ يَلْحَقُوا بِهِمْ مِنْ خَلْفِهِمْ أَلَّا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ *يَسْتَبْشِرُونَ بِنِعْمَةٍ مِنَ اللَّهِ وَفَضْلٍ وَأَنَّ اللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجْرَ الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም (እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ፡፡ አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ተደሳቾች ሲኾኑ (ይመገባሉ)፡፡ በነዚያም ከኋላቸው ገና በእነርሱ ባልተከተሉት በእነርሱ ላይ ፍርሃት ባለመኖሩና እነርሱም የማያዝኑ በመኾናቸው ይደሰታሉ፡፡ ከአላህ በኾነ ጸጋና ልግስና አላህም የምእምናንን ምንዳ የማያጠፉ በመኾኑ ይደሰታሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

አዎን ህያው ናቸው ሙታን አይደሉም፡፡ እነሱም ከአላህ ዘንድ ተመጋቢዎች ናቸው፡፡ አላህም በሰጣቸው ሲሳይ ደስተኞች ናቸው፡፡ ዓይን ያለየው፣ ጆሮም ያልሰማው በሰው ልጅ ሀሳብ ምጥቶ በማያወቅ ነገር በተሞላው ዘውታሪ በሆነው ገነት ውስጥ ሲደሰቱ ወደነሱ የሚመጡት ወንድሞቻቸው የማያዝኑና የማይጨነቁ ለመሆናቸው ብስራት እየሰጡ በአላህ ትሩፋትና ተድላ ይኖራሉ፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር ኢብን ዓብድላህ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንድ ቀን የአላህ መልክተኛ መንገድ ላይ አገኙኝ፡፡ እንድህም አሉኝ፡ (ጃቢር ሆይ! ምነው ቀልብህ የተሰበረ ትመስላለህ? ) እኔም የአላህ መልክተኛ ሆይ! አባቴ ልጆችና እዳም ትቶ ሰማእት ስለሆነ ነው አልኩኝ፡፡ እሳቸውም (አላህ (ዐ.ወ.) አባትህን በምን እንደተቀበለው አላበስርህም ወይ?) አሉ፡፡ ጃቢርም ይሁን ያለህ መልክተኛ ሆይ! አሉ፡ ፡ እሳቸውም (አላህ (ሱ.ወ.) አንድንም ፍጡር ከመጋረጃ ጀርባ ቢሆን እንጂ አናግሮ አያውቅም ነገር ግን አባትህን አስነስቶ ከመካከላቸው መጋረጃ ወይም መልክተኛ ሳይኖር አናገረው፡፡ እንድህም አለው፡ ባሪያዬ ሆይ! የምትመኘውን ነገር ሁሉ ጠይቀኝ እሰጥሃለሁ፡፡ እሱም ጌታዬ ሆይ! ሕያው አድርገኝና እንደገና ባንተ መንገድ ልገደል አለ፡፡ ጌታውም (ዐ.ወ.) እኔ ከዚህ በፊት እነሱ እንደገና ወደሷ አይመለሱም የሚል ፍርድ አሳልፌያለሁ አለ፡፡ ከዚያም እንድህ የምትለዋ አንቀጽ ወረደች አሉ)፡

وَلاَ{تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا}.

ትርጉሙም (እነዚያ በአላህመንገድ የተገደሉት ሙታን ናቸው ብለህ አታስብ) ማለት ነው፡፡

የሰማእታትን ታለቅ ቦታ የሚያመለክቱ ስድስት ባህርያት ያሉ መሆኑን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አል ሚቅዳም ኢብን መዕድ የክሪብ እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ እንድህ ብለዋል፡ (ለሰማእት አላህ ዘንድ ስደስት ገጽ ባህርያት አሉት -እነሱም- በመጀመሪያው ዙር ምህረት ይደረግለታል፡፡ በጀነት ያለውንም መቀመጫውን ያያል፡፡ ከገሀነም ቅጣት ይጠበቃል፡፡ ከታላቁ ድንጋጤም ይድናል፡፡ አንዷ ፊርጥ የከበረች ድንጋይ ከአለማችንና በውስጧም ካለው ሁሉ የምትበልጥ የሆነን የክብር ዘውድ በራሱ ላይ ይደፋል፡፡ ከሑረል ዓይንም የሆኑን ሰባ ሁለት ሚስቶችን ያገባል፣ ሰባ የሚሆኑ ዘመዶቹንም ይታደጋል፡፡)

ለሰማእት ከሚቸሩ ክብሮች ሌላው ደግሞ መላእኮች በከንፋቸው ጥላ የሚያደርጉለት መሆኑ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር ኢብን አብዷላህ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹በኡሑድ ጦርነት እለት አባቴ ሰማእት ሆኖ ከወደቀና አካላቱንም ከቆራረጡት በኋላ ወደነብያችን አመጡት፡፡ ፊቱን ለመግለጥ ብቃጣ ወገኖቼ ከለከሉኝ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድት ሴት ስትጮህ በሰሙ ጊዜ፡ (ለምን ታለቅሻለሽ? አታልቅሺ መላኮቹኮ አሁንም በክንፋቸው ጥላ እንዳደረጉለት ናቸው) አሉ፡፡

በአላህ መንግድ የተዋደቀ ሰማእት ሌላው ክብር ደግሞ ያለቅጣትና ያለሂሳብ በመጀመሪያ ወደጀነት የሚገባው ቡድን አካል መሆኑ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላ ኢብን አምር ኢብን ኢል ዓስ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ያለህ

መልክተኛ እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (አላህ ሱ.ወ.) በትንሳኤ ቀን ገነትን ይጠራታል፡ በውብቷም አሸብርቃ ትመጣለች፡፡ አላህም እነዚያ በአላህ መንገድ የተዋጉት፣ በመንገዴ የተገደሉት፣ በመንገዴም የተጎዱትና በመንገዴ የታገሉት ባሮቼ የታሉ ይላል ከዚያም ገነት ግቡ ይላቸዋል፡፡ እነሱም ያለሂሳብና ያለቅጣት ገነትን ይገባሉ፡፡ መላእክትም ይመጡና ጌታችን ሆይ እኛ ሌት ተቀን ስናጠራህና ስናሞግስህ ኖረን እነዚያ ከኛ ያስቀድምካቸው እነማን ናቸው? ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ የበረከት ባለቤት የሆነው ጌታችንም እነዚህ እነዚያ በኔ መንገድ የታገደሉና የተጎዱ ባሮቼ ናቸው ይላል፡፡ መላእክትም ስለታገሳችሁ ሰላም ለናንተ ይሁን ምን ያመረ የመጨረሻ አገር እያሉ በየጀነቱ በር ወደነሱ ይገባሉ፡፡)

በነዚህ ሁሉ ነገሮች ምክኒያት ሰማእት ብቻ ነው ወደዚች ዓለም መመልስና እንደገና በአላህ መንገድ መገደለን የሚመኘው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡ የአላህ መልክተኛ እንድህ ብለዋል፡ (በምድር ላይ ያለው ሁሉ ቢሰጠውም ገነት ከገባ በኋላ ወደዚህች ዓለም መመለስን የሚፈልግ አንድም ሰው የለም ከሰማእት በስተቀር እሱ ከሚያየው ታላቅ ክብር አንፃር ወደዚህች ዓለም ተምልሶ አስር ጊዜ በአላህ መንገድ መገደልን ይመኛል፡፡

ይህን ቃሌን እናገራለሁ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡ ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

በዚህች ዓለም ስንኖር ተላቅና የተከበረን አላማ ለማሳካት በዚሁ መጠን ታላቅ መስዋእትነትን ይጠይቃል፡፡ ይህንም ማለትም የግብ ታላቅነትና የአላማ ክቡርነት ታላቅ መስዋእትነትን ይጠይቃል ማለት ነው፡፡ ይህም የደረጃውን ታላቅነት ያስከትላል፡፡ ይህም በአላህና በሀገር መንገድ የተሰዋ ሁሉ ባሕርይ ነው፡፡
ስለክብሩ ሀገራችንና ስለቅኑ ሃይማኖታችን ያለብንም ግዴታ ጳጥታውን ለማስከበር የሚቃጣ ትንኮሳን ለመመከትና የተደቀነበትን አደጋ ለመቋቋም በጋራና በመተባበር መስራት ነው፡፡ ሀገራችን ለመዳፈር የሚያስብን ማንኛውንም ወገን ለመመከት ነቅተን መጠበቅና ሀላፊነታችንን ለመወጣት ያለመሰልቸትና ያለመታከት ሁሉም እንደችሎታው መታተር ይኖርብናል፡፡
በአላህ መንገድ በመጠበቅና በመተሳሰር የሚሰሩና ለአላህ የገቡትንም ቃል በማክበር፣ በጠንካራ እምነትና በተረጋጋ እርግጠኝነት ውድ ሀገራችን ግብጽን ወደግንባታና ልማት ያሸጋገረው የሀገር መከላከያችንን በዚህ በማይረሳው ድል ባእል እንኳን ደስ ያላችሁ እንላለን፡፡

በአሁኑ ወቅት እኛ ልንጫወተው የሚገባው ሚና ወደ ልማት፣ ሥራና ምርት መስክ ለመሸጋገር በትጋት መስራት ይሆናል፡፡ ይህውም አይበገሬ የተበላውን ባርሊቭ የተባለውን የእስራኢልን የመከላከያ ምሽግ የሰባበረው በዚህ የተከበረ ቀን የጠላትን ነበልባል ያለመፍራት ወደሲናይ የተሻገረው የግብጽ ጀግኖችና ልጆቻቸው እንድሁም የልጅ ልጆቻቻው ማንኛውንም መከራ በመሰባበር ደህነነትን የማስከበር፣ ልማትን የማረጋገርጥና አንድነትን እውን የማድረግ ብቃት ያለቸው መሆኑን ለአለም ህዝብ ለመረጋገጥ ነው፡፡
ጌታችን ሆይ አገራችንና ህዝባችንን ጠብቅልን የሰላምና ደህንነትን ጸጋ ዘላቂ አድርግልን፡፡ አሜን፡፡

(30)

## ጓደኝነትና የአንድን ሰው ማንነት በማዋቀር ያለው ተጽእኖ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ٱلْأَخِلَّاءُ يَوْمَئِذٍۭ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ إِلَّا ٱلْمُتَّقِينَ}

ለአለው ለዐለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ወዳጆች በዚያን ቀን ከፊላቸው ለከፊሉ ጠላት ነው፡፡ አላህን ፈሪዎች ብቻ ሲቀሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዷሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማህበራዊ ፍጡር ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖር ከሌላው ሰው በሚለየው የማንነት ባሕርዩ አማካይነት የማህበረሰቡ ተጽእኖ ያድርበታል፡፡ እንድሁም ከሱ ጋር የጋራ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናል፡፡ አብሮ መኖርና ጓደኝነት በአንድ ሰው እሳቦትና ስርኣተ ሕይወት ግልጽ የሆነ ተጽእኖ አላቸው፡፡ በእነሱም አማካይነት የአንድ ሰው የወደፊት እጣፋንታዎና በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም የሚኖረው ደስታ ይወሰናል፡፡
የሚገነባና የማያፈርስ፣ የሚያለማና የማያበላሽ እንድሁም ከማንኛውም ሌላ ጥቅም አጠቃላይ የሀገርን ጥቅም የሚያስቀድም ትውልድ ለማዘጋጀት በታላቅ ሰብእነትና

በከፍተኛ ሐገራዊ ፍቅር ደረጃ የታነጸ ትክክለኛ ማንነት የሚያስፈልገን መሆኑ አያነጋግርም፡፡
ቅኑ የእስልምና ህግ አደጋን ፈጥኖ የሚረዳ ሙሉ ግንዛቤ ያለውና የህይወትን ችግሮች በተገቢው መልኩ የሚቋቋም እንድሁም መከራዎችንና አጠራጣሪ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያልፍ ማንነት ያለው ግለሰብ መገንባት መስፈርቱን አሟልቶ እንድከናወን አዟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَاتَّقُوا فِتْنَةً لَّا تُصِيبَنَّ الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنكُمْ خَاصَّةً }

ትርጉሙም (ያችን እነዚያን የበደሉት ሰዎች ብቻ የማትነካን ፈተና ተጠንቀቁ፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህው የእስልምና ህግ ማንኛውም ሰው ጠቃሚ ቀጥተኛ መንገድን የሚረዳ፣ እውነትን የሚከተልና ከጭፍን ተጓዦች ጋር አብሮ የማይነጉድ የማያውላውል በራሱ መተማመንን መሰረት ያደረገ ማንነት እንድኖረው መምሪያ ሰጥቷል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሰዎች መልካም ሲሠሩ መልከም እንሠራለን ከበደሉም እንበድላለን የምትሉ አብሮ ነጓጅ አትሁኑ፡፡ ነገር ግን ሰዎች መልካም ሲሠሩ መልካም በመስራትና ሲበድሉ ባለመበደል መንፈሳችሁን ግሯት፡፡)
የአንድን ሰው ማንነት በማዋቀር ረገድ ጥልቅ ተጽእኖ ካለቸው አበይት ነገሮች አንደኛው ጓደኝነት መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ አንድ ሰው አቀማማጩ ትጽእኖ ያሳድርበታል እንድሁም በእሳቦት፣በእምነት፣ በስነ ምግባርና በስራ የሱን ገጽታ ይይዛል፡፡ ይህ ጉዳይ በህግ፣ በአአምሮ፣ በተሞክሮ፣ በተጨባጭ ነገሮችና በምልከታ ተረጋግጧል፡፡
እዚህ ላይ እንግድህ የመልካም ጓደኝነት አስፈላጊነት ለሃይማኖቱ፣ ለሀገሩና ለማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆንን ትክክለኛ ማንነት በመዋቀር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ነው እንላለን፡፡ በዚህም ሁኔታ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.)የተከበሩ ባልደረቦቻቸውን አስተምረዋል፡፡ ከነሱም መካከል በቀደምትነት የሚጠቀሱት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በመልካም ጓደኝነት አርኣያነት ያለው ተግባር የፈጸሙትና የምልካም ጓደኝነትን ሙሉ መብት ያደረሱት አቡ በክር አል ሲዲቅ ናቸው፡፡ ይህም የመካ ሰዎች ይህ ባልደረባህ ዛሬ ሌሊት ወደበይተል መቅድስ ሄዶ ከዚያም እንደተመለሰ ያወራል ባሉ ጊዜ በጓደኛቸው ያለቸውን ሙሉ እምነት በማጉላትና በእርግጠኝነት ‹እንደዚህ በለው ከሆነ በእርግጥም እውነት ተናግረዋል፡፡ እኔ ከዚያ በራቀ ነገር አምናቸዋለሁ በሰማይ ወሬ› በማለታቸው ነው፡፡
ይህ ተግባር የነብያችን ባልደረቦች (ሰ.ዐ.ወ.) ከመካከላቸው ሲያከናዉነት የኖረ ተግባር ነው፡፡ እነሱም በወንድም ተማማችነት፣ ከራስ ሰዎችን በማስቀደም፣ በአንድነት፣ ጠቃሚ በሆነ አዎንታዊ ሥራ በመዋደድና በመተዛዘን የታነጸ ደግ የሆነ መልካም ጓደንነት ልንከተለው የሚገባ አርኣያ ናቸው፡፡ ኑዕማን ኢብን በሺር እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (ምእምናን በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና እንዱ ለሌላው በመጨነቃቸው አንድ የአካል ክፍል ህመም

በተሰማው ጊዜ ሌሎቹም አካላት እንቅልፍ በማጣትና በመሰቃየት እንደሚጠራሩለት አንድ ሰውነት ናቸው፡፡)

እንድሁም የጻድቃን ጓደኝነት በዚህችም ዓለም ሆነ በመጭው ዓለም ልዩ በረከትና ትሩፋት ያለው መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጠዋል፡ (የበረከት ባለቤትና ታላቅ ለሆነው አላህ የተከበሩ በራሪ መላእኮች አሉት፡፡ እነሱም አላህን ማስታወስ ያለባቸውን የሰዎች ስብስብ ይከታተላሉ፡፡ አንድ አላህ የሚወሳበትን ስብስብ ሲያገኙ እነሱ ጋር ይቀመጣሉ፡፡ ከፊላቸው በከፊላቸው ክንፍ ከነሱና ከመድር ሸፋን ሰማይ መካከል ያለውን ቦታ ይሸፍናሉ፡፡ ሲበታተኑም ተነስተው ወደሰማይ ያርጋሉ፡፡ ከዚያም እንድህ አሉ፡ አላህ (ዐ.ወ.) የነሱን ሁኔታ እያወቀ ሳለ ከየት መጣችሁ ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ እነሱም እኛ የመጣነው በምድር ከሚኖሩ ለአንት ከሆኑ ባሮች ዘንድ ነው፡፡ እነሱም ያጠሩሃል፣ ታላቅነትህን ይናገራሉ፣ ካንተ በስተቀር አምላክ እንደሌለም ይመሰክራሉ፣ ያመሰግኑሃል ይለምኑሃልም ይላሉ፡፡ እሱም ምንድነው የሚለምኑኝ? ሲል ይጠይቃቸወል፡፡ እነሱም ጀነተህን ነው የሚለምኑህ ይላሉ፡፡ እሱም ጀነቴን አይተዋል እንዴ? በማለት ይጠይቃቸዋል፡፡ እነሱም አላዩአትም ጌታችን ሆይ! ይላሉ፡፡ እሱም ጀነቴን በዩዋት ኖሮ እንደት ይሆኑ ነበር? ይላል፡፡ እነሱም ካንትም ጥበቃን ይጠይቃሉ ይላሉ፡፡ እሱም ከምን እንዲጠብቃቸው ነው የሚጠይቁት? ይላል፡፡ እነሱም ጌታችን ሆይ! ከእሳትህ እንዲትጠብቃቸው ነው የሚጠይቁህ ይላሉ፡፡ እሱም እሳቴን አይተዋታል እንዴ? ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ እነሱም አላየዋትም ጌታችን ሆይ! እሱም ቢያዩዋት ኖሮ እንዴት ይሆኑ ነበር ይላል፡፡ እነሱም ምህረትንም ይጠይቁሃል ይላሉ፡፡ እሱም በእርግጥ ምህረት አድርጌላቸዋለሁ፣ የለመኑትንም ስጥቻቸዋለሁ፣ እንድጠብቃቸው ከጠየቁኝም ነገር ጠብቂያቸዋለሁ፣ ከዚያም ነብያችን እንድህ አሉ እነሱ እንድህ ይላሉ፡ ጌታችን ሆይ! ስህተት ፈጻሚው አገሌኮ ከነሱ መካከል አለ እሱም በዚያ ሲያልፍ ነው ከነሱ ጋር የተቀመጠው ይላሉ፡፡ እሱም ለሱም ምህረት አድርገሁ እነሱ አቀማማጫቸው መናጢ የማይሆን ሰዎች ናቸውና፡፡)

ከመልካም ጓደኝነት ጥቅም አንደኛው የአላህን ውዴታ እንድሁም ጀነትን የሚያስገኝ መሆኑ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ብለዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (አንድ ሰው በሌላ መንደር የሚኖር ወንድሙን ሊጠይቅ ሄደ በመንገዱ ላይ መላእክ አስቀመጠለት ወደሱ በደረሰ ጊዜ ወዴት እየሄድህ ነው? ሲል ጠየቀው፡፡ እሱም እዚህች መንደር ያለን ወንድሜን ለመጠየቅ ነው አለ፡፡ ከሱ የምታገኘው ጥቅም አላህን? በማለት ጠየቀው፡፡ እሱም የለም ነገር ግን ለአላህ ብዬ የወደድሁት ወንድሜ ነው፡፡ መላእኩም እኔ ወዳንተ የተላክሁ መልክተኛ ነኝ፡፡ አላህ ለሱ ብለህ ወንድምህን እንደወደድህ ሁሉ አላህ ወዶሃል አለው፡፡)

እንደዚሁም መልካም ጓደኝነት በትንሳኤ ቀን ከመልካሞቹ ጋር መሰብሰብን ያስገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድን) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንድ ሰውዬ መቼ ነው የትንሳኤ ቀን ሲል ስለትንሳኤ ቀን ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ጠየቀ፡፡

እሳቸውም (ለሱ ምን አዘጋጅተህላታል?) ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም ምንም አለዘጋጀሁም ነገር ግን አላህንና መልከተኛውን እወዳለሁ አለ፡፡ እሳቸውም (አንተ ከወደድከው ጋር ነህ፡፡) አሉት፡፡ አነሱም ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ‹አንት ከወደድከው ጋር ነው› በማለታቸው የተደሰትነውን ያህል ተደስተን አናውቅም› አሉ፡፡ አነሱም አኔ የአላህን መልከተኛ (ሶ.ዐ.ወ.)ን፣ አቡ በክር ሲዲቅንና ዑመርን እወዳለሁ አነሱን በመውደዴም ከነሱ ጋር መሆንን ተስፋ አደርጋለሁ የንሱን ዓይነት ሥራ ባልሰራም እንኳ አሉ፡፡›
ኢማሙ አሻፊዒ የተባሉት ሊቅ እንድህ በማለታቸው ይደነቃሉ፡
ከነሱ አይደለሁም ጻድቃንን እወዳቸዋለሁ፡፡ በነሱ ምናልባት መታደግን እከጅላለሁ፡፡ በወንጅል የሚነግድን ሰው እጠላለሁ፡፡ በእቃ ከነሱ ጋር እኩል በንሆንም እንኳ፡፤

ከጻድቃን ጓደኝነት ጥቅሞች ሌላው ደግሞ አላህን እንድናስታውስ ያደርገናል እንድሁም በተለያዩ ዘርፎች በዚህችም ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም በርካታ መልካም ነገሮችን ያስገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዓባስ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ብለዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ያላህ መልከተኛ ሆይ! የትኛው አቀማማጭ ነው መልካሙ የሚል ጥያቄ ተጠየቁ እሳቸውም (ስታዩት አላህን እንድታስታውሱ፣ ንግግሩ እውቀታችሁን እንድትጨምሩ፣ ሥራው መጭውን ዓለም የሚያስታውሳችሁ ነው፡፡)

ትክክለኛ ጓደኛ የወንድሙ መስተዋት ነው፡፡ ወደመልካምም ነገር ይመራል፡፡ ከተንኮልም ይከልክላል፡፡ ለራሱ የሚወደን ለወንድም እንድወድ ያደርጋል፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

{ وَالْعَصْر *إِنَّ الإِنْسَانَ لَفِي خُسْرٍ *إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَتَوَاصَوْا بِالْحَقِّ وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْر }

ትርጉሙም (በግዚያቱ እምላለሁ፡፡ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ በኪሳራ ላይ ናቸው፡፡ እነዚያ መኑት መልካሞችን የሠሩት በእውነት አደራ የተባባሉት በትግስትም አደራ የተባበሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ብለዋል፡ አላህ መልከተኛ እንድህ አሉ፡ (ወንድምህን በዳይም ይሁን ተበዳይ እርዳ፡፡) አሉ፡፡ እኛም ያለህ መልከተኛ ሆይ! ተበደይ ሲሆን እንረደዋለን በዳይ ሲሆን እንደት እነረደዋለን አልን፡፡ እሳቸውም (ከበደል ታግደዋለህ ይህም ለሱ የምታደርገው እርዳታ ነው፡፡) አሉ፡፡

ይህን መሰረት በማድረግ መልካሙ ጓደኛ ጓደኛው ከቀጥተኛ መስመር በወጣና ጀመረ ጊዜ ምክሩን ይለግሰዋል፣ እውነቱንም ያብራራለታል፣ መስራት ያለበትንም ነገር ይግልጽለታል፣ ከአላህ መራቅ የሚያስከትለውንም ችግር ያስጠነቅቀዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{قَالَ لَهُ صَاحِبُهُ وَهُوَ يُحَاوِرُهُ أَكَفَرْتَ بِالَّذِي خَلَقَكَ مِن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ سَوَّاكَ رَجُلًا *لَّكِنَّا هُوَ اللَّهُ رَبِّي وَلَا أُشْرِكُ بِرَبِّي أَحَدًا *وَلَوْلَا إِذْ دَخَلْتَ جَنَّتَكَ قُلْتَ مَا شَاءَ اللَّهُ لَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللَّهِ إِن تَرَنِ أَنَا أَقَلَّ مِنكَ مَالًا وَوَلَدًا *فَعَسَى رَبِّي أَن يُؤْتِيَنِ خَيْرًا مِّن جَنَّتِكَ وَيُرْسِلَ عَلَيْهَا حُسْبَانًا مِّنَ السَّمَاءِ فَتُصْبِحَ صَعِيدًا زَلَقًا *أَوْ يُصْبِحَ مَاؤُهَا غَوْرًا فَلَن

تَسْتَطِيعَ لَهُ طَلَبًا *وَأُحِيطَ بِثَمَرِهِ فَأَصْبَحَ يُقَلِّبُ كَفَّيْهِ عَلَى مَا أَنفَقَ فِيهَا وَهِيَ خَاوِيَةٌ عَلَى عُرُوشِهَا وَيَقُولُ يَا لَيْتَنِي لَمْ أُشْرِكْ بِرَبِّي أَحَدًا}.

ትርጉሙም (ጓደኛው (አማኙ) እርሱ ለርሱ የሚመላለሰው ሲሆን በዚያ ከአፈር ከዚያም ከፍተወት ጠብታ ከፈጠረህ ከዚያም ሰው ባደረገህ (አምላክ) ካድክን? አለው፡፡ እኔ ግን እርሱ አላህ ጌታዬ ነው (እላለሁ)፡፡ በጌታየም አንድንም አላጋራም፡፡ አትክልትህም በገባህ ጊዜ አላህ የሻው ይሆናል በአላህ ቢሆን እንጂ ሃይል የለም አትልም ኖሯልን? እኔን በሃብትም በልጅም ካንተ በጣም ያነስኩ ሆኜ ብታየኝ ጌታየ ከአትክልትህ የበለጠን ሊሰጠኝ በርሷም (በአትክልትህ) ላይ ከሰማይ መብረቆችን ሊልክባትና የምታንዳልጥ ምልጥ ምድር ልትሆን ይችላል፡፡ ወይም ውሃ ሰራጊ ሊሆን ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ለርሱ መፈለግን ፈጽሞ አትችልም (አለው) ሀብቱም ጠፋ እሷ በዳሶቿ ላይ የወደቀች ሆና በእርሷ ባወጣው ገንዘብ ላይ (እየተጸጸተ) መዳፎቹን የሚያገላብጥና ወይ ጸጸቴ በጌታዬ አንድም ባላጋራሁ የሚል ሆኖ ለእርሱም ከአላህ ሌላ የሚረዱት ጭፍሮች አልነበሩትም፡፡) ማለት ነው፡፡

እንድህ ያለው ገጣሚ እንድህ በማለቱ በጣም ይደነቃል፡

ትክክለኛ ወንድምህ ካንተ ጋር የሚሆን ነው፡፡ አንተን ሊጠቅምም ራሱን የሚጎዳው፡፡ ቀን በጣለህም ጊዜ አንተን ሊሰበስብህ አራሱን ይበታትናል፡፡

ለመልካም ጓደኝነት በዚህም ዓለም ይሁን በመጭው ዓለም መልካምና ጠቃሚ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ሁሉ አፍራሽና መስመር ሳች አሉታዊ ማንነት በማዋቀር መጥፎ ጓደንነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በመሆኑም በዚህች ዓለም ጎጂና አበላሽ ተጽእኖ በመጭውም ዓለም ኪሳራ ያደርሳል፡፡ መጥፎ ጓደኝነት መልካም እሴቶችን ያፈርሳል፡፡ መልካም ምግባራትን ያብሳል፡፡ እንድሁም ታዳጊውንም ይሁን ወጣቱን ያበላሻል፡፡ ሥራን ያስተጓጉላል፡፡ አሉባልታና ጥሜት ይስፋፋል፡፡ መጥፎ ሰሪ ጓደኛው እምነትን በማበላሸት፣ አፍራሽ እሳቦትን በማስፋፋት መጥፎ እንድስራ ይጥራል፡፡ የመጥፎ ጓደኝነትን ገጽታ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{فَأَقْبَلَ بَعْضُهُمْ عَلَى بَعْضٍ يَتَسَاءَلُونَ *قَالَ قَائِلٌ مِنْهُمْ إِنِّي كَانَ لِي قَرِينٌ *يَقُولُ أَإِنَّكَ لَمِنَ الْمُصَدِّقِينَ *أَإِذَا مِتْنَا وَكُنَّا تُرَابًا وَعِظَامًا أَإِنَّا لَمَدِينُونَ *قَالَ هَلْ أَنْتُمْ مُطَّلِعُونَ * فَاطَّلَعَ فَرَآهُ فِي سَوَاءِ الْجَحِيمِ *قَالَ تَاللَّهِ إِنْ كِدْتَ لَتُرْدِينِ *وَلَوْلَا نِعْمَةُ رَبِّي لَكُنْتُ مِنَ الْمُحْضَرِينَ *أَفَمَا نَحْنُ بِمَيِّتِينَ *إِلَّا مَوْتَتَنَا الْأُولَى وَمَا نَحْنُ بِمُعَذَّبِينَ *إِنَّ هَذَا لَهُوَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ * لِمِثْلِ هَذَا فَلْيَعْمَلِ الْعَامِلُونَ}

ትርጉሙም (የሚጠያየቁም ሆነው ከፊላቸው ወደከፊላቸው ይመጣሉ፡፡ ከነርሱ የሆነ ተናጋሪ ይላል እኔ ጓደኛ ነበረኝ፡፡ በእርግጥ አንተ ከሚያምኑት ነህን? የሚል፡፡ በሞትንና አፈር አጥንቶች በሆን ጊዜ እኛ በርግጥ እንመረመራለን? የሚል፡፡ እናንተ ተመልካቾች ናችሁን? ይላል፡፡ ይመለከታልም በገሀነም መካከልም (ጓደኛውን) ያየዋል ይላል በአላህ እምላለሁ፡፡ በእርግጥ ልታጠፋኝ ቀርበህ ነበር የጌታየም ጸጋ ባይኖር ኖሮ ወደእሳት የምቀርብ እሆን ነበር፡፡ እኛ የምንሞት አይደለንምን የመጀመሪያውን

ሞታችንን እንጂ እኛም የምንቀጣ አይደለንምን፡፡ ይህ ታላቅ ስኬት ነው፡፡ ለዚህም አምሳያ ሰሪዎች ይስሩ፡፡) መለት ነው፡፡

{وَيَوْمَ يَعَضُّ الظَّالِمُ عَلَى يَدَيْهِ يَقُولُ يَا لَيْتَنِي اتَّخَذْتُ مَعَ الرَّسُولِ سَبِيلًا *يَا وَيْلَتَى لَيْتَنِي لَمْ أَتَّخِذْ فُلَانًا خَلِيلًا*لَقَدْ أَضَلَّنِي عَنِ الذِّكْرِ بَعْدَ إِذْ جَاءَنِي وَكَانَ الشَّيْطَانُ لِلْإِنسَانِ خَذُولًا}

ትርጉሙም (በዳይም ከመልክተኛው ጋር ቀትኛውን መንገድ ይዤ በሆነ ዋ ምኞቴ እያለ (በጸጸት) ሁለት እጆቹን የሚነክስበትን ቀን (አስታውስ) ማለት ነው፡፡ ዋ ጥፋቴ እገሌን ወዳጅ ባልያዝኩ ኖሮ እመኛለሁ፡፡ (የእመነት ቃልን) ከመጣልኝ በኋላ ከማስታወስ በእርግጥ አሳሳተኝ፡፡ (ይላል) ሰይጣንም ለሰው አጋላጭ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጥፎ ጓደኝነት ወናፍ እንደሚነፋ ሰው መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (የመልካም አቀማማጭና የመጥፎ አቀማማጭ ምሳሌ እንደሚስክ ተሸካሚና እንደወናፍ ነፊ ነው፡፡ ሚስክ ተሸካሚ ወይም በሽታው ይስበሃል ወይም ከሱ ትገዛለህ፡፡ ወይም ከሱ መልካም ሽታ ታገኛለህ፡፡ ወናፍ ነፊ ደግሞ ጨርቅህን ያቃጥልለሃል ወይም መጥፎ ሽታ ያስከትልብሃል፡፡)

መጥፎ ጓደኝነት ራስን እንድሁም ሌላን ለመበደል በር ይከፍታል፡፡ እንድሁም ወደአፍራሽና በምድር አበላሽ ቡድኖች ጎዳናም ይመራል፡፡ እንድሁም ወደአደንዛዥ እጽና ወደሱስ የሚያደርስ ሲሆን ማንኛውንም ሰው በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም ወደጥፋትና አላህ ወደሚጠላው ነገር ይመራል፡፡

ይህን ነገር ተናገርሁኝ ለኔና ከናንተ ከአላህ ዘንድ ምህረትን እጠይቃለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

እኛ ሁላችንም ከመጥፎ ሰዎች መጠንቀቅና ከነሱ ጋር አለመቀላቀል ይኖርብናል፡፡አላህ (ሱ.ዐ.) እንድህ ይላል፡

{وَقَدْ نَزَّلَ عَلَيْكُمْ فِي الْكِتَابِ أَنْ إِذَا سَمِعْتُمْ آيَاتِ اللَّهِ يُكْفَرُ بِهَا وَيُسْتَهْزَأُ بِهَا فَلَا تَقْعُدُوا مَعَهُمْ حَتَّى يَخُوضُوا فِي حَدِيثٍ غَيْرِهِ إِنَّكُمْ إِذًا مِثْلُهُمْ إِنَّ اللَّهَ جَامِعُ الْمُنَافِقِينَ وَالْكَافِرِينَ فِي جَهَنَّمَ جَمِيعًا}

ትርጉሙም (በእናንተም ላይ በመጽሐፉ ውስጥ የአላህን አንቀጾች በርሷ ሲካድባትና በርሷ ሲላገጥባት በሰማችሁ ጊዜ በሌላ ወሬ ውስጥ እስከሚገቡ ድረስ ከነሱ ጋር አትቀመጡ፡፡ ማለትን በእርግጥ አወረደ፡፡ እናንተ በዚያን ጊዜ በጥያቸው ናችሁ፡፡ አላህ ምናፍቃንን እና ከሃደዎችን በሙሉ በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

{وَإِذَا رَأَيْتَ الَّذِينَ يَخُوضُونَ فِي آيَاتِنَا فَأَعْرِضْ عَنْهُمْ حَتَّى يَخُوضُوا فِي حَدِيثٍ غَيْرِهِ وَإِمَّا يُنْسِيَنَّكَ الشَّيْطَانُ فَلَا تَقْعُدْ بَعْدَ الذِّكْرَى مَعَ الْقَوْمِ الظَّالِمِينَ}

ትርጉሙም (እነዚያን በአንቀጾቻችን የሚገቡትን ባየህ ጊዜ ከእርሱ ሌላ በሆነ ወሬ እስከሚገቡ ድረስ ተዋቸው ፡፡ ሰይጣንም (መከልከልህን) ቢያስረሳህ ከትውስታ በኋላ ከበደለኞች ጋር አትቀመጥ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው በወዳጁ ሃይማኖት ይመራልና አንዳችሁ ማነን እንደሚወዳጅ መገምገም አለበት፡፡) እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (ምእምንን እንጂ ጓደኛ አታድርግ፡፡ መግብህንም አላህን የሚፈራ እንጂ አይብላ፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን ማስዑድ እንድህ ብለዋል፡ ‹ሰዎችን በወዳጆቻቸው ገምግሙ አንድ ሰው የሚደንቀውን እንጂ ወዳጅ አያደርግም፡፡›

እንድህ የሚለው ግጥም ደራሲ እጂጉን ይደነቃል፡

በአንድ ህዝብ ውስጥ የምትኖር ከሆነ ምርጣቸውን ወዳጅ አድርግ፡፡ ዝቅተኛውን አትወዳጅ አብረህ እርኩስ ተኋናለህና፡፡

ስለአንድ ሰው አትጠይቅ ነገር ግን ስለጓደኛው ጠይቅ፡፡ አንድ ሰው ጓደኛውን ይከተላልና፡፡

እዚህ ላይ በመልካም ጓደኝነት አማካይነት ማንነትን ማዋቀር ማህበረሰቡ ሁሉ ሊረባረብበት የሚገባ የጋራ ሃላፊነትን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡ ሁሉም የማህበረሰቡ አባል ይህ ሃላፊነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ ሁላችሁም ስለሚጠብቁት ነገር ሁሉ ይጠየቃል፡፡ አንድ መሪ ስለህዝቡ ተጠያቂ ነው፡፡ አንድ ሰው ቤተሰቡን ይጠብቃል እሱም ስለሚጠብቀው ነገር ይጠያቃል፡፡ ሴትም የባሏን ቤት ትጠብቃለች እሷም ስለምትጠብቀው ተጠያቂ ናት፡፡ አገልጋይ የጌታውን ገንዘብ ይጠብቃል እሱም ስለሚጠብቀው ነገር ይጠየቃል፡፡)

ታዳጊዎችን በማስተማርና በመጠበቅ በቤተሰብ በትምህርት ቤት እንድሁም በትምህርታዊና ምርምራዊ የማህበራዊ ደርጅቶች፣ በማስታወቂያ ተቋማት አማካይነት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ እንድህም ታዳጊዎችን አፍራሽ ከሆነው ከጸንፈኛና አታላይ ቡድኖች አስተሳሰብ ለመጠበቅ የሀገር ፍቅር ለማጽረጽ ሁሉም ወገን መረባረብ ይጠበቅበታል፡፡ ታዳጊዎችን በሚገባው መልኩ መጠበቅ ታላቅ ሃላፊነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَاأَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا قُوا أَنْفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ራሳችሁንና ቤተሰቦቻችሁንም ከእሳት ጠብቁ፡፡) ማለት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ ጠባቂን ከሚጠብቀው ነገር ጠብቋል ወይስ አጥፍቷል በማለት ጠያቂ ነው፡፡ አንድን ሰው ከቤተሰቡም እንኳ ይጠይቀዋል፡፡)
ጌታችን ሆይ መልካም ጓደኛን ስጠን፡፡ የአለማቱ ጌታ ሆይ የመልካም ጓደኝነትን ፍሬ እውን አድርግልን፡፡

# (31)

## የቁርጠኝነት ጥንካሬ የሰለጠኑ ህዝቦች የእድገት መሰረት ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
**سَابِقُوا إِلَى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا كَعَرْضِ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ أُعِدَّتْ لِلَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ ذَلِكَ فَضْلُ اللَّهِ يُؤْتِيهِ مَنْ يَشَاءُ وَاللَّهُ ذُو الْفَضْلِ الْعَظِيمِ}**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነችም ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡ ለእነዚያ በአላህና በመልክተኞቹ ላመኑት ተዘጋጅታለች፡፡ ይህ የአላህ ችሮታ ነው፡፡ ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል፡፡ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
የእስልምና ሃይማኖት የላቁ በሆኑት አስተምህሮዎቹ የሰው ልጅ ቁርጠኛ፣ ታታሪና ለልማት የሚጣጣር እንዲሆን ይገፋፋል፡፡ በአንፃሩም ስንፍናን፣ ዝለትንና ማበላሸትን እንዲርቅ ያሰገነዝባል፡፡ ይህም ተግባር የቀደምት መልክተኞች መልእክት እንደነበረ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል አመልክቷል፡፡
**أَمْ لَمْ يُنَبَّأْ بِمَا فِي صُحُفِ مُوسَى *وَإِبْرَاهِيمَ الَّذِي وَفَّى * أَلَّا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَى *وَأَنْ لَيْسَ لِلْإِنْسَانِ إِلَّا مَا سَعَى *وَأَنَّ سَعْيَهُ سَوْفَ يُرَى *ثُمَّ يُجْزَاهُ الْجَزَاءَ الْأَوْفَى}**

ትርጉሙም (ይልቁንም በዚያ በሙሳ ጽሑፎች ውስጥ ባለው ነገር አልተነገረምን? በዚያም (የታዘዘውን) በፈጸመው በኢብራሂም (ጽሑፎች ውስጥ ባለው አልተነገረምን?) (እርሱም ኃጢያት) ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ነፍስ ኃጢአት አትሸከምም፡፡ ለሰውም ሁሉ የሠራው እንጅ ሌላ የለውም፡፡ ሥራውም ሁሉ ወደ ፊት ይታያል፡፡ ከዚያም ሙሉውን ምንዳ ይመነዳዋል፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የቁርጠኝነት ጥንካሬን ከፍተኛ ደረጃ እንዲህ በማት ገልጸውታል፡ (አላህ ቸር ነው፡፡ ቸርነትንም ይወዳል፡፡ የላቁ ስነ ምግባሮችንም ይወዳል፡፡ እርኩስ ምግባሮችን ደግሞ ይጠላል፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ እንደህ ይላሉ፡ ‹ቁርጠኝነታችሁን (ወኒያችሁን) ዝቅ አታድርጉ፡፡ እኔ ከቁርጠኝነት ማነስ የበለጠ ክብርን ዝቅ የሚያደርግ ነገር አላየሁም፡፡› የጥንት አበውም ‹የቁርጠኝነት ጥንካሬ የአንድ ሰው አእምሮ ምሉእነት ምልክት ነው፡፡› ይሉ ነበር፡፡ አቡ አጠይብ እልሙተነቢ የተሰኘው የግጥም ደራሲ እንድህ በማለቱ ይደነቃል፡፡

ለሙሉነት ችሎታ እያላቸው ከሚያጎድሉ የከፉ ለሰዎች ነውር ምክኒት የሚሆን ነገር አይቸ አላውቅም፡፡

የቁርጠኝነት ጥንካሬ በተለየ መስክ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን አንድ ሰው በህይወቱ በሚያደርጋቸው ሁሉም ተግባራት እውን ሊሆን የሚገባ ተግባር ነው፡፡ የአስልምና መመሪያዎች የሰው ልጆች ወደበዒባዳ በፍጥነት እንዲያመሩና በዚህም መስክ እንዲሽቀዳደሙ ይገፋፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَسارعُوا إِلى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّماواتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ}

ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) በዒባዳ መስክ ለሚጣጣር ሰው መንዳውን የሚያበዛለት መሆኑን እንድህ በማለት ገልጹአል፡

{وَمَنْ أَرَادَ الْآخِرَةَ وَسَعَى لَهَا سَعْيَهَا وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُولَئِكَ كَانَ سَعْيُهُمْ مَشْكُورًا}

ትርጉሙም (መጨረሻይቱንም ዓለም የፈለገ ሰው እርሱ አማኝ ኾኖ ለርሷ (ተገቢ) ሥራዋን የሠራም ሰው እነዚህ ሥራቸው የተመሰገነ ይኾናል፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በሕይወታቸው ሁሉ ጠንካራ ቁርጠኝነት ነበራቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል አዟቸዋል፡

{يَا أَيُّهَا الْمُزَّمِّلُ قُمِ اللَّيْلَ إِلَّا قَلِيلًا نِصْفَهُ أَوِ انْقُصْ مِنْهُ قَلِيلًا *أَوْ زِدْ عَلَيْهِ وَرَتِّلِ الْقُرْآنَ تَرْتِيلًا إِنَّا سَنُلْقِي عَلَيْكَ قَوْلًا ثَقِيلًا}

ትርጉሙም (አንተ ተከናናቢው ሆይ፡፡ ሌሊቱን ሁሉ ጥቂት ሲቀር ቁም፤ (ስገድ)፡፡ ግማሹን (ቁም)፤ ወይም ከርሱ ጥቂትን ቀንስ፡፡ ወይም በእርሱ ላይ ጨምር፡፡

ቁርአንንም በዝግታ ማንበብን አንብብ፡፡ እኛ ባንተ ላይ ከባድ ቃልን እንጥላለንና፡፡) ማት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እግራቸው እስከሚሰነጠቅ ሌሊት ይሰግዱ ነበር፡፡ ለምን እንደዚህ ይሆናሉ ያለፈውንም የሚመጣውንም ወንጀለዎትን አላህ መህረት አድርጎለዎት እያለ ተብለው በተጠየቁ ጊዜም የሰጡት መልስ፡ (እጅጉን አመስጋኝ ባሪያ ልሆን አይገባኝምን? ) የሚል ነበር፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦቻቸውና መላ ህዝቦቻቸውም የተለየ የቁርጠኝነት ጥንካሬ እንድኖራቸው በተለያየ መልኩ ይገፋፉ ነበር፡፡ እንድህም ብለዋል፡ (አላህን በምትለምኑ ጊዜ ፊርደውስን ለምኑት፡፡ እሱ ከበላያ የአላህ ዐርሽ ያለና የጀነት ወንዞች የሚመነጩበት የጀነት ማእከላዊ ወይም የላይኛው ክፍል ነው፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ረቢዓ አብን ካዕብ የተባሉት የነብያችን ባልደረባ እንድህ ይላሉ፡ ‹ብዙውን ጊዜ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር አድር ነበር አንድ ወቅት የውዱ ውሃና የሚያስፈልጉ ነገሮችን አቀረብኩላቸው፡፡ ያን ጊዜ (የምትፈልገውን ነገር ጠይቅኝ) አሉኝ፡፡ እኔም በጀነት ከርሰዎ ጋር መሆንን እፈልጋለሁ አልኩኝ፡፡ እሳቸውም (ከሱ ሌላ ነገር በጠየቅሀኝ) አሉኝ፡፡ እኔም እሱን ብቻ ነው የምፈልገው አልኩኝ፡፡ ያን ጊዜ (እንግዳውስ ስግደት በማብዛት እገዘኝ) አሉኝ፡፡

በዒባዳ የቁርጠኝነት ጥንካሬ ስንል አሳምሮ ማከናውን ማለታችን ሲሆን ይህ ተግባር በአንድ ሰው የማይዋሽ፣ የማይከድ፣ የማያታልልና በከንቱ የሰዎችን ገንዘብ የማይበላ በመሆን በስነ ምግባሩና በአጠቃላይ ጸባዩ ጎልቶ ይታያል፡፡ በዚህም የዒባዳው ተግባር ከአላማው ጋር የተጣጣመ ይሆንና የእምነቱዋና አላማ የሆነው ቅንነት በሰውዬው ላይ እውን ይሆናል፡፡

የቁርጠኝነት ጥንካሬ የሚያስፈልገው ሌላው መስክ ደግሞ ትምህርት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፋይዳው የሰው ልጆችን የሚሸፍን የሆነን እውቅት ይሰጠን ዘንድ አላህን እንድንለምን እንድህ በማለት መክረውናል፡ (ጠቃሚ እውቀትን እንድሰጣችሁ አላህን ለምኑት፡፡ ከማይጠቅም እውቀት እንዲሰውራችሁ በአላህ ተጠበቁ፡፡)

ጠቃሚ የሆነ እውቀት ሀገራት ኃይል የሚያገኙበትና ህዝቦች የሚበለጽጉበት እውነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ያአደጉ አገሮች የእድገታቸው መሰረት አውቀት ሲሆን ወደኋላ የቀሩም ሀገራት የኋላ ቀርነታቸው ምክኒያት በእወቀት ዘርፍ ጠንካራ ጥረት ባለማድረጋቸው ነው፡፡

ባልደረቦችና ተከታዮቻቸውም እውቀትን በማካበት ጠንካራ ቁርጠኝነት ነበራቸው፡ ፡ እነሆ አቡ ሁረይራ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እውቀትን ከማግኘት በወንዝ አትክልትን መትከልም ሆነ በገበያ የመሸጥ መለወጥ ውል አያግደኝም ነበር፡፡ የአላህ መልክተኛ ቃላትን እንዲያስተምሩኝ እከታተል ነበር...› አብደላህ ኢብን ዓባስ የተባሉት ባልደረባ ደግሞ እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹ከአንድ ሰው ዘንድ የነብያችን ሃዲስ መኖሩን በሰማሁ ጊዜ ቀን ላይ አረፍ ባለበት ወቅት ሄድኩ፡፡ እበሩም መጎናጸፊያን ተንተርሸ ጋደም አልኩኝ፡፡ ንፋስም አቧራን በፊቴ ላይ ነሰነሰብኝ፡፡ እሱም ተንስቶ ሲወጣ ባየኝ ጊዜ የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምን አመጣህ?

ብትልክብኝ እኔ አለህበት እመጣ አልነበረም ወይ? አለኝ፡፡ እኔም አይደለም እኔ ነኝ ወዳለህበት መጥቼ ሰለሐዲሱ መጠየቅ ያለበኝ አልኩት፡፡›

የቀደምት ዑለሞች በተለያዩ ዘርፎች እውቀትን በማከማቸትና መልእክቱንም ለቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ የነበራቸው ታታሪነት ይህ ነው አይባልም ነበር፡፡ በዚህም ስማቸውን በታሪክ ማህደር በብርሃናዊ ፊደሎች አስመዝግበው አልፈዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَأَمَّا الزَّبَدُ فَيَذْهَبُ جُفَاءً وَأَمَّا مَا يَنفَعُ النَّاسَ فَيَمْكُثُ فِي الْأَرْضِ}

ትርጉሙም (ኮረፋቱማ ግብስብስ ኾኖ ይጠፋል፡፡ ለሰዎች የሚጠቅመውማ በምድር ላይ ይቆያል፡፡ እንደዚሁ አላህ ምሳሌዎችን ይገልፃል፡፡) ማለት ነው፡፡

ሥራን በሚገባ ማከናውን የቁርጠኝነት ጥንካሬን የሚጠይቅ ሌላው መስክ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ሥራ ከዒባዳ ጋር የተሳሰረ ተግባር መሆኑን እንድህ በማለት አመልክቷል፡

{فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِن فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيراً لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

ትርጉሙም (ሶላቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ሥራውን ለአሳመረ ሰው በዚህች ዓለም መልካም ሕይወት እንድሁም በመጭው ዓለም ዘላቂ ተድላ የሚሰጠው መሆኑንእንድህ በማለት ገልጹአል፡

{مَنْ عَمِلَ صَالِحاً مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَى وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ}

ትርጉሙም (ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፡፡ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلاً}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ለሥራ ክብርነት ከጥንት ጀምሮ ነብያት በሙሉ ሰርተው ይበሉ የነበረ ከመሆኑ የበለጠ ማስረጃ አያስፈልገውም፡፡ አባታችን አደም፣ ኢብራሂምና ሉጥ አርሶ አደሮች ነበሩ፡፡ ነብዩ ኑሕ አናጢ፣ ነብዩ ኢድሪስ ልብስ ሰፊ፣ ነብዩ ሷሊሕ ነጋዴ እንድሁም ነብዩ ዳዉድ ብረት ቀጥቃጭ ነበሩ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَقَدْ آتَيْنَا دَاوُودَ مِنَّا فَضْلًا يَا جِبَالُ أَوِّبِي مَعَهُ وَالطَّيْرَ وَأَلَنَّا لَهُ الْحَدِيدَ * أَنِ اعْمَلْ سَابِغَاتٍ وَقَدِّرْ فِي السَّرْدِ وَاعْمَلُوا صَالِحًا إِنِّي بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}

ትርጉሙም (ለዳውድም ከእኛ የኾነን ችሮታ በእርግጥ ሰጠነው፡፡ (አልንም)፡- «ተራራዎች ሆይ! ከእርሱ ጋር ውዳሴን መላልሱ፡፡ በራሪዎችንም (ገራንለት)፡፡ ብረትንም ለእርሱ አለዘብንለት፡፡» ሰፋፊዎችን ጥሩሮች ሥራ፡፡ በአሠራርዋም መጥን፡፡ መልካምንም ሥራ ሥሩ፡፡ እኔ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና (አልነው)፡፡) ማለት ነው፡፡

ሥራ ክብር የሚኖረው ብጥራት ሲከናወን ብቻ መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አብራርተዋል፡ (አንዳችሁ ሰጠውም ከለከለውም አንድን ሰው ከሚጠይቅ በጀርባው እንጨት ተሸክም ሽጦ ገንዘብ ማግኘት ይሻለዋል፡፡) እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) አንዳችሁ በሥራ በሚሰማራበት ወቅት በጥራት መሰራቱን ይወድለታል፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እያንዳንዱ ሰው ራሱንና ወገኖቹን የሚጠቅምበት መልካም ሥራ እንድኖረው ይገፋፉ ነበር፡፡ ከዚህም አንፃር እንድህ ይላሉ፡ (ሁሉም ሙስሊም ምጽዋት መስጠት ይኖርበታል) ሰዎችም የአላህ ነብይ ሆይ! ከሌለውስ? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (በእጁ ይስራና ራሱን ይጥቀም መጽዋትም ይስጥ) አሉ፡፡ እነሱም ባያገኝስ? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (እገዛ የሚያስፈልገውን ሰው ጉዳይ ያውጣ) አሉ፡፡ አነሱም ባይቻለውስ? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (በመልካም ነገር ይዘዝ ከተንኮልም ይታቀብ ይህ ለሱ ምጽዋቱ ነው) አሉ፡፡ በዚህም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ሥራ ባይኖረውም በሰዎች ላይ ጉዳት ከማድረስ መታቀቡ ከአላህ ዘንድ ምንዳ የሚያገኝበት መልካም ምግባር መሆኑን አስተምረውናል፡፡

ማህበረሰቡን በማገልገል፣ ደካማን በማገዝ፣ የሰውችን ጉዳይ ማውጣትና ድሆችን መርዳት ከፍተኛ ቁርጠኝነት ጥንካሬ ከሚጠይቁ ተግባራት ተቀዳሚው ነው፡፡ አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሄደና እንድህ ሲል ጠየቀ፡ ‹የአላህ መልክተኛ ሆይ? የትኛው ሰው ነው አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጁ የትኛውስ ሥራ ነው አላህ በጣም የሚወደው ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም ከሶወች አላህ ዘንድ ተወዳጁ ያ ከነሱ መካከል ለሰው የሚያበረክተው ጥቅም ከፍተኛ የሆነው ነው፡፡ ከአላህ ዘንድ ተዋዳጁ ሥራ ደግሞ በሙስሊም ልብ ደስታን ማስገባት፣ ወይም ከሱ ጭንቀትን ማስወገድ ወይም ለሱ እዳን መክፈል ወይም ከሱ ረሃብን ማስወገድ ነው፡፡ እኔ የውንድሜን ጉዳይ ለማውጣት ከሱ ጋር መጓዜን በዚህ መስጊድ -በመዲና መስጊድ- አንድ ወር ያህል ለዒባዳ ከመቀመጤ አብልጬ እወደዋለሁ፡፡) ቁጣውን የተቆጣጠረ አላህ ነውሩን ይደብቅለታል፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

*ሁላችንም ለንፎካከርበትና በሱም ጠንከራ ቁርጠኝነት ሊኖረን የሚገባው እጅግ ታላቅ መስክ ደግሞ የሀገር አገልግሎት መስክ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለሀገር ጥቅም ባላቸው መልካም ሥራዎች እንድንፎካከር እንድህ በማለት አዞናል፡*

**{فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ إِلَى اللَّهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا فَيُنَبِّئُكُمْ بِمَا كُنْتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ}**

*ትርጉሙም (በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፡፡ በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡*

*አላህ (ዐ.ወ.) ለሰዎች መልካም ሥራ ለመስራት የሚጥሩ ባሪያዎቹን እንድህ በማለት አሞግሷቸዋል፡*

**{إِنَّهُمْ كَانُوا يُسَارِعُونَ فِي الْخَيْرَاتِ وَيَدْعُونَنَا رَغَباً وَرَهَبًا وَكَانُوا لَنَا خَاشِعِينَ}**

*ትርጉሙም ( እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ፡፡ ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ፡፡) ማለት ነው፡፡*
*የሀገር ግንባታና የማህበረሰቡን ሃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ጠንካራ ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡ መስጊዶችን ማደስ፣ ትምህርት ቤቶችን መስራት፣ ሆስፒታሎችን ማዘጋጀት ዘላቂነት ያላቸው መልካም ሥራዎች በመሆናቸው የተቻለንን ያህል ጥረት ልናደርግባቸው ይገባል፡፡ ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሰባት ነገሮች አንድ ባሪያ ከሞተ በኋላ በመቃብሩም እያለ መንዳቸው ቀጣይ ይሆናል፡ እነሱም ትምህርትን ያስተማረ፣ ወንዝን የቀደደ፣ የውሃ ጉድጓድ የማሰ፣ የቴምርን ዛፍ የተከለ፣ መስጊድን የሠራ፣ ቁርአንን ያወረሰና ከሞተ ቧላ ከአላህ ዘንድ ምህረት የሚለምንለት ልጅ የተወ) የሚሉት ናቸው፡፡*
*ሁላችንንም ያቀፈንና ጸጋውና ትሩፋቱ መላ ነዋሪዎቹን የሚያካትት የሆነውን አገር ለማገልገል መሽቀደዳደማችን እጅጉን ደስ የሚል ነው፡፡ ይህን ተግባር በሚገባ ለማከናወን መታባበር፣ መተጋገዝ፣ መተዛዘን፣ አንድነትና ጥልቅ ግንዛቤ ያስፈልገናል፡፡ ይህን የጋራ አገራችን ለማበልጸግ በኃል፣ በጥረትና በሀሳብ ከማነም አናንስም፡፡ እኛ የስልጣኔና የታሪክ ባለቤቶች ነን፡፡ ቀዳሚነትንና የበላይነትን እውን ለማድረግ ብዙ ውጣ ውረድን እንድሁም ራስን ከቅንጦት ማራቅን የሚጠይቅ መሆኑን ጠንቅቅን ማወቅም ይጠብቅብናል፡፡ ክብር በመከራ የተከበበ ነው፡፡ ጥቅምና ደግ ነገርም በድካምና በጥረት እንጂ አይገኝም፡፡ አቡ ተማም የተባለው የግጥም ደራሴ እንድህ በማለቱ ይደነቃል፡*

ታለቋን እረፍት ተመከትኩኝ የድካምን ድልድይ በማቋረጥ እንጂ የማትገኝ መሆኗንም አየሁኝ፡፡
ጌታችን ሆይ፤ በሱ ቀዳሚነት፣ የበላይነት፣ እድገትና ብልጽግና የምናገኝበትን ታላቅ ቁርጠኝነትን ስጠን፡፡ ሀገራችንና የሌሎች ሀገራትንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# (32)

## ሀገራት የሚገነቡት በሥራ መስዋእትነት በመከፈልና ላብን በማፍሰስ ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَقُلِ اعْمَلُوا فَسَيَرَى اللَّهُ عَمَلَكُمْ وَرَسُولُهُ وَالْمُؤْمِنُونَ وَسَتُرَدُّونَ إِلَى عَالِمِ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ فَيُنَبِّئُكُمْ بِمَا كُنْتُمْ تَعْمَلُونَ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በላቸውም ሥሩ አላህ ሠራችሁን በእርግጥ ያያልና፡፡ መልክተኛውና ምእምናንም (እንደዚሁ ያያሉ)፡፡ ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ወደ ኾነውም (አላህ) በእርግጥ ትመለሳላችሁ፡፡ ትሠሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (አንዳችሁ የሚትክላት ፍል በእጁ ይዞ የቂያማ ቀን ቢደርስበት ሳይተክላት ላለመነሳት አቅም ቢያገኝ ይተከላት) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡፡**
ከእስልምና መሰረታዊ መርሆዎችና ሞገሳዊ አስተምህሮዎቹ መካከል የሀገር ፍቅር፣ ስለሀገር መከላከልና ለሀገር እድገትና ብልጽግና መስራት የሚሉት ይካተታሉ፡፡ የአንድ ሰው የክብር ክብር ለሀገሩ በአለው እውነተኛ ስሜት፣ ልግንባታው በሚያደርገው ጠንካራ ጥረት እንዲሁም ለስልጣኔውና ከፍታው በሚፈጽመው ተግባር ይገለጻል፡፡

ማንኛውም በሳይንስና በስልጣኔ አድገት ያሳየ ህዝብ ሁሉ ልባቸው በሀገራቸው ፍቅር የተሞላና ለሀገርና ለህዝብ የሚጠቅሙ ተግባራትን ለማከናውን ባጭር የታጠቁ ታማኝ ዜጎች በስተጀርባው ይገኛሉ፡፡ ክብር ሀገራችን ግብጽ የዚህ ዓይነቱ እድል እንዲያም የበለጠም ይገባታል፡፡ ይህች አገራችን ለአረቡ ብሎም ለሙስሊሙ ማህበረሰብ የልብ ትርታ፣ ጋሻና ጎራዴ፣ ሽብርና የተለያዩ ተግዳሮቶችን ለመቋቋም ጠንካራ መከታ ነች፡፡ በመሆኑም ደህንነቷን ለማስከበር፣ ለተሃዲሶዋና ለእድገቷ መታተር ሃይማኖታዊና ሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ ይህች ሀገራችን የስልጣኔ አንቀልባ፣ የመለኮታዊ ትንቢቶች መስፈሪያ ነች፡፡ ይህች አገራችን በቅዱስ ቁርአን ስሟ ከሰላምና ደህንነት ጋር ተቆራኝቶ የተወሳ አገር ስትሆን ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ (ሱ. ወ.) በስይዲና ዩሱፍ (ዐ.ሰ.) ልሳን አንድህ ይላል፡

﴿ادْخُلُوا مِصْرَ إِنْ شَاءَ اللَّهُ آمِنِينَ.

ትርጉሙም (በአላህም ፈቃድ ጥብቆች ስትሆኑ ምስርን ግቡ አላቸው) ማለት ነው፡፡ የሚከተለውን ግጥም የገጠሙት የሰላህ ኢልዲን አሰፈዲ ቃል የአላህ ስጦታ ነው፡፡ መድሯንና ከፍለሀገራቷን እንዲሁም የተላያየ ጎሳና ዜግነት ያለቸውን ሰዎቹዋን የተመለከተ ማነው
በዚህ መልክ የተወቀረችውን ግብጽንና ነዋሪዎቹዋን ያላየ ይህችን አለማችንን እንዲሆም ሰዎችን አላየም፡፡

እድገት፣ ግንባታና ቀዳሚነት ለአንድ ህዝብ የአሸናፊነት፣ ክብርና የሌሎች አክብሮት ዋስትና መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ይሁን እንጂ አንድ አገር በቃል፣ በማለምና በምኞት ብቻ ሊገነባ አይችልም፡፡ በመሆኑም ድካም፣ ላብ፣ ጥረትና መስዋእትነትን እንዲሁም የግንባታ አላባዎች፣ የእድገትና የስልጣኔ መሰረቶችን ማካበትን ይጠይቃል፡፡

ከእድገትና ስልጣኔ መሰረቶች በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ሌላው ደግሞ ስለተደቀኑ ተግዳሮቶች ሙሉ ግንዛቤ መኖር የሚለው ጉዳይ ይሆናል፡፡ ስለሀገር እሴት፣ ስለተደቀኑባት ተግዳሮቶች፣ በዙሪያዋ ስላሉት አደጋዎች የሚኖረው ግንዛቤ ቀድሞ የተደቀኑ ተግዳሮቶችን መጠን መገንዘብን የሚጠይቅ ጉዳ ነው፡፡ የእነዚህን ተግዳሮቶች ምንነት ሳናውቅና ስለነሱም ሙሉ ግንዛቤ ሳይኖረን የተሳካ ወይም ፍቱን የሚባል መፍትሄ ልናስቀምጥ ከቶ አንችልም፡፡

የሀገር እሴት ግንዛቤ፣ የብሄራዊ መንግስት ሃጋዊነት፣ የሀገርን አይበገሬነት መደገፍ፣ ለክብሯና አድገቷ በትጋት መሰራት ጠንካራ አገርን የመገንባት ዋልታዎች፣ የሀገር ታማኝነት፣ ሀብቷንና ስንዝርም አንኳን ብተሆን ለምለም አፈሯን የመጠበቅ ምሰሶዎች መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡

እንደዚሁም ስለሀገር አስፈላጊነት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ቀድሞ አሸባሪና ጸንፈኛ ብዲኖች በህዝቡ ልብ እንሰርጹ የሚሞክሩትን የተሳሳቱ አስተምህሮዎችን ማስተካከልን ይጠይቃል፡፡ እንደሚታወሰው እነዚህ ቡዲኖች የገነቡት ፍልስፍና ከሌሎች ህዝቦች፣ መሪዎቻውና ተጠያቂዎቻቸው ጋር ያለውን ግንኙት መቆረጥንና አመኔታ ማሳጣትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህውም የሃይማኖት አስተምህሮዎች ፍትሃዊ መሪን እንዲናከብር የሰነዘረውን ጥሪ በመዘንጋት ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል

(የሸበተ ሙስሊም አዛውንትን፣ ያለምንም ማጋነንና እሱን ቸል ያለማለት ቁርኣን የተሸከመን ‹ብቃሉ ያዘን›ና ፍትሃዊ ገዢን ማክበር አላህን ከማሞገስ ይካተታል)፡፡

ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ (ሱ.ወ.) ፍትሃዊ ገዢ የእሱ ጥላ እንጂ ምንም ጥላ በሌለበት በእለተ ትንሳኤ ቀን በአርሹ ጥላ ስር ከሚያደርጋቸው ሰባት ወገኖች አንዱ እንዲሆን አደርጓል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ (ሰባት ወገኖች የሱ ጥላ እንጂ ሌላ ጥላ በሌለበት ቀን አላህ ጥላ ያደርግላቸዋል...) ከዚያም ከነሱ በቀደምትነት ፍትሃዊ ገዢን ጠቅሰዋል፡፡

ከአገር ግንባታ መሰረቶችና አላባዎች በዋናነት የሚጠቀሰው ሌላው ደግሞ ለሀገር መስዋእትነት መክፈል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ እወነተኛ ሀገራዊነት የምናነግበው መፈክርና በየጊዜው የምናሰማው ዐረፍተ ነገር ብቻ አይደልም፡፡ ሀገራዊነት ማለት የሕይወት ስርአት፣ በሀገር ትርታና በተደቀኑበት ተግዳሮቶች፣ የሚሰማን ስሜት፣ ለህመሙ መታመማችን፣ ምኞቱ ሲሳካ መደሰታችን፣ ለሱም መስዋእትነት ለመክፈል ምንግዜም ዝግጁ መሆናችን ነው፡፡

ስለሀገር መከላከል፣ ሀገርን መጠበቅና ስለእሱም መስዋእትነት መክፈል ህጋዊ ፍላጎትና በምድሩ ላይ የሚኖሩ በሰማዩ የሚጠለሉ ሁሉ ሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ የሀገር ፍቅር ታዲያ የሚሰማን ስሜት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ወደስራ እንዲሁም ለግለሰቡና ለማህበረሰቡ ጥቅም ወዳለው መልካም ምግባር መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ሀገር የማይበገር ጠንካራ ሆኖ እንዲኖር መስዋእትነት መክፈል ግድ ይሆናል፡፡ የአንድ አገር ዜግነት ዜጎቹ ሊኮሩበት፣ ለደህንነቱም በጋራ ሊሰሩለት ይገባል፡፡ የአገር መረጋጋት ስለሱ የፈጠረንን የዚህችን አለም ግንባታን እውን ለማደረግ፣ ሃይማኖትን ከፍ ለማድረግ፣ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በእስልማና እምነት ጂሃድ የተደነገገው ስለአገር ለመከላከልና በደለን ለመግታት እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም፡፡ በመሆኑም አላህ (ዐ.ወ) የነዚያን ሀገረን ለመከላከል የተዋደቁትን ወገኖች ደረጃ እንዲህ በማለት ከፍ አድርጎታል፡፡

: ﴿إِنَّ اللَّهَ اشْتَرَىٰ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ أَنفُسَهُمْ وَأَمْوَالَهُم بِأَنَّ لَهُمُ الْجَنَّةَ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ وَعْدًا عَلَيْهِ حَقًّا فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنجِيلِ وَالْقُرْآن.

ትርጉሙም (አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለነሱ ብቻ ያላቸው በመሆን ገዛቸው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፡፡ ይገድላሉም ይገደላሉም በተውራት፣ በኢንጂልና በቁርኣንም (የተነገረውን) ተስፋ በርሱ ላይ አረጋገጠ) ማለት ነው፡፡

ለሀገርና ስልጣኔ ግንባታ ዋና ከሆኑት መሰረቶችና አላባዎች ሌላው ደግሞ ሥራን በትጋትና በጥራት ማከናወን የሚለው ጉዳ ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት የሥራን እሴት ከፍ ከማድረጉም ሌላ ከኢባዳ ክፍሎች አንዱ መሆኑን ብሎም ከኢባዳዎች ታላቁን ቦታ የያዘ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በአላህ መንገድ ከመታገል ድረጃ የሚመደብ መሆኑን እንዲህ በማለት ጠቅሰዋል ሲሉ ካዕብ ኢብኑ ዑጅራህ የተባሉ የነብያችን ባልደረባ ዘግበዋል፡፡ አንድ ቀን አንድ ሰውዬ በነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አጠገብ ሲያልፍ (ከነሱ አላህ ይውደድና) ባልደረቦች በትጋቱና በእንቅስቃሴው ተደነቁ

እንዲህም አሉ ያላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህ ትግባሩ በአላህ መንገድ በሆነ ኖሮስ ያን ጊዜ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡ (ትጋቱ ህፃናት ልጆቹን ለመመገብ እንደሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ ትጋቱም አረጋዊያን አባትና እናቱን ለመመገብ ከሆነም በአላህ መነገድ ነው፡፡ ራሱን ጥብቅና ነጹህ ለማደረገም የሚተጋ ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ ነግር ግን ለይዩለኝና ይስሙልኝ ወይም ለኩራት የሚተጋ ከሆነ ትጋቱ በሰይጣን መንገድ ነው)

መለኮታዊ ሃይማኖት ሀገርን በጋራ ጥረትና ላብን በማፍሰስ መገንባትን እንዲሁም የሚያስፈልጉንን ነገሮች ለማምረት ጠንካራ ስራን ከኛ ይጠብቃሉ፡፡ በተለይም ደግሞ ሃይማኖታችን የሥራና የጥራት ሃይማኖት በመሆኑ አላህ (ዐ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

{الَّذِي خَلَقَ الْمَوْتَ وَالْحَيَاةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا وَهُوَ الْعَزِيزُ الْغَفُورُ }

ትርጉሙም (ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፡፡ እሱም አሸናፊው መሀሪው ነው ) ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا نُودِيَ لِلصَّلَاةِ مِنْ يَوْمِ الْجُمُعَةِ فَاسْعَوْا إِلَى ذِكْرِ اللَّهِ وَذَرُوا الْبَيْعَ ذَلِكُمْ خَيْرٌ لَكُمْ إِنْ كُنْتُمْ تَعْلَمُونَ * فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانْتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِنْ فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيرًا لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ * وَإِذَا رَأَوْا تِجَارَةً أَوْ لَهْوًا انْفَضُّوا إِلَيْهَا وَتَرَكُوكَ قَائِمًا قُلْ مَا عِنْدَ اللَّهِ خَيْرٌ مِنَ اللَّهْوِ وَمِنَ التِّجَارَةِ وَاللَّهُ خَيْرُ الرَّازِقِينَ}

ትርጉሙም ( እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ሂዱ መሸጥንም ተው፡፡ ይሃችሁ ይምታውቁ ብትሆኑ ለናንተ በጣም የተሻለ ነው፡፡ ስግደቱም በተፈጸመ ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታን ፈልጉ፡፡ አላህን በብዛት አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡ ንግድን ወይም ዛዛታን ባዩ ጊዜም ቆመህ የተውህ ሲሆኑ ወደሷ ይበተናሉ፡፡ አላህ ዘንድ ያለው ዋጋ ከዛዛታም ከንግድም በላጭ ነው፡፡ አላህም ከሰጭዎቹ ሁሉ ይበልጥ ሲሳይን ሰጭ ነው በላቸው ) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንዲህ ይላሉ (አንድ ሰው በእጁ ከሰራው ስራ ውጤት የበለጠ የሚጣፍጥን ምግብ ሊመገብ ከቶ አይችልም የአላህ መልእክተኛ ዳውድ (ዐ.ሰ.) በእጃቸው ከሰሩት ስራ ወጤት ነበር የሚመገቡት)፡፡

እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የሚገባ ነገር አለ፣ እሱም እስልምና ሃይማኖታችን ከኛ የሚጠብቅብን እዲሁ በዘልማድ ስራን ማከናውንን ብቻ ሳሆን ትጋትና ጥራትንም ጭምር ነው የሚለው ጉዳ ነው፡፡ ግኘነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

{إِنَّا لَا نُضِيعُ أَجْرَ مَنْ أَحْسَنَ عَمَلًا}

ትርጉሙም (አላህ የበጎ ስራዎችን ምንዳ አያጠፋም) ማለት ነው፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አላህ አንዳችሁ ሥራ በሚሰራበት ወቅት በጥራት እንዲያከናውነው ይወዳል)

ከሀገርና ስልጣኔ ግንባታ መሰረቶች ሌላው ደግሞ እውቀትና መልካም አስተዳደር ነው፡፡ ግንባታ በዝንባሌ ብቻ የሚከናውን ስራ ሳሆን እውቀት፣ ልምድ፣ ስልጠናና ልዩ ሞያን ይጠይቃል፡፡ ቅዱስ ቁርኣንና የነብያችንን ሓዲሶች ስንመለከት አንድን ነገር ለማከናውን ልምድ፣ ብቃትና ታማንነት የሚጠይቅ መሆኑን እንደሚያረጋግጡ እናገኛለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በንብዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) ልሳን እንዲህ ይላል፡

اجْعَلْنِي عَلَى خَزَائِنِ الأَرْضِ إِنِّي حَفِيظٌ عَلِيمٌ

ትርጉሙም (በምድር ግምጃ ቤቶች ላይ (ሹም) አድርገኝ እኔ ጠባቂ አዋቂ ነኝና አሉ) ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በነብዩ ሹዓይብ ሴት ልጅ ልሳን እንዲህ ይላል፡፡

يَا أَبَتِ اسْتَأْجِرْهُ إِنَّ خَيْرَ مَنِ اسْتَأْجَرْتَ الْقَوِيُّ الأَمِينُ.

ትርጉሙም (አባቴ ሆይ! ቅጠረው ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ ብርቱ ታማኙ ነውና አለች) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ብቃት ለሌለው ሰው ኃላፊነት መስጠትን አስጠንቅቀዋል፡፡ ይህ የሚደረግ ከሆነ እሱ የትንሳኤ ቀን መቃረብ ምልክት መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ እንዲህም ይላሉ (አንድ ነገር ተገቢ ላልሆነ ሰው የሚሰጥ ከሆነ ያን ጊዜ የቂያመን ቀን ጠብቅ) በማንኛውም ዘርፍ አንድን ነገር ለመፈጸም ተገቢ ሰው የምንለው ብቃትና ታማኝነት በአንድ ላይ ያሉትን ሰው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለባልደረቦቻቸውና ስራተኞቻቸው ኃላፊነትን ሲያከፋፍሉ እውቀትና ብቃትን እንዲሁም የሃላፊነት መወጣትን አቅም መሰረት በማድረግ ነበር፡፡ እንዲሁ በከንቱ አክብሮት ወይንም በዝምድና ስልጣን አይሰጡም ነበር፡፡አቡ ዘር የተባሉ ባልደረባቸው (ከሳቸው አላህ ይውደድና) እንዲህ ሲሉ አውርተዋል፡ ከእለታት አንድ ቀን ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አንድ ኃላፊነት አትሰጡኝምን አልኳቸው በእጃቸው ትከሻየን መታ አደረጉኝና እንዲህ አሉ( አባዘር ሆይ! አንተ ደካማ ነህ እሱ (ኃላፊነት) ደግሞ በአንድ ሰው ላይ የሚጣል አደራ ነው፡፡ እሱም በእለተ ቂያመ ደንቡን ጠብቆ የፈጸመውና ግዴታውን የተወጣ ካልሆነ ውርደትና ጸጸት ይሆናል)፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አብደራህማን ኢብን ሰሙራህ ለተባሉት ባልደረባቸው እንዲህ ብለዋቻዋል፡ (አብደራህ ማን ሆይ! ገዢነትን አትጠይቅ፡፡ አንተ ጠይቀህ የምታገኘው ከሆነ ማንም ሊያግዝህ ፈቃደኛ አይሆንም ፡፡ ሳትጠይቅ ከተሰጠህ ደግሞ አጋዢህ ይበዛል)

ይህን ቃሌን እንደሰማችሁት ሁሉ ተናግሪያለሁ ለኔና ለናንተም ከአላህ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ብቸኛ አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን

ሰይዲና ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! እዝነትህን፣ሰላምህንና በረከትህን በሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው አውርድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች፡**

ከሀገራት ግንባታ መሰረቶችና ዋልታዎች እጅጉን ዋናው ደግሞ የስነ መግባርና ስርአትን እሴቶች ከፍ ማድረግ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ማህበረሰብም ሆነ ስልጣኔ ያለስነ ምግባር የሚዋቀር ከሆነ የውድቀቱ ምንስኤዎች በግንባታውና በህልውናው መሰረት ውስጥ እንዲሆን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የሚከተለውን ቃል የተናገረው ሰው ቃል የአላህ ተሰጥኦ ነው፡፡

እንድ ህዝብ የስነ ምግባር እክል ካጋጠመው ለቅሶ ይዘጋጅለት ሙሾም ይወረድለት፡፡ የሌላወም ቃል እንደዚሁ የፈጣሪ ተሰጥኦ ነው፡፡

የአንድ ማህበረሰብ ህልውናው የሚኖረው መልካም መግባሩ አስካለ ነው፡፡ መልካም ስነ መግባሩ ከሌለ እሱም የለም፡፡

መልካም ስነ ምግባር በእስልምና እምነት ዘንድ ታላቁ ቦታ አለው፡፡ የአንድ ሙስሊም የእምነት ደረጃ ከፍ የሚለው በመልካም ስነ መግባር ነው፡፡ በአንዱና ፈራጁ ጌታ በፈጣሪ ፊት ሲቆምም የስራው ሚዛን ክብደት የሚኖረው እንደዚሁ በመልካም ስነ መግባር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (በእለተ ቂያማ በአንድ ምእምን ስራ ሚዛን ከመልካም ስራው ከባደ ነገር የለም፡ አላህም እርኩስ የሆነ ድንበር አላፊን ይጠላል) አንዲሁም በብዛት ጀነት ስለሚስገቡ ነገሮች ተጠይቀው ነብያችን እንዲህ ሲሉ መልሰዋል (አላህን መፍራትና መልካም መግባር)፡፡

ነብየችን (ሶ.ዐ.ወ.) መልካም ምግባር የእምነት ምሉእነትና መጓደል መለኪያ መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡ (ከምእምናን እምነቱ ምሉእ የሆነው በመልካም መግባር የተሻለው ነው)፡፡ እንዲሁም እነደዚህ ይላሉ (በየትኛውም ቦታ ብትሆን አላህን ፍራ፣ መጥፎ ስራ ከሰራህ ወዲያውኑ መልካም ስራ ለመስራት ጥረት አድርግ መጥፎውን ያብሰዋልና የሰዎች ጋር ግንኙነትህ በመልካም ስነ ምግባር የታነጸ ይሁን)

መልካም ምግባር አንድ ሰው እንደርህራሄ፣ ለሌሎች መልካምን መውደድ፣ ለኔ ለኔ ከማለትና ከራስ ወዳድነት በመራቅ ለሰዎች ጥቅም መትጋት እንዲሁም ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም መረጋገጥ ትግል ባሉ መልካም ባህሪዎች እንዲታነጽ ያደርጋል፡፡ ሃይማኖታችን ሌላውን በማስቀደምና ስጦታን በመውደድ እንጂ ለኔ ለኔ በማለት፣ በጨቅነትና በራስ ወዳድነት አልተመሰረተም፡፡

ሌላው የሀገራትና የስልጣኔ ግንባታ መሰረት ደግሞ ፍትህ ነው፡፡ ጠንካራ ሀገራት የሚገነቡት ሰዎችን ሁሉ አንዱን ከሌላው ያለመለየት በሙብትና ግዴታ እኩል በሚያደርገው ፍትህ መሆን አለበት፡፡ ይህም ተግባር የአላህ (ሱ.ወ.) ትእዛዝ ነው፡፡ በተከበረው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፡፡

إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَى وَيَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَالْبَغْيِ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ}

ትርጉሙም (አላህ በማስተካከል በማሳመረም ለዝምድና ባለ ቤት በመሰጠትም ያዛል ከአስከፊም (ከማንዘር) ከሚጠላም ነገር ሁሉ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገንዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል) ማለት ነው፡፡ ጥንታዊያን እንደዚህ ብለዋል፡፡ አላህ (ዐ.ወ) ከሃዲም እንኳን ቢሆን ለፍትሃዊ መንግስት ድልን ይሰጣል፡፡ ለፈጣሪ ተገዢም እንኳን ቢሆን ፍትህ ለጓደለ መንግስት ድልን አይሰጥም፡፡ ምክኒያቱም በእውነት ለፈጣሪ ተገዢ ቢሆን ኖሮ በደልን ባልወደደ ነበርና፡፡ በመሆኑም እሁንም ጥንታዊያን እንደዚህ ብለዋል፡ ሀገራት ከህደት ከፍትህ ጋር ካቀላቀሉ እድሜ ይኖረቸዋል፡፡ ለፈጣሪ ተገዢነትና በደልን ካቀላቀሉ ግን እድሜ አይኖራቸውም፡፡ ምክኒያቱም የኒዘህ አገራት ሃይማኖት በዚያን ጊዜ የተገዢነትን አስተምህሮ፣ በእውነትና በፍትህ፣ በማንኛውም መልኩና ቅርጹ በደልንና ወሰን መተላለፍን ባለመቀበል የታነጸውን የላቀ ይዞታውን የዘነጋ ቅርጽን ብቻ መሰረት ያደረገ ይሆናልና፡፡
ጌታዬ ሆይ! በአገራችን ሰላምን አስፍንልን፡፡ መሪዎቻችንና ገዢዎቻችን ቅኑን መንገድ ምራቸው፡፡ አገራችንን ከሴረኞች ተንኮልና ከብለሹዎች አበላሽነት ጠብቅልን፡፡

(33)

## ለአንድ አገር ውህደት የኃይል ምንጩ ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ፡፡ አትለያዩም፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የተላኩበት መልእክት ለአንድነትና መፈቃቀር መስመር የሚየመቻች ሲሆን መለያትንና መነታረክን ይከለክላል፡፡ ይህ መልክት የተበታተኑና

የተላያዩ ዓረቦችን አሰባስቦ አንድ ማህበረሰብ አድርጓቸዋል፡፡ በእምነት ወንደም ተማማችነትም አስተሳስሯቸዋል፡፡ ልቦቻቸውንም በመላመድ ገመድ አያይዟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ}

ትርጉሙም ((በእርግጥም)ምእመናኖች ወንድማመኞች ናቸው፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِهِمْ لَوْ أَنفَقْتَ مَا فِي الأَرْضِ جَمِيعًا مَا أَلَّفْتَ بَيْنَ قُلُوبِهِمْ وَلَكِنَّ اللَّهَ أَلَّفَ بَيْنَهُمْ إِنَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ}

ትርጉሙም (በልቦቻቸውም መካከል ያስማማ ነው፡፡ በምድር ያለውን ሁሉ (ሀብት) በለገስክ ኖሮ በልቦቻቸው መካከል ባላስማማህ ነበር፡፡ ግን አላህ በመካከላቸው አስማማ፡፡ እርሱ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድንዋደድ፣ እንድንተዛዘንና እንድተጋገዝ እንድህ በማለት አመልከተዋል፡ (በመዋደዳቸው፣ በተዛዘናቸውና በመተጋገዛቸው የምእምናን ምሳሌ ከሱ አንድ ክፍል ህመም ሲሰማው ሌሎችም አካላት እንቅልፍ በማጣትና በስቃይ እንዲሚጋሩት አንድ አካል ነው)፡፡

ይሁን እንጂ ይህ መተጋገዝ ከሙሰሊሞች መካከል ብቻ እንዲፈጸም የተወሰነ አይደለም፡፡ እሱ ሁሉንም የሰው ልጅ ያከተተ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) ከነብያትና በአምነት ከማይከተሏቸው ሰዎች መካከል ያለውን የሰብእ ወንድም ተማማችነትም እንድህ በማለት አውስቷል፡

{وَإِلَى عَادٍ أَخَاهُمْ هُودًا}

ትርጉሙም (ወደ ዓድም ወንድማቸውን ሁድን ላክን፡፡) ማለት ነው፡፡
እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَإِلَى ثَمُودَ أَخَاهُمْ صَالِحًا}

ትርጉሙም (ወደ ሰሙድም ወንድማቸውን ሷሊሕን ላክን፡፡) ማለት ነው፡፡

አሁንም እንድህ ይላል፡

{وَإِلَى مَدْيَنَ أَخَاهُمْ شُعَيْبًا}

ትርጉሙም (ወደ መድየንም ወንድማቸውን ሹዓይብን ላክን፡፡) ማለት ነው፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) ያለፉ ነብያትን ታሪክ ከዘረዘረ በኋላም እንድህ ይላል፡

{وَإِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاتَّقُونِ}

ትርጉሙም (ይህችም (በአንድ አምላክ የማመን ሕግጋት) አንድ መንገድ ስትኾን ሃይማኖታችሁ ናት፡፡ እኔም ጌታችሁ ነኝና ፍሩኝ፡፡) ማለት ነው
እንድሁም እንድህ ይላል፡

{إِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاعْبُدُونِ}

ትርጉሙም (ይህችም (በአንድ አምላክ የማመን ሕግጋት) አንድ መንገድ ስትኾን ሃይማኖታችሁ ናት፡፡ እኔም ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ፡፡) ማለት ነው፡፡
ኢማሙ አልበገዊ የተባሉት የቅዱስ ቁርአን ተንታኝ እንድህ ብለዋል፡ ‹አላህ (ሱ.ወ.) ሁሉንም ነብያት የላከው ቅን ሃይማኖትን፣ መተጋገዝንና እንድነትን እንዲያጠናክሩ እንድሁም ከመበታተንና በአቋምም ከመለያየት እንዲታቀቡ እንዲያዙ ነው፡፡›
የእስልምና እምነት ወደአንድነትና ወደመሰባሰብ መጥራቱና ከመበታተንና ከራስ ወዳድነት ማስጠንቀቁ ከሀገር ኃይል ጥንካሬና ከማህበረሰቡ ደህንነት ጥበቃ መሰረቶች ዋነኛው መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡
ምክኒያቱም አንድ ግለሰብ ምንም ብርቱ ቢሆንም እንኳ በደካማ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር ከሆነ ምንጊዜም ደከማ ይሆናልና፡፡ በአንጻሩም አንድ ግለሰብ በጠንካራ ማህበረሰብ መካከል የሚኖር ከሆነ የኃይል ምንጩ ማህበረሰቡ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የእስልምና እምነት የዜግነት እሴት ጠንካራነትን ያረጋግጣል፡፡ ሀገርም በውስጡ ለሚኖሩ ዜጎች በሙሉ መጠለያ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ምክኒያቱም የሀገር ጥንካሬ ይጠበቅ ዘንድ ከነዋሪዎቹ መካከል በሃማኖት፣ በቀለምና በጾታ መለያየት አለመኖር አስፈላጊ ነውና፡፡ ከነጭና ጥቁር መካከል ብልጫ አይኖርም አላህን በመፍራትና በመልካም ስራ ብቻ ቢሆን እንጂ፡፡
ስለሆነም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከአይሁዶች ጋር ያጸደቁት የመዲና ውል ለአይሁዳዊያን ነጻነት፣ ደህንነትና ሰላም ከሙስሊሞች ጋር እኩል ሰጥቷል፡፡ እንድሁም ከሙስሊሞች ጋር ከተመዋን በጋራ የመከላከል ግዴታ እንዳለባቸውም ደንግገዋል፡፡ ይህም ታዲያ እስልምና የሀገር ግዴታቸውንና መብታቸውን አውቀው የሚኖሩ ከሆነ የመላ ነዋሪዎች መጠለያ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
የእስልምና እምነት የጋራ ሥራ መንፈስ እሴትንም ከፍ አድርጓል፡፡ ተባብሮ መስራትንና የጋራ ጥረትን እንድሁም የተላያየ አቋም ከመያዝ መራቅን የእምነቱ ግዴታዎች አድርጓል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا}

ትርጉሙም (የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ፡፡ አትለያዩም፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ አላህ (ዐ.ወ.) ከናንተ ሦስት ነገሮችን ይወዳል፡፡ ሦስት ነገሮችንም ይጠላል፡፡ በሱ ምንንም ሳታጋሩ እሱን መገዛታችሁን፣ ሁላችሁም በአለህ ገመድ መጠበቃችሁንና አለመለያየታችሁን ይወድላችኋል፡፡ አሉባልታን፣ ጥያቄ ማብዛትንና ገንዘብ ያላግባብ ማጥፋትን ከናንተ ይጠላል፡፡) ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ማህበረሰቡን በማዋሃድ፣ በማስተሳሰርና በመተጋገዝ ዘርፍ ባልደረቦቻቸውን ሲያስተምሩ እንድህ ይላሉ፡ (ምእምን ለምእምን ከፊሉ ከከፊሉን እንሚያጠነክር ካብ ነው አሉና ጣቶቻቸውን በማወሳሰብ አመለከቱ)፡፡

ሀገረን በመጠበቅና የማህብሰቡን ደህንነት በማስከበር ዘርፍ ውህደት የሚጫወተውን ሚና አስመልክቶ ቅዱስ ቁርአን በርካታ ምሳሌዎችን ጠቅሷል፡፡ ከነሱም መካከል ሰይዲና ዩሱፍ የነደፉት እቅድ ለማሳካት ያደረጉት የህዝቦች አንድነት በመጀመሪያ ይጠቀሳል፡፡ በእቅዱ መሰረት የተፈጸመው የጋራ ሥራ ብልጸግናን እውን በማድረግ ሀገርን በማስከበርና ኢኮኖሚውን በማጠንከር ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይህን ጉዳይ አላህ (ሱ.ወ.) በሰይዲና የሱፍ ልሳን በቅዱስ ቁርአን እንድህ በማለት አመልክቶታል፡

**{قَالَ تَزْرَعُونَ سَبْعَ سِنِينَ دَأَبًا فَمَا حَصَدتُّمْ فَذَرُوهُ فِي سُنبُلِهِ إِلَّا قَلِيلًا مِّمَّا تَأْكُلُونَ * ثُمَّ يَأْتِي مِن بَعْدِ ذَٰلِكَ سَبْعٌ شِدَادٌ يَأْكُلْنَ مَا قَدَّمْتُمْ لَهُنَّ إِلَّا قَلِيلًا مِّمَّا تُحْصِنُونَ * ثُمَّ يَأْتِي مِن بَعْدِ ذَٰلِكَ عَامٌ فِيهِ يُغَاثُ النَّاسُ وَفِيهِ يَعْصِرُونَ} .**

ትርጉሙም ((እርሱም) አለ፡- «ሰባትን የተከታተሉ ዓመታት ትዘራላችሁ፡፡ ያጨዳችሁትንም ሁሉ ከምትበሉት ጥቂት በስተቀር በዘለላው ውስጥ ተዉት፡፡ «ከዚያም ከእነዚያ በኋላ ካደለባችሁት ጥቂት ሲቀር ለእነሱ ያደለባችሁትን ሁሉ የሚበሉ ሰባት የችግር ዓመታት ይመጣሉ፡፡ «ከዚያም ከእነዚያ በኋላ ሰዎቹ በርሱ የሚዘነቡበት በርሱም (ወይንን) የሚጨምቁበት ዓመት ይመጣል፡፡») ማለት ነው፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ሰዎች በአንድ መስመር ተሰልፈው እንዲሰሩ የሚያግዝን ነገር ሁሉ ይደግፋል፡፡ በመሆኑም መተዛዘን፣ ገራገርነትና ለዘብተኝነት እንዲስፋፋ ጥረት ያደርጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ اللَّهِ لِنتَ لَهُمْ وَلَوْ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ الْقَلْبِ لَانفَضُّوا مِنْ حَوْلِكَ فَاعْفُ عَنْهُمْ وَاسْتَغْفِرْ لَهُمْ وَشَاوِرْهُمْ فِي الْأَمْرِ فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُتَوَكِّلِينَ}**

ትርጉሙም (ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብከላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡ ከእነርሱም ይቅር በል፡፡ ለእነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው፡፡ በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡ ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ፡፡ አላህ በርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡

መተዛዘን ለዘብተኝነትና መተጋገዝ ለአንድነትና ለልቦች መቀራረብ ታላቅ ሚና አላቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሃይማኖት ገር ነው፡፡ አንድም ሰው ሃማኖትን አይታገለውም የሚያሸንፈው ቢሆን እንጂ፡፡ ትክክለኛውን ነገር ፈጽሙ ካልተቻለ ደግሞ ለሱ የቀረበውን ሥሩ፡፡ በዚህም ሆነ በዚያም ታላቅ ምንዳ እንደምታገኙ እወቁ፡፡ ማለዳ በመነሳት፣ ማታም፣ በጥቂቱም ቢሆን በሌሊት ኢባዳን በማድረስ ታገዙ፡፡)

አሁንም እምነቱ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በእምነት ቢለያዩም እንኳ በመቀራረብና በሰላም እንድኖሩ ይገፋፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَقُولُوا لِلنَّاس حُسْنًا}

ትርጉሙም (ለሰዎችም መልካምን ነገር ተናገሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

{لَّا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ}

ትርጉሙም (ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር የነበራቸው ግንኙነት በዚህ መልኩ ነበር፡፡ በመሆኑም ከነሱ ስጦታቸውን ይቀበሉ፣ ህመምተኛቸውን ይጠይቁ ነበር፡፡ ይህውም የእስልምናን ገራገርነትና የመቻቻል ገጽታ ለማሳየት የማህበረሰቡን አንድነትና ትስስሩን ለማጠናከር ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት የአንድ አገር ልጆች ተቀዳሚ ጉዳዮችን በመገንዘብ ሁሉም በየ ሥራ ዘርፉ ለሀገር ደህንነት መስራት አለበት፡፡ ሃኪሞች፣ የህግ ባለሞያዎች፣ መሃንዲሶች፣ ገበሬዎችና መምህራን ሃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው፡፡ የስጦታና የጥረት መንፈስን በማስፋፋት ይህ በጉልበቱ ያም በገንዘቡ ያኛውም በትምህርቱ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህ ሁሉ የሃይማኖታችን አካል መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አመልክቷል፡

{هُوَ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ ذَلُولًا فَامْشُوا فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُوا مِن رِّزْقِهِ وَإِلَيْهِ النُّشُورُ }

ትርጉሙም (እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፡፡ በጋራዎችዋና በመንገዶችዋም ኺዱ፡፡፡ ከሲሳዩም ብሉ፡፡ (ኋላ) መመለሻውም ወደእርሱ ብቻ ነው፡፡ ) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ብሏል

{فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِن فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيرًا لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ} .

ትርጉሙም (ሶለቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁኝ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ታሪክን ወደኋላ መለስ ብሎ የሚመራመር ሰው መለያየትና አለምግባባት የማንኛውም ማህበረሰብ ሽንፈትና ድክመት መሆኑን በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ይህንም አደጋ ቅዱስ ቁርኣን እንድህ በማለት አስጠንቅቆናል፡

**{وَلَا تَكُونُوا كَالَّذِينَ تَفَرَّقُوا وَاخْتَلَفُوا مِنْ بَعْدِ مَا جَاءَهُمُ الْبَيِّنَاتُ وَأُولَئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ عَظِيمٌ}**

ትርጉሙም (እንደነዚያም ግልጽ ተዓምራት ከመጣላቸው በኋላ እንደተለያዩትና እንደ ተጨቃጨቁት አትኹኑ፡፡ እነዚያም ለእነርሱ ታላቅ ቅጣት አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{وَلَا تَنَازَعُوا فَتَفْشَلُوا وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ وَاصْبِرُوا إِنَّ اللَّهَ مَعَ الصَّابِرِينَ}**

ትርጉሙም (አትጨቃጨቁም፡፡ ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትኼዳለችና፡፡ ታገሱም፤ አላህ ከትዕግስተኞች ጋር ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

አለመግባባትና መለያየት የአንድን ሀገር ግርማ ሞገስ ይገፋል፡፡ ከዚያም አልፎ ደካመነትና አቅመቢስነትን ያላብሳል፡፡ በመሆኑም የእስልምና ሃይማኖት መለያየትንና መነታረክን የሚያስከትልን ማንኛውንም ነገር አጥብቆ ይዋጋል፡፡ የእስልምና እምነት የድንቁርና ዘመን ገጽታ የነበሩ ነገሮችን በሙሉ አውግዟል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ሱ.ወ.) የድንቁርና ዘመንን ኩራትና በአባት መፎከርን አስወግዶላችኋል፡፡ ፈሪሀ አላህ ምእምን ወይም መናጢ አመጸኛ እናነት የአደም ልጆች ናችሁ አባታችሁ አደም ደግሞ ከአፈር ነው የተፈጠረው፡፡)

ነብያችን አሁንም የሰዎችን በሙብትና በግዴታ እኩል መሆናቸውን ሲያብራሩ እንድህ ይላሉ፡ (እናንተ ሰዎች ሆይ! ንቁ ጌታችሁ አንድ ነው፡፡ አባታችሁም አንድ ነው፡፡ ንቁ አንድ ዐረብ አዓረብ ያልሆነን ሰው አይበልጥም ዓረብ ያልሆነም ዓረብን አይበልጥም ቀይም ጥቁርን አይበልጥም ጥቁርም ቀይን አይበልጥም አላህን በመፍራቱ ቢሆን እንጂ፡፡)

ጌታችን ሆይ! ውህደታችን አጥንክርልን፡፡ ልቦቻችንን አስማማልን፡፡ ለምትወደውም ነገር ምራን፡፡በሥራም ሆነ በቃል ታማኝነትን ስጠን፡፡ ሀገራችንን ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# (34)

## የወጣቶች መብቶችና ግደታች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

إِنَّهُمْ فِتْيَةٌ آمَنُوا بِرَبِّهِمْ وَزِدْنَاهُمْ هُدًى}

ለአለው ለዓለማቱጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነሱ በጌታቸው ያመኑ ጎበዞች ናቸው፡፡ መመራትንም ጨመርንላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የወጣትነት ዘመን ከሰው ልጅ የህይወት ዘመናት የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ዘመን ነው፡፡ ይህ ዘመን የአካል ብርታት፣ እድገት፣ ንቃት፣ ጥንካሬ፣ ስጦታ፣ የሰፊ ተስፋና ለህይወት መጋፈጫ ዘመን ነው፡፡ ወጣቶች የህበረተሰቡ የጀርባ አጥንት፣ ትርታው የሞላ ልቡና ጠንካራ ክንዱ መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ በህዝብ እድገትና ሀገር ግንባታ ያላቸውን ጉልህ ሚና ማነም ሊክደው አይችልም፡፡

ቅዱስ ቁርአን የወጣትነት ዘመን ከደካማው የህፃንነትና የአቅመ ቀላል አረጋዊነት ዘመን መካከል የኃል ዘመን መሆኑን እንድህ በማለት ገልጾታል፡

**{اللَّهُ الَّذِي خَلَقَكُمْ مِنْ ضَعْفٍ ثُمَّ جَعَلَ مِنْ بَعْدِ ضَعْفٍ قُوَّةً ثُمَّ جَعَلَ مِنْ بَعْدِ قُوَّةٍ ضَعْفًا وَشَيْبَةً }**

ትርጉሙም (አላህ ያ ከደካማ (ፍትወት ጠብታ) የፈጠራችሁ ነው፡፡ ከዚያም ከደካማነት በኋላ ኀይልን አደረገ፡፡ ከዚያም ከብርቱነት በኋላ ደካማነትንና ሽበትን አደረገ፡፡) ማለት ነው፡፡

በመሆኑም ትንቢቶች በብዛት የወረዱት በወጣትነት ዘመን ነበር፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ስለ ሰይዲና ዩሲፍ ሲገልጽ እንድህ ብሏል፡

{وَلَمَّا بَلَغَ أَشُدَّهُ آتَيْنَاهُ حُكْمًا وَعِلْمًا وَكَذَلِكَ نَجْزِي الْمُحْسِنِينَ}

ትርጉሙም (ጥንካሬውንም በደረሰ ጊዜ ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠነው፡፡ እንደዚሁም መልካም ሠሪዎችን ሁሉ እንመነዳለን፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም ስለሰይድና ሙሳም ሲያወሳ እንድህ ብሏል፡

{وَلَمَّا بَلَغَ أَشُدَّهُ وَاسْتَوَى آتَيْنَاهُ حُكْمًا وَعِلْمًا وَكَذَلِكَ نَجْزِي الْمُحْسِنِينَ}

ትርጉሙም (ብርታቱንም በደረሰና በተስተካከለ ጊዜ ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠነው፡፡ እንዲሁም መልካም ሠሪዎችን እንመነዳለን፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን አባስ እንድህ ብለዋል፡ ‹አላህ አንድንም ነብይ አላከም በወጣትነቱ ቢሆን እጂ አንድም ሰው እውቀትን አልተሰጠም በወጣትነቱ ቢሆን እንጂ፡፡› እነሆ ነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) የጣኦት አምላኪዎችን የተጋፈጡት በወጣነት ዘመናቸው መሆኑን አላህ እንድህ ሲል አውስቷል፡

{قَالُوا سَمِعْنَا فَتًى يَذْكُرُهُمْ يُقَالُ لَهُ إِبْرَاهِيمُ}

ትርጉሙም («ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል» ተባባሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) የሰይድና ሱለይማንም ብልህነት ጎልቶ የታየው በወጣትነት ዘመናቸው መሆኑን እንድህ ሲል አወስቷል፡

{فَفَهَّمْنَاهَا سُلَيْمَانَ وَكُلًّا آتَيْنَا حُكْمًا وَعِلْمًا}

ትርጉሙም (ለሱለይማንም (ትክክለኛይቱን ፍርድ) አሳወቅናት፡፡ ለሁሉም ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠን፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም አላህ (ሱ.ወ.) ስለነብዩ ሙሳና ስለሁለቱ ሴቶች ሲገልጽ እንድህ በማለት ወጣትነትን አመልክቷል፡

{قَالَتْ إِحْدَاهُمَا يَا أَبَتِ اسْتَأْجِرْهُ إِنَّ خَيْرَ مَنِ اسْتَأْجَرْتَ الْقَوِيُّ الْأَمِينُ}

ትርጉሙም (ከሁለቱ አንደኛይቱም «አባቴ ሆይ ቅጠረው፡፡ ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጬ ብርቱው ታማኙ ነውና» አለችው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ሰይድና ያሕያ የእውቀትን አደራ ያደርሱ ዘንድ ሲያናግራቸውም በወጣትነት ብርታትና ቁርጠኝነት መሆን እንዳለበት እንድህ ሲል አውስቷል፡

{يَا يَحْيَى خُذِ الْكِتَابَ بِقُوَّةٍ وَآتَيْنَاهُ الْحُكْمَ صَبِيًّا}

ትርጉሙም («የሕያ ሆይ! መጽሐፉን በጥብቅ ያዝ!» (አልነው)፡፡ ጥበብንም በሕፃንነቱ ሰጠነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ከሰው ልጅ የእድሜ ዘመን ይህ የወጣትነት ዘመን ልዩ ትኩረት የሚሰጠው በመሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) በትንሳኤ ቀን ስለወጣነት ዘመን በተለየ መልኩ ባሪያውን የሚጠይቅ መሆኑን ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.) የገለጹት ሰዎች በወጣትነት ዘመን ጠቃሚ ነገሮችን ሁሉ እንድፈጽም ለመገፋፋት መሆኑን ሊቃውንት ጠቁመዋል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (በትንሳኤ ቀን የማንኛውም ባሪያ እግሮች ከአራት ነገሮች ሳይጠየቅ ከሂሳብ ቦታ አይንቀሳቀሱም፡፡ ስለእድሜው በምን እንዳሰለፈው፣ ስለወጣትነቱ በምን እንዳጠፋው፤ ስለገንዘቡ ከየት እንዳመጣውና በምንም እንዳጠፋው፣ ስለእውቀቱ ምን እንደሰራበት)፡፡

የእስልምና እምነት ለወጣቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ እንዳዋቂዎች ሁሉ የተለየ መብትና ግዴታም አድርጎላቸዋል፡፡ ለወጣቶች የመማር፣ የመመራትና የመልካም ማሰናዳት መበት አላቸው፡፡ ጠቢቡ ሉቅማን በልጁ መንፈስ ሃይማኖትን ለማስረጽ ያደረጉት ሙከራና ለቅንነት፣ ለስጦታ፣ መልካም ምግባርን ለመላበስ ዝግጁ እንድሆን የሰጡትን ምክር አላህ (ሱ.ወ.)እንድህ በማለት አውስቶታል፡

**وَإِذْ قَالَ لُقْمَانُ لِابْنِهِ وَهُوَ يَعِظُهُ يَا بُنَيَّ لَا تُشْرِكْ بِاللَّهِ إِنَّ الشِّرْكَ لَظُلْمٌ عَظِيمٌ }**

ትርጉሙም (ሉቅማንም ለልጁ እርሱ የሚገሥጸው ሲኾን «ልጄ ሆይ! በአላህ (ጣዖትን) አታጋራ፡፡ ማጋራት ታላቅ በደል ነውና» ያለውን (አስታውስ)፡፡ ማለት ነው፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{يَا بُنَيَّ إِنَّهَا إِن تَكُ مِثْقَالَ حَبَّةٍ مِّنْ خَرْدَلٍ فَتَكُن فِي صَخْرَةٍ أَوْ فِي السَّمَاوَاتِ أَوْ فِي الْأَرْضِ يَأْتِ بِهَا اللَّهُ إِنَّ اللَّهَ لَطِيفٌ خَبِيرٌ * يَا بُنَيَّ أَقِمِ الصَّلَاةَ وَأْمُرْ بِالْمَعْرُوفِ وَانْهَ عَنِ الْمُنكَرِ وَاصْبِرْ عَلَى مَا أَصَابَكَ إِنَّ ذَلِكَ مِنْ عَزْمِ الْأُمُورِ * وَلَا تُصَعِّرْ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمْشِ فِي الْأَرْضِ مَرَحًا إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ * وَاقْصِدْ فِي مَشْيِكَ وَاغْضُضْ مِن صَوْتِكَ إِنَّ أَنكَرَ الْأَصْوَاتِ لَصَوْتُ الْحَمِيرِ}**

ትርጉሙም (ሉቅማንም አለ) «ልጄ ሆይ! እርሷ የሰናፍጭ ቅንጣት ክብደት ያህል ብትሆንና በቋጥኝ ውስጥ ወይም በሰማያት ውስጥ ወይም በምድር ውስጥ ብትሆን አላህ ያመጣታል፡፡ አላህ ሩኅሩኅ ውስጥ ዐዋቂ ነውና፡፡ «ልጄ ሆይ! ሶላትን አስተካክለህ ስገድ፡፡ በበጎ ነገርም እዘዝ፡፡ ከሚጠላም ሁሉ ከልክል፡፡ በሚያገኝህም መከራ ላይ ታገስ፡፡ ይህ በምር ከሚያዙ ነገሮች ነው፡፡ «ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር፡፡ በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሂድ፡፡ አላህ ተንበጥራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና፡፡ «በአካኼድህም መካከለኛ ኹን፡፡ ከድምጽህም ዝቅ አድርግ፡፡ ከድምጾች ሁሉ አስከፊው የአህዮች ድምጽ ነውና፡፡» ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለወጣቶች ልክያለፈ ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡ ሙሉ ብቃት እንድኖራቸውም ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ እንድሁም በመንፈሳቸው የሃይማኖት መርሆች፣ የእውቀት ፍቅርና የተለየ ሙያ እንድኖራቸው በቀጣይነት ይሰሩነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን አባስ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንድ ቀን ከአላህ መልክተኛ በኋላ እያለሁ ሳለ እንድህ አሉኝ፡፡ (አንተ ልጅ ሆይ እኔ ምክር አዘል

ቃላትን ለአስተምርህ ወደደሁ፡፡ የአላህን ወሰኖች አውቀህ ላለመተላለፍ ጣር፡፡ እሱ ይጠብቅሃል፡፡ እንድሁም እንድህ ካደረግህ ምንጊዜም ከፊትህ ታገኘዋለህ፡፡ ስለአንድ ነገር መጠየቅ ስትፈልግ አላህን ብቻ ጠይቅ፡፡ በአንድም ነገር መታገዝ ስትፈልግ ከአላህ ብቻ እገዛን ጠይቅ፡፡ ህዝቦች በአንድ ነገር ሊጠቅሙህ ቢሰባሰቡም አላህ ለአንት በፈረደልህ ነገር እንጂ ሊጠቅሙህ አይችሉም፡፡ በአንድ ነገር ሊጎዱህ ቢሰባሰቡም በአንተ ላይ አለህ በፈረደብህ ነገር እንጂ ሊጎዱህ አይችሉም፡፡ ብእሮች መፃፋቸውን አቁመዋል፡፡ አላህ የጻፈው ነገር ሁሉ አልቆ የወረቀቶች ቀለምም ደርቋል)፡፡

ወጣቶች በሚገባ ከተማሩና በቂ ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ ለያንዳንዱ በሰለጠነበት ሞያ ዘርፍ ወደሥራ፣ አመራርና ሃላፊነት የመሰማራት መብታቸው መከበር ይኖርበታል፡፡ ነብያችን በዚህ መስክ አርአያነት ያላቸውን ተግባራት አከናውነዋል፡፡ ለእስልምና ጥሪ የማድረግን ሃላፊነት ሃያ አመት ላልሞላው አርቀም ኢብን አቢል አርቀም ለተባለው ወጣት ሰጥተው ቤቱ ለነብያችንና ለባልደረቦቻቸው አስተማማኝ መጠለያ እንዲሆን ማድረጋቸው ለዚህ ጉዳይ መረጃ ነበር፡፡ እንድሁም ኡሳማ ኢብን ዘይድን የሙስሊሞች ጦር አዛዥ አድርገው ሲመርጡት እድሜው አስራ ሰምንት አመትን አላለፈም ነበር፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ ስብሰባ በሚቀመጡ ጊዜ ወጣቶችም ከሺማግሌዎች ጎን እንዲሰተፉ ያደርጉና በተለያዩ ጉዳዮች ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ይፈቅዱላቸው ነበር፡፡ እንድሁም ‹ከነአንተ አንዳችሁንም የእድሜው ዝቅተኛነት አስተያየት ከመስጠት ሊከለክለው አይገባም፡፡ ምክኒያቱም እውቀት በእድሜ ዝቀተኛነትም ሆነ በእድሜ መግፋት አይወሰንም፡፡ ነገር ግን አላህ ከፈለገው ቦታ የሚያስቀምጠው ስጦታ ነው›፡፡ ይሉ እንደነበረም ተዘግቧል፡፡ ዑመር ኢብን አልኸጣብ በስብሳባቸው ከሚሳተፉ ወጣቶች አንዱ የሆኑትን አብደላ ኢብን አባስን እንድህ በማለት አሞግሰዋል ‹እሱኮ ጥያቄ የሚያበዛ ምላስና ልባማ አእምሮም አላው፡፡

የዚህ ዓይነቱ ተግባር በወንድ ወጣቶች ብቻም የተወሰነ አልነበረም፡፡ ሴት ወጣቶችም በእስልምና ስልጣኔ ግንባታ ማነም ሊከደው የማይችል ሚና ነበራቸው፡፡ ከዚህ ዓይነቱ የሴት ወጣቶች ሚና (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የአቡ በክር ሴት ልጅ አስማእ በነብዩና አባቸው የስደት ጉዞ የተጫወቱት ሚና አንደኛው ነው፡፡ ሴት ወጣቶች እጅግ በተፋፋመ ጦርነት በመሳተፍ ወታፈደሮችን ውሃ በማጠጣትና ቁስለኞችን በማገዝ አደገኛ ሚና ይጫወቱም ነበር፡፡

ሴቶች በኡሁድ ጦርነት የተጫወቱትን ሚና (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ብለዋል ‹ እኔ በዚያን ቀን ዓኢሻ አቡበክርና ኡሙ ሱለይም የውሃ ቀርባታ በጀርባቸው ተሸክመው ወደጦር ግንባር እያደረሱ ተምልሰውም እንደገና ሲያመጡ አሁንም እንደዚያው ሲያደርጉ አይቻለሁ፡፡›

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የወጣቶች ግዴታ እጅግ በጣም ብዙ ነው፡፡ በቀደምትነት የሚጠቀሰው ግን በቂ እውቀትና ትምህርት በማካባት ራሳቸውን የመጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ እውቀት በየጊዜው የሚሻሻል በመሆኑ ወጣቶቻችን ከዘመኑ የእውቀት አድገት ጉዞ ጋር መንቀሳቀስ፣ የሥራ ገበያ የሚጠይቀውን መለኪያ ማሟላት፣ ለሀገር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማመቻቸት መቻል አለባቸው፡፡ ይህን ሁሉ እውን ለማድረግ ታዲያ ቀጣይነት በላቸው የስልጠና መርሀ ግብሮች መሳተፍና አስፈላጊ ልምዶችን ለመቅሰም መጣር ግድ ይሆንባቸዋል፡፡ በዚህ መልኩም የተደነቀኑ ተግዳሮቶችን ለመቋቋም ያለቸው ብቃት አስተማማኝ ይሆናል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ነብዩ በዚህች ዓለም ከአንድም ነገር ጭማሬን እንድጠይቁ አለዘዛቸውም ከእውቀት ብቻ እንጂ፡፡ አንደህ በማለት፡

{وَقُلْ رَبِّ زِدْنِي عِلْمًا}

ትርጉሙም (ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ በል፡፡) ማለት ነው፡፡

ሌላው የወጣቶች ግዴታ ከተሞክሮዎች መጠቀምና በአላቸው እውቀትም ከመታለልና መሸንገል መራቅ ነው፡፡ ወጣቶች ከትውልዶች መካከል ያለው ግንኙነት እንዱ ሌላውን የማስወገድ ወይም የፍልሚያ ግንኙነት  ሳይሆን አንዱ ሌላውን የሚገነባበት ግንኙነት መሆኑን አምነው በመቀበል ከአበው ተሞክሮ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፡፡ ወጣቶቻችን ባለቤቱን አጥፊ ከሆነው በራስ ከመታለል አደጋ መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَمْشِ فِي الْأَرْضِ مَرَحًا إِنَّكَ لَن تَخْرِقَ الْأَرْضَ وَلَن تَبْلُغَ الْجِبَالَ طُولًا}

ትርጉሙም (በምድርም ላይ የተንበጣረረክ ሆነህ፤ አትሂድ፡፡ አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና በርዝመትም ፈጽሞ ጋራዎችን አትደርስምና፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ (ሦስት ነገሮች አጥፊዎች ናቸው፡፡ የማይገቱት ስስታምነት፣ በሄደበት የሚከተሉት የመንፈስ ፍላጎትና አንድ ሰው በራሱ መደነቁ፡፡)

አንድ ወጣት ሃይማኖቱንና ሀገርን ለማገልገል በየጊዜው ሀሳብን ማደስ ሌላው የወጣቶች ግዴታ ነው፡፡ አንድ ሰው የሥራው ውጤት በሥራው ጥራትና በሀሳቡ ጥልቅነት ተመዝኖ ነው የሚሰጠው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የሥራዎች ምንነት የሚመዘነው በሀሳቦች ነው፡፡ ለሀሉም ሰው ያሰበው ይሰጠዋል....)

ሌላው የወጣቶች ግዴታ ደግሞ ጉዞው ረዢምና አደራውም ከባድ መሆኑን ተገንዝቦ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ግድ ይላል የሚለው ነው፡፡ ይህውም የምንኖርበት ህብረተሰብ በፍጥነት የሚከንፍና በታታሪነት ለማይሰራ ቦታ የሌለ ስለሆነ ነው፡፡

ጽኑ ፍላጎታችንን ለመረጋገጥ፣ ለራሳችንና ለሀገራችን የምንመኘውን ቦታ ለመያዝ እንድንችል በሥራዎቻችን ያቅማችንን ሁሉ ጥረት ማድረግና መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻም ወጣቶች ለአሳደጋቸውና ላስተማራቸው ሀገራቸው ውለታን የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡ እኛ ሁላችንም የማይለየን ስንቃችን በሀሳባችን መጥናት፣ መሳሪያችን እውቀት፣ መፍከራችን የሀገር ፍቅርና ስጦታና የሀገርን ክብር ለማስጠበቅ መንጊዜም ዝግጁ መሆን የሚሉት ጉዳዮች ሊሆኑ ይገባል፡፡

ጌታችን ሆይ! ወጣቶቻችን ባርክ፡፡ ከማኝናውም መጥፎ ነገር ጠብቃቸው፡፡ የግንባታንና ልማት ስኬትንም ስጣቸው፡፡ ለሀገርና ህዝብ የሚጠቅሙ ቅን ነገሮችን ምራቸው፡፡ ሀገራችንንም ጠብቅልን አሜን፡፡

# (35)

.

## የአሉባልታና ግንዛቤን የማዛባት አደጋ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

يَا أَ{يُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَقُولُوا قَوْلًا سَدِيدًا *يُصْلِحْ لَكُمْ أَعْمَالَكُمْ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ وَمَنْ يُطِعِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ فَقَدْ فَازَ فَوْزًا عَظِيمًا}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ተርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ፡፡ ሥራዎቻችሁን ለእናንተ ያበጅላችኋልና፡፡ ኀጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል፡፡ አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው በእርግጥ ታላቅን እድል አገኘ፡፡) ማለት ነው፡፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ከእውነትና ከከንቱ መካከል ያለው ትግል ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር እንደጀመረ ይታወቃል፡፡ አንድሁም አላህ (ሱ. ወ.) ምድርንና በውስጧም ያለውን ነገር ሁሉ እስከሚወርስበት እስከት ትንሳኤ እለትም ይቀጥላል፡፡ የከንቱ ትግባር ባለቤቶች ከእውነት ተግባር ባለቤቶች ጋር በሚያደርጉት ትግል የሚጠቀሙበት አበይ መሳሪያ አሉባልታን መፍጠርና ማስፋፋት መሆኑን ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡ የሚነበብ፣ የሚሰማም ይሁን የሚታይ ቃል መከበር ያለበት አደራና ታላቅ ሃላፊነት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አሉባልታ ልበ በሽተኛ ሰው ወይም በምስጢር የሚሰራ የተንኮል ሃይል ከሰዎች መካከል የሚያናፍሱት ቃል እንጂ ሌላ ነገር

አይደልም፡፡ ከዚያም በኋላ ያለማረጋገጥና ያለማስረጃ ልሳናት ከቦታ ወደቦታ ሲያሽጋግሩት በአእምሮዎችና በልቦናዎች መካከል አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በዚህ መልኩም አፍራሽ እሳቦቶችና ብልሹ እምነቶች ይስፋፉና ህብረተሰቡ በጭንቀትና በጥርጣሬ ውሎ ያድራል፡፡ ብሎም ጸጥታ ይደፈርሳል፣ ከሰዎች መካከል ያለው አመኔታም ይዳከማል፡፡ በመሆኑም የአንድ ህዝብ አካል አንዱ ሌላውን ይጠራጠራል በክህደትም ይወነጃጀላሉ፡፡ ስለዚህም ነብያችን (ሶ. ዐ. ወ. ) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ለመዋሸት የሚሰማውን ሁሉ ማውራቱ በቂው ነው፡፡) አንድ ሰው የሰማውን ሁሉ ማውራቱ የውሸት ዓይነት ይሆናል በሱም በመጭው አለም ይቀጣበታል ከተባለ ያልሰማውንና ያለየውን የሚያወራ ሰው ቅጣት እንዴት ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም፡፡

የአስልምና እምነት ስለአሉባልታና አሉባልታን ስለሚያስፋፉ ሰዎች ጥብቅ አቋም ወስዷል፡፡ አሉባልታ የእምነቱ መሰረቶች የሆኑት የመልካም ስነ ምግባርና የጠቃሚ እሴቶች ተፃራሪ ጠባይ መሆኑን እምነቱ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ለዚህም የእምነቱ ተከታዮች በማህበረሰቡ መካከል ህውከትንና ብጥብጥን ከሚያስፋፉ ወሬ ምላሳቸውን እንዲጠብቁ እንድሁም ቃላቸውን እውነተኛ እንዲያደርጉ ህውከትን በማስፋፋት ተሳታፊ እንዳይሆኑ ወደጆሯቸው የሚደርሱ ቃላትን ትክክለኛነት እንዲያጣሩ አዟል፡፡ አላህ (ዐ. ወ. ) አንድህ ይላል፡

{يَآَ يُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَكُونُوا مَعَ الصَّادِقِينَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ከእውነተኞቹም ጋር ኹኑ፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{مَا يَلْفِظُ مِنْ قَوْلٍ إِلَّا لَدَيْهِ رَقِيبٌ عَتِيدٌ}

ትርጉሙም (ከቃል ምንም አይናገርም በአጠገቡ ተጠባባቂና ዝግጁ የኾኑ (መላእክት) ያሉበት ቢኾን እንጅ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَقْفُ مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ إِنَّ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْفُؤَادَ كُلُّ أُولَئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْئُولًا}

ትርጉሙም (ለአንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር አትከተል፡፡ መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዝ ኢብን ጀበል ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የእስልምናን ግዴታዎችና የመልካም ነገር በሮችን ከዘረዘሩላቸው በኋላ እንድህ ያሏቸው መሆኑን አውርተዋል፡ (ብትፈልግ የነገሩን ራስና ዋልታ እንድሁም የሻኛውን ቁንጮ ልነግርህ እችላለሁ፡፡) ሙዓዝም አዎን የአላህ መልክተኛ ሆይ አሉ፡ እሳቸውም እንድህ አሉ፡ (የነገሩ ራስ እስልምና ነው፡፡ ዋልታው ደግሞ ስግደት ነው፡፡ የሻኛው ቁንጮ ደግሞ በአላህ መንገድ መታገል ነው፡፡ ብትፈልግም ይህን ሁሉ በእጅህ የምታስገባበትን ነገር አነግርሃለሁ፡፡) ሙዓዝም እሱ ምንድን ነው ያላህ መልክተኛ ሆይ! አሉ፡፡ ከዚያም ነብያችን ጣታቸውን ወደምላሳቸው አስገቡና ይህን ተቆጣጠር አሉ፡፡ ሙዓዝም ያለህ መልክተኛ ሆይ! እኛ በምላሳችን

ስለምንናገረው ነገር ተጠያቂዎች እንሆናለን እንዴ? አሉ፡፡ እሳቸውም (እናትህ ትጣህና ሰዎችን በህገነም በአፍንጫቸው የሚደፋቸው በምላሳቸው የሚጭዱት እንጂ ሌላ ነገር ነው እንዴ? ) አሉ፡፡
አሉባልታን ማናፈስና ማስፋፋት ጸጥታን በማደፍረስ፣ የሀገረን አንድነት አደጋ ላይ በመጣል፣ የኢኮኖሚ ልማቱን በማዳከምና መረጋጋቱን ኢላማ በማድረግ እንድሁም በህዝቡ ዘንድ በተለይም ደግሞ በወጣቱ መንፈስ የተስፋ መቁረጥና የመጥፎ ገድ መንፈስን በማሰራጨት መናፍቃን ወደጉዳያቸውና አላማቸው ለመድረስ የሚከተሉት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{لَئِنْ لَمْ يَنْتَهِ الْمُنَافِقُونَ وَالَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمْ مَرَضٌ وَالْمُرْجِفُونَ فِي الْمَدِينَةِ لَنُغْرِيَنَّكَ بِهِمْ ثُمَّ لَا يُجَاوِرُونَكَ فِيهَا إِلَّا قَلِيلًا}.

ትርጉሙም (መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ (የአመንዝራነት) በሽታ ያለባቸው በመዲናም ውስጥ (በወሬ) አሸባሪዎቹ (ከዚህ ሥራቸው) ባይከለከሉ በእነርሱ ላይ በእርግጥ እንቀሰቅስሃለን፡፡ ከዚያም በእርሷ ውስጥ ጥቂትን እንጂ አይጎራበቱህም፡፡) ማለት ነው፡፡
አሉባልታ በነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ላይ ሳይቀር ጉዳት ያደረሰ ከጦርነት ዘዴዎች አንደኛው ነው፡፡ የመካ ኢጋሪዎች ሰበካቸውን ኢላማ በማድረግና ገጽታቸውን በማበላሸትና ስማቸውን በማጥፋት አሉባልታዎችን እያናፈሱ ነብያችንን ይዋጉ ነበር፡፡ ከሰዎችም መካከል በሀሰት ነብያችን ድግምተኛ መሆናቸውን አናፈሱ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{ وَقَالَ الْكَافِرُونَ هَذَا سَاحِرٌ كَذَّابٌ}

ትርጉሙም (ከሓዲዎቹም «ይህ ድግምተኛ (ጠንቋይ) ውሸታም ነው» አሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ በቅጥፈትም ገጣሚና አብድ መሆናቸውን አናፈሱ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{وَيَقُولُونَ أَئِنَّا لَتَارِكُو آلِهَتِنَا لِشَاعِرٍ مَجْنُونٍ}

ትርጉሙም (እኛ ለዕብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉም ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡ በሌላም ጊዜ ካህን ነው ሲሉ አናፈሱ፡፡ ያን ጊዜ አላህ እንድህ በማለት መልሶላቸዋል፡
{إِنَّهُ لَقَوْلُ رَسُولٍ كَرِيمٍ * وَمَا هُوَ بِقَوْلِ شَاعِرٍ قَلِيلًا مَا تُؤْمِنُونَ * وَلَا بِقَوْلِ كَاهِنٍ قَلِيلًا مَا تَذَكَّرُونَ * تَنْزِيلٌ مِنْ رَبِّ الْعَالَمِينَ}.

ቃል (ግጥም) አይደለም፡፡ ጥቂትን ብቻ ታምናላችሁ፡፡ የጠንቋይም ቃል አይደለም፡፡ ጥቂትን ብቻ ታስታውሳላችሁ፡፡ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
በእሑድ ጦርነት ቀንም ኢጋሪዎች ነብያችን ሞተዋል የሚል አሉባልታ አናፈሰው ነበር፡፡ ይህውም ሰዎች ጥለዋቸው እንዲሸሹና ኃይላቸውም እንዲዳከም በማሰብ ነበር፡፡ በእርግጥም ከሙስሊሞች መካከል ህውከት ተፈጠረ፡፡

የመንፈሳዊ ኃይላቸውም ተዳከመ፡፡ ከፊሎቻቸውም ሸሹ፡፡ ከፊሎችም መሳሪያ ጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከፊሎቹ ከነብያችን ጋር በሙሉ እምነት ያለመንቀሳቀስ ተረጋግተው ቆይተዋል፡፡
በሐምራእ ኢል አሰድ ጦርነትም ከሃዲዎች የቁረይሽ ጎሳዎች ነብያችን ለመዋጋት፣ መዲናን ለመውረርና አስልምናን ከስር መሰረት ለማጥፋት ከፍተኛ ጦር አዘጋጅተዋል የሚል አሉባልታ አናፍሰው ነበር፡፡ ሙስሊሞች ግን በዚህ አሉባልታ ያለመበገር በሃይማኖታቸው ጸንተው ነበር፡፡ በመሁኑም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል አመስግኗቸዋል፡
{الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَانًا وَقَالُوا حَسْبُنَا اللَّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ * فَانْقَلَبُوا بِنِعْمَةٍ مِنَ اللَّهِ وَفَضْلٍ لَمْ يَمْسَسْهُمْ سُوءٌ وَاتَّبَعُوا رِضْوَانَ اللَّهِ وَاللَّهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ}.

ትርጉሙም (እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- «ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው» ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!» ያሉ ናቸው፡፡ ከአላህም በኾነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ፡፡ የአላህንም ውዴታ ተከተሉ፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡
የእስልምና ጠላቶች የስግዴት ቂብላ ከበይተል መቅድስ ወደ በይቱላሂልሐራም በተዛወረበት ጊዜ አሉባልታ መናፈስ ጀመሩ፡፡ አይሁዶች ወደበይቱልሐራም ስለመዞር እውነተነት የመጠራጠሩን ተግባር በቅንጂት ያከናውኑ ነበር፡፡ እናንተ ሙስሊሞች የመጀመሪያው ቂብላችሁ እውነተኛ እንደሆነ የምታምኑ ከሆናችሁ እነሆ እውነትን ትታችኋል፡፡ የመጀመሪያው ቂብላችሁም ከንቱ በመሆኑ የምታምኑ ከሆናችሁ ደግሞ ከዚህ በፊት የሰራችሁት ኢባዳችሁ ከንቱ ነው፡፡ መሀሐመድም በእውነት ነብይ ቢሆን ኖሮ የቀደምት ነብያትን ቂብላ ትቶ ወደሌላ ባልዞረና ዛሬ የፈጸመውን ነገር ነገ በተጻራሪው መልኩ ባላከናወነው ነበር እያሉ የህዝቡን አመለካከት አዘበራረቁ፡፡
መናፍቃን በበኩላቸው እነዚህ ሙስሊሞች ምነካቸው ወደአንድ ቂብላ ሲሰግዱ የነበር አሁን ደግሞ ተውት እያሉ መሳለቅ ጀመሩ፡፡ ኢጋሪዎችም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ በሃይማኖቱ ግራ ተጋብቷል ወደቂብላችን እንደተመለሰ ሁሉ ወደሃይማኖታችንም ሳይመለስ አይቀርም የሚል ወሬ አናፈሱ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ቀድሞ እነዚህ ሞኞች የሚሉትን ሁሉ ለመልከተኛው በማሳወቁ ይህን አሉባልታ በማስተባበል የምእምናን መንፈስ አረጋግቶ እምነታቸውንም አጠንክሯል፡፡
እንድሁም በሑነይን ጦርነት ቀን ነብያችን እንደተገደሉ አሉባልታ ተናፍሶ ነብያችን ይህን አሉባልታ በራሳቸው ቁመው (ሀሰት አይደለም እኔ ነብይ ነኝ እኔ የአብደልሙጠሊብ ልጅ ነኝ፡፡) በማለት ተጋፍጠዋል፡፡
አሉባልታን በመመላስና በማስፋፋት ነፍስና ንብረት እንደሚጠፋ ክብር እንደሚነካና ሕይወት እንደሚበጣበጥ ለማንም ልበኛ ድብቅ ነገር አይሆንም፡፡ ለዚህ ጉዳይ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በከሊፋው ኡስማን ኢብን አፋን መገደል ጉልህ መረጃ አለን፡፡ አይሁዳዊው አብደላ ኢብን ሰበእ ባናፈሰው

አሉባልታ ምክኒያት አረመኔዎች ከበቧቸው፡፡ በራሳቸው ገንዘብ ከገዙት ሙእታ ውሃ ጉድጓድ እንዳይጠጡም ከለከሏቸው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የኡስማን ባለቤት ናኢላህ የሚከተለውን አውርተዋል፡፡ ኡስማን ከተገደሉበት ቀን በፊት ቀኑን ጹመው ዋሉ፡፡ በማፍጠሪያ ሳዓት ውሃ ቢጠይቁ ጊዜ ከለከሏቸው፡፡ ሳያፈጥሩም ተኙ፡፡ የጾም መያዣ ሳዓት ሲደርስ ወደጎረቤት ሴቶች ሄጄ ውሃ ለመንኩኝ፡፡ እነሱም አንድ ኮዳ ውሃ ሰጡኝ፡፡ መጣሁና ነቅነቅ ሳደርጋቸው ነቁ፡፡ ይህውና የመጠጥ ውሃ አመጣሁ አልኳቸው፡፡ ቀጥ አሉና ወደጎህ ተመለከቱ፡፡ እኔ ጾም ይዤ አድሪያለሁ አሉ፡፡ ቀጥለውም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ውሃ ይዘው በዚህ ጣራ በኩል ብቅ ብለው (ኡስማን ሆይ! ጠጣ) አሉኝ፡፡ እስከምረካም ጠጣሁኝ (ጨምር) አሉኝ፡፡ ሆዴ እስከሚሞላ ጠጣሁ፡፡ ከዚያም እንድህ አሉኝ፡ (እነዚህ ሰዎችኮ ይበዙብሃል፡፡ ሆኖም ብተዋጋቸው ድልን ትቀዳጃለህ፡፡ ብትተዋቸው ግን ከኛ ጋር ታፈጥራለህ፡፡) በዚያን ቀን ገቡና ገደሏቸው፡፡

ባለነብት ዘመን ደግሞ የመገናኛ ዘዴዎችና ቴክኖሎጂ በፍጥነት እየተለወጠ በመምጣቱ ምክኒያት በርካታ ሁኔታዎች ተቀይረዋል፡፡ የዚህ እርኩስ ሥራ ቅርጾችና ገጽታዎች የተለያዩና በርካታዎች ሆነዋል፡፡ በዚህ ዘመን የአሉባልታ ስርጭት እጅግ ፈጣን ተጽእኖውም ሰፊ ሆኗል፡፡ ይልቁንም ከጦርነት መሳሪያዎችና ዘዴዎች አንዱ በመሆኑ ጦርነት እንደተለመደው በመሳሪያ፣ በደህንነት ክትትልና በመረጃ ማሰባሰብ ብቻ የተወሰነ አልሆነም፡፡ ጦርነት በአሁኑ ወቅት አሉባልታንና ግንዛቤ ማወዛገብን በአደገኛ መሳሪያነት ይጠቀምበታል፡፡ እሱም በተለያዩ ተቋማት አማካይነት ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥበት ታዋቂ መሳሪያ ሆኗል፡፡ ለሱም የሰለጠነ የኤሌክተሮኒክስ ግብረ ኃይልም እየተመደበለት ከፍተኛ የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚና የመንፈሳዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ህዝብ በመንግስት ላይ አመጽ እንዲያስነሳ፣ የህዝብ አርአያ አካላትም ስም እንዲጠፋ፣ የተመዘገቡ ስኬቶችን በማቃለል ዘርፍ የሚደረጉ ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች የሰዎችን ወቅታዊ ፍላጎት መሰረት ከአደረገው የአሸባሪ ቡድኖች የተቀናጀ የመበታተን መካኒዝም ጋር ተደምሮ የህዝቡን ጽኑ ፍላጎት በመስበር፣ የባለስልጣናትን ሞገስ በመግፈፍ፣ በሀገር ወዳድ ሊቃውንትና ተመራማሪዎች አመኔታ ጉዳት በማድረስ፣ እውነተኛ መርሀቸውን አንለቅም ለአሉ ታማኝ አገር ወዳድ ወገኖች ዛቻ በማስተላለፍ ወደከህደት ወገን እንዲቀላቀሉ በማድረግና እጅ ሰጥተው እንዲምበረከኩ ከዚያም ሁሉም እነሱን ተከትሎ እንዲምበረከክ ይህ ነው የማይባል ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ይህን ሁሉ አደገኛ ሞገድ ለመቋቋም ጠንካራ ሀገራዊ ፍቅርና ወሰን የለሽ የፈጣሪ እምነት የሚጠይቅ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ጥቂት የሚባሉ በእውነተኛ መረጃ ያልተደገፉ ወሬዎችን፣ እስታቲስቲኮችንና ትረካዎችን ማስተላፋቸውን እንደቀላልነገር ይመለከቱታል፡፡ በዚህም አሉባልታና ህውከት በማሰራጨት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ አንድ ሰው መሰረት ቢስ ቃልን በመናገር፣ በመፃፍ ወይም በማስተላለፍ በትንሳኤ ቀን ከፍተኛ ቅጣት ሊደርስበት ይችላል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ባሪያ እንድሁ ልብ ሳይል አላህን የሚያስደስት ቃል ይናገርና በሱ ምክኒያት አላህ ወደከፍተኛ ደረጃዎች ያደርሰዋል፡ ፡ አንድ ባሪያ ደግሞ እንድሁ ልብ ሳይል አላህን የሚያስቆጣ ቃል ይናገርና በሱ

ምክኒያት በገሀነም ይዘፈቅበታል፡፡)
ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

*   *   *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የእስልምና እምነት ማህበረሰቡን ከአሉባልታ አደጋ ለመጠበቅ በሚከተሉት ነጥቦች አማካይነት ጥበብ የተሞላበት ስርአት አስቀምጧል፡
* አንድ ወሬ ስንሰማ በማህበረሰቡ መካከል ከማሰራጨታችን በፊት ማጣራት አለብን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
يَا أَيُّهَاالَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}، وقال(صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ): (التَّأَنِّي مِنَ اللهِ، وَالْعَجَلَةُ مِنَ الشَّيْطَانِ)

ትርጉሙም (እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጻቾች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡") ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ዝግታ ከአላህ (ዐ.ወ.) ነው፡፡ መቻኮል ደግሞ ከሰይጣን ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (በማንኛውም ነገር ዝግታ ደግ ነው በመጭው ዓለም ሥራዎች ሲቀር፡፡)
* በሚነበብ፣ በሚሰማና በሚታይ የመገናኛ ዘዴ አማካይነት አሉባልታዎችን አለመደጋገም፡፡ አሉባልታ የሚደጋግም ልሳን፣ የሚያዳምጥ ጆሮና የሚቀበል መንፈስ ሲያገኝ በፍጥነት ይስፋፋል፡፡ አላህ (ሶ.ወ.) እንድህ ይላል፡
تَقُولُونَ بِأَفْوَاهِكُمْ مَا لَيْسَ لَكُمْ بِهِ عِلْمٌ وَتَحْسَبُونَهُ هَيِّنًا وَهُوَ عِنْدَ اللَّهِ عَظِيمٌ }،

ትርጉሙም (በምላሶቻችሁ በምትቀበባሉት ጊዜ ለእናንተም በእርሱ ዕውቀት በሌላችሁ ነገር በአፎቻችሁ በተናገራችሁና እርሱ አላህ ዘንድ ከባድ ኀጢአት ኾኖ ሳለ ቀላል አድርጋችሁ ባሰባችሁት ጊዜ (ከባድ ቅጣት በነካችሁ ነበር)፡፡ ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ ( በአላህና በመጨረሻውም ቀን የሚያምን ሰው በጎረቤቱ ላይ ጉዳት አያድረስ፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው እንግዳውን ያክብር፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው ደግን ነገር ይናገር ወይም ጸጥ ይበል፡፡)
* ለሌሎች መልካም ግምትን መስጠትና በነሱ ላይ ወንጀል ለመሰንዘር

አለመቸኮል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَوْلَا إِذْ سَمِعْتُمُوهُ ظَنَّ الْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بِأَنْفُسِهِمْ خَيْرًا وَقَالُوا هَذَا إِفْكٌ مُبِينٌ}

ትርጉሙም ((ውሸቱን) በሰማችሁት ጊዜ ምእምናንና ምእምናት በነሶቻቸው ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም፡፡)
ማንኛውም ሙስሊም ሌሎችን በበጎ መገመትና ለተግባራቸውም መልካም ግምት እንዲሰጥ ታዟል፡፡ ሰዎችን በመጥፎ መገመት ሕይወትን የሚያወዛግብ አውዳሚ በሽታ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ከዚህ አደገኛ በሽታ አስጠንቅቀዋል፡ (አደራ በመጥፎ ከመገመት ተጠንቀቁ፡፡ በመጥፎ መገመት የሀሰት ወሬ ነው፡፡ የሰዎችን ወሬ አታዳምጡ ነውራቸውንም አትከታተሉ አትመቀኛኙ ጀርባም አትሰጣጡ አትጠላሉም ወንድም ተማማች የአላህ ባሪያዎች ሁኑ፡፡)
* ለነገሮች ብያኔ ለመስጠት ያለመቻኮል ነገሮችን ለማጣራትና ለማረጋገጥ በባለልምዶችና በባለሞያዎች መታገዝ፡፡ አላህ (ሶ.ዐ.ወ.) የመናፍቃንን ሁኔታ እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{وَإِذَا جَاءَهُمْ أَمْرٌ مِنَ الْأَمْنِ أَوِ الْخَوْفِ أَذَاعُوا بِهِ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى الرَّسُولِ وَإِلَى أُولِي الْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ الَّذِينَ يَسْتَنْبِطُونَهُ مِنْهُمْ وَلَوْلَا فَضْلُ اللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُ لَاتَّبَعْتُمُ الشَّيْطَانَ إِلَّا قَلِيلًا}

ትርጉሙም (ከጸጥታ ወይም ከፍርሃት አንዳች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ፡፡ ወደ መልክተኛውና ከእነርሱ ወደ ትዕዛዙ ባለቤቶች (ወደ ዐዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር፡፡ በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከጥቂቶች በስተቀር ሰይጣንን በተከተላችሁ ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህን ማለትም እንነሱ በመዲና ማህበረሰብ ችግር ለማድረስ አድፍጠው ነበርና በሙስሊሞች ደህንነት ጉዳት የሚያደርስ እንድሁም ፍራት የሚያስከትል ወሬ ሲሰሙ በማህበረሰቡ ዘንድ ፍርሃት፣ ጭንቀትና ብጥብጥ እንዲሰፍን በፍጥነት ያናፍሱት ነበር፡፡
ለሃይማኖቱ ቅናት ያለበትና ለሀገሩ ታማኝ የሆነ ምእምን ሁሉ የዚህ ኣይነቱን አደገኛ አሉባልታ በማስተባበል ለመቋቋም አፈሩን አራግፎ ይነሳ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በወንድሙ ክብር ላይ የተሰነዘረን ስም ማጥፋት የመለሰ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን እሳትን ከፊቱ ይመልስለታል፡፡) በመጨረሻም ቃል በትንሳኤ ቀን አላህ (ዐ.ወ.) ፊት የምንጠይቅበት አደራ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡
ሁላችንም ጠላቶቻችን ጀኔሬሽን አራትና አምስትን፣ አሉባልታን፣ ማንኛውንም ሀገራዊ ነገርን ቅርጽ ማጥፋትን መሰረት በማድረግ ሀገሮቻችንን ስኬት አልባ ለማድረግ ወይም ለመጣል አለዚያም ለመበታተን እየተዋጉን መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡ ውጊያውም እጅጉን የተፋፋመ በመሆኑ በጠላቶቻችን ደባ እንዳንጠለፍ በራሳችን አንድሁም በመሪዎቻችን ሙሉ እምነት ሊኖረን ይገባል፡፡ ስለዚህ ለጠላቶቻችን ጆሯችንን መስጠት የለብንም፡፡ እነሱ ደህንነታችንነ አደጋ ላይ ለመጣል፣ ሞራላችንንም ዝቅ ለማድረግ፣ የተስፋ መቁረጥ መንፈስም እንድስፋፋ

ጥረት ኢያቆሙምና ለመላ ማህበረሰቡ በተለይም ደግሞ በወጣቶቻችን ዘንድ ብቁ ግንዛቤ እንድኖርና የተደቀኑ ችግሮችን መጠን እንዲያውቁ በችግሮች መፍትሄም ተሳታፊ እንድሆኑ መታገል አለብን፡፡
ጌታችን ሆይ! ጠባያችንን አሳምርልን ሀገራችንንም ጠብቅልን የምትወደውንም ነገር እንድንሰራ ሰኬትን ስጠን፡፡

***

# (36)

## የኩራት፣ የትእቢትና ከአላህ (ዐ.ወ.)ሃይማኖት የመከልከል ገጽታዎች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
سَأَصْرِفُ عَنْ آيَاتِيَ الَّذِينَ يَتَكَبَّرُونَ فِي الأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَإِنْ يَرَوْا كُلَّ آيَةٍ لا يُؤْمِنُوا بِهَا وَإِنْ يَرَوْا سَبِيلَ الرُّشْدِ لاَ يَتَّخِذُوهُ سَبِيلاً وَإِنْ يَرَوْا سَبِيلَ الْغَيِّ يَتَّخِذُوهُ سَبِيلاً ذَلِكَ بِأَنَّهُمْ كَذَّبُوا بِآيَاتِنَا وَكَانُوا عَنْهَا غَافِلِينَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያን ያለአግባብ በምድር ላይ የሚኮሩትን ከአንቀጾቼ በእርግጥ አዞራቸዋለሁ፡፡ ተዓምርንም ሁሉ ቢያዩ በርሷ አያምኑም፡፡ ቅንንም መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው አይዙትም፡፡ ግን የጥመትን መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው ይይዙታል፡፡ ይህ እነርሱ በአንቀጾቻችን ስለአስተባበሉና ከእርሷም ዘንጊዎች ስለኾኑ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የኩራተኞች መጨረሻ በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም እጅጉን አስከፊ ነው፡፡ የነዚያ ያመጡና በትእቢት የተወጠሩ ህዝቦችና መንደሮቻቸው ጥፋት በሰው ልጅ ሕይወት የደነገገው የአላህ (ዐ.ወ.) ቋሚ ህግ ነው፡፡ ለአላህም ድንጋጌ ፈጽሞ መለወጠን እንድሁም መዛወርን አታገኝም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَأَمَّا عَادٌ فَاسْتَكْبَرُوا فِي الْأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَقَالُوا مَنْ أَشَدُّ مِنَّا قُوَّةً أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّ اللَّهَ الَّذِي خَلَقَهُمْ هُوَ أَشَدُّ مِنْهُمْ قُوَّةً وَكَانُوا بِآيَاتِنَا يَجْحَدُونَ * فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ رِيحًا صَرْصَرًا فِي أَيَّامٍ نَّحِسَاتٍ لِّنُذِيقَهُمْ عَذَابَ الْخِزْيِ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَلَعَذَابُ الْآخِرَةِ أَخْزَى وَهُمْ لَا يُنصَرُونَ}

ትርጉሙም (ዓድም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ፡፡ «ከእኛ ይበልጥ በኀይል ብርቱ ማን ነው?» አሉም፡፡ ያ የፈጠራቸው አላህ እርሱ በኀይል ከእነርሱ ይበልጥ የበረታ መኾኑን አያዩምን? በተዓምራታችንም ይክዱ ነበሩ፡፡ በቅርቢቱ ሕይወት የውርደትን ቅጣት ልናቀምሳቸውም በእነርሱ ላይ የሚንሻሻን ብርቱ ነፋስ መናጢዎች በኾኑ ቀናት ውስጥ ላክንባቸው፡፡ የመጨረሻይቱም (ዓለም) ስቃይ በጣም አዋራጅ ነው፡፡ እነርሱም አይረዱም፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡
{وَكَأَيِّن مِّن قَرْيَةٍ عَتَتْ عَنْ أَمْرِ رَبِّهَا وَرُسُلِهِ فَحَاسَبْنَاهَا حِسَابًا شَدِيدًا وَعَذَّبْنَاهَا عَذَابًا نُّكْرًا* فَذَاقَتْ وَبَالَ أَمْرِهَا وَكَانَ عَاقِبَةُ أَمْرِهَا خُسْرًا} .

ትርጉሙም (ከከተማም ከጌታዋ ትዕዛዝ ከመልክተኞቹም ያመጸች፣ ብርቱንም ቁጥጥር የተቆጣጠርናት፣ መጥፎንም ቅጣት የቀጣናት ብዙ ናት፡፡ የነገርዋንም ቅጣት ቀመሰች፡ ፡ የነገርዋም መጨረሻ ከሳራ ኾነ፡፡) ማለት ነው፡፡
ኩራት አላህ (አ.ወ.) ለመጀመሪያ ጊዜ የተወነጀለበት ኃጢአት ነው፡፡ ይህውም ታላቁ አላህ መላእኮች ለአደም እንዲሰግዱ ባዘዘ ጊዜ ሁሉም ሰገዱ ከኢብሊስ በስተቀር፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡፡
{وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَائِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَى وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ الْكَافِرِينَ}.

ትርጉሙም (ለመላእክትም «ለአደም ስገዱ» ባልን ጊዜ (አስታውስ) ፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ ኮራም ከከሓዲዎቹም ኾነ፡፡”) ማለት ነው፡፡
ኩራተኞች በዚህች ዓለም ይለዩባቸው በነበሩት አጻያፊ ገጽታዎች በመጭው ዓለምም እንደዚሁ ይለዩባቸዋል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡
{وَنَادَى أَصْحَابُ الْأَعْرَافِ رِجَالًا يَعْرِفُونَهُم بِسِيمَاهُمْ قَالُوا مَا أَغْنَى عَنكُمْ جَمْعُكُمْ وَمَا كُنتُمْ تَسْتَكْبِرُونَ}

ትርጉሙም ( የአዕራፍም ሰዎች በምልክታቸው የሚያውቁዋቸውን (ታላላቅ) ሰዎች ይጣራሉ፡፡ «ስብስባችሁና በብዛታችሁ የምትኮሩ መኾናችሁም ከእናንተ ምንም አልጠቀማችሁ» ይሏቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡
በመሆኑም የእስልምና እምነት የኩራት መጨራሻው አስከፊ መሆኑን አስጠንቅቋል፡፡ ከአላህ እዝነት የሚያርቅ መንገድ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡ ኩራተኞችም አሳማሚ ቅጣት እንደሚተብቃቸው ዝቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ كَذَّبُوا بِآيَاتِنَا وَاسْتَكْبَرُوا عَنْهَا لاَ تُفَتَّحُ لَهُمْ أَبْوَابُ السَّمَاءِ وَلاَ يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ حَتَّى يَلِجَ الْجَمَلُ فِي سَمِّ الْخِيَاطِ وَكَذَلِكَ نَجْزِي الْمُجْرِمِينَ}

ትርጉሙም ( እነዚያ አንቀጾቻችንን ያስተባበሉ ከእርሷም የኮሩ ለእነርሱ የሰማይ ደጃፎች አይከፈቱላቸውም፡፡ ግመል በመርፌ ቀዳዳ እስከሚገባም ድረስ ገነትን አይገቡም፡፡ እንደዚሁም አጋሪዎችን እንቀጣለን፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَيَوْمَ الْقِيَامَةِ تَرَى الَّذِينَ كَذَبُوا عَلَى اللَّهِ وُجُوهُهُم مُّسْوَدَّةٌ أَلَيْسَ فِي جَهَنَّمَ مَثْوًى لِّلْمُتَكَبِّرِينَ}

ትርጉሙም (በትንሣኤ ቀንም እነዚያን በአላህ ላይ የዋሹትን ፊቶቻቸው የጠቆሩ ኾነው ታያቸዋለህ፡፡ በገሀነም ውስጥ ለትዕቢተኞች መኖሪያ የለምን?) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ገነትና እሳት ተከራከሩ፡ እሳት በኔ ውስጥ ኃያላንና ኩሩዎች አሉ አለች፡፡ ጀነትም በኔ ውስጥ ከሰዎች ደካሞቹና ምስኪኖቹ አሉ አለች፡፡ ከዚያም አላህ (ዐ.ወ.) ከነሱ መካከል በመዳኘት እንድህ አለ፡ (አንቺ ገነት እዝነቴ ነሽ ባንቺ ለፈለግሁት ምህረት አደርጋለሁ፡፡ አንቺ አሳት ደግሞ ቅጣቴ ነሽ ባንች የፈለግሁትን እቀጣለሁ፡፡ ሁለታችሁንም እኔ ልሞላችኋለሁ ቃል እገባለሁ፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (... የእሳት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ልንገራችሁን? ገብጋባ ገንዘብ አካባችና ትእቢተኛ ሁሉ ናቸው)፡፡
ኩራት በበሽተኛ ልብ ውስጥ የሚሰፍን ባሕርይ መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ አንድ ሰው ኑሮው ዝቅተኛና ንብረቱም ቀላል ሆኖ እያለ ሲምበጠረር ይስተዋላል፡፡ ሌላው ደግሞ ባለሰፊ ጸጋና ይህች ዓለም ስፍታለት እያለ ራሳቸውን ዝቅ ከሚያደርጉና ከሚተናነሱት ሰዎች መካከል ይገኛል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በልቡ ቅንጣትም ብትሆን ኩራት ያለችበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡) ያን ጊዜ አንድ ሰው አንድ ሰው ልብሱ ጫማውም ያማረ እንድሆን ይፈልጋል ሲል ጠየቀ፡ እሳቸውም (አላህ (ሱ.ወ.) ውብ ነው ውበትንም ይወዳል፡፡ ኩራት ማለት ሙብትን መጋፋትና ሰዎችን ማንኳሰስ ነው፡፡) አሉ፡፡ ኩራት መንፈስን የሚሰብሩና ማህበረሰብን የሚያወድሙ አደገኛ ከሚባሉት የስነ ልቦናና የማህበራዊ በሽታዎች እንደኛው ነው፡፡ የኩራት ባለቤት በኩራቱ ሰዎችን ዝቅ አድርጎ በማየቱ ራሱን የሚያታልል ሰው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِن فِي صُدُورِهِمْ إِلاَّ كِبْرٌ مَا هُمْ بِبَالِغِيهِ}.

ትርጉሙም(በልቦቻቸው ውስጥ እነርሱ ደራሾቹ ያልኾኑት ኩራት ብቻ እንጅ ምንም የለም፡፡) ማለት ነው፡፡

ኩራት በመንፈስ ውስጥ የሚሰፍን ባሕርይ ቢሆንም በስርኣትና ከሰዎች ጋር በሚደረግ እንቅስቃሴ ጎልተው የሚታዩ በርካታ ገጽታዎች አሉት፡፡ ከነሱም በቅድሚያ

የሚጠቀሱት ትእቢቱ በኃጢያት ሥራ የሚገፋፋው መሆኑና ለእውነት አለመገዛቱ የሚሉት ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሳል፡

{.وَإِذَا قِيلَ لَهُ اتَّقِ اللَّهَ أَخَذَتْهُ الْعِزَّةُ بِالْإِثْمِ}

ትርጉሙም (ለእርሱ «አላህን ፍራ» በተባለም ጊዜ፤ ትዕቢቱ በኃጢአት (ሥራ) ላይ ትገፊፋዋለች፡") ማለት ነው፡፡

ኩራተኛ ሰው አስከፊው መታለሉና አጻያፊ ኩራቱ እውነትን እንዳይቀበል የሚያደርጉት ሲሆን ወደእውነት ሲጠሩት መታለልንና መንበጣረረን ይጨምረዋል፡፡ በመሆኑም ራሱን ወደጥፋት ይከታል፡፡ በገሀነምም ይቀጣል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَحَسْبُهُ جَهَنَّمُ وَلَبِئْسَ الْمِهَادُ}

ትርጉሙም(ገሀነምም በቂው ናት፤ (እርሷም) በእርግጥ የከፋች ምንጣፍ ናት፡፡") ማለት ነው፡፡

ከሰዎች መካከል በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ትእዛዝም ሳይቀር የሚተበትና የትእቢቱንና የሞገዱን ዋጋ የሚያገኝ ሰው አለ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢያስ ኢብን ሰለማህ ኢብን ኢል አክወዕ አባታቸውን ጠቅሰው የሚከተለውን እውርተዋል፡ ‹አንድ ሰውዬ ከነብያችን አጠገብ በግራ እጁ መመገብ ጀመረ እሳቸውም (በቅኝ ብላ) አሉት፡፡ እሱም አልችልም አለ፡፡ እሳቸውም (አትቻል) አሉት፡፡ ያ ሰው ኩራቱ እንጅ በቀኙ ከመብላት የሚያግደው ነገር አልነበረም፡፡ ኢብን ሰለማ እንድህ አሉ፡ ያ ሰውዬ እጁን ወደአፉ ማድረስ አልቻለም፡፡›

ሌላው የኩራት ገጽታ ደግሞ በኩራት ፊትን ከሰዎች ማዞር የሚለው ነው፡፡አላህ (ሱ.ወ.) በሉቅማን ልሳን እንድህ ይላል፡

{وَلَا تُصَعِّرْ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمْشِ فِي الْأَرْضِ مَرَحًا إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ}

ትርጉሙም («ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር፡፡ በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሂድ፡፡ አላህ ተንበጥራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና፡፡) ማለት ነው፡፡
በአረማመድ መንበጣረር ሌላው የኩራት ገጽታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَمْشِ فِي الْأَرْضِ مَرَحًا إِنَّكَ لَنْ تَخْرِقَ الْأَرْضَ وَلَنْ تَبْلُغَ الْجِبَالَ طُولًا كُلُّ ذَٰلِكَ كَانَ سَيِّئُهُ عِنْدَ رَبِّكَ مَكْرُوهًا}

ትርጉሙም(በምድርም ላይ የተንበጣረርክ ሆነህ፤ አትሂድ፡፡ አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና በርዝመትም ፈጽሞ ጋራዎችን አትደርስምና፡፡) ማለት ነው፡፡
በእርስትና አላህ በቸረው ጸጋም መፎከር ከኩራት ገጽታ ይመደባል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በፊት ከነበሩት ህዝቦች አንድ ሰው አንድ ቀን ውብ ሸማና ሽርጡን ለብሶ በኩራት በሰዎች መካከል ወጣ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) መሬትን

እንድትውጠው አዘዛት እነሆ እስከ ትንሳኤም ቀን ድረስ እንደሰጠመ ይኖራል፡፡) ትእቢት በልብስ እንደሚሆን ሁሉ በቤት ምንጣፍ፣ በመኪናና የተለየ ቤትን በመግዛትም ሊከሰት ይችላል፡፡ ከድሆችና ከደካሞች ጋር መቀመጥን መናቅ ሌላው የትእቢት ገጽታ ነው፡፡ አጋሪዎች ከድሃ የነብያችን ባልደረቦች ከሰልማን፣ ከሱሃይብና ከቢላል ጋር መቀመጥን ይንቁ ነበር፡፡ ከዚያም አልፎ ለአላህ መልክተኛ እነዚህን አባር በኛ ላይ እጠዳፈሩ ነውና በማለታቸው ታላቁ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ የምትለዋን አንቀጽ አወረደ፡

{وَلاَ تَطْرُدِ الَّذِينَ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ بِ ٱلْغَدَاةِ وَٱلْعَشِيِّ يُرِيدُونَ وَجْهَهُ}

ትርጉሙም (እነዚያን ጌታቸውን ፊቱን (ውዴታውን) የሚሹ ኾነው በጧትና በማታ የሚጠሩትን አታባር፡፡) ማለት ነው፡፡
በድግስ ጊዜ ባለጸጋዎችን መጥራትና ድሆችን ንቆ መተው ሌላው የኩራት ገጽታ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ብለዋል፡ ‹ከመግብ እጅግ መጥፎው ሃብታሞች የሚጠሩበትና ድሃዎች የሚተውበት ድግስ ምግብ ነው፡፡› ከኩራት ገጽታዎች ሌላው ደግሞ በደረጃ ከሱ በታች የሆነን ሰው ንቆ ሰላምታ አለማለት ወይም እሱን አለመጨበጥ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በህጻናት አጠገብ ሲያልፉ ሰላምታ ያቀርቡላቸው ነበር፡፡ በክርክር መፋጠጥና በሱም መሰመርን መልቀቅ የኩራት ሌላው ገጽታ ነው፡፡ መቆራረጥና ብልሹነትን ስለሚያስከትል አንድ ሰው ወንድሙን ከሦስት ቀን በላይ እንዳያኮርፍ ተከልክሏል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ወንድሙን ከሦስት ቀን በላይ ያኮረፈ አላህ በቸርነቱ ምህረት ካለደረገለት በስተቀር እሱ እሳት ይገባል፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን ከሦስት ቀናት በላይ ሊያኮርፈው አይፈቀድለትም፡፡ እነሱ ሲገናኙ አንዱ ለሌላው ጀርባውን ይሰጣል፡፡ ከነሱም በላጩ ያ በሰላምታ የቀደመው ነው፡፡)
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አራት ነገሮች በሱ ያሉበት ሰው ሙሉ መናፍቅ ነው፡፡ ከነሱ አንዱ ያለበት ደግሞ እሱን እስከሚያሰውገድ ድረስ ከመናፍቅነት ገጽታዎች አንዱ አለበት፡፡ -እነሱም- እምነት ሲጣልበት ይከዳል፣ ሲያወራም ይዋሻል፣ ቃል ሲገባም ቃሉን ያፈርሳል፣ ሲከራከርም መስመር ይለቃል፡፡) አጋሪዎች እስልምናን እንዳይቀበሉ የከለከላቸውና (لا إِلَٰهَ إلا الله) ከማለትም ያገዳቸው ኩራትና ትእቢት ብቻ ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّهُمْ كَانُوا إِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ يَسْتَكْبِرُونَ}

ትርጉሙም (እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ፡፡) ማለት ነው፡፡
አይሁዳዎችም በነብይነታቸው እውነተኛነት እርግጠኞች ሆነው ሳል ነብያችንን ከመከተል የከለከላቸው ትእቢት ብቻ ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ آتَيْنَاهُمُ الْكِتَابَ يَعْرِفُونَهُ كَمَا يَعْرِفُونَ أَبْنَاءَهُمْ وَإِنَّ فَرِيقًا مِّنْهُمْ لَيَكْتُمُونَ الْحَقَّ وَهُمْ يَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም(እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል፡፡ ከነሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያወቁ ሲኾኑ እውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ፡፡) ማለት ነው፡፡
የእስራኢል ልጆች ነብዮቻቸውን ውሸታም እንድሉና ከፊሎችንም እንድገድሉ ያደረጋቸው ያው ትእቢት ነው፡፡ አላህ(ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡
أَفَكُلَّمَا جَاءَكُمْ رَسُولٌ بِمَا لاَ تَهْوَى أَنفُسُكُمُ اسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقاً كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقاً تَقْتُلُونَ}.

ትርጉሙም (ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ ከፊሉንም ትገድላላችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡
የላፉት ህዝቦት ነብዮቻቸውን ውሸታም ናችሁ እንድሉ ያደረው ራሱ ትእቢት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) በነብዩ ኑሕ ልሳን እንድህ ይላል፡
{وَإِنِّي كُلَّما دَعَوْتُهُمْ لِتَغْفِرَ لَهُمْ جَعَلُوا أَصابِعَهُمْ فِي آذانِهِمْ وَاسْتَغْشَوْا ثِيابَهُمْ وَأَصَرُّوا وَاسْتَكْبَرُوا اسْتِكْباراً}

ትርጉሙም(«እኔም ለእነርሱ ትምር ዘንድ (ወደ እምነት) በጠራኋቸው ቁጥር ጣቶቻቸውን በጆሮዎቻቸው ውስጥ አደረጉ፡፡ ልብሶቻቸውንም ተከናነቡ፡፡ (በመጥፎ ሥራቸው ላይ) ዘወተሩም፡፡ (ያለ ልክ) መኩራትንም ኮሩ፡፡ ) ማለት ነው፡፡
እንድሁም ስለነብዩ ሁድ ሰዎች ሲያብራራ እንድህ ይላል፡
{فَأَمَّا عَادٌ فَاسْتَكْبَرُوا فِي الْأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَقَالُوا مَنْ أَشَدُّ مِنَّا قُوَّةً}

ትርጉሙም(ዓድም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ፡፡ «ከእኛ ይበልጥ በኀይል ብርቱ ማን ነው?» አሉም፡፡) ማለት ነው፡፡ ስለሷሊሕ ሰዎችም እንድህ ብሏል፡
{قَالَ الْمَلأُ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُواْ مِن قَوْمِهِ لِلَّذِينَ اسْتُضْعِفُواْ لِمَنْ آمَنَ مِنْهُمْ أَتَعْلَمُونَ أَنَّ صَالِحًا مُّرْسَلٌ مِّن رَّبِّهِ قَالُوْاْ إِنَّا بِمَا أُرْسِلَ بِهِ مُؤْمِنُونَ قَالَ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُواْ إِنَّا بِالَّذِيَ آمَنتُمْ بِهِ كَافِرُونَ}

ትርጉሙም(ከወገኖቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች ለእነዚያ ለተሸነፉት ከነሱ ላመኑት፡- «ሷሊህ ከጌታው መላኩን ታውቃላችሁን» አሏቸው፡፡ « (አዎን)፡- እኛ እርሱ በተላከበት ነገር አማኞች ነን» አሉ፡፡ እነዚያ የኮሩት፡- «እኛ በዚያ እናንተ በርሱ ባመናችሁበት ከሓዲዎች ነን» አሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ ስለሹዓይብ ህዝቦችም እንድህ ብሏል፡

(قَالَ الْمَلأُ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُواْ مِن قَوْمِهِ لَنُخْرِجَنَّكَ يَا شُعَيْبُ وَالَّذِينَ آمَنُواْ مَعَكَ مِن قَرْيَتِنَا أَوْ لَتَعُودُنَّ فِي مِلَّتِنَا)

ትርጉሙም(ሕዝቦቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች፡- «ሹዓይብ ሆይ! አንተንና እነዚያን ከአንተጋር ያመኑትን ከከተማችን በእርግጥ እናስወጣችኋለን፡፡ ወይም ወደ ሃይማኖታችን መመለስ አለባችሁ አሉ፡፡) ማለት ነው፡፡
በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በአላህ ትእዛዝ ላይ የተበተ ህዝብ ሁሉ መጨረሻ ጥፋት ነበር፡፡ ምን ይከፋ መጨረሻ፡፡ በዚህ አስቸጋሪ በሽታ የተለከፈ ሰው ከህመሙ ለመዳን ለልቡ ፈውስ ማፈላለግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ፈውስ እንዲሳካ የራሱን ደረጃ ማወቅና ከአፈር ከዚያም ከፍተወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደምና ከስጋ የተፈጠረ መሆኑን አለመርሳት ይኖርበታል፡፡ ማንኛውም ትእቢተኛ ሰው በመጭው ዓለም በነበረበት ተጻራሪ የሚቀጣ መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ትእቢተኞች በትንሳኤ ቀን በሁሉም አቅጣጫ ውርደት ያካበባቸውና የሰው ቅርጽ ያለው ቅንጣት ሆነው ይነሳሉ...) አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{تِلْكَ الدَّارُ الْآخِرَةُ نَجْعَلُهَا لِلَّذِينَ لَا يُرِيدُونَ عُلُوًّا فِي الْأَرْضِ وَلَا فَسَادًا وَالْعَاقِبَةُ لِلْمُتَّقِينَ}.

ትርጉሙም (ይህች የመጨረሻይቱ አገር ለእነዚያ በምድር ውስጥ ኩራትንና ማመፅን ለማይፈልጉት እናደርጋታለን፡፡ ምስጉኒቱም መጨረሻ ለጥንቁቆቹ ናት፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

***

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትና በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ከአላህ (ዐ.ወ.) መንገድ መከልከል ገጽታዎች አንዱ ደግሞ የአንድ ሰው ቃላት የተግባራቱ ተጻራሪ መሆናቸው ነው፡፡ ከዋና አላማዎችና መሰረታዊ ነገሮች ይልቅ ለቅርጽና ለውጫዊ ገጽታ ከፍተኛ ትኩረትና ሙሉ ቅድሚያ የሚሰጡ ሰዎች በትክክለኛው የአላህ መንገድ ላይ አይደሉም፡፡ ምክኒያቱም በርካታ ለውጫዊ ገጽታ ቅድሚያ የሚሰጡ ወገኖች ባሕርያቸውና ስርአታቸው ከእስልምና መመሪያዎች ጋር የሚጻረር በመሆኑ ሰዎች ከሃይማኖቱ እንድደነብሩ ያደርጋልና ነው፡፡ በዚህም ከአላህ መንገድ የተከላከሉና ሃይማኖቱንም የሚጎዱ ይሆናሉ፡፡ እነሱም ነብያችን (ከናንተ መካከል ከሃይማኖት የሚያስደብሩ አሉ፡፡) ከአሏቸው ወገኖች ይካተታሉ፡፡
አንድ ሰው ውጫዊ ገጽታው ሃይማኖተኛ መስሎ ከሰው ጋር በሚዋዋልበት ወቅት በአስከፊ ውሸት፣ ክዳት፣ ክህደትና የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ መብላት ሲዘፈቅ የሚታይ

ከሆነ ነገሩ እጅግ አደገኛ ይሆናል፡፡ ይልቁንም ይህ ሰው ከመናፍቃን ተርታ ይመደባል፡፡ ይህም በአላህ ሃማኖት የሚነግዱት አማፂያን አሸባሪ ቡድኖች ባሕርይ ነው፡፡ እንዚህ ቡድኖች ሽብርን እያስፋፉና እየደገፉ ሳለ ማንኛውንም መንገድ በመከተልና ሁሉንም መዳረሻ የጠፈቀደ በማድረግ በሀገራት በትረ ስልጣኑን ለመጨበጥ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡
እንድሁም ሃይማኖትን በአምልኮትና ለሱም ጥረት በማድረግ ብቻ የሚወስኑ ሃይማኖቱን በተሳሳተ መልኩ የተገነዘቡ ወገኖች በሰዎች ላይ መሳሪያ አንግበው በመነሳታቸው ከአላህ መንገድ ይከለከላሉ፡፡ ኸዋሪጅ በመባል የሚታወቁት ቡድኖች በስግደታቸውና በጾማቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው ሆነው ሳለ በደም ማፍሰስ ወንጀል እንዳይገቡ የሚግዳቸው በቂ የሃይማኖት ህግ እውቀት ባለማካበታቸው በሰዎች ላይ መሳሪያ አንግበው ወጥተው ያልሆነ ውጤት ላይ አድርሷቸዋል፡፡ የእስልምና እምነት የእዝነት ሃይማኖት ነው፡፡ ከእዝነት የሚያርቅ ነገር ሁሉ ከእስልምናም ያርቃል፡፡ የማንኛውም ነገር መመዘኛ ትክክለኛ ስርኣትና ተግባር እንጂ ቃል ብቻ አይደለም፡፡
ጌታችን ሆይ እውነተኛ እውነትን አሳውቀን መከተሉንም አሳካልን፡፡ ግልጽ ከንቱንም አሳውቀን ከሱ መራቅንም አሳካልን፡፡ አሜን፡፡

## (37)

### ንፍቅናና ክዳት እንድሁም በግለሰብና በሀገር ደረጃ የሚያስከትሉት አደጋ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{الْمُنَافِقُونَ وَالْمُنَافِقَاتُ بَعْضُهُمْ مِنْ بَعْضٍ يَأْمُرُونَ بِالْمُنْكَرِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمَعْرُوفِ وَيَقْبِضُونَ أَيْدِيَهُمْ نَسُوا اللَّهَ فَنَسِيَهُمْ إِنَّ الْمُنَافِقِينَ هُمُ الْفَاسِقُونَ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም ( መናፍቃንና መናፍቃት ከፊሎቻቸው ከከፊሉ ናቸው፡፡ በመጥፎ ነገር ያዛሉ ከደግም ነገር ይከለክላሉ፡፡ እጆቻቸውንም (ከልግስና) ይሰበስባሉ፡፡ አላህን ረሱ፡፡ ስለዚህ (እርሱ) ተዋቸው፡፡ መናፍቃን አመጸኞቹ እነሱ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (የምናፍቅ መለያ መልከቶቹ ሦስት ናቸው፡ በሚያወራ ጊዜ ይዋሻል፣ ቃል በገባም ጊዜ በቃሉ አይገኝም፣ አደራ ሲጣልበትም ይከዳል፡፡) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእከተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣

በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

መናፍቅነት መድሃኒት የማይገኝለት በሽታ፣ ገዳይ የሆነ ወረርሽኝና ግለሰብንም ሆነ አጠቃለይ ህዝብን አውዳሚ መሆኑ ጥርጥር የለበተም፡፡ መናፍቅነት እውነተኛ እምነትን የሚበክል፣ መሰረቱን የሚቀንስ፣ ማእዘናቱን የሚያፈራርስ አደገኛ የልብ በሽታ ሲሆን በማህበረሰቡ ጸጥታ፣ ደህንነትና መረጋጋት ላይ የተደቀነ አደገኛ ማህበራዊና ስነ ምግባራዊ ቁስልም ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው ከክህደትና ከማጋራት አደጋ እጅጉን የከፋ ነው፡፡ ምክኒያቱም እሱ በህዝቡ አካል እየተሳበ በገባ ጊዜ የዚህ ተቋም አጥንቱ ይበሰብሳል በሀሳብ መለያየትም ያጠቀዋል፡፡

እንድሁም የከህደትና የቅጥረኝነት ጦርም ታሪክ ከጀመረ አንስቶ በሀገራት ህልውና መኖር ላይ የተጋረጡ አደገኛ ተግዳሮቶች መሆናቸው ይነገራል፡፡ ታሪክ እንደሚመሰክረው አያሌ ሀገራት የተዳከሙት፣ የተበታተኑት ብሎም የተሰወሩት የጥፋታቸውና ውድቀታቸው መንስኤ ከውስጥ የተከሰተ ነበር፡፡ በዚህም ተግባር የከዳተኞችና ቅጣረኞች እንድሁም በሀገራቸው ላይ ሴረኛ ሆነው የሚሰሩ ወገኖች ሚና እጅጉን ከፍተኛ እንደነበር ይነገራል፡፡ ምንጊዜም ከውስጥ በኩል የተደቀኑ አደጋዎች ከውጭ በኩል ከተደቀኑት አስጊነታቸው የከፋ ነው፡፡

እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የሚገባ ነገር ቢኖር መናፍቅነት ከፍተኛና ዝቅተኛ ተብሎ ወደሁለት የሚከፈል መሆኑን ነው፡፡ ከሁለቱ ክፍሎች እጅጉን አደገኛው ከፍተኛ የተባለው የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡ እሱም አንድ ሰው በይፋ ሙስሊምነትን እያሳየ በልቡ ክህደትን የሚሰርጽበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ክፍል ታድያ ባለቤቱ ለዘላለም በገሀነም ይቀጣል፡፡ ብሎም ከሷ በጥልቁ አዘቅጥ ክፍል እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ዝቅተኛ የተባለው መናፍቅነት ሲሆን ተግባራዊ መናፍቅነት በመባል ይታወቃል፡፡ እሱም አንድ ሰው በስነ ምግባር ከመስመር የሚወጣበትና የምናፍቅ መለያ ከሆኑ ተግባራት አንዱን የሚላበስበት ሁኔታ ሲሆን በይፋ ጽድቅናን እያሳየ በልቡ እሱን የሚፃረር ሁኔታን ያሰርፃል፡፡

ይህኛው ክፍል ከሃይማኖቱ ሙሉ በሙሉ አልወጣም፡፡ ይሁን እንጂ ወደከፍተኛ መናፍቀነት በሚያደረስ ጎዳና ላይ እየተጓዘ ነው፡፡ ባለቤቱ በአፋጣን ተጽጽቶ ካልተመለሰ መድረሻው ከፍተኛ መናፍቅነት ይሆናል፡፡

የተከበረው ቁርአንና ንጹሃን ነብያዊ ፈለጎች ስለመናፍቃን፣ ስለባህርያቸው፣ ስለጠባያቸውና ስለተግባራቸውም በሰፊው አውርተውልናል፡፡ እነሱም ጠለቅ ብለን እንደተገነዘብነው በዘመን ርዘመት አልተለወጡም፣ ከሀገር አገር በመለየትም አልተቀየሩም፡፡ ከነዚህ መናፍቃን ከሚለዩባቸው ምልክቶች አጅግ አደገኞቹ፡

ወሸት፣ ቃልን ማፍረስ፣ አደራን መብላትና በክርክር ማጭበርበር የሚሉት ናቸው፡፡ አነሱም ነብያቸውን (ሶ.ዐ.ወ.) ለመናፍቃን የሰጧቸው አጅግ አስከፊ የሆኑ ባሕርዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ባህርዮች ነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት የገለጹዋቸውና ከተግባራዊ መናፍቅነት የሚመደቡት ናቸው፡ (አራት ነገሮች እነሱ በሙሉ ያሉበት

ሰው የተጣራ መናፍቅ ነው፡፡ ከነሱ አንደኛው ምግባር ያለበት አስከሚተወው ድረስ አንድ የመናፍቅነት ምግባር አለበት፡ እምነት ሲጣልበት ይከዳል፣ ሲያወራ ይዋሻል፣ ቃል ሲጋባም ክህደት ይፈጽማል፣ ሲከራከርም ያጭበረብራል፡፡) እነዚህ አራቱ ምግባሮች በሙሉ ወይም ከነሱ አንድ ምግባር ያለበት ሰው መናፍቅ ነው፡፡ እነዚህ ባህርዮች የህዝቡን ጥቅም ከንቱ ያደርጋሉ ያወድሙታልም፡፡ ብዙውን ጊዜ መናፍቅ ሌላው ሰው የቃሉንም ሆነ የተግባሩን አውነተኛነት እንዲያምን ለማድረግ ሲዋሽ እናያለን፡፡ አላህ (አ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَمِنَ النَّاسِ مَن يُعْجِبُكَ قَوْلُهُ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيُشْهِدُ اللَّهَ عَلَى مَا فِي قَلْبِهِ وَهُوَ أَلَدُّ الْخِصَامِ}

ትርጉሙም (ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲሆን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚደንቅህና በልቡ ውስጥ ባለው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አለ፡፡) ማለት ነው፡፡ አላህም በቁርአን መናፍቅነትን፣ ማታለልንና የአደራ ክዳትን በጠቀሰ ጊዜ ውሸትን አብሮ ያነሳወዋል፡፡ እንድህም ይላል፡

يُخَادِعُونَ اللَّهَ وَالَّذِينَ آمَنُوا وَمَا يَخْدَعُونَ إِلَّا أَنفُسَهُمْ وَمَا يَشْعُرُونَ *فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٌ فَزَادَهُمُ اللَّهُ مَرَضًا وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ بِمَا كَانُوا يَكْذِبُونَ}

ትርጉሙም (አላህንና እነዚያን ያመኑትን (ሰዎች) ያታልላሉ፡፡ የማያውቁ ሲሆኑ ነፈፍሳቸቸውን እንጅ ሌላን አያታልሉም፡፡ በልቦቻቸው ውስጥ (የንፍቅና) በሽታ አለባቸው፡፡ አላህም በሽታን ጨመረባቸው፡፡ ለነርሱም ይዋሹ በነበሩት ምክኒያት አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከውሸትና ሌያስከትለው ከሚችለው ጉዳት እንድህ ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡ (አደራ እምላችሁ ከውሸት እንድትርቁ ነው፡፡ ምክኒያቱም ውሸት ወደከህደት ይመራል ከህደትም ወደእሳት ይመራል፡፡ አንድ ሰው አየዋሸና ውሸትንም ሆን ብሎ ኢያከታተለ ሲፈጽም ይኖርና ከአላህ ዘንድ ቀጣፊ ተብሎ ይጻፋል..)

ከእለታትአንድ ቀን ነበይችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ምእምን ሰው ፈሪ ሊሆን ይችላልን? ተብለው በተጠየቁ ጊዜ (አዎን) አሉ፡፡ አንድ ምእምንስ ስስታም ሊሆን ይችላልን? ተባሉ፡፡ እሳቸውም (አዎን) አሉ፡ አንድ ምእምን ዋሾ ሊሆንስ ይችላልን? ተብለው በተጠየቁ ጊዜ (ሊሆን አይችልም) በማለት መለሱ፡፡ አቡ በክር አሲዲቅ ውሸትን ከህደት ነው ብለውታል፡፡ እንድህም ብለዋል ‹እውነት ታማኝነት ነው፡፡ ውሸት ደግሞ ክህደት ነው...›

እንደዚሁም ክህደትና ቅጥረኝነት ለፍቅር ገመደ መበጠስ ምክኒያት አእንደሚሆኑ፣ ወደጭቅችቅና ንትርክ የሚያደርስ ጥላቻ እንደሚፈጥሩና የህዝብን ግንኙነት እንደሚያበላሹ ይነገራል፡፡ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የተጣለበትን አደራ ያልጠበቀ ሰው በትንሳኤ ቀን ውርደትና ጸጸት እንደሚያስከትለበት እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (አላህ የበፊቶቹንም የኋለኞቹንም በሚሰበስብበት በትንሳኤ ቀን ለያንዳንዱ ከዳተኛ ሰንድቅ አላማ ይተክልለትና ይህ የእገሌ ልጅ እገሌ ከህደት ነው በመባል ይለፈፍበታል፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐወ.) በትንሳኤ ቀን የዚህ ከዳተኛ ተከራካሪ አላህ (አ.ወ.) እንደሚሆን እንድህ በማለት አስጠንቅቀዋል፡ አላህ (አ.ወ.) እንድህ አለ፡ (ሦስት ወገኖች በትንሳኤ ቀን እኔ ተከራካሪያቸው እሆናለሁ፡፡ በተትንሳኤ ቀን እኔ ተከራካሪው የሆንኩትን ሰው አሸንፈዋለሁ፡፡ (እነሱም) በእኔ ስም ቃል ኪዳን ግብቶ የከዳ ሰው፡ ጨዋን ሰው ሸጦ ዋገውን የበላ ሰውና ቅጥረኛን ቀጥሮ ሙሉ ጊዜውን አሰርቶ የላቡን ዋጋ የከለከለ ሰው፡፡)
ከክህደት ዓይነቶች እጅግ በጣም አደገኛው የአገር ክህደትና አሸባሪ ቡድኖች፣ ደጋፊዎቻቸውና ሀገረን በመሸጥ የነሱን ፈር የሚከተሉ ወገኖች እንደሚያደርጉት በዚህች ዓለም በሚጠፋ ርካሽ ዋጋ አገርን መሸጥ ነው፡፡
የአስልምና እምነት ከአሰጠነቀቀን ርኩስ ባህርዮች አንዱ በክርክር ጊዜ ማጭበርበር ነው፡፡ ይህ ምግባር የተንኮል ተንኮለ፣ የአርኩስነት ሁሉ መሰረት፣ እውነትን ከንቱ ከንቱን ደግሞ እውነት የሚያደርገው ከእውነት መስመር የሚያወጣ ጎዳና መሆኑን ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡ አላህ (አ.ወ.) በክርክር ማጭበረበርን ብርቱ ሲል ገልጾታል እንድህም ይላል፡
{ وَمِنَ النَّاسِ مَن يُعْجِبُكَ قَوْلُهُ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيُشْهِدُ اللَّهَ عَلَى مَا فِي قَلْبِهِ وَهُوَ أَلَدُّ الْخِصَامِ}

ትርጉሙም (ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲሆን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚደንቅህና በልቡ ውስጥ ባለው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አለ፡፡) ማለት ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን አዒሻ እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ አንድህ አሉ፡ (ከሰዎች ከአላህ ዘንድ እጅጉን የተጠላው ክርክረ ብርቱ የሆነው ነው፡፡) ንፍቅና ያለባቸው ሰዎች ሁኔታቸውን መግለጽ ብንፈልግ ባለሁለት ፊቶች ከሚለው ቃል የተሸለ መግለጫ አናገኝላቸውም፡፡ ብሎም በዘመናችን ያሉ መናፍቃን ይህን ደረጃ በሰፊ መጠን በማለፍ እልፍ አላፍ ፊት ያለቸው ሆነው አናያቸዋለን፡፡ እነሱም ከፍጥረታት እጅግ ተንኮለኞቹ እነሱ ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከሰዎች እጅግ ተንኮለኛው እነዚህን በአንድ ፊት እነዚያን ደግሞ በሌላ ፊት የሚገናኘው ባለ ሁለት ፊት ሰውዬ ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡)

የንፍቅና ምልክቶች
ከመናፍቅነት ምልክቶች አንዱ በምድር ላይ አያበላሽ አሳማሪ ነኝ የሚል መሆኑ ነው፡፡ ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ قَالُوا إِنَّمَا نَحْنُ مُصْلِحُونَ * أَلَا إِنَّهُمْ هُمُ الْمُفْسِدُونَ وَلَكِن لَّا يَشْعُرُونَ}

ትርጉሙም (ለነርሱም በምድር ላይ አታበላሹ በተባሉ ጊዜ እኛ አሳማሪዎች ብቻ ነን ይላሉ፡፡ ንቁ እነሱ አጥፊዎች እነሱው ናቸው፡፡ ግን አያውቁም፡፡) ማለት ነው፡፡ በምድር ማበለሸት የተላያዩ ቅርጾች አሉት፡ በሀገር ውስጥ ሰብቅ ማናፈስ በእውነተኛ ምእምናን መንፈስ ውድቀትን መንዛት፣ መስመር የሳቱ ሀሳቦችንና የተሳሳቱ

ግንዛቤዎችን ማስረጽና ከሰዎች መካከል መከራን ማስፋፋት የሚሉት ይካተቱበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَوْ خَرَجُوا فِيكُمْ مَا زَادُوكُمْ إِلَّا خَبَالًا وَلَأَوْضَعُوا خِلَالَكُمْ يَبْغُونَكُمُ الْفِتْنَةَ وَفِيكُمْ سَمَّاعُونَ لَهُمْ وَاللَّهُ عَلِيمٌ بِالظَّالِمِينَ}

ትርጉሙም (ከናንተ ጋር በወጡ ኖሮ ጥፋትን እንጅ አይጨምሩላችሁም ነበር፡፡ እውከትንም የሚፈልጉላችሁ ሲሆኑ በመካከላችሁ (በማሳበቅ) ይቻኮሉ ነበር፡፡ በናንተም ውስጥ ለነሱ አዳማጮች አሏቸው፡፡ አላህም በዳዮችን አዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

وَقَالُوا لَا تَنْفِرُوا فِي الْحَرِّ قُلْ نَارُ جَهَنَّمَ أَشَدُّ حَرًّا لَوْ كَانُوا يَفْقَهُونَ}

ትርጉሙም (በሐሩር አትሂዱ አሉም፡፡ የገሀነም እሳት ተኳሳነት በጣም የበረታ ነው በላቸው፡፡ የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ (አይቀሩም ነበር)፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{قَدْ يَعْلَمُ اللَّهُ الْمُعَوِّقِينَ مِنْكُمْ وَالْقَائِلِينَ لِإِخْوَانِهِمْ هَلُمَّ إِلَيْنَا وَلَا يَأْتُونَ الْبَأْسَ إِلَّا قَلِيلًا}

ትርጉሙም (ከናንተ ውስጥ የሚያሳንፉትን ለወንድሞቻቸውም ወደኛኑ የሚሉትን ውጊያንም ጥቂትን እንጅ የማይመጡትን በእርግጥ አላህ ያውቃቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም ሌላው የብልሽት ገጽታ የሰዎችን መብት ማጓደልና እነሱንም ማንኳሰስ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تَعْثَوْا فِي الْأَرْضِ مُفْسِدِينَ}

ትርጉሙም (ሰዎችንም እንዳቶቻቸውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉድሉባቸው አመጠኞች ሆናችሁ በምድር ላይ አታበላሹ፡፡) ማለት ነው፡፡ ሌሎቹ የንፍቅና ገጽታዎች ደግሞ ማፍረስ፣ ማበላሸት፣ ንጹሃንን መግደል፣ በጸጥታ የሚኖሩ ሰዎችን ማሸበር፣ የሰዎችን ጉዳይ ማስተጓጎል፣ ሃላፊነትን አለመወጣት፣ እንድሁም ኪራይ ሰብሳቢነት፣ በወገን ወይም በዕውቂያ ሰዎችን ማስቀደምና የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ መብላት የሚሉት ናቸው፡፡

እንድሁም ከንፍቅና መለያዎች አንዱ አምልኮ (ዒባዳ) በሚያደረሱ ጊዜ በተለይም የተከበሩ ኢባዳዎች ሲፈጽሙ መስነፍና በሚያከናውኑም ጊዜ ይዩልኝ ይስሙልኝ አቀላቅሎ መፈጸም የሚለው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الْمُنَافِقِينَ يُخَادِعُونَ اللَّهَ وَهُوَ خَادِعُهُمْ وَإِذَا قَامُوا إِلَى الصَّلَاةِ قَامُوا كُسَالَى يُرَاءُونَ النَّاسَ وَلَا يَذْكُرُونَ اللَّهَ إِلَّا قَلِيلًا}

ትርጉሙም (መናፍቃን አላህን ያታልላሉ፡፡ እሱም አታላያቸው ነው (ይቀጣቸዋል)፡፡ ወደሶላትም በቆሙ ጊዜ ታካቾች፣ ሰዎችን የሚያሳዩ ሆነው ይቆማሉ፡፡ አላህንም ጥቂትን እንጅ አያወሱም፡፡) ማለት ነው፡፡

{ وَمَا مَنَعَهُمْ أَن تُقْبَلَ مِنْهُمْ نَفَقَاتُهُمْ إِلَّا أَنَّهُمْ كَفَرُوا بِاللَّهِ وَبِرَسُولِهِ وَلَا يَأْتُونَ الصَّلَاةَ إِلَّا وَهُمْ كُسَالَىٰ وَلَا يُنفِقُونَ إِلَّا وَهُمْ كَارِهُونَ}

ትርጉሙም(ልግሰናዎቻቸውን ከነሱ ተቀባይ የሚያገኙ ከመሆን እነሱ በአላህና በመልክተኛው የካዱ ሶላትንም እነሱ ታካቾች ሆነው በስተቀር የማይሰግዱ እነሱም ጠይዎች ሆነው በስተቀር የማይሰጡ መሆናቸው እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ከፈጅርና ከዒሻ ሶላቶች የበለጠ ለምናፍቃን እጅግ ሸክም የሆነ ስግደት የለም፡፡ በነሱ ያለውን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እያዳሁም እንኳ ቢሆን ወደነሱ ይሄዱ ነበር፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር አብን አብደላህ እንድህ ብለዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን ወጡና እንድህ አሉ፡ (እናንተ ሰዎች ሆይ! አደራችሁን የምስጢር መጋራትን እራቁ፡፡) ባልደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! መስጢራዊ መጋራት ማለት ምን ማለት ነው? ሲሉ ጠየቁ፡፡ አሳቸውም (አንድ ሰው ለስግደት ይቆምና ሰዎች ወደሱ የሚመለከቱ መሆኑን ያያል ያን ጊዜም ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ሶላቱን ያሳምራል፡፡ ያም ነው ምስጢራዊ ማጋራት ማለት፡፡) አሉ፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

ከመናፍቅነት መለያዎችና ምልክቶች ሌላው ደግሞ ጠላት ጋር ቃል ኪዳን መጋባትና በስለላ፣ በከህደት፣ ወሬና መረጃ በማስተላለፍና የሀገርን መስጢር በማጋለጥ ሃይማኖትና አገርን አራክሶ ከነሱ ጋር ግንኙነት መፍጠር ነው፡፡ መናፍቅ በቤተሰቦቹ፣ ጎረቤቶቹና ዘመዶቹ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ወደጎን በመተው የሀገሩን ጠላት የሚደግፍ ቅጥረኛ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَتَرَى الَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٌ يُسَارِعُونَ فِيهِمْ يَقُولُونَ نَخْشَىٰ أَن تُصِيبَنَا دَائِرَةٌ فَعَسَى اللَّهُ أَن يَأْتِيَ بِالْفَتْحِ أَوْ أَمْرٍ مِّنْ عِندِهِ فَيُصْبِحُوا عَلَىٰ مَا أَسَرُّوا فِي أَنفُسِهِمْ نَادِمِينَ}

ትርጉሙም (እነዚያንም በልቦቻቸው ውስጥ (የንፍቅና) በሽታ ያለባቸውን ሰዎች የጊዜ መለዋወጥ እንዳያገኘን እንፈራለን የሚሉ ሲሆኑ በነርሱ (ለመረዳት) ሲቻኮሉ ታያቸዋለህ፡፡ አላህም ድል መንሳትን ወይም ከርሱ ዘንድ የሆነን ነገር (ማጋለጠን) ሊያመጣ በነፍሶቻቸው ውስጥ በደበቁትም ነገር ተጸጻቾች ሲሆኑ ተረጋገጠ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَإِنَّ مِنْكُمْ لَمَنْ لَيُبَطِّئَنَّ فَإِنْ أَصَابَتْكُمْ مُصِيبَةٌ قَالَ قَدْ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيَّ إِذْ لَمْ أَكُنْ مَعَهُمْ شَهِيدًا * وَلَئِنْ أَصَابَكُمْ فَضْلٌ مِنَ اللَّهِ لَيَقُولَنَّ كَأَنْ لَمْ تَكُنْ بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُ مَوَدَّةٌ يَا لَيْتَنِي كُنْتُ مَعَهُمْ فَأَفُوزَ فَوْزًا عَظِيمًا}

ትርጉሙም (ከእናንተም ወስጥ በእርግጥ (ከዘመቻ) ወደኋላ የሚንጓደድ ሰው አለ፡፡ አደጋም ብታገኛችሁ ከነሱ ጋር ተጣጅ (የተገኘሁ) ባልሆንኩ ጊዜ አላህ በእኔ ላይ በእርግጥ ለገሰበኝ ይላል፡፡ ከአላህም የሆነ ችሮታ ቢያገኛችሁ በናንተና በርሱ መካከል ፍቅር እንዳልነበረች ሁሉ ታላቅ እድልን አገኝ ዘንድ ከነሱ ጋር በሆንኩ ወይ ምኞቴ ይላል፡፡) ማለት ነው፡፡ መናፍቅ በሀገርና በህዝብ ላይ መከራ ሲደርስ፣ ችግር ሲስፋፋ፣ በሽታ ሲበዛና ልብ የሚሰብር ነገር ሲከሰት ይደሰታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنْ تَمْسَسْكُمْ حَسَنَةٌ تَسُؤْهُمْ وَإِنْ تُصِبْكُمْ سَيِّئَةٌ يَفْرَحُوا بِهَا وَإِنْ تَصْبِرُوا وَتَتَّقُوا لَا يَضُرُّكُمْ كَيْدُهُمْ شَيْئًا إِنَّ اللَّهَ بِمَا يَعْمَلُونَ مُحِيطٌ}

ትርጉሙም (ደግ ነገር ብታገኛችሁ ታስከፋቸዋለች፡፡ መጥፎም ነገር ብታገኛችሁ በርሷ ይደሰታሉ፡፡ ብትታገሱና ብትጠነቀቁም ተንኮላቸው ምንም አይጎዳችሁም፡፡ አላህ በሚሰሩት ሁሉ (በዕውቀቱ) ከባቢ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

ይሁን እንጂ አዳድስ መናፍቃን እንደ ውሸት፣ ከህደት፣ ከዳት፣ ቃልን ማፍረስና የህዝብን ሀሳብ ማመሰቃቀል ከሚሉት ከዚህ በፊት ከነበሩት የመናፍቃን መለያዎች አዳድስ የከህደት ዓይነቶች ጨምረዋል፡፡ ከነሱም መካከል በቅድሚያ የሚጠቀሰው በሃይማኖት መነገድ የሚለው ይሆናል፡፡ አንዳንድ ቡድኖች በርካታ የቅርጽና የፖሊቲካ ሃይማኖተኛነትን ተጎናጽፈው ሃይማኖትን ኮርቻ በማድረግ ወደስልጣን ለመውጣት በሃይማኖት ይነግዳሉ፡፡ እሱንም ለተጠቀሰው አላማቸው መሳካት መገልገያ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡

እነዚህ ቡድኖች አምነትን ለራሳቸው ያደርጉና ሌላውን እምነተ ቢስ በማድረግ ሃይማኖትን ለተንኮላቸው ህጋዊ መከለያ ያደርጋሉ፡፡ እነሱም ሀገርን በመካድ፣ በማራከስና በቀላል ዋጋ በመሸጥ ይታወቃሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) እነዚህ ሰዎች የሚጋለጡበት ቀን እንዳለና በዚህች አለምና በመጭውም አለም የአላህ ቁጣ እንደማይለያቸው እንድሁም በሙስሊሞች ላይ ችግርና መከራ ለማድረስ የሚጠነስሱት ሴራ በራሳቸው ላይ እንደሚመለስ እንድህ በማለት ዝቶባቸዋል፡

{وَلَا يَحِيقُ الْمَكْرُ السَّيِّئُ إِلَّا بِأَهْلِهِ}

ትርጉሙም (ከፉ ተንኮልም በባለቤቱ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይሰፍርም፡፡)

አላህ (ሱ.ወ.) የታላቁ ንፍቅና ባለቤቶችን በመወላወልና አለመረጋጋት እንድሁም በፍርሃትን በታላቅ ድንጋጤ የቀጣቸው መሆኑን እንድህ በማለት ገልጧል፡

{مُذَبْذَبِينَ بَيْنَ ذَلِكَ لَا إِلَى هَؤُلَاءِ وَلَا إِلَى هَؤُلَاءِ وَمَنْ يُضْلِلِ اللَّهُ فَلَنْ تَجِدَ لَهُ سَبِيلًا}

ትርጉሙም (በዚህ መካከል ወላዋዮች ሆነው (ያሳያሉ) ወደነዚህም ወደነዚያም አይደሉም። አላህም ያሳሳተውን ሰው ለርሱ (የቅንነት) መንገድን በፍጹም አታገኝለትም።) ማለት ነው። እንድሁም እንድህ ብሏል፡

{ يَحْسَبُونَ كُلَّ صَيْحَةٍ عَلَيْهِمْ هُمُ الْعَدُوُّ فَاحْذَرْهُمْ قَاتَلَهُمُ اللَّهُ أَنَّى يُؤْفَكُونَ}

ትርጉሙም (ጩኸትን ሁሉ በነሱ ላይ ነው ብለው ያስባሉ። እነሱ ጠላቶች ናቸውና ተጠንቀቃቸው። አላህ ይጋደላቸው (ከእምነት) እንዴት ይመለሳሉ።) ማለት ነው። እነዚህ መናፍቃን አላህ (ሱ.ወ.) ልባቸውን ስለአላህና መልክተኛው እንዳያውቁ ያዞረው በመሆኑ ቅንነት ወደልባቸው አይደርስም፣ ወደሱም ደግ ነገር አይሰርግም። አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

ذَلِكَ بِأَنَّهُمْ آمَنُوا ثُمَّ كَفَرُوا فَطُبِعَ عَلَى قُلُوبِهِمْ فَهُمْ لا يَفْقَهُونَ}

ትርጉሙም (ይህ እነሱ (በምላስ) ያመኑ ከዚያም (በልብ) የካዱ በመሆናቸው ነው። በልቦቻቸውም ላይ ታተመባቸው። ስለዚህ እነሱ አያቁም።) ማለት ነው። በመጨው ዓለም ስለሚጠብቃቸው ቅጣት አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمِمَّنْ حَوْلَكُمْ مِنَ الْأَعْرَابِ مُنَافِقُونَ وَمِنْ أَهْلِ الْمَدِينَةِ مَرَدُوا عَلَى النِّفَاقِ لَا تَعْلَمُهُمْ نَحْنُ نَعْلَمُهُمْ سَنُعَذِّبُهُمْ مَرَّتَيْنِ ثُمَّ يُرَدُّونَ إِلَى عَذَابٍ عَظِيمٍ}

ትርጉሙም (በዙሪያችሁ ካሉቱት ከዐረብ ዘላኖች መናፍቃን አሉ። ከመዲና ሰዎችም በንፍቅና ላይ በማመጿ የዘወተሩ አሉ። አታውቃቸውም እኛ እናውቃቸዋለን። ሁለት ጊዜ እንቀጣቸዋለን። ከዚያም ወደታላቁ ቅጣት ይመለሳል።) ማለት ነው። የመጀመሪያው ቅጣት በዚህች ዓለም ሲሆን ሁለተኛው ቅጣት በመቃብር ነው። ታላቁ ቅጣት ደግሞ በመጭው ዓለም ይሆናል። አላህ (ሱ.ወ.) መናፍቃንና መሰል ተንኮለኞችን በገሀነም የሚያሰባስባቸው መሆኑን እንድህ በማለት ይገልጻል፡

{إِنَّ اللَّهَ جَامِعُ الْمُنَافِقِينَ وَالْكَافِرِينَ فِي جَهَنَّمَ جَمِيعًا}

ትርጉሙም ( አላህ መናፍቃንንና ከሃዲዎችን በሙሉ በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነው።) ማለት ነው። እንድሁም እንድህ ይላል፡
إِنَّ الْمُنَافِقِينَ فِي الدَّرْكِ الْأَسْفَلِ مِنَ النَّارِ وَلَنْ تَجِدَ لَهُمْ نَصِيرًا * إِلَّا الَّذِينَ تَابُوا وَأَصْلَحُوا وَاعْتَصَمُوا بِاللَّهِ وَأَخْلَصُوا دِينَهُمْ لِلَّهِ فَأُولَئِكَ مَعَ الْمُؤْمِنِينَ وَسَوْفَ يُؤْتِ اللَّهُ الْمُؤْمِنِينَ أَجْرًا عَظِيمًا.{

ትርጉሙም (መናፍቃን በእርግጥ ከእሳት በታችኛው አዘቅጥ ውስጥ ናቸው። ለነሱም ረዳት አታገኝላቸውም። እነዚያ የተመለሱ (ሥራቸውን) ያሳመሩም በአላህም የተጠበቁ ሃይማኖታቸውንም ለአላህ ፍጹም ያደረጉ ሲቀሩ። እነዚህስ ከምእምናን ጋር ናቸው። ለመእምናንም አላህ ታላቅን መንዳ በእርግጥ ይሰጣል።) ማለት ነው።

የአገረን ደህንነት ለመጠበቅና ህልውናውን፣ ውህደቱንና ሰላሙን ለማስከበር በግልም ሆነ በተቋም ደረጃ ዘብ የቆሙ ፍጹም ታማኝና መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑት የሀገር ልጆች አይን ንቁ ሊሆን ይገባል፡፡ የከሃዲና ቅጥረኞችን ከጠላት ጋር ግንኙነት የፈጠሩ አድመኞችን መጨረሻ ለመቁረጥ፣ እነሱንም በአደባባይ ለማጋለጥ፣ በከህደትና ቅጥረኝነት ለመሳተፍ ለሚያስብ ሁሉም መቀጣጫ እንድሆኑ ለማድረግ የክቡራን ርብርብ አጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህውም ሃማኖታችንን፣ አገራችንን፣ ክብራችንን፣ ህይወታችንን አንድሁም የሀገራችንና የልጆቻችን የወደፊት እጣ ፋንታ ለመጠበቅ ከዚያም ሁሉ በፊት ደግሞ የጌታችንን ውዴታ ለማግኘት ነው፡፡ እንድሁም የካሃድዎችና ሴረኞችን ሁኔታ እንደቀላል በማየት መከራ እንደረሰባቸው አገሮች እንዳትሆን አገራችንንም ለመጠበቅም ጭምር ሲሆን የሀገር ታሪክ እንደቀላል ሊታይ አይገባም፡፡
ጌተችን ሆይ! ልቦቻችንን ከንፍቅና፣ ዓይኖቻችንን ከክህደት፣ ምላሶቻችንንም ከውሸት አጥራለን ገብጽና ነዋሪዎቹዋንም ጠብቅ፡፡

# (38)

## የኢባዳዎችና የበጎ ሥራዎችን ወራት አጋጣሚ በሚገባ መጠቀም

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَسَارِعُوا إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّمَاوَاتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ * الَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي السَّرَّاءِ وَالضَّرَّاءِ وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡ ለእነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም ገቺዎች ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)፡፡ አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (አንድም በአላህ ባሮች ላይ የሚነጋ ሌሊት የለም ሁለት መልኣኮች ወርደው አንደኛው ፡ ጌታዬ ሆይ ለጋሽን ሰው በለገሰው ነገር ምትክ ስጠው ሌላኛው ደግሞ ጌታዬ ሆይ ግነዘቡን ጨምድዶ ያዘን ሰው ጥፋትን ፍረድበት የሚሉ ቢሆን እንጂ)፡፡ ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ!

በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**
አላህ (ዐ.ወ.)ባሮቹ ዘወትር ወደሱ ለመቃረብ እንድጥሩና ወደሱ መዞራቸውንም እንዲያሳምሩ ለመገፋፋት ከዘመን ቀናት የመልካም ሥራ ምንዳ እጥፍ ድርብ የሚሆኑባቸው፣ በጎ ነገሮች የሚበዙባቸውና ደረጃዎች ከፍ የሚሉባቸው ወራቶችን በመለየት አስቀምጧል፡፡ ልበኛ ሰው ሊባል የሚገባው የነዚህን ወራቶች መልካም አጋጣሚ በሚገባ ለመጠቀም ሀሳብን ያጠራ፣ በነሱም ሥራውን ያሳመረ፣ ወደጌታው አላህ (ዐ.ወ.) በመመለስ በጎሥራዎችን ያበረከተና የአላህ እዝነትና ርህራሄ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግ ሰው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለጌታችሁ በዘመናችሁ ቀናት የእዝነት ጊዜያት አሉት፡፡ እነሱንም ለማግኘት ጥረት አድርጉ፡፡ ምናልባትም አንዳችሁ ከነሱ አንድ ጊዜ እዝነት ያጋጥመውና ከሱ በኋላ መንገዜም መናጢነት የሚባል ነገር ላያጋጥው ይችላልና፡፡)
እነዚህ አሁን ያለነባቸው ቀናት መንዳቸው እጅግ ታላቅና ደረጃው በጣም ከፍተኛ ከሆኑት የመልካም ሥራ ወራቶች በመጀመሪያ የሚጠቁሱት መሆናቸው ጥርጥር የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) በነዚህ ቀናት የሚፈጸሙ ዒባዳዎች ከነሱ ሌላ ባሉ ቀናት ከሚከናወኑት በሰፊው እንድበልጡ አድርጓል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ወቅት ቀናቱን የተከበሩና ጊዜያቱንም የላቁ አድርጓል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አላህ (ሱ.ወ.) የነዚህን ቀናት ትሩፋትና ታላቅ ደረጃቸውን በተከበረው መጸሐፉ የማለባቸው በመሆኑ ገልጾልናል ሲሉ ማብራራታቸውን ሊቃውንት ጠቁመዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَالْفَجْرِ * وَلَيَالٍ عَشْرٍ * والشفع والوتر}

ትርጉሙም (በጎህ እምላለሁ፡፡ በዐሥር ሌሊቶችም፡፡ በጥንዱም በነጠላውም፡፡) ማለት ነው፡፡
ብዙኃን የቅዱስ ቁርአን ተንታኞች ዐሥር ሌሊቶች የተባሉት የዙልሒጃ መጀመሪያ ዐሥር ቀናት በመሆናቸው አንድ አቋም ወስደዋል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ደግሞ በታለቅ ነገር እንጂ የመሃላ ቃል አያሰፍርም፡፡ በነዚህ ቀናት የመሃላ ቃል ማስፈሩም የተከበሩ መሆናቸውንና ደረጃቸው የላቀ መሆኑን ለመግለጽ፣ በላጭነታቸውን ለማብራራትና አበይትነታቸውን ለመጠቆም ነው፡፡ ከነዚህ ቀናት ትሩፋት መካከል አላህ (ዐ.ወ.) የታወቁ ቀናት ሲል የገለጻቸው መሆኑን ነው፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

{وَيَذْكُرُوا اسْمَ اللَّهِ فِي أَيَّامٍ مَعْلُومَاتٍ عَلَى مَا رَزَقَهُمْ مِنْ بَهِيمَةِ الْأَنْعَامِ}

ትርጉሙም (ለእነሱ የሆኑ ጥቅሞችን ይጣዱ ዘንድ በታወቁ ቀኖችም ውስጥ ከለማዳ እንስሳዎች በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ያወሱ ዘንድ (ይመጡሃል)) ማለት ነው፡፡ በነዚህ ቀናት ለማንኛውም ሙስሊም እንደ ስግደት፣ መጽዋት፣ ጾምና ሓጅ ያሉ ተላላቅ ዒባዳዎች የሚካተቱ ሲሆን ከነሱ ሌላ ባሉ ቀናት በእንድ ላይ አይሰባሰቡም፡፡

ከነዚህ ቀናት ትሩፋት ሌላው ደግሞ አላህ የሚወዳቸው ቃናት መሆናቸውና በጎ ሥራም ከነሱ ሌላ ካሉት ቀናት በጎ ሥራዎች የበለጠ አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ የተወደዱ መሆናቸው ሲሆን እነሱም የትርፍ ወራት፣ የስኬት ጎዳናና የበጎ ሥራ መሽቀዳደሚያ አደባባይ ናቸው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከነዚህ ቀናት  የበለጠ በነሱ መልከም ሥራ አላህ ዘንድ አጅግ የሚወደድባቸው ቀናት የሉም፡፡) የዙል ሒጃ ዐሥር ቀናትን ማለታቸው ነበር፡፡ ያን ጊዜም ባልደረቦች  የአላህ መልክተኛ ሆይ! በአላህ መንገድ ከመወጋትም? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (-አዎ- በአላህ መንገድ ከመዋጋትም አንድ ገንዘቡንና ሕይወቱን ሰዉቶ የወጣና ከነሱም በምንም ያልተመለሰ ሰው ሲቀር፡፡) በማለት መለሱ፡፡ በመሆኑም ማነኛውም ሙስሊም በተለያዩ የዒባዳ ዓይነቶች ወደአላህ (ዐ.ወ.) በመቃረብ የዚህን ታላቅ ትርፍና ሰፊ ምንዳ መልካም አጋጣሚ በተገቢው መልኩ ሊጠቀምበት ይገባል፡፡
በነዚህ ቀናት የአላህ ባሮች ወደአላህ (ዐ.ወ.)ሊቃረቢባቸው ከሚችሉ ዒባዳዎች መካከል የገንዘብና የአካል አቅም ለአለው ሰው የሓጅን ሥራ ማድረሱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ٱلْحَجُّ أَشْهُرٌ مَّعْلُومَاتٌ فَمَنْ فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي ٱلْحَجِّ}

ትርጉሙም (ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፡፡ በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም፡፡) ማለት ነው፡፡ ሓጅን ማድረስ ከእስልምና ማእዘናት አምስተኛው ማእዘን መሆኑ ይታወቃል፡፡ በሱም ነገሮች ይሟላሉ፣ ኃጢአቶች ይማራሉ አንድሁም በነሱ ለአንድ የአላህ ባሪያ አድስ ልደት ይከተብለታል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሴትን መገናኘትና ማመጸንም ሳይፈጽም ሐጆን የሰራ ሰው እናቱ እንደወለደችው ቀን ሆኖ ይመለሳል፡፡)
ሐጅ ትሩፋትንና የላቀ ሥነ መግባርን ለመማር ታላቅ አጋጣሚ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ሙስሊም በአላህ ፍራቻ ይታነጻል፣ የመንፈሱን ተፈጥሯዊ ፍላጎትና ስሜቷን መቆጣጠርም ይችላል፡፡ እንደከራስ ሰዎችን ማስቀደም፣ ጥብቅነትና ከውርደት መራቅን የመሳሰሉ ሥነ ምግባርን ይማራል፡፡ እንዲሁም በዚህ አጋጣሚ አንድ ሙስሊም በስራና በቃል ጥንቁቅነትና ሥነ ስርአትን ይማራል፡፡ አንድ የሀጅን ሥራ የጀመረ ሰው የሐጅ ሥነ መግባራዊና ስርአዊ ይዘቶቹ እንዲሟሉለት የአስልምና እምነት መሰረታዊ መመሪያ የሆኑትን እሴቶችና ሥነ ምግባርት እውን ማድርግ ይጠበቅበታል፡፡
እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የሚገባ ነገር ቢኖር የሐጅ ዒባዳ ለአለም ሁሉ የሚተላለፍ የሠላም መልእክት መሆኑን ነው፡፡ ሐጅ በአጠቃላይ መልኩ ጸጥታን፣ ሰላምንና ደህንነትን ያቀፈ ዒባዳ ነው፡፡ አንድ የሀጅን ሥራ የጀመረ ሰው አይጠቃጨቅም፣ አይከራከርም፣ አውሬንም አንድደነብር አያደርግም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لا تَقْتُلُوا الصَّيْدَ وَأَنْتُمْ حُرُمٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንት በሐጅ ሥራ ውስጥ ስትኾኑ አውሬን አትግደሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

በነዚህ ቀናትና በዚህ ቦታ የሰው ልጅ ሰላም እንሰሳትንም አልፎ እጽዋትንም ያካትታል፡፡ አንድ በሐጅ ሥራ ውስጥ ያለ ሰው ከእጽዋትም ጋር ሰላም እንድፈጥር ተዟል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ሀገር እርም አድርጎታል፡፡ እሾኩ አይቆረጥም፣ በአውሬውም ጉዳት መድረስ አይፈቀደም፡፡ እንድህም ወድቆ የተገነ ነገር ባለቤቱን ለማፈላለግ እንጂ አይነሳም፡፡) ይህም ለአንድ ሙስሊም ከሐጅ ከተመለሰ በኋላ በሰዎች፣ በዛፍና በደንጋይም ላይ ተንኮል እንዳይፈጽም ልዮ ግንዛቤ እንድቀስም ያደርጋል፡፡

እውነተኛ ሙስሊም ማለት የሰው ልጅ ከምላሱም ሆነ ከእጁ ተንኮል የዳነ ሰው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በመጨረሻ በአደረጉት ድስኩር እንድህ ይላሉ፡ (ንቁ ሙእሚን ማለት ማን እንደሆነ ልንገራችሁን? ሰዎች በገንዘባቸውና በሕይወታቸው እምነት የጣለቡት ሰው ነው፡፡ ሙስሊም ማለት ደግሞ በሰዎች ላይ በምላሱም ሆነ በእጁ ተንኮል የማይፈጽም ሰው ነው፡፡ የሃማኖት ተጋዳይ ማለት ደግሞ ለአላህ ታዛዥ እንድትሆን መንፈሱን ተጋድሎ ያሸነፈ ሰው ነው፡፡ የሃይማኖት ስደተኛ ማለት ደግሞ ኃጢአትና ወንጀልን የተወ ሰው ነው፡፡)

አንድ የአላህ ባሪያ ወደጌታው ከሚቃረብባቸው በላጭ ሥራዎች መካከል በነዚህ የተባረኩ ቀናት ጾምን መጾም ይካተታል፡፡ ጾም ከበላጭ ዒባዳዎችና ከአላህ መቃረቢያ ታላቅ ዒባዳዎች አንዱ ነው፡፡ የጾም ደረጃ ከፍተኛ በመሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) የራሱ እንድሆን ገልጧል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በተናገሩት የቁድስ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡ (የአደም ልጅ ሥራ ሁሉ የራሱ ነው፡፡ ከጾም በስተቀር፡ ፡ አሱማ የኔ ነው እኔ በሱ ባሪያን እመነዳለሁ፡፡) አንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (በአልህ መንገድ አንድን ቀን የጾመ ሰው አላህ (ሱ.ወ.) ከፊቱና ከገሀነም መካከል የሰባ ወራት ጉዞ እርቀት ያህል ያራርቃል፡፡) በመሆኑም አንድ ሙስሊም በነዚህ በዘጡኙ የዙልሒጃ መጀመሪያ ቀናት የተቻለውን ያህል ሊጾም ይገባል፡፡ በተለይም ደግሞ የሐጅ ሥራ ላልያዝ ሰው የዐረፋን ቀን መጾም በጣም የተወደደ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የዐረፋን ቀን መጾም አላህ አንድ ያለፈውን አንድ ዓመትና የቀጣዩን አንድ ዓመት ወንጀል እንደሚያስምር ተስፋ ይደረጋል፡፡)

የዐረፋ ቀን አላህ (ዐ.ወ.) በባሮቹ ላይ እዝነት፣ ምህረትና ከእሳት ነፃነት መሆንን የሚቸርበት ታላቅ ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን አላህ ጸሎትን ይቀበላል፡፡ ለስህተቶችም ምህረት ያደርጋል፡፡ በዚህ ቀን አላህ በምድር ነዋሪዎች ያለውን ኩራት ለሰማያት ነዋሪዎች ይነግራል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከዐረፋ ቀን የበለጠ አላህ ባሪን ከእሳት ነፃ የሚያደርግበት አንድም ቀን የለም፡፡ እሱም ይቀርብና -በእዝነቱ- በነሱም በመልኣኮች ላይ ይፎክራል፡፡) ይህ ቀን አላህ በሱ እምነትን ምሉእ እንድሁም ተድላን የተሟላ ያደረገበት ቀን ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ለኡመር ኢብን አልኸጣብ ከእለታትአንድ ቀን አንድ አይሁድ እንድህ አላቸው፡ ‹የምእምናን አዛዥ ሆይ! አንድት አንቀጽ በመጻሐፋችሁ የምታነቧት አለች፡፡ በኛ በአይሁዳዊያን ላይ

ብትወርድ ኖሮ ያን የወረደችበትን ቅን የሚከበር በአል ባደረግነው ነበር፡፡› እሳቸውም የትኛዋን አንቀጽ ማለትህ ነው? በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም እንድህ የምተለውን አንቀጽ ማለቴ ነው አለ፡

{الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الإِسْلاَمَ دِينًا}

ትርጉሙም (ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡) ማለትነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አለ ኸጣብ (ያነን ቀን በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ላይ የወረደችበትንም ቦታ አውቀነዋል፡፡ እሱም በዐረፋ ቁመው እያሉ ዓርብ ቀን ነበር፡፡) አሉ፡፡

ማንኛውም ሙስሊም በነዚህ ቀናት አላህ (ዐ.ወ.)ን በሰፊው ሊያወሳ ይገባል፡፡ አላህን ማውሳት የልብ ሕይወት ሲሆን በሱም እርጋታ ይገኛል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُمْ بِذِكْرِ اللَّهِ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ}

ትረጉሙም((እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡) ነብያችንም እንድህ ይላሉ፡ (ከነዚህ ዐሥር ቀናት የበለጠ አላህ ዘንድ እጅግ ተላላቅ የሆኑ አንድሁም እሱ ዘንድ በነሱ በጎ ሥራ እጅጉን የተወደደ የሆኑ ቀናት የሉም፡፡ በነሱም ተህሊልን፣ ተክቢርንና ተሕሚድን አብዙ፡፡) ሰይድና ዑመር ሚና ውስጥ በማረፊያ ቦታቸው ተቀምጠው ሲከብሩ በመስጊድና በገበያም ያሉ ሰዎች ይሰሟቸውና አብረዋቸው ሲከብሩ የሚና ክልል በተክቢራ ይናወጥ እንደነበር ተወርቷል፡፡ አብን ኡመርም እንደዚሁ ሚና ወስጥ ከስገደት በኋላ፣ በምንጣፋቸው ተኝተውና በሚቀመጡበትና በመሄዱበትም ቦታ ይከብሩ እንደነበር ታውቋል፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ሙስሊም በነዚህ ቀናት የአላህን ታላቅነት በመግለጽ ድምጹን ከፍ አድርጎ ተክቢራ ማለት የተወደደ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ንቁ ከስራችሁ ሁሉ የበለጠ የሆነውን፣ በደረጃም ከፍ ያለውን፣ እንጉሳችሁ ዘንድ የጠራ የሆነውን፣ ለናንተም ወርቅና በር ከመለገስም የበለጠ የሆነውን፣ ጠላታቶቻችሁን አግኝታችሁ አንገቶቻቸውን ከመምታትና አንገቶቻችሁን ከሚመቷችሁ የሚበልጠውን ተግባር ልንገራችሁን?) ባልደረቦችም አዎን ይንገሩን አሉ፡፡ እሳቸውም (አላህን (ሱ.ወ.) ማውሳት ነው በማለት መለሱ፡፡ ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዝ ኢብን ጀበል እንድህ ብለዋል፡ ‹ለአንድ ሰው አላህ (ዐ.ወ.)ን ከማውሳት በተሻለ መልኩ ከአላህ ቅጣት በከፍተኛ ደረጃ ሊያድነው የሚችል ሥራ የለም፡፡

ይህ ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

በነዚህ ቀናት እንድ የአላህ ባሪያ ወደጌታው ከሚቃርብባቸው ተላላቅ ሥራዎች አንዱ ኡድሒያ ማረድ ነው፡፡ ኡድሑያ ማረድ ከአላህ (ዐ.ወ.) ሃይማኖት ምልከቶች አንደኛው፣ የኢብራሂማዊ እመነት መለያና የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈለግ ማስረጃ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

(ذَٰلِكَ وَمَنْ يُعَظِّمْ شَعَائِرَ اللَّهِ فَإِنَّهَا مِنْ تَقْوَى الْقُلُوبِ)

ትርጉሙም(ነገሩ) ይህ ነው፡፡ የአላህንም የሃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የኾነች ጥንቃቄ ናት፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለኡድሒያ ተጠይቀው መልስ ሲሰጡ እንድ ብለዋል፡ (የአባታችሁ የኢብራሂም ፈለግ ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የሰው ልጅ በነሕር ቀን ከሚሰራቸው መልካም ስራዎች እርድ ከመጣል አላህ ዘንድ እጅግ የተወደደ የለም፡፡ እሱም በትንሳኤ ቀን ከነቀንዱ፣ ከነጸጉሩና ከነሸኮናው ይመጣል፡፡ የእርዱ ደም ከምድር ከማረፉ በፊት አላህ ዘንድ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያርፋልና በመልካም መንፈስ አበርክቱት፡፡)

የኡድሑያ እርድ መፈቃቀር፣ መተዛዘንና ከማህበረሰቡ አባላት መካከል ጠንከራ ትስሰር እንድኖር የሚያደርገው የማህበራዊ ትብብር ገጽታ አንዱ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በህዝቡ ዘንድ ችግር መስፋፋቱን ባዩ ጊዜ እንድህ አሉ፡ (ከናንተ መካከል የኡድሒያ አርድ የጣለ ሰው ከሱ ምንም ነገር እያለ ሦስተኛ ቀን እንዳይነጋበት፡፡) በቀጣዩ ዓመት ሰዎች የአላህ መልክተኛ ሆይ ባለፈው ዓመት እንዳደረግነው እናደርግን? ሲሉ ጠየቁ፡፡ አሳቸውም (ብሉ ለድሃ ምጽዋትም ስጡ ከፊሉንም አስቀምጡ፡፡ በዚያ ዓመት ችግር ነበርና በኡድሒያው ሰዎችን እንድታግዙ አስቤ ነበር፡ ፡) አሉ፡፡

ይህን ማለትም በሀገር ችግር ከሌለና ምግብ በተትረፈረፈ ጊዜ (ብሉ አብሉም ከፊሉንም አስቀምጡ) የሚለው የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሐዲስ ተቀዳሚ ሲሆን በሀገር ችግር ሲኖር ደግሞ (ከናንተ መካከል የኡድሒያ እርድ የጣለ ሰው ከእርዱ ምንም ነገር እያለ ሦስተኛ ሌሊት እንዳነጋበት) የሚለው የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሐዲስ ተቀዳሚ ይሆናል፡፡

እንደሚታወቀው ኡድሒያ በማረድ እንዲሚረጋገጥ ሁሉ ዋጋውን እርዶ ለሚያከፋፍል ወገን በመስጠትም ይረጋገጣል፡፡ምክኒያቱም የዚህ ዓይነቱ የተደራጀ ከፍል በሚገባ አርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች አንድሁም ከብራቸውን በምንም ዓይነት መልኩ ሳይነካ የሚያደርስ በመሆኑ ጥቅሙ የሰፋ ይሆናል፡፡ ችሎታ ያለው ደግሞ እርዱን በመጣልና ዋጋውንም በመስጠት ለወገኖቹ እርዳታ ቢያበርክት እጅግ የተወደደ ነው፡፡ ማንኛውም ሙስሊም ጥቅማቸው በሁሉም የህበረተሰቡ ክፍል ተደራሽ የሚሆኑ የተለያዩ መልካም ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ሰው ምጽዋት በሚሰጥበት ወቅት በድሆችና ችግረኞች ልብ ደስታን የሚፈጥር በመሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገፋፍቷል፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَنفِقُوا مِمَّا رَزَقْنَاكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِيَ يَوْمٌ لَّا بَيْعٌ فِيهِ وَلَا خُلَّةٌ وَلَا شَفَاعَةٌ وَالْكَافِرُونَ هُمُ الظَّالِمُونَ}

ትርጉሙም( እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ውስጥ ሽያጭ (መበዠት)፣ ወዳጅነትም፣ ምልጃም የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ነገር ለግሱ፡፡ ከሓዲዎችም በዳዮቹ እነርሱ ናቸው፡፡)
ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ገንዘብ በምንም መልኩ) ምጽዋት በመስተት አይጓደልም) የሚል ሐዲስ ተውረቷል፡፡
እኛ በአሁኑ ወቅት መተጋገዝ፣ መተባበርና የሌሎችን ሁኔታ መረዳት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ይህውም እንድህ ለሚለው ለነብያችን ቃል ለመታዘዝ ነው፡ (ሙስሊም የሙስሊም ወንድም ነው፡፡ አይበድለውም፣ አሳልፎም አይሰጠውም፡፡ የወንድሙን ጉዳይ ለማውጣት የቆመ ሰው፡፡ አላህ ጉዳዩን ያወጣለታል፡፡ ከአንድ ሙስሊም ጭንቅን ያቃለለ ሰው አላህ ከትንሳኤ ቀን ጭንቀቶች አንዱን ጭንቀት የቃልልለታል፡፡ አንድን ሙስሊም ከመጋለጥ የታቀበ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን አያጋልተውም፡፡) ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.)አንድ ቀን (ማንኛውም ሙስሊም ምጽዋት መስጠት አለበት) አሉ፡ ፡ ባልደረቦችም የአላህ ነብይ ሆይ! ገንዘብ ባይኖረውስ? ሲሉ ጠየቁ፡፡ በእጁ ይስራ ከዚያም ራሱንም ይጥቀሞ ምጽዋትም ይስጥ አሉ፡፡ አነሱም ባያገኝስ? አሉ፡፡ እሳቸውም ባለጉዳይንና የተጨነቅን ይገዝ አሉ፡፡ አነሱም ባይችልስ? አሉ፡፡ እሳቸውም ውለታን ይዋል ተንኮል ከመፈጸምም ይታቀብ ይህ ለሱ ምጽዋቱ ነው አሉ፡፡)
ጌታችን ሆይ አንተን እንድናወሳ፣ እንድናመሰግንና ዒባዳህንም እንድናሳምር አገዘን አሜን፡፡

## (39)

### በኢስራእ ምእራፍ ዙሪያ

ምስጋና ሁሉ ለዚያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረከው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ለአስኼደው (ጌታ) ይገባው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ሱ.ወ.) (በነርሱ ላይ ሰላም ይውረድና) መልክተኞቹን በተለያዩ ታምራቶች አግዟቸዋል፡፡ ከነዚህም ታምራቶች ለነብያችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) የተሰጡት የኢስራእና የሚዕራጅ ታምር አንደኛው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{سُبْحَانَ الَّذِي أَسْرَى بِعَبْدِهِ لَيْلًا مِنَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ إِلَى الْمَسْجِدِ الْأَقْصَى الَّذِي بَارَكْنَا حَوْلَهُ لِنُرِيَهُ مِنْ آيَاتِنَا إِنَّهُ هُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ}**

ትርጉሙም (ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው (ጌታ) ጥራት ይገባው፡፡ ከተዓምራቶቻችን ልናሳየው (አስኼድነው)፡፡ እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቹው ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ ይህችን የፈጣሪን ታእምር ያቀፈችውን ምእራፍ የሚመራመር ሰው በርካታ ትምህርቶችንና ማስጠንቀቂያዎችን ያቀፈች መሆኗን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ከነዚህ ትምህርቶች አንደኛው ወሰን የለሽ የአላህ (ዐ.ወ.) ችሎታ ምእራፏ የሚያብራራ መሆኑ ነው፡፡ የአላህ ፍላጎት ለምክኒያታዊ ህግጋቶች ተገዢ አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{إِنَّمَا أَمْرُهُ إِذَا أَرَادَ شَيْئًا أَنْ يَقُولَ لَهُ كُنْ فَيَكُونُ}**

ትርጉሙም (ነገሩም አንዳችን በሻ ጊዜ ኹን ማለት ነው፡፡ ወዲያው ይኾናልም፡፡) ማለት ነው፡፡

በምእራፏ ከተካተቱ ከነዚህ ትምህርቶች ሌላው ደግሞ ከችግር በኋላ ምቾት፣ ከጭንቀቅ በኋላ ግልግል ያለ መሆኑን መግለጹዋ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የጌታቸውን መልክት ለማስተላለፍ በጀመሩበት ጊዜ ከአጋሪዎች በኩል የደረሰባቸውን የስቃይ ዓይነት ሁሉ በትእግስት ካሳለፉ በኋላ አላህ (ዐ.ወ.) ነብዩን በማክበርና እሳቸውንም ለማገዝ ከመከራ በኋላ ለሚመጣ ግልግል ተምሳሌት ይሆን ዘንድ የኢስራእና የሚእራጅ ታምርን ሰጣቸው፡፡አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَإِنَّ مَعَ الْعُسْرِ يُسْرًا * إِنَّ مَعَ الْعُسْرِ يُسْرًا}

ትርጉሙም (ከችግርም ጋር ምቾት አልለ፡፡ ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አልለ፡፡) ማለት ነው፡፡ ከነዚህ ትምህርቶች ሌላኛው ደግሞ የባርነት ደረጃ እጅጉን ታላቅ መሆኑን ምእራፏ ማብራራቷ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَأَوْحَى إِلَى عَبْدِهِ مَا أَوْحَى}

ትርጉሙም (ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ፡፡) ማለት ነው፡፡ የአላህ ባርነት ለአንድ ሰው ታላቅ ክብርና ልቅና ነው፡፡ አላህም የሰውን ልጅ ማክበሩን ሲገልጽ መልክተኞቹ ሁሉ የተላኩት ለዚህ ዓላማ መሆኑን አውስቷል፡፡

በምእራፏ ከተካተቱ ትምህሮች ሌላው ደግሞ የአቅሷን መስጊድ ታላቅ ቦታ ማብራራቷ ነው፡፡ ወደዚህ መስጊድ ነበር አላህ (ዐ.ወ.) ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌሊት ከመካ

ተነስተው እንዲጓዙ ያደረገው፡፡ እንድሁም ከዚህ መስጊድ በመነሳት ነበር ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደላይኛው ሰማያት ያረጉት፡፡ ይህ መስጊድ በስግድት ፊታችንን ወደነሱ ከምናዞርባቸው ሁለት ቦታውች የመጀመሪያው ሲሆን ከሶስቱም እርም ከተደረጉ ቦታዎች አንደኛው ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለሱ ዘብ የቆሙ ምእምናን አላህ ብርታት እንዲሰጣቸውና ይህን መስጊድም ያለችግር ወደሙስሊሞች ይዘት እንዲመልሰው አላህን እንለምናለን፡፡

በኢስራእ ምእራፍ ከተካተቱ አስተምህሮዎች ሌላው የስግደትና ታላቅነትና ያለውን ከፍተኛ ትሩፋት እንድሁም የተለየነቱን ማብራራቷ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከአቅሷመስጊድ ተነስተው ወደሰማያት ካደረጉት ጉዞ በኋላ ሲድረት አልሙንተሃ ከሚባል ቦታ ደረሱ፡፡ እሱም በስደስተኛው ሰማይ ላይ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ በዚህ ቦታ ሦስት ነገሮችን ተሰጡ፡፡ እነሱም በቀንና ሌሊት የሚፈጸሙ የአምስት ወቅት ስግደቶችን፣ የበቀራ ምእራፍ የመጨረሻ አንቀጾችና ከህዝባቸው በአላህ የማያጋራ ሆኖ የሞተ ሰው ምህረት የሚደረገለት መሆኑ የሚሉት ናቸው፡፡

ከምእራፏ የምንማረው ሌላው እውቀት ደግሞ ከሃይማኖቱች መካከል የጋራ ትስስር ያለ መሆኑን ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ነብያት የአባት ልጅ ወንድም ተማማኞች፣ እናቶቻቸው የተለያዩ ነገር ግን ሃይማኖታቸው አንድ የሆኑ ናቸው፡፡) በኢስራእና ሚዕራጅ ሌሊት ነብያት በአቅሷ መስጊድ ተሰባስበው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በስግደት በመሯቸው ወቅት መልካም አቀባብል አድርገው የአላህ በረከትም እንዳይለያቸው ጸሎት አድርገውላቸዋል፡፡

ከምእራፏ የምንቀስመው ሌላው ትምህርት ደግሞ ለማንኛውም ነገር ሰበብን ማድረስ ግድ መሆኑን ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደበይትልመቅድስ በደረሱ ጊዜ ከመካ ወደ እየሩስ ዓሌም የተጓዙበትን ቡራቅን ውጭ አሰሩት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)እንድህ ይላሉ፡ (...ነብያት በሚያስሩበት ችካል አሰርሁት)

ከምእራፏ የምንቀስመው ሌላው እውቀት ደግሞ እውነተኛ አማኞችን ከሌላዎቹ መለየቷን ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ በክር የቁረይሽ ባላባቶች ‹ስለዚህ ሰለጓደኛህ ምን ትላለህ በዚህ ሌሊት ወደበይተልመቅድስ ተወስዶ እንደተመለስ ያወራል? በማለት የፌዝ ጥያቄ በጠየቋቸው ጊዜ እሳቸው እንደዚያ ብለዋልን? በማለት የማጣራት ጥያቄ ሰነዘሩ፡፡ እነሱም አዎን አሉ፡፡ እንደዚያ ብለው ከሆነ በእርግጥ እውነት ተናግረዋል አሉ፡፡ እነሱም በዚህ ሌሊት ወደበይተልመቅድስ እንደሄደና ጎህ ሳይቀድም መምጣቱን ትቀበለዋለህን አሏቸው፡ እሳቸውም አዎን እኔ ከዚያ በሚደንቅ ነገር አምናቸዋለሁ እኔ ከሰማይ በጧት በማታ የሚያመጡትን ወሬ እቀበለዋለሁ በማለት መለሱላቸው፡፡ ለዚህም ሲዲቅ የሚለውን ውብ ቅጽ ስም ተሰጥተዋል፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የኢስራእ ምእራፍ ስለዚህ ስለተባረከው የሌሊትና ሰማያት ጉዞ እንዳብራራችው ሁሉ ለወላጆች መልካም ውለታ ስለመዋልም በአጭሩ ገልፃለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡፡

{وَقَضَى رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوا إِلَّا إِيَّاهُ وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا}

ትርጉሙም (ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፡- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፡፡ በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፡፡) ማለት ነው፡፡ ከዎላጆችም በእርግዝና ከዚያም በምታጠባበት ወቅትና አጠቃላይ በማሳደግ ሄደት የምታደርገው ጥረት ወሰን የለሽ በመሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) እናትን በተጨማሪ ትኩረት ለይቷታል፡፡

{ وَوَصَّيْنَا الانسَانَ بِوَالِدَيْهِ حَمَلَتْهُ أُمُّهُ وَهْنًا عَلَى وَهْنٍ}

ትርጉሙም (ሰውንም በወላጆቹ (በጎ እንዲያደርግ) በጥብቅ አዘዝነው፡፡ እናቱ ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው...) ማለት ነው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ለንብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሰዎች በመልካም ጓደኝነቴ ተቀዳሚው ማነው? ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (እናትህ ናት) አሉ፡፡ እሱም ከዚያስ? ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (ከዚያም እናትህ) አሉት፡፡ እሱም ከዚያስ? በማለት ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (ከዚያም እናትህ) አሉት፡፡ እሱም ከዚያስ? በማለት እንደገና ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (ከዚያም አባትህ) አሉ በእስልምና እምነት ለእናት መልካም ውለታ መዋል የአላህን ውዴታ ከሚያስገኙ ኢባዳዎች ተቀዳሚው መሆኑን አስምሮበታል፡፡ አንድ ቀን አንድ ሰውዬ በሃይማኖት ጦርነት ለመሳተፍ ፈቃድ ሊጠይቅ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በመጣ ጊዜ (እናትህ በሕይወት አለች?) ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም አዎን አለ፡፡ እሳቸውም (ተመለስ ወደቤትህ ለሷም ታዘዝ) አሉት፡፡ እሱም ሙጥኝ ባለ ጊዜ (አትሰማም እንዴ! እግሯ ስር ሆነው አገልግላት እዚያ ዘንድ ጀነትን ታገኛለህ) አሉት፡፡

እናትን መታዘዝ በአክብሮት፣ ውለታን በመመለስና በሷም ልብ ደስታን በማስገባት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ ከሞትም በኋላ ለሷ ጸሎት በማድረግ፣ ከአላህም ምህረትን በመጠየቅና ስለሷ ምጽዋት በመስጥ እንድሁም ወዳጆቹዋን በማከበር ለሷ ታዛዥነቱ ይቀጥላል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (ከመታዘዝ እጅጉን ታላቁ አንድ ልጅ የአባቱን ወዳጆች ቤተሰቦች ማክበር ነው)፡፡

ጌታችን ሆይ በሃይማትህ አጽናን እናትና አባቶቻችን ጠብቅልን ማርልንም ሀገራችንንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን አሜን፡፡

(40)

## የቂብላ መዛወር ትምህርቶችና ልባዊ ምክሮች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሓፉ

( سَيَقُولُ السُّفَهَاءُ مِنَ النَّاسِ مَا ولاَّهُمْ عَن قِبْلَتِهِمُ الَتِي كَانُوا عَلَيْهَا قُل لِّلَّهِ المَشْرِقُ والْمَغْرِبُ يَهْدِي مَن يَشَاءُ إلَى صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ )

ለአላው የአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከሰዎቹ ቂሎቹ «ከዚያች በርሷ ላይ ከነበሩባት ቂብላቸው ምን አዞራቸው?» ይላሉ፤ «ምሥራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው፤ የሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል» በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
በቸኛ ለሱም አጋር ከሌላው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ እንደሆኑም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ እዘነትህ፣ ሰላምህና በረከትህ በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም አሰከእለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ሰዎች ሁሉ ይውረድ፡፡ ከዚህም በመቀጠል፡
ታላቁ አላህ (ዐ.ወ.) በፈቃዱ ከፊል ወራቶችን ከከፊሎች በደረጃ አብልጧል፡፡ እንዲሁም ሙእሚኖች በመልካም ሥራ እንዲተጉ የሚገፋፉም መለያዎች አድርጎላቸዋል፡፡ የሻዕባን ወር የመልካም ሥራ መስመሮቹ በርካታ ከሆኑና ችሮታዎች ከሚበዙባቸው ብልጫ ካላቸው ወራቶች አንዱ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡ ( ለጌታችሁ ክብርና ሞገስ ይገባውና ከዘመናችሁ በተወሰኑት ቀናት ችሮታዎች አሉት በነዚህ ቀናት ለኢባዳ ትጉ መናልባትም አንዳችሁ ከነዚያ ችሮታዎች አንዱ ያጋጠመውና ከሱ በኋላ እስከዘላለም ምንም ዓይነት ምንድክና የማያገኘው ሊሆን ይችላልና፡፡) በዚህ በተከበረ ወር ከታላቁ አላህ ችሮታዎችን ለማግኘት በኢባዳ የሚተጋ በነዚያ ቀናት ያለውን የኢባዳና የትእዛዝ ማክበር ጥቅምን በከንቱ የማያሳልፍ ሙእሚን ብልጥ ሰው ማለት እሱ ነው፡፡

የሻዕባን ወር ከንብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ዘንድ ልዩ ቦታና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ስለነበር ከሌሎች ወራቶች በተጨማሪ ኢባዳ ይለዩትና ፆምም ያበዙበት ነበር፡፡ እናታችን ኣኢሻ (አላህ ከርሳቸው ይወደድና) እንዲህ ብለዋል፡ (የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) በሻዕባን ወር ምንም አያፈጥርም እስክንል ይፆሙ አንዲሁም ደግሞ ምንም አይፆሙም አስክንል ያፈጥሩ ነበር፡፡ የአላህ ምልእክተኛ ሙሉ ወር ከሮመዳን ሌላ ሲፆሙ አይቸ አላውቅም፡፡ አንዲሁም ከሻዕባን ወር የበለጠ አንድንም ወር ሲፆሙ አላየሁም፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለዚህ ተግባራቸው በተጠየቁ ጊዜ አሱ የሰው ልጅ ሥራዎች ወደአላህ የሚወጡበትና ሰዎች የኢባዳ ስንቅ ከማካበት የሚዘነጉበት ወር ስለሆነ ነው በማለት አብራርተዋል፡፡ ኡሳማ ቢን ዘይድ የተባሉ የነብያችን ባልደረባ (አላህ ከርሳቸው ይውደድና) ለነብያችን እንዲህ እለኳቸው (የአላህ መልእከተኛ ሆይ! ከወራቶች በአንዱም በሻዕባን ወር የምተፆሙት ያህል ስትፆሙ አላየዎትም፡፡ ያን ጊዜም ይህ ወር ከረጀብና ከሮመዳን ማህል በመሆኑ ሰዎች የሚዘነጉት ወር ነው፡፡ እሱም የሰው ልጅ ሰራዎች ወደአለማቱ ጌታ የሚወጣበት ወር ሲሆን እኔም ሥራዬ በፆም እያለሁ ወደአለማት ጌታ እንዲወጣ እወዳለሁ፡፡) አሉኝ የሚል ሓዲስ አውርተዋል፡፡

በዚህ በተከበረ ወር ከተከናወኑ ተላላቅ ክስተቶች አንዱ ወደበይተል መቅድስ የነበው የስግደት ቂብላ ወደበይቱላሂል ሐራም መዛወሩ ነው፡፡ ይህውም የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ፍላጎት ለማሟላትና መኞታቸውንም ለማሳከት ነበር፡፡ ይህ ክስተት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከፈጣሪ ከተቸሯቸው የክብር ግጽታዎች እጅጉን ታላቁ እንዴሆነ ይታመናል፡፡ ምክኒያቱም አላህ (ሱ.ወ.) ለወዳጁና ከሰው ሁሉ ለመረጣቸው ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደመዲና ከተዛወሩ በኋላ ለአስራ ስድስት ወይም ለአስራ ሰባት ወራት ያህል በጌታቸው ትእዛዝ በስግደት ወቅት ወደ በይተል መቅዲስ እየዞሩ ሲሰግዱ ከቆዩ በኋላ ወደ አባታቸው ወደኢብራሂም (ዐ.ሠ.) ቂብላ ወደካዕባ እንዲዞሩ ያቀርቡት ለነበረው የውስጥ ጥያቄ መልስ የሰጠበት በመሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደቤቱላሂል ሐራም ዞረው እንዲስግዱ ከአላህ ትንቢት መውረዱን በከፍተኛ ጉጉት ሲጠባበቁ ነበር፡፡ እንዲሁም በልባቸው አላህ ይህን ተግባር እንዲፈጽም ይመኙ ነበር፡፡ አላህ ይህን ጉዳይ እንደሚያሳካውም በመተማመን በህሌናቸውም ጸሎት ያደርሰበት ነበር፡፡ ታላቁ አላህ ታዲያ ጸሎታቸውን ተቀብሎ ምኞታቸውንም አረጋግጦ በስግደታቸው ወደተከበረው ካዕባ እንዲዞሩ አንዲህ በማለት አዘዛቸው፡፡

( قَدْ نَرَى تَقَلُّبَ وَجْهِكَ فِي السَّمَاءِ فَلَنُوَلِّيَنَّكَ قِبْلَةً تَرْضَاهَا فَوَلِّ وَجْهَكَ شَطْرَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ وَحَيْثُ مَا كُنْتُمْ فَوَلُّوا وُجُوهَكُمْ شَطْرَهُ وَإِنَّ الَّذِينَ أُوتُوا الْكِتَابَ لَيَعْلَمُونَ أَنَّهُ الْحَقُّ مِنْ رَبِّهِمْ وَمَا اللَّهُ بِغَافِلٍ عَمَّا يَعْمَلُونَ ).

ትርጉሙም ‹የፊትህን ወደሰማይ መገለባበጥ በእርግጥ እናያለን ወደምተወደውም ቂብላ እናዞርሃለን ስለዚህ ፊትህን ወደተከበረው መስጊድ (ካዕባ) አግጣጫ አዙር፡፡ የትም ስፍራ ብትሆኑም (ስትሰግዱ) ፊታችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ፡፡ እነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት እርሱ የጌታቸው ሲሆን እውነት መሆኑን ያውቃሉ፡፡ አላህም ከምትሰሩት ስራ ዘንጊ አይደለም› ማለት ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ታዲያ ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡፡ በመጀመሪያ የነብያችንን (ሰ..ዐ.ወ.) ከፍተኛ ቦታና ያላቸውን ታላቅ ደረጃ እንዲሁም ከጌታቸው ዘንድ ያላቸወን ከበሬታ ያንጸባርቃል፡፡ ሁለተኛም የተከበረውን የካዕባን ታለቅ ቦታና ያለውን ከፍተኛ ደረጃ ያመልክታል፡፡ ይህም ተግባር እንግዳና የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፡፡ ምክኒያቱም እርሱ መኖሩ የተረጋገጠ የሆነው አላህ እንዲህ ይላልና

(قُلْ إِنْ كُنْتُمْ تُحِبُّونَ اللَّهَ فَاتَّبِعُونِي يُحْبِبْكُمُ اللَّهُ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ ).

ትርጉሙም ‹ በላቸው አላህን የምተወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋልና ኃጢያቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና አለህም ከሀሪ አዛኝ ነው› ማለት ነው፡፡
እንደዚሁም እንዲህ ይላል፡

( مَنْ يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللَّهَ وَمَنْ تَوَلَّى فَمَا أَرْسَلْنَاكَ عَلَيْهِمْ حَفِيظًا ).

ትርጉሙም ‹ ምልእክተኛውነ የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡ ከትእዛዝም የሸሸ ሰው (አያሳስብህ) በነሱ ላይ ጠባቂ አደርገን አላክንህም› ማለት ነው፡፡

( وَمَنْ يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِمْ مِنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ وَحَسُنَ أُولَئِكَ رَفِيقًا ).

ትርጉሙም ‹ አላህንና መልእክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚህ እነዚያ አላህ በነርሱ ላይ ከለገሰባቸው ከነብያት፣ ከጻዲቃን፣ ከሰምኣታትና ከመልካሞቹ ጋራ ይሆናሉ፡፡ የነዚያም ጓደኝነት አማረ› ማለት ነው፡፡

( فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّى يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنْفُسِهِمْ حَرَجًا مِمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا ).

ትርጉሙም ‹በጌታህ እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ አስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን አስከማያገኙና ፍጹም መታዘዘንም እስከሚታዘዙ አይምኑም› ምእምን አይሆኑም ማለት ነው፡፡

የቂብላ መዛወር ክስተት ለማህበረሰቡ ተሃዲሶና ለአጠቃላይ የሰው ልጅ ስልጣኔ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጎ ነበር፡፡ ይህውም በርካታ ትምህርቶችንና ልባዊ ምክሮችን ያቀፈ በመሆኑ ነው፡፡ ከነዚህም ትምህርቶችና ምክሮች መካከል፡

መከራ እንዲሁም ፈተና በፍጥረቱ ላይ ከወሰናቸው የታለቁ አላህ ድንጋጌዎች አንዱ ነው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የቂብላ መዛወር መልእከተኛውን የሚከተለውን ሰው ወደከህደት ከሚመለሰው ሰው ለመለየት እንዲሁም (አላህ ከነርሱ ይውደድና) ባልደረቦች ምንያህል ይህን ጉዳይ ይቀበላሉ አንዴትስ የመልእክተኛውን ትእዛዝ ይፈጽማሉ የሚለውን ሁኔታ ለመግለጽ አላህ (ሱ.ወ.) በባሮቹ ላይ ያወረደው ፈተና ነበር፡፡ ቂብላ ከበይተል መቅዲስ ወደተከበረው ካዕባ መዛወሩ በነዚያ  ነገሮችን ለሱ በመተው አላህ በመራቸው ሰዎች ላይ በስተቀር ለህሌና እጅግ አዳጋች ነበር፡፡ አላህ በእርግጥም የፈለገውን ይሰራል በሻውም ይፈርዳል፡፡ መኖሩ የተረጋገጠ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡፡

وَمَا جَعَلْنَا الْقِبْلَةَ الَّتِي كُنْتَ عَلَيْهَا إِلَّا لِنَعْلَمَ مَنْ يَتَّبِعُ الرَّسُولَ مِمَّنْ يَنْقَلِبُ عَلَى عَقِبَيْهِ وَإِنْ كَانَتْ لَكَبِيرَةً إِلَّا عَلَى الَّذِينَ هَدَى اللَّهُ وَمَا كَانَ اللَّهُ لِيُضِيعَ إِيمَانَكُمْ إِنَّ اللَّهَ بِالنَّاسِ لَرَؤُوفٌ رَحِيمٌ

ትርጉሙም ‹ያችንም በርሷላይ የነበርክባትን አቅጣጫ መልእከተኛውን የሚከተለውን ሰው ወደከህደት ከሚመለሰው ሰው ልናውቅ (ልንገልጥ) እንጂ ቂብላ አላደረግናትም፡ ፡ እርሷም በነዚያ አላህ በመራቸው ሰዎች ላይ በስተቀር በእርግጥ ከባድ ናት፡፡ አላህም እምነታችሁን (ስግደታችሁን) የሚያጠፋ አይደለም፡፡ አላህ ለሰዎች በጣም ርህሩህ አዛኝ ነውና› ማለት ነው፡፡

በእምነታቸው የጸኑ እወነተኛ ሙእሚኖች ከነብዩ (ሶ.ዐ.ወ›) በሚመጣ ነገር ሁሉ ከቶ አይጠራጠሩም፡፡ ምክኒያቱም በነብዩ  (ሶ.ዐ.ወ.) የሚወርድ ነገር ሁሉ ጥርጥር የሌለበት እውነት መሆኑን በእርግጠኝነት ያውቀሉና፡፡ በመሆኑም  ያለህን ትእዛዝ በመቀበል ሰማን ታዘዝንም በማለት ያለማወላወል በስግደታቸው ወደተከበረው ካዕባ ፊታቸውን አዞሩ፡፡ ከፊሎቹ በሰግደት ሩኩዕ ላይ እያሉ በሰሙ ጊዜ ሰግደቱን እስኪጨርሱ ያለመጠበቅ በዚያው ባሉበት በሩኩዕ ሁኔታ እንዳሉ አላህ ወደመረጠላቸው አቅጣጫ ፊታቸውን አዞሩ፡፡

የእውነተኛ ሙስሊም ሁኔታ እንደዚህ ነው፡፡ የአላህ ትእዛዝ ወደሄደበት አቅጣጫ ይሄዳል፣ በየትኛውም ቦታ ቢሆን አቅጣጫው ወደ አላህ ነው፡፡ ታላቁ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

( وَلِلَّهِ الْمَشْرِقُ وَالْمَغْرِبُ فَأَيْنَمَا تُوَلُّوا فَثَمَّ وَجْهُ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ وَاسِعٌ عَلِيمٌ ).

ትርጉሙም ‹ምስራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው፡፡ (ፊታችሁን) ወደየትም ብታዞሩ የአላህ ፊት እዚያ ነው፡፡ አላህ ችሮታው ሰፊ አዋቂ ነውና› ማለት ነው፡፡

ኢብን ዑመር (ከርሳቸውና ከአባታቸውም አላህ ይውድና) እንዲህ ሲሉ አውርተዋል፡ (ከእለታት አንድ ቀን ቁባእ መስጊድ ሰዎች የፈጅርን ሶላት እየሰገዱ ባለበት ወቅት አንድ ሰው መጣና የአለህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ዛሬ ምሽት በስግደታቸው ወደካዕባ እንዲዞሩ ትእዛዝ የያዘ ቁርኣን ወርዶላቸዋል አለ፡፡ እንሱም ፊታቸውን ወደሻም ዞረው እየሰገዱ የነበር በቀጥታ ወደካዕባ ዞሩ)፡፡ (ከነሱ አላህ ይውደድና) የነብዩ ባልደረቦች በዚህ አይነት ፍጥነት የአላህና የመልእክተኛው ትእዛዝ የሆነውን የእስልምናን አስተምህሮ እንዴት መቀበል እንዳለብን አስተምረውናል፡፡ ባልደረቦች በቂብላ መዛወር ክስተት እንደዞሩ ሁሉ እኛም በከፊልም ሆነ በአጠቃላይ መልኩ ወደእስልምና መመሪያ አላህ በሚወደው መልኩ ለመላ ሰው ልጅም በሚጠቅም ሁኔታ አወንታዊ መዞርን እንዙር፡፡

ከቂብላ መዛወር ከምንቀስማቸው ትምህርቶች ሌላው ትምህርት ደግሞ **የማህበረሰቡ ልከኛነት ነው፡፡** ይህ ታላቅ ክስተት የዚህን ማህበረሰብ መስረታዊ ልከኛነት በግልጽ አንጸባርቋል፡፡ መኖሩ የተረጋገጠ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፡

كَذَلِكَ جَعَلْنَاكُمْ أُمَّةً وَسَطًا لِتَكُونُوا شُهَدَاءَ عَلَى النَّاسِ

ትርጉሙም ‹እንደዚሁም በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑ ምርጥ ሕዝብ አደረግናችሁ› ማለት ነው፡፡

የማህበረሰቡ ልከኛነት ሁሉን ነገር ያካተተ ሲሆን፡ የእምነትና ያመለካከት ልከኛነት፣ ከማጋንና ከችልተኝነት፣ ወሰን ከመተላለፍና ልክ ከማጣት በመራቅ የኢባዳና የስርአተ ኢባዳ ልከኛነት፣ የስነ ምግባርና የጠባይ ልከኛነት፣ የህግጋትና የደንብ ልከኛነት እንዲሁም የህሳብና የስሜት ልከኛነት ያካትታል፡፡

ከዚህ ላይ የነብዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ህዝቦች በሌሎች ህዝቦች ላይ ምስክርነታቸው ክብራቸውን ያመለክታል ስንል ለዚህ ምስክርነት ብቃት ሊኖራቸው የሚገባ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ አቡ ሰኢድንል ኹድሪ የተባሉት የነብያችን ባልደረባ

የሚከተለውን ሃዲስ አውርተዋል፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡ (በቂያመ አለት ነብዩ ኑህ ከአላህ ፊት ይቀርቡና የወረደልህን መልእክት አድርሰሃልን በመባል ይጠየቃሉ፡፡ እሳቸውም አዎን ጌታዬ ሆይ ይላሉ፡፡ ህዝቦቸዎ በተራቸው መልእክቱን ለናንተ አድርሷልን በመባል ይጠየቃሉ እነሱም ኧረ መንም አስጠንቃቂ ሰው ወደኛ አልመጣም በማለት ይመልሳሉ፡፡ ያን ጊዜ አላህ ማን ምስክር አለህ ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ እሳቸውም ሙሐመድና ህዝቦቹ ይመሰክሩልኛል በማለት ይመልሳሉ እናንተም ትጠሩና ትመሰክራላችሁ)፡፡ ከዚያም የአላህ መልእክተኛ እንዲህ የሚለውን አንቀጽ አነበቡ፡

وَ كَذَلِكَ جَعَلْنَاكُمْ أُمَّةً وَسَطًا لِتَكُونُوا شُهَدَاءَ عَلَى النَّاسِ وَيَكُونَ الرَّسُولُ عَلَيْكُمْ شَهِيدًا

ትርጉሙም ‹እንዚሁም (እንደመራናችሁ) በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑና መልእክተኛውም በናንተ ላይ መስካሪ ሆን ዘንድ ምርጥ ህዝቦች አደረግናችሁ፡፡
የአላህ መልእክተኛ ከእለታት አንድ ቀን ለኢብን መስኡድ (ቁርኣን ቅራልኝ) አሏቸው ኢብ መስኡድም በርሰዎ ላይ ወርዶ እያለ እኔ እቀራለዎታለሁን አሉ፡፡ እሳቸውም (እኔ ከሌላ ሰው ስሰማው እደሰታለሁ) አሉ፡፡ ከዚያም የኒሳእ ምእራፍን መቅራት ጀመርኩ እንዲህ ከምትለው አንቀጽ ጋ ስደርስ፡

فَكَيْفَ إِذَا جِئْنَا مِنْ كُلِّ أُمَّةٍ بِشَهِيدٍ وَجِئْنَا بِكَ عَلَى هَؤُلَاءِ شَهِيدًا

ትርጉሙም ‹ከህዝቦችም ሁሉ መስካሪን ባመታን ጊዜ አንተንም በነዚህ ላይ መስካሪ አድርገን በምናመጣህ ጊዜ› (የከሃዲዎች ሁኔታ እንዴት ይሆን) ማለት ነው፡፡
(አሁን በቃህ) አሉኝ፡፡ ወደሳቸውም ዘወር ስል ጊዜ ዓይኖቻቸው እንባ እያዘነቡ አየሁኝ፡፡
በአሁኑ ወቅት በሱ ታላቁ አላህ (ሱ.ወ.) ወደአከበረን ወደልከኛነት መመለስ ይኖርብናል፡፡ ከወሰን መተላለፍና መስመር ከመልቀቅ በመራቅ እውነተኛ ልከኞች ልንሆንም ይገባል፡፡ መኖሩ ተረጋገጠ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡

وَلَا تَجْعَلْ يَدَكَ مَغْلُولَةً إِلَىٰ عُنُقِكَ وَلَا تَبْسُطْهَا كُلَّ الْبَسْطِ فَتَقْعُدَ مَلُومًا مَحْسُورًا

ትርጉሙም ‹እጅህንም ወደአንገትህ የታሰረች አታድርግ መዘርጋትንም ሁሉ አትዘርጋት የተወቀስክ የተቆጨህ ትሆናለህና› ማለት ነው፡፡
እንዲሁም እንዲህ ይላል

وَٱلَّذِينَ إِذَآ أَنفَقُواْ لَمْ يُسْرِفُواْ وَلَمْ يَقْتُرُواْ وَكَانَ بَيْنَ ذَٰلِكَ قَوَامًا

ትረረጉሙም ‹እነዚያም በለገሱ ጊዜ የማያባክኑት፣ የማይቆጥቡትም ናቸው፡፡ በዚህ መካከል (ልግስናቸው) ትክክለኛ የሆነ ነው› ማለት ነው፡፡
ኢማሙል አውዛኢ የተባሉ ኣሊም እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡ ‹ታላቁ ኣላህ በእስልምና እምነት መመሪያ አንድን ነገር አያዝህም ሰይጣን ማንኛው ትክክለኛ እንደሆነ ትኩረት ሳይሰጥ ከወሰን መተላፍና ከልክ ከመውጣት በአንደኛው ሊወስድህ ያሰበ ቢሆን እጂ›
በመሆኑም ከገርነትና ከችሎታ ጋር እንጂ ወሰን ከመተላለፍና ከለክ ከመውጣት ጋር መሆን የለብንም፡፡ እንዲሁም ከማክረርና ከጽንፈኝነት በመራቅ በእምነታዊና ስነመግባራዊ ተገዢነት የጸናን መሆን ይኖርብናል፡፡
ይህን ቃሌን እንደሰማችሁት ብያለሁ ለኔና ለናንተም ከአላህ ምህረትን አለምናለሁ፡፡

መስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዘነትና ሰላም የነብያቱና የመልእክተኞቹ መደምደሚያ በሆኑት በሰይዲና ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በቤተሰበቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸውም ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

ከቂብላ መዛወር ከምን ቀስማቸው ትምህርቶችና ምክሮች ሌላው ደግሞ በተከበረው መካ ክልል ካለው መስጂደል ሐራምና ቁድስ ውስጥ ካለው የአቅሷመስጊድ መካከል ያለውን ጥብቅ ትስስርና ከመካከላቸው ያለውን ጠንካራ ግንኙነት በግልጽ ማንጸባረቁ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ይህ የቂብላ ጉዳይ የሁለቱን መስጊዶች ወንድምተማማችነት በጉልህ መልኩ አሳይቷል፡፡ መስጂዱል ሐራም በዚህች ምድር አላህ(ሱ. ወ. )ን ለመገዛት የተገነባው የመጀመሪያ መስጊድ ሲሆን መስጂዱል አቅሷ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የተገነባው መስጊድ ነው፡፡ አቡ ዘር የተባሉ የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባ እንዲህ ብለዋል፡ (የአለህ መልእክተኛ ሆይ! የተኛው መስጊድ ነው እምድር ላይ መጀመሪያ የተሰራው አልኩኝ እሳቸውም ‹መስጂዱል ሐራም› አሉ፡፡ ከሱስ በኋላ አልኩኝ (መስጂዱል አቅሷ) አሉ፡፡ ከመካከላቸው ያለው ዘመን መን ያህል ነበር አልኩኝ (አርባ አመት፣ በየትኛውም ቦታ ሁነህ የሶላት ወቅት ከደረሰ አዚያ ቦታ ስገድ እሱ መስጊድ ነው ) አሉ፡፡
የቂብላ መዛወር ሁለቱን መስጊዶች ያስተሳስ ሲሆን ኢስራእ (የሌሊት ጉዞ)ና ሚዕራጅ (ወደሰማይ መውጣት)ም በዚሁ መልክ እነዚህን መስጊዶች አስተሳስረቻቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡

( سُبْحَانَ الَّذِي أَسْرَى بِعَبْدِهِ لَيْلًا مِنَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ إِلَى الْمَسْجِدِ الْأَقْصَى الَّذِي بَارَكْنَا حَوْلَهُ لِنُرِيَهُ مِنْ آيَاتِنَا إِنَّهُ هُوَالسَّمِيعُ الْبَصِيرُ ).

ትርጉሙም ‹ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደባረክነው ወደሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኬደው (ጌታ) ጥራት ይገባው፡፡ ከታምራቶቻችን ልናሳየው (አስኬድነው) እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቹው ነው› ማለት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ አላህ ምድርንና በርሷም ላይ ያለውነ ሁሉ እስኪወርስ ድረስ በመላ ሙስሊሙ ማህበረሰብ የተጣሉ አደራወች በመሆናቸው ሁለቱንም መስጊዶች በአንድ ላይ መጠበቁና አንዳቸውንም በቸልታ አለመዘንጋት ግድ ሆኗል፡፡
ማህበረሰቡ የተቀደሱ ቦታዎችን መጠበቅ አይችልም፣ በመጀመሪያ አላህ (ዐ.ወ.)ን በመፍራትና በሱም በመመካት ከዚያም አንድነቱን በማስከበር ቢሆን እንጂ፡፡ ማህበረሰቡ በእውቀትና በስራ የኃይል መሰረቶችን በእጁ ሲያስገባ የእለት ከለት ጉርሱን፣ ምግቡን፣ ልብሱን፣ መድሃኒቱን በእጁ ያደርጋል፡፡ ያንጊዜም የቃሉ፣ የነፃነቱ፣ የውሳኔው ባለቤት ይሆናል፡፡ የህይወት መሰረታዊ ነገሮችን በእጁ ያላደረገ ማንኛውም ማህበረሰብ ምንጊዜም የቃሉና የፍላጎቱ እንዲሁም የነፃ ውሳኔው ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡
ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በፊት ልዩ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ አንድ ነግር አላ፡፡ እሱም መዞር ስንል ከቦታ ወደሌላው መዛወርን ብቻ ማለታችን አይደለም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የጠቀስነው መዞር ጠንካራውን መሰረተ እምነት፣ የማይበገረውን ፍላጎት፣ ባአላህ (ሱ.ወ.)ና በመልእክተኛው (ሶ.ዐ.ወ.) አንፃር ያለውን ሙሉ እምነት ለመሞከር የተከናወነ ጉዳይ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ያለንበትን ሁኔታ በሁሉም መስክ ወደተሻለ እንዲያዛውርልን ከሻን በአላህ (ዐ.ወ.) መመካታችንን በማሳመርና መጠጊያችንን እሱን ብቻ በማድረግ እንዲሁም ስራና ትጋታችንን በማጠናከር ራሳችንን መቀየር ይጠበቅብናል፡፡ ከማፈረስ ወደመገንባት፣ ከስራፈትነትና ስንፍና ወደተጨማሪ ስራና ምርት መዛወር ይኖርብናል፡፡ ከማክረርና ከማጋነን ወደመቻቻልና ገራገርነት፣ ከደረቅነትና ከጭፍን መከተል ወደማስንተንና ወደማሰብ እንዛወር፡፡ ምክኒያቱም አላህ (ዐ.ወ.) እንዲህ ይላልና፡

إِنَّ اللَّهَ لا يُغَيِّرُ مَا بِقَوْمٍ حَتَّى يُغَيِّرُوا مَا بِأَنْفُسِهِمْ

ትርጉሙም ‹አላህ በህዝቦች ዘንድ ያለው ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ሁኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም› ማለት ነው፡፡
ታላቅና የበላይ የሆነውን አላህን በዚህ በተከበረ ወር ስራቸውን ከሚቀበላቸው ባሮቹ መካከል እንዲያደርገን እንለምናል፡፡

# (41)

## ሮመዳን የኢባዳና የሥራ ወር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላ ተጻፈ፡፡ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና) ማለት ይሆናል፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጇጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (የረመዳንን ወር በሙሉ እምነትና ምንዳን አስቦ የፆመ ሰው ከዚያ በፊት የሰራው ወንጀሉ ይማርለታል) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህ በመቀጠልም**

ታላቁ አላህ በችሮታው ለባሮቹ የደጋግ ነገሮች ወራቶች አድርጓል፡፡ በነሱም ችሮታዎች በተከታታይ ይገለፃሉ፣ እዝነቶች ይወርዳሉ፣ ምንዳዎችም እጥፍ ድርብ ይሆናሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ (ለጌታችሁ (ዐ.ወ.) በዘመናችሁ ቀናት ችሮታዎች አሉት፣ እነሱንም ለማግኘት ጣሩ፡፡ ምናልባትም እንዲያችሁ ከነዚያ ችሮታዎች አንዱ ያጋጥመውና ከዚያ በኋላ እሰከምንጊዜም መናጢነት የማያገኘው ሊሆን ይችላልና)፡፡ ከነዚህ ወራቶች በክብር እጅግ ታላቁ በረከቱና ልግስናው የበዛው የወራቶቹ ሁሉ ሊቅ የሆነው የሮመዳን ወር ነው፡፡ የሮመዳን ቀናት ከቀናት ሁሉ የበለጡ፣ ሌሊቶቹም ከሌሊቶች ሁሉ ሌሊቶች የጸዱ ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በረመዳን ወር መምጣት

ይደሰቱና በዚህ በፈጣሪ ስጦታም ባልደረቦቻቸውን ያበስሩ ነበር፡፡ አቡ ሁረይራ የተባሉ የነብያችን ባልደረባ የአላህ ምልእክተኛ እንዲህ አሉ ሲሉ አውርተዋል (የተባረከ የሆነው የሮማዳን ወር መጣላችሁ፡፡ እንዲተፆሙት አላህ ግድ አድርጎባችኋል፡፡ በሱም የሰማይ በሮች ይከፈታሉ፡፡ የገሀነም በሮች ደግሞ ይዘጋሉ፡፡ አመጸኛ ሰይጣናትም ይጠፈራሉ፡፡ በሱም ለአላህ የሆነች ከአንድ ሽህ ወራቶች የምትበልጥ ሌሊት አለች፡፡ የሷን መልካም ያጣ መልካሙን ሁሉ አጣ)፡፡

(ከነሱ አላህ ይውደድና) የነብያችን ባልደረቦች አላህ ለሮመዳን ወር እንዲያደርሳቸውና በሱም ለመልካም ስራ እንዲያበረታቸው አላህን ይለምኑ ነበር፡፡ ኢብን ረጀብ የተባሉ ሊቅ እንዲህ ብለዋል፡፡ ብዙሃኑ የነብዩ ባልደረቦች ስድስቱን ወራት አላህ ለሮመዳን እንዲያደርሳቸው ይለምኑ ነበር እንዲሁም ስድስቱን ወራት ደግሞ አላህ ከነሱ ሮመዳንን እንዲቀበላቸው ይለምኑ ነበር፡፡ ያህያ ኢብን አቢ ከሲር የተባሉት ሊቅ ደግሞ የባልደረቦች ፀሎት ‹ጌታዬ ሆይ! ለሮመዳን አሳልፈህ ስጠኝ ሮመዳንንም ለኔ ስጠኝ አሱንም ከኔ የወደድህ ስትሆን ተቀበለኝ› የሚል ነበር ሲሉ አውርተዋል፡፡

(ከሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር ኢብን አብዲላህ የተባሉ ባለደረባ የሚከተለውን አውርተዋል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ቀን ወደድስኩር መንበር ሲወጡ የመጀመሪያውን ደረጃ ከወጡ በኋል አሚን አሉ፡፡ ሁለተኛውንም ከወጡ በኋላ አሚን አሉ፡፡ ከሦስተኛውም በኋላ እንደዚሁ አሚን አሉ፡፡ ያን ጊዜ ባልደረቦች ያለህ መልእክትኛ ሆይ! ሦስት ጊዜ አሚን ሰትሉ ሰማን አሉ፡፡ ነብያችንም (ሰ.ዐ.ወ.) (የመጀመሪያውን ደረጃ በወጣሁ ጊዜ ጂብሪል (ዐ.ሰ.) መጣና ‹አንድ ባሪያ የሮመዳን ወር መጥቶለት አላህ ሳይመርለት ያሳለፈው ሰው መናጢ ሆነ› አለ ያን ጊዜ ታዲያ እኔ አሚን አልኩኝ አሉና ቀጠሉ...)

ከጥቂት ቀናት በኋላ ይህን የተከበረ እንግዳ ለመቀበል በምንዘጋጅበት ወቅት የአላህን መላክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲሁም የተከበሩ ባልደረቦቻቸው በዚህ በተከበረ ወር ይሰሩት የነበረውን ኢባዳ አይነት በመስራት ፈለጋቸውን ልንከትል ይገባል፡፡ በመሆኑም አንድ ሙስሊም በዚህ ወር ኒያውን (ሀሳቡን) ማደስ ይኖርበታል፡፡ ኒያ የኢባዳ ምስጢር በመሆኗ የባሪያዎች ደረጃ የሚበላለጠው በሷ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንዲህ ብለዋል፡፡ (ሥራዎች የሚመዘኑት በኒያ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የኒያውን ውጤት ያገኛል፡፡ ጉዞው ወደአላህና መላክተኛው የሆነ ሰው ጉዞው ወደአላህና መላክተኛው ነው፡፡ ጉዞው ሃብት ለማግኘት ወይም አንዲት ሴት ለማግባት የሆነ ሰው ደግሞ ጉዞው ለተጓዘለት ነገር ነው)፡፡

(ከሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ የተባሉ ባልደረባም የሚከተለውን አውርተዋል፡፡ የአላህ መላክተኛ እንዲህ አሉ (አላህ (ዐ.ወ.) አንዲህ አለ ማንኛውም የሰው ልጅ የሠራው ሥራ የራሱ ነው፡፡ ከፆም በስተቀር እሱ የኔ ነው ምንዳውን እኔ

በራሴ ነው የምሰጠው፡፡ ፆም መከታ ነው ፡፡ አንዳችሁ ፆም በሚይዝበት ቀን እርኩስ ቃል አይናገር እንዲሁም ደምጹን ከፍ አያደርግ፡፡ አንድ ሰው ቢሰደበው ወይም ሊታገለው ቢሞክር እኔ ፆም የያዝኩ ሰው ነኝ ይበል የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ ይሁንብኝ የአንድ ፆመኛ አፍ ጠረን ከአለህ ዘንድ ከምስክ መዓዛ የበለጠ ነው)፡፡

እንዲሁም ማንኛውም ሙስሊም በሮመዳን ውር ለአላህ መገዛትና መልካም ሥራን ሊያበዛ፣ እንዲሁም ነብያችን(ሶ.ዐ.ወ.) ያዘዙትንና ይሠሩት የነበረውን ሁሉ ሊፈጽም ይገባል፡፡ ለምሳሌ ፈጥነን እንዲናፈጥር እንዲህ በማለት ያዙ ነበር፡፡ (የኔ ህዝቦች ፈጥነው ከማፍጠርና የሌሊት ምግብንም ዘግየት ከማድረግ እስካልተወገዱ ድረስ ደግ ነግር አይርቃቸውም) እንዲሁም (በሌሊት ምግብን ውሰዱ በሱም በረከት አለና)፡፡ በአንፃሩም ደግሞ አንድ ሙስሊም መግብንም ሆነ መጠጥን ከማባከን ሊቆተብ ይገባል፡፡ ታላቁ አላህ እንዲህ ብሏል፡

وَكُلُوا وَاشْرَبُوا وَلَا تُسْرِفُوا إِنَّهُ لَا يُحِبُّ الْمُسْرِفِينَ

ትርጉሙም (ብሉም ጠጡም አታባክኑም እርሱ አባካኞችን አይወድምና) ማለት ነው፡፡ የላህ መላክተኛም (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡ (አንድ ሰው ከሆዱ የበለጠን እቃ በተንኮል ሊሞላ አይችልም፡፡ የአደም ልጅ አካላቱን የሚያቆሙ ጥቂት ኩርሻዎች ይበቁታል፡፡ ከዚያ በላይ ካልጨመርኩ ብሎ አንበ ካለ ደግሞ ሲሶውን ለምግቡ ሲሶውን ለመጠጡና ሲሶውን ለስትንፋሱ ያድርግ)

በዚህ በተከበረው ወር ባለጸጋዎች የድሆችን እጦት በልባቸው ቢያስቡት እንዴት መልካም በሆነ ነበር፡፡ የሮመዳን ውር የልግሳና፣ የቸርነትና የስጦታ ወር እንደሆነ ይታወሳል፡፡ በዚህ ወር ለሙታን ልጆች፣ ባል ለሞተባቸው ሴቶች፣ ለድሆችና ለምስኪኖች እገዛ በማድረግ የርህራሄ፣ የእዝነትና የመራራት ትርጉም ጎልቶና ደምቆ ይታያል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በማንኛውም ጊዜ የሚያደርጉት ቢሆንም በሮመዳን ወር በችሮታ በድሆች መንፈስ በበለጠ ደስታን ያሰገቡ ነበር፡፡ (ከሳቸውና ከአባታቸው አላህ ይውደድና) ኢብን አባስ የተበሉ የነበያችን ባልደረባ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ፡ ያላህ መላክተኛ የቸሮች ቸር ነበሩ፡፡ ችሮታቸው በጣም የሚበዛው ደግሞ በሮመዳን ወር ጂብሪል ጋር በሚገናኙበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ወር በየሌሊቱ ከጅብሪል ጋር እየተገናኙ ቁርኣንን ይማማሩ ነበር፡፡ በአላህ ይሁንብኝ ያለህ መላክተኛ በበጎ ሥራ ከልቅ ንፋስ የበለጠ ቸር ነበሩ፡፡ ይህም ታድያ ገንዘብ በመስጠት የተወሰነ ሳይሆን ወላጅ ማክበርን፣ ዝምድና መቀጠልን፣ መተዛዘን፣ መዋደድን እንዲሁም መብትና ግዴታ ማክበርንም ያካትታል፡፡

አንድ ሙስሊም በዚህ ውር አሁንም ቁርአን መቅራትና ትርጉሙን ማስተንተን ተራዊሀን በመስገድ ኢባዳውን ሊያበረክት ይገባል፡፡ ነብያችን እንዲህ ይላሉ፡ በሙሉ እምነት መንዳንም አስቦ በሮመዳን ወር ሌለት ስግደት ያደረሰ ሰው ከዚያ በፊት የነበረው ወንጀሉ ይማርለታል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን አኢሻእንዲህ ብለዋል፡፡ ያለህ መላከተኛ አንድቀን በሌለት ወጡና መስጊድ ውስጥ ሰገዱ ሰዎችም አብረዋቸው ሰገዱ፡፡ ጧትም ሰውች ሰሊዚህ ስግደት አወሩ በሚቀጠለው ቀን ብዛት ያለቸው ሰዎች ተጨመሩ፡፡ አሁንም ጧት ሰዎች ስለስግደቱ ተነጋገሩ በሦስተኛው ቀን በመስጊድ የተገኙት ሰዎች ቁጥር በጣም ጨመረ፡፡ ነብያችንም ወጡና አብረዋቸው ሰገዱ፡፡ በአራተኛው ቀን መስጊዱ ሰዎችን አልቻለም፡፡ ነብያችንም ለፈጅር ሶላት እንጂ አልወጡም፡፡ የፈጅርን ሶላት አንደጨረሱ ወደሰዎቹ ዞር አሉና የምስክር ቃለን ተናገሩ ከዚያ (ከዚህ በመቀጠልም የናንተን ሁኔታ አጥቸው አይደልም ሌሊት ለስግደት ያልወጣሁት ነገር ግን ግድ ይደረግባችሁና እናነትም አቅም ታጡ ይሆናል ብየ ስለፈራሁ ነው አሉ)፡፡ በኋላ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ የተባሉት ኸሊፋ በዘመናቸው ሰዎች በአንድላይ እንዲስግዱ መወሰናቸውን አብደራህምን ኢብን አብደልቃሪዪ የተባሉት ባልደረባ እንዲህ በማለት አውርተዋል፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ከዐመር ቢንኸጣብ ጋር ወደመስጊድ ወጣሁ ሰዎች ተበታትነው አንዱ ለብቻው ሌላው ጥቂት ሰዎችን እየመራ ሲሰግዱ አየን፡፡ እነዚህን ሰዎች አንድ አንባቢ አየመራቸው እንዲስግዱ ባሰባሰባቸው ደግ ይመስለኛል አሉ፡፡ የሙስሎሙችን መሰባሰብና እንዷነት በማሰብ ኡብይ ኢብን ካዕብ የተባሉት ባልደረባ እንዲመሯቸው አደረጉ፡፡

እዚህ ላይ እውነተኛ ፆም ማለት ከክፉ ሥራ፣ ወንጀልና ኃጢያት መፆም መሆኑን ለመረጋገጥ አንወዳለን፡፡ ከራሀብና ጥም የዘለለ ትርፍ የሌለው ስንት ፆመኛ አለ፡፡ ያለህ መላከተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) አንዲህ ይላሉ (በዙ ሰዎች ከፆማቸው ያላቸው እጣ ፈንታ ረሀብና ጥም ብቻ ነው፡፡ ብዙ ሰዎችም የሌሊት ስግደታቸው እጣፈንታ እንቀልፍ ማጣት ብቻ ነው)፡፡ እንዲሁም እንዲህ ይላሉ (የሃሰትን ቃልና በሱም መስራትን ያላቆመ ሰው አላህ የሱን ምግብና መጠጥ መተው አይፈለገውም)፡፡ ጃቢር የተባሉ ባልደረባ እንደዚህ ብለዋል፡ ‹በምትፆምበት ጊዜ ጆረህ፣ዓይንህና ምላሰህ ከእርም ነገርና ውሸት ይጹሙ፡፡ አገልጋይህን ማሰከፋትህን ተው፡፡ ክብርና ርህራሄ ይኑርህ የጾምና የፍሰካህን ቀናት አኩል አታድርጋቸው፡፡

ሁላችንም የተባረከው የሮመዳን ወር የልግሳና፣ የጥረትና የሥራ ወር መሆኑን የማወቅ ግዴታ አለብን፡፡ በድካምና ዝለት ምክኒያት ጥረታችንና ስራችን ከሌላው ወራት ጥረታችን ሊቀንስ አይገባም፡፡ በርካታ ሰወች ለስንፍናና ድካም በመሸነፍ በሮመዳን

ወር መተኛት ያበዛሉ፡፡በዚህም የሰዎችን ጥቅም ይጋፋሉ፡፡ ይህ ደግሞ አላህን መፍራት ከሆነው ከፆም መሰረታዊ አላማ ጋር ይፃረራል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላ ተጻፈ፡፡ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና) ማለት ይሆናል፡፡ አላህን መፍራት ለትክትናና ስንፍና በመሸነፍ ሳይሆን በኢባዳ፣ በመልካም ሥራና በታማኝነት የአላህን ትእዛዝ በመከታተል ነው እውን ሊሆን የሚችለው፡፡
ከፆመኛ ባህርዮች እጅግ በጣም የተለየ የሚባለው የአላህን ትእዛዝ መከታተል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ታድያ በስራ ግዴታን መወጣትን ያካትታል፡፡ ስግደታችንና ፆማችን የሚከታተለው ጌታችን ስራችንን በሚገባ ማከናወናችንን ወይንም ለይስመላ መስራታችንንም ይከታተላል፡፡
አንደ ሰው ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ነገሮች ተቀዳሚው የተፈቀደ ስራ ውጤትና ተቀባይነት ያለው ፀሎት ነው ስንል አንዳችን ደመወዝ እተቀበለ ለስራው ተገቢውን ጥረት የማያደርግ ከሆነ ያሰው እርም ነግር እየበላ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ምክኒያቱም እንደዚያ ከሆነ ያለስራ ደመወዝ ወሰደ ማለት ስለሚሆን ነው፡፡ በተጨማሪም የግልም ይሁን የመንግስት የሥራውን ውል፣ ቃልና መስፈርትም ያጓደለ ይሆናል፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁ ለኔም ለናንተም ከአላህ ምህረትን እጠይቃለሁ፡፡

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ብቸኛ አጋሪ ከሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው አውርድ፡፡

## ሙስሊም ወንድሞች፡

ስራና ኢባዳ መንትያዎች ናቸው ኢባዳ ለአላህ አጥርተን የምናከናውነው ስራ ሲሆን በታማኝነት የምንፈጽመውም ስራ የአላህ የሆነ ኢባዳ ነው፡፡ ይህን ማለትም አንዱ ከሌላው ሊለይ አይችልም ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.) እንዲህ ይላል፡

وَقُلِ اعْمَلُوا فَسَيَرَى اللَّهُ عَمَلَكُمْ وَرَسُولُهُ وَالْمُؤْمِنُونَ وَسَتُرَدُّونَ إِلَىٰ عَالِمِ الْغَيْبِ وَالشَّ
هَادَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ

ትርጉም (በላቸውም ሥሩ አላህ ስራችሁን በርግጥ ያያልና መላክተኛውና ምእምናንም (እንደዚሁ ያያሉ) ሩቁንና ቀርቡን ሁሉ አዋቂ ወደሆነው (አላህ) በእርግጥ ትመለሳላችሁ፡፡ትሰሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል) ማለት ይሆናል፡፡
የነብያችንን፣ የባልደረቦቻቸውን እንዲሁም በመላው የእስልምናን ታሪክ ስንመራመር የሮመዳን ወር ስራና የምርት ወራት መሆኑን በግልጽ እናያለን፡፡ እንዲያውም በርካታ የእስላማዊ ድሎች የተከሰቱት በዚሁ በሮመዳን ወር ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ ወር የድሎች ወር ነው ማለት ይቻል፡፡ እውነት ከከንቱ የተለየበት ታላቁ የበድር ድል የተከናወነው በሮመዳን ውር ነበር፡፡ ታላቁ አላህ በዚያን ጊዜ ምእምናን ቁጥራቸውና ትጥቃቸው እጅግ አነስተኛ ቢሆንም በፈቃዱ ድል በማቀዳጀት እንዳከበራቸው እንዲህ ሲል ይገልፃል፡

وَلَقَدْ نَصَرَكُمُ اللَّهُ بِبَدْرٍ وَأَنتُمْ أَذِلَّةٌ فَاتَّقُوا اللَّهَ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ إِذْ تَقُولُ لِلْمُؤْمِنِينَ أَلَن
يَكْفِيَكُمْ أَن يُمِدَّكُمْ رَبُّكُم بِثَلَاثَةِ آلَافٍ مِّنَ الْمَلَائِكَةِ مُنزَلِينَ بَلَىٰ إِن تَصْبِرُوا وَتَتَّقُوا
وَيَأْتُوكُم مِّن فَوْرِهِمْ هَٰذَا يُمْدِدْكُمْ رَبُّكُم بِخَمْسَةِ آلَافٍ مِّنَ الْمَلَائِكَةِ مُسَوِّمِينَ وَمَا جَعَلَهُ
اللَّهُ إِلَّا بُشْرَىٰ لَكُمْ وَلِتَطْمَئِنَّ قُلُوبُكُم بِهِ وَمَا النَّصْرُ إِلَّا مِنْ عِندِ اللَّهِ الْعَزِيزِ الْحَكِيمِ

ትርጉሙም (በበድርም እናንተ ጥቂቶች ሁናችሁ ሳለ አላህ በእርግጥ ረዳችሁ፡፡ አላህንም ታመሰግኑት ዘንድ ፍሩት፡፡ ለምእምናን ጌታችሁ በሦስት ሺህ መላእክት የተወረዱ ሆነው ቢረዳችሁ አይበቃችሁምን በምትል ጊዜ (አስተውስ)፡፡ አዎን ብትታገሱና ብትጠነቀቁ ከዚህም ፍጥነታቸው (ጥላቶቻችሁ) ቢመጡባችሁ ጌታችሁ ምልክት ባላቸው አምስት ሺህ መላእክቶች ይረዳችኋል፡፡ አላህም (እርዳታውን) ለናንተ ብስራትና ልቦቻችሁ በርሱ እንዲረኩ እንጂ አላደረገም፡፡ ድልም መንሳት አሸናፊ ጥበበኛ ከሆነው አላህ ዘንድ እንጂ ከሌላ አይደለም፡፡
ታላቁ አላህ መላክተኛውንና ምእምናን ያከበረበት እንዲሁም ከሀደትና ከሃዲዎችን ያዋረደበት ታላቁ የመካ ከፈታ ድልም የተከናወነው በዚሁ በሮመዳን ወር ነበር፡፡ በዘመናችንም ታላቁ አላህ ግብጽ ክብሯንና ምድሯን እንዲታስመልስ ስኬትን የቸረበት የሮመዳን አስር (አክቶበር ስድስት) ድል የተከሰተው በሮመዳን ወር ነበር፡፡ የግብጽ ጦር አርማ አላሁ አክብር፣ ጾም፣ ስግደትና የልብ ጸሎት ስለነበር ሙሉ ድል ተቸረ፡፡

ለሃማኖት፣ ለአገርና ለክብር ባደረገው ትግል ጠላትን ከሀገር አባረረ፡፡ ያም ተግባሩና ያተቀዳጀው ድል በግብጽ ጥቃትን ለመፈጸም ለሚያስብ ወገን ሁሉ ተጨባጭ ትምህርት ሆነ፡፡
ድልን እንዲንቸርና የፍትህና እውነትን መሰረት ለማጠናከር፣ አገርና ክብርን ለመጠበቅ አቅም እንዲኖረን እንዲሁም የሙስሊሙ ማህበረሰብን ከአለም ማህበረሰብ መካከል ቦታና ሞገሱን ያስመልስ ዘንድ በተለያዩ የህወታችን ዘርፎች የመሮመዳንን መንፈስ እንደገና ማስመለስ እጅጉን ያሰፈልገናል፡፡ ይህም ሊረጋገጥ የሚችለው አንድ አቋም በመያዝ፣ ለአንድ አላማ በመስራት፣ ጥረትን በማስፋትና ለመላ የሰው ልጅ መልካምን በመስራት ብቻ ነው፡፡
የአለማቱ ጌታ ጌታችን ሆይ! በሻዕባን ወር በረከትን አብዛልን ከሮመዳንም አድርሰን እሱንም ከኛ ተቀበለን፡፡

**(42)**

## ረመዳን ከእሳት ነፃ መሆኛ ወር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጸሐፍ

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ፡፡ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና) ማለት ይሆናል፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (የረመዳንን ወር በሙሉ እምነትና ምንዳን አስቦ የፆመ ሰው ከዚያ በፊት የሰራው ወንጀሉ ይማርለታል) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም

ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል**

አላህ (ዐ.ወ.) የረመዳንን ውር በሌሎች ወራቶች በማይገኙ በርካታ ስጦታዎችና በተለዩ ነገሮች ለየት ያለ ወር አድርጎታል፡፡ በሱ የሰማይ መጽሐፎች የወረዱበት መሆኑና የቅን መንገድ መምሪያ ወርነቱ ከነዚህ ችሮታዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡

شَهْرُ رَمَضَانَ الَّذِي أُنْزِلَ فِيهِ الْقُرْآنُ هُدًى لِلنَّاسِ وَبَيِّنَاتٍ مِنَ الْهُدَى وَالْفُرْقَانِ

ትርጉሙም (እንዲተጾሙት የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ፣ ከቅን መንግድና (ወነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲሆን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (የኢብራሂም ጽሑፎች በረመዳን ወር የመጀመሪያ ሌሊት ተወረዱ፣ ተውራት ደግሞ ከረመዳን ወር ስድስት ቀናት ካለፉ በኋላ ተወረደ፣ ኢንጂልም ከረመዳን አስራ ሶስት ቀናት ካለፉ በኋላ ተወረደ፣ ዘቡርም ከረመዳን አስራ ሰምንት ቀናት ካለፉ በኋላ ተወረደ እንዲሁም ቁርኣን ከረመዳን ሃያ አራት ቀናት ካለፉ በኋላ ተወረደ)፡፡

ከነዚህ ችሮታዎች መካከል ሌላው ደግም የጸሎት ወር መሆኑ ነው፡፡ ጸሎት ከአምልኮት ስርኣቶች ታላቁና አንድ ባሪያ ወደጌታው ከሚቃረብባቸው ትእዛዛት እጅጉን ግዙፉ ነው፡፡ የታላቁ አላህን መጽሐፍ የሚያስተነትን ሰው የጸሎት አንቀጽ ከጾም አንቀጾች መካከል ሰፍራ ያገኛታል፡፡ ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡

وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌ أُجِيبُ دَعْوَةَ الدَّاعِ إِذَا دَعَانِ فَلْيَسْتَجِيبُوا لِي وَلْيُؤْمِنُوا بِي لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ

ትርጉሙም (ባሮቼ ከኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው) እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፡፡ በኔም ይመኑ፡፡ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና)፡፡

ይህም ታዲያ የጾመኛ ሰው ጸሎት ተቀባይነት እንደሚያገኝ ያለውን ተስፋ ያንጸባርቃል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (ለአንድ ጾመኛ የማይመለስ የሆነ ጸሎት አለው)፡፡ በሌላ ሐዲስም እንዲህ ይላሉ፡ (ሦስት ሰዎች ጸሎታቸው አይመለስም፡ ፍትሃዊ መሪ፣ ጾመኛ እስከሚያፈጥር ድረስ፣ የተበዳይን ጸሎት ፈጣሪ

ከደመና በላይ ያነሳታል የሰማይ በሮችም ይከፈቱላታል፡፡ ጌታም (ዐ.ወ.) እንዲህ ይላል በአሸናፊነቴ እምላለሁ ከጊዜም በኋላ ቢሆንም እንኳ ድል እንዲተቀዳጂ አድርጋለሁ)፡፡ ከነዚያ ከረመዳን ወር መለያ ነገሮች ዋናው ደግሞ አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ወር ከእሳት ነፃ መሆኛ ወር ማድረጉ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (የረመዳን የመጀመሪያ ሌሊት በገባ ጊዜ ሰይጣናትና አመጸኛ አጋንንት ይጠፈራሉ፡፡ የገሀነም በሮች ይዘጋሉ አንዱም እንኳ አይከፈትም፡፡ የጀነት በሮች ደግሞ ይከፈታሉ አንዱም እንኳ አይዘጋም፡ ፡ ከዚያም ለፋፊ እንዲህ በማለት ይለፍፋል፣ ደግ ነግር ከጃይ የሆንክ ሁሉ ወዲህ ና፣ ተንኮል ከጃይ የሆንክ ሁሉ ከተንኮልህ ተቆጠብ፡፡ (በዚህ ወር) ለአላህ ከእሳት ነፃ የሚያደርጋቸው (ባሮች) አሉት)፡፡በሌላ ሐዲስም እንዲህ ይላሉ፡ (ለአላህ በፊጥራ ጊዜ ከእሳት ነፃ የሚያደርጋቸው ባሮች አሉት፡፡ እሱም በየአንዳንዱ የረመዳን ሌሊት ነው)፡ ፡ ከእሳት ነፃ ሆነ ማለት አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ታላቅ ተድላ የቸረው ሰው ምንም እሳት አይነካውም ማለት ነው፡፡

ጾም ከመልካም ስራ በሮች አንደኛው ነው፡፡ መለያውም ማንኛውም ባሪያ ከእሳት አጥብቆ የሚጠነቀቅበት መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ (ጾም አንድ ባሪያ ከእሳት የሚድንበት መከታ ነው)፡፡ በሌላ ሐዲስም እንዲህ ይላሉ፡ (አንድ ባሪያ በአላህ መንገድ አንድን ቀን አይጾምም አላህ በዚያ ቀን ምክኒያት አካሉን ከእሳት የሰባ ምጻው(ወራት) ያህል ያራቀው ቢሆን እንጂ)፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይወደድና) ሙኣዝ ኢብን ጀበል እንዲህ ብለዋል፡ አንድ ወቅት ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር አብሬ እጓዝ ነበር፡፡ አንድ ቀን ማለዳ በጣም ቀርቢያቸው መጓዝ ጀምርን፡፡ ገለል ብለው ባያኋቸውም ጊዜ እንዲህ አልኳቸው፡ ያላህ መላክተኛ ሆይ ከእሳት አርቆ ጀነት የሚያስገባኝ ስራ ንገሩኝ፡፡ ያን ጊዜ እንዲህ አሉ (ስለአንድ ታላቅ ነገር ነው የጠየቅሀኝ፡፡ እሱም አላህ ላገራለት ሰው ገር ነው፡፡ በሱ ምንንም ነገር ሳታጂጋራ አላህን መገዛትህ፣ ስግደትን ደንቡን ጠብቀህ መስገድህ፣ ዘካን መስጠትህ፣ ረመዳንን መጾምህና በበይቱላህ ሃጅን ማድግህ ነው፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡፡ ስለመልካም ስራ በሮች ልንገርህን ጾም መከታ ነው፣ ምጽዋት ውሃ እሳትን እንደሚያጠፋ ሁሉ ኃጢያትን ያጠፋል)፡፡ እንዲሁም ጾም በእለተ ትንሳኤ አላህ (ዐ.ወ.) ምልጃቸውን ከሚቀበላቸው አማላጆች አንዱ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (ጾምና ቁርአን በቂያማ እለት ለአንድ ባሪያ ያማልዳሉ ጾም ጌታ ሆይ! እኔ በቀን ምግብና ፍተወትን ከልከየው ነበርና የሱን ምልጃ ተቀበለኝ ይላል፡፡ ቁርኣንም በሌሊት እንቅልፍን ከልከየው ነበርና የሱን ምልጃ ተቀበለኝ ይላል፡፡ ከዚያም ምልጃቸው ተቀባይነት ያገኛል አሉ)፡፡

እንዲሁም ጾም ከኣለህ ምህረትን ከሚያስገኙ ነገሮች አንዱና ከጀነት መንገዶች አንደኛው መንገድ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለጹዋሚ ባሮች ምህረት እንደሚያደርግና ታላቅ ምንዳም እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቷል፡፡ እንዲህም ብሏል፡

إِنَّ ٱلْمُسْلِمِينَ وَٱلْـ مُسْلِمَاتِ وَٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَاتِ وَٱلْقَانِتِينَ وَٱلْقَانِتَاتِ وَالصَّادِقِينَ وَالصَّادِقَاتِ وَالصَّابِرِينَ وَالصَّابِرَاتِ وَٱلْخَاشِعِينَ وَٱلْخَاشِعَاتِ وَٱلْمُتَصَدِّقِينَ وَٱلْمُتَصَدِّقَاتِ وَالصَّائِمِينَ وَالصَّائِمَاتِ وَٱلْحَافِظِينَ فُرُوجَهُمْ وَٱلْحَافِظَاتِ وَٱلذَّاكِرِينَ اللَّهَ كَثِيرًا وَٱلذَّاكِرَاتِ أَعَدَّ اللَّهُ لَهُمْ مَغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا

ትርጉሙም (ሙስሊሞች ወንዶችና ሙስሊሞች ሴቶች፣ ምእምናንና ምእምናትም፣ ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶችም፣ እውነተኛ ወንዶችና እውነተኛ ሴቶችም፣ ታጋሾች ወንዶችና ታጋሾች ሴቶችም፣ አላህን ፈሪዎች ወንዶችና አላህን ፈሪዎች ሴቶችም፣ መጽዋቾች ወንዶችና መጽዋቾች ሴቶችም፣ ጹዋሚዎች ወንዶችና ጹዋሚዎች ሴቶችም፣ (ካልተፈቀደ ስራ) ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ወንዶችና ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ሴቶችም፣ አላህን በብዙ አውሽዎች ወንዶችና አላህን በብዙ አውሽዎች ሴቶችም፣ አላህ ለነርሱ ምህረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡ (ረመዳንን በሙሉ እምነትና ምንዳን አስቦ የጾመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል)፡፡ በዚህ በረመዳን ወር አንድ ሰው በኢባዳ ያሳለፋት ከሆነ ወንጀሎቹ የሚማሩለት የሆነቸው የቀድር ሌሊትም ትገኛለች፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (የቀድርን ሌሊት በሙሉ እምነትና ምንዳን አስቦ በስግደት ያሳለፈ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል)፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጾም ወደጀነት ከሚያደርሱ መንገዶች አንደኛው መንገድ መሆኑን ሲያበራሩ እንዲህ ይላሉ፡ (በጀነት ውስጥ የውጭ ክፍሏ ከውስጥ በኩል የውስጥ ክፍሏም ከውጭ በኩል የሚታይ የሆነች ክፍል አለች፡፡ ይህችን ክፍል አላህ ያዘጋጃት ምግብን ለመገበ፣ ቃሉን ልዝብ ላደረገ፣ ጾሙን ለቀጠለና ሰዎች ሲተኙ ተነስቶ ስግደት ለሰገደ ሰው ነው) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ የሚከተለውን አውርተዋል፡ የአላህ መላክተኛ ከእለታት አንድ ቀን ባልደረቦችን እንዲህ በማለት ጠየቁ፡ (ከናንተ ማነው ዛሬ ጾም ይዞ ያነጋ አቡ በክርም እኔ አሉ፡፡ እንደገናም እንዲህ አሉ (ከናንተ ማነው ዛሬ በሽተኛን የጠየቀው አሁንም አቡ በክር አኔ አለሁ፡፡ ነብያችንም (ከናንተ ማነው በአስከሪን ሽኘታ የተሳተፈው እደገናም አቡ በከር አኔ አሉ ነብያችንም ( ከናት ማነው ዛሬ ለምስኪን ምግብ የሰጠው አሁንም አቡ በክር እኔ አለ፡ ፡ ያን ጊዜ ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ አለ፡ (እነዚህ ባህሪዎች ባንድ ቀን ውስጥ በአንድ ሰው ባንድ ላይ አይሰባሰቡም አላህ ጀነት ያስገባው ቢሆን እንጂ)፡፡ አቡ ኡማማ አልባሂሊ የተባሉ ባልደረባ ነብያችን ጋ (ሶ.ዐ.ወ.) ሄደው ያአላህ መላክትኛ

ሆይ! በሱ ጀነት የምገባበትን ስራ እንዲሰራ እዘዙኝ አሉ በዚያን ጊዜ ነብያችን እንዲህ አሉ (ጾምን አጥበቀህ ያዝ አሱ አምሳያ የለውምና)፡፡
ጾም ስር መሰረቱን ማንም የማይደርስበት ከአላህና ከባሪያው መካከል ያለ ምስጢር ነው፡፡ አንድ ጾም የያዘ ሰው አላህ እንጂ ሌላ ፍጡር በማያየበት ቦታ ሊገኝ ይችላል፡፡ በዚያን ጊዜ በጾም አላህ እርም ያደረገውን ነገር መፈጸም ሲችል የሚታቀበው ሁሉን ነገር የሚያውቅ ጌታ በመኖሩ እርግጠኛ ስለሆነና ቅጣተን በመፍራት እንዲሁም ምንዳውን በመከጀል ብቻ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ ۖ مَا يَكُونُ مِن نَّجْوَىٰ ثَلَاثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمْ وَلَا خَمْسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمْ وَلَا أَدْنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَا أَكْثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمْ أَيْنَ مَا كَانُوا ۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوا يَوْمَ الْقِيَامَةِ ۚ إِنَّ اللَّهَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ

ትርጉሙም (አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውን በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያቅ መሆኑን አታይምን ከሦስት ሰዎች መሸካሾክ አይኖርም አርሱ አራተኛቸው ቢሆን እንጂ ከአምስትም (አይኖርም) እርሱ ስድስተኛቸው ቢሆን እንጂ ከዚያ ያነሰም የበዛም (አይኖርም) አርሱ የትም ቢሆኑ አብሯቸው ቢሆን እንጂ ከዚያም በትንሳኤ ቀን የሰሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አላህ ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው) ማለት ነው፡፡
ጾም አላህ (ሱ.ወ.) ወደሱ በማስጠጋት ክብር ከሰጣቸውና ምንዳውን ለሱ ካደረጋቸው ኢባዳዎች አንዱ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.0.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አላህ (0.ወ.) እንዲህ ብሏል የሰው ልጅ የሰራው ስራው ሁሉ የራሱ ነው ጾም ሲቀር አሱ የኔ ነው አኔ በራሲ ምንዳውን እሰጣለሁ)፡፡ በሌላ ሓዲስም እንዲህ ብለዋል (የሰው ልጅ የሰራው ስራ ሁሉ እጥፍ ድርብ ይሆንለታል፡፡ አንድ መልካም ስራ አስር እጥፍ አስከ ሰባት መቶም እጠፍ ይሆንለታል፡፡ አላህ አንዲህ ብሏል ጾም ሲቀር እሱ የኔ ነው እኔ በራሴ ምንዳውን እሰጣለሁ...) በመሆኑም የእምነቱ ሊቆች ‹ጾም ከሌሎች ኢባዳዎች ለመብለጡ አለህ (ሱ.ወ.) ጾም የኔ ነው ማለቱ ብቻ በቂ ነው ይላሉ፡፡ ይሀውም ጾም ይዩልኝ ይስሙልኝ የማይገባበት ለአላህ የጠራ ኢባዳ በመሆኑ ነው፡፡
ጾመኛ ሰው መንጊዜም የፈጣሪውን ትእዛዝ ይከታተላል፣ በዚህ በተባረከ ወርም አላህ ከእሳት ነፃ ከሚደርጋቸው ባሮች ውስጥ ለመካተት ተስፋ በማድረግም ችሮታውን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

መስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሳለም የነብያትንና የመልእክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሎም ወንድሞች**

ከእሳት ነፃ የሚያደርገው ጾም ያ ጾመኛውን ከመጥፎ ባህሪ ሁሉ የሚገታ፣ ከሱና ከወንጀል መካከል ጠንካራ አጥር የሚሆነውና የጾመ መሰረትና ፍሬ የሆነውን አላህን መፍራትን እውን የሚያደርገው ጾም ነው፡፡ በመሆኑም እርም ነገር ከመብላት፣ የሰውችን ክብር ከመንካት፣ አንዲንም ሰው ከማማት፣ ሰዎችን ከማጣላትና በሀሰት ከመመስከር ሊቆጠብ ይገባል፡፡ አላህ የሚወደውን እንጂ አለመናገር፣ አንዲሁም የጾመኞችን ባህርይ በመላበስ በደግ ነግር መከላከል እንጂ ለመጥፎ ነገር መጥፎ አጸፋ አለመስጠት ይጠበቅበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

وَإِذَا سَمِعُوا اللَّغْوَ أَعْرَضُوا عَنْهُ

ትርጉሙም (ውድቅንም ቃል በሰሙ ጊዜ ከርሱ ይርቃሉ) ማለት ነው፡፡

وَالَّذِينَ هُمْ عَنِ اللَّغْوِ مُعْرِضُونَ

ትርጉሙም (እነዚያም አነርሱ ከውድቅ ንግግር ራቂዎች) ማለት ነው፡፡

ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ

ትርጉሙም (በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው (ጠባይ) መጥፎይቱን ገፍትር) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡ (ጾም መከታ ነው፡፡ አንዳችሁ ጾም በሚይዝበት ቀን እርኩስ ቃል አይናገር፣ ድምጹንም ከፍ አያድርግ አንድ ሰው ቢሳደበው ወይም ሊታገለው ቢሞክር እኔ ጾመኛ ነኝ ይበል)፡፡ አንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡ (ጾም ማለት ከመብል መጠጥ መታቀብ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጾም ማለት ከውድቅና እርኩስ ቃል መታቀብ ነው)፡፡ አንድ ሰው ከአገር የሌለ ውንድሙን ክብር በመጠበቅም ከእሳት ነፃ ሊሆን ይችላል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡ (ከሃሜት የወንድሙን ሲጋ የተከላከለን ሰው አላህ በእውነት ከእሳት ነፃ ሊያደርገው ይገባል)፡፡

እውነተኛ ጹዋሚ የሚባለው ያ በጾም ምንዳ የሚጠቀመው ጾመኛ ነው፡፡ ይህም ጾመኛ የጾሙ ገጽታ ለሰዎች በሚያሳየው ጠባይ ጎልቶ ይታያል፡፡ ምክኒያቱም ጾም ጾመኛን የነፍሱን ልጓም መቆጣጠርንና ማስተካከልን ያስተምራልና፡፡ ነፍስ ሁሉ ጌታዬ የጠበቃት ካልሆነች በስተቀር በመጥፎ ነገር በእርግጥ አዛዥ ናት፡፡ አንድ ሰው ነፍሱን

ያለልጓም የለቀቃት ከሆነ ጥፋት ወስት ተከተዋለች፡፡ ነገሮቹዋን ከተቆጣጠረ ግን ወደከፍተኛ ደረጃና ወደፈለገው ቦታ እንዲታደርሰው ሊገራት ይችላል፡፡ ይህ ተግባር ታዲያ የጌታን ታላቅነት በማሰብ ሆዱ፣ ብልቱ፣ ምላሱና መላ አካላቱ አላህ (ዐ.ወ.) እርም ካደረገው ነገር ሁሉ በእምነት ለጾመ ሰው እንጂ እውን ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲሁም እውነተኛ ጾመኛ የሚባለው መልካምን ስራ ለጌታው በማጥራት የሚያበዛና ተቀባይነት ያገኝ ይሆን ወይስ ይመለስብኝ ይሆን እያለ የሚሰጋ ሰው ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ነብዩ ኢብራሂም የተከበረውን ካዕባ እንዲገነቡ በታዘዙ ጊዜ የነበሩበትን ሁኔታ እንዲህ በማለት ይገልጽልናል፡

وَإِذْ يَرْفَعُ إِبْرَاهِيمُ الْقَوَاعِدَ مِنَ الْبَيْتِ وَإِسْمَاعِيلُ رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ أَنْتَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ

ትርጉሙም (ኢብራምና ኢስማኢልም ጌታችን ሆይ ከኛ ተቀበል አንተ ሰሚውና አዋቂው አንተ ነህና የሚሉ ሲሆኑ ከቤቱ መሰረቶችን ከፍ ባደረጉ ጊዜ (አስታውስ) ማለት ነው፡፡
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰይዲና አሊ እንዲህ ይሉ ነበር፡ ከስራ ይልቅ ለተቀባይነቱ ትኩረት ስጡ እንዲህ የሚለውን የአላህን ቃል አልሰማችሁምን ፡

إِنَّمَا يَتَقَبَّلُ اللَّهُ مِنَ الْمُتَّقِينَ

ትርጉሙም (አላህ የሚቀበለው እኮ ከጥንቅቆቹ ብቻ ነው አለ) ማለት ነው፡፡ ጌታዬ ሆይ ከእሳት ነፃ ከደረግሃቸውና ስራቸው ከተቀብለካቸው ባሮችህ አድርገን፡፡

# (43)

## ረመዳን የልግስና፣ የቸርነትና  የድሎች ወር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

الَّذِينَ يُنْفِقُونَ أَمْوَالَهُمْ بِاللَّيْلِ وَالنَّهَارِ سِرًّا وَعَلَانِيَةً فَلَهُمْ أَجْرُهُمْ عِنْدَ رَبِّهِمْ وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ.

ትርጉሙም (እነዚያ ገንዘቦቻቸውን በሌሊትና በቀን በድብቅም በግልጽም የሚለግሱ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፡፡ በነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነርሱም አያዝኑም) ማለት ነው፡፡ ለአለው ለአለማቱ ጌታ ይገባው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሐዲሳቸው (አንድም በአላህ ባሮች ላይ የሚነጋ ሌሊት የለም ሁለት መልኣኮች ወርደው አንደኛው ፡ ጌታዬ ሆይ ለጋሽን ሰው በለገሰው ነገር ምትክ ስጠው ሌላኛው ደግሞ ጌታዬ ሆይ ግነዘቡን ጨምድዶ ያዘን ሰው ጥፋትን ፍረድበት የሚሉ ቢሆን እንጂ)፡፡ ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡፡**

የአስልምና ሃይማኖት የላቀ ደረጃ ያለቸው እሴቶችና አርኣያነት ያላቸው መልካም መግባሮች ሃይማኖት ነው፡፡ ከነዚህ ንጹሁ ሃይማኖታችን ከሚያዝባቸውና እንዲንላበሳቸው ከሚያዘን መልካም ምግባሮች አንዱ የቸርነት ጠባይ ነው፡፡ ይህ ምግባር የአላህ መልእክተኞች ምግባርና የጻዲቃን ባህርይ ነው፡፡ በዚህ ምግባር አማካይነት ከሰዎች መካከል ፍቅር፣ መዋደድና ወንድማዊ ስሜት ይሰፍናሉ፡፡ እሱም ታድያ በመተሳሰርና በስጦታ የታነጸ በታማኝነትና ቃል አክባሪነት የተሞላ ጠንካራና ውሁድ ማህበረሰብ ያዋቅራል፡፡ በሱም እንዲህ የሚለው የነብያችን(ሶ.ዐ.ወ.) ቃል ጎልቶ ይታይበታል (ምእምናን በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና በመተሳሰባቸው ከሱ አንዱ ክፍል በሚታመም ጊዜ ሌሎችም አካላት እንቅልፍ በማጣትና በመሰቃየት እንደሚጠራሩለት አንድ አካል ናቸው)፡፡

ቸርነት ግኝነቱ የተረጋገጠ የሆነውና በረከት የሚያወርደው የፈጣሪ ባህርይና ከደጋግ ስሞቹም አንደኛው ስሙ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እሱ ያ በሩ የማይዛጋ፣ ስጦታው

የማያልቅ፣ እሱን የሚለምን ባዶውን የማይመለስና በሱም ተስፋ የጣለ ተስፋው የማይመነምን ለጋሽና ስጦታው የሰፋ ጌታ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አላህ ቸር ነው ቸርነትነም ይወዳል መልካም ምግባርን ይወዳል መጥፎውን ደግሞ ይጠላል)፡፡ በሌላ ሐዲስም (አላህ ቸር ነው ቸርነትን ይወዳል፣ ለጋስም ነው ልግስናንም ይወዳል) ይላሉ፡፡ በሌላ የተቀደሰ ሐዲስም አላህ እንዲህ ይላል ብለዋል(...ባሮቼ ሆይ! እኔ ቅንን መንገድ ከመራሁት በስተቀር ሁላችሁም በጥሜት ውስጥ ናችሁ፡፡ ቅንን መንገድ እንዲመራችሁ ለመኑኝ ቅኑን መንገድ እመራችኋለሁ፡፡ ባሮቼ ሆይ! እኔ ከመገበሁት በስተቀር ሁላችሁም ረሀብተኞች ናችሁ፡፡ ምግብን ከኔ ለምኑ እኔ ምግብን እሰጣችኋለሁ፡፡ ባሮቼ ሆይ! እኔ ካለበስሁት በስተቀር ሁላችሁም እርዝተኞች ናችሁ  ከኔ ልብስን ለምኑ እኔ ልብስን እሰጣችኋለሁ ባሮች ሆይ እናንተ በሌትም በቀንም ስህተትን ተፈጽማላችሁ እኔ ወንጀልን በሙሉ እምራለሁ ከኔ ምህረትን ለምኑ እኔ ምህረት አደርግላችኋለሁ... ባሮች ሆይ! ከናንተ የመጀመሪያችሁም የመጨረሻችሁም፣ ሰዋችሁም ጅናችሁም በአንድ ቦታ ቆመው ቢለምኑኝና ለያንዳንዱም ሰው የጠየቀውን ሁሉ ብሰጠው ያ ስጦታ ከኔ መንግስት መርፌ በባህር ገብታ ስትወጣ የምታጎለውን ያህል እንጂ አያጎለም)

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ይላሉ (የአላህ እጅ ወሰን በሌለው ሲሳይ የተሞላ ነው፡፡ ሌት ተቀን የማያቋርጥ ስጦታ አያጓድለውም ምድርና ሰማን ከፈጠረ ጀምሮ የሰጠውን ሁሉ አያችሁን ይህ ሁሉ በእጁ ካለው ሲሳይ ምንም አላጓደልም)፡፡

የተከበረው ቁርአንም ቸርነት የነብያትና የአላህ መልእክተኞች ባህርይ መሆኑን በኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ታሪክ አማካነት እንዲህ በማለት ገልጧል፡

**هَلْ أَتَاكَ حَدِيثُ ضَيْفِ إِبْرَاهِيمَ الْمُكْرَمِينَ *إِذْ دَخَلُوا عَلَيْهِ فَقَالُوا سَلامًا قَالَ سَلامٌ قَوْمٌ مُنكَرُونَ فَرَاغَ إِلَىٰ أَهْلِهِ فَجَاءَ بِعِجْلٍ سَمِينٍ فَقَرَّبَهُ إِلَيْهِمْ قَالَ أَلَا تَأْكُلُونَ**

ትርጉሙም (የተከበሩት የኢብራሂም እንግዶች ወሬ መጥቶሃልን  በርሱ ላይ በገቡና ሰላም ባሉ ጊዜ (አስታውስ) ሰላም ያልታቃችሁ ህዝቦች ናችሁ አላቸው፡፡ ወደቤተሰቡም ተዘነበለ፡፡ ወዲያውም የሰባ ወይፈን አመጣ፡፡ ለነርሱም (አርዶና ጠብሶ) አቀረበው፡፡ አትበሉም ወይ አላቸው) ማለት ነው፡፡

ነብዩ ኢብራሂም ከቸርነታቸው ብዛት የእንግዶች አባት የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) የሱን ችሮታና ተጨማሪ ትሩፋቱን እንዲናገኝ አንዳችን ሌላችንን እንዲናከብር እንዲህ በማለት አዟል፡

وَلَا يَأْتَلِ أُولُو الْفَضْلِ مِنكُمْ وَالسَّعَةِ أَنْ يُؤْتُوا أُولِي الْقُرْبَىٰ وَالْمَسَاكِينَ وَالْمُهَاجِرِينَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ ۖ وَلْيَعْفُوا وَلْيَصْفَحُوا ۗ أَلَا تُحِبُّونَ أَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَكُمْ ۗ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ .

ትርጉሙም (ከናንተም የችሮታና የክብረት ባለቤቶች የሆኑት ለቅርብ ዘመዶችና ለድሆች በአላህም መንገድ ለተሰደዱ ሰዎች ላይሰጡ አይማሉ፡፡ ይቅርታም ያደርጉ፡፡ (ጥፋታቸውን) ይለፉም አላህ ለናንተ ሊምር አትወዱምን  አላህም መሃሪ አዛኝ ነው) ማለት ነው፡፡

እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡

مَثَلُ الَّذِينَ يُنْفِقُونَ أَمْوَالَهُمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ كَمَثَلِ حَبَّةٍ أَنْبَتَتْ سَبْعَ سَنَابِلَ فِي كُلِّ سُنْبُلَةٍ مِائَةُ حَبَّةٍ ۗ وَاللَّهُ يُضَاعِفُ لِمَنْ يَشَاءُ ۗ وَاللَّهُ وَاسِعٌ عَلِيمٌ .

ትርጉሙም (የእነዚያ ገንዘቦቻቸውን በአላህ መንገድ የሚለግሱ ሰዎች (ልግስና) ምሳሌ በየዘለላው ሁሉ መቶ ቅንጣት ያለባቸውን ሰባት ዘለላዎች እንደ አበቀለች አንድት ቅንጣት ብጤ ነው፡፡ አላህም ለሚሻው ሰው (ከዚህም በላይ) ያነባብራል አላህም ችሮታው ሰፊ አዋቂ ነው) ማለት ነው፡፡

እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡

لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَٰكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَىٰ حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ

ትርጉሙም (መልካም ስራ ፊቶቻችሁን ወደምስራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ስራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመልአክትም በመጽሐፍትም በነብያትም ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሙች ለምስኪኖችም ለመንገደኞችም ለለማኞችም ... የሰጠ ሰው ስራ ነው) ማለት ነው፡፡

አሁንም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ላል፡

وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا . إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنْكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا . إِنَّا نَخَافُ مِنْ رَبِّنَا يَوْمًا عَبُوسًا قَمْطَرِيرًا . فَوَقَاهُمُ اللَّهُ شَرَّ ذَٰلِكَ الْيَوْمِ وَلَقَّاهُمْ نَضْرَةً وَسُرُورًا.

ትርጉሙም (ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለደሀ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ የምናበላችሁ ለአላህ ወዴታ ብቻ ነው፡፡ ከናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡ እኛ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱን ቀን ከጌታችን

አንፈራለንና (ይላሉ)፡፡ አላህም የዚያን ቀን ከፉት ጠበቃቸው (ፊታቸው) ማማርንና መደሰትንም ገጠማቸው) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ (ከገንዘብህ ምጽዋትን ስጥ አላህ ለአንተ ይሰጠሃልና) የረመዳን ወር የልግስና፣ የቸሮታ፣ የመናኘትና የስጦታ እንዲሁም የትብብር ወር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የቸሮች ቸር ሲሆኑ ችሮታቸው በጣም የሚበዛው በረመዳን ወር ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) ኢብን አባስ እንዲህ ብለዋል (ነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የቸሮች ቸር ነበሩ ችሮታቸው እጅጉን የሚበዛው በረመዳን ወር ከጅብሪል ጋር በሚገናኙበት ወቅት ነበር፡፡ ከጀብሪል ጋር በየሌሊቱ እየተገናኙ ቁርአንን ይማማሩ ነበር፡፡ በአላህ ይሁንብኝ የአላህ መልእክተኛ በመልካም ችሮታቸው ከልቅ ንፋስ የበለጠ ፈጣን ነበሩ፡፡
ነብያችን (ሶ.አወ.) በማንኛውም ሁኔታ ድሆችን አንዲንመግብ እንዲህ በማለት የሚያዙ ቢሆንም፡ (እናንተ ሰዎች ሆይ! ሰላምታን አሰራጩ፣ ምግብንም መግቡ፣ ሌሊት ሰዎች ሲተኙም ተነስታችሁ ስገዱ፡፡ በሰላም ጀነትን ትገባላችሁና)፡፡ እንዲሁም በማንናውም ጊዜ እንግዳን ማስተናገድ ታለቅ ምንዳ ያለው መሆኑን እንዲህ በማለት የሚያበስሩ ቢሆንም፡ (በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያመን ሁሉ እንግዳውን ያክብር)፡፡
ምግብ ማብላትም ሆነ እንግዳን ማስተናገድ በዚህ በረመዳን ወር ምንዳው እጅግ ታላቅና ከፍተኛ መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡ (አንድን ጾመኛ ያስፈጠረ ሰው የዚያን የጾመኛውን ያህል መንዳ ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የጾመኛው ምንዳ ምንም አይቀንስም) አንድን ጾመኛ የሚለው የነብያችን ቃል ሀብታምንም ደሀንም ዘመድንም ወዳጅንም የሚያካትት መሆኑን የእምነቱ ሊቆች አመልክተዋል፡፡ እንዲሁም ይህ ሐዲስ ችግርን ማቃለልንም ሆነ ጉዳይ ማውጣትን አልፎ በቤተሰብ፣ በጓደኛና በባልደረባ ማእድ በመሰባሰብ ከሰዎች መካከል ያለውን ትስስር ማጠናከርን ይጠቁማልም ይላሉ፡፡
ከላይ የተጠቀሰው ሐዲስ አሁንም ወደኢፍጣር መጥራትን፣ ምግብ ወደሱ መላክን፣ ስጦታ ማበርከትንና የኢፍጣር ማዘጋጃ ገንዘብ መስጠን የሚያካትት በመሆኑ በዚህ በተከበረው ወር እጦትን በማስወገድ ትብብርን እውን ማድረግ እንዲሁም ከሰዎች መካከል ያለውን የማህበራዊ ትስስር መጠናከር የሚሉትን ሁለት አላማዎች እቅፏል ይላሉ፡፡
(ከነርሱ አላህ ይውደድና) ባልደረቦች የአላህን ውዴታ በመከጀል በገንዘብም ሆነ በአካል አርአያነት ያለቸውን በርካታ የስጦታ፣ የልግስናና የችሮታ ተግባራት ይፈጽሙ ነበር፡፡ በተለይም በችግርና በመከራ ጊዜ የነበራቸው ትብብርና መረዳዳት እጅጉን የሚደነቅ ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የአሽአርዪዎችን ቤተሰብ ትብብረና መረደዳት

እንዲህ ሲሉ አሞካሽተዋል፡ (አሽአርዪዎች በጦርነት ገዚ ስንቃቸው ሲያልቅባቸው ወይም መድና ከተማ የልጆቻቸው ምግብ አነስተኛ በሆነ ጊዜ ያለቸውን ሁሉ በአንድ ጨርቅ ያከማቹና በአንድ እቃ ወስጥ አድርገው እንደገና እኩል ይካፈሉታል እነሱ የኔ ወገን ናቸው እኔም ደግሞ የነሱ ወገን ነኝ)፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይወደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንዲህ ብለዋል፡ አቡ ጠልሓ የተባሉት ሰው መዲና ውስጥ ከአንሷሮች የበለጠ ባለጸጋ ነበሩ ከንብረታቸው በጣም የሚወዱት (በይሩሓእ) የተባለውን አትክልት ነበር፡፡ መስጊዱ ፊትለፊት ነበርና ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እየገቡ በወስጡ ካለው ጥሩ ውሃ ይጠጡ ነበር፡፡ እንዲህ የምትለዋ አንቀጽ በወረደች ጊዜ፡

لَنْ تَنَالُوا الْبِرَّ حَتَّىٰ تُنْفِقُوا مِمَّا تُحِبُّونَ

(የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጎን ስራ (ዋጋውን) አታገኙም ) ምተለዋ አንቀጽ በወረደች ጊዜ አቡ ጠልሓ ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሄዱና የአላህ መላክተኛ ሆይ! ታላቁ አላህ (የምትወዱትን አስከምትለግሱ ድረስ በጎን ስራ አታገኙም) የምተለውን አንቀጽ በርሰዎ ላይ አወረደ ከንብረቴ ሁሉ የመወደው (በይሩሓእ) ነው፡፡ እሱን ከአላህ ዘንድ ምንዳውንና ድልቡን  የምጠበቀው ስጦታ አድረግሁት፡፡ የአላህ መላከተኛ ሆይ! እርሰዎ በአላህ ፈቃድ ለሚፈልጉት ይስጡት አሉ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ጎሽ ያ ትርፋማ ገንዘብ ነው አዎ ያ ትርፋማ ገንዘብ ነው አሉና ያልከውን ሰማሁ እኔ ለዘመዶችህ አድርገው አላለሁ አሉ፡፡ አቡ ጠልሓም እንዳልኩኝ አደርጋለሁ አሉና ለዘመዶቸዎና ለአጎተዎ ልጆች አከፋፈሉት)

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዑመር እንዲህ ብለዋል፡ (ከነብያችን ባልደረቦች አንዱ አንዲት ፍየል ስጦታ መጣችላቸው እርሳቸውም አገሌ ወንድሜና ልጆቹ ከኛ የበለጠ ይህች ፍየል ታስፈልጋቸዋለች በማለት ላኩላቸው ያኛውም እንደዚሁ አደረጉ በዚህ መልኩ ሰባት ቤት ዞራ ወደመጀመሪያው ሰውዬ ተመለሰች፡፡ የንጊዜ እንዲህ ምትለው አንቀጽ ወረደች፡

وَيُؤْثِرُونَ عَلَىٰ أَنْفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ

ትርጉሙም(በነሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ...) ማለት ነው፡፡ ባልደረቦች በዚህ መልኩ በልግስናና በቸርነት ይፎካከሩ ነበር፡፡ የአላህና የመልእክትኛውን ትእዛዝ ለመፈጸምና ለልግስናና ችሮታ ባለቤቶች አላህ ያዘጋቸውን ምንዳ በመከጀል በስጦታ ይሽቀዳደሙ ነበር፡፡

እኛ በአሁኑ ወቅት ይህን ዓይነት ባህርይ ለመላበስ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ የነብያችንን አስተምህሮ መሰረት በማድረገም ከስስምነትና ንፉግነት ገጽታ ልንርቅ ይገባል፡፡

ነብያችን (ሰ.አ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አጠገቡ ያለው ጎረቤቱ መራቡን እያወቀ እሱ ጠግቦ ያደረ ሰው በኔ አላመነም)፡፡ እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ይላሉ፡ (አንተ የሰው ልጅ ሆይ! የተረፈህን ብትሰጥ ላንተ መልካም ነው ሳትሰጥ ብትቀር ደግሞ ለአንተ መጥፎ ነው፡፡ የሚበቃህ ብቻ ከሆነ ግን አትወቀስም፡፡ ስትሰጥ ደግሞ ቀለባቸውን መስፈር ግድ በሆነብህ ዘመዶችህ ጀምር ሰጭ የሆነው የላይኛው እጅ ተቀባይ ከሆነው የታችኛው እጅ የተሻለ ነው)፡፡
እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡ (ትርፍ የጭነት ከብት ያለው ሰው የጭነት ከብት ለሌለው ሰው ይስጥ፡፡ ትርፍ ስንቅ ያለውም ስንቅ ለሌለው ሰው ይስጥ)፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአለህ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

እጅግ በጣም ታላቅና ከፍተኛ ልግስናና ቸርነት የሚባለው እራሱን መለግስና ራሱን በችሮታ አሳልፎ መስጠት ነው፡፡ እሱም የቸሮች ባህሪይና የክቡራን ገጽታ፣ ከራሱ ሰዎችን የማስቀደም ምግባር ከፍተኛው ደረጃ ነው፡፡ ባለቅኔ እንዲህ ይላል፡
ንፉግ በሰሰተ ጊዜ ራሱን ይለግሳል የራስ ልግስናም የልግስና ቁንጮ ነው
ከራስ ልግስና ታላቁ ደግሞ አገሩን፣ ድንበሩን፣ ወገኑንና ክብሩን ለመጠበቅ ድንበር አስከባሪ ወታደር የሚያደርገው መዋደቅ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (በአላህ መንገድ አንድ ቀን ዘብ መቆም ከዚህች አለምና በውስጧም ከለው ነገር ሁሉ የበለጠ ነው)፡፡ በሌላ ሐዲስም እንዲህ ይላሉ፡ (ሁለት ዓይኖች እሳት ፈጽሞ አትነካቸውም፡፡ አንደኛዋ አላህን በመፍራት ያነባች ዓይን ስትሆን ሁለተኛዋ ደግሞ በአላህ መንገድ በጥበቃ ያነጋች ዓይን ናት)፡፡ አሁንም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ይላሉ፡ (በኋላ እሳት ሊነካው የአንድ የአላህ ባሪያ እግር በአላህ መንገድ አፈር አይለወስም)፡፡ አንድ ሰው የራስ ልግስናን ሲፈጽም በዚህች አለምና በመጨው አለም የስኬት ዋስትና እንደሚያገኝ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ በማለት አብስሯል፡

يا أيها الذين آمنوا اصبروا وصابروا ورابطوا واتقوا الله لعلكم تفلحون

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ታገሱ ተበራቱም (በጦር ኬላ ላይ) ተሰለፉም ትድኑም ዘንድ አላህን ፍሩ)፡፡

የረመዳን ወር የድሎች ወር መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ምእምናን ከጥላቶቻቸው ጋር ሲነጻጸር ቁጥራቸውና ስንቃቸው እጅጉን ዝቅተኛ ከመሆኑ ጋር አላህ ድልን የቸረበት ታላቁ የበድር ጦርነት በዚሁ በረመዳን ወር ነው የተከናወነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

وَلَقَدْ نَصَرَكُمُ اللَّهُ بِبَدْرٍ وَأَنْتُمْ أَذِلَّةٌ ۖ فَاتَّقُوا اللَّهَ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ إِذْ تَقُولُ لِلْمُؤْمِنِينَ أَلَنْ يَكْفِيَكُمْ أَنْ يُمِدَّكُمْ رَبُّكُمْ بِثَلَاثَةِ آلَافٍ مِنَ الْمَلَائِكَةِ مُنْزَلِينَ بَلَىٰ ۚ إِنْ تَصْبِرُوا وَتَتَّقُوا وَيَأْتُوكُمْ مِنْ فَوْرِهِمْ هَٰذَا يُمْدِدْكُمْ رَبُّكُمْ بِخَمْسَةِ آلَافٍ مِنَ الْمَلَائِكَةِ مُسَوِّمِينَ .وَمَا جَعَلَهُ اللَّهُ إِلَّا بُشْرَىٰ لَكُمْ وَلِتَطْمَئِنَّ قُلُوبُكُمْ بِهِ ۗ وَمَا النَّصْرُ إِلَّا مِنْ عِنْدِ اللَّهِ الْعَزِيزِ الْحَكِيمِ

ትርጉሙም (በበድርም እናንተ ጥቂቶች ሁናችሁ ሳለ አላህ በእርግጥ ረዳችሁ፡፡ አላህንም ታመሰግኑት ዘንድ ፍሩት፡፡ ለምእምናን ጌታችሁ በሦስት ሺህ መላእክት የተወረዱ ሆነው ቢረዳችሁ አይበቃችሁምን በምትል ጊዜ (አስተውስ)፡፡ አዎን ብትታገሱና ብትጠነቀቁ ከዚህም ፍጥነታቸው (ጥላቶቻችሁ) ቢመጡባችሁ ጌታችሁ ምልክት ባላቸው አምስት ሺህ መላእክቶች ይረዳችኋል፡፡ አላህም (እርዳታውን) ለናንተ ብስራትና ልቦቻችሁ በርሱ እንዲረኩ እንጂ አላደረገም፡፡ ድልም መንሳት አሸናፊ ጥበበኛ ከሆነው አላህ ዘንድ እንጂ ከሌላ አይደለም) ማለት ነው፡፡ መካ የተከፈተውም በዚሁ በረመዳን ወር ነው፡፡ በዚሁ በስምንተኛው የሂጅራ አመት በተካሄደው ጦርነት ድልን የተቀዳጁት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ምህረት በማድረግ፣ ይቅር በማለትና በእዝነት አርአያነት ያለው ታለቅ የመልካም ምግባር ተግባር ፈጽመዋል፡፡ ከድሉ በኋላ ሲያሰቃየዋቸው የነበሩትን፣ ከአገር ያበረሯቸውን ሊገድሏቸው ሲዶልቱባቸው የነበሩትን ሰዎች ሰብስበው እንድህ አሏቸው (እኔ ምን አደርጋችሁ ይመስሏችኋል እነሱም ደግን ነገር አንተ የተከበርክ ወንድምና የተከበረ ወንድም ልጅ ነህና አሉ፡፡ እሳቸውም ሂዱ እናንተ ከአሁን ጀምሮ ነፃ ናችሁ አሏቸው)፡፡

በረመዳን ወር በ1973ዓ.ም 1397 ሂ. የተካሄደው የረመዳን አስር የኦክቶበር ስድስት ጦርነት የተካሄደ ሲሆን ጠላት የማይበገር ይለው የነበረውን መከላከያ ጀግናው የግብጽ ጦር በአላህ ፈቃድ አፈራርሶበታል፡፡ የጠላትን ክብር አዋርዶ አለም ሁሉ ግብጽንና የግብጽ መከላከያ ኃይል እንዲያከብር አስገድዷል፡ የግብጽም ጦር መፈክር አላህ አክበር፣ ስግደት ቁርኣን ማንበብና እውነተኛ ጸሎት ስለነበር አላህ ድል እንዲቀዳጅ አደረገው ጠላቱንም ለማባረር በቃ፡፡ እዚህ ላይ የግብጽ ጦር ሰራዊት አባላት ሀገረን፣ ሃይማኖትን፣ ምድርንና ክብርን ለመጠበቅ የሀገረን መሬት በደሙ ያጠጣውን ሰማእት ልናስታውስ ይገባል፡፡

ጀግናው የግብጽ ጦር ሰራዊት ለወድቷ ግብጽ ብሎም ለአረቡና ለሙስሊሙም ህበረትሰብ የደህንነት መከታ መሆኑን እነዲሁም የተንኮልና የሽብር ሃይሎችን በመፋለም ዛሬም ትግሉን እንደቀጠለ ነው፡፡ በየቀኑም ለሀገር ደህንነት፣ ሰላምና ክብር መስዋእትነቱን አላቆመም፡፡ ሌላው በሰላም ሊኖር በሰማእትነት እየወደቀም የዚህን ሀገር አፈር ለመጠበቅ ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ለረጅም ጊዜ የማህበረሰቡ ጋሻና ጦር የሆነው መከላከያ ኃይል የሀገረን ድህንነት ለአደጋ ለማጋላጥና ሰላሙን ለማደፍረስ የሚያስብን ወገን እጅ ለመቁረጥ በተጠንቀቅ ላይ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል፡፡

ጌታዬ ሆይ! መንፈሳችንን ቅኑን መንገድ ምራት፡፡ አንተ መልካም አጽጂዋ ነህና ከመጥፎ ነገርም አጽዳት፡፡ አንተ ወኪሏና መጠጊያዋ ነህና፡፡

# (44)

## ረመዳን የእምነትና የጀግኖች መከወኛ ወር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

مِنَ الْمُؤْمِنِينَ رِجَالٌ صَدَقُوا مَا عَاهَدُوا اللَّهَ عَلَيْهِ ۖ فَمِنْهُمْ مَنْ قَضَىٰ نَحْبَهُ وَمِنْهُمْ مَنْ يَنْتَظِرُ ۖ وَمَا بَدَّلُوا تَبْدِيلًا

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከአማኞች በርሱ ላይ ለአላህ ቃል ኪዳን የገቡበትን በውነት የፈጸሙ ወንዶች አሉ፡፡ ከነሱም ስለቱን የፈጸመ (ለሃማኖቱ የተገደለ) አለ፡፡ ከነሱም ገና የሚጠባበቅ አለ፡፡ (የገቡበትን ቃል) መለወጥንም አለወጡም) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ.) የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል**

አላህ (ዐ.ወ.) በአንድ ባሪያ ላይ ከለገሳቸው ስጦታዎች እጅግ በጣም ታላቁ በአላህ የማመን ስጦታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

وَلَكِنَّ اللَّهَ حَبَّبَ إِلَيْكُمُ الْإِيمَانَ وَزَيَّنَهُ فِي قُلُوبِكُمْ وَكَرَّهَ إِلَيْكُمُ الْكُفْرَ وَالْفُسُوقَ وَالْعِصْيَانَ ۚ أُولَئِكَ هُمُ الرَّاشِدُونَ

ትርጉሙም (ግን አላህ እምነትን ወደናንት አስወደደ ፡፡ በልቦቻችሁም ውስጥ አጌጠው፡፡ ክህደትንና አመጥንም እንቢተኛነትንም ወደናንተ የተጠላ አደረገ፡፡ እነዚያ (እምነትን የወደዱና ክህደትን የጠሉ) እነርሱ ቅኖች ናቸው) ማለት ነው፡፡

የረመዳን ወር የእውነተኛ እምነት ወር መሆኑ ጥርጥር የለበተም፡፡ ለዚህም ነው በቅዱስ ቁርኣን የጾም አንቀጾች የእምነት ባህርይን በመጥቀስ የጀመሩት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

أَيُّهَا الَّذِينَآمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِنْ قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ፡፡ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና) ማለት ይሆናል፡፡

እውነተኛ እምነት ማለት ከአላህ ዘንድ በመጣው ሁሉ ማመንና ይዘቱን በተግባር ማዋል ነው፡፡ በአንድ ምእምን ልብ ሊሰፍን የሚገባውን የእምነት ምንነት፣ በታወቂው የጅብሪል ሓዲስ (ዐ.ሰ) እንደሚከተለው ሰፍሮ እናገኘዋለን፡ ጅብሪል ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለእምነት በጠየቃቸው ጊዜ እንዲህ በማለት መለሰዋል፡ (በአለህ፣ በመልአኮቹ፣ በመጻሐፎቹ፣ በመልእክተኞቹና በመጨረሻው ቀን ማመነህ እንዲሁም ደግም ደግም ይሁን መጥፎ በአላህ ፍርድ ማመነህ ነው)፡፡ እምነት በምላስ የምንናገረው ቃል ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን እምነት በለብ የሰፈነ እምነት ሲሆን በተግባርም ሊደግፍ ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ . الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنْفِقُونَ أُولَئِكَ هُمُ الْمُؤْمِنُونَ حَقًّا

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነት የሚጨምሩላቸው፡ በጌታቸውም ብቻ የሚያመልኩት ናቸው፡፡ እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው...) ማለት ነው፡፡

ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (ሙስሊም ብሎ ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና ከእጁ ተንኮል የዳኑ ሲሆን ነው፡፡ ምእምን ብሎ ማለት ደግሞ ሰዎች በገንዘባቸውና

በነፍሳቸውም እምነት የጣሉበት ሲሆን ነው)፡፡ በጠባዩና በተጋባራቱ አላህ ካዘዛቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ያጋደለ ሰው በእርግጥ ከእምነት መስመር ወጥቷል፡፡ ስለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ያሉት፡ (ዝሙተኛ ዝሙት ሲፈጽም በእምነት ላይ እያለ አይደለም፡፡ የሚያሰክር ነገርም ሲጠጣ በእምነት ላይ እያለ አይደለም፡፡ ሲሰርቅም እንደዚሁ በእምነት ላይ እያለ አይደለም፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በጎረቤቱ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ሰው ወይም እንደተራበ እያወቀ እሱ ጠግቦ ያደረ ሰው ሙሉ እምነት እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እምነት በተግባር መደገፍ ያለበት መሆኑን እንዲህ በማለት አመልክተዋል፡ (በአላህ ይሁንብኝ አላመነም፡ በአላህ ሁንብኝ አላመነም፡ በአላህ ይሁንብኝ አላመነም አሉ፡፡ ያአላህ መላክተኛ ሆይ! እሱ ማነው ሲሉም ጠየቋቸው እሳቸውም ያ ጎረቤቱ ተንኮሉን የሚፈራ የሆነው ሰው) እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡ (በጎኑ ያለው ጎረቤቱ እንደተራበ እያወቀ ጠግቦ ያደረ ሰው በኔ አላመነም)፡፡

እውነተኛ እምነት የሚባለው ያ አማኙን የሌሎችን መብት እንዳይዳፈር የሚከለክል፣ ልቡን ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከቂም፣ ከክህደትና ከብለሹነት የሚያፀዳ እምነት ነው፡፡ እንዲሁም ጠባዩን ገርቶ በእለት ትእለት ህይዎቱ የአላህን ወዴታ ብቻ መሰረት በማደረግ ለሰው ልጅ፣ ለአንሰሳ ብሎም ለማንኛውም ፍጥረት ርህራሄና እዝነት የሚያሳይ ሲሆን ነው፡፡ ታላቁ አላህ እንዲህ ይላል፡

وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا . إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنْكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا .

ትርጉሙም (ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለደሀ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ የምናበላችሁ ለአላህ ወዴታ ብቻ ነው፡፡ ከናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡ ማለት ይሆናል፡፡

እምነት ስሯ በምድር ውስጥ የተደላደለች ቅርንጫፏም ወደሰማይ የረዘመች ዛፍ ነች፡፡ መሰረቶቿ በጠነከሩና ስሮቿም በተደላደሉ ጊዜ ፍሬዋን በጌታዋ ፈቃድ ትሰጣለች፡፡ እውነተኛ ጾምም ከዚህ ዓይነት እምነት የመነጨ በመሆኑ በመንፈስ መረጋጋትንና እርካታን ያሰፍናል፡፡ ጾመኛውም አላህ (ዐ.ወ.)የሚቆጣጠረው መሆኑን በማረጋገጥ ከውሸት የራቀ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምክኒያቱም ጾምና ውሸት አይገናኙምና፡፡ ጾም መሰረቱ በግልጽም ሆነ በምስጢር አላህ የሚቆጣጠር መሆኑን መሰረት ያደረገና ከአላህና ከባሪያው መካከል ያለ ምስጢር ነው፡፡ ውሸት በአንጻሩ የንፍቅና ጉልህ መለያ ነው፡፡ እሱም ከጾም ማንነት ጋር ሙሉ በሙሉ ይጻረራል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ጾመኛ ወይም ውሸታም ይሆናል እንጂ ጾመኛና ውሸታም ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ያሉት፡ (ከሃሰት ቃልና በሱም ከመስራት ያልራቀ ሰው የሱን ምግብና መጠጥ መተው አላህ አይፈልገውም)፡፡ በሌላ ሐዲስ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከእለታት አንድ ቀን አንድ ምእምን ፈሪ ሊሆን ይችላልን የሚል ጥያቄ ተጠይቀው አዎን አሉ፡፡ ስስታምስ ሊሆን ይችላልን ለሚለውም አዎን አሉ፡ ወሸታምስ ሊሆን ይችላልን ለሚለው ጥያቄ ግን ሊሆን አይችልም ብለዋል)፡፡

በአላህ ማመን፣ በእምነት ልባቸው የተሞላ የሆኑት አላህ የወደዳቸው ሰዎች እንጅ ሊያጣጥመው የማይችል የሆነ ጣእምና ጥፍጥና አለው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል ( በአላህ ጌታነት፣ በእስልምና እመነትና በሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.)መልእክተኛነት የረካ ሰው የእምነትን ጣእም ይቀምሳል)፡፡ እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡ (ሦስት ነገሮች በልቡ የሰፈኑበት ሰው የእምነትን ጣእም ያገኛል፡፡ አላህና መላክተናውን ከማነም አብልጦ የወደደ፣ አንድን ሰው ለሌላ ነገር ሳሆን ለአላህ ብቻ የወደደ ሰው፡፡ ወደሳት መወርወርን እንደሚጠላ ሁሉ ከሱ አላህ ካዳነው በኋላ ወደክህደት መመለስን የሚጠላ)፡፡

እምነትና መልካም ምግባር ጣምራ ነገሮች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ ከሰዎች እምነታቸው ምሉእ የሆነው በምልካም ምግባር በላጫቸው የሆኑት፣ አብሯቸው ለሚኖር የሚመቹት፣ አነዚያም ሰዎችን የሚቀርቡት፣ ሰዎችም የሚቀርቧቸው ናቸው፡፡ ሰዎች የማይቀርብና ሰዎችም የማይቀርቡት ሰው ፋይዳ ቢስ ነው)፡፡ እምነት ብርሃን ነው ኢባዳም እንደዚሁ፡፡ የእምነትን ጣእምና የኢባዳን ጥፍጥና የቀመሰ ሰው መቻቻልን፣ ገራገርነትን፣ መልካም ውለታን እንጅ ሌላ ነግር አያውቅም፡፡ በአላህ ፍጥረታት ላይ አይኮራም ፊቱንም አይጨፈግግባቸውም፡፡ ለመጥፎ ተግባር መጥፎ አጸፋ ከመመለስ ይልቅ ምህረትንና ይቅር ማለትን ይመርጣል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አንዳችሁ ጾም በሚይዝበት ቀን እርኩስ ቃል አይናገር ድምጹንም ከፍ አያደርግ አንድ ሰው ቢሳደበው ወይም ሊታገለው ቢሞክር እኔ ጾም የያዝኩ ሰው ነኝ ይበል)፡፡ አንድ ልባም ሰው በኢባዳው ጀነት ላይገባ እንደሚችል ማሰብ እንዲሁም ደግሞም በመልካም ጸባዩ፣ በመቻቻል ተግባሩ፣ ለሰዎች በሚያደርገው ምልካም ውለታ ጀነት ሊገባ እንደሚችል መገመት ይኖርበታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (ከናንተ በፊት ከነበሩት ሰዎች አንዱ ስራዎቹ ተመዘኑ፡፡ ምንም መልካም ስራ አልተገኘለትም፡፡ ነገር ግን እሱ ከሰዎች ጋር ሰፊ ግንኙነት ነበረው፡፡ ባለጸጋም ነበርና አገልጋዮች በጣም ችግረኛ የሆነን ሰው እዳ ክፍል ብለው እንቅ አርገው እንዳይዙና እንዲተውለትም ያዝ ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.)ም እኛ በዚህ ዓይነቱ ተግባር ከሱ ቀዳሚዎች ነንና በይቅርታ እለፉት አለ)፡፡
እዚህ ላይ ልናረጋግጥ የምነወደው ነገር ቢኖር እውነተኛ እምነት ታላቁ አላህ በአንድ ባሪያ ልብ የሚረጨው ብርሃን መሆኑን ነው፡፡ ይህም ብርሃን ታዲያ ብልሃትና እርግጠኝነትን ያወርሰውና በአላህ (ዐ.ወ.) ብርሃን ሁሉን ነገር ያያል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡፡ ያለህ መልእክትኛ ከእለታት አንድ ቀን ከቤታቸው ወጡ፡፡ ከአንሷሮች ወገን የሆነ ሓሪሳ ኢብን አኑዕማን የተበላ ወጣት አገኙ፡፡ እናም እንዲህ አሉት (ሓሪሳ ሆይ! እንደምን አደርህ  እሱም በእውነት ምእምን ሆኜ አድሪያለሁ አላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም የምትናገረውን ልብ በል፡፡ ማንኛውም እውነት ለእውነትነቱ መሰረት አለው፡፡ ያንተ እምነት ውነኛነት መሰረቱ ምንድን ነው አሉት፡፡ አሱም ራሴን ከዚህች አለም በማራቄ ብዙውን የሌሊቱን ክፍል በኢባዳ ነቅቼ አሳልፋለሁ፡፡ ቀኔንም በጥም አሳልፋለሁ፡፡ ይህንም ሳደርግ የጌታዬን ዙፋን፣ የጀነት ሰዎች በውስጧ እንዴት እንደሚጠያየቁ፣  የገሀነም

ሰዎችም እንዴት በውስጧ እንዲሚጨቃጨቁ በገሃድ እንደሚያይ ሰው በመሆን ነው አላቸው፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ልብ አድርገሃል ቀጥልበት አሉት (ሁለት ጊዜ) እናም ይህ አላህ በልቡ እምነትን ያበራለት ባሪያነው አሉ)፡፡

እምነት እንድ ምእምን ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የሚገባ የተለያዩ ክፍሎች አሉት፡፡ ነብይችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ ( እምነት ሰባ ከምናምን ወይም ስድሳ ከምናምን ክፍሎች አሉት፡፡ በጣም በላጩ (ካለህ በስቀር የሚገዙት የለም) ማለት ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ አሾህን ከመንገዳ ማጋለል ነው፡፡ ያክብሮት ዓይናፋርነት የእምነት ክፍል ነው)፡፡ አንድ ሰዎዬ ሐሰን አልበስሪ የተባሉትን ሊቅ አንት ምእምን ነህን ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ እመነት ሲባል ሁለት ዓይነት ነው አሉና በአላህ፣ በመላክቱ፣ በመጽሐፎቹ፣ በምልእክተኞቹ፣ በጀነትና በእሳት፣ ሞቶ በመነሳትና ለሒሳብ በመቅርብ ማመንን እንደሆነ የምትጠይቀኝ እኔ አዎ መእምን ነኝ፡፡ ነግር ግን የምትጠይቀኝ እንዲህ ስለሚለው የአላህ ቃል ከሆነ

إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ . الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنفِقُونَ .أُولَٰئِكَ هُمُ ٱلْمُؤْمِنُونَ حَقًّا

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነት የሚጨምሩላቸው፡ በጌታቸውም ብቻ የሚያመልኩት ናቸው፡፡ እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው...) ማለት ነው፡፡ በአላህ ይሁንብኝ እኔ ከነሱ ውስጥ አንዱ እሆን አልሆን አላውቅም አሉት፡፡

እውነተኛ እምነት አማኙን ጸጥታና ሰላም ያላብሳል፡፡ በእሱ እንጅ እውን ሊሆን የማይችልንም ህይወት ያወርሳል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِنْ ذَكَرٍ أَوْ أُنْثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً ۖ وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُمْ بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ

ትርጉሙም (ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሰራ መልካም ኖሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፡፡ ይሰሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን) ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል

الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُمْ بِذِكْرِ اللَّهِ ۗ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ ٱلْقُلُوبُ

ትርጉሙም (እነዚያ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ) ማለት ነው፡፡ ይህን ግጥም የተቀኘ ደራሲ በጣም የሚደነቅ ነው

እምነት የታጣ ከሆነ ሰላምመ ሊኖር አይችልም ሃይማኖትን የማይጠብቅ ሰው ኑሮው የተሳካ አይሆንም

ያለሃይማኖት በኑሮው እርካታ የሚመኝ ጥፋትን ለህይወት ባላንጣ አደርጓ ህይወትን የሚመራ ሰው ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡
ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በሰዷና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡
ሙስሊም ወንድሞች
ረመዳን የእምነት ወር ነው ስንል ይህ ወር እንደዚሁም የጀግኖች መከወኛ ወር መሆኑን መጠቆማችን ነው፡፡ ጾም እውነተኛ ጀግኖች ጎልተው የሚታዩበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ አሕመድ ሸውቂ የተሰኘው የግጥም ደራሲ እንዲህ ይላል፡ ‹ጾም ህጋዊ እገዳ፣ በረሃብ መንፈስ መግራትና ለታላቁ አላህ መገዛት ነው፡፡ ማንኛም የፈጣሪ ግዴታ የተለየ ጥበብ አለው፡፡ የጾም ግዴታ በገሀድ ሲታይ ስቃይ ቢመስልም መስጢሩ እዝነትን የሚፈጥር፣ ለስጦታ የሚገፋፋ፣ ኩራትን የሚሰብርና ትእግስትን የሚያስተምር የርህራሄ ባህርይን ያጎናጽፋል፡፡ ጥጋብን እንጅ የማያወቀው ሰው ሲራብ፣ ደልቃቃውም ሰው የቅንጦት መገልገያዎችን ሲያጣ እጦት ምን እንደሆነ ያውቃል፡፡ ሲነድፍም ስቃዩ ምን እንደሚመስል ይገነዘባል›፡፡
የተከበረውን ቁርኣን የሚመራመር ሰው አላህ (ዐ.ወ.) የወንድነትን (ጀግንነት) ባህርይ ብቃት ላላቸው ሰዎች እንጅ ያልሰጠ መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ከነዚህ ባህርዮች ቀዳሚነትን የሚይዘው አንድ ሰው ሳይቀይር፣ ሳይለውጥና ሳያዛባ ለአላህ የገባውን ቃል ማክበር የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡
مِنَ الْمُؤْمِنِينَ رِجَالٌ صَدَقُوا مَا عَاهَدُوا اللَّهَ عَلَيْهِ ۖ فَمِنْهُمْ مَنْ قَضَىٰ نَحْبَهُ وَمِنْهُمْ مَنْ يَنْتَظِرُ ۖ وَمَا بَدَّلُوا تَبْدِيلًا

ትርጉሙም (ከአማኞች በርሱ ላይ ለአላህ ቃል ኪዳን የገቡበትን በውነት የፈጸሙ ወንዶች አሉ፡፡ ከነሱም ስለቱን የፈጸመ (ለሃማኖቱ የተገደለ) አለ፡፡ ከነሱም ገና የሚጠባበቅ አለ፡፡ (የገቡበትን ቃል) መለወጥንም አለወጡም) ማለት ነው፡፡ እውነተኛ ወንዶች (ጀግኖች) የሚባሉት ነፍሳቸውንና ገንዘባቸውን ለአለማቱ ጌታ የሸጡት (የሰጡት) ናቸው፡፡ እነሱም የአላህን ውዴታ በመከጀል ለሃይማኖት፣ ለሀገርና ለክብር ደህንነት ገንዘባቸውን ብሎም ነፍሳቸውን ይሰዋሉ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንዲህ ይላል፡
إِنَّ اللَّهَ اشْتَرَىٰ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ أَنْفُسَهُمْ وَأَمْوَالَهُمْ بِأَنَّ لَهُمُ الْجَنَّةَ ۚ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ ۖ وَعْدًا عَلَيْهِ حَقًّا فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنْجِيلِ وَالْقُرْآنِ ۚ وَمَنْ أَوْفَىٰ بِعَهْدِهِ مِنَ اللَّهِ ۚ فَاسْتَبْشِرُوا بِبَيْعِكُمُ الَّذِي بَايَعْتُمْ بِهِ ۚ وَذَٰلِكَ هُوَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ

ትርጉሙም (አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለነሱ ብቻ ያለቸው በመሆን ገዛቸው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ ይገድላሉም ይገደላሉም በተውራት፣ በኢንጅልና በቁርኣንም (የተነገረውን ) ተስፋ በርሱ ላይ አረጋገጠ፡፡ ከአላህም የበለጠ በኪዳኑ የሚሞላ ማን ነው? በዚያም በርሱ በተሻሻጣችሁበት ሽያጫችሁ ተደሰቱ ይህም እርሱ ታላቅ እድል ነው) ማለት ነው፡፡

ረመዳን በሌሊት ሶላት መስጊዶችን የምናውብበት ወር ነው፡፡ ሌሊት መስገድና መስጊድን ማዋብ የማንነት ግንባታና የወንድነት(ጀግንነት) ክወና መሰረት ድንጋይ ናቸው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ነብዩን ተነጋሪ በማድረግ እንዲህ ይላል፡
يَا أَيُّهَا الْمُزَّمِّلُ قُمِ اللَّيْلَ إِلَّا قَلِيلًا . نِصْفَهُ أَوِ انْقُصْ مِنْهُ قَلِيلًا . أَوْ زِدْ عَلَيْهِ وَرَتِّلِ الْقُرْآنَ تَرْتِيلًا . إِنَّا سَنُلْقِي عَلَيْكَ قَوْلًا ثَقِيلًا إِنَّ نَاشِئَةَ اللَّيْلِ هِيَ أَشَدُّ وَطْئًا وَأَقْوَمُ قِيلًا

ትርጉሙም (አንተ ተከናናቢ ሆይ! ሌሊቱን ሁሉ ጥቂት ሲቀር ቁም (ስገድ)፡፡ ግማሹን ቁም ወይም ከርሱ ቀንስ፡፡ ወይም በርሱ ላይ ጨምር፡፡ ቁርአንንም በዝግታ ማንበብን አንብብ፡፡ እኛ ባንተ ላይ ከባድ ቃልን እንጥላለንና፡፡ የሌሊት መነሳት እርሱ (ህዋሳትንና ልብን) ለማስማማት በጣም ብርቱ ነው፡፡ ለማንበብም ትክክለኛ ነው) ማለት ነው በሌላም አንቀጽ እንዲህ ይላል፡

فِي بُيُوتٍ أَذِنَ اللَّهُ أَن تُرْفَعَ وَيُذْكَرَ فِيهَا اسْمُهُ يُسَبِّحُ لَهُ فِيهَا بِالْغُدُوِّ وَالْآصَالِ * رِجَالٌ لَّا تُلْهِيهِمْ تِجَارَةٌ وَلَا بَيْعٌ عَن ذِكْرِ اللَّهِ وَإِقَامِ الصَّلَاةِ وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ يَخَافُونَ يَوْمًا تَتَقَلَّبُ فِيهِ الْقُلُوبُ وَالْأَبْصَارُ

ተርጉሙም (አላህ እንድትከበርና ስሙ በውስጧ እንዲወሳ ባዘዘው ቤቶች ውስጥ (አወድሱት) በውስጧ በጧትና በማታ ለርሱ ያጠራሉ፡፡ አላህን ከማውሳትና ሶላትን ከመስገድ ዘካንም ከመስጠት ንግድም ሽያጭም የማያታልላቸው ልቦችና ዓይኖች በርሱ የሚገላበጡበትን ቀን የሚፈሩ የሆኑ ሰዎች (ያጠሩታል) ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የጀነትን ሰዎች ማንነት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡
كَانُوا قَلِيلًا مِنَ اللَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ . وَبِالْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ

ትርጉሙም (ከሌሊት ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበር፡፡ በሌሊቱ መጨረሻዎችም እነሱ ምህረትን ይለምናሉ) ማለት ነው፡፡ በሌላ አንቀጽም እንዲህ ይላል፡
تَتَجَافَىٰ جُنُوبُهُمْ عَنِ الْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنفِقُونَ . فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَّا أُخْفِيَ لَهُم مِّن قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ

ትርጉሙም (ጌታቸውን በመፍራትና በመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራቸው ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ጸጋ) ይለግሳሉ፡፡ ይሰሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለነሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም) ማለት ነው፡፡
የሌሊት ስግደት በተለይም ደግሞ በመጨረሻዎቹ አስር ሌሊቶች ልዩ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በነዚህ ሌሊቶች ከሌሎች ሌሊቶች በተለዩ መልኩ የኢባዳ ጥረት ያደርጉባቸው ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ኣኢሻ እንዲህ የሚል ሐዲስ አውርተዋል፡ (የአላህ መልእክተኛ በረመዳን ውር የመጨረሻዎቹ አስር ሌሊቶች በገቡ ጊዜ ባጭር ይታጠቁ፣

ሌሊታቸውን በስግደት ያሳልፉና ቤተሰቦቻቸውን ለኢባዳ ያነቃቁ ነበር)፡፡ ባጭር ይታጠቁ ነበር ማለት ለኢባዳ ተጨማሪ ጥረት ያደርጉ ነበር ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ተንታኞች ደግሞ ከሴት ይርቁ ነበር ማለት ነው የሚል እንድምታ ሰጥተውታል፡፡

ረመዳን የነፍስን ልጓም በመግታት፣ በመንፈስ እርካታን በመፍጠር፣ በአይምሮ ንቃት፣ በስርኣት ማስከበርና መልካሙን እርምጃ በመውሰድ ጀግኖችን ይከውናል፡፡ እንዲሁም ጾመኛው ሰብአ ነክ እሴቶችንና የሰውን ልጅ ስርኣት የሚያስተካክለውን የመልካም ምግባር ደረጃን ከፍ በማድረግ በህይወት ጉዳዮች ሁሉ ቅን እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ጾመኛው ሙብትን ያከብራል፣ ግዴታውንም ይወጣል እንዲሁም ለራሱ፣ ለማህበረሰቡ፣ ለሀገሩና ለዜጎቹ በሙሉ መልካምንና ደግን ነገር እውን ለማድረግ ይጥራል፡፡ ይህም ታዲያ በማህበረሰቡ ሰላምና እድገት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በህዝብ ብልጽግናና ስልጣኔ ሰፊ ቦታ ያለው የፍቅር፣ የመቀራረብና የእዝነት መንፈስም እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

በነዚህ ቀናት ያሉት መልካም ነገሮች እንዳያመልጡን አላህን ለማስታወስና ለመጸለይ፣ ቁርኣንን ለመቅራት፣ ወደአላህ የሚያቃርቡ ነገሮችን በንቃት ለመስራት ልዩ ትኩረት ልንሰጥ ይገባል፡፡ አለዚያ በነዚህ በተባረኩ ቀናት የሚወርዱትን ስጦታዎች እንከለከላለን፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (ለጌታችሁ ከዘመናችሁ ባሉ ቀናት የሚያወርዳቸው ስጦታዎች አሉት፡፡ አነዚህን ስጦታዎች ለማግኘት ጥረት አድርጉ፡፡ መናልባትም እንዳችሁ ከነዚህ ስጦታዎች አንዷን ያገኝና ከዚያ በኋላ መናጢነት የሚባል ነገር ላያገኘው ይችላልና)፡፡

ጌታችን ሆይ! አንተ ሰሚ አዋቂም ነህና ስራችንን ተቀበለን፡፡ አንተም ምህረት ሊጋሽና አዛኝም ነህና ምህረትን ስጠን፡፡

## (45)

## ረመዳን የመልካም ሥራ፣ የዝምድና መቀጠልና የአላህን ስጦታ የማግኘት ጥረት ወር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَٰكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ
وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَىٰ حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ
السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَاهَدُوا ۖ
وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ ۗ أُولَٰئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا ۖ وَأُولَٰئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም ( መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደምስራቅና ወደምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመልአክትም፣ በመጽሐፍትም፣ በነብያትም ያመነ ሰው፣ ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች፣ ለምስኪኖችም ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቂያ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር፣ በበሽታና፣ በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን) እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጀጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡፡**

የተባረከው የረመዳን ወር የፈጣሪ ትእዛዝ መከበሪያ፣ የስጦታና የእዝነት ወር ነው፡፡ እንዲሁም የጾም፣ የስግደት፣ የዝምድና መቀጠል፣ የመዋደድ፣ ሰዎች በመልካም ስራና በአላህ ፍራቻ የሚተጋገዙበት ወርም ነው፡፡ ይህ ወር አንድ ሙስሊም በትእግስቱ፣ ምንዳን በማሰቡና የአላህን ትእዛዝ በመከታተሉ የሚፈተንበት ወር ነው፡፡ አንደ ጾመኛ ረሀብና መጠጥን በትእግስት ያሳልፋል፣ የመንፈስን ልጓም ይገታል፡፡ የሚደርስበትን ስቃይ በትእግስት ይቀበላል፡፡ አንድ ሙስሊም በዚህ ወር እንደቁርአን መቅራት፣ ጸሎት፣ የሌሊት ስግደት፣ ምጽዋት መስጠት፣ ሰዎችን ማስታረቅና ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም መስራት ባሉ የተላያዩ ኢባዳዎች ወደታላቁ አላህ ይቃረባል፡፡ እንደዚህ ያሉት መልካም ምግባሮች ለአንድ ባሪያ የአላህ(ሊ.ወ.)ን እዝነት ያመጡለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል

إِنَّ رَحْمَتَ اللَّهِ قَرِيبٌ مِنَ الْمُحْسِنِينَ

ትርጉሙም (የአላህ ችሮታ ከበጎ አድራጊዎች ቅርብ ነውና)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (ይህ መልካም ነገር መጋዘን ነው፡፡ ያም መጋዘን ቁልፎች አሉት፡፡ አላህ የመጥፎ ነገር መዝጊያና የመልካም ነገር ቁልፍ ያደረገው ባሪያ ምንኛ አድለኛ ነው! አላህ ለመጥፎ ነገር መክፈቻና ለመልካም ነገር መዝጊያ ያደረገው ባሪያ ወዮለት)፡፡

የተባረከው የረመዳን ወር በመልካም ነገርና በበጎስራ የመፎካከሪያ መድረክ ነው፡፡ በዚህ ወር የአላህ ባሪያዎች ወደአላህ (ዐ.ወ.) ለመቃረብ በንጹህ ስራዎች ይሽቀዳደማሉ፡፡ ይህውም የነብያችንን ፈለግ በመከተል ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን አባስ እንዲህ ብለዋል፡ የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ከሰዎች ሁሉ የበለጠ ቸር ነበሩ፡፡ ችሮታቸው የሚበዛው ደግሞ በሮመዳን ጅብሪል ጋር

በሚገናኙበት ወቅት ነበር፡፡ ጅብሪል ወደነብያችን በመምጣት በረመዳን ወር በየሌሊቱ ከነብያችን ጋር ቁርአንን ይማማሩ ነበር፡፡ ነብይችንም በዚያን ወቅት በቸርነት ከልቅ ንፋስ የበለጠ ፈጣን ነበሩ)፡፡
ረመዳን የመልካም ስራ በተለይም የዚህ ወር መለያ የሆነው የምግብ በማብላት ዘርፍ ሰፊ መስክ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን ሰላም የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደመዲና በመጡ ጊዜ ሰዎቸ ሁሉ ወደርሳቸው አመሩ እኔም ከነሱ መካከል ነበርሁ፡፡ ፊታቸውንም ባየሁ ጊዜ የውሸታም ሰው ፊት እንዳልሆነ አረጋገጥሁ፡፡ እንዲህም ሲሉ ሰማኋቸው (ሰዎች ሆይ! ምግብን አብሉ፣ ሰላምታንም አስፋፉ፣ ዝምድናንም ቀጥሉ፣ ሰዎች ሲተኙ ስገዱ፣ (ይህን ካደረጋችሁ) በሰላም ጀነት ትገባላችሁና)፡፡›
ይህ የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቃል አራት ነገሮችን አቅፏል፡፡ ሦስቱ ከሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከቱ ሲሆኑ እነሱም ምግብ ማብላት፣ ሰላምታ ማስፋፋትና ዝምድና መቀጠል የሚሉት ናቸው፡፡ አራተኛው ደግሞ ከአንድ ባሪያና ከፈጣሪው መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ እሱም ሰዎች ሲተኙ መስገድ የሚለው ነው፡፡ አንድ ሰውዬ ከእስልምና ተግባራት የተኛው ነው መልካሙ ሲል ነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) በጠየቀ ጊዜ (ምግብ ማብላትህ፣ ለምታውቀውም ለማታውቀውም ሰው ሰላምታ ማቅረብህ ነው) አሉት በሌላ ሐዲስ እንዲህ ይላሉ፡ (ማንኛውም ሰው ምጽዋት መስጠት አለበት)፡፡ ያን ጊዜ ግንዘብ ባይኖረውስ ተብለው ተጠየቁ፤፡ አሳቸውም (በጁ ሰርቶ ራሱን ይጥቀም ምጽዋትም ይስጥ አሉ፡፡ መስራት ባይችልስ ተብለው ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም የተቆጨን ባለጉዳይ ይገዝ አሉ፡፡ ባይችልስ የሚል ጥያቄም ቀረበላቸው፡፡ አሳቸውም በበጎ ስራ ወይም በፍትህ ይዘዝ አሉ፡፡ አሁንም ባይችልስ የሚል ጥያቄ ሰሙ፡፡ እሳቸውም ተንኮል ከመስራት ይታቀብ ይህ ለሱ ምጽዋቱ ነው አሉ፡፡)
እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የምነፈልገው ነገር ቢኖር በጎ ስራ ማለት በጎ ነገርን፣ አላህ የሚወደውን፣ ለሰው ልጅ የሚጠቅምን ነገር ሁሉ ያካተተ ሰፊ ፍች ያለው ቃል መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ታድያ በመልክም ጠባይ ይካተታሉ፡፡ ለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ያሉት፡ (በጎ ስራ ማለት መልካም ጠባይ ነው)፡፡ እንዲሁም ቃልን ማክበር፣ ለውለታና ትሩፋት እውቅና መስጠት ከቡራን እንጅ የማላበሱት መሰረታዊ መልካም ጠባይ ነው፡፡ የሚከተለውን ግጥም የተቀኘው ደራሲ እንዴት ይደነቃል!
ቃልን ማክበር የክቡር ሰው ግዴታው ነው     ብልግና የቃል አጣፊዎች ቁራኛ ነው፡፡
ክቡር ሰው ምንግዜም አብሮት ለሚኖር ግልጽ ነው    ባለጌ ደግሞ ግልጽ አይሆንም፡፡
ሌላኛው ተቀኝም እንዲህ ይላል፡፡
ክቡራን መልካም ስራ ሲያከናውኑ  በደሳሳ ጎጆ በነበሩበት ጊዜ ይቀርቧቸው የነበሩትን ሰዎች ያስታውሳሉ፡፡
ከመልካም ስራ እጅግ በጣም ታላቁ ከቤተሰብ፣ ከዘመዳሞች፣ ከጎረቤቶችና ከመላ ሰዎች መካከል የሚኖረው መቀራረብና ግንኙነት የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ከሰዎች መካከል መለማመድንና መተሳሰርን፣ ከመላ ሰው ልጅ መካከል

የመተዛዘንን እሴት በማስፋፋት ያለው ሚና እጅጉን ሰፊ ነው፡፡ በረመዳን ለጭቅጭቅም ሆነ ለተጨቃጫቂዎች ቦታ ሊኖር አይገባም፡፡

የረመዳን ወር የግንኙነት ማደሺያ ወር ነው ስንል ሁለት ግንኙነቶች በተለዬ መልኩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ አንደኛው የዘመዳሞች ግንኙነት መታደስ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የዚህን ግንኙነት ደረጃና ያለውን ታላቅ ቦታ በሚከተለው የቁድስ ሓዲስ አብራርተዋል፡ አለህ (ዐ.ወ.) እንዲህ ይላል፡ (እኔ አላህ ነኝ፡፡ እኔም እዝነቴ የሰፋ ነው፡ ፡ ዝምድናን ፈጠርሁኝ፡፡ ከስሜም ቃላት (ረሒም) የሚል ስያሜ ሰጠኋት የቀጠላትን ሰው እቀጥለዋለሁ፡፡ የቆረጣትን ደግሞ እበጥሰዋለሁ፡፡ ከዚያም አንዲህ አሉ ብትፈልጉ የሚከተሉትን አንቀጾች አንብቡ፡

فَهَلْ عَسَيْتُمْ إِنْ تَوَلَّيْتُمْ أَنْ تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ وَتُقَطِّعُوا أَرْحَامَكُمْ أُولَٰئِكَ الَّذِينَ لَعَنَهُمُ اللَّهُ فَأَصَمَّهُمْ وَأَعْمَىٰ أَبْصَارَهُمْ أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ الْقُرْآنَ أَمْ عَلَىٰ قُلُوبٍ أَقْفَالُهَا

ትርጉሙም (ብትሾሞም በምድር ላይ ማበላሸትን ዝምድናችሁንም መቁረጥን ከጀላችሁን፡፡ እነዚህ እነዚያ አላህ የረገማቸው ያደነቆራቸውም ዓይኖቻቸውንም ያወራቸው ናቸው፡፡ ቁርአንንም አያስተነትኑምን በውነቱ በልቦቻቸው ላይ ቁልፎቿ አሉባትን፡፡)

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ይላሉ፡ (ስራዎች ሰኞና ሐሙስ ፈጣሪ ዘንድ ይቀርባሉ በነዘህ ቀናትም በአላህ ያላጀጋራን ሰው ወንጀል አላህ ይምራል፡፡ ከወንድም ጋር በጭቅጭቅ ያለ ሰው ሲቀር እነዚህን አስከሚታረቁ ድረስ እለፏቸው ይባልና ምህረታቸው ይዘገያል፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) መጀመሪያ መልእክት እንዲያደርስ በታዘዘበት ዝምድና መቀጠል ከእምነት ዋልታዎች አንደኛው መሆኑን ይገልጹ ነበር፡፡ አምር ኢብን አብሳ የተባሉት ባልደረባ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት እንድ ቀን ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ቦታ ገባሁና አንተ ማነህ ስል ጠየቅሁኝ አሳቸው ያለህ ነብይ ነኝ አሉ፡፡ እኔም ያለህ ነብይ ማለት ምን ማለት ነው ስል ጠየቅሁኝ፡፡ እሳቸውም የአላህ መላክተኛ ማለት ነው አሉ፡፡ እኔም አላህ ልኮሃል ማለት ነው ስል እንደገና ጠየቀሁ፡፡ አሳቸውም አዎን አሉ፡፡ እኔም በምን ጉዳይ ነው የላከህ የሚል ጥያቄ ሰነዘርሁ፡፡ እሳቸውም (አላህ ብቸኛ አምላክ እንዲሆንና፣ በሱም ማንም እንዳይጀጋራ፣ ታቦቶች እንደሰባበሩ፣ ዝምድናም እንዲቀጠል) በማለት መለሱልኝ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ዝምድናን መቀጠል ከአምነት ምልክቶች አንደኛው መሆኑን እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል፡ (በአላህና በመጨረሻውም ቀን የሚያምን ሰው ዝምድናን ይቀጥል)፡፡ ይህን ጉዳይ አላህ (ዐ.ወ.) እንዲህ ሲል ገልጾታል፡

وَأُولُو الْأَرْحَامِ بَعْضُهُمْ أَوْلَىٰ بِبَعْضٍ فِي كِتَابِ اللَّهِ ۗ

ትርጉሙም (የዝምድና ባለቤቶችም በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው በከፊሉ (መውረስ) የተገቡ ናቸው) ማለት ነው፡፡

ሌላኛው ግንኙነት ደግሞ በአካባቢያችን ካሉት ሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ማደሳችን ነው፡፡ ከአንድም ሰው ጋር መቆራረጥ የለብንም፡፡ ነብይችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡

(አንድ ሰው ወንድሙን ከሦስት ሌሊቶች የበለጠ ሊያኮርፈው አይፈቀድም፡፡ በሚገናኙበት ወቅት ይህኛው ፊቱን ማዞር ያኛውም እንደዚሁ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ከነሱ በላጩ ቀድሞ ሰላም ያለው ነው)፡፡ ይህን ስንል ታድያ በመንገድ ሲያገኘው ሰላምታ ሰንዝሮ ማለፉን ብቻ ማለታችን አይደደለም፡፡ ልቡ እየጠላ በምላሱ ሰላም ማለት በቂ አይደለም፡፡ ሰላምታውም ከይዘቱ የተራቆተ ቅርጻዊ ሰላምታ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ የታሰበው ሰላምታ ሰላም የሚለው ቃል ያዘለው እውነተኛው ሰላምታ ሲሆን ከራስ፣ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከጎረቤት፣ ከባልደረባ፣ ከሰው ልጅ፣ ከእንሰሳ፣ ከእጽዋትና ከአላም ሁሉ ጋር ሰላም መፍጠርን ያካትታል፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡
يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا ادْخُلُوا فِي السِّلْمِ كَافَّةً وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ ۚ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُبِينٌ

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁም በመታዘዝ ውስጥ ግቡ፡፡ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፡፡ እርሱ ለናንተ ግልጽ ጠላት ነውና) ማለት ነው፡
፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ፡፡ ለኔና ለናንተም ከአላህ መህረት እለምናለሁ፡፡

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

አላህ (ዐ.ወ.) በጥበቡ የረመዳን ወር የመጨረሻ አስር ቀናት መልከም ሲሰራ የሰነበተው ከበጎ ስራው እንዲጨምር፣ በችልታ ያሰለፈው ደግሞ ያመለጠውን በቀሪዎቹ ቀናት እንዲያካስ መልካም አጋጣሚ አድርጓል፡፡ እንዚህ ቀናት በፈጣሪ ስጦታዎችና በጌታ ችሮታዎች የተሞሉ ቀናት ናቸው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ሙስሊም እነዚህን ችሮታዎች ለማግኘት ጥረት ማደረግ ይኖርበታል፡፡ ነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ (ለጌታችሁ በዘመናችሁ ቀናት ቸወሮታዎች አሉት፡፡ እነዚህን ችሮታዎች ለማግኘት ጥረት አድርጉ፡፡ መናልባትም አንዳችሁ ከነዚህ ችሮታዎች አንዷን ያገኝና ከዚያ በኋላ መናጢነት እስከዘላለም የማያገኘው ሊሆን ይችላልና)፡፡ ለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)የረመዳንን የመጨረሻ አስር ቀናት በተጨማሪ ኢባዳና ወደአላህ በቃረብ ይለዩዋቸው የነበረው፡፡
በነዚህ አስር ቀናት ትኩረት ከምንሰጣቸው ነገሮች ተቀዳሚው የነብያችንን ፈለግ በመከተል ሌሊቶቹን ነቅተን በኢባዳ ማሳለፋችን ነው ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ኣኢሻ እንዲህ ሲሉ አውርተዋል፡ (አስሮቹ ‹የረመዳን ወርመጨረሻ ቀናት› በገቡ ጊዜ የአላህ መላከተኛ በአጭር ይታጠቁ፣ ሌሊታቸውን በኢባዳ ነቅተው ያሳለፉና ቤተሰቢቻቸውንም ለኢባዳ ያነቃቁ ነበር)፡፡

በረከት ለጋሹ አላህ (ሱ.ወ.) እነዚህን አስር የረመዳን መጨረሻ ሌሊቶች ሁሉ በላጭና ታላቅ በሆነችው በቀድር ሌሊት በመለየት አክብሯቸዋል፡፡ ይህውም የወዳጁን የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ.) ህዝብ በማክበር ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙጃሂድ የሚከተለውን አውረተዋል፡ (ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከእስራኢል ነገድ ስለሆነ አንድ ሰወዬ አወሩልን፡፡ ይህ ሰው በአለህ መንገድ መሳሪያ አንግቦ ለአንድ ሺህ ወራት ያህል ተዋጋ ባሉ ጊዜ ሙስሊሞች በጣም ተደነቁ ያን ጊዜ ይህች ምዕራፍ ወረደች፡

إِنَّا أَنْزَلْنَاهُ فِي لَيْلَةِ الْقَدْرِ { 1 }وَمَا أَدْرَاكَ مَا لَيْلَةُ الْقَدْرِ { 2 }لَيْلَةُ الْقَدْرِ خَيْرٌ مِنْ أَلْفِ شَهْرٍ { 3 } تَنَزَّلُ الْمَلَائِكَةُ وَالرُّوحُ فِيهَا بِإِذْنِ رَبِّهِمْ مِنْ كُلِّ أَمْرٍ { 4 } سَلَامٌ هِيَ حَتَّى مَطْلَعِ الْفَجْرِ

ትርጉሙም (እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው፡፡ መወሰኛይቱ ሌሊት ምን እነደሆነች ምን አሳወቀህ፡፡ መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺህ ወር በላጭ ናት፡፡ በርሷ ውስጥ መልአክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ፡፡ እርሷ እስከጎህ መውጣት ድረስ በሰላም ብቻ ናት) ማለት ነው ፡፡

በዚህች ሌሊት በፍጹም ልብ የሚሰራ ኢባዳ በአላህ መንገድ አንድ ሺህ ወር ከመዋጋት የበለጠ ምንዳ አለው፡፡

ነብያችን በዚህች ሌሊት የሚሰግድ ስግደት የወንጀል ምህረት እንደሚያስገኝ እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡ (የቀድርን ሌሊት በሙሉ እምነትና ምንዳን በማሰብ በስግደት ያሳለፈ ሰው ከዚያ በፊት የነበረው ወንጀሉ ይማርለታል)፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሙስሊም ወደአላህ ለመቃረብና ምህረቱን ተስፋ በማድረግ ይህችን ሌሊት ነቅቶ በኢባዳ ለማሳለፍ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህች ወሰን የሌለው የአላህ ችሮታ የሚወርድባትን ሌሊት በየትኛው ጊዜ በልዩ ትኩረት እንዴት አንደምንፈልጋት ነብያችን አንዲህ በማለት ጠቁመዋል (የቀድርን ሌሊት በረመዳን መጨረሻ አስር ቀናት በነጠላ ቁጥር ሌሊቶች ፍልጓት) ይህን ማለትም በ23/25/27/29 ሌሊቶች ማለት ነው፡ በነዚህ ቀናት ከሚከናወኑ ኢባዳዎች አንዱ ደግሞ የፊጥርን ዘካ ማውጣት ነው፡፡ የፊጥር ዘካ ለጾመኛው ጽዳት ለድሆችና ምስኪኖች ደግሞ ምግብ መሆኑን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና)ኢብን አባስ አንዲህ ሲሉ አውርተዋል፡ (የአላህ መልእክተኛ የፊጥርን ዘካ ግድ ያደረጉት ጾመኛው ከጨዋታና መጥፎ ቃል እንዲጸዳ እንዲሁም ለምስኪኖች ምግብ እንዲሆን ነው፡፡ ከኢድ ሶላት በፊት ያወጣት ሰው ዘካው ተቀባይነት ያገኛል፡፡ ከስግደት በኋላ ያወጣት ሰው ደግሞ አንደማንኛውም ተራ ምጽዋት አንጅ እንደዘካ አይቆጠርም)

እንዲሁም በነዚህ ቀናት የምንፈጽመው ሌላው ኢባዳ በጸሎት መታተራችን ነው፡፡ በረመዳን የጾሎት ተቀባይነት ተስፋው ሰፊ ነው ስንል በነዚህ በአስሩ ቃናት ደግሞ የበለጠ ሰፊ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን አኢሻ አንዲህ ሲሉ አውርተዋል፡ (የአላህ መላክተኛ ሆይ! እኔ እንደው የቀድርን ሌሊት ካጋጠመኝ ያን ጊዜ ምን እላለሁ አልኳቸው፡፡ እሳቸውም

اللَّهُمَّ إِنَّكَ عُفُوٌّ كَرِيمٌ تُحِبُّ الْعَفْوَ فَاعْفُ عَنِّي

በይ አሉኝ፡፡ የነዚህን የተባረኩ ሌሊቶችን ትሩፋት ላለማስመለጥ፣ የቀድርን ሌሊት በጸሎት፣ አላህን በማስታወስ፣ ቁርአንን በመቅራት እንዲሁም ወደአላህ የሚያቃርቡ ነገሮችን በመስራት ልናሳልፋቸው ይገባል፡፡ የአላህ ችሮታዎች እንዳያመልጠን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ በዚህች ሌሊት የአላህን እዝነት ማስመለጥ ማለት ታላቅ ነገር ማጣት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (... በሱ አላህ ከአንድ ሺህ ወር የበለጠችን ሌሊት አድርጓል የሷን በጎ ስራ ያጣ መልካሙን ሁሉ አጣ ማለት ነው)

*ጌታችን ሆይ! አንተ ምህረት አድራጊ ነህ ምህረትንም ትወዳለህና ለኛ መህረት አድርግልን*

## (46)

### ስለሸዋል ወርስ?

*ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ*

{إِنَّ الَّذِينَ قَالُوا رَبُّنَا اللَّهُ ثُمَّ اسْتَقَامُوا تَتَنَزَّلُ عَلَيْهِمُ الْمَلَائِكَةُ أَلَّا تَخَافُوا وَلَا تَحْزَنُوا وَأَبْشِرُوا بِالْجَنَّةِ الَّتِي كُنتُمْ تُوعَدُونَ}،

*ለአለው ለአለማቱ ጌታ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ ከዚያም ቀጥ ያሉ፣ አትፍሩ አትዘኑም በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ፡፡ በማለት በነሱ ላይ መልአክት ይወርዳሉ) ማለት ነው፡፡*
*ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (አንድም በአላህ ባሮች ላይ የሚነጋ ሌሊት የለም ሁለት መልአኮች ወርደው አንደኛው ፡ ጌታዬ ሆይ ለጋሽን ሰው በለገሰው ነገር ምትክ ስጠው ሌላኛው ደግሞ ጌታዬ ሆይ ግነዘቡን ጨምድዶ ያዘን ሰው ጥፋትን ፍረድበት የሚሉ ቢሆን እንጂ)፡፡ ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡*

**ከዚህም በመቀጠል፡**
በፍጥረታት አንፃር ያለውን የአላህ (ኢ.ወ.)ን ደንብ የሚመራመርና የሚያስተነትን ሰው ቀናት፣ ወራትና ዓመታት በፍጥነት የሚከንፉ መሆናቸውን በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ የዚህች የዓለማችን ህይወት የተወሰኑ ስትንፋሳትና የተወሰኑ ጊዜያት እንጅ ሌላ ነገር

አይደለችም፡፡ ይህም ለሚያስተነትንና ለሚመራመር ጥልቅ ትምህርት አላው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

{وَهُوَ الَّذِي جَعَلَ اللَّيْلَ وَالنَّهَارَ خِلْفَةً لِمَنْ أَرَادَ أَنْ يَذَّكَّرَ أَوْ أَرَادَ شُكُورًا}

ትርጉሙም (እርሱ ያ (ያመለጠውን ሥራ) ማስታወስን ለሚፈልግ ወይም ማመስገንን ለሚፈልግ ሰው ሌሊትንና ቀንን ተተካኪ ያደረገ ነው) ማለት ነው፡፡
እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡

فَلَا تَعْجَلْ عَلَيْهِمْ إِنَّمَا نَعُدُّ لَهُمْ عَدًّا

ትርጉሙም (በነሱ (መቀጣት) ላይ አትቻኮል፡፡ ለነሱ (ቀንን) መቁጠርን እንቆጥርላቸዋለንና) ማለት ነው፡፡
ማንኛውም የሰው ልጅ በዚህች ዓለም ሲኖር የህይወቱ መሰረት ስራው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

{وَأَنْ لَيْسَ لِلْإِنْسَانِ إِلَّا مَا سَعَى*وَأَنَّ سَعْيَهُ سَوْفَ يُرَى*ثُمَّ يُجْزَاهُ الْجَزَاءَ الْأَوْفَى}

ትርጉሙም (ለሰውም ሁሉ የሠራው እንጅ ሌላ የለውም፡፡ ሥራውም ሁሉ ወደፊት ይታያል፡፡ ከዚያም ሙሉውን ምንዳ ይመነዳዋል) ማለት ነው፡፡
በመሆኑም ልባም ሰው አላህ (ዐ.ወ.) መጨረሻውን አሳምሮለት ጌታውን ከሱ የወደደለት ሆኖ ይገናኝ ዘንድ ያለማቋረጥ ለአላህ ታዛዥ ለመሆን ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡ አንድ ሰው የቀቡለነት በር በየትኛው ኢባዳ ሊከፈትለት እንደሚችል አያውቅም፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እዝነቱን በኢባዳው ውስጥ መደበቁን ንብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ገልጸውልናል፡
ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ በመንገድ እየተጓዘ ሳለ ውሃ ጥም በጣም ጠናበት፡፡ ከዚያም የጉድጓድ ውሃ አገኘ፡፡ ወደጉድጓዱ ወርዶም ውሃ ጠጣ፡፡ ከወጣ በኋላ አንድ ውሻ እያለከለከ ከውሃ ጥም ብዛት አፈር ሲበላ አየ፡፡ ይህ ውሻ በኔ የነበረው አይነት ውሃ ጥም ይዞታል አለና እንደገና ወደጉድጓዱ ገብቶ በኩፍ ጫማው ውሃ ሞልቶ በጥርሱ ይዞ ወጣና ውሻውን አጠጣው፡፡ ይህን ተግባሩን አመስግኖለት አላህ (ሱ.ወ.) ወንጀሉን ማረለት፡፡ በሌላ ሃዲስ ደግሞ አላህ ይህን ሥራውን አመስግኖለት ጀነት አስገባው ይላል)፡፡
እንደዚሁም አላህ (ሊ.ወ.) ቁጣውን በወንጀሎች ወስጥ ደብቋል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በየትኛው ኃጢያት እንደሚያዝ ወይም እንደሚቀጣ ሊያውቅ አይችልም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አንዲት ሴት በድመት ምክኒያት ገሀነም ገባች፡፡ ምክኒያቱም አሰረቻት ከመሆኑም ጋር ምግብ አልሰጠቻትም፡፡ ወይም ደግሞ ከምድር ነፍሳት ትመገብ ዘንድም አልተወቻትም)፡፡ የእውነተኞች እውነተኛ ከልብ ወለድ የማይናገሩት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የሥራ ምንነት የሚወሰነው መጨረሻውን በማየት መሆኑን እንዲህ በማለት አብራርተውልናል፡ (አንድ ባሪያ ሰዎች ሲመለከቱት የጀነት ሥራ የሚመስልን ሥራ ይሠራል፡፡ እሱ ግን የእሳት ሰው ነው፡፡ እንዲሁም ሌላው ሰዎች ሲመለከቱት የገሀነም ሥራ የሚመስልን ሥራ ይሰራል፡፡ እሱ ግን የጀነት ሰው ነው፡፡ ምክኒያቱም ሥራዎች የሚወሰኑት በመጨረሻቸው ነውና)፡፡ በመሆኑም

ነብያችን መጨረሻዬን አሳምርልኝ እያሉ ይጸልዩ ነበር እንዲሁም ይህን ጸሎት ለህዝባቸው ያስተምሩ ነበር፡፡
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.)

( يَا مُقَلِّبَ الْقُلُوبِ ثَبِّتْ قَلْبِي عَلَى دِينِكَ )

ማለት ያበዙ ነበር፡፡ ትርጉሙም (አንተ ልብን የምታገለባበጥ የሆንከው ጌታ ልቤን በሃይማኖትህ አርጋልኝ)፡፡ እኔም ያለህ መላክተኛ ሆይ እኛ በርሶ አምነናል የማጡትንም ሁሉ ተቀብለናል፡፡ ይህ ሆኖ እያለ በኛ ላይ መጥፎ ነገር ይድርስብናል ብለው ይፈራሉ እንዴ ስል ጠየቅኳቸው፡፡ እሳቸውም (አዎን ምክኒያቱም ልቦች በአራህማን ሁለት ጣቶች መካከል የሚገኙ ሲሆን እሱም እንደፈለገ ያገባብጣቸዋል)፡፡ አሉኝ፡፡
ልባም ሰዎች ታዲያ የረመዳን ወር ጌታ እሱ ራሱ የሸዋል ወርና የሌሎቹም ወራት፣ ቀናትና ዘመናት እንዲሁም ቦታዎችም ጌታ መሆኑን ጠንቅው ያውቃሉ፡፡ ከዚህ ላይ ልናነሳው የሚገበናን ጥያቄ ቢኖር የረመዳን ወር ደግ ነገሮችን፣ በረከቶችን፣ ችሮታዎችን ይዞ አለፈ ስንል ስለሸዋልስ ምን ልንል ይገባል የሚለው ጥያቄ ነው፡፡
የመልካም ነገር በሮች ሁሉም አሁንም ከፍት ናቸው፡፡ የልቅና ባለቤት አላህ (ሱ.ወ.) ዛሬም በረመዳንም፣ በሸዋል ሆነ በዙልቀዕዳ በማንኛውም ጊዜ ጸሓይ በመጥለቂያዋ እስከምትወጣ ድረስ የቀን ጥፋተኞች ተጽጽተው እንዲመለሱ ሌለት እንዲሁም የሌሊት ጥፋተኞች እንዲመለሱ ቀን እጁን አንደዘረጋ ነው፡፡
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሙሳ የሚከተለውን አውርተዋል፡ የአላህ መላክተኛ እንዲህ አሉ (አላህ (ዐ.ወ.) የቀን ጥፋተኞች ተጸጽተው እንዲመለሱ ሌሊት እጁን ይዘረጋል፡፡ እንዲሁም የሌሊት ጥፋተኞች እንዲመለሱ ቀን እጁን ይዘረጋል፡፡ ይህውም ጸሓይ ከመጥለቂያዋ አስከምትወጣበት ጊዜ ድረስ ነው)፡፡
በረመዳን ወር የጀነት በሮች የሚከፈቱ መሆናቸውን ስንገልጽ ከረመዳን በኋላም አይዘጉም፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡሁረይራ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ያለህ መላክተኛ እንዲህ ብለዋል፡ (የጀነት በሮች ሰኞና ሐሙስ ይከፈታሉ፡፡ በነሱም በአላህ የማያጀጋራ ሁሉ ወንጀሉ ይማርለታል፡፡ ከወንድሙ ጋር የተጣላ ሰው ሲቀር ፡ ፡ እነሱ እሰከሚታረቁ ተዋቸው ይባላሉ)፡፡ ከዚህ አኳያ ታዲያ የቀመሰ ያውቃል፣ ያወቀ ደግሞ ብሩህ ይሆናል፣ ብሩህ የሆነ ደግሞ ታላቅ ደረጃ ይደርሳል ማለት ይቻላል፡፡ የጾምን፣ የሌሊት ስፍደትንና የቁርኣን ማንበብን ጣእም የቀመሰ ሰው ከረመዳን በኋላ ከነዚህ ኢባዳዎች በምንም መልኩ ሊያቋርጥ አይችልም፡፡
የሙስሊም ኡለሞች አንድ ሰው ኢባዳው ተቀባይነት ማግኙቱ የሚታወቀው ለነዚያ ኢባዳዎች ያለው ውዴታ የማይቀንስ ሲሆንና እነሱን ለማከናውንም ፍላጎት ሲጨምር ነው ይላሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡
{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ}

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው) ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በሌላ አንጽ እንዲህ ይላል፡

{اللَّهُ نَزَّلَ أَحْسَنَ الْحَدِيثِ كِتَابًا مُّتَشَابِهًا مَّثَانِيَ تَقْشَعِرُّ مِنْهُ جُلُودُ الَّذِينَ يَخْشَوْنَ رَبَّهُمْ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمْ وَقُلُوبُهُمْ إِلَى ذِكْرِ اللَّهِ ذَلِكَ هُدَى اللَّهِ يَهْدِي بِهِ مَن يَشَاءُ وَمَن يُضْلِلِ اللَّهُ فَمَا لَهُ مِنْ هَادٍ}

ትርጉሙም (አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ ተደጋጋሚ የሆነን መጸሐፍ አወረደ፡፡ ከርሱ (ግሳጼ) የነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ፡፡ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ማስታዎስ ይለዝባሉ፡፡ ይህ የአላህ መምሪያ ነው፡፡ በርሱ የሚሻውን ሰው ይምርበታል፡፡ አላህም የሚያጠመው ሰው ለርሱ ምንም አቅኚ የላውም) ማለት ነው

በረመዳን ወር ከቁርኣን ጋር የኖረ ሰው ከረመዳን በኋላ ሊተውው ከቶ አይችልም፡፡ እንዲሁም የሌሊት ስግደትን የተላመደና ጣእሙን የቀመሰ ሰው ከረመዳን በኋላ አይተወውም፡፡ አሁንም በረመዳን ወር በአላህ መንገድ የስጦታና ልግሳናን ጥፍጥና የቀመስም ሰው ከረመዳን በኋላ ከዚህ ተግባሩ ሊቆጠብ አይችልም፡፡ አንድ ሰው በረመዳን ኢባዳን ከተለማመደ፣ ከወደደውና እርካታ ካገኘበት በኋላ አመቱን ሙሉ በዚሁ ስርኣት መዝለቅ ይኖርበታል፡፡ ነብያችን ረመዳን አለቀ ብለን ጾምን እንዳንተው ሲገፋፉን ረመዳንን በጾም ያስከተለ ሰው ታላቅ ምንዳ እንዲያለው እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡ (ረመዳን ከጾመ በኋላ ከሸዋል በስድስት ቀናት ያስከተለ ሰው እንደ አመትን ሙሉ ጾም ይቆጠርለታል)፡፡

እውነተኛ ጾመኛ ማለት ጾሙ የአላህ (ዐ.ወ.)ን ፍራቻን ያወረሰው ጾም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አላህን የሚፈሩትን ሰዎችና ምንዳቸውን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡

{إِنَّ الْمُتَّقِينَ فِي جَنَّاتٍ وَعُيُونٍ *آخِذِينَ مَا آتَاهُمْ رَبُّهُمْ إِنَّهُمْ كَانُوا قَبْلَ ذَلِكَ مُحْسِنِينَ *كَانُوا قَلِيلًا مِّنَ اللَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ*وَبِالْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ}

ትርጉሙም (አላህን ፈሪዎቹ በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው፡፡ ያነን ጌታቸው የሰጣቸውን ተቀባዮች ሆነው (በገነት ውስጥ ይሆናሉ) እነርሱ ከዚህ በፊት መልካም ሰሪዎች ነበሩና፡፡ ከሌሊቱ ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበር፡፡ በሌሊቱ መጨረሻም እነርሱ ምህረትን ይለምናሉ) ማለት ነው፡፡

ከአንቀጹዋ እንደምንረዳው አላህን የሚፈሩትን ሰዎች ተግባራት በረመዳን ሌሊቶች አልወሰነውም፣ እንዲሁም አላህ (ሱ.ወ.) የሌሊት ስግደት የሚያደርሱን ምእምናን ማንነት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡

{تَتَجَافَى جُنُوبُهُمْ عَنِ الْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنفِقُونَ * فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَّا أُخْفِيَ لَهُم مِّن قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ }

ትርጉሙም (ጌታቸውን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ጸጋ) ይለግሳሉ፡፡ ይሰሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለነሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም) ማለት ነው፡፡
በዚህችኛዋም አንቀጽ የሰጋጆችን ተግባር አጠቃላይ በሌሎችም ወራትና ቀናት የሚካተት መሆኑን እንጅ በረመዳን ወር እልሰነውም፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሙስሊም መልካም ሥራዎችን ማዘውተርና ያለማቋረጥም የአላህን ትእዛዝ ለመፈጸም ይኖርበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

{فَاسْتَقِمْ كَمَا أُمِرْتَ وَمَنْ تَابَ مَعَكَ وَلَا تَطْغَوْا إِنَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}

ትርጉሙም (እንደታዘዝከውም ቀጥ በል ከአንተ ጋር ያመነቱም (ቀጥ ይበሉ) ወሰንንም አትለፉ እርሱ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና) ማለት ነው፡፡
እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡

{أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ مَا يَكُونُ مِنْ نَجْوَى ثَلَاثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمْ وَلَا خَمْسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمْ وَلَا أَدْنَى مِنْ ذَلِكَ وَلَا أَكْثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمْ أَيْنَ مَا كَانُوا ثُمَّ يُنَبِّئُهُمْ بِمَا عَمِلُوا يَوْمَ الْقِيَامَةِ إِنَّ اللَّهَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ.

ትርጉሙም (አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውን በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያቅ መሆኑን አታይምን ከሦስት ሰዎች መሾካሾክ አይኖርም አርሱ አራተኛቸው ቢሆን እንጂ ከአምስትም (አይኖርም) እርሱ ስድስተኛቸው ቢሆን እንጂ ከዚያ ያነሰም የበዛም (አይኖርም) አርሱ የትም ቢሆኑ አብሯቸው ቢሆን እንጂ ከዚያም በትንሳኤ ቀን የሰሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አላህ ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው) ማለት ነው፡፡
ሱፍያን ኢብን አብደላህ አሰቀፊ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ከእለታት አንድ ቀን ለነብያችን እንዲህ አልኳቸው፡ የአላህ ምልእክተኛ ሆይ! (ስለእስልምና ከርሰዎ ሌላ ማነንም ለመጠየቅ የማያሰፈልገኝ ቃል ነግሩኝ፡፡ አሳቸውም (በአላህ አምኛለሁ በል ከዚያም ቀጥተኛውን መንገድ አትልቀቅ) አሉ)፡፡ በኢባዳ ቀጥ ብሎ መዘውተር የምእምናን ገጽታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ قَالُوا رَبُّنَا اللَّهُ ثُمَّ اسْتَقَامُوا فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ}

ትርጉሙም (እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉትና ቀጥ ያሉት በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፡፡ አነርሱም አያዝኑም) ማለት ነው፡፡ እነንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ قَالُوا رَبُّنَا اللَّهُ ثُمَّ اسْتَقَامُوا تَتَنَزَّلُ عَلَيْهِمُ الْمَلَائِكَةُ أَلَّا تَخَافُوا وَلَا تَحْزَنُوا وَأَبْشِرُوا بِالْجَنَّةِ الَّتِي كُنْتُمْ تُوعَدُونَ .

ትርጒሙም (እነዚያ ጌታችን አለህ ነው ያሉ ከዚያም ቀጥ ያሉ፡፡ አትፍሩ አትዘኑም በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ በማለት በነርሱ ላይ መልአክት ይወርዳሉ፡፡
ሐስን ኢል በስሪ የተባሉት ሊቅ እንዲህ ይላሉ ‹አንድ መልካም ሥራ ስንሰራ አላህ ተጨማሪ መልካም ስራ እንዲንሰራ ችሎታ በመስጠት ወሮታ ይቸረናል፡፡ አንድ መጥፎ ስራ ስንሰራም ተጨማሪ ኃጢያት እንዲንሰራ በማድረግ ይቀጣናል፡፡ አላህ አንድን ባሪያ ሲቀበለው ሌላ ኢባዳ እንዲሰራ ያሳካለታል፡፡ ከወንጀልም ያርቀዋል፡፡ አንድ ሰው ምልካም ስራ ሰርቶ እንደገናም ሌላ መልካም ስራ እንዲፈጸም ከተሳካለት የሚጀመሪያው መልካም ስራ ተቀባይነት ማግኘቱን ያመለክታል፡፡ በአንፃሩም መልካም ስራ ሰርቶ በኋላ ምጥፎ ስራ ካስከተለው የመጀመሪያው መልካም ስራ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ይገልጻል፡፡
እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የሚገባ ነገር ቢኖር በኢባዳ መዘውተርና ኢባዳን አለማቋረጥ የሚከተለውን የአላህን ቃል በማክበር መሆኑን ነው፡

{وَٱعۡبُدۡ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأۡتِيَكَ ٱلۡيَقِينُ}

ትርጒሙም (እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ) ማለት ነው፡፡
በሌላ እንቀጽ እንዲህ ይላል፡

{فَإِذَا فَرَغۡتَ فَٱنصَبۡ ۞ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَٱرۡغَبۡ}

ትርጒሙም (በጨረስክም ጊዜ ልፋ (ቀጥል)፡፡ ወደጌታህም ብቻ ከጅል) ማለት ነው፡፡ ፍችውም አንድን ኢባዳ ከጨረስክ በኋላ የአላህ (ዐ.ወ.)ን ውዴታ በመከጀል ሌላን ኢባዳ እንደገና ጀምር ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በዚህ መልኩ ኢባዳን ያደርሱ ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናነታችን አኢሻ የነብያችን ኢባዳ ምን ይመስል ነበር የሚለዩትስ ቀን ነበረን የሚል ጥያቄ በተጠየቁ ጊዜ እንዲህ ሲሉ መልሰዋል( አልነበረም ብቻ ስራቸው ቀጣይነት ያለው ነበር) በሌላ ወሬም (አንድን ስራ በሰሩ ጊዜ ይዘወትሩበት ነበር) በማለት መለሰዋል፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁ፣ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

በአላህ (ዐ.ወ.) ኢባዳ መዘውተር እሱም እንደሚከታተለን መገንዘብ የመጨረሻ ማማር ጠቋሚ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛ መሰረት ባለቤቱን ወደሚፈለገው

ትክክለኛ ውጤት ያድርሳልና፡፡ ይህን ጉዳይ በርካታ ሊቃውንት ከሚከተለው የአላህ ቃል በምርምር እንደደረሱበት ይጠቁማሉ፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنْتُمْ مُسْلِمُونَ }

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ) ማለት ነው፡፡

አነዚያ ሊቃውንት የዚህች አንቀጽ ትክክለኛ ፍች ‹እስልምናችሁን ጠብቁ፣ በመልካም ስራም ዘውትሩ፣ አላህንም እንደሚገባው አድርጋችሁ ፍሩት፡፡ በዚህም ተግባር ኑሩ፣ ሙቱ፣ በሱ ከሞት ትቀሰቀሳላችሁና፡፡ በፍጥረቱ ውስጥ ያለው የአላህ ደንብ ‹በአንድ ነገር ላይ የኖረ ሰው በሱ ይሞታል በሱም ከመቃብር ይቀሰቀሳል› ማለት ነው ይላሉ ሊቃውንት፡፡

በተከበረው ነብያዊ ሐዲስ ነብያችን እንዲህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው በአላህ መንገድ አይቆስልም፣ አላህ በሱ መንገድ የሚቆስለን አዋቂ ነው፣ በእለተ ቂያማ ቀለሙ የደም ቀለም ጠረኑ ግን የምስክ ጠረን ሆኖ የሚመጣ ቢሆን እንጅ) ብለዋል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰወዬ የሀጅን ሥራ እያከናወነ ሳለ ግመሉ ጥላው መሞቱን ባዩ ጊዜ እንዲህ ብለዋል (በውሃና በቁርቁራ ቅጠል እጠቡት በለበሰውም ልብሱ ገንዙት፡፡ ራሱን አትሸፍኑት ሽቱም አታድርጉለት አላህ የቂያማ እለት የሐጅን ስራ እንደያዘ ያስነሳዋልና)፡፡

መጨረሻ እንዲያመር ከሚያደርጉ ነገሮች እንዱ አንድ ባሪያ ከጌታው ገር እውነተኛ መሆኑ ነው፡፡ እውነተኛ ሃሳብ ከኢላማ ለመድረስ ታላቅ አስተዋጽኡ አለውና፡፡ ይህን ጉዳይ የሚከተለው ዘላን አረብ ታሪክ በግልጽ ያሳየዋል፡፡ ይህ ዘላን አረብ ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሄደና በሳቸው ማመኑን ገልጾ እንደሚከተላቸው አስታወቀ፡፡ ከዚያም ከርሶ ጋር ለሃይማኖቴ እሰደታለሁ አለ፡፡ እሳቸው ባልደረቦቻቸው እንድንከባከቡት አዘዙ፡፡ ከዚያም ነብያችን ካገኙት ገንዘብ እንደሌሎቹ ሁሉ እጣፋንታውን ላኩለት፡፡ እሱም ይህ ምንድን ነው ሲል ጠየቀ፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የላኩልህ ድርሻህ ነው አሉት፡፡ ይህን ድርሻውን ይዞ ወደነብያችን ሄደና ይህ መንድን ነው ሲል እንደገና ጠየቀ፡፡ እሳቸው የላኩልህ ድርሻህ ነው አሉት፡፡ እሱም በዚህ መልኩ ዓይደለም የተከተልኩዎት፡፡ ነገር ግን እኔ የተከተልኩዎት ወደ አንገቱ እያመለከተ እዚህ ላይ በጦር ልወጋና ጀነት ልገባ ነው አላቸው፡፡ እሳቸውም (ለአለህ እውነተኛ ብተሆን እሱም ለአንተ እውነተኛ ይሆናል) አሉት፡፡ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ከጠላት ጋር ጦርነት ጀመሩ እሱንም ከአመለከተው ላይ በጦር ተወግቶ ተሸክመው ወደነብያችን አመጡት፡ ፡ ነብያችንም (እሱ ያ ሰውዬ ነውንዴ) ሲሉ ጠየቁ፡፡ አዎን አሏቸው፡፡ እሳቸውም (ለአላህ እውነተኛ ሆነና አላህ ከሱ ጋር እውነተኛ ሆነ) አሉና በራሳቸው መጎናጸፊያ ገነዙት ከዚያም ሰገዱበት በስግደቱም ወቅት እንዲህ ሲሉ ጸለዩለት ( ጌታዬ ሆይ ይህ ባሪያህ ባንተ መንገድ ተሰደተ ሰማእትም ሆኖ ሞተ እኔ በዚህ ጉዳይ ምስክር ነኝ)፡፡

አላህ ኢባዳ እንዲያደርግ ያሳካለት፣ ስራውን ያሰመረለት፣ ጠባዩም ያመረለት፣ የሰዎችን ጉዳይ እንዲያዎጣና ጭንቅንም እነዲያቃልል እንዲሁም በማህበረሰቡና በሀገሩ ደግን ነገር በማከናወን አላህ ያገዘው፣ ሰው እጅጉን ታድሏል፡፡ ይህ ተግባሩ

የሚያመለክተው አላህ (ዐ.ወ.) የተቀበለውና ሁሉን ያሳካለት መሆኑን ብቻ ነው፡፡ መጨረሻ የሚያምረው አላህ ለአንድ ባሪያ መልካምን ያሰበለት ሲሆን ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ የሚከተለውን አውርተዋል፡ የአላህ መላክተኛ እንዲህ አሉ፡ (ለአንድ ባሪያ አለህ ደግን ነገር ሲያስብለት ያሰረዋል) ሰዎችም እንዴት ነው የሚያሰራው ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ከሞቱ በፊት መልካም ስራ እንዲሰራ ያሳካለታል) አሉ፡፡ በሌላ ሐዲስም እንዲህ ብለዋል፡ (አላህ ለአንድ ባሪያ ደገን ነገር ሲያስብለት ከመሞቱ በፊት ያጣፍጠዋል አሉ) አንዴት ነው የሚያጣፍጠው ተብለው በተጠየቁ ጊዜ (ከመሞቱ በፊት የመልካም ስራን በር ይከፍትለታል ከዚያም ከሱ ይወድለታል) ሲሉ መልሰዋል፡፡
ጌታችን ሆይ ከሞት በፊት ተጸጽቶ መመለስን፣ ስንሞትም ሰማእትነትን፣ ከሞት በኋላም ጀነትና ተድላዋን ለግሰን፡፡

# (47)

## ከስንብቱ ሐጅ ድስኩር (ኹጥበተል ሒጀቲል ወዳዕ) የምንቀስማቸው ትምህርቶች

*ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ*

{ الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الإِسْلاَمَ دِينًا }

ለአለው ለኣለማቱ ጌታ ኢ,ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም( ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ዐ.ወ.) ሰዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን ሊያወጣቸና አጃቸውን ይዞ ከጥሜት ወደ ቅን መንገድ ሊያደርሳቸው እንድሁም በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም የስኬትና የድስታን ጎዳና ሊመራቸው መልክተኛውን በቅን መንገድና በትክክለኛው ሃይማኖት ልኳል፡፡ በመሆኑም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሰዎች ትሩፋታዊ እሴቶችንና ከፍተኛ አርአያነት ያላቸውን ተግባራት እንድፈጽሙ በማዘዝ የጌታቸውን መልክት በተገቢው መልኩና በምሉእ ገጽታው አድርሰዋል፡፡ በህይዎታቸው እስካሉ ድረስ በቃላቸው፣

በተግባራቸውና እንዲፈጸም በመፍቀዳቸው ሰብአዊ እሴቶች በሰው ልጅ መንፈስ እንዲሰርጹ ሲጥሩ ኖረዋል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ከእስልምና ማእዘናት አምስተኛውን ማእዘን እንዲያከናውኑ በፈቀደላቸው ጊዜ ታላቁ የሰው ልጅ መከማቻ በነበረው በዐረፋት ምድር በአለታማ ኮረብታ ላይ ቆመው ለባልደረቦቻቸውና ከነሱም በኋላ ለመላ የሰው ልጅ በሕወታቸው ሙሉ ሲሰብኩለት የኖሩትን ሰብአዊና ሥነ ምግባራዊ እሴቶችን ያከተተውን የሐጅን ሥራ ምክኒያት በማድረግ ታላቅ ትምህርት ያዘለውን ድስኩር አደረጉ፡፡ የሕይወታቸው መጨረሻና የእድሚያቸው መደምደሚያ መቃረቡ ስለተሰማቸው በዚህ ቀን ያደረጉት የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ንግግር ለአጠቃላይ የሰው ልጅ ስርአተ ሕይወት የሚሆኑ በርካታ ጥልቅ ትምህርቶችንና ርቱዓዊ ምሳሌዎችን ያከተተ ነበር፡፡

* ከነዚህ ትምህርቶችም ውስጥ ከመላ የሰው ልጅ መካከል የፍትህና እኩለነት መርህ መስፈን የሚለው የመጀመሪያ ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (እናንተ ሰዎች ሆይ! ጌታችሁ አንድ ነው፡፡ አባታችሁም አንድ ነው፡፡ ልብ በሉ! ዐረብ ዐረብ ካልሆነ ሰው፣ ዐረብ ያልሆነ ሰው ከዐረብ፣ ቀይ ሰው ከጥቁር ሰውና ጥቁር ሰው ከቀይ ሰው የሚበልጥበት ነገር የለም፡፡ በአላህ ፍራቻ ቢሆን እንጂ፡፡ ከአላህ ዘንድ ከእናንት እጅጉን የተከበረው በጣሙን አላህን ፈሪው ሰው ነው፡፡) በዚህ ቃላቸው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የመበላለጫ መለኪያና መመዘኛ ያደረጉት አላህን መፍራትንና መልካም ሥራን ነው፡፡ ይህውም እንደህ የሚለውን የአላህን ቃል መሰረት በማድረግ ነው፡

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ ሁሉም ሰው በሙብትም ሆነ በግዴታ በመደብና በጎሳ ሳይለይ እኩል ነው፡፡ ይህም የእውነት ሚዛንና የህዝብ እኩልነት እንዳይዛባ የሚጠብቀው የፍትህ መሰረት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.) አንድህ ይላል፡

{وَإِذَا قُلْتُمْ فَاعْدِلُوا وَلَوْ كَانَ ذَا قُرْبَى}

ትርጉሙም (በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢኾንም እንኳ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንደሁም አንድህ ይላል፡

{وَإِذَا حَكَمْتُم بَيْنَ النَّاسِ أَن تَحْكُمُوا بِالْعَدْلِ}

ትርጉሙም (በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ (ያዛችኋል)፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንደህ ይላል፡

{وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَآنُ قَوْمٍ عَلَى أَلَّا تَعْدِلُوا اعْدِلُوا هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَى .

ትርጉሙም (ሕዝቦቻችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፡፡ አስተካክሉ፡፡ እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

* የድም፣ የገንዘብና የክብር እርመነት ሌላው ከነብችን (ሶ.ዐ.ወ.) ድስኩር የምንቀስመው ትምህርት ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደረህማን ኢብን አቢ በክረህ አባታቸውን ጠቅሰው የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ፡ዐ.ወ.) እግመላቸው ላይ ተቀመጡ፡፡ አንድ ሰው የግመሉን ልጓም ያዘና ቆመ፡፡ ከዚያም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ይህ ቀን ምን ቀን ነው? አሉ፡፡ ሁላችንም ዝም አልን፡፡ ከስሙ ሌላ ስም ያወጡለት ይሆን ብለንም ጠረጠርን፡፡ የነሕር ቀን አይደለምን? አሉ፡፡ እኛም አዎ ነው አልን፡፡ አሳቸውም ይህ ያለንብት ወር ምን ወር ነው? አሉ፡፡ አሁንም ሁላችንም ዝም አለን፡፡ ከስሙ ሌላ ስም ይሰጡት ይሆን ብለንም ተጠራጠርን፡፡ የዙልሒጃ ወር አይደለምን? አሉ፡፡ እኛም አዎ ነው፡፡ አልን፡፡ ከዚያም ደሞቻችሁ፣ ንብረቶቻችሁና ክብሮቻችሁ ይህ ቀናችሁ ይህ ወራችሁና ይህ አገራችሁ እርም እንደተደረገ ሁሉ ከናንተ መካከል እርም ናቸው፡፡ አዚህ ቦታ ተገኝቶ ይህን ምክር የሰማ ሰው ላልሰማ ያስተላልፍ፡፡ ምክኒያቱም እዚህ የተገኘና የሰማ ሰው ይህን ምክር ከሱ በተሻለ መልኩ ለሚገነዘበው ሰው ሊያስተላልፍ ይቻላልና፡፡)

በዚህ ወቅት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የድም፣ የንብረትና የክብር እርምነት ታላቅነትን በሚያካትት አስደናቂ ነብያዊ ዘይቤና ርቱእን ቃላት የባልደረቦቻቸውን ትኩረት በመሳብና አእምሯቸውን በማነቃቃት እነዚህ እርም የተደረጉ ነገሮች ሁሉ በምንም መልኩ ሊዳፈሯቸው የማይችሉ ነገሮች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የእስልምና እምነት የሰው ልጅ ሁሉ በደህንነትና በጸጥታ እንድሁም በሰላምና በአማን እንድኖሩ የሚገፋፋ ሲሆን ለመላው የሰው ልጅ ከጎሳ፣ ቀለምና ሃይማኖት ልዩነት ነፃ የሆነ የተረጋጋ ሕይወት እንድመሩ ይሻል፡፡ የእስልምና ህግ ይህን ሙብት ለሁሉም ሰው ያጎናጸፈ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አረጋግጧል፡

{وَلَا تَقْتُلُوا النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ ذَلِكُمْ وَصَّاكُمْ بِهِ لَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ}

ትርጉሙም (ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢኾን እንጅ አትግደሉ፡፡ ይህን ታውቁ ዘንድ (አላህ) በእርሱ አዘዛችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ያለምንም ሙብት አንድትን ሕይወት ማጥፋት የሰውን ልጅ ከመድረ ገጽ እንደማጥፋት መሆኑን እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{مَن قَتَلَ نَفْسًا بِغَيْرِ نَفْسٍ أَوْ فَسَادٍ فِي الأرض فَكَأَنَّمَا قَتَلَ الناس جَمِيعًا وَمَنْ أَحْيَاهَا فَكَأَنَّمَا أَحْيَا النَّاسَ جَمِيعًا}

ትርጉሙም (ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት (ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የደም እርምነትና በማንኛውም መልኩ ይህን ወሰን መተላለፍ የማይፈቀድ መሆኑን እንድህ በማለት አስጠንቅቀዋል፡ (ከኔ በኋላ ከፊላችሁ የከፊላችሁን አንገት በመምታት ወደከህደት

አትመለሱ፡፡) አላህ (ሱ.ወ.) በሕይወት ላይ ወሰን ማለፍን እርም እንዳደረገ ሁሉ ንብረት መዳፈርንም እንደዚሁ እርም ያደረገ መሆኑን እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ إِلَّا أَنْ تَكُونَ تِجَارَةً عَنْ تَرَاضٍ مِنْكُمْ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ፡፡ ግን ከእናንተ በመዋደድ የኾነችውን ንግድ (ብሉ)፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ብሏል፡

{وَلَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ وَتُدْلُوا بِهَا إِلَى الْحُكَّامِ لِتَأْكُلُوا فَرِيقًا مِنْ أَمْوَالِ النَّاسِ بِالْإِثْمِ وَأَنْتُمْ تَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም (ገንዘቦቻችሁንም በመካከላችሁ በከንቱ (ያለ አግባብ) አትብሉ፡፡ እናንተም የምታውቁ ስትኾኑ ከሰዎች ገንዘቦች ከፊልን በኃጢአት ትበሉ ዘንድ ወደ ዳኞች አትጣሏት፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና ህግጋት በአጠቃላይ መልኩ የሰው ልጅ ንብረት እንድከበር መስረቅን እርም ከማድረጉም በላይ ገሳጭ የሆነን ቅጣት ያስቀመጠለት መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አብራርቷል፡

{وَالسَّارِقُ وَالسَّارِقَةُ فَاقْطَعُوا أَيْدِيَهُمَا جَزَاءً بِمَا كَسَبَا نَكَالًا مِنَ اللَّهِ وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ}

ትርጉሙም (ሰራቂውንና ሰራቂይቱንም በሠሩት ነገር ለቅጣት ከአላህ የኾነን መቀጣጫ እጆቻቸውን ቁረጡ፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ በእስልምና ህግ በማንኛውም መልኩ የአንድ ሰው መሬትን መቀማት የተከለከለ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ስንዝር በምትሆን መሬት በደል የፈጸመ ሰው በትንሳኤ ቀን አላህ በሷና በስሯ ትይዩ ባለው ሰባት ምድር አንገቱን ያንቀዋል፡፡) የእስልምና እምነት እንደዚሁ በማንኛውም መልኩ የአንድ ሙስሊምም ይሁን የሌላ እምነት ተከታይ ሰው ክብር መዳፈርን እርም አድርጓል፡፡ የዝሙት እርመነትን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَقْرَبُوا الزِّنَا إِنَّهُ كَانَ فَاحِشَةً وَسَاءَ سَبِيلًا}

ትርጉሙም (ዝሙትንም አትቅረቡ፡፡ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፡፡ መንገድነቱም ከፋ!) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጥብቅ ንጹሃን ሴቶችን መወንጀልን ከመከልከላቸውም በላይ ከተላላቅ ወንጀሎች እንደሚመደብ እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (ሰባት እጥፊዎችን ተጠንቀቁ) አሉ፡፡ በልደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! እነሱ ምን ምንድን ናቸው? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም ነገሮችን ሲዘረዝሩ (... ጥበቆች ከዝሙት ዘንጊዎች ምእምናትን የሚሰድቡ...) አሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በአጠቃላይ መልኩ ስድብና ዘለፋን የከለከሉ ሲሆን አመጽም መሆኑን እንድህ በማለት ጠቁመዋል፡ (ሙስሊምን መሳደብ አመጽ ነው፡ እሱን መዋጋት ደግሞ ክህደት ነው፡፡)

* ከዚህ ድስኩር የምንቀስመው ሌላው ትምህርት ደግሞ ለአንድነት መጣር ጠቃሚ መሆኑን መጠቆማቸውንና ከመለያየት ማስጠንቀቃቸውን ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በድስኩሩ ማህል እንድህ ብለዋል፡ (ሰይጣን በመጨረሻው ዘመን በዚህ በሀገራችሁ እንደማይመለክ በአርግጥ ተስፋ ቆርጧል፡፡ በመሆኑም ከናንተ ዝቅተኛ በሆኑ ወንጀሎች ለመርካት ተገዷል፡፡ ስለዚህ በሃይማኖታችሁ ችግር እንዳያደርስ ተጠንቀቁት...) እዚህ ላይ ታድያ አንድ እነሁን፡፡ በአላህ የማመንን ገመድም ሁላችንም አጥብቀን እንያዝ እንላለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَاعْتَصِمُواْ بِحَبْلِ اللّهِ جَمِيعًا وَلاَ تَفَرَّقُواْ}

ትርጉሙም( የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ፡፡ አትለያዩም፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَأَطِيعُواْ اللّهَ وَرَسُولَهُ وَلاَ تَنَازَعُواْ فَتَفْشَلُواْ وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ}

ትርጉሙም (አላህንና መልክተኛውንም ታዘዙ፡፡ አትጨቃጨቁም፡፡ ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትኼዳለችና፡፡) ማለት ነው፡፡ መለያየትና መበታተን ከአላህ ሃይማኖት ውጭ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አብራርቷል፡

{إِنَّ الَّذِينَ فَرَّقُواْ دِينَهُمْ وَكَانُواْ شِيَعًا لَّسْتَ مِنْهُمْ فِي شَيْءٍ }

ትርጉሙም( እነዚያ ሃይማኖታቸውን የለያዩ አሕዛብም የኾኑ በምንም ከእነሱ አይደለህም፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና እመነት ወደአንድነት ሲጠራ ጭቅጭቅና መለያየትን ይከለክላል፡፡

* ከዚህ የነብያችን (ሶ.አ.ወ.) ድስኩር የምንቀስመው ሌላው ትምህርት ደግሞ የአለህን ኪታብና የነብዩን ፈለጎች አጥብቆ ማያዝ የተጣለብን ግዴታ መሆኑን ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (... ከናንተ መካከል እሱን አጥብቃችሁ ከያዛችሁት ምንም ዓይነት ጥሜት የማያገኛችሁ የሆነን ነገር ትቻላችኋለሁ፡ እሱም የአላህ መጽሐፍ ነው፡፡ እናንተም ስለኔ ተጣያቂዎች ናችሁ...) የአላህ (ዐ.ወ.) መጽሐፍ ከፊቱም ሆነ ከኋላው ከንቱነት የመያመጣበት፣ አመታት ቢያልፉም፣ ዘመናት ቢነጉዱም የማይለወጥና የማይቀየር የሆነው አላህ በሱና በነብዩ ፈለጎች ከንቱ ፍለጎቶችን የቆረጠበትና መለያየትን ከንቱ ያስቀረበት ለዘላለም ነዋሪ የሆነው ታምር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنْكُمْ فَإِنْ تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ إِنْ كُنْتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ذَلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡ መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት፡፡ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ የአላህን መጽሐፍና

የነበዩን ፈለጎች አጥብቆ መያዝ የእምነት ምልክትና የፈሪሃ አላህነት ማስረጃ ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّى يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنْفُسِهِمْ حَرَجًا مِمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا .

ትርጉሙም(በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ፡፡ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እጠይቃለሁኝ፡፡

*  *  *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የስንብት ሐጅ ድስኩር የመጀመሪያው አለም አቀፍ የሰብኣዊ መብት ጥበቃ ቃል ኪዳንና መግለጫ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ይህውም የሰው ልጅ ክብርን የሚጠብቁና ደህንነቱንና ሰላሙን እውን የሚያደረጉ በርካታ ሰብኣዊ እሴቶችን ያካተተ በመሆኑ ነው፡፡ ከስንብቱ ሐጅ ድስኩር ከምንቀስማቸው ትምህርቶችን በጣም ዋና የሚባለው የሴቶችን ደረጃና በእስልምና ህግጋት ያላቸውን ቦታ በግልጽ ማብራራቱ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የሴትን ከብርና ያለትን ከፍተኛ ቦታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሰዎች ይህን እውነት እንዲያቁና ተግባራዊም እንዲያደርጉ ትእዛዝ አስተላልፈዋል፡፡ ሴቶች የወንዶች ተከፋዮች ሲሆኑ በሙብትም ሆነ በግዴታ እኩል የሚለዋወጧቸው ሁኔታዎች አሉ፡ ነብያችን እንድህ ይላሉ፡ (ለናንተ በሴቶቻችሁ ላይ መብት አላችሁ፡፡ ለነሱም በናንተ ላይ መብት አላቸው፡፡)
የአስልምና እምነት እናት፣ እህት፣ ልጅና ሚስት የሆነችውን ሴትን እጅጉን አከብሯታል፡፡ እንድሁም የሰብኣዊ ክብሯን የሚጠበቁና በዚህችም አለም ይሁን በመጭው አለም ለደስታዋ ዋስትና ያለቸውን መብቶች ሰጥቷታል፡፡ ነብያችን ከኔ የመልካም ጓደኝነት ተቀዳሚ መብት ያለው ማነው ብሎ ለጠየቃቸው ሰው የሰጡት መልስ (እናትህ) የሚል ነበር፡፡ ከዚያስ ብሎ ቢጠይቅም (ከዚያም እናትህ) አሉት፡፡ አሁንም ከዚያስ ብሎ ሲጠይቅ (ከዚያም እናትህ) አሉት፡፡ አንደገናም ከዚያስ ብሎ ጠየቀ አሳቸውም (ከዚያም አባትህ) አሉት፡፡
ነብያችን እንድህ ብለዋል፡ (ሦስት ሴት ልጆች ያሉትና በነሱ ላይ የተጋሰ፣ ያበላቸው፣ ያጠጣቸውና ፈጣሪ ከለገሰው ጸጋ ያለበሳቸው ሰው በትንሳኤ ቀን ከእሳት መከታ

ይሆኑለታል፡፡) በሌላ ዘገባ ደግሞ እንድህ ብለዋል(ሁለት ወይም ሦስት ሴት ልጆቹን ወይም ሁለት ወይም ሦስት እህቶቹን አስከሚለዩ ወይም እሱ እስከሚሞት ደረስ ያሳደገ ሰው እኔና እሱ እንደነዚህ እንሆናለን አሉና ሌባ ጣትና ማህል ጣታቸውን አሳዩ፡፡)
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ አሉ፡ ‹የአላህ መልክተኛ እንድህ ብለዋል፡ (በሴቶች አደራ ተባባሉ፡፡ ሴቶች ከጎን አጥንት ነው የተፈጠሩት፡፡ ከጎን አጥንት እጅግ ጠማማው የላይኛው ከፍል ነው፡፡ ቀጥ አደርጋለሁ ብለህ የተነሳህ እንደሆን ትሰብረዋለህ፡፡ ከተውከውም ከጠማማነቱ አይወገድም፡፡ ስለሴቶች በበጎ ነገር አደራ ተባባሉ፡፡) በነብያችን ሐደስ የተጠቀሰው በጎ ነገር የሚለው ቃል እምቅ ፍች ያለው ቃል ነው፡፡ ወንዶች ከሴቶች ጋር በሚዋዋሉበት ጊዜ ታላቁን የወንድነት ትርጉም እንድላበሱ ግድ የሚል መሆኑንም ይጠቁማል፡፡
እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት ይህን ለሰው ልጅ ሁሉ መልካም ነገሮችን ሁሉ ያቀፉ እሴቶችን ተግባራዊ ማድረግ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ አነዚህ በእርግጥ ግዚያቸውን ቀድመው የተከሰቱ የሰብኣዊ መብትን ያሰፈኑ መሰረታዊ የሰብእና እሴቶችን ያካተቱ መርሆች ለሰው ልጅ የዚህች አለምና የመጭውም አለም ደስታ መንሰኤዎች ናቸው፡፡
ጌታችን ሆይ! ከኛ መልካም ሥራን ተቀበል አንተ ሰሚና አዋቂም ነህና፡፡ ጸጸትንም ለግሰን አንተ ጸጸትን ሊጋሽና አዘኝም ነህና፡፡ አሜን፡፡

# (48)

## ከሐጅ በኋላ ምን ማድረግ አለብን?

ምስጋና ሁሉ በተከበረው

**إِنَّ الَّذِينَ قَالُوا رَبُّنَا اللَّهُ ثُمَّ اسْتَقَامُوا تَتَنَزَّلُ عَلَيْهِمُ الْمَلَائِكَةُ أَلَّا تَخَافُوا وَلَا تَحْزَنُوا وَأَبْشِرُوا بِالْجَنَّةِ الَّتِي كُنْتُمْ تُوعَدُونَ}**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ተርጉሙም (እነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ያሉ ከዚያም ቀጥ ያሉ «አትፍሩ፤ አትዘኑም፤ በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ» በማለት በነሱ ላይ መላእክት ይወርዳሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣

በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

*አላህ (ዐ.ወ.) ለፍጥረታቱ ያስቀመጠውን ደንብ የሚመራመር ሰው ቀናት፣ ወራትና ዐመታት በፍጥነት ሲጓዙ ይመለከታል፡፡ ቀናት ሲያልፉ ዓመታት ሲተካኩ ሲመለከትም የዚህች ዓለም ኑሮ የተወሰኑ ስትንፋሳትና ገደብ የተደረገላቸው ጊዚያትእንጂ ሌላ ነገር አለመሆኗን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ጉዳይ ለሚያስተውል ሰው ታላቅ ታምር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡*

{وَهُوَ الَّذِي جَعَلَ اللَّيْلَ وَالنَّهَارَ خِلْفَةً لِمَنْ أَرَادَ أَنْ يَذَّكَّرَ أَوْ أَرَادَ شُكُورًا}

(እርሱም ያ (ያመለጠውን ሥራ) ማስታወስን ለሚፈልግ ወይም ማመስገንን ለሚፈልግ ሰው ሌሊትንና ቀንን ተተካኪ ያደረገ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው የሐጅን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት በሱ አላህ ወንጀልን የሚምርበት ከሆነና እናቱ እንደወለደችበት ቀን ሆኖ የሚመለስ ከሆነ ለበኛ ሰው ይህን የአላህን ትሩፋት ላለማስመለጥ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ከሁሉም ሃጢያት ራሱን አርቆ በታማኝነትና በንጹህ ልብ ወደአላህ መንገድ ሊገባ ይገበዋል፡፡ ማንኛውም የሐጅን ሥራ ማከናውን የቻለ ሰው አላህ ለዚህ ታላቅ ትሩፋት ስለአበቃው ምስጋና ማድረስና ተድላውንም አጉልቶ ማሳየት ይወደድለታል፡፡ ለታላቁ አላህ መገዛት በቦታም ሆነ በዘመን የማይወሰንና ማንኛውም ሰው ስትንፋሱ እስካለች ድረስ የሚቀጥል ግዴታ በመሆኑ ከመልካም ሥራ መቼም ቢሆን አለመቦዘን ይጠበቅበታል፡፡ ይህ የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ተግባር ሲሆን እንድህ የሚለውን የአላህን ቃል በማክበር ነው፡

{وَاعْبُدْ رَبَّكَ حَتَّى يَأْتِيَكَ الْيَقِينُ}

(እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ የሚለውን ቃል በመፈጸም ነው፡

{فَإِذَا فَرَغْتَ فَانْصَبْ ۝ وَإِلَى رَبِّكَ فَارْغَبْ}

(በጨረስክም ጊዜ ልፋ፡፡ (ቀጥል)፡፡ ወደ ጌታህም ብቻ ከጅል፡፡) ማለት ነው፡፡ ይህን ማለትም አንድ አምልኮን ስትጨርስ በሌላ አምልኮ መጠመድ ይጠበቅበሃል ማለት ነው፡፡

መልካም ሥራን ማዘውተር አላህ ከሚወዳቸው ሥራዎች አንዱ ሲሆን የአንድ ሰው መረሻ መልካምነት ምልክትም ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናትን ዓኢሻ እንድህ ብለዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አላህ (ዐ.ወ.) የሚወደው ሥራ የትኛው እንደሆነ ተጠይቀው የሰጡት መልስ (ቢያንስም እንኳ ያለማቋረጥ የሚሠራ መልካም ሥራ

ነው) የሚል ነበር፡፡ ለአላህ የሚገዛ፣ *ሥራው* ያመረ፣ ጠባዩ ደግ የሆነ፣ የሰዎችን ጉዳይ የሚያጣ፣ ለማህበረሰቡና ለህገሩ ደግ የሚሠራ ሰው ምንጊዜም ደስታ አለየውም፡፡
አላህ የሐጅን *ሥራ* እነዲያከናውን እድሉን የሰጠው ሰው ይህን ችሮታ በማመስገን በስግደትም ሆነ በጾም በፈቃድ የሚደረሱ ኢባዳዎችን በማብዛት ለደሆችና ለሙታን ልጆች ምጽዋት በመስጠት የማያቋርጥ መልካም *ሥራውን* መቀጠል አለበት፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡ (... ባሪያዬ በሱ ላይ ግድ ካደረግሁበት ነገር የበለጠ በምወደው ነገር ወደኔ ሊቃረብ አይችልም፡፡ ባሪያዬ ዘወትር በትርፍ ዒባዳዎች ወደኔ ወደኔ የሚቃረብ አይሆንም በመጨረሻ የምወደው ብሆን እንጂ፡፡ እኔ ከወደድሁት ደግሞ የሚያዳምጥበት መስሚያው፣ በሱ የሚመለከትበት ማያው፣ በሱም ጀብዱ የሚሠራበት እጁና በሱ የሚራመድበት እግሩ እሆነዋለሁ፡፡ ከጠየቀኝም እሰጠዋለሁ፡፡ በኔም መጠበቀን ከለመነ እጠብቀዋለሁ፡፡)
አንድሁም አንድ ሰው ከሐጀ ከተመለሰ በኋላ በመልካም ምግባሩ፣ በመቻቻሉና ከሰዎች ጋር በሚኖረው ልዝብ ግንኙነት የሐጅ *ሥራ* ያሰደረበት መልካም ተጽእኖ ጎልቶ መታየት ይኖርበታል፡፡ በሐጅ *ሥራ* ምናልባት የተጓደለ ነገር ካለ ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት በማሻሻልና መልካም ምግባሮችን በማብዛት ሊያካከስ ይገባል፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَى حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَاهَدُوا وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ أُولَئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ .

*(መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፡፡ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡)*

የሐጀ *ሥራ* አላማ አልባ በዘ ልማድ የሚፈጸም ወሰጠባዶ ተግባር አይደለም፡፡ ይልቁንም የሰውን ልጅ ከፍ ለማድረግና ጸባዩንም ለማዋብ የተደነገገ ኢባዳ ነው፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

ٱلۡحَجُّ أَشۡهُرٞ مَّعۡلُومَٰتٞۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلۡحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي ٱلۡحَجِّۗ وَمَا تَفۡعَلُواْ مِنۡ خَيۡرٖ يَعۡلَمۡهُ ٱللَّهُۗ وَتَزَوَّدُواْ فَإِنَّ خَيۡرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقۡوَىٰۖ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ}

ትርጉሙም (ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፡፡ በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም፡፡ ከበጎም ሥራ የምትሠሩትን ሁሉ አላህ ያውቀዋል፡፡ ተሰነቁም፤ ከስንቅም ሁሉ በላጩ ጥንቃቄ (አላህን መፍራት) ነው፡፡ የአእምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ፡፡) ማለትነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ ይህን ቤት ለመጎብኘት የመጣ ሰው ጽያፍ ቃል ካልተናገረና አመጽ ካልፈጸመ እናቱ እንደወለደችበት ቀን ሁኖ ይመለሳል፡

ሐሰን አልበስሪ የተባሉት የእምነቱ ሊቅ ተቀባይነት ያለው የሐጅ ሥራ ምንዳው ጀነት ነውን? የሚል ጥያቄ በቀረበላቸው ጊዜ ‹የሱ ምልክቱ ይህችን ዓለም የናቀ ለመጭው ዓለም የሚሠራ መሆኑነው› የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ እንድሁም የሐጅ ስራ ምንዳው ከአለህ ዘንድ ምህረትን ማግኘት ነውን? የሚል ጥያቄ በተጠየቁም ጊዜ ‹የሱ ምልክቱ ከዚህ በፊት ይሰራው ከነበረው መትፎ ሥራ ከነመሰረቱ መራቁ ነው› በማለት መልሰዋል፡፡

ማንኛውም ኢባዳ በአንድ ሰው ሥነ ምግባር ተጽእኖ ካላሳደረና ጠቅላላ ስራውን በማስተካከል ሚና ከሌለው በዚህች ዓለም ዋጋ አይኖረውም በምጭውም ዓለም ፍሬ አያስገኝም፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን(ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ሲሉ ባልደረቦችን ጠየቁ፡ ( ድሃ የሚባለው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን?) እነሱም የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኛ ጋ ድሃ የሚባለው ብርና እቃም የሌለው ነው አሉ፡፡ እሳቸውም (ሶ.ዐ.ወ.) (ከህዝቦች ድሃ የሚባለው በትንሳኤ ቀን ስግደቱን፣ ጾሙንና ምጽዋቱን ይዞ የሚመጣና በሌላም በኩል ይህን የሰደበ ያን የዘለፈ፣ የዚህን ገንዘብ የበላ የዚያን ደም ያፈሰሰና ይህን የመታ ሆኖ የሚቀርብ ሰው ነው፡፡ እሱም ይቀመጥና ከመልካም ሥራው ለዚህ ካሳ ሲከፍል ለዚያም እዳ ሲወጣ ይቆይና ካሳውና እዳው በሙሉ ሳይከፈል መልካም ሥራው ካለቀ ከነሱ ወንጀል ይነሳና ከሱላይ ይጨመራል በዚህም ገሀነም ይዘፈቃል፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እገሊት የስግደቷ፣ የጾሟና የምጽዋቷ ብዛት ይወሳል፡፡ ነገር ግን እሷ በምለሷ ጎረቤቶቿን ታስቸግራለች ሲሉ ባልደረቦች ነገሯቸው፡፡ እሳቸውም (እሷ እሳት ትገባለች) አሉ፡፡ እንድሁም እገሊት የጾሟ፣ የምጽዋቷና የስግደቷ ማነስ ይወራል ነገር ግን እሷ በምላሷ ጎረቤተቿን አታስቸግርም በማለት በጠየቁ ጊዜ (እሷ ጀነት ትገባለች) አሉ፡፡

አንድ ሰው ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባው ነገሮች በመጀመሪያ የሚጠቀሰው የመጨረሻ ማማር ነው፡፡ መጨረሻ ማማር ማለት አንድ ሰው ከመሞቱ በፊት አላህ

ከሚጠላው ነገር ለመራቅ የሚያደርገውን ጥረት አላህ (ዐ.ወ.) የሚያሳካለት መሆኑና ከሃጢአትም ወደጸጸትም የሚመራው መሆኑ መልካም ሥራን ገር በገር አድርጎ በዚህ መልካም ሁኔታ ይህችን ዓለም መለየቱ ነው፡፡
አንድ ሰው በዚህች ኣለም ሲኖር የሚመዘነው በሥራው ስለሆነ የመልካም ሥራው ጠረት መሳካት በሱም መጽናቱና በዚህ ሁኔታ እለተ ህልፈቱ መድረስ የመጨረሻ ማማር ዋና መረጃ ነው፡፡ ነብችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሥራዎች የሚለኩትኮ በመደምደሚያቸው ነው) እንድሁም በሌላ ሐዲስ (ሥራዎች እንደእቃ ናቸው ከሥር ያለው ከአማረ ከላይ ያለውም ያምራል ከሥር ያለው ከተበላሸም ከላይ ያለው ይበላሻል፡፡) ብለዋል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው በመልካም ሥራ አላህን ለመገናኘት መታር ይጠበቅበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْعَمَلاً صَالِحًاوَلاَ يُشْرِكْبِعِبَادَةِ رَبِّهِأَحَدًا}

ትርጉሙም (የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ፡፡ በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

እንደ ሰው አላህ ያዘዘውን ከፈጸም የከለከለውንም የሚርቅ ከሆነ አላህ መልካም ሥራን ይመራውና በሱም እንዳለ ይሞታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ቀን እንድህ አሉ፡ (አላህ ለአንድ ባሪያ መልካሙን ሲሻለት ያሰራዋል) ሰዎችም እንዴት ነው የሚያሰራው ሲሉ ጠየቁ እሳቸውም (ከመሞቱ በፊት መልካም ሥራን ያሳካለታል) አሉ፡፡ መጨረሻው ያማረለት ሰው ጀነትን ከተሰጡት ደስተኞች ጋር ይኖራል፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

{وَأَمَّاالَّذِينَ سُعِدُوا فَفِي الْجَنَّةِ خَالِدِينَ فِيهَا مَا دَامَتِ السَّمَوَاتُ وَالْأَرْضُإِلَّا مَا شَاءَ رَبُّكَ عَطَاءً غَيْرَ مَجْذُوذٍ.}

ትርጉሙም (እነዚያም ዕድለኞቹማ ጌታህ ከሻው (ጭማሪ) ሌላ ሰማያትና ምድር እስከ ዘወተሩ ድረስ በውስጧ ዘውታሪዎች ኾነው በገነት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ የማይቋረጥ ስጦታን ተሰጡ፡፡)

የሀጅ ሥራ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች ሌላው ሰበቦችን አድርሶ ነገሮችን ሁሉ ለአላህ (ዐ.ወ.) የመተው ጽኑ እምነት መኖር ነው፡፡ ምክኒያቱም አላህ የፈረደው ነገር መከሰቱ የማይቀር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡
{وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلا مُؤْمِنَةٍإِذَا قَضَى اللَّهُوَرَسُولُهُأَمْرًاأَن يَكُونَلَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْأَمْرِهِمْ وَمَن يَعْصِ اللَّهَوَرَسُولَهُ فَقَدْ ضَلَّ ضَلالامُّبِينًا}

(አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም! የአላህንና የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡) ማለት ነው፡፡

مَّا يَفْتَحِ ٱللَّهُ لِلنَّاسِ مِن رَّحْمَةٍ فَلَا مُمْسِكَ لَهَا ۖ وَمَا يُمْسِكْ فَلَا مُرْسِلَ لَهُۥ مِنۢ بَعْدِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ

(አላህ ለሰዎች ከችሮታ የሚከፍታት ለእርሷ ምንም አጋጅ የላትም፡፡ የሚያግደውም ከእርሱ በኋላ ለእርሱ ምንም ለቃቂ የለውም፡፡ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

وَإِن يَمْسَسْكَ ٱللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَ ۖ وَإِن يَمْسَسْكَ بِخَيْرٍ فَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ
وَهُوَ ٱلْقَاهِرُ فَوْقَ عِبَادِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلْحَكِيمُ ٱلْخَبِيرُ .

አላህም በጉዳት ቢነካህ ለእርሱ (ለጉዳቱ) ከእርሱ በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም፡፡ በበጎም ነገር ቢነካህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡ እርሱም ከባሮቹ በላይ ሲኾን አሸናፊ ነው፡፡ እርሱም ጥበበኛው ውስጥ ዐዋቂው ነው፡፡") ማለት ነው፡፡ ሰበቦችን ካደረሱ በኋላ ነገሮችን ሁሉ ለአላህ መተው የጥልቅ እምነት ምልክት ነው፡፡ አንድ ሰው በአላህ ላይ ያለው እምነት ከፍተና መሆንና ከሱም መልካሙን ሁሉ በመተበቅ ይኖርበታል፡፡ አለህ የፈረደውንና ያዘዘውን ሁሉ አሜን ብሎ የሚቀበል ሰው እርካታን ያገኛል ርጋታና ጸጥታም ይሰማዋል፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ለሐጅ ሥራ የተጓዘው የአላህ ባሪያ ወንጀሉ ተምሮ፣ ጥረቱ ተምስግኖና ለሥራው መንዳ ተችሮ ተመልሷል፡፡ እዚህ ላይ ከሰዎች በሚሰነዘር ሞገስ መታለል የለበትም፡፡ ሐጅ አዲስ ስም ለማትረፍና በሰዎች ላይ ለመፎከር የሚፈጸም ስራ ባለመሆኑ ከሐጅ የተመለሰ ሰው ራሱን ዝቅ ዝቅ በማድረግ ለአላህ ተገዢነቱን በአዲስ መልኩ ማጠነካር ይጠበቅበታል፡፡ በልቡ ኩራትና በራስ መደነቅ  የሚባል ነገር እንዳይሰርጽ ከኢባዳ ወደኢባዳ በመሸጋገር ወደታማኝ ባሪያነት ለመድረስ የሚጥር ከሆነ ሐጁ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ወደደግ ነገር የሚፈጥኑ የእምነት ባለቤቶች ለአላህ የሚያደርጉት ኢባዳ ተቀባይነት አያገኝ ይሆን የሚል ስጋትና ታላቅ ምንዳዉን የማግኘት ተስፋ ምንገዜም የማይለያቸው መሆኑን እንድህ በማለት አመልክቷል፡

إِنَّ ٱلَّذِينَ هُم مِّنْ خَشْيَةِ رَبِّهِم مُّشْفِقُونَ. وَٱلَّذِينَ هُم بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمْ يُؤْمِنُونَ وَٱلَّذِينَ هُم بِرَبِّهِمْ لَا يُشْرِكُونَ .وَٱلَّذِينَ يُؤْتُونَ مَآ ءَاتَواْ وَّقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَىٰ رَبِّهِمْ رَٰجِعُونَ. أُوْلَـٰٓئِكَ يُسَٰرِعُونَ فِي ٱلْخَيْرَٰتِ وَهُمْ لَهَا سَٰبِقُونَ

(እነዚያ እነርሱ ጌታቸውን ከመፍራት የተነሳ ተጨናቂዎች የኾኑት፡፡ እነዚያም እነርሱ በጌታቸው ተዓምራቶች ከሚያምኑት፡፡ እነዚያም እነርሱ በጌታቸው (ጣዖትን) የማያጋሩት፡፡ እነዚያም የሚሰጡትን ነገር እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መኾናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ኾነው የሚሰጡት፡፡) ማለት ነው፡፡

ለሐጅ ሥራ የተጓዘው የአላህ ባሪያ ወንጀሉ ተምሮ፣ ጥረቱ ተምስግኖና ለሥራው መንዳ ተችሮ ተመልሷል፡፡ እዚህ ላይ ከሰዎች በሚሰነዘር ሞገስ መታለል የለበትም፡፡ ሐጅ አዲስ ስም ለማትረፍና በሰዎች ላይ ለመፎከር የሚፈጸም ስራ ባለመሆኑ ከሐጅ የተመለሰ ሰው ራሱን ዝቅ ዝቅ በማድረግ ለአላህ ተገዢነቱን በአዲስ መልኩ ማጠነካር ይጠበቅበታል፡፡ በልቡ ኩራትና በራስ መደነቅ የሚባል ነገር እንዳይሰርጽ ከኢባዳ ወደኢባዳ በመሸጋገር ወደታማኝ ባሪያነት ለመድረስ የሚጥር ከሆነ ሐጁ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ወደደግ ነገር የሚፈጥኑ የእምነት ባለቤቶች ለአላህ የሚያደርጉት ኢባዳ ተቀባይነት አያገኝ ይሆን የሚል ስጋትና ታላቅ ምንዳዉን የማግኘት ተስፋ ምንገዜም የማይለያቸው መሆኑን እንድህ በማለት አመልክቷል፡

وَٱلَّذِينَ يُؤْتُونَ مَآ ءَاتَواْ وَّقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَىٰ رَبِّهِمْ رَٰجِعُونَ

(እነዚያም የሚሰጡትን ነገር እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መኾናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ኾነው የሚሰጡት፡፡) ማለት ነው፡፡

ኢብን ከሲር የተባሉት የቅዱስ ቁርአን ተንታኝ እንድህ ይላሉ፡ ‹ይህን ማለትም አማኞች፣ መልካም ሰሪዎችና ደግ ተግባር እየፈጸሙም እንድ ወቅት አላህ ሁኔታቸውን እንዳይቀይር ይሰጋሉ ማለት ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን አዒሻ እንድህ ይላሉ፡ ‹አንድ ቀን ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንደህ ስል ጠየቀሁኝ፡ የአላህ መልክተኛ ሆይ!

{وَالَّذِينَ يُؤْتُونَ مَا آتَوْا وَقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَى رَبِّهِمْ رَاجِعُونَ}

የሚለው የአላህ ቃል አላህን እየፈራ የሚሰርቅ፣ ዝሙትሚፈጽምና የሚያሰክር ነገር የሚጠጣ ማለት ነውን? እሳቸውም (የአቡ በክር አሲዲቅ ልጅ ሆይ! ነገሩ እንደዚህ

አይደለም፡፡ ነገር ግን ያ የእየሰገደ፣ እየጾመና ምጽዋት እየሰጠም አላህ አይቀበለኝ ይሆን? በማለት የሚሰጋ ማለት ነው፡፡) አሉ፡፡

ማንኛውም ምእምን ኢባዳ ለማብዛት ሳይሆን ቁቡልነት ለማግኘቱ ቀድሞ ማሰብ ይኖርበታል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) መልከተኛው (ሶ.ዐ.ወ.) ለዒባዳ ጥረት እንዲያደርጉና ትንሽም ቢሆን ኢባዳን እንዳይተው አዟል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በራስ መደነቅ ሥራን ከሚያበላሹ አደገና ነገሮች እንዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን አባስ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል ይላሉ፡ ( ሥራን አውዳሚ ነገሮች ሦስት ናቸው፡፡ አንድ ሰው በራሱ መደነቁ፣ አሜን ብለው የተቀበሉት ስስትና ያለመግታት የሚከተሉት ፍላጎት፡፡)

ጌታችን ሆይ! አንተን እንዲናስታውስ፣ እንዲናመሰግንና ኢባዳን እንዲናሳምር እገዘን፡፡ ለአንተ በመታዘዝና ለአንት በመገዛት ጎዳና ቀጥ ብለን እንዲንጓዝም ስኬትን ለግሰን አሜን፡፡

## (49)

## በአለፈውና ባለንበት ዘመን የስደት ግንዛቤ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{إِلَّا تَنْصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللَّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُوا ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لَا تَحْزَنْ إِنَّ اللَّهَ مَعَنَا فَأَنْزَلَ اللَّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُوا السُّفْلَى وَكَلِمَةُ اللَّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ}

ለአለው የዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም ((ነቢዩን) ባትረዱት እነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፡፡ የአላህም ቃል እርሷ ከፍተኛ ናት፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

መካ ውስጥ በነብዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ላይ የሚደርሰው ስቃይ እጅጉን በበረታ ጊዜ ነብያችን በተላኩ በአመወስተኛው ዓመት ወደሐበሻ ምድር እንድሰደቱ ፈቀዱላቸው፡፡ እንድህም አሏቸው፡ (በሐበሻ ምድር እርሱ ዘንድ አንድም ሰው የማይበደል የሆነ ንጉስ አለ፡፡ አላህ ለናንተ አሁን ለአላችሁበት ችግር መፍትሄና መውጫ እስኪያደርግላችሁ ድረስ ወደሱ አገር ተጠጉ፡፡) ከዚያም ጥቂት ባልደረቦች ወደሐበሻ ምድር ወጡ፡፡ በምድሯም ሰፈሩ፡፡ በደግ አገርና ከመልካም ጎረቤት ጋርም መኖር ጀመሩ፡፡ ለሃይማኖታቸውም ሰላም አገኙ ጌታቸውንም መገዛት ቀጠሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያሉም የመካ ሰዎች እስልምናን ተቀበሉ የሚል ወሬ በሰሙ ጊዜ እንደገና ወደሀገራቸው ለመመለስ ወሰኑ፡፡ ከተመለሱም በኋላ ነገሩ እንደሰሙት ሳይሆን ቀርቶ እንደገና ስቃይ ማድረሱን የመካ ሰዎች በመቀጠላቸው አሁንም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለሁለተኛ ጊዜ ወደሐበሻ እድሰደቱ ፈቀዱላቸው፡፡ ይሀህኛ ጉዞ የተመራው (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በጃዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብ ነበር፡፡ የቁረይሽ ነገዶች እነሱ በዚያ ሐቀኛ ንገስ ምድር በጸጥታ፣ በክብርና በሙሉ መከታ እየኖሩ መሆኑን በሰሙ ጊዜ እነሱን እንደገና ወደመካ ለማስመለስ አሰቡ፡፡ መልክተኞቻቸውን ወደነጃሺ ላኩና አነሱን ለመልክተኛቸው እንደሰጥላቸው ጠየቁ፡፡ ነገር ግን እሱ እንዲህ አለ፡ ‹አይሆንም በአላህ ይሁንብኝ ወደአገሬ የተጠጉና ከሌሎች ግርብተና ይልቅ ጉርብትናዬን የመረጡ ሰዎችን ጠርቼ ሁኔታቸውን ሳልጠይቅ አሳልፌ አልሰጣቸውም፡፡›

ከዚያም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃዕፈር ኢብ አቢ ጧሊብ የቁረይሽን መሰረተ ቢስ አባባልና ቅጥፈታቸውን ለመግለጽ ነጃሺ ፊት ቆሙ፡፡ አንድህም አሉ፡ ‹አንተ ንጉስ ሆይ! እኛ ጣዖታትን የምናመልክ፣ በክትን የምንበላ፣ እርም ነገሮችን የምንዳፈር፣ ዝሙት የምንፈጽም፣ ዝምድናን የምንቆርጥ፣ ጎረቤተን የምንጎዳና ከኛ ጉልበተኛው የደካማውን ገንዘብ የሚበላ ሰዎች ነበርን፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን አላህ ከኛ የሆነንና ዘሩን፣ እወነተኛነቱን፣ ታማኝነቱንና ጥብቅነቱን የምናውቀው የሆነን መልክተኛ ወደኛ ላከ፡፡ በአንድ አላህ አንድናምን፣ እሱንም እንድንገዛ፣ ከዚህ በፊት እኛና አባቶቻችን ከሱ ሌላ ያመልኳቸው ከነበሩ የድንጋዮችና ጣዖታት አምልኮ እንድንወገድ ጥሪ አደረገልን፡፡ እንድሁም እውነት እንድንናገር፣ አደራን እንድንመልስ፣ ዝምድናን እንድንቀጥል፣ የጉርብትናን መብት እንድናከብር፣ እርም የሆኑን ነገሮች ከመፈጸምና ደመን ከማፍሰስ እንድንታቀብ አዘዙን፡፡ ዝሙትን እንዳንፈጽም፣ በሀሰት እንዳንመሰክር፣ የሙት ልጅ ገንዘብን እንዳንበላና ጥብቅ ሴቶችንም ከዘለፍ ከለከለን፡፡ አንድ አላህን መንንም ያለማጋራት እንድናመልክ፣ ስገደትን እንድናደርሰ፣ ምጽዋትንም እንድንሰጥና ጾምንም እንድናደርስ አዘዘን፡፡ ሰይድና ጃዕፈር ሌሎችንም በርከታ የእስልምና ጉዳዮች ከቆጣጠሩለት በኋላ እንድህ አሉ፡ እኛም አመነው፣ በመልክተኘነቱም አመን፣ የመጠባቸውንም ነገሮች በመከተልን ምንንም ያለማጋራት አላህን ተገዛን፣ በኛ ላይ እርም ያደረጉትን ነገር ሁሉ እርም አደረግን፣ ለኛም የተፈቀደ ያደረገልንን ነገር ሁሉ የተፈቀደ አደረግን፡፡

በዚህ ተግባራችን ብቻ ወገኖቻችን፣ ጠሉን ስቃይም አደረሱብን፣ በሃይማኖታችንም ፈተና አደረሱብን፣ እንደገና አላህን ከመገዛት ይልቅ ሌላ ጣዖታትን ወደማምለክ እንድንመለስ፣ ፊት ስንሰራ ወደነበረው አርኩስ ነገሮችን የተፈቀዱ አደርገን እንድንፈጽም ሊያስገድዱን ሞከሩ፡፡ አነሱም በኛ ላይ ባየሉና በበደለን እንድሁም ባስቸገሩን፣ ከኛና ከእምነታችን መካከል ጣልቃ ለመግባት በሞከሩ ጊዜ ወደአንተ አገር ወጣን፣ ከሌሎችም አንተን መረጥንህ፣ ጉርብትናህንም ፈለግን፡፡ አንት ንጉስ ሆይ! አንተ ዘንድም አለመበደለን ተመኘን፡፡ ያን ጊዜ ነጃሺ እንድህ አላቸው፡፡ በመልክተኛው ላይ ከአላህ ዘንድ ከመጣው ነገር የምታውቀው ነገር አላህን? ሰይድና ጃዕፈርም አዎን አሉት፡፡ ነጃሺም አንብብለኝ አላቸው፡፡ አሳቸውም ከመርየም መዕራፍ የመጀመሪያውን ክፍል አነበቡለት፡፡ ነጃሺም ጺሙ አስኪርስ ድረስ አለቀሰ፡፡ የተነበበውን በሰሙ ጊዜ ቀሳውስትም አብረው አለቀሱ፡፡ በዚህን ጊዜ ነጃሺ እንድህ አለ፡ በአላህ ይሁንብኝ ይህ ቃል ዒሳ ከማጣው ብርሃን የወጣ ቃል ነው፡፡ ሂዱ በአላህ ይሁንብኝ እኔ አነሱን ለናንተ አሳልፌ አልሰጥም፡፡›

ወደሐበሻ ምድር የተደረጉ ሁለቱን ስደቶች ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው የጥንት ሙስሊሞች ስደት ከከህደት አገር ወደእምነት አገር የሚደረግ ስደት አለመሆኑን በግልጽ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ምክኒያቱም በመሰረቱ ስለሀገር መከላከል በሁሉም ላይ የተጣለ ግዴታ ስለሆነና ለበዳይም ሆነ ለጠላት አገርን ትቶ መሰደድ የተከለከለ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ያ ስደት ከፍርሃት አገር ወደሰላም አገር የተደረገ ስደት ነበር፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው የሐበሻው ንጉስ ነጃሺ በዚያን ጊዜ የእስልምና እመነትን የተከተለ ንጉስ አልነበረም የሚለው እውነት ሲሆን እሱ ሰዎች ለሃይማኖታቸው፣ ሕይወታቸውና ገንዘባቸው ደህንነት ሲሉ የሚጠጉበት ፍትሓዊ ንጉስ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ‹አላህ (ሱ.ወ.) በክህደት ላይ ቢሆንምኳ ፍትሃዊ አገርን ይረዳል በደለኛ አገርን የሙስሊም አገር ቢሆንምኳ ያዋርዳል› የተበላው፡፡

ስልጣን ከክህደት ጋር ሊዘልቅ የሚችል ሲሆን ከበደል ጋር ግን የሚቆይ አይሆንም፡፡ እንድሁም በዳይ አገር ገዢው ሙስሊምንኳን ቢሆን ዘላቂነት አይኖረውም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የፍትሃዊ ገዢ ደረጃ ከፍተኛ ቦታውም የላቀ መሆኑንና በትንሳኤም ቀን ምንም ዓይነት ጥላ በሌለበት አላህ በዙፋኑ ጥላ ከሚከልላቸው ሰባቱ ወገኖች ግንባር ቀደም እንደሚሆን አውስተዋል፡፡ ይህውም በፍትሃዊነቱ መላ ህብረተሰቡ የሚስተካከል እንድሁም በበደለኝነቱ መላ ማህበረሰቡ የሚበላሽ በመሆኑ ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) ለነብዩ ወደመዲና እንደሰደዱ በፈቀደ ጊዜ ከአላህ በሆነ ድል የታገዙ ሆነው ነበር የወጡት፡፡ ምክኒያቱም ይህ ጉዞ ሀገረን ለመገንባት አወንታዊ ሽግግር እንድሁም የመቻቻል ኑሮን፣ ወንድም ተማማችነትን እውን ለማድረግና ነብያችን ወደ ዓለም እንዲያደርሱ የታዘዙትን መልእክት በተሳካ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የሚያግዘውን አንድነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ስለነበር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِلاَّ تَنصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُواْ ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لاَ تَحْزَنْ إِنَّ اللّهَ مَعَنَا فَأَنزَلَ اللّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَّمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُواْ السُّفْلَى وَكَلِمَةُ اللّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَاللّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ} .

ትርጉሙም (((ነቢዩን) ባትረዱት እነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፡፡ የአላህም ቃል እርሷ ከፍተኛ ናት፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

በነብዩ ሂጅራ ስምንተኛ ዓመት አላህ (ዐ.ወ.) ለነብዩ መካ አልሙከረማን ግልጽ የሆነን መከፈት ከፈተላቸው፡፡ ሰዎችም ጭፍሮች ጭፍሮች እየሆኑ በአላህ ሃይማኖት ገቡ፡፡ በዚያን ጊዜ ጠባብና ውስን የነበረው የስደት ትርጉም ወሰን ወደሌለው ሰፊ ፍች የተሸጋገረ ሲሆን መላ የሕይወት አቅጣጫዎችን ሁሉ የሚያካትት ሆኗል፡፡ መካ ከተከፈተች በኋላ በድክመቱ ዘመን አስፈላጊ የነበረው ከአገር ወደአገር የሚደረገው ስደት ተቋርጧል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ تَوَفَّاهُمُ الْمَلَائِكَةُ ظَالِمِي أَنْفُسِهِمْ قَالُوا فِيمَ كُنْتُمْ قَالُوا كُنَّا مُسْتَضْعَفِينَ فِي الْأَرْضِ
قَالُوا أَلَمْ تَكُنْ أَرْضُ اللَّهِ وَاسِعَةً فَتُهَاجِرُوا فِيهَا فَأُولَئِكَ مَأْوَاهُمْ جَهَنَّمُ وَسَاءَتْ مَصِيرًا}

ትርጉሙም (እነዚያ (ለእምነት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ» አሏቸው፡፡ «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ፡፡ «የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን» አሉዋቸው፡፡ እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ በመመለሻነትም ከፋች!) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ከመካ መከፈት በኋላ ስደት የለም፡፡ ነገር ግን ትጋድሎና ሀሳብ ነው ያለው፡፡) በማለታቸው የስደት መሰረተ ትርጉም ተለውጧል፡፡

በመካ እንባ ይኖር የነበረው ሰፍዋን ኢብን ኡመያ የተባለው ሰው እስልምና በገበበት ወቅት ያልተሰደደ ሰው እምነት የለውም ሲባል ሰማ፡፡ ወደመዲና ከመድረሴ በፊት እቤቴ አልገባም አለና ወደመዲና ሄደ፡፡ በዓባስ ኢብን አብደል ሙጠሊብ ቤት እንግድነት አረፈና ከዚያም ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አመራ፡፡ እዚያ በደረሰም ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (የዋህብ አባት ሆይ! ምን አግር ጣለህ? ) ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም ያልተሰደደ ሰው እምነት የለውም ሲባል ሰለሰማሁ ነው አለ፡፡ ከዚያም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የዋህብ አባት ሆይ! ወደመካ ሜዳዎች ተመለስ በእምነታችሁም ጽኑ፡፡ ስደት በእርግጥ ተቋርጧል ነገር ግን ያለው ተጋድሎና ሀሳብ ብቻ ነው፡፡) አሉ፡፡

በሌላ ሐዲስም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሙስሊም ብሎ ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና ከጁ ተንኮል የዳኑ የሆነው ሰውዬ ነው፡፡ ስደተኛ ማለትም አላህ የከለከለውን ነገር የተወ ሰው ነው፡፡) ከመካ ኢል ሙከረማህ ወደመዲና ኢል ሙነወራህ የሚደረገው የቦታ ቦታ ስደት በመካ መከፈት የተቋረጠ ቢሆንም ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው በርከታ የስደት ዓይነቶች ዛሬም እንዳሉ ናቸው፡፡ እኛ አነሱን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እውነተኛ ስደት ማለት ወደተሻለና ጠቃሚነት ወዳለው ሁኔታ ለመሸጋገር የሚደረግ አወንታዊ

ዝውውር መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ከስራፈትነትና ስንፍና ወደታታሪነትና ጥራት ወዳለው ሥራ፣ ከለኔባነትና ራስ ወዳድነት እንድሁም ከጭፍን ወገናዊነት ወደሰውችን ከራስ ማስቀደም፣ ወደወንድማዊ አጋዥነት፣ ወደእውነተኛ ሰብእነት, በብዝኃነት ወደማመን፣ የሰውን ልጅ ምርጫና የእምነት ነፃነት ወደማክበር መሸጋገር እውነተኛ የሃማኖት ስደት መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አረጋግጠዋል፡፡ እንድሁም የሰውን ልጅ በእምነት፣ በእውቀት፣ በእሳቦት፣ በስርኣት፣ በስነ ምግባር፣ በምጣኔ ሃብትና በማህበራዊ ዘርፍ ለመገንባት ጥረት ማድረግ ሀገረን የሚገነባ፣ ስልጣኔ የሚፈጥር፣ የማህበረሰቡን ጥቅምና የሰብኣዊ ሙብትን የሚያስከብር ትውልድ ለመፍጠር ያሚያስችል እውነተኛ ስደት መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የእውነተኛ ስደት ትክክለኛ ግንዛቤ ለዘላለም የማይቋረጠው የሃይማኖት ስደት ከድንቁርና ወደእውቀት፣ ከጥሜት ወደቅንነት፣ ከመጥፎ ጠባይ ወደመልካም ጠባይ፣ ከብልሹነት ወደአልሚነት መሸጋገር መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይህም ሽግግር እውን በሚሆንበት ወቅት ስልጣኔን በመግንባትና ዓለምን በማልማት ረገድ ታላቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ሃማኖታችን መላ ዓለምን ወደማልማት እንድናመራ ያዘናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ብሏል፡

{هُوَ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الْأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا}

ትርጉሙም (እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሚትም አደረጋችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

የሙስሊሙ ህብረተሰብ የስንፍና ሳይሆን የሥራ ህዝብ፣ አፍራሽና አበላሽ ሳይሆን ገንቢ ህዝብ ሲሆን በዚህ የሰለጠነ ማህበረሰብ ዘንድ የኋላ ቀርነት ገጽታ በመንም ዓይነት መልኩ አይታይበትም፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ሙስሊም ሃማኖቱን ሊወድና በሱም ሊኮራ ይገባል፡፡ እንድሁም የሃይማኖቱን ደረጃ ከፍ ለማድረግና ከስህተቶች፣ ወሰን ካለፈ ቃልና ከጸንፈኝነት በመራቅ የሀገሩን ሉኣላዊነት ለማስከበር ጥረት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ እዚህ ላይ በተሳሳተ ሰንደቅ አላማ በሀሰተኛ ጂሃድ ስም ወደአሸባሪ ቡድኖች ከመኳዝና በህግም ሆነ በሃይማኖት ወደተከለከለው ውርደት አውራሽና አጥፊ ወደሆነው ህገ ወጥ ስደት ከማምራት መታቀብ ይኖርብናል እንላለን፡፡ የአንድ አገር ክብር እንደ አንድ ቤት ክብር ስለሆነ በአንድ ቤት ያለፈቃድ መግባት እንደተከለከለ ሁሉ ወደአንድ አገርም ህጋዊ ደንቦችን ያለማክበር መግባት የተከለከለ ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

በዚህ የተከበረ አጋጣሚ የሙሐረም ወር እርም ከሆኑ ወሮች አንደኛው መሆኑን ሳናስታውስ አናልፍም፡፡ በሱም በአጠቃላይ ጾምን ማብዛት የተወደደ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የግዴታ ከሆኑ ስግደቶች ቧላ እጅግ በላጩ ስግደት በማህል ሌሊት የሚሰገድ ሶላት ነው፡፡ ከሮመዳን ወር በኋላ በጣም በላጩ ጾም የአላህ ወር የሙሐረም ጾም ነው፡፡) በዚህ ወር በተለየ መልኩ የሚጾመው ቀን ደግሞ የዓሹራእ ቀን ነው፡፡ ነብያችን እንድህ ብለዋል፡ (የዓሹራእ ቀን ጾም አላህ በሱ ከሱ በፊት ያለውን ዓመት ወንጀል ያስተሰርያል ብዬ እገምታለሁ፡፡)ነብያችን ወደመዲና በመጡበት ጊዜ አይሁዳን የዓሹራእን ቀን ሲጾሙ አዩ እናም ስለምንድን ነው ብለው ጠየቁ፡፡ እነሱም ይህ የተባረከ ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን አላህ የእስራኢልን ልጆች ከጠላታቸው ስላዳነ ሙሳ ጾሙት አሉ፡፡ ነብያችንም (እኔ ስለሙሳ ከናንተ ተቀዳሚ ነኝ) አሉና ጾሙት፡፡ ሰዎችም እንድጾሙት አዘዙ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዓባስ የሚከተለውን አውርተዋል፡ (የአላህ መልክተኛ የዓሹራእን ቀን በጾሙና ሰዎችም እንድጾሙ ባዘዙበት ወቅት ሰዎች የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይህ ቀንኮ አይሁዳዊያንና ክርስቲያኖች የሚያከብሩት ቀን ነው አሏቸው እሳቸውም (የሚቀጥለው ዓመት ሲመጣ በአላህ ፈቃድ ሰጠነኛውን ቀን እንጾማለን፡፡) አሉ፡፡ ማለትም ዘጠነኛውን ቀን ከዓሥረኛው ቀን ጋር እንጾማለን ማለታቸው ነው፡፡ የዓሹራእን ቀን መጾም የተወደደ ሲሆን ተወዳጅነቱም ምሉእ የሚሆነው ዘጠነኛውንና ዐሥረኛውን ቀን በመጾም ነው፡፡

አላህ እሱ የሚወደውንና እሱን የሚያስደስተውን ሥራ እንዲያሳካልን፣ አደሱን የሂጅራ ኣመት የደገ፣ የበረከት፣ የድልና የብልጽግና ዓመት እንዲያደርግልን እሱኑ እንለምናለን፡ ፡ አሜን፡፡

**(50)**.

## ከነብያዊው ስደት ከምንቀስማቸው ትምህርቶች አንዱ አገር ግንባታ ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَالَّذِينَ هَاجَرُوا وَجَاهَدُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أُولَئِكَ يَرْجُونَ رَحْمَتَ اللَّهِ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑትና እነዚያም (ከአገራቸው) የተሰደዱት በአላህም መንገድ ላይ የተጋደሉት እነዚያ የአላህን እዝነት ይከጅላሉ፡፡ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የአላህ መልክተኛ ከመካ ኢል ሙከረማ ወደመዲና ኢል ሙነወራ ያደረጉት የሃይማኖት ስደት የሰውን ልጅ ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ የለወጠ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት ነበር፡፡ እኛ በአሁኑ ወቅት በህበረተሰቡ እድገትና በስልጣኔው ግንባታ ረገድ አስተዋጽኦ ያለውን የዚህን ስደት ትርጉም ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ይህ ስደት እውነትን ከከንቱ በጉልህ መልኩ የለየ ከመሆኑም ባሻገር ፍትህ፣እኩለነት፣ የእምነት ነጻነት የሰብአዊ መብት መከበረን መሰረት ያደረገ ሲቪላዊ ሀገር ለማዋቀር አወንታዊ ሽግግር ነበር፡፡ እንድሁም ይህ ስደት ለሰላማዊ አብሮ መኖር መጠናከርና በአንድ አገር ለሚኖሩ ሰዎች የማህበራዊ ትስስርና ለተለያዩ የጋራ ኢኮኖሚዊ አንቅስቃሴ የመሰረት ድንጋይ ነበር፡፡

ነበያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ከስደታቸው በኋላ የዋቀሩት መንግስት የተላያዩ መሰረቶችና ግብአቶች የነበሩት ሲሆን በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት አንደኛው ቀድመው መስጊድ መስራታቸው ነበር፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) መዲና ኢልሙነወራ እንደደረሱ ከአከናወኗቸው ነገሮች መጀመሪያው መስጊድ መገንባት ሲሆን ይህም የሆነበት ከጌታው ጋር ያለው የሰው ልጅ ግንኙነት ለማንኛውም ነገር ደህንነት ጠንካራ ዋስትና ስለሆነ ነው፡፡ ትክክለኛ እምነት አፍራሽ ሳይሆን ገንቢና አበላሽ ሳሆን አልሚ የሆነ ቅን ማንነትን ለመፍጠር ዋነኛ መሳሪያ ሲሆን ከትክክለኛው እምነት በማፈንገጡ ወይም እሱን በተሳሳተ መልኩ በመገንዘቡ መጠን የአንድ ሰው ማንነት ከቅንነት ይርቃል፡፡ እንድሁም መስጊድ በማህበረሰቡ ቋሚ መርሆችንና ጠቃሚ እሴቶችን በማስረጽና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ በኩል ትምህርታዊና ማህበራዊ ተልእኮ አለው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ደግሞ የምጣኔ ሀብታዊ ግንባታ ነው፡፡ አንድ አገር ያለሱ ሊገነባና ሊቆም ያማይችል ከሆኑ የሀገር ግንባታ ምሰሶዎች አንዱ ጠንካራ የምጣኔ ሀብት ነው፡፡ ጠንካራና የተረጋጋ የምጣኔ ሀብት አንድ አገር ሀገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ግዴታውን እንዲወጣ ያስችላል፡፡ እንድሁም ለህዝቡ አኩሪ ሕወትም

ዋስትና ይሆናል፡፡ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ሲዳከም ድህነትና በሽታ ይስፋፋል፡፡ ኑሮም ይወዛገባል፡፡ አዳድስ ችግሮችም ይከሰታሉ፡፡ ስነ ምግባር ይበላሻል፡፡ ወንጀሎች ይበዛሉ፡፡ ያን ሀገር ለመጉዳት፣ ለመጣልና መጨረሻ ወደሌለው ስርኣት አልባነት ለመክተት ለአደፈጡ ጠላቶች እድሎች ይመቻቻሉ፡፡

በመሆኑም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የመዲና ማህበረሰብ የልጆቹን ፍላጎት ለማሟላት፣ ራሱን ለመከላከል፣ የእስልምና ተልእኮ እንድሳካና ድህንነት እንድሰፍን የሚያስችል ጠንካራ ኢኮኖሚ ያለው ማህበረሰብ እንድሆን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ ይህንም ጉዳይ ለማሳካት ሲባል ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለመዲና ሰዎች የተፈቀደ ትርፍና ንግድ ሥራ አድል የሚፈጥር እንድሁም ለእጅ ባለሞያዎችና ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሳታፊዎች ማእከል የሚሆን -መናኻ- የተባለን ትልቅ ገበያ አዋቀረዋል፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዐጣእ ኢብን የሳር የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ ለመዲና ገበያ እንዲኖራት ባሰቡበት ወቅት ወደ በኑ ቀይኑቃዕ ገበያ ሄደው አዩ ከዚያም ወደመዲና ገበያ ቦታ አመሩና እዚይም ሲደርሱ በግራቸው መታ መታ አደረጉና (ይህ ገበያችሁ ነው አታጥቡት፡፡) አሉ፡፡› ተላላቅ የነብያችን ባልደረቦች በተላያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ተሳትፈዋል፡፡ ይህውም በግንዘብ እርዳታና በአንሳር ወንድሞቻቸው እገዛ በዘላቂነት መኖርን ባለመፈለጋቸው ነበር፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዓብደራሕማን ኢብን ዓውፍ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹በርካታ ስድተኞች ወደመዲና በመጡ ጊዜ የአላህ መልክተኛ ዓብደረሕማን ኢብን ዐውፍን ከሰዕድ ኢብን አረቢዕ ጋር ወንድም ተማማኞች እንድሆኑ አዘዙ፡፡ ሰዕድም ለዓብደረህማን እንድህ አሉ፡ ከአንሷሮች በጣም ባለጸጋው እኔ ነኝ፡፡ ገንዘቤንም ከኔና ካንተ መካከል ከሁለት እከፍለዋለሁ፡፡ ዓብደራህማንም አላህ ቤተሰብህንና ገንዘብህን ይባርክልህ ገበያቸው በየት በኩል ነው? › አሉ፡፡

ይህውም ቀለቡን፣ ልብሱን፣ መድሃኒቱንና ጦር መሳሪያውን በእጁ ያለደረገ ማህበረሰብ ነገሩን፣ ፍላጎቱን፣ ቃሉንና ክብሩን በቁጥጥሩ ስር ሊያደርግ አይችልምና ነው፡፡ የጥንት አበው እንድህ ይላሉ፡ ‹ለፈልግህው ሰው ውለታ ዋል ከዚያም አዛገፉ ትሆናለህ፡፡ ከአንድ ሰው ምንም የማትፈለግ ከሆነ አቻው ትሆናለህ፡፡ ከአንድ ሰው አንድን ነገር ከፈለግህ የሱ ምርኮኛ ትሆናለህ፡፡› የላቀው ሃይማኖታችን የላይኛው እጅ ከታችኛው እጅ የበለጠ መሆኑን አስተምሮናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ላይኛው እጅ -የሚሰጠው- ከታችኛው እጅ -የሚቀበለው- መልካም ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሓዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ሰጭው እጅ የላይኛው ነው፡፡ ለማኙ የታችኛው ነው፡፡)

ይህ ተግባር በማህበረሰብ፣ በድርጅቶችና በግለሰብም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ገንዘብ በማህበረሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ሕይወትን በማሳካት እንድሁም ብልጽግናውን

እውን በማድረግ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አሕመድ ሸውቂ የተባለው የግጥም ደራሲ እንድህ በማለቱ ይደነቃል፡

ሰዎች ገሀራቸውን የሚገነቡት በእውቀትና በገንዘብ ነው፡፡ ሀገር በድንቁርናና በእጦት ሊገነባ አይችልም፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የዚህ ዓይነቱን መርህ ገቢራዊ ለማድረግ የስርኣት ደንቦችን አስቀምጠዋል፡፡ መቻቻልና በግዥና ሽያጭ ወቅት መልካም መንፈስ መኖር አስፈላጊ መሆኑንም እንድህ በማለት አስገንዝበዋለ፡ (በሚሸጥበት፣ በሚገዛበትና በሚፋረድበት ወቅት ገራገር የሆነን ሰው አላህ ምህርትን ይለግሰው፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እውነተኛና ተማኝ እንድንሆን እንድህ በማለት አዘውናል፡ (እውነተኛና ተማኝ ነጋዴ ከነብዮች፣ ከጻዲቃንና ከሰምዓታት ጋር ነው፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሸቀጥ ማካበትን እንድህ በማለት እርም አድርገዋል፡ (ምግብን ለአርባ ቀናት ያካበተ ነጋዴ ከአላህ ራሱን አርቋል አላህም ከሱ ርቋል፡፡) ከዚያም አልፎ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በገበያ በራሳቸው በመገኘት ግብይትን ይከታተሉና ሰዎችም ለወገን የሚጠቅሙ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይመክሩም ነበር፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልተኛ እንድ ቀን በገበያ ባለ የምግብ ክምችት አለፉ፡፡ በሱም አጃቸውንም ባስገቡ ጊዜ ጣታቸው እርጥበት ባለበት ክፍል ደረሰ፡፡ (አንት ባለምግቡ ይህ መንድን ነው?) አሉት፡፡ እሱም የአላህ መልክተኛ ሆይ ዝናብ ደርሶበት ነው አለ፡፡ እሳቸውም (ሰዎች እንዲያዩት ከላይ በኩል አታደርገውም ነበርን) አሉትና (የሚያታልል ሰው ከኛ አይደለም) አሉ፡፡

ከተጠቀሱት ድንቦች ሌላው ደግሞ የመዲና ሰነድ ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከስደት በኋላ ጠንከራ አገር ለማዋቀር ባሰቡ ጊዜ የመዲና ሰነድ የተበላውን መመሪያ አስቀመጡ፡፡ ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) ከሙሃጂሮችና አንሷሮች መካከል ወንድም ተማማችነት በመፍጠር ብቻ አልተወሰኑም፡፡ ይልቁንም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ ታላቅ የሚባለውን የመዲናን ሰነድ ሲነድፉ የሰብአዊ መብት፣ የማህበረሰቡ አባላት መብትና ግዴታን እንድሁም የሰላማዊ አብሮ መኖርን መሰረት በማድረጋቸው ወደአድስ የስብእነት ትርጉም ተሸጋግረዋል፡፡ በመሆኑም ሰነዱ በገራ ኑሮ ህግ ዘርፍ ታላቅ ሰነድ የሚል ስያሜን አትርፏል፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከመዲና አይሁዶችና ከሌሎችም የመዲና ነዋሪዎች ጋር በፈረሙት ውል ለነሱ በደህንነት፣ በሰላም፣ በነጻነትና በጋራ መከላከል ዘርፎች ለአይሁዶች ሃይማኖታቸው እንደተከበረ ሆኖ በደል እስካልፈጸሙ ድረስ የሙስሊሞችን ሙሉ መብት ስጥተዋቸዋል፡፡ በዚህ ሰነድ የሃይማኖት ነጻነት በግልጽ ተወስቷል፡፡ ይህም ማንኛውም ሲቪላዊ መንግስት ሙስሊሞችንና የሌላ እምነት ተከታዮችን የሚያካትት መሆኑንና በምብትም ሆና በግዴታ እኩልነታቸው የተከበረ መሆኑን ያረጋግጣል

ማለት ነው፡፡ይሁንና ውል ማክበርና ከትንኮሳ መራቅ የሚለው ነጥብ የተከበረ መሆን ይኖርበታል፡፡
መላ የሰው ልጅ በሰላም አብሮ መኖር ወቅታዊ ተጨባጩ ግድ የሚያደርገው ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ግዴታ ነው፡፡ ይህም እውን ይሆን ዘንድ የአንድ ሀገር ነዋሪዎች ያለማዳላት ተመሳሳይ መብትና ግዴታ ያላቸው መሆኑ እንዲረጋገጥላቸው ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{لاَ إِكرَاهَ فِي الدِّين قَدْ تَبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ .

ትርጉሙም (በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን መርህ በተጨባጭ ሙሉ በሙሉ ገቢራዊ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም አምነቱን እንድቀበል ማነንም አላስገደዱም፡፡ ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ማንኛውንም ቤተ ጸሎትን አላፈረሱም፡፡ ምክኒያቱም የእስልምና እምነት ለእምነት ነጻነት ዋስትና ሰጥቷልና፡፡ ይህን ዓይነት የሃይማኖት ልዩነት ማነም ሊለውጠው አይችልም ምክኒያቱም የፈጣሪን ፍርድ ይጻረራልና፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَنْ فِي الْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًاأَ فَأَنْتَ تُكرِهُ النَّاسَ حَتَّى يَكُونُوا مُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም (ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን፡፡) ማለት ነው፡፡ በአንድ አገር ግንባታ የእምነት ነጻነት፣ መብትና ግዴታ መከበር ዋና ዋና መሰረቶች ናቸው፡፡ ምክኒያቱም ለህዝቡና ለማህበረሰቡ ትስስር ከፍተኛ ሚና ያለቸው በመሆኑ ነው፡፡ የአስልምና እምነት የሌላ እምነት ተከታዮችን ለነሱና ለሃይማኖታቸው የሚያስከፋ ነገር መናገርን ከልክሎናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{ وَلَا تَسُبُّوا الَّذِينَ يَدْعُونَ مِنْ دُونِ اللَّهِ فَيَسُبُّوا اللَّهَ عَدْوًا بِغَيْرِ عِلْمٍ كَذَلِكَ زَيَّنَّا لِكُلِّ أُمَّةٍ عَمَلَهُمْ ثُمَّ إِلَى رَبِّهِمْ مَرْجِعُهُمْ فَيُنَبِّئُهُمْ بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ .

ትርጉሙም (እነዚያንም ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸውን (ጣዖታትን) አትስደቡ፡፡ ድንበርን በማለፍ ያለዕውቀት አላህን ይሰድባሉና፡፡ እንደዚሁ ለሕዝቦች ሁሉ ሥራቸውን ደግ አስመሰልንላቸው፡፡ ከዚያም መመለሻቸው ወደ ጌታቸው ነው፡፡ ይሠሩት የነበሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች የስነ ምግባርና መልካም ጉርብትና መንፈስ እንድኖራቸው ያዛል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُمْ مِنْ دِيَارِكُمْ أَنْ تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ .

ትርጉሙም (ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም ተከታዮቹ የሌላ እምነት ተከታዮችን ስሜት በውይይትና በክርክር ጊዜም እንኳ ቢሆን እንዲያከብሩ ያዛል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{وَلَا تُجَادِلُوا أَهْلَ الْكِتَابِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِلَّا الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنْهُمْ وَقُولُوا آمَنَّا بِالَّذِي أُنْزِلَ إِلَيْنَا وَأُنْزِلَ إِلَيْكُمْ وَإِلَهُنَا وَإِلَهُكُمْ وَاحِدٌ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ .

ትርጉሙም (የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም «በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡) ማለት ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ አንጻር ነው እንግዲህ የመዲና ሰነድ የአንድ አገር ነዋሪዎችን ትስስር እውን የሚያደርገውን፣ ስልጣኔ የሚፈጥረውንና የሰው ልጅ ጥቅም እንድከበር የሚያግዘውን የሰብአዊ መብትን በማክበር ረገድ ሊከተሉት የሚገባ አርአያነት ያለው ሰነድ ነው የተባለው፡፡
ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

***

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**
አገር ከፍተኛ እሴትና ታላቅ ደረጃ ያለው መጠጊያ ነው፡፡ እሱን ማፍቀር ስለእሱ መከላከል የሰው ልጅ መንፈስ የታነጸበት ተፈጥሮ ሲሆን ሃይማኖት የሚደግፈውና የሀገር ወዳድነት ግዴታ ነው፡፡ ነብያችን በሀገር ፍቅር፣ ልባቸው በሱ በመታሰሩ አርአያነት ያለው ተግባራቸውን የመጀመሪያ አገራቸውን መካን በማናገር እንድህ

በማለታቸው አረጋግጠዋል፡ (ለኔ ተወዳጅ የሆንሽ ምን ያማርሽ አገር ነሽ ሰዎችሽ ካንች ባያወጡኝ ኖሮ ባልወጣሁ ነበር፡፡)

ነብያችን ወደመዲና ተሰደው በሏም ከተረጋጉ በኋላ ይህን ሁለተኛውን አገራቸውን እንዲወዱት በሱም ሰላምና መረጋጋት እንድሰፍን አላህን እንድህ በማለት ጸሎት አድርገዋል፡ (ጌታችን ሆይ እኛ መካን እንደምነወድ ወይም ከዚያበላይ መዲና እድንወድ አድርገን፡፡) ከመንግሰትና ከሃይማኖት መካከል ያለው ግንኙነት ተጻራሪ ሳይሆን አንዱ ሌላውን የሚያሟላ ግንኙነት ነው፡፡ ሀገርን መጠበቅ መሟላታቸው ግዴታ ከሆኑ አጠቃላይ አላማዎች አንዱ ነው፡፡ ስለሀገር መከላከልና ድህንነቱን መጠበቅ ለሱም መስዋእትነት መክፈል በምድሩ የሚኖርና በሰማዩ የሚጠለል ሰው ሁሉ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው፡፡ የሀገር ፍቅር በዘተፍጥሮ ሚሰማን ስሜት ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡና ለግለሰቡም በሚጠቅሙ ነገሮች መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ሀገር ጠንካራና የተከበረ ሆኖ እንድኖር መስዋእትነት መክፈል ለሁሉም የማይቀር ተግባር ነው፡፡ እውነተኛ ሀገር ወዳድነት የምናነግበው መፍክርና የምንደጋግመው ቃል ብቻ ሳይሆን እምነት፣ ስርአትና ስጦታን ያካተተ ተግባር ነው፡፡ ሀግር ወዳድነት የሕይወት ሰርአት እንድሁም የሀገር ልብ ትርታና የተደቀነበትን ችግር የምናውቅብት ስሜትና ለሱ መስዋእትነት ምንጊዜም ዝግጁ የምንሆንለት መጠለያ ነው፡፡ ለአላህ የገቡትን ቃል ያከበሩና ሀገራቸውን ለማስከበርና ከፍተኛ ደረጃም ለማድረስ መስዋእትነት የከፈሉ ሰዎች እንኳን ደስ ያላቸው፡፡

ጌታችን ሆይ ሐገራችንና ህዝባችንን ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን በሱም የሚቃጣን የተንኮለኞችን ተንኮል፣ የምቀኞችን ሴራና የጠንቀኞችም ደባ በነሱው ላይ መልስባቸው፡፡